ከበደ ፡ ሚካኤል ፡

# ሥ ል ጣ ኔ ፡

## ማለት ፡ ምንድነች ?

# ማውጫ ።


| | ገጽ፡ |
|---|---|
| መቅድም ፡ | ፭ |
| ግርማዊ ፡ ሆይ ፡ | ፲፫ |
| የሥልጣኔ ፡ ትርጉም ፡ | ፲፭ |
| የድርኸት ፡ ታሪክ ፡ | ፳፫ |
| ሥነ ፡ ጥበባት ፡ | ፴፩ |
| ልዩ ፡ ልዩ ፡ አስተያየቶች ፡ | ፴፱ |
| ቪቬካናንዳና ፡ ጋንዲ ፡ | ፵፭ |
| የሥልጣኔ ፡ ደዌ ፡ | ፶፯ |
| የከተማ ፡ ሕዝብ ፡ (ዴሞክራሲ) ፡ | ፷፯ |
| ተጠራጣሪዎችና ፡ ከሓድያን ፡ | ፸፯ |
| የዓለም ፡ መንግሥታትና ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ | ፺፩ |
| የኢትዮጵያ ፡ ተግባር ፡ | ፺፯ |
| ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴና ፡ ጋንዲ ፡ | ፻፲፯ |
| ሰውና ፡ ጥበብ ፡ | ፻፴፫ |
| ጥበብ ፡ ከየት ፡ ተገኘች ? | ፻፵፭ |
| የሥልጣኔ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ | ፻፷፭ |
| ጋንዲና ፡ ኢንዱስትሪ ፡ | ፻፸፫ |
| ጋንዲና ፡ ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ | ፻፹፩ |
| የተስፋ ፡ ጮራ ፡ | ፻፺፯ |
| የማይሞቱ ፡ ቃሎች ፡ | ፪፻፲፩ |

ስለ ፡ ሥልጣኔ ፡ ትርጉምና ፡ ሐተታ ፡ የደራሲውን ፡ አስተያየት ፡ በሙሉ ፣ ለማወቅ ፡ ሲፈለግ ፡ «የሥልጣኔ ፣ አየር ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ታትሞ ፡ የሚወጣውን ፡ መጽሐፍ ፡ ጨምሮ ፡ መመልከት ፡ የሚያስፈልግ ፡ መሆኑን ፡ ደራሲው ፡ ላንባቢ ፡ ያስገነዝባል ። እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ መጻሕፍት ፡ ባሳብ ፡ የተሳሰሩ ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ ነው ።

ያለደራሲው ፡ ፈቃድ ፡ ማሳተም ፡ ወይም ፡ መተርጐም ፡ አይቻልም ።

Copyright

በአርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፣ ሊሚትድ ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ታተመ ።

# መ ቅ ድ ም ።

ሰውን ፡ ከሌሎች ፡ ፍጡሮች ፡ በላይ ፡ አድርገን ፡ እንድንመለከተው ፡ የሚያስገድደን ፡ ምክንያት ፡ ሥልጣኔን ፡ የሠራ ፡ እሱ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። ይህ ፡ ችሎታ ፡ የተሰጠው ፡ ባይሆን ፡ ኖሮ ፡ በቢዎሎዢ ፡ አኳኋን ፡ ሥነ ፡ ፍጥረቱን ፡ ስንመለከተው ፡ በዚች ፡ ፕላኔት ፡ ላይ ፡ ከሚኖሩት ፡ ከቀሩት ፡ ፍጡሮች ፡ የተለየ ፡ አድርጎ ፡ የሚያስቈጥረው ፡ ምንም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ባላገኘንበት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ ከተፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ ያለውን ፡ ታሪክ ፡ ስናስተውለው ፡ ይህን ፡ የሥልጣኔ ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ አብሮት ፡ የተወለደውና ፡ ለሥነ ፡ ፍጥረቱ ፡ መለያ ፡ ሆኖ ፡ የተሰጠው ፡ ባሕርይ ፡ ሲወድቅ ፡ ሲነሣ ፡ በብዙ ፡ ደረጃ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ አሁን ፡ ካለንበት ፡ ከአቶም ፡ ዘመን ፡ ለመድረስ ፡ እንሆ ፡ የበቃ ፡ ሆኖ ፡ ለመገኘት ፡ ቻለ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ለመድረስ ፡ ከመቻሉ ፡ በፊት ፡ ረዥም ፡ ጕዞ ፡ ማድረግ ፤ ዝግተኛና ፡ ጠንካራ ፡ የሆነ ፡ መጣጣርን ፡ መፈጸም ፡ አስፈልጎታል ። ይህን ፡ የፈጸመውን ፡ የመሻሻል ፡ ጕዞ ፡ ለማወቅ ፡ ስንፈልግ ፡ በህንድ ፡ አገር ፡ ሪሺ ፡ የተባሉት ፡ አስተዋዮች ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ሰባቱ ፡ ጠቢባን ፡ የሚባሉት ፡ ግሪኮች ፡ ከነበሩበት ፡ ዘመን ፡ አንሥተን ፡ የተደረጉትን ፡ እርምጃዎች ፡ በመከተል ፡ ባሳብ ፡ ብቻ ፡ በሆነው ፡ መመራመርና ፡ ወይም ፡ ያሳብን ፡ ዕውቀት ፡ በሥራ ፡ ገልጦ ፡ በማሳየት ፡ የተፈጸመውን ፡ ነገር ፡ እየተከታተልን ፡ መመልከት ፡ ይኖርብናል ፤ ይህንንም ፡ ስናደርግ ፡ ይህ ፡ አንደዬ ፡ ሲቋረጥ ፡ ደግሞ ፡ ተመልሶ ፡ ሲቋቋም ፡ አንዳንደዬም ፡ ለጊዜው ፡ ሲሰናከል ፡ የኖረውን ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መቼም ፡ ቢሆን ፡ ጨርሶ ፡ ለመበጠስና ፡ ለመደምሰስ ፡ ያልቻለውን ፡ ሰው ፡ በዕውቀት ፡ መንገድ ፡ ያደረገውን ፡ ጕዞ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ተገልጦ ፡ በዐይነ ፡ አእምሯችን ፡ ልንመለከተውና ፡ ልናስተውለው ፡ እንችላለን ።

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አነጋገር ፡ የሥልጣኔ ፡ መሪ ፡ የሆኑት ፡ ሕዝቦች ፡ በሰው ፡ አሳብ ፡ ሊፀነስ ፡ ይችላል ፡ ተብሎ ፡ ከማይታመን ፡ አዲስ ፡ ከሆነ ፡ ከሥልጣኔ ፡ ሁኔታ ፡ ሲደርሱ ፡ ተመልከትን ፡ አሳባችን ፡ የመደነቅ ፡ ስሜት ፡ ያድርበታል ። ስለ ፡ ሲያንስና ፡ ስለ ፡ ቴክኒክ ፡ የተወጠኑት ፡ አያሌ ፡ የሆኑ ፡ አሳቦች ፡ በሥልጣኔ ፡ የገፉ ፡ ዕውቀት ፡ ባላቸው ፡ አገሮች ፡ ተቋቁመው ፡ በሚገኙት ፡ (ላቦራቷሮች) ፡ ማለት ፡ የጥበብ ፡ መመርመሪያዎች ፡ የሚጠኑት ፡ ጥናቶች ፤ በዓለም ፡ ላይ ፡

ያሉ ፡ ብዙዎች ፡ የሆኑ ፡ ሊቃውንት ፡ ድካም ፡ ሳይሰማቸው ፡ በሚያስደ ንቅ ፡ ትጋት ፡ የሚያደርጉት ፡ የተመራማሪነት ፡ ተግባር ፤ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ የሚገኘው ፡ ውጤት ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በሚመጣው ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሥልጣኔን ፡ መልክ ፡ አሁን ፡ ካለው ፡ ይበልጥ ፡ ሊለውጠው ፡ ይችላል ። በሲያንስና ፡ በቴክኒክ ፡ ረገድ ፡ የሚፈጸሙት ፡ ነገሮች ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ለማወቅ ፡ ስንፈልግ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ባጭርና ፡ በቀላል ፡ አነጋገር ፡ እየሆኑ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ሊቃውንት ፡ የሚጻፉትን ፡ መጻሕፍት ፡ ማንበብ ፡ እንችላለን ። ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ ከዓለም ፡ ፊት ፡ ተደቅነው ፡ ከ ሚገኙት ፡ ዋኖች ፡ ጉዳዮች ፡ አንዱ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀሩ ፡ አገሮች ፡ ጉዳይ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉትን ፡ ጥያቄዎች ፡ አሳባችን ፡ ሳያስታው ሳቸው ፡ ሊቀር ፡ አይገባም ። ይኸውም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀሩ ፡ አገሮች ፡ ችግሮቻቸውን ፡ ሊወጧቸው ፡ የሚችሉት ፡ እንዴት ፡ ነው ? ለዚህ ፡ የ ሚሆን ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ መፍትሔ ፡ ይገኛል ፡ ወይ ? የሚል ፡ ነው ። እኔ ፡ በራሴ ፡ አስተያየት ፡ እኛ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ በቀሩ ፡ አገሮች ፡ የምንኖር ፡ ሕዝ ቦች ፡ ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ በሳይንስና ፡ በቴክኒክ ፡ በኩል ፡ በሠለጠኑት ፡ አ ገሮች ፡ የተፈጸሙትን ፡ ሥራዎች ፡ ብቻ ፡ እንድንወርሳቸውና ፡ ከኑሯችን ፡ ጋራ ፡ እንድናዋሕዳቸው ፡ ስንፈልግ ፡ ይህ ፡ ተግባር ፡ የቱን ፡ ያኽል ፡ ጊዜና ፡ ድካም ፡ እንደሚጠይቀን ፡ ገምተን ፡ የተረዳነው ፡ አይመስለኝም ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ የሚጠብቀን ፡ አደጋ ፡ ሁለት ፡ ዐይነት ፡ ነው ። ሁሉ ፡ ቀኙ ፡ የሆኑ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ እንደሚያስቡት ፡ ሁሉ ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ልንደ ርስበት ፡ እንችላለን ፡ ብለን ፡ ብናስብ ፡ በመካከላችን ፡ ስላለው ፡ መራ ራቅ ፡ ግምት ፡ የማናውቅ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠርብናል ። ይህ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ በመካከላችን ፡ ያለውን ፡ ትልቅ ፡ የሆነ ፡ መራራቅ ፡ በሚገባ ፡ ገምተን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተስፋ ፡ መቍረጥ ፡ ያደረብን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ደግሞ ፡ የሚደ ርስብን ፡ አደጋ ፡ ቀድመን ፡ ከጠቀስነው ፡ አደጋ ፡ የባሰ ፡ እንጂ ፡ ያነሰ ፡ ሆኖ ፡ አይገኝም ። ምክንያቱም ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ኑሮ ፡ ትግል ፡ ምሕረት ፡ የሌለው ፡ ውድድር ፡ ገጥመው ፡ የሚታገ ሉበት ፡ ወቅት ፡ በመሆኑ ፡ በራሳቸው ፡ የማይተማመኑ ፡ ሕዝቦች ፡ ሊፈ ጽሙት ፡ የሚችሉት ፡ ምንም ፡ ተግባር ፡ ባለመኖሩ ፡ ይህን ፡ ለመሰለው ፡ ትግል ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ የታታሪነት ፡ መንፈስ ፡ ለሚያሳዩት ፡ ቦታ ፡ መል ቀቅ ፡ ግድ ፡ ስለሚሆንባቸው ፡ ነው ።

በኛ ፡ ዘመን ፡ የሚታየውን ፡ የመሰለ ፡ የዕውቀት ፡ መጠማት ፡ የሰ ውን ፡ መንፈስ ፡ ሲያስክረው ፡ በማናቸውም ፡ ዘመን ፡ ታይቶ ፡ አይታ ወቅም ። የሚፈለሰፉትና ፡ የሚገለጡት ፡ አዲስ ፡ ጥበቦች ፡ በአስደናቂ ፡ ሁኔታ ፡ እየተፋጠኑ ፡ ሲፈጸሙ ፡ ይታያሉ ። ሴት ፡ ፀንሳ ፡ ካረገዘች ፡



በኋላ ፡ ምንም ፡ ቢደረግ ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ሳይሞላ ፡ ልጅ ፡ እንደማትወ ልድ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ የ ሚሆነውን ፡ የጥበብና ፡ የዕውቀት ፡ መፋጠን ፡ ስንመለከተው ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ የደነገገችውን ፡ ሕግ ፡ ሽራ ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ ልጅ ፡ እንደምት ወልድ ፡ ሴት ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ። የሚያገኟቸው ፡ አዲስ ፡ ጥበቦች ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ እንደ ፡ ናዳ ፡ እየተከታተሉ ፡ በብዛት ፡ ሲፈጸሙ ፡ ይታያሉ ። ይህን ፡ በብዛት ፡ የሚፈጸመውን ፡ ያዲስ ፡ ጥበብ ፡ መፈጠር ፡ የዓለም ፡ ሰዎች ፡ እየተቀበሉ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ለማድረግ ፡ ያቅታቸውና ፡ በቃን ፡ ጠገብን ፡ ከሚሉበት ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ያደርሳቸዋል ፡ ሲሉ ፡ የግምት ፡ አስተያየት ፡ የሚሰጡ ፡ ሊቃውንት ፡ አሉ ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ በዘመናችን ፡ የደረሰ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አለ ። ይኸውም ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ያደረጉት ፡ የመገናኘትና ፡ የመቀ ራረብ ፡ ሥራ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ሕዝቦች ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ሁሉም ፡ በየአ ህጉሮቻቸውና ፡ በየቦታቸው ፡ ተዘግተው ፡ አንዱ ፡ ከሌላው ፡ ሳይገናኝ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ሕዝቦችን ፡ የሚያመላልሱ ፡ መገናኛዎች ፡ እንደ ፡ ባቡር ፡ መርከብና ፡ አኤሮፕላን ፡ የመሰሉት ፡ በቴክኒክ ፡ በኩል ፡ የመሻሻላቸው ፡ ሥራ ፡ አሁን ፡ ባለንበት ፡ በቅርቡ ፡ ዘመን ፡ በጣም ፡ ስለ ፡ ተፋጠነ ፡ ይህን ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ እንዲፈጠር ፡ ያደረጉ ፡ እነሱ ፡ ናቸው ። በማንኛውም ፡ ስብ ሰባ ፡ ላይ ፡ በኮክቴልም ፡ ሆነ ፡ በቀረውም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በሚሰበሰቡ በት ፡ የግብዣ ፡ ቦታ ፡ አስደናቂ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ይታያል ። ሰዎች ፡ መምጣት ፡ሲጀምሩ ፡ ቍጥራቸው ፡ የተወሰነ ፡ ጥቂት ፡ በመሆኑ ፡ ሁሉም ፡ የሚነጋገሩት ፡ ነገር ፡ በቅክክል ፡ ይሰማል ። ነገር ፡ ግን ፡ ተጋባዦቹ ፡ እየተጨመሩ ፡ ቍጥራቸውም ፡ እያደገ ፡ በሚሄድበት ፡ ጊዜ ፡ ድምፃቸውም ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ ስለሚበዛ ፡ ታዛቢ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ልብ ፡ ብሎ ፡ ቢሰማቸው ፡ ከጠቅላላው ፡ ስብሰባ ፡ ላይ ፡ የሚነሣውን ፡ ጫጫታ ፡ ባዳ መጠ ፡ ጊዜ ፡ እብዶች ፡ በተሰበሰቡበት ፡ ቤት ፡ የሚገኝ ፡ የሚያስመስል ፡ ስሜት ፡ ያድርበታል ። ነገር ፡ ግን ፡ በያንዳንዱ ፡ ወገን ፡ የሚያደርጉትን ፡ ንግግር ፡ በየቦታው ፡ እየተዘዋወረ ፡ ቢከተልና ፡ ከቅርብ ፡ ሆኖ ፡ ቢሰማ ፡ ሁሉም ፡ በየበኩላቸው ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያለው ፡ ጭውውትና ፡ ንግግር ፡ ወይም ፡ ክርክር ፡ እንደሚያደርጉ ፡ ይረዳዋል ። እንሆ ፡ ይህ ፡ አሁን ፡ ላለንበት ፡ ዓለም ፡ ምሳሌ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ ዕውቀትና ፡ የሲያንስ ፡ ጥበቦች ፡ በተወሰኑ ፡ በጥ ቂት ፡ ሕዝቦች ፡ እጅ ፡ ብቻ ፡ የተጨበጡ ፡ መሆናቸው ፡ ቀርቶ ፡ ለብዙ ፡ ሕዝቦች ፡ የተዳረሱ ፡ ሆነዋል ። የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅትና ፡

ሌሎችም ፡ ኤንቴርናሲዮናል ፡ የሆኑ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ድርጅቶች ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ነጻ ፡ አገሮችና ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉም ፡ ስለ ፡ ግል ፡ መብቶቻቸውና ፡ ጥቅሞቻቸው ፡ ጥበቃ ፡ ድምፆቻቸውን ፡ ለማሰማት ፡ የሚችሉበትን ፡ መንገድ ፡ ከፍተውላቸዋል ። ይህ ፡ መቀራረብ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የተቋቋመ ፡ ቢሆንም ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ በተፈጥሮ ፡ አስተያየታቸው ፡ በግል ፡ አሳባቸው ፡ ሁኔታ ፡ ባደረባቸው ፡ እምነት ፡ ምክንያት ፡ በመካከላቸው ፡ ያለውን ፡ የሃይማኖትም ፡ ሆነ ፡ የኢዴዎሎጊ ፡ ወይም ፡ የዘር ፡ ልዩነት ፡ እየተመረኰዘ ፡ ይህን ፡ የመለያየት ፡ መሣሪያ ፡ እስከ ፡ ፉናቲክነት ፡ እንደሚያደርሱት ፡ መዘንጋት ፡ አይገባንም ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ በጋዜጦች ፡ በራዲዮ ፡ በንግግሮችና ፡ በመጻሕፍትም ፡ አማካይነት ፡ ሁሉም ፡ በየበኩላቸው ፡ የሚገልጡትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አሳቦችና ፡ አስተያየቶች ፡ ጥያቄዎችም ፡ ተከታትለን ፡ ያስተዋልናቸውና ፡ የሰማናቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የተዘበራረቁ ፡ የተደበላለቁና ፡ የተማቱ ፡ ሊስማሙም ፡ የማይችሉ ፡ ሆነው ፡ ከመታየታቸው ፡ የተነሣ ፡ ተመልካች ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ነገሩን ፡ ሲያስተውለው ፡ እብድ ፡ በሆነ ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ የሚኖር ፡ ይመስለዋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እነዚህ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮች ፡ የሚከተሉት ፡ ዐላማ ፡ ዞሮ ፡ ዞሮ ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ መግባባትን ፡ የሚሻ ፡ በሰላም ፡ አብሮ ፡ ለመኖር ፡ የሚቻልበትንም ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ መፈለግ ፡ የተሰነዘረ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በመካከላቸው ፡ ያለው ፡ መለያየት ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ የበረታ ፡ ሆኖ ፡ አይገኝም ።

እንግዲህ ፡ ይህን ፡ መጻፍ ፡ ለማዘጋጀት ፡ ስንነሣ ፡ አሳባችን ፡ በእነዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በዘረዘርናቸው ፡ ጉዳዮች ፡ መጠመዱንና ፡ መዋጡን ፡ እነዚሁም ፡ ነገሮች ፡ የዘመናችንን ፡ ሥልጣኔ ፡ በቅርብ ፡ የሚመለከቱ ፡ መሆናቸውን ፡ ልንረዳው ፡ ያስፈልጋል ።

አሁን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የሚገኙት ፡ ጥያቄዎች ፡ ባሳባችን ፡ የተደቀኑ ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ። የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ሥልጣኔ ፡ ጉዳይ ፡ አሳባቸው ፡ በግለት ፡ የተነሣሣ ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡ ከባድ ፡ ችግሮች ፡ ሆነው ፡ የተቈጠሩት ፡ ነገሮች ፡ ምንድናቸው ? መድኀኒቱስ ፡ ምንድነው ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ? በዚህ ፡ ረገድ ፡ የተወጠኑት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ያሳብ ፡ ዕቅዶች ፡ ምንድናቸው ? እነዚህን ፡ ጥያቄዎች ፡ ተከትለን ፡ ጉዳዩን ፡ የመረመርነው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስተያየታችን ፡ ነገሩን ፡ በጥልቅ ፡ ሊመለከተው ፡ ይችላል ፤ እኛም ፡ ሥልጣኔ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ የቱን ፡ ያኽል ፡ ሰፊ ፡ ትርጉም ፡ ያቀፈ ፡ መሆኑን ፡ እንደርስበታለን ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ነገሩን ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ዘልቀን ፡ በዝርዝር ፡ ከመመርመራችን ፡ በፊት ፡ አንባቢ ፡ ሊዘነጋው ፡ የማይገባ ፡ አንድ ፡ ዋና ፡ ነገር ፡



መኖሩን ፡ ሳናሳስብ ፡ አናልፍም ። የመሬትን ፡ ክብደትና ፡ ትልቅነት ፡ በጥበብ ፡ መስፈር ፡ ይቻላል ። ከዋክብትም ፡ በምን ፡ ዐይነት ፡ የሺሚ ፡ ቅመም ፡ እንደ ፡ ተቀመሙ ፤ እንዴት ፡ እንደ ፡ ተፈጠሩ ፡ በውስጣቸው ፡ የሚገኙት ፡ ነባር ፡ ፍጡሮች ፡ ባሕርያቸው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከውስጣቸውም ፡ ኀይል ፡ የሚሰጠውን ፡ ዘዴ ፡ እንዴት ፡ ለማግኘት ፡ እንደሚቻል ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ሰው ፡ ጠልቆ ፡ ለማወቅ ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ የሰው ፡ መንፈስ ፡ ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ ማንኛውም ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፤ የሚኖረውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የማሰብ ፡ ችሎታ ፤ አሳቡም ፡ የሚከተላቸውን ፡ ተዘዋዋሪ ፡ መንገዶች ፡ መርምሮ ፡ ሊደረስበት ፡ አይቻልም ። በዚህ ፡ በኩል ፡ የሚደረገው ፡ ተመራማሪነት ፡ አስቸጋሪ ፡ በመሆኑ ፡ የሚበገር ፡ አይዶለም ። ስለዚህ ፡ ማንኛውም ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ ነገድ ፡ ሊመረመር ፡ የሚቻል ፡ ነገር ፡ አይደለም ፤ ከቀሩትም ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ ጉዳይ ፡ መፍትሔ ፡ የሌለው ፡ (ፕሮብሌም) ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገር ፡ ነው ።

ሌላው ፡ ሁሉ ፡ ቀርቶ ፡ በታሪክ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ምሳሌ ፡ አድርገን ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ በሜይጂ ፡ ዘመን ፡ የሆነውን ፡ መለዋወጥ ፡ ይኸውም ፡ የጃፓን ፡ ታምር ፡ እስከ ፡ መባል ፡ የደረሰውን ፡ እንዲሁም ፡ በቅርብ ፡ ዘመን ፡ የደረሰውን ፡ በመስኮብ ፡ አገር ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ፡ በ፲፱፻፲፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተፈጸመውን ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በሺና ፡ አገር ፡ የሆነውን ፡ የኮሚኒስት ፡ ሬቦሊሲዮን ፡ በኩባና ፡ በኮንጎ ፡ የሆነውንም ፡ ሁከት ፡ እናስተውል ። እስቲ ፡ የትኛው ፡ ባለታሪክ ፡ ወይም ፡ ማንኛው ፡ ሊቅ ፡ ነው ፡ በታሪክ ፡ ክፍል ፡ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ እንደሚፈጸሙና ፡ የሚያስከትሉትንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ለማወቅ ፡ ዐውቆም ፡ ለመናገር ፡ የቻለ ? እንግዲህ ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ደንቈሮችና ፡ ዕውሮች ፡ ሆነው ፡ እስከሚኖሩበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ይህም ፡ ማለት ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮና ፡ በፖሊቲካ ፡ በኩል ፡ በመካከላቸው ፡ ባሉት ፡ ግንኙነቶች ፡ የሚሆነውን ፡ ለማወቅና ፡ ሊደርስ ፡ የሚችለውንም ፡ ነገር ፡ ለመቈጣጠር ፡ የማይችሉ ፡ ሆነው ፡ እስከሚገኙበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ሥልጣኔም ፡ ሆነች ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ ዕድል ፡ የሚያደርጉት ፡ እርምጃ ፡ ያልተረጋገጠ ፤ የማያስተማምን ፤ አጋጣሚን ፡ ተከትሎ ፡ የሚጓዝ ፡ ሆኖ ፡ ይኖራል ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የሚፈጠሩት ፡ ነገሮች ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ መመለሻ ፡ የሌላቸውና ፡ አመጣጣቸው ፡ ሊታወቅ ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ እየቀጠለ ፡ ይሄዳል ።

ይህ ፡ የምንናገረው ፡ ነገር ፡ ግልጥነት ፡ እንዲኖረው ፡ ለማድረግ ፡ እንዲህ ፡ ስንል ፡ በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ እናብራራዋለን ። አውሮፓውያን ፡

ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔን ፡ በመፍጠራቸው ፡ ምክንያት ፡ ድንቅ ፡ የሆነ ፡
ሥራ ፡ መፈጸማቸው ፡ ሊካድ ፡ የማይቻል ፡ ነገር ፡ ነው ። ዋጋውም ፡
የላቀ ፡ መሆኑን ፡ ማንም ፡ ሊስተው ፡ አይችልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህቺን ፡
ሥልጣኔ ፡ መሣሪያ ፡ አድርገው ፡ የቀሩትን ፡ ሕዝቦች ፡ የተገዥነት ፡
ቀንበር ፡ ሊጭኑባቸው ፡ ስላሰቡ ፡ እነዚህ ፡ ሕዝቦች ፡ ከዚህ ፡ ከተሰነዘረ
ባቸው ፡ ግፍ ፡ ለማምለጥ ፡ መንገድ ፡ መፈለግ ፡ ማግኘትም ፡ ግዴታ ፡
ሆነባቸው ። ይህቺን ፡ ሥልጣኔ ፡ የፈጠሩ ፡ ሕዝቦች ፡ በግዙፍ ፡ አካል ፡
በኩል ፡ በፈጸሙት ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ ያገኙትን ፡ የኀይል ፡ ብልጫ ፡
ሊገምቱት ፡ ችለዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ በእነሱ ፡ የተገፉ ፡ የተበደሉ ፡ ሕዝቦች ፡ ራሳ
ቸውን ፡ ለማዳን ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ዘዴ ፡ በፕሲኮሎጂ ፡ በኩል ፡ እንደሚ
ያመጡ ፡ ሊያውቁት ፡ አልቻሉም ። ምክንያቱም ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ እንደተ
ናገርነው ፡ ሰው ፡ ሳይንስን ፡ መሣሪያ ፡ በማድረግ ፡ በድን ፡ በሆነው ፡
አካል ፡ ላይ ፡ የበላይነቱንና ፡ የገዥነቱን ፡ ሥልጣን ፡ ሊጭንበት ፡ ይች
ላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በዚሁ ፡ መጠን ፡ የሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ኅደኛው ፡ በሆነው ፡
በመሰሉ ፡ ማለት ፤ በሰብአዊ ፡ ፍጡር ፡ ላይ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አግኝቶ ፡
ሊገዛው ፡ ወይም ፡ አሳቡን ፡ ሊቈጣጠረው ፡ አይችልም ። ምክንያቱም ፡ የ
ሰው ፡ ነፍስ ፡ ይልቁንም ፡ በእንቢተኛነት ፡ መንፈስ ፡ ስትነሣሣ ፡ ይቈጣ
ጠሯት ፡ ዘንድ ፡ የማይቻል ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። ለዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡
ባለቤት ፡ የሆነችውን ፡ የምዕራባውያንን ፡ ሕዝቦች ፡ ታሪክና ፡ ይህቺም ፡
ሥልጣኔ ፡ በቀረው ፡ ዓለም ፡ ክፍል ፡ አንጻር ፡ ላሳየችው ፡ ሁኔታ ፡ ተቃ
ዋሚ ፡ ሆኖ ፡ የተነሣውን ፡ የኰሚኒስምን ፡ አነሣሥ ፡ እያመዛዘን ፡ አስተ
ያይተን ፡ ስናስተውለው ፡ ለዚህ ፡ ጒዳይ ፡ የምንሰጠው ፡ ትርጉም ፡ ይህ ፡
ብቻ ፡ ነው ።

ኰሙኒስም ፡ ማለት ፡ ምንድነው ? የሚል ፡ ጥያቄ ፡ አለ ። ለዚህ ፡
ጥያቄ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ሲፈለግ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የተሰጠው ፡
መግለጫ ፡ ጒዳዩን ፡ በኢዴዎሎጂ ፡ በፍልስፍና ፡ ወይም ፡ በኤኰኖሚ ፡
በኩል ፡ በመመልከት ፡ የተደረገ ፡ በመሆኑ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የተሰጠው ፡
መግለጫ ፡ ትክክለኛነት ፡ ያለው ፡ አይደለም ። መግለጫው ፡ ሊፈለግ ፡
የሚገባው ፡ በእነዚህ ፡ ነገሮች ፡ በመመራት ፡ ሳይሆን ፡ በታሪክ ፡ በኩል ፡
ያለውን ፡ መልክ ፡ በመከተል ፡ ሊደረግ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ነው ። ሊቁ ፡
ኦርቴጋ ፡ ኢ ፡ ጋሴ ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ ያለውን ፡ የትምህርት ፡ አሰጣጥ ፡
ጒዳይ ፡ ድንቅ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ እየዘረዘረ ፡ ባደረገው ፡ ምርመራ ፡ በታ
ሪክ ፡ ትምህርት ፡ አሰጣጥ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ጒድለት ፡ አሳምሮ ፡ ገል
ጦታል ። እንደኔ ፡ አስተያየት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚያሳዝኑ ፡ ብዙ ፡
ስሕተቶች ፡ ሊደረጉ ፡ የቻሉት ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ።



የማርክሲስም ፡ ጒዳይ ፡ ባዲስ ፡ አስተያየት ፡ ሊጠናና ፡ ሊመረመር ፡
የሚገባው ፡ መሆኑን ፡ ደራሲው ፡ ሲያሳስብ ፡ ይህን ፡ ጒዳይ ፡ በዚህ ፡
መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ዘልቆ ፡ ለመመልከት ፡ አስቦ ፡
ያልተነሣ ፡ መሆኑን ፡ ላንባቢ ፡ ያስገነዝባል ። እንደ ፡ ኰሚኒስቶች ፡
አስተያየት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማርክሲስም ፡ አሳብ ፡ ዋና ፡ ዐላማው ፡
በሕዝብ ፡ ኑሮ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ የመበላለጥ ፡ ደረጃዎች ፡ ጨርሶ ፡
ለመሠረዝ ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚፈጠር ፡ ገነት ፡ ተብሎ ፡
የተሰየመው ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሊሆን ፡ የማይችል ፡ የሐሰት ፡
ሐሰት ፡ ነው ። ማርክሲስም ፡ ተፈጻሚነት ፡ ያለው ፡ ዐላማ ፡ አይደለም ፤
ነገር ፡ ግን ፡ ለሌላ ፡ ነገር ፡ የሚያገለግል ፡ መሣሪያ ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠር ፡
ነው ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ መሣሪያ ፡ በመሆኑ ፡ መጠን ፡ እሱ ፡ የሚ
ሠራውን ፡ ሥራ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ተመሳሳይነት ፡ ባላቸው ፡ በሌሎች ፡
መሣሪያዎች ፡ መፈጸም ፡ ይቻላል ።

# ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ግርማዊነትዎ ፡ ለሕዝብዎ ፡ የአዲሷን ፡ ሥልጣኔ ፡ ዘመን ፡ ሲከፍትለት ፡ ከማያውቀው ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ እንዲገባ ፡ አድርጎለታል ። ላንድ ፡ ሕዝብ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ ሊደረግለት ፡ አይችልም ። የሥልጣኔን ፡ ተግባሮች ፡ ለመፈጸም ፡ የሚያስፈልጉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ለማግኘት ፡ እንዲቻል ፡ በያይነቱ ፡ ከፍተኞች ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ከፍቷል ፤ አሁንም ፡ በየጊዜው ፡ በተጨማሪ ፡ የመክፈቱን ፡ ተግባር ፡ በመቀጠል ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። ዩኒቤርሲቲ፡ ኮሌጅ ፤ የእርሻ ፡ የጤና ፤ የመሐንዲስና ፡ የሕንጻ ፡ ኮሌጆች ፡ ተከፍተዋል ። በውስጡም ፡ ብዙ ፡ ፋኩልቴዎች ፡ የሚገኙበት ፡ ዩኒቬርሲቲ ፡ ተቋቁሟል ። እንደዚሁም ፡ ፓርላማ ፤ የጦር ፡ አካዴሚ ፤ የመርከብ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የአየር ፡ ኀይልና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ ቆመዋል ። ኢትዮጵያ ፡ የተባበሩት ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ ከተቋቋመ ፡ ጀምሮ ፡ የድርጅቱ ፡ አባል ፡ ሆና ፡ በውስጡ ፡ ትገኛለች ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ሕዝብዎ ፡ ከሦስት ፡ ሺ ፡ ዘመናት ፡ በላይ ፡ አባቶቻችን ፡ በትዕግሥት ፡ በትምህርት ፤ በማመዛዘን ፡ በጀግንነት ፤ በማስተዋልና ፡ በኢክስፔሪያንስ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እያሉ ፡ ያቋቋሙትና ፡ እንደ ፡ ቅርስ ፡ አድርገው ፡ አውርሰውት ፡ የነበረውን ፡ ሥልጣኔ ፡ ትቶ ፡ በሷ ፡ ቦታ ፡ አዲስ ፡ የተገኘችውን ፡ ሥልጣኔ ፡ በመቀበል ፡ ላይ ፡ በመሆኑ ፡ ይህም ፡ የቀድሞ ፡ ጠባዩን ፤ የቀድሞ ፡ አስተያየቱንና ፡ የቀድሞ ፡ ሁኔታውን ፡ እየተወ ፡ አዲስ ፡ ባህልና ፡ አዲስ ፡ አኳኋን ፡ እንዲይዝ ፡ አስገድዶታል ። ያውሮፓ ፡ ሥልጣኔ ፡ የተመሠረተችው ፡ ከግሪኮች ፡ በተገኘው ፡ ጥበብና ፡ በክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብም ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ክርስትናን ፡ የተቀበለ ፡ ሲሆን ፡ ካውሮፓውያን ፡ ጋራ ፡ የሃይማኖት ፡ ወንድማቸው ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ይህም ፡ የሥልጣኔያቸው ፡ ተካፋይ ፡ ሆኖ ፡ እንዲገኝ ፡ ስለሚያደርገው ፡ አዲሷን ፡ ሥልጣኔ ፡ በሚቀበልበት ፡ ጊዜ ፡ በመካከላቸው ፡ መግባባት ፡ እንዲኖር ፡ በጣም ፡ ይረዳዋል ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ለምሳሌ ፡ ዐረብ ፡ የሆኑ ፡ አገሮች ፡ ከቀድሞ ፡ ጀምሮ ፡ የግሪክን ፡ ሊቃውንት ፡ መጻሕፍት ፡ በቋንቋቸው ፡ የተረጐሚቸው ፡ በመሆናቸው ፡ በሕክምና ፤ በፍልስፍናና ፡ በሳይንስ ፡ በኩል ፡ ተቀዳሚ ፡ የሆነ ፡ ዕውቀት ፡ አግኝተዋል ። ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ ክርስትናን ፡ ከተቀበለች ፡ በኋላ ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ቅዱሳን ፡ መጻሕፍት ፡ የሆኑትን ፡ ከግሪክ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ የተረጐመቻቸው ፡ ሆና ፡

ስትገኝ ፡ እነዚያ ፡ ለግሪክ ፡ ሥልጣኔ ፡ መሠረት ፡ የሆኑትን ፡ የጥበብና ፡ የዕውቀት ፡ መጻሕፍት ፡ ግን ፡ ባልታወቀ ፡ ምክንያት ፡ በቋንቋዋ ፡ ሳትተረጕማቸው ፡ ቀርታለች ። ይህ ፡ ደግሞ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ በጣም ፡ ሳያጐድላት ፡ አልቀረም ። የሆነው ፡ ሆኖ ፡ አሁን ፡ ከዓለም ፡ ተለይታ ፡ የኖረችውን ፡ ያኽል ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ድካም ፡ ከዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ጋራ ፡ ተቀላቅላ ፡ የዘመኗን ፡ ሥልጣኔ ፡ ስትሳተፍ ፡ ትታያለች ። ሁል ፡ ጊዜ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ድካም ፡ ይልቁንም ፡ ደግሞ ፡ አሁን ፡ የተባበሩት ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ያፍሪቃን ፡ አገሮች ፡ በሰፊው ፡ ለመርዳት ፡ አስበው ፡ በኤክስፔርቶቻቸው ፡ አማካይነት ፡ በዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ለሚያደርጉት ፡ የኤኮኖሚ ፡ ጥናት ፡ ዋናውን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ላይ ፡ እንዲቋቋም ፡ መፍቀዳቸው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጓደኞቿ ፡ በሆኑት ፡ በአፍሪቃ ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ የሚገባትን ፡ ደረጃ ፡ ይዛ ፡ እንድትገኝ ፡ አድርጎላታል ።

ባለፉት ፡ ዘመናት ፡ የዓለምን ፡ ሕዝቦች ፡ የሚያንቀሳቅሷቸው ፡ ጉዳዮች ፡ የተለያዩ ፡ ነበሩ ። ክርስቲያኖችና ፡ እስላሞች ፡ ጦርነት ፡ በሚዋጉባቸው ፡ ዘመኖች ፡ መንፈሳቸው ፡ የተጠመደበት ፡ ዋናው ፡ ጉዳይ ፡ ሃይማኖት ፡ ነበር ። የቀሩትም ፡ ሕዝቦች ፡ በየበኩላቸው ፡ ሌሎች ፡ ጉዳዮች ፡ ነበሩባቸው ። ቀጥሎ ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ ሽሚያ ፡ መጣ ። በዚሁ ፡ ዘመን ፡ ግማሾቹ ፡ አጥቂዎች ፡ ግማሾቹም ፡ ተጠቂዎች ፡ ሆነው ፡ ተገኙ ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ የዓለምን ፡ ሕዝቦች ፡ በክፊል ፡ ሳይሆን ፡ በጠቅላላ ፡ የሚያንቀሳቅሳቸውና ፡ የሚያተራምሳቸው ፡ ጉዳይ ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ ለመራመድና ፡ ለመፎካከር ፡ ነው ። የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ ሥልጣኔን ፡ ዐላማ ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ እሷ ፡ ሲሽቀዳደሙ ፡ ይታያሉ ። ኢትዮጵያም ፡ ከዚህ ፡ ውድድር ፡ ውስጥ ፡ ገብታ ፡ አብራ ፡ ትገሠግሣለች ። ስለዚህ ፡ የሥልጣኔን ፡ ትርጉም ፡ ለማወቅ ፡ ብንሞክር ፡ መንፈሳችን ፡ ሊጠመድበት ፡ የሚገባው ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ጉዳይ ፡ ሊኖር ፡ አይችልም ።

ግርማዊነትዎ ፡ መላ ፡ ሕይወቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ላደረገበት ፡ ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የሚረዳ ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ አዘጋጅተን ፡ ብናበረክት ፡ እንደ ፡ ዐቅማችን ፡ የድካምዎ ፡ ተካፋዮች ፡ ሆነን ፡ እንገኛለን ፡ በማለት ፡ ይህቺን ፡ መጽሐፍ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ አድርጌ ፡ በታላቅ ፡ ትሕትና ፡ አቀርባለሁ ።

«ሁሉም ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ያረጃሉ ፤ እንደ ፡ መጐናጸፊያ ፡ ትለዋውጣቸዋለህ ፤ እነሱም ፡ ይለወጣሉ ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ያው ፡ ነህ» ።

ዳዊት ፡ መዝ ፡ ፻፪ ፡ ቍ ፡ ፳፮-፳፯ ።

# የ ሥ ል ጣ ኔ ፡ ት ር ጕ ም ።

ሰዎች ፡ ራሳቸውን ፡ ለማረምና ፡ ኑሯቸውን ፡ ለማሻሻል ፡ ሲሉ ፡ በሥጋና ፡ በመንፈስ ፡ ያፈሩት ፡ ከመጀመሪያ ፡ ጀምሮ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ የተከማቸው ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ ሥልጣኔ ፡ ይባላል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህንኑ ፡ በሚገባ ፡ ለመረዳት ፡ ሲታሰብ ፡ ከዝርዝር ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፡ ያስፈልጋል ። ፀሐይ ፡ እሷ ፡ በመካከል ፡ ሆና ፡ ዙሪያውን ፡ ከውስጧ ፡ በሚፈነጠቁ ፡ ጮራዎች ፡ ተከባ ፡ እንደምትታይ ፡ ሁሉ ፡ ሥልጣኔ ፡ የምትባለው ፡ ቃልም ፡ እንደዚሁ ፡ አካሎቿና ፡ ጭፍሮቿ ፡ በሆኑ ፡ በብዙ ፡ ቃሎች ፡ ታጅባ ፡ ትታያለች ። ፀሐይ ፡ ሥነ ፡ ፍጥረቷ ፡ የተቀመመው ፡ በምን ፡ ዐይነት ፡ (ማቴየር) ፡ አካላት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማወቅ ፡ ሲፈለግ ፡ የሚቻልበት ፡ መንገድ ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ፤ ይኸውም ፡ የብርሃኗን ፡ ጠባይ ፡ በልዩ ፡ መነጥር ፡ እያነጠሩና ፡ እያጣሩ ፡ በመመርመር ፡ ነው ። ይህም ፡ መነጥር ፡ ስፔክትሮስኮፕ ፡ የሚባለው ፡ ነው ። እኛም ፡ የሥልጣኔን ፡ ትክክለኛ ፡ ትርጉም ፡ ልንደርስበት ፡ የምንችለው ፡ እነዚህን ፡ የተባሉትን ፡ ቃሎች ፡ በመመርመርና ፡ በማበጠር ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ስናደርግ ፡ ሊቃውንት ፡ የዕውቀት ፡ መነጥራቸውን ፡ እንዲያውሉን ፡ እንጠይቃቸዋለን ።

ስለዚህ ፡ በብዙ ፡ ዐይነት ፡ ጠባይ ፡ የምትገለጠውን ፡ ሥልጣኔ ፡ የተባለችውን ፡ ቃል ፡ በመልክ ፡ በመልኳ ፡ እየለየን ፡ ለማጥናት ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ እንሞክራለን ። ይህንንም ፡ ስናደርግ ፡ ካንድ ፡ ሙዜ ፡ ገብተን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የታሪክ ፡ ዕቃዎች ፡ እየዞርን ፡ እንደ ፡ መጐብኘት ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ። ሳይንስ ፤ ሥነ ፡ ጥበብ ፤ ፍልስፍና ፤ ድርሰት ፤ ፓርለማ ፤ ዴሞክራሲ ፤ ማቴሪያሊስም ፤ ፊናንስ ፤ ኤኮኖሚ ፡ የሚባሉ ፡ እነሱንም ፡ የመሰሉ ፡ ከሥልጣኔ ፡ የፈለቁ ፡ ሌሎችም ፡ ብዙ ፡ ቃሎች ፡ ከፊታችን ፡ ተደርድረው ፡ እናያለን ። እነዚህም ፡ ቃሎች ፡ በጆሮ ፡ ሲሰሟቸውና ፡ በዐይን ፡ ሲያዩዋ

ቸው ፡ ስለሚያምሩ ፡ በሙዜ ፡ ውስጥ ፡ የተቀመጡ ፡ የታሪክ ፡ ዕቃዎች ፡ መስለው ፡ ቀርበውልናል ። ሁኔታቸውን ፡ ጠልቀን ፡ ለማወቅ ፡ ልባችን ፡ ሳይፈልግ ፡ አይቀርም ። ነገር ፡ ግን ፡ በሙዜ ፡ ውስጥ ፡ አስረጅና ፡ መሪ ፡ የሚሆን ፡ ታሪኩን ፡ የሚያውቅ ፡ ብልኅ ፡ ሰው ፡ እንደሚያስፈልግ ፡ ሁሉ ፡ እኛም ፡ የእነዚህን ፡ ቃሎች ፡ ታሪክ ፡ የሚነግረን ፡ ሰው ፡ እንዲኖር ፡ ያሻል ።

ሥልጣኔ ፡ ብዙ ፡ መልክ ፡ ያላት ፡ በመሆኗ ፡ እነዚህ ፡ ቃሎች ፡ የጠባይዋን ፡ ስልቶች ፡ የሚገልጡልን ፡ ናቸው ። እኛም ፡ በእነዚህ ፡ ቃሎች ፡ ተከበን ፡ እንኖራለን ። የዋህ ፡ የሆነ ፡ አንባቢ ፡ ሥልጣኔ ፡ ለምትባለው ፡ ላንዲት ፡ ቃል ፡ አንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ሊጻፍላት ፡ ያስፈልጋል ፡ ወይ ፡ ብሎ ፡ ሳያስብ ፡ አይቀርም ። ዐውቀን ፡ ካላሳጠርነው ፡ በቀር ፡ ይህን ፡ የሚያኽሉ ፡ መቶ ፡ መጻሕፍት ፡ ብንጽፍ ፡ በቂ ፡ አይሆንም ። የሰው ፡ አሳብ ፡ ሰፊ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ መጠን ፡ ሥልጣኔና ፡ በውስጧ ፡ ያሉም ፡ ቃሎች ፡ ትርጉማቸው ፡ ባጫር ፡ የሚገለጥ ፡ መስሎ ፡ የሚታይ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ በሰፊው ፡ እንረዳው ፡ ያልን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ላስቲክ ፡ እየተሳበ ፡ ሩቅ ፡ ይወስደናል ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ ቃል ፡ ማለት ፡ ምንድነው ? የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ይመጣል ። መቼም ፡ ቢሆን ፡ አሳብና ፡ ቃል ፡ ተመዛዛኞች ፡ ሆነው ፡ ሊገኙ ፡ አይችሉም ። የሰው ፡ አሳብ ፡ መጨረሻ ፡ የሌለው ፡ ሰፊ ፡ ነገር ፡ ሲሆን ፡ የአሳብ ፡ መግለጫ ፡ የሆኑት ፡ ቃላት ፡ ግን ፡ በመዝገብ ፡ ይጠቀለላሉ ። ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ሰው ፡ ላሳቡ ፡ ወሰን ፡ ያበጅለት ፡ ዘንድ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ያገኘዋል ። አሳብ ፡ የነፍስ ፡ ባሕርይ ፡ ሲሆን ፡ ቃል ፡ የሥጋን ፡ ጠባይ ፡ የሚያሳይ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ነፍስ ፡ በሥጋ ፡ ውስጥ ፡ አድራ ፡ እንደምትገኝ ፡ አሳብም ፡ በቃል ፡ ውስጥ ፡ አድሮ ፡ ይኖራል ። ነፍስ ፡ ሥጋን ፡ እንደምታንቀሳቅሰው ፡ አሳብም ፡ ለቃሎች ፡ ሕይወት ፡ ይሰጣቸዋል ። ነፍስ ፡ ከሄደች ፡ በኋላ ፡ ሥጋ ፡ በድን ፡ እንደምትሆን ፡ ሁሉ ፤ አሳብም ፡ የተሰወረ ፡ ሲሆን ፡ ቃሎች ፡ በድን ፡ ሬሳ ፡ ይሆናሉ ። ለምሳሌ ፤ በሂየሮግሊፍና ፡ በኩኔኢፎርም ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ የጥንት ፡ ቃሎች ፡ ይህ ፡ መጥፎ ፡ ዕድል ፡ ደርሶባቸዋል ። ስለዚህ ፡ የያንዳንዱን ፡ ቃል ፡ ትርጉም ፡ በትክክል ፡ ማወቅ ፤ አሳቡንና ፡ መንፈሱን ፡ እንደ ፡ መጨበጥ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ። ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ሥልጣኔ ፡ የምትባለው ፡ ቃል ፡ ትልቅ ፡ አሳብ ፡ የያዘች ፡ ሰፊ ፡ ትርጉም ፡ ያላት ፡ ነች ። በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የምንጣጣረው ፡ መንፈሱን ፡ ለመጨበጥ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ብዙ ፡ ሳያደክመን ፡ አይቀርም ። ከደከምን ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ሳያጠግበን ፡ ቢቀር ፡ ወሰን ፡ በሌለው ፡ በሰው ፡ መንፈስ ፡ ውስጥ ፡ ገብተን ፡ የምንጓዝ ፡ ነንና ፡ ዐውቀን ፡ ካላሳጠርነው ፡ የማይገፋ ፡ መሆኑን ፡ አለመዘንጋት ፡ ይገባናል ። በቃል ፡ ትር



ጉም ፡ ምክንያት ፡ በመካከላቸው ፡ አለመግባባት ፡ እየተፈጠረ ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ጦርነት ፡ ተዋግተዋል ፤ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ ፈሷል ።

አንድ ፡ ሊቅ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ በታሪክ ፡ አማካይነት ፡ ጥናት ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ በሦስት ፡ ሺ ፡ ዘመናት ፡ ውስጥ ፡ ስምንት ፡ ሺ ፡ ጊዜ ፡ የወዳጅነት ፡ ውል ፡ ተፈራርመው ፤ ስምንት ፡ ሺ ፡ ጊዜ ፡ ውላቸውን ፡ አፍርሰው ፡ ስምንት ፡ ሺ ፡ ጊዜ ፡ ጦርነት ፡ እንደ ፡ ተዋጉ ፡ ያረጋግጥልናል ። እንግዲህ ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ ወረቀትና ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ ፊርማ ፡ ለምን ፡ ጠቀመ ? ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የወዳጅነት ፡ ውል ፡ የሚፈረመው ፡ አንዱ ፡ ጎረቤቱን ፡ እንቅልፍ ፡ ለማስተኛት ፡ እያሰበ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።

ኢትዮጵያና ፡ ኢጣልያ ፡ ዐድዋ ፡ ላይ ፡ የተዋጉት ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ ምክንያት ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ ክርስቲያኖች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የተለያዩት ፡ ባንዳንድ ፡ ቃሎች ፡ ምክንያት ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ የቃል ፡ ትርጉም ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ አይደለም ።

የመንግሥታት ፡ ወኪሎች ፡ በሚሰበሰቡበት ፡ ጉባኤ ፡ ስንት ፡ ሊቃውንት ፡ ባለማቋረጥ ፡ ሲጨቃጨቁና ፡ ሲከራከሩ ፡ ከርመው ፡ በመጨረሻ ፡ ሳይስማሙ ፡ ሁሉም ፡ ቅር ፡ ብሏቸው ፡ ይለያያሉ ። ምክንያቱም ፡ የማይስማሙባቸው ፡ ቃሎች ፡ በመኖራቸው ፡ ነው ። ቃል ፡ አስማት ፡ ያደረባት ፡ ነገር ፡ ነች ። ሰው ፡ ጨበጥኋት ፡ ብሎ ፡ ሲደስት ፡ ትሰወርና ፡ ባዶ ፡ እጁን ፡ ይቀራል ። ስንት ፡ መንግሥታት ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ ዘለዓለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ የወዳጅነት ፡ ውል ፡ ተዋውለው ፡ ከተፈራረሙ ፡ በኋላ ፡ ምንም ፡ ሳይጠቀሙበት ፡ የማይረባ ፡ ወረቀት ፡ ታቅፈው ፡ ቀርተዋል ። ምክንያቱም ፡ በወረቀት ፡ ላይ ፡ ለሰፈሩት ፡ ቃሎች ፡ ሰጥተዋቸው ፡ የነበረው ፡ የትርጉም ፡ ዋጋው ፡ ስለ ፡ ጠፋ ፡ ነው ። መንፈስና ፡ አሳብ ፡ ስለማይጨበጡ ፡ ወኪላቸው ፡ ነገረ ፡ ፈጃቸው ፡ የሆነችው ፡ ቃል ፡ የምትባለው ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ራእይ ፡ አብራ ፡ ከእነሱ ፡ ጋራ ፡ ትሰወራለች ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሐተታ ፡ ያመጣነው ፡ የሥልጣኔ ፡ ትርጉም ፡ ምንድነው ? በማለት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ጉዳያችን ፡ እንመለስ ።

አሁን ፡ ባለንበት ፡ ዘመን ፡ የሚገኘው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥበብ ፡ ባለፈው ፡ ዘመን ፡ ያልነበረ ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ። ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ወደ ፡ ስምንት ፡ ሺሕ ፡ ዓመታት ፡ የሚደርስ ፡ ሲሆን ፤ ወይም ፡ ሊቃውንት ፡ እንደሚሉት ፡ ሰው ፡ ከተፈጠረ ፡ ከኻያ ፡ አምስት ፡ ሺሕ ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ ሚሊዮን ፡ ዓመታት ፡ የሚጠጋ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ያለፉት ፡ ትውልዶች ፡ ሁሉ ፡ እኛ ፡ ያሁኑ ፡ ሰዎች ፡ ያየነውን ፡ ጥበብ ፡ አላዩም ፡ ማለት ፡ ነው ። በአይሮፕ

ላን ፡ በባቡር ፡ በኦቶሞቢል ፡ ፈጣንና ፡ ምቹ ፡ በሆነ ፡ መርከብ ፡ ያለድካም ፡ እንጓዛለን ። በቤታችን ፡ ውስጥ ፡ ራዲዮ ፤ ስልክ ፤ የኤሌክትሪሲቲ ፡ ብርሃንና ፡ ሙቀት ፤ ፍሪጂዴር ፡ አሉን ። ስንታመም ፡ የምንፈወስበት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መድኀኒትና ፡ ሐኪም ፡ የምናገኝበት ፡ ሆስፒታል ፡ ተዘጋጅቶልናል ። ሕዝቡ ፡ በወኪሎቹ ፡ አማካይነት ፡ በፓርለማ ፡ እየቀረበ ፡ ድምፁን ፡ እየሰጠ ፡ መንግሥቱ ፡ ላገር ፡ የሚጠቅሙትን ፡ ጉዳዮች ፡ ሲወስን ፡ አላፊነቱን ፡ ይካፈላል ። በየስፍራው ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በብዛት ፡ ተከፍተዋል ። በቀን ፡ በቀኑ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የሚሆነውንና ፡ ባገር ፡ ውስጥም ፡ የተደረገውን ፡ ለሕዝቡ ፡ የሚገልጡለትና ፡ አዲስ ፡ የተፈጠረውን ፡ ጥበብ ፡ የሚያካፍሉት ፡ ወሬ ፡ አቀባዮች ፡ የሆኑት ፡ ጋዜጦች ፡ ይታተማሉ ። ኢንዱስትሪዎች ፡ በመራቀቅ ፡ አሳምረው ፡ ያዘጋጁዋቸው ፡ ለኑሮ ፡ የሚጠቅሙ ፡ በያይነቱ ፡ ዕቃዎች ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ እየተሻሻሉ ፡ ተሠርተው ፡ በርካሽ ፡ ዋጋ ፡ ይሸጣሉ ። እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ንብረቱና ፡ ሀብቱ ፡ እንዲከበር ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ተሠርቶ ፡ የፍርድ ፡ ቤቶችም ፡ ቆመውለታል ። ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የታየውን ፡ በመጽሐፍ ፡ እየጻፈ ፡ ዕውቀቱንና ፡ አስተያየቱን ፡ እንዲገልጥ ፡ ያሳብ ፡ ነጻነት ፡ ተሰጥቶታል ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ስንመለከት ፡ ሜትርሊንክ ፡ (Maeterlinck) የተባለው ፡ ደራሲ ፡ (ሰማያዊ ፡ ወፍ) ፡ ብሎ ፡ በሰየመው ፡ ቴያትር ፡ ውስጥ ፡ የገለጠልንን ፡ ድንቅና ፡ ትንግርት ፡ የሆኑ ፡ ነገሮች ፡ የሚታዩበትን ፡ በመሰለ ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ ገብተን ፡ የምንዋኝ ፡ ይመስለናል ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡ ባንድ ፡ አገር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ እየተስፋፋ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ፤ ምንጩም ፡ ካውሮፓ ፡ ሥልጣኔ ፡ የመጣ ፡ ነው ።

መኪና ፡ ባሪያ ፡ ሆኖ ፡ ሁሉን ፡ በሚሠራበት ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ የተፈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ ምቾትና ፡ ተድላ ፡ ዕውቀትና ፡ ጥበብ ፡ ሀብትና ፡ ዕረፍት ፡ ያገኙ ፡ በመሆናቸው ፡ ዕድላቸውን ፡ ያመሰግናሉ ። ከኛ ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ነበሩት ፡ ትውልዶች ፡ ተመልሰን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ባራቱ ፡ ማእዘን ፡ ተበታትነው ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩትን ፡ ሕዝቦች ፡ ታሪክ ፡ ስንመለከት ፡ ብዙዎች ፡ በየበኩላቸው ፡ ኑሯቸውን ፡ በማሻሻል ፡ ትልቅ ፡ እርምጃ ፡ አድርገው ፡ ይገኛሉ ። በእስያ ፡ ውስጥ ፡ የሺንና ፡ የህንድ ፡ ሕዝቦች ፡ በሕንጻ ፡ አሠራር ፤ በሃይማኖት ፤ በእርሻና ፡ በእጅ ፡ ጥበብ ፡ በሞራል ፡ ሠልጥነው ፡ በተለይም ፡ ሺን ፡ በሳይንስ ፡ ከብዙ ፡ ሺሕ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ከፍ ፡ ካለ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ደርሳ ፡ ነበር ። ሱሜሪና ፡ ግብጽ ፡ ፋርስና ፡ ሜድ ፡ ከለዳውያንና ፡ ባቢሎናውያን ፡ እንደዚሁ ፡ በብዙ ፡ ነገር ፡ ሥልጣኔያቸው ፡ የሚያስመሰግን ፡ እድገት ፡ አግኝቶ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ታውቋል ። በደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ አዝቴክ ፤ ማያና ፡ ኢንካ ፡ የሚባሉት ፡ ሕዝቦች ፡ የሠሯቸው ፡ ሕንጻዎችና ፡



መልካም ፡ ሕግ ፤ በቤተ ፡ ክህነትና ፡ በጦር ፡ ሰራዊት ፡ በኩል ፡ የነበረው ፡ ደንብና ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፤ ቤተ ፡ መንግሥታቸውና ፡ መቅደሶቻቸው ፡ የሀብታቸውንም ፡ ደረጃ ፡ የሚገልጥ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሐውልት ፡ የወርቅና ፡ የከቡር ፡ ድንጊያ ፡ ጌጥ ፡ የሚያስደንቅ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ታሪክ ፡ መርማሪዎች ፡ ያረጋግጡልናል ።

የእነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ሕዝቦች ፡ የግል ፡ ሥልጣኔያቸው ፡ በመጨረሻ ፡ ከነበረበት ፡ እድገት ፡ ላይ ፡ ሊደርስ ፡ የቻለው ፡ በብዙ ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ በሚቈጠር ፡ ዘመን ፡ በዕውቀት ፤ በጥበብ ፡ በተመራማሪነት ፤ ባደረጉት ፡ መራቀቅ ፡ መሆኑ ፡ አይካድም ። ከግሪክ ፡ አገር ፡ የፈለቀችው ፡ ሥልጣኔ ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ በጠራናቸው ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ የሚገኙት ፡ ዕውቀቶችና ፡ ጥበቦች ፡ ሳይጐድሏት ፡ በተጨማሪ ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ አነጋገር ፡ ሳይንስና ፡ ቴክኒክ ፡ ተብለው ፡ የሚጠሩትንና ፡ በመጀመሪያዎቹ ፡ መሥመሮች ፡ የጠቀስናቸውን ፡ ነገሮች ፡ ያፈራቻቸው ፡ ከሥር ፡ ከመሠረቱ ፡ ዘሩን ፡ ችግኙን ፡ አግኝታ ፡ ለአውሮፓ ፡ ሕዝቦች ፡ ማውረሷ ፡ ይህም ፡ ለእነሱ ፡ አሁን ፡ የምንመለከተውን ፡ ገናናነት ፡ እንዲያገኙ ፡ አድርጎላቸው ፡ መታየቱ ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ ነው ? ለዚህ ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገር ፡ ነው ። ብዙ ፡ ሊቃውንት ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ አጥንተውት ፡ ከሁሉም ፡ የሚሻለው ፡ ረናን ፡ (Renan) የተባለው ፡ የፈረንሳይ ፡ ሊቅ ፡ «የግሪክ ፡ ተአምር» ፡ ብሎ ፡ በተናገረው ፡ ቃል ፡ መስማማት ፡ የተሻለ ፡ መሆኑን ፡ ገልጠዋል ። ግሪኮች ፡ ለሳይንስና ፡ ለቴክኒክ ፡ ዕውቀቶች ፡ መሠረት ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ደርሰውባቸው ፡ በትምህርታቸውና ፡ በጥናታቸው ፡ ውስጥ ፡ አግብተዋቸዋል ። የሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ መሠረት ፡ አቶም ፡ መሆኑን ፡ ተናግረውታል ። በፍልስፍና ፡ በጂዎሜትሪና ፡ በማቴማቲክ ፡ በሳይንስ ፡ በጣም ፡ የገፉ ፡ ዕውቀት ፡ ነበራቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ጦርነት ፡ ባስከተለው ፡ ጥፋት ፡ እነሱ ፡ መሥርተዋት ፡ የነበረችው ፡ ሥልጣኔ ፡ ስለ ፡ ተቋረጠች ፡ ዓለምም ፡ ወደ ፡ ኋላዋ ፡ በመመለሷ ፡ ካሁኑ ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ ረዥም ፡ ዘመን ፡ ዘገየች ። እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ነገሩን ፡ ስንመረምረው ፡ የተመሰገነ ፡ የሕዝብና ፡ የመንግሥት ፡ አስተዳደር ፡ ማግኘት ፤ ውብ ፡ የሆኑ ፡ ሕንጻዎች ፡ መሥራት ፤ በድርሰትና ፡ በሙዚቃ ፡ በሥዕልና ፡ በሐውልት ፡ ቅርጽ ፡ መራቀቅ ፤ በጽዳትና ፡ በምቾት ፡ መኖር ፤ ጥሩ ፡ የጦር ፡ ሰራዊት ፡ አቋቁሞ ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ ማግኘት ፤ ርኅራኄና ፡ ትሕትና ፤ ትዕግሥትና ፡ ሠራተኛነት ፤ ሌሎች ፡ እነዚህን ፡ የመሰሉ ፡ መልካም ፡ ጠባዮች ፡ የሰውን ፡ ባሕርይ ፡ ትልቅና ፡ ለጋስ ፡ አድርገውት ፡ መመልከት ፡ እንሆ ፡ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ የሥልጣኔ ፡ ፍሬዎች ፡ ናቸው ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ የሳይንስና ፡ የቴክኖሎጂ ፡ ዕውቀቶች ፡

በተጨማሪነት ፡ ከፍተኛውን ፡ ደረጃ ፡ ይዘውት ፡ ይታያሉ ። ያም ፡ ሆነ ፡ ያ ፡ ሥልጣኔ ፡ በብዙ ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ ተገልጣ ፡ ልትታይ ፡ ትችላለች ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ዞሮ ፡ ዞሮ ፡ የሥልጣኔ ፡ ጠባይ ፡ በሁለት ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ፡ ይገለጣል ። ይኸውም ፡ በሰው ፡ ባሕርይና ፡ በግዙፍ ፡ አካሎች ፡ ሥራ ፡ ነው ። ሰው ፡ ብልኅ ፤ ደግ ፤ ትሑት ፤ ርኅሩኅ ፤ ተደሳች ፤ የታረመ ፤ ጨዋ ፤ መንፈሰ ፡ ሰፊ ፡ ልበ ፡ ትልቅ ፡ ሲሆን ፡ የሠለጠነ ፡ ሰው ፡ ያሰኘዋል ። እንደዚሁም ፡ ስሜቱ ፡ ደበዘዝ ፤ ክፉ ፤ ጨካኝ ፤ ትዕቢተኛ ፤ ነጭናጫ ፤ ባለጌ ፤ ሕገ ፡ ወጥ ፡ መንፈሰ ፡ ጠባብ ፡ ምኞተ ፡ ወራዳ ፡ ሲሆን ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ ያልሠለጠነ ፤ አውሬ ፤ እንስሳ ፤ ያሰኘዋል ። ባጭሩ ፡ አሳቡና ፡ ባሕርዩ ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ የተመራ ፡ ሲሆን ፡ ሥልጣኔ ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ሲመሰክርለት ፡ ወደ ፡ ክፉ ፡ ሲያደላ ፡ ደግሞ ፡ ከሰው ፡ ባሕርይ ፡ የወጣና ፡ ወደ ፡ እንስሳነት ፡ የሚያዘነብል ፡ ሆኖ ፡ ይገመታል ፤ ይህም ፡ ያልሠለጠነ ፡ ያሰኘዋል ።

በግዙፍ ፡ ነገሮች ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ሰው ፡ አለባበሱና ፡ መኖሪያ ፡ ቤቱ ፡ የጸዳ ፤ በኑሮው ፡ ዙርያ ፡ ጌጥና ፡ ኪነ ፡ ጥበብ ፡ በተራቀቀ ፡ አኳኋን ፡ ተሠርቶ ፡ የሚታይ ፤ ሀብትና ፡ ንዋይ ፡ በሕዝቡና ፡ ባገሪቱ ፡ ላይ ፡ የተናኘ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ እነዚህና ፡ እነሱንም ፡ የመሰሉት ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ የሥልጣኔ ፡ ምልክቶች ፡ ወይም ፡ ማስረጃዎች ፡ ሆነው ፡ ይቈጠራሉ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ ያከማቹ ፡ ሕዝቦች ፡ በከተሞቻቸው ፡ ጽዳት ፤ በሕንጻዎቻቸው ፡ ውበት ፤ በጦር ፡ መሣሪያዎቻቸው ፡ ኀይለኛነት ፡ በሥልጣኔ ፡ በኩል ፡ የሚሰጣቸው ፡ ደረጃ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ይገኛል ። የጥንት ፡ ሕዝቦች ፡ የነበራቸው ፡ ሥልጣኔ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መሆኑ ፡ በሕንጻዎቻቸው ፤ በፒራሚዶቻቸው ፤ ጽፈው ፡ ባስተላለፉልን ፡ መጻሕፍቶቻቸው ፤ በተዉልን ፡ የጥበብ  መታሰቢያዎቻቸው ፡ በሠሯቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጌጦች ፤ በቤተ ፡ ክህነትና ፡ በእርሻ ፡ በጦር ፡ ሰራዊትና ፡ በሕዝቡ ፡ አስተዳደር ፡ በኩል ፡ በነበሯቸው ፡ ሕጋጋትና ፡ ሥነ ፡ ሥርዐቶች ፡ መሆኑን ፡ ተናግረናል ።

ቶይዶንቢ ፡ ባለፉት ፡ ዘመናት ፡ እየተፈጠሩ ፡ ተመልሰው ፡ የጠፉት ፡ ሥልጣኔዎች ፡ ቍጥራቸው ፡ ከሃያ ፡ የደረሰ ፡ መሆኑን ፡ ይናገራል ።

አሁን ፡ ግን ፡ ከእነዚህ ፡ ጥንታውያን ፡ ከሆኑት ፡ ሕዝቦች ፡ የተገኘው ፡ የሥልጣኔ ፡ ቅርስ ፡ እየተረሳና ፡ እየቀረ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ ያውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ በመከተል ፡ ላይ ፡ ናቸው ። ይህ ፡ የሆነበት ፡ ምክንያቱ ፡ ምንድነው? ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ከሁሉም ፡ በልጣ ፡ ስለ ፡ ተገኘች ፡ ነዋ ፡ ተብሎ ፡ ይታመናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከፍ ፡



ብለን ፡ እንደተናገርነው ፡ የሥልጣኔ ፡ ትርጉም ፡ በሁለት ፡ ዐይነት ፡ መንገድ ፡ ሄዶ ፡ አንደኛ ፡ የሰውን ፡ ጠባይ ፡ በማሻሻል ፤ ሁለተኛ ፡ ለሰው ፡ ኑሮ ፡ የሚበጀውን ፡ ምቾትና ፡ ሀብት ፡ በማፍራት ፡ በእነዚህ ፡ በሁለቱ ፡ ነገሮች ፡ ይገለጣል ። ይህ ፡ ሲሆን ፡ የዘመናችን ፡ ሥልጣኔ ፡ ባሕርይዋ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያለ ፡ ነው ? ጥሩ ፡ ነች ፡ ወይስ ፡ መጥፎ ? ጠቃሚ ፡ ናት ፡ ወይስ ፡ የምትጐዳ ? ከሌሎች ፡ ሥልጣኔዎች ፡ ትሻላለች ፡ ወይስ ፡ ትከፋለች ፡ የሚሉ ፡ ጥያቄዎች ፡ ቀርበዋል ። ለእነዚህ ፡ ጥያቄዎች ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ በጒዳዩ ፡ ላይ ፡ ጥናት ፡ ስናደርግ ፡ ባንድ ፡ ትልቅ ፡ ዋሻ ፡ ገብተን ፡ በውስጡ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ለማወቅ ፡ ፈልገን ፡ ለመፈተሽ ፡ እንደ ፡ ተነሣን ፡ ያኽል ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ። ባንድ ፡ ትልቅ ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ስንገባ ፡ በውስጡ ፡ ምን ፡ እንዳለ ፡ አናውቅም ። አንድ ፡ የቆመ ፡ ትልቅ ፡ ቋጥኝ ፡ ድንጋይ ፡ አፍንጫችንን ፡ ሊመታን ፡ ወይም ፡ ከጒድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ልንወድቅ ፤ ወይም ፡ እባብም ፡ ሆነ ፡ ዘንዶ ፡ አንበሳም ፡ ሆነ ፡ ነብር ፡ ሊያጋጥመን ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ አልማዝ ፡ ሆነ ፡ ዕንቍ ፡ ልናገኝበት ፡ እንችላለን ። ስለዚህ ፡ መጥፎውንም ፡ ሆነ ፡ ጥሩውን ፡ ነገር ፡ ልናየው ፡ የምንችለው ፡ ብርሃን ፡ በማግኘት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ መብራት ፡ ይዘን ፡ ከዋሻው ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። በሥልጣኔ ፡ ውስጥም ፡ እንደዚሁ ፡ የሚጐዳና ፡ የሚጠቅም ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ለማወቅ ፡ እያንዳንዱ ፡ ጒዳይ ፡ ምግባሩና ፡ ባሕርዩ ፡ ዓላማውና ፡ ግቡ ፡ ደግ ፡ ወይም ፡ መጥፎ ፡ የሚያጠፋን ፡ ወይም ፡ የሚያለማን ፡ መሆኑን ፡ ስለማናውቅ ፡ ብርሃን ፡ ሰጥቶ ፡ የሚገልጥልን ፡ ሰው ፡ መሪ ፡ አድርገን ፡ ካልሄድን ፡ ከስሕተት ፡ ላይ ፡ ወድቀን ፡ እንጐዳለን ። ብርሃን ፡ ሆነው ፡ ሊመሩን ፡ የሚችሉ ፡ ሊቃውንት ፡ ናቸው ። ከእነሱ ፡ ጋራ ፡ ተገናኝተን ፡ ተመሪና ፡ መሪ ፡ ለመሆን ፡ የምንችለው ፡ በጻፏቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ማለት ፡ በድርሰታቸው ፡ አማካይነት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ድርሰት ፡ ሥልጣኔ ፡ ካፈራቻቸው ፡ ከማንኞቹም ፡ ነገሮች ፡ በላይ ፡ ሆኖ ፡ ቀደምትነት ፡ ሊሰጠው ፡ ይገባል ። ከሁሉ ፡ ነገር ፡ አስቀድመን ፡ ስለ ፡ ድርሰት ፡ ታሪክ ፡ መናገር ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የምናገኘው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ።

# የድርሰት ፡ ታሪክ ።

ድርሰት ፡ ማለት ፡ ታሪክና ፡ ቴአትር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ባለቅኔዎች ፤ ሊቃውንትና ፡ ፈላስፎች ፡ የሚጽፏቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ናቸው ። ሕዝቦች ፡ በሥልጣኔ ፡ በኩል ፡ ያደረጉትን ፡ እርምጃ ፡ ስንመለከተው ፡ በታሪካቸው ፡ ውስጥ ፡ የሥልጣኔ ፡ ዜናና ፡ የድርሰት ፡ ዜና ፡ በቅርብ ፡ የተያያዙና ፡ የተቈራኙ ፡ የተሳሰሩ ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ። ያለድርሰት ፡ ሥልጣኔ ፡ የለም ። እንደዚሁም ፡ ሥልጣኔ ፡ በሌለችበት ፡ ስፍራ ፡ ድርሰት ፡ አይገኝም ። አንድ ፡ ሕዝብ ፡ በሥልጣኔ ፡ ጐዳና ፡ መጓዝ ፡ ሲጀምር ፡ ለሕይወቱ ፡ ምዕራፎች ፡ ዕልባት ፡ ሆነው ፡ የሚታዩት ፡ ድርሰቶች ፡ ናቸው ። ለምሳሌ ፤ የእንግሊዝ ፡ ታሪክ ፡ በእነ ፡ ሚልተን ፡ ሼክስፒር ፡ ዲኬንስ ፡ ስኰት ፤ የጀርመን ፡ ታሪክ ፡ በእነ ፡ ገት ፤ ሺለር ፤ ሄን ፤ የፈረንሳይ ፡ ታሪክ ፡ በእነ ፡ ሮንሣር ፤ ኰርኔይ ፤ ራሲን ፤ ቮልተር ፤ ቪክቶር ፡ ሂጎ ፡ ድርሰቶች ፡ እየተለየ ፡ ለዘመኑ አካሄድ ፡ ምዕራፍ ፡ ሆኖ ፡ ይጠራበታል ። የሕዝቡ ፡ መንፈስ ፡ አዲስ ፡ ዐላማ ፡ የሚያገኘው ፤ ስሜቱ ፡ አዲስ ፡ ዝንባሌ ፡ የሚፈጥርለት ፤ አስተያየቱ ፡ አዲስ ፡ ግብ ፡ የሚወስንለት ፤ በጠቅላላው ፡ የሕዝቡ ፡ ሕይወት ፡ አዲስ ፡ ትርጕም ፡ መንፈሱም ፡ አዲስ ፡ ንቅናቄ ፡ የሚኖረው ፡ ጸሓፊዎቹ ፡ በሚያፈሩት ፡ ድርሰቶች ፡ አማካይነት ፡ ነው ። እስቲ ፡ ከእነዚህ ፡ ከጠራናቸው ፡ አገሮች ፡ አንዱን ፡ ወስደን ፡ ጸሓፊዎቹ ፡ የፈጸሟቸውን ፡ ሥራዎች ፡ ብንሠርዛቸው ፡ ይህ ፡ የተባለው ፡ አገር ፡ በቀረው ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ሲወሰን ፡ በዓለም ፡ ፊት ፡ የሚሰጠው ፡ ዋጋ ፡ የቱን ፡ ያኽል ፡ እንደሚያጐድል ፡ እንገምተው ። ለምሳሌ ፤ እንግሊዝ ፡ ያለሼክስፒር ፡ በሥልጣኔ ፡ በኩል ፡ ለዓለም ፡ ልታበረክት ፡ የምትችለው ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ በመቶ ፡ ሰማኒያ ፡ የተቀነሰ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። የቀሩትም ፡ አገሮች ፡ ይህንኑ ፡ ያኽል ፡ ነው ። አንድ ፡ ድርሰት ፡ ዋጋው ፡ በሦስት ፡ ዋኖች ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ ይመሠረታል ። አንደኛ ፡ የንግግር ፡ ውበት ፡ ሁለተኛ ፡ ያሳቡ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ሦስተኛ ፡ ደንበኛ ፡ አቀራረብ ፡ ናቸው ። በድርሰት ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ የቀሩት ፡ ዝርዝር ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ለእነዚህ ፡ ለሦስቱ ፡ መሠረታዊ ፡ ነገሮች ፡ እንደ ፡ ዘርፎች ፡ ሆነው ፡ ይቈጠራሉ ። አሁን ፡ እንግዲህ ፡ የእነዚህን ፡ የሦስቱን ፡ ነገሮች ፡ ጠባይ ፡ እንመልከት ።

አንደኛ ፡ የንግግር ፡ ውበት ፡ ብለናል ። አንድ ፡ ሰው ፡ ለንግግሩ ፡ ውበት ፡ ሊሰጠው ፡ የሚችለው ፡ ባለሙያ ፡ ሲሆን ፡ ነው ። ይህን ፡ የመሰለው ፡

ችሎታ ፡ ወይም ፡ ሙያ ፡ የሚገኘው ፡ በስጦታ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስጦታም ፡
አብሮ ፡ ይወለዳል ፡ እንጂ ፡ በትምህርት ፡ ሊያገኙት ፡ አይቻልም ። በትም
ህርት ፡ ሊገኝ ፡ ቢቻልማ ፡ ኖሮ ፡ ከየዩኒቨርሲቲው ፡ በያመቱ፡የሚወጡት ፡
በብዙ ፡ ሺሕ፡የሚቈጠሩት ፡ ተማሪዎች ፡ ሁሉ ፡ ደራስያን ፡ ይሆኑ ፡ ነበር ።
ነገር ፡ ግን ፡ ድርሰት ፡ በስጦታ ፡ ብቻ ፡ የሚገኝ ፡ በመሆኑ ፡ በየዘመኑ ፡
የሚነሡት ፡ ደራስያን ፡ ቊጥራቸው ፡ በጣም ፡ ያነሰ ፡ ሆኖ ፡ የሚታይበት ፡
በዚህ ፡ ነው ። የደራሲ ፡ ስጦታ ፡ የሚመነጨው ፡ ከስሜቱ ፡ ነው ። ይህም፡
የድርሰት ፡ ምንጭ ፡ ስሜት ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ። የደራሲ ፡ ስሜት ፡
ተቃኝቶ ፡ እንደተቀመጠ ፡ በገና ፡ ይቈጠራል ። የተቃኘ ፡ በገና ፡ ጥቂት ፡
ነገር ፡ ሲነካው ፡ ድምፅ ፡ ይሰጣል ፤ ድምፁም ፡ ያምራል ፤ ለጆሮ ፡ ይጣ
ፍጣል ። ደራሲም ፡ ስሜቱን ፡ እንዲንቀሳቀስ ፡ ለማድረግ ፡ ጥቂት ፡ ነገር ፡
ይበቃዋል ። ስሜቱም ፡ በተናወጠ ፡ ጊዜ ፡ በሚያምር ፡ ንግግር ፡ ድም
ፁን ፡ ያሰማል ።

ሁለተኛ ፡ የድርሰት ፡ መሠረት ፡ ያሳቡ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ነው ። ማንኛ
ውም ፡ ድርሰት ፡ በውስጡ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ከሌለ፡ዋጋው ፡ ጐደሎ፡ይሆናል።
አንድ ፡ ድርሰት ፡ ንግግሩ ፡ በጣም ፡ ያማረ ፡ ሆኖ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የሆነ ፡
አሳብ ፡ በውስጡ ፡ ላይኖርበት ፡ ይችላል ። የቃሉ ፡ አሰካክ ፤ የንግግሩ ፡
መጣራትና ፡ በጠቅላላው ፡ የጽሑፉ ፡ አቀራረብ ፡ ውብ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ አሳቡ ፡
ማለት ፡ በውስጡ ፡ ያለው ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ባዶ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ የድርሰቱን ፡
ዋጋ ፡ ሰማንያ ፡ በመቶ ፡ ጐደሎ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ። ይህ ፡ ሁለተኛው
መሠረታዊ ፡ ነገር ፡ ከየት ፡ ይገኛል ? ብዙ ፡ በማንበብ ፤ ብዙ ፡ በማሰብ ፤
ብዙ ፡ በመመልከት ፤ በመድከምና ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የሆነውን ፡ ጕዳይ ፡
በመፈለግ ፡ ባጭሩ ፡ በብልኅነት ፡ ይገኛል ። ይህ ፡ እንደ ፡ ሁለተኛ ፡ ሙያ ፡
የሚቈጠረው ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ጐደላቸው ፡ ብዙ ፡ ደራስያን ፡ ድርሰታቸው ፡
ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ የተወደደ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡ ምንም ፡ ያኽል ፡ ሳይ
ቈይ ፡ እየተረሳ ፡ ሄዶ ፡ ጨርሶ ፡ ይሞታል ። ይህን ፡ የመሰለው ፡ ድርሰት ፡
በሥሥ ፡ የወርቅ ፡ ቅጠል ፡ ተለብዶ ፡ እንደ ፡ ተሠራ ፤ ውስጡ ፡ ግን ፡
ድንጋይ ፡ ወይም ፡ ዕንጨት ፡ በሆነ ፡ የጌጥ ፡ ዕቃ ፡ ሊመስል ፡ ይችላል ።
በዚህ ፡ ዐይነት ፡ የተሠራ ፡ ጌጥ ፡ ሁሉ ፡ ከላይ ፡ ያለው ፡ የሚያብረቀርቅ ፡
ወርቅ ፡ እየለቀቀ ፡ ሲሄድ ፡ በመጨረሻ ፡ ከውስጥ ፡ ያለው ፡ ድንጋይ ፡
ወይም ፡ ዕንጨቱ ፡ ብቻ ፡ ሲቀር ፡ እንደሚወድቅ ፡ ሁሉ ፡ ድርሰቱም ፡
እንደዚሁ ፡ ለጊዜው ፡ ካብለጨለጨ ፡ በኋላ ፡ ይሞታል ።

ሦስተኛ ፡ ደንበኛ ፡ የሆነ ፡ አቀራረብ ፡ የሌለው ፡ ድርሰት ፡ ጨርሶ ፡
ባይሞት ፡ እንኳ ፡ ጕድለቱ ፡ ዋጋውን ፡ በጣም ፡ ሊቀንሰው ፡ ይችላል ።
ማንኛውንም ፡ ሙያ ፡ ለመፈጸም ፡ ሊከተሉት ፡ የሚገባ ፡ አካሄድ ፡ ወይም ፡



ደንብ ፡ አለ ። በዓለም ፡ ላይ ፡ የታወቁትን ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹን ፡ ድርሰቶች ፡
ያነበበ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ መዝገብ ፡ ሆኖ ፡ ሊያገለግለው ፡ የሚችል ፡ ብዙ ፡
ምሳሌ ፡ ስለሚያገኝ ፡ ከዚህ ፡ ከተባለው ፡ ስሕተት ፡ ወይም ፡ ጕድለት ፡
በቀላሉ ፡ ሊድን ፡ ይችላል ። ስለዚህ ፡ ከሦስቱ ፡ መሠረታዊ ፡ ነገሮች ፡ አን
ድ ፡ ደራሲ ፡ በጣም ፡ ሊጠነቀቅበት ፡ የሚገባው ፡ ስለ ፡ አንደኛውና ፡ ስለ ፡
ሁለተኛው ፡ መሠረታዊ ፡ ነገሮች ፡ ነው ። ፍሬ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ አሳብ ፡
በራሱ ፡ ውስጥ ፡ እያለ ፡ በተጣራና ፡ በሚያምር ፡ አነጋገር ፡ አሳቡን ፡ ለመ
ግለጥ ፡ ችሎታ ፡ ወይም ፡ ስጦታ ፡ ከሌለው ፡ ማንኛውም ፡ ጸሓፊ ፡ ቢሆን ፡
የድርሰቱ ፡ ተግባር ፡ ሊቃናለት ፡ አይችልም ። ስለዚህ ፡ እነዚህ ፡ ባንደ
ኛና ፡ በሁለተኛ ፡ ክፍል ፡ የተጠቀሱት ፡ ችሎታዎች ፡ አንድነት ፡ ሆነው ፡
ለደራሲው ፡ የተሰጡ ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፡ ማንኛውም ፡ የድርሰት ፡ ሥራ ፡
የተዋጣ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። ይህኑንም ፡ ዝቅ ፡ ብለን ፡ በዝርዝር ፡ እን
መለከተዋለን ።

አሁን ፡ ደግሞ ፡ የድርሰት ፡ ዋጋ ፡ ወይሞ ፡ ደረጃ ፡ እንዴት ፡ እንደ
ሚከፈል ፡ እናስተውል ። አንደኛውን ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ የያዙ ፡ በግጥም ፡
ብቻ ፡ የተጻፉ ፡ ሰፊ ፡ ድርሰቶች ፡ ናቸው ። እነሱም ፡ (épopées) ወይም ፤
(poèmes épiques) ይባላሉ ። ይህን ፡ ዐይነት ፡ ድርሰት ፡ የጻፉ ፡ ሆሜር ፡
ቪርጊል ፤ ዳንቴ ፤ ሚልተን ፡ ካሞኤንስና ፡ ለ ፡ ታስ ፡ ናቸው ። ቀጥሎ ፡ በማ
ዕርግ ፡ ከፍተኛነት ፡ የሚመጡ ፡ በግጥም ፡ ቴአትር ፡ የጻፉ ፡ ባለቅኔዎች ፡
ናቸው ። እነሱም ፡ በግሪክ ፡ ኤሺል ፤ ኤሪፔድ ፤ ሶፎክል ፤ በፈረንሳይ ፡ ኰር
ኔይ ፤ ራሲን ፤ ቮልቴር ፤ ቪክቶር ፤ ሂጎ ፤ በእንግሊዝ ፡ ሼክስፒር ፤ በጀርመን ፡
ገት ፤ ሺለር ፡ ናቸው ። ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በያይነቱ ፡ ቅኔ ፡ የጻፉ ፡ (ባለቅኔዎች) ፡
ይመጣሉ ። ከዚያም ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ መጻሕፍት ፡ የጻፉ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡
ዲኬንስ ፤ ስኮት ፤ በፈረንሳይ ፡ ቪክቶር ፡ ሂጎ ፡ ባልዛክ ፡ አሌክሳንድር ፤ ዱ
ማስ ፤ በመስኮብ ፡ አገር ፡ ቶልስቶይ ፤ ዶስቶዬቭስኪ ፤ ጎጎል ፤ ሌሎችም ፡
እነዚህን ፡ የመሰሉ ፡ ብዙዎች ፡ ይከተላሉ ። ስለ ፡ ድርሰት ፡ ታሪክ ፡ ስን
ናገር ፡ በስድ ፡ ንባብ ፡ (prose) ከተጻፈ ፡ ብዙ ፡ ሺሕ ፡ ገጽ ፡ ካለው ፡
መጽሐፍ ፡ ጥቂት ፡ ገጾች ፡ ያሉት ፡ ጥሩ ፡ ግጥም ፡ እንደሚበልጥ ፡ መዘን
ጋት ፡ አይገባንም ። ስለዚህ ፡ ነው ፡ ባለቅኔዎች ፡ ከፍተኛውን ፡ ደረጃ ፡ ይ
ዘው ፡ የሚገኙ ። ምክንያቱም ፡ ቅኔ ፡ ባጭር ፡ ቃል ፡ ሰፊ ፡ አሳብ ፡ ለመናገር ፡
የሚረዳ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። የአልማዝ ፡ ውበት ፡ ከወርቅ ፡ ጸዳል ፡ እንደሚ
በልጥ ፡ ሁሉ ፡ በምንም ፡ ዐይነት ፡ አኳኋን ፡ ቢጽፈው ፡ አንድ ፡ ዶስቶዬቭ
ስኪ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ አሌክሳንድር ፡ ዱማስ ፡ በሁለት ፡ መሥመሮች ፡
ላይ ፡ የሚያሰፍራቸው ፡ ቃሎች ፡ ሆሜር ፡ ወይም ፡ ሺክስፒር ፡ በሁለት ፡
መሥመሮች ፡ ላይ ፡ ካሰፈሯቸው ፡ ቃሎች ፡ ጋራ ፡ በውበትና ፡ በምስጢር ፡

ሊተካከሉ ፡ አይችሉም ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ መጥፎ ፡ ግጥም ፡ ከመጻፍ ፡ በጥሩ ፡ አጻጻፍ ፡ ያለግጥም ፡ መጻፍ ፡ ይሻላል ። ለድርሰት ፡ ሥራ ፡ መምህራን ፡ ሆነው ፡ የሚኖሩ ፡ ግሪኮች ፡ ናቸው ። የግሪክ ፡ ደራስያን ፡ በቴአትር ፡ በኩል ፡ የጻፏቸው ፡ ድርሰቶች ፡ እንሆ ፡ ከሁለት ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ከእነሱ ፡ ቀጥሎ ፡ በየዘመኑና ፡ በያገሩ ፡ ከተጻፉት ፡ ቴአትሮች ፡ ጋራ ፡ ስናስተያያቸው ፡ በንግግር ፡ ውበት ፡ በፍሬ ፡ ነገሩና ፡ በምስጢሩ ፡ በቅርጹና ፡ ባቀራረቡ ፡ በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሌላቸው ፡ የማያረጁ ፡ መዝገቦች ፡ ሆነው ፡ ይኖራሉ ። ከግሪክ ፡ የድርሰት ፡ ታሪክ ፡ ጋራ ፡ ስማቸው ፡ የማይለያይ ፡ ሁለት ፡ ልጃገረዶች ፡ አንቲጎንና ፡ ኢፊዤኔ ፡ የሚባሉ ፡ ይገኛሉ ። ሁለቱም ፡ ልዕልቶች ፡ ናቸው ። አንቲጎን ፡ ለቤተ ፡ ሰቦቿ ፡ ያላት ፡ ፍቅር ፡ ምሳሌ ፡ ሆኖ ፡ የሚኖር ፡ ወጣት ፡ ልጃገረድ ፡ ናት ። ስለ ፡ አባቷ ፡ ስለ ፡ ኤዲፕ ፡ ፍቅር ፡ ስትል ፡ የመከራው ፡ ተካፋይ ፡ ሆና ፡ ኖረች ። ዐይኑ ፡ ጠፍቶ ፡ ዕውር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ መሪው ፡ ነበረች ። በኋላ ፡ ደግሞ ፡ የምትወደው ፡ ወንድሟ ፡ ፖሊኒስ ፡ የሚባለው ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ተፈርዶበት ፡ ተሰቅሎ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ እንዳገሩ ፡ ልማድ ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ የተቀጣ ፡ ሰው ፡ እንዳይቀበር ፡ ሕግ ፡ ይከለክል ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ስለ ፡ ወንድሟ ፡ ፍቅር ፡ ይህን ፡ ሕግ ፡ ጥሳ ፡ በድብቅ ፡ ቀበረችው ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ በሞት ፡ ተቀጣች ። ስለዚህ ፡ አንቲጎን ፡ የራሷን ፡ ደስታ ፡ የራሷን ፡ ሰላም ፡ የራሷን ፡ ሕይወት ፡ ስለ ፡ አባቷና ፡ ስለ ፡ ወንድሟ ፡ ማለት ፡ ስለ ፡ ቤተ፡ ሰቧ ፡ ፍቅር ፡ ስትል ፡ መሥዋዕት ፡ ያደረገች ፡ ልዕልት ፡ ናት ።

ኢፊዤኒ ፡ የተባለችው ፡ ደግሞ ፡ ሕይወቷን ፡ ስለ ፡ አገር ፡ ፍቅር ፡ ጉዳይ ፡ መሥዋዕት ፡ ያደረገች ፡ ልዕልት ፡ ናት ። ግሪኮች ፡ የትሮያን ፡ ከተማ ፡ ሊወጉ ፡ ወደ ፡ ዘመቻ ፡ በተነሡ ፡ ጊዜ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ መርከቦቻቸውን ፡ እየገፋ ፡ የሚወስደው ፡ ነፋስ ፡ እንቢ ፡ ብሎ ፡ አገዳቸው ። ስለዚህ ፡ እንደ ፡ ዘመኑ ፡ ልማድ ፡ የአማልክቶቻቸውን ፡ አሳብ ፡ ሊያውቁ ፡ የሚችሉ ፡ ሰዎች ፡ (ካህናት) ፡ ምክንያቱን ፡ መርምረው ፡ እንዲያስረዱ ፡ በተጠየቁ ፡ ጊዜ ፡ ልዕልቲቱ ፡ ኢፊዤኔ ፡ ራሷን ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጋ ፡ በጣዖት ፡ መቅደስ ፡ ላይ ፡ ደሟን ፡ ካላፈሰሰች ፡ የአማልክቶቹ ፡ ቍጣ ፡ እንደማይመለስ ፡ ላባቷ ፡ ለንጉሥ ፡ አጋመምኖን ፡ ገለጡለት ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ኢፊዤኒ ፡ መሥዋዕት ፡ ሆነች ። የእነዚህ ፡ የሁለት ፡ ልዕልቶች ፡ ታሪክ ፡ በግሪክ ፡ ድርሰት ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ቦታ ፡ ተሰጥቶት ፡ ይኖራል ። ኤሺል ፣ ኤሪፒድ ፣ ሶፎክል ፣ እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ ደራስያን ፡ የእነዚህን ፡ ልዕልቶች ፡ ታሪክ ፡ በቴአትር ፡ ሠርተው ፡ አቅርበ



ውታል ። ከእነሱ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ የአውሮፓ ፡ ደራስያን ፡ ሮትሩ ፣ ገት ፣ አኑይ ፣ የግሪኮችን ፡ ድርሰቶች ፡ መዝገብ ፡ አድርገው ፡ በመቅዳትና ፡ በመገልበጥ ፡ ሠርተውታል ። ከግሪኮች ፡ ደራስያን ፡ ላይ ፡ መቅዳትና ፡ መገልበጥ ፡ እንደ ፡ ነውር ፡ መቈጠሩ ፡ ቀርቶ ፡ የሚያኰራና ፡ የሚያስመካ ፡ ተግባር ፡ ሆኖ ፡ እንደሚቈጠር ፡ ማወቅ ፡ ይገባናል ። ተማሪ ፡ ከመምህሩ ፡ ላይ ፡ ቢቀዳ ፡ ምን ፡ ያሳፍራል ። እንግዲህ ፡ የግሪክ ፡ ደራስያን ፡ በዓለም ፡ ደራስያን ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ዘለዓለም ፡ የሚከበሩ ፡ መምህራን ፡ ናቸው ።

በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ ማለት ፡ የድርሰት ፡ ሥራ ፡ ባውሮፓ ፡ የገነነ ፡ ከመሆኑ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ደራሲ ፡ የተተበተበና ፡ የተወሳሰበ ፡ ጨለማ ፡ የሆነ ፡ ድርሰት ፡ በግጥምም ፡ ሆነ ፡ በስድ ፡ ንባብ ፡ ማለት ፡ በ(ፕሮዝ) ፡ ሲጽፍ ፡ በውስጡ ፡ ያለው ፡ የተሸፈነ ፡ አሳብ ፡ ምን ፡ ይሆን? እየተባለ ፡ በያንዳንዱ ፡ ቃል ፡ ውስጥ ፡ ምስጢሩን ፡ በመፈለግና ፡ በማተት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሲጨነቅበት ፡ መመልከትን ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ሙያ ፡ አድርጎ ፡ ደራሲው ፡ ይመካበት ፡ ነበር ፣ ሰዎችም ፡ በዚሁ ፡ ያደንቁታል ። አሁን ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ደራሲ ፡ ዋጋው ፡ የሚታወቀው ፡ አሳቡና ፡ ንግግሩ ፡ የተጣራና ፡ የተገለጠ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ። ደራሲ ፡ የሚመሰገነው ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡ አሳብ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የሆነውን ፡ ፍሬ ፡ ያለውን ፡ አሳብ ፡ ደስ ፡ በሚያሰኝ ፡ ንግግር ፡ ሲገልጠው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ለምሳሌ ፣ ሼክስፒርን ፡ ወይም ፡ ገትን ፡ ስናነባቸው ፡ ውብ ፡ የሆነውን ፡ አሳብና ፡ አስተያየት ፡ በማይጠገብ ፡ ውብ ፡ በሆነ ፡ ንግግር ፡ ይገልጡልናል ፣ እኛም ፡ የምናደንቃቸውና ፡ የምናከብራቸው ፡ ድርሰታቸው ፡ የውበት ፡ ገበያ ፡ ሆኖ ፡ ስለምናገኘው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ እንቆቅልሽ ፡ ፍቱኝ ፣ ተርጒሙኝ ፡ የሚል ፡ አሳብ ፡ ስለሚያቀርቡልን ፡ አይደለም ። ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ተራ ፡ ነገር ፡ አድርገው ፡ በየቀኑ ፡ የሚናገሩትን ፡ ነገር ፡ እነሱ ፡ ውብ ፡ የሆነ ፡ መልክ ፡ ሰጥተው ፡ ያሳዩናል ። ባለሙያ ፡ የሆነ ፡ ሐውልት ፡ የሚቀርጽ ፡ አርቲስት ፡ ከድንጋይ ፡ ውስጥ ፡ የሚያምር ፡ መልክ ፡ ቀርጾ ፡ እንደሚያወጣ ፡ ሁሉ ፡ እነሱም ፡ እንደዚሁ ፡ ለተራው ፡ ነገር ፡ ታይቶ ፡ ተሰምቶ ፡ የማይጠገብ ፡ ውብ ፡ የሆነ ፡ መልክ ፡ ይሰጡታል ። ተሸፍኖ ፡ የሚኖር ፡ ነገር ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ አለው ? ለምሳሌ ፡ አልማዝ ፡ በጨለማ ፡ እንደሚያብረቀርቅ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ አልማዝ ፡ እንኳ ፡ ውበቱ ፡ በሙሉ ፡ የሚገለጠው ፡ በብርሃን ፡ ሲታይ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ድርሰት ፡ እንቆቅልሽ ፡ አይደለም ። ግልጥነት ፡ የሌለው ፡ ድርሰት ፡ ሁሉ ፡ ሊያምር ፡ አይችልም ። የተሸፈነ ፡ አጻጻፍም ፡ መራቀቅን ፡ ማሳየቱ፡ ቀርቶ ፡ ያሳብን ፡ እንካሳነትና ፡ ዝብርቅርቅነት ፡ ያመለክታል ። ግልጥ ፡

ሆኖ ፡ የተጣራ ፡ አጻጻፍ ፡ ግን ፡ ያሳብን ፡ ብሩህነት ፡ ያስረዳል ። ለዚሁም ፡ ቡዋሎ ፡ የተባለው ፡ ደራሲ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ቃል ፡ ተናግሮታል።

Ce que l'on conçoit bien s'énonce clairement
Et les mots pour le dire arrivent aisément.

በመልካም ፡ ያሰቡት ፡ በርቶ ፡ ይገለጣል ፡
አስፈላጊው ፡ ቃልም ፡ በቀላል ፡ ይመጣል ።

አንድ ፡ ትልቅ ፡ ደራሲ ፡ ዋጋው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጥለት ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ ድርሰቱ ፡ በሌላ ፡ ቋንቋ ፡ ሲተረጐም ፡ በሚሰጠው ፡ ተስሚነት ፡ መጠን ፡ ነው ። ታላላቅ ፡ ድርሰቶች ፡ ሁሉ ፡ ለምሳሌ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የሆሜር ፡ የዳንቴ ፤ የሼክስፒር ፡ ድርሰቶች ፡ በማንኛውም ፡ ቋንቋ ፡ ሲተረጐሙ ፡ ምስጢሩም ፡ ሆነ ፡ ውበቱ ፡ መቶ ፡ በመቶ ፡ ባይሆን ፡ እንኳ ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ ተገልጦ ፡ ይሰማል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ማንኛውም ፡ ድርሰት ፡ ቢሆን ፡ በተጻፈበት ፡ ባገሩ ፡ ቋንቋ ፡ የሚሰጠውን ፡ ያኽል ፡ ሲተረጐም ፡ ላንባቢው ፡ ስሜት ፡ እንደማይሰጠው ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፤ ውብ ፡ የሆኑ ፡ አንዳንድ ፡ የአማርኛ ፡ ግጥሞች ፡ ወስደን ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ወይም ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ተርጕመን ፡ ብንሞክረው ፡ በመቶ ፡ ዘጠናው ፡ በሚስጢርም ፡ ሆነ ፡ በውበት ፡ አጕድሎ ፡ እናገኘዋለን ። ሆኖም ፡ ታላላቅ ፡ ደራስያን ፡ የጻፏቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡ ጥሩ ፡ ተርጓሚ ፡ ካገኙ ፡ ምንም ፡ ያኽል ፡ አያጐድሉም ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። በመጥፎ ፡ ተርጓሚ ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ የተተረጐሙ ፡ ድርሰቶች ፡ ይበላሻሉ ። ለምሳሌ ፤ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የሼክስፒርንና ፡ የጌትን ፡ ድርሰቶች ፡ በሚገባ ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ሊተረጕም ፡ የቻለ ፡ ደኅና ፡ ተርጓሚ ፡ አለመገኘቱ ፡ ይነገራል ። በትርጉም ፡ በኩል ፡ በጣም ፡ የሚያስቸግሩ ፡ በግጥም ፡ የተጻፉት ፡ ድርሰቶች ፡ ናቸው ። በስድ ፡ ንባብ ፡ የተጻፉትን ፡ ድርሰቶች ፡ ግን ፡ በሁለቱም ፡ ቋንቋ ፡ በቂ ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ተርጓሚ ፡ በሚገባ ፡ ሊተረጕማቸው ፡ ይችላል ።

በሰው ፡ ስሜት ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጥረው ፡ ሁኔታ ፡ የደራስያን ፡ ሙያ ፡ ሁለት ፡ ዐይነት ፡ ባሕርይ ፡ አለው ። አንዳንዶቹ ፡ አጻጻፋቸው ፡ ስሜታችንን ፡ ይቀሰቅሰዋል ፤ መንፈሳችንን ፡ ያግለዋል ፤ እንደ ፡ ዐረቄም ፡ ያሰክረናል ። መጽሐፉን ፡ ካጠፍነው ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ አናስታውሰውም ፤ በቶሎ ፡ እንረሳዋለን ። አንዳንዶቹ ፡ ደግሞ ፡ የሚማርከን ፡ የንግግራቸው ፡ ውበት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በሚያምር ፡ ንግግር ፡ የተጐናጸፈ ፡ አድር



ገው ፡ የሚያቀርቡልን ፡ አሳብ ፡ በአንጐላችን ፡ ውስጥ ፡ ጠልቆ ፡ ይገባል ፤ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከመንፈሳችን ፡ ውስጥ ፡ አይጠፉም ፤ እንቅልፍና ፡ ዕረፍት ፡ ይነሣናል ፤ ዘለዓለም ፡ አዲስ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ፤ ትንባኾ ፡ እንደሚጐርስ ፡ ሰው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ባንጐላችን ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጦ ፡ ስናኝከው ፡ እንኖራለን ። ኒች ፡ ሲናገር ፡ ናፖሊዮን ፤ ዶስቶዬብስኪ ፤ ኤመርሰን ፤ መምህር ፡ ኤካርት ፡ ከተናገሯቸው ፡ ንግግሮች ፡ መካከል ፡ መቼም ፡ ቢሆን ፡ ሳልረሳቸውና ፡ ሳያረጁብኝ ፡ በመንፈሴ ፡ ውስጥ ፡ ዕድሜዬን ፡ ሙሉ ፡ ካሳቤ ፡ ሳለያቸው ፡ የሚኖሩ ፡ ቃሎች ፡ አሉ ፡ ብሏል ። እሱም ፡ ራሱ ፡ ኒች ፡ በደራሲነቱ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ስጦታ ፡ አለው ። ሌሎች ፡ ደራስያን ፡ ከጻፉት ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ መጽሐፍ ፡ ይልቅ ፡ እሱ ፡ በሦስትና ፡ ባራት ፡ መሥመሮች ፡ የተናገራቸው ፡ አጭር ፡ ቃሎች ፡ ይበልጣሉ ። ምስጢራቸውና ፡ ፍሬ ፡ ነገራቸው ፡ በጣም ፡ የጠለቀ ፤ አገላለጡም ፡ የጠራ ፤ የበራ ፤ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ዕድሜውን ፡ ሙሉ ፡ እየተመገባቸው ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ። የኒች ፡ ቃሎች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የተጻፉት ፡ በስድ ፡ ንባብ ፡ ቢሆን ፡ በውበታቸው ፡ ከቅኔ ፡ ጋራ ፡ እኩል ፡ ሆነው ፡ ይቈጠራሉ ። ድርሰትና ፡ ሥነ ፡ ጥበባት ፡ የማይለያዩ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ አሁን ፡ ስለ፡ ሥነ ፡ ጥበብ ፡ ጥቂት ፡ እንናገራለን ።

# ሥነ ፡ ጥበባት ።

የሥነ ፡ ጥበብ ፡ ባሕርይ ፡ በሙዚቃ ፡ በድርሰት ፤ በተለይም ፡ በቅኔ ፤ በሐውልት ፡ ቅርጽ ፤ እነዚህን ፡ በመሰሉት ፡ ይገለጣል ። የሥነ ፡ ጥበባት ፡ ባሕርይ ፡ ምንድነው ? ለምንስ ፡ ይጠቅማል ? ሰው ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የተፈጠረው ፡ ለምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስንመረምር ፡ ለእነዚህ ፡ ጥያቄዎች ፡ መልሱን ፡ እናገኘዋለን ። አንድ ፡ ሰው ፡ መልካም ፡ ምግብ ፡ በልቶ ፤ መልካም ፡ መጠጥ ፡ ጠጥቶ ፤ መልካም ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፤ በመልካም ፡ ቤት ፡ ኖሮ ፡ ለምቾት ፡ የሚሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ካገኘ ፡ በኋላ ፡ የሕይወቱ ፡ ዐላማ ፡ በእነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ብቻ ፡ ከተፈጸመ ፡ በሥጋዊ ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ ተወስኗል ፡ ያሰኛል ። ይህም ፡ ከእንስሳነት ፡ ምንም ፡ ያኸል ፡ የተራራቀ ፡ ሆኖ ፡ አይገኝም ። ደስታ ፡ ብለን ፡ የምንጠራው ፡ ሥጋዊ ፡ ደስታን ፡ ከሆነ ፡ የሚበላው ፡ ባቄላ ፡ የቀረበለት ፡ በሬ ፡ ደስታን ፡ አግኝቷል ፡ ማለት ፡ ነዋ ! ሲል ፡ ሄራክሊት ፡ የተባለው ፡ ፈላስፋ ፡ ተናግሯል ። ነገር ፡ ግን ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ የሠለጠኑ ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ ከእነዚህ ፡ ሥጋዊን ፡ ባሕርይ ፡ ከሚመለከቱት ፡ ፍላጎቶች ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ሥነ ፡ ጥበባትን ፡ የሚያስወድድ ፡ ስሜት ፡ እንደ ፡ ነበራቸውና ፡ አሁንም ፡ እንዳላቸው ፡ ታውቋል ። ለዚሁም ፡ አንድ ፡ ምሳሌ ፡ እንጠቅሳለን ። በገዳም ፡ አንድ ፡ መነኵሴ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። እሱም ፡ እውነት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ አለች ፡ ወይ ? የሚል ፡ ወደ ፡ ጥርጣሬ ፡ ያዘነበለ ፡ ስሜት ፡ አድሮበት ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በመንፈሱ ፡ ውስጥ ፡ እየመጣበት ፡ ሲያስጨንቀው ፡ ይኖር ፡ ነበር ። አንድ ፡ ቀን ፡ ዕንጨት ፡ ለመቍረጥ ፡ ከገዳሙ ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ከሚገኝ ፡ ካንድ ፡ ጫካ ፡ ሄዶ ፡ እዚያ ፡ ዕንጨት ፡ ሲቈርጥ ፡ በድንገት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ተገለጠችለትና ፡ ድንቅ ፡ የሆነ ፡ የሙዚቃ ፡ ድምፅ ፡ ሰማ ። ይህቺውም ፡ የሙዚቃ ፡ ድምፅ ፡ አንዲት ፡ ሰኮንድ ፡ ያኸል ፡ ቈይታ ፡ ተሰወረችበት ። እሱም ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ላንድ ፡ አፍታ ፡ ቢሆንም ፡ በዐይኑ ፡ አይቶ ፡ በመደሰቱ ፡ ከልቡ ፡ የነበረውን ፡ ጥርጣሬ ፡ ፍቆለት ፡ ዕንጨቱን ፡ ተሸክሞ ፡ ወደ ፡ ገዳሙ ፡ ተመለሰ ። ነገር ፡ ግን ፡ እገዳሙ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የሚያውቃቸውን ፡ መነኰሳትና ፡ ተማሪዎች ፡ በማግኘት ፡ ፈንታ ፡ ጨርሶ ፡ የማያውቃቸው ፡ ሰዎች ፡ ገብተውበት ፡ አገኘ ። እነሱም ፡ አንተ ፡ ማነኽ? ከወዴትስ ፡ መጣኽ? ብለው ፡ ጠየቁት ። ታሪኩን ፡ በነገራቸው ፡ ጊዜ ፡ መዝገብ ፡ ቢያገላብጡ ፡ አንድ ፡ መነኵሴ ፡ ዕንጨት ፡ ሊቈርጥ ፡ ሄዶ ፡ አውሬ ፡ ስለ ፡ በላው ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ ቀርቷል ፡ የሚል ፡

ማስታወሻ ፡ ተጽፎ ፡ አገኙ ። ዘመኑን ፡ ቢቈጥሩት ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ ሆኖታል ። በመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ከሚገኙት ፡ ደስታዎች ፡ ዋናው ፡ ካህናተ ፡ ሰማይ ፡ የሆኑት ፡ እነ ፡ ኪሩቤል ፡ ከነሰራዊታቸው ፡ ቃል ፡ በማይገኝለት ፡ በሚያምር ፡ ዜማ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሲያመሰግኑ ፡ መስማት ፡ መሆኑን ፡ እናውቃለን ። ለዚህ ፡ መነኵሴ ፡ አንድ ፡ ሰኮንድ ፡ የመሰለችው ፡ ጊዜ ፡ የመከራና ፡ ያሣር ፡ ዓለም ፡ በሆነችው ፡ በምድራዊ ፡ ሕይወት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ሆና ፡ ተቈጥራለች ። በሰማይ ፡ ቤት ፡ ባለው ፡ ደስታ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ሰኰንድ ፡ ነች ። ረዥሙን ፡ ዘመን ፡ አጭር ፡ ጊዜ፡ አድርጋ፡ ለመነኵሴው ፡ እንዲሰማው ፡ ያደረገችለት ፡ ውብ ፡ የሆነችው ፡ ሙዚቃ ፡ ናት ። በሥዕል ፡ በኩልም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። አንድ ፡ ፈላስፋ ፡ ሲናገር ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ውበቶች ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መልክ ፡ የሚያሳዩን ፡ ሥሥ ፡ መጋረጃዎች ፡ ናቸው ፡ ብሏል ። በቀለም ፡ የደመቀችው ፡ የንጋትና ፡ የምሽት ፡ ፀሐይ ፡ በለምለም ፡ ዕፀዋትና ፡ አበቦች ፡ የተኰላቸውና ፡ የተሸለመችው ፡ በተራራና ፡ በሸለቆ ፤ በወንዝና ፡ በሜዳ ፡ አምራ ፡ የተቀረጸችው ፡ መሬት ፤ እንደዚሁም ፡ የተራሮችና ፡ የውቅያኖስ ፤ የነጐድጓድና ፡ የባሕር፡ ሞገድ ፤ የሚያቀርቡልን ፡ ልዕልና ፡ ያለበት ፡ ግርማና ፡ ሞገስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትልቅነት ፡ የሚገልጡልን ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ። አንድ ፡ ሥዕል፡ ሠዓሊ ፡ ከሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ያገኘውን ፡ እንደነዚህ ፡ ያሉትን ፡ ውበቶች ፡ ሠርቶ ፡ ሲያሳየን ፡ ስሜታችን ፡ በደስታ ፡ ይረካል ። እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ በመልካችን ፡ እንፍጠር ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ሥዕል ፡ ሠዓሊ ፡ ደግሞ ፡ የሥነ ፡ ፍጥረትን ፡ ውበት ፡ በሰሌዳው ፡ ላይ ፡ የሚያሰፍርልን ፡ አምላክን ፡ መስለን ፡ የፈጣሪነትን ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ እንሞክር፡ ለማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ እሱ ፡ በፈጠራቸው ፡ ውበቶች ፡ አማካይነት ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንደ ፡ ማመስገንና ፡ እንደ ፡ መወደስ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ። በሙዚቃ ፤ በድርሰትና ፡ በሐውልት ፡ ቅርጽ ፡ በኩል ፡ የሚደክሙ ፡ ሰዎች ፡ (አርቲስቶች) ፡ ካንጐላቸው ፡ ፈጥረው ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ ሲያበረክቱ ፡ የሚፈጽሙት ፡ ተግባር ፡ ይህንኑ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እነዚህን ፡ ለመሰሉ ፡ ነገሮች ፡ የሚሰጣቸው ፡ ዋጋ ፡ ከሁሉም ፡ ይበልጣል ። በሥነ ፡ ጥበባት ፡ በኩል ፡ ዐቢይ ፡ ሥራዎች ፡ (chefs-d'œuvre) የፈጸሙት ፡ አርቲስቶች፡ በጣም ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። ከእነዚህ ፡ ጥበቦች ፡ የሚገኘው ፡ ደስታ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ለተከበረው ፡ ሥነ ፡ ፍጥረቱ ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ የመጨረሻው ፡ ፍሥሓ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ በቀላል ፡ የሚገኙ ፡ ጥበቦች ፡ አይደሉም ። ሰውም ፡ ከእነሱ ፡ የሚመነጨውን ፡ ደስታ ፡ በሙሉ ፡ ሊደርስበት ፡ የሚችለው ፡ ስሜቱ ፡ በጣም ፡ የተራቀቀ ፡ ሲሆን ፡ ነው ። ለእነዚህም ፡ ጥበቦች ፡ መሪ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኝ ፡ ድርሰት ፡ ነው ። ድርሰት ፡ ሲባል ፡ በጽሑፍ ፡ የሚገለጥ ፡ ውብ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ ነው ። ድርሰት ፡ ሁሉን ፡ ጠቅልሎ ፡



ይይዛል ። በጠቅላላው ፡ ለኑሯችን ፡ ብርሃን ፡ እየሰጠን ፡ የሚመራን ፡ ድርሰት ፡ ነው ። ሙዚቃና ፡ ሥዕል ፡ ባንድ ፡ ነገር ፡ ከድርሰት ፡ ይበልጣሉ ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ይኸውም ፡ ድርሰትን ፡ አንብቦ ፡ ለመጠቀም ፡ ትምህርት ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ የሙዚቃና ፡ የሥዕል ፡ ውበት ፡ ግን ፡ ለማንኛውም ፡ መሀይምን ፡ ለሆነ ፡ ሰው ፡ ሊገለጡለት ፡ ይችላሉ ። ይሁን ፡ እንጂ፡ መሠረቱ ፡ ድርሰት ፡ ነው ። ድርሰት ፡ ሁሉንም ፡ ጠቅልሎ ፡ በመያዝ ፡ ሕይወት ፡ አግኝቶ ፡ እንዲኖር ፡ እያደረገ ፡ መሪያቸው ፡ ሆኖ ፡ ይኖራል ። ለምሳሌ ፤ ኦሪትና ፡ ወንጌል ፡ ለሙዚቃም ፡ ሆነ ፡ ለሥዕል ፡ የልዩ ፡ ልዩ፡ አርእስቶች ፡ ምንጭ ፡ ናቸው ። ከቫቲካን ፡ ሄደን ፡ ያየን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እነ ፡ ሚኬላንጄሎ ፤ ራፋኤልና ፡ ሌዎናርድ ፡ ደቢንቺ ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሌላቸውን ፡ ሥዕሎች ፡ ሲሠሩ ፡ አርእስቱን ፡ የቀዱት ፡ ከኦሪትና ፡ ከወንጌል ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ እነ ፡ ሹበርት ፤ ሞዛር ፤ ቢቶቨን ፤ ባክ ፤ ባግነር ፤ የደረሷቸው ፡ የሙዚቃ ፡ ድርሰቶች ፡ አርእስቶቹ ፡ የመጡት ፡ ከክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ድርሰት ፡ የሥነ ፡ ጥበባት ፡ ምንጭ፤ የአእምሮ ፡ ብርሃን ፤ የኅሊና ፡ መሪ ፤ በጠቅላላው ፡ የሰውን ፡ መንፈስ ፡ እየመገበ ፡ የሚያጐለምስ ፡ የተከበረ ፡ መና ፡ ነው ።

የዓለም ፡ ውበት ፡ ሁሉ ፡ ያልፋል ። የቀኑን ፡ ብርሃን ፡ የሌሊቱ ፡ ጨለማ ፡ ይደመስሰዋል ። በጋን ፡ ክረምት ፡ ይሽረዋል ። የሰውን ፡ ቍንጅናም ፡ ሞት ፡ ያጠፋዋል ። ሰዎች ፡ በጠባያቸው ፡ ትልቅነት ፡ የፈጸሟቸው ፡ ክብር ፡ ያላቸው ፡ መልካም ፡ ሥራዎች ፡ ይረሳሉ ። ሐውልት ፡ የሚቀርጽ ፡ ሠዓሊ ፡ ደራሲና ፡ ሙዚቀኛ ፡ እነዚህ ፡ አርቲስቶች ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ የጠራናቸው ፡ ውበቶች ፡ ጨርሰው ፡ እንዳይጠፉና ፡ መታሰቢያቸው ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ እንዲኖር ፡ ያደርጉልናል ።

በብረትም ፡ ሆነ ፡ በድንጋይ ፡ በዕንጨትም ፡ ሆነ ፡ በጨርቅ ፡ ላይ ፡ የሚሠሩ ፡ የጌጥ ፡ ቅርጾች ፤ የሕንጻ ፡ ውበት ፡ አርሺቴክቱር ፤ ሙዚቃና ፡ ዘፈን ፤ ቅኔና ፡ በጠቅላላው ፡ ድርሰት ፤ ሰው ፡ በእጁ ፡ የሚሠራውና ፡ ከመንፈሱም ፡ የሚያፈልቀው ፡ ጥበብ ፡ ሁሉ ፡ በሥነ ፡ ጥበባት ፡ መደብ ፡ ውስጥ ፡ ይገባል ። እነዚህን ፡ ጥበባት ፡ የሚፈጽሙ ፡ ሰዎችም ፡ አርቲስቶች ፡ ይባላሉ ። አውሮፓውያን ፡ (አርትስ ፡ Arts) የሚሉትን ፡ ቃል ፡ ነው ፡ እኛ ፡ ሥነ ፡ ጥበባት ፡ ብለን ፡ የተረጐምነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በሥነ ፡ ጥበባት ፡ ማለት ፡ በአርቲስትነት ፡ የተፈጥሮ ፡ ዝንባሌ ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ። ይህ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ በጣም ፡ አድርጎ ፡ የሚያሳዝነው ፡ ያውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ መቀበል ፡ ከጀመርን ፡ ወዲህ ፡ ሥልጣኔ ፡ ማለት ፡ ሕክምና ፡ መሐንዲስነት ፤ ቴክኒክ ፤ ሳይንስ ፡

እነዚህ ፡ ዕውቀቶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡ የማለት ፡ አሳብ ፡ አድሮብን ፡ መታ
የቱ ፡ ነው ። ታላላቅ ፡ ፈላስፎችና ፡ ደራስያን ፡ ከእነዚህ ፡ ዕውቀቶች ፡
ሁሉ ፡ በላይ ፡ የሚያደርጉት ፡ ሥነ ፡ ጥበባት ፡ መሆኑን ፡ አላስታወስንም ።
ሾፐንሃወር ፤ ኒች ፡ ሄጌል ፡ የቀሩትም ፡ ስንቱ ፡ ፈላስፎችና ፡ ሊቃውንት ፡
በድርሰታቸው ፡ ውስጥ ፡ ለሥነ ፡ ጥበባት ፡ ከፍተኛውን ፡ ቦታ ፡ እየሰጡ ፡
እነዚህ ፡ የጥበብ ፡ ሙያዎች ፡ እየተኰተኰቱ ፤ እየተስፋፉ ፤ እያደጉና ፡
እየተራቀቁ ፡ የሚሄዱበትን ፡ መንገድ ፡ መፈለግ ፡ የሥልጣኔ ፡ ዋናው ፡
ትርጉም ፡ መሆኑን ፡ የገለጡልን ፡ መሆናቸውን ፡ አልተገነዘብነውም ።
ማቴሪያሊስም ፡ የገነነው ፡ በምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ ብለን፡
ስናስብ ፡ ከእነሱ ፡ የበለጠ ፡ ማቴሪያሊስምነት ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ እንዳረፈብን ፡
አልተሰማንም ። ከለማበት ፡ የተጋባበት ፡ እንደሚባለው ፡ ሁሉ ።

ለምሳሌ ፡ ኒች ፡ ስለ ፡ ሶክራት ፡ ሲናገር ፡ ሶክራት ፡ የቅኔና ፡ የቴአ
ትር ፡ ጥቅሙ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አይገባውም ፡ ነበር ። ፕላቶን ፡ ባለቅኔ፡
ለመሆን ፡ ሲችል ፡ የሶክራትን ፡ አሳብ ፡ ተቀብሎ ፡ ባለቅኔነቱን ፡ ትቶ ፡
ፈላስፋ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ቀረ ። ስለዚህ ፡ ሶክራት ፡ (የአርት) ፡ የሥነ ፡ ጥበብ ፡
ጠላት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በመርዝ ፡ እንዲሞት ፡ የተፈረደበት ፡ ፍርድ ፡ በሚገባ፡
ነው ፡ ሲል ፡ ይወቅሠዋል ። ይህም ፡ ቅኔ ፡ በቀሩት ፡ ጥበባት ፡ መካከል፡
እንዴት ፡ ያለ ፡ ስፍራ ፡ እንደሚሰጣት ፡ ይገልጥልናል ። ኢትዮጵያ ፡ በሥ
ዕል ፤ በዜማ ፤ በሙዚቃ ፤ በዘፈንና ፡ በቅርጽ ፡ ከፍ ፡ ካለ ፡ ደረጃ ፡ ደርሳ
ለች ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ በፓሪስ ፡ ከተማ ፡ ሳለሁ ፡ ጃፓኖች ፡ በሥነ ፡ ጥበባት ፡
በኩል ፡ ያላቸውን ፡ ሙያ ፡ ላውሮፓውያን ፡ ለማሳወቅ ፡ ከፈረንሳይ ፡
መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ስምምነት ፡ አድርገው ፡ ቴአትር ፡ ማሪኚ ፡ የሚባለ
ውን ፡ ስሙ ፡ የታወቀ ፡ የቴአትር ፡ ሕንጻ ፡ ተከራይተው ፡ ዘፋኞቻቸውን ፡
አስመጥተው ፡ ጨዋታ ፡ ያሳዩ ፡ ነበር ። በሚያሳዩት ፡ ጨዋታ ፡ ውስጥ ፡
የጀግንነት ፡ ጨዋታ ፡ በሰፊው ፡ ከፕሮግራሙ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ የአንበሳ ፡
ዳንስ ፤ የጀግና ፡ ዘፈን ፡ እያሉ ፡ የሚያሳዩት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ ነበር ።
ነገር ፡ ግን ፡ ዘፈኑ ፡ የቀዘቀዘ ፡ ዳንሱም ፡ የተዳከመ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡
ከጃፓኖቹ ፡ አርቲስቶች ፡ መካከል ፡ አንዳንዶቹ ፡ ሙዚቃ ፡ እየመቱ ፡ እነ
ሱው ፡ ራሳቸው ፡ እንቅልፍ ፡ ሲወስዳቸው ፡ ተመልክተናል ። እኔም ፡ በ
ዚያ ፡ ጊዜ ፡ ያገራችን ፡ አርቲስቶች ፡ ትዝ ፡ አሉኝ ። ባገራችን ፡ በመሸ
ለል ፤ በማቅራራትና ፡ የሰንጎን ፡ ዘፈን ፡ በመዝፈን ፡ ያሉን ፡ ተጫዋ
ቾች ፡ (አርቲስቶች) ፡ ያላቸው ፡ ወኔ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ የሚፋጅ ፡ ከመሆኑ ፡
የተነሣ ፡ ከማሲንቋቸው ፤ ካንደበታቸውና ፡ ከመላ ፡ ሰውነታቸው ፡ የሚ
ወጣው ፡ ግለት ፡ እንኳንስ ፡ ሰብአዊ ፡ ስሜት ፡ ያላቸውን ፡ ተመልካቾች ፡
ይቅርና ፡ በዙሪያቸው ፡ ያለውን ፡ በድን ፡ አካል ፡ የሆነ ፡ ዕንጨቱን ፡



ድንጋዩን ፤ ወንበሩንና ፡ የቤቱን ፡ ግድግዳ ፡ ነፍስ ፡ ዘርቶበት ፡ ያንቀሳ
ቅሰዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ እስከ ፡ ጠላት ፡ ወረራ ፡ ዘመን ፡ የነበረው ፡
የሥነ ፡ ጥበባችን ፡ መግለጫ ፡ ከጠላት ፡ ወዲህ ፡ እየሞተ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡
ነው ። ዛሬ ፡ በየቦታውና ፡ በጠቅላላው ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ የሚገኙትን ፡ ተጫዋ
ቾች ፡ ሲመለከት ፡ ጨዋታቸው ፡ መናኛ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ የጉዳዩ ፡ ቁም ፡
ነገረኛነት ፡ የሚገባው ፡ ሰው ፡ በልቡ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የአርት ፡ ፍቅር ፡
ታንቆ ፡ ሲሞት ፡ ይሰማዋል ። ይህ ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ነው ።
ከሁሉ ፡ ነገር ፡ አስቀድሞ ፡ ለዘፈንና ፡ ለሙዚቃ ፡ ስጦታ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡
ትልቅ ፡ ሙያ ፡ መሆኑን ፡ ዘንግተውት ፡ የተናቀ ፡ ነገር ፡ እየመሰላቸው ፡
ያፍሩበታል ። በሠለጠኑት ፡ አገሮች ፡ ዘፋኞች ፤ ሙዚቀኞች ፤ በጠቅላላው ፡
ተጫዋቾች ፡ የቱን ፡ ያኽል ፡ እንደሚከበሩ ፡ አያስቡትም ። በገና ፤ ዋሽንት፤
ማሲንቆ ፤ ክራር ፡ የሚጫወቱት ፡ ሰዎች ፡ በሙያቸው ፡ እየተራቀቁና ፡
እያደጉ ፡ ካልሄዱ ፡ ሲኒማ ፡ ለመሥራት ፡ ቴአትር ፡ ለማስፋፋት ፤ ኦፔራ ፡
ለማቋቋም ፡ እንደማንችል ፡ አላሰብነውም ። አሁን ፡ ሌሎች ፡ ሕዝቦች ፡
ለራሳቸው ፡ የሠሩትን ፡ ሲኒማ ፡ እናያለን ፤ የባዕድ ፡ ሕዝብ ፡ ዘፋኞች ፡ የሚ
ዘፍኑባቸውን ፡ ዲስኮች ፡ እንገዛለን ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ እኛ ፡
ያለንን ፡ ሙያ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ብናደርገው ፡ የበለጠ ፡ ሀብት ፡
ያለን ፡ መሆኑን ፡ አላሰብነውም ። ይህን ፡ ጥበብ ፡ እንዲዳከም ፡ ያደረገው ፡
አንድ ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ደግሞ ፡ አለ ። በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ አዝማሪዎች ፡
ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፤ ከመሳፍንቱና ፡ ከመኳንንቱ ፡ ፊት ፡ እየቀረቡ ፡ በመጫ
ወት ፡ ምስጋናና ፡ ሽልማት ፡ ያገኙ ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ከከፍተኛ ፡
ቦታ ፡ ሲቀርቡ ፡ ሙያቸውን ፡ ለማራቀቅ ፡ እንዲተጉበት ፡ ያበረታታቸው ፡
ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ሥራቸው ፡ በዝቅተኛ ፡ ደረጃ ፡ ብቻ ፡ ተወስኖ ፡
ስለ ፡ ቀረ ፡ ከእነሱ ፡ መካከል ፡ ሙያቸው ፡ ደካማ ፡ የሆነው ፡ ለእንጀራ
ቸው ፡ ሲሉ ፡ በየመሸታው ፡ ቤት ፡ እየተጫወቱ ፡ ሲኖሩ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡
ሙያ ፡ ያላቸው ፡ ግን ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ የሚያሳፍር ፡ ሥራ ፡ እየመሰላ
ቸው ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ከዝቅተኛ ፡ ቦታ ፡ ከመዋል ፡ ይልቅ ፡ ሌላ ፡
ተግባር ፡ እየሠሩ ፡ መኖርን ፡ ይመርጣሉ ። ስለዚህ ፡ አንደኛ ፡ ከማንኛውም
ዕውቀት ፡ የሚበልጥ ፡ እንጂ ፡ የማያንስ ፡ መሆኑን ፡ እንዲያውቁት ፡
በማድረግ ፤ ሁለተኛ ፡ መናኞች ፡ በሆኑ ፡ ቍጥራቸው ፡ በተወሰነ ፡ ተጫዋ
ቾች ፡ ብቻ ፡ ሥራውን ፡ የታነቀ ፤ የተጨቈነ ፡ ማድረግ ፡ ቀርቶ ፡ ስጦታ ፡
ያላቸው ፡ ሁሉ ፡ ሳያፍሩበት ፡ የሚወዳደሩበትን ፡ መንገድ ፡ መፍጠር ፤
እንደዚሁ ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሽልማት ፡ ማሰጠት ፤ ሌላም ፡ ይህን ፡ በመ
ሰለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ድርጅት ፡ የአርቲስቶች ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡
ቤት ፡ እያቆሙ ፡ ማሠልጠንና ፡ ማወዳደር ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ይህ ፡ ካል
ሆነ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በብዙ ፡ ሺሕ ፡ ዓመታት ፡ ካፈራችው ፡ ሥልጣኔ ፡ ል

ትኰራበትና ፡ ልትጠቀምበት ፡ የሚገባው ፡ በብዙ ፡ ሚሊያርድ ፡ ብር ፡ የማይገዛው ፡ ጥበቧ ፡ ይሞታል ። በኋላም ፡ ጥቅሙን ፡ ባወቀችው ፡ ጊዜ ፡ ወቅቱ ፡ የተላለፈ ፡ በመሆኑ ፡ ትንሣኤ ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልም ። በማስተማርም ፡ የማይገኝ ፡ ይሆናል ።

ለምሳሌ ፡ ያኸል ፡ ሾፐንሃወርና ፡ ሄጌል ፡ እነዚህ ፡ ፈላስፎች ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ በድርሰታቸው ፡ ውስጥ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሰፊ ፡ ቦታ ፡ እንደሰጡትና ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርገው ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ጥናት ፡ እንዳደረጉበት ፡ ብንመለከተው ፡ ይህ ፡ ጉዳይ ፡ ትልቅ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ እንጂ ፡ ጨዋታ ፡ አለመሆኑን ፡ በቶሎ ፡ እንረዳዋለን ። እንዲያውም ፡ ሥልጣኔ ፡ ለመድረስ ፡ ከምትጣጣርላቸው ፡ ከከፍተኞቹ ፡ ዐላማዎች ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። ይህ ፡ ጉዳይ ፡ ዝቅተኛ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠረው ፡ የሥልጣኔያቸው ፡ ደረጃ ፡ በጣም ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ በሚገኘው ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ከሱዳን ፤ ከጃፓን ፤ ከኰሬ ፡ የተቀዱ ፡ ናቸው ፡ የሚባሉ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ስሜት ፡ ፈጽሞ ፡ ባዕድ ፡ የሆኑ ፡ ዘፈኖች ፡ ባማርኛ ፡ ሲዘፈኑ ፡ እንሰማለን ። ይህም ፡ በጣም ፡ የሚያሳዝን ፡ ነው ። በኰሚኒስትነቷ ፡ ማቴሪያስት ፡ የሆነችው ፡ መስኮብ ፡ እንኳ ፡ ይህን ፡ ጥበብ ፡ ትልቅ ፡ ደረጃ ፡ ሰጥታው ፡ እንመለከታለን ። የኛ ፡ ቅርስ ፡ ከእነሱ ፡ ያነሰ ፡ ሆኖ ፡ ነውን ? እንደዚሁም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዜማ ፡ በጣም ፡ የተራቀቀና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የተመሥጦ ፡ ስሜት ፡ ያለበት ፡ በመሆኑ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ከሚገኙት ፡ ዜማዎች ፡ ጋራ ፡ ገብቶ ፡ ቢወዳደር ፡ የመጀመሪያውን ፡ ደረጃ ፡ እንደሚይዝ ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ። ነገር ፡ ግን ፡ ዋጋው ፡ እንዲታወቅ ፡ ለማድረግ ፡ ይቻል ፡ ዘንድ ፡ ከሁሉ ፡ ነገር ፡ አስቀድሞ ፡ እኛ ፡ ነገሩ ፡ እንዲገባን ፡ ያስፈልጋል ። ለዓለም ፡ ሊታወቅና ፡ ሊገለጥ ፡ የሚችለው ፡ በኛ ፡ አማካይነት ፡ ነው ። እኛም ፡ ይህንን ፡ ለማድረግ ፡ የምንችለው ፡ ዘመናዊውን ፡ ትምህርት ፡ የተማሩ ፡ በጉዳዩ ፡ መንፈሳቸው ፡ የሚሳብና ፡ በሳይንቲፊክ ፡ መንገድ ፡ ጉዳዩን ፡ አጥንተው ፡ ለውጭው ፡ ዓለም ፡ የሚያስተላልፉ ፡ ሰዎች ፡ (ወጣቶች) ፡ ስናገኝ ፡ ነው ። በዚህ ፡ በኩል ፡ የሚገባውን ፡ ለመፈጸም ፡ ስናስብ ፡ ጨዋታ ፡ በመሆኑ ፡ በቀላሉ ፡ የሚከናወን ፡ እንዳይመስለን ። ብዙ ፡ ቴክኒሲያኖችና ፡ ኤክስፔርቶች ፤ መሐንዲሶችም ፡ የሚጠይቅ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ የሥራ ፡ ድርጅት ፡ ለማቋቋም ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ያኸል ፡ ጥናትና ፡ ጥንቃቄ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሥራ ፡ ነው ። እያንዳንዱ ፡ ሕዝብ ፡ በጥበብ ፡ በኩል ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ የተለየ ፡ እድርጋ ፡ የምትሰጠው ፡ ዕድል ፡ አለ ። ለምሳሌ ፤ ፈረንሳዮች ፡ በድርሰት ፤ ጀርመኖች ፡ በሙዚቃና ፡ በፍልስፍና ፤ እንግሊዞች ፡ በንግድና ፡ በባንክ ፤ ኢጣልያኖች ፡ በሥዕልና ፡ በዘፈን ፡ ተወዳዳሪ ፡ የላቸውም ። አሜሪካኖች ፡ ደግሞ ፡ በኢንዱስትሪና ፡ በሀብት ፡ ከሁሉ ፡ የላቁ ፡ ናቸው ። አሜሪካኖች ፡ ምንም ፡ ያኸል ፡ ሀብታሞች ፡ ቢሆኑ ፡ እንደ ፡ መስኮቦች ፡ ዶስቶዬቭስኪን ፤ ቶልስቶዩን ፤ ጐጐልን ፡ የመሰሉ ፡ ደራስያን ፡ ሊፈጥሩ ፡ አልቻሉም ። እንደዚሁም ፡ መስኮቦች ፡ በዳንስ ፡ የመጀመሪያውን ፡ ደረጃ ፡ ይዘው ፡ ይገኛሉ ። ለዚሁም ፡ የዳጊሊየብንና ፡ የኒዢንስኪን ፡ ታሪክ ፡ መመልከት ፡ ነው ።



ሥነ ፡ ጥበብ ፡ ማለት ፡ ውብ ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የሚያስወድድ ፡ ስሜት ፡ ነው ። ካንት ፡ የሚባለው ፡ የጀርመን ፡ ፈላስፋ ፡ «ውብ ፡ ነገር ፡ ማለት ፡ ከውስጡ ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡ ሳናገኝበት ፡ የሚያምር ፡ በመሆኑ ፡ ብቻ ፡ የምንወደው ፡ ነገር ፡ ነው» ፡ ሲል ፡ ይተረጉምለናል ። በጣም ፡ የሚያምር ፡ አበባ ፡ ባየን ፡ ጊዜ ፡ አሳብ ፡ የሚማርክ ፡ ዜማ ፡ በሰማን ፡ ጊዜ ፡ መንፈሳችን ፡ በደስታ ፡ ይሰክራል ። የሚበላ ፤ የሚጠጣ ፤ የሚለበስ ፤ ማለት ፡ ሥጋዊን ፡ ፍላጎት ፡ የሚመለከት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ባገኘን ፡ ጊዜ ፡ ፍላጎታችንን ፡ በመፈጸም ፡ እንጠግባለን ፤ ከጠገብንም ፡ በኋላ ፡ ደስታችን ፡ ይሞላል ። አበባን ፤ ዜማን ፤ ሥዕልን ፡ ውብ ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በማየትና ፡ በመስማት ፡ የምናገኘው ፡ የመንፈስ ፡ ደስታ ፡ ግን ፡ መቼም ፡ ቢሆን ፡ ስለማይጠግብ ፡ ደስታው ፡ ወሰን ፡ የለውም ። ምክንያቱም ፡ ነፍስን ፡ የሚመለከት ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። ቪክቶር ፡ ሂጎ ፡ ካንድ ፡ ሙዜ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ በጣም ፡ የሚያምር ፡ አንድ ፡ ሥዕል ፡ ስላየ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ ሲመለከት ፡ ዋለ ፡ ይባላል ። የሰማይ ፡ ደስታ ፡ የማይጠገብና ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ እናምናለን ። ከሥነ ፡ ጥበባት ፡ የሚገኘው ፡ ደስታም ፡ ከሰማያዊው ፡ ደስታ ፡ የተገኘ ፡ ፍርፋሪ ፡ በመሆኑ ፡ አይጠገብም ።

አሁን ፡ በትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ሥነ ፡ ጥበባት ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ የሥራ ፡ ድርጅት ፡ በተለየ ፡ ስለ ፡ ተቋቋመ ፡ ጉዳዩ ፡ በጥብቅ ፡ እንደሚታሰብበት ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

# ልዩ ፡ ልዩ ፡ አስተያየቶች ።

አሁን ፡ እንግዲህ ፡ አቋርጠነው ፡ የነበረውን ፡ ለጒዳዩ ፡ መነሻ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘውን ፡ አርእስት ፡ ማለት ፡ የሥልጣኔን ፡ ጠባይ ፡ የመመርመራችንን ፡ ሥራ ፡ መከታተላችንን ፡ እንቀጥላለን ። ይህንን ፡ ስናደርግ ፡ የተሰወረ ፡ ሆኖ ፡ የሚታየን ፡ ነገር ፡ ሲገጥመን ፡ ሊቃውንት ፡ በጸፉቸውና ፡ በተናገሯቸው ፡ ቃሎች ፡ ጨለማውን ፡ በማብራራት ፡ ርዳታቸውን ፡ እንዲያደርጉልን ፡ እንጠይቃቸዋለን ። አስፈላጊ ፡ በሆነው ፡ ስፍራ ፡ ላይ የሚያበድሩን ፡ ጥቅሶች ፡ የብርሃን ፡ ፋና ፡ ሆነው ፡ እንደሚያገለግሉን ፡ አይጠረጠርም ። የዓለም ፡ ሊቃውንት ፡ በዛሬይቱ ፡ ሥልጣኔ ፡ ላይ ፡ ጥናት ፡ ሲያደርጉ ፡ የሰጡትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አስተያየቶች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ በተራ ፡ በተራ ፡ እንመለከታቸዋለን ። አንዳንዶቹ ፡ ሊቃውንት ፡ ዓለም ፡ አሁን ፡ የተከተለችው ፡ መንገድ ፡ ከሁሉም ፡ የተሻለ ፡ መሆኑን ፡ ይናገራሉ ። ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ በማቴሪያሊስም ፡ በኩል ፡ ብቻ ፡ እርምጃዋ ፡ ተፋጥኖ ፡ በመንፈስ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርታለች ፤ ወይም ፡ ከነበረችበት ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡ ኋላዋ ፡ አፈግፍጋለች ፡ አያሰኝም ። እንደነ ፡ ቮልታ ፤ ኤዲስን ፤ ስቲፈንሰን ፤ ኮፔርኒክ ፤ ንውተን ፤ ማርኮኒ ፡ የመሰሉት ፡ ሊቃውንት ፡ በሳይንስና ፡ በቴክኒክ ፡ በኩል ፡ ሥልጣኔ ፡ ሰፊ ፡ እርምጃ ፡ እንድታደርግ ፡ የረዱ ፡ ሲሆኑ ፡ እንደነ ፡ ዴካርት ፤ ሩሶ ፤ ቮልቴር ፤ ካንት ፤ ገት ፤ የመሰሉት ፡ ፈላስፎችና ፡ ደራስያን ፡ ደግሞ ፡ የሰው ፡ ጠባይ ፡ እየተሻሻለ ፡ እንዲሄድ ፡ ለማድረግ ፡ ጥረውበታል ። ስለዚህ ፡ የመንፈስና ፡ የግዙፍ ፡ አካል ፡ እርምጃ ፡ እንደ ፡ ፈረስ ፡ ጆሮ ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ሆነው ፡ ስለሚሄዱ ፡ የሚያሠጋ ፡ ነገር ፡ የለበትም ፡ ይላሉ ።

ሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ በሁለቱ ፡ መንገዶች ፡ የሚራመደው ፡ የሥልጣኔ ፡ አካሄድ ፡ ፈጽሞ ፡ ኅብረት ፡ አላገኘም ። በሳይንስና ፡ በቴክኒክ ፡ በኩል ፡ የሚደረገው ፡ እርምጃ ፡ ይልቁንም ፡ ከመጨረሾቹ ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ዓመታት ፡ ጀምሮ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አለመጠን ፡ እየተፋጠነ ፡ ስለሄደ ፡ ሰው ፡ በማቴሪያሊስም ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ተሸንፏል ። ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ማንኛውም ፡ ሕዝብ ፡ ቢሆን ፡ ፋብሪካ ፡ ማቋቋምን ፤ ከተማውን ፡ ማሳመርን ፤ እርሻን ፡ ማሻሻልን ፤ መንገዶች ፤ የውሃ ፡ ግድቦችና ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ መሥራትን ፤ ስልክ ፡ ራድዮና ፡ ቴሌቪዥን ፡ ማግኘትን ፡ ነው ፡ የሚፈልገው ። ይህንንም ፡ ለማድረግ ፡ ብዙ ፡ ቴክኒሲያኖችና ፡ መሐንዲ

ሶች ፡ ማስተማርና ፡ ማሠልጠን ፡ ግዴታ ፡ አለበት ። እንደዚሁም ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ዛሬ ፡ ትምህርት ፡ የሚማረው ፡ ዕውቀት ፡ መልካም ፡ ነች፡ ምክንያቱም ፡ ሰውን ፡ ከእንስሳነት ፡ ወደ ፡ መልአክነት ፡ ትለውጠዋለች ፡ ብሎ ፡ በማሰብና ፡ በዚህ ፡ አሳብ ፡ መሠረት ፡ ዕውቀትን ፡ በመውደድ ፡ ሳይሆን ፡ ቴክኒሲያን ፡ ወይም ፡ መሐንዲስ ፡ ወይም ፡ ሐኪም ፡ ሆኖ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፡ ነው ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ የራሷን ፡ ልጆች ፡ ማለት ፡ ምዕራባውያንን ፡ ብቻ ፡ ማበላሸቷ ፡ አልበቃ ፡ ብሏት ፡ ሥልጣኔዋን ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ነዝታ ፡ የመላው፡ ዓለምን ፡ ሕዝቦች ፡ በማበላሸት ፡ ላይ ፡ ትገኛለች ። እነዚህ ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉም ፡ በየበኩላቸው ፡ ሥልጣኔ ፡ ነበራቸው ። አሁን ፡ ግን ፡ ከብዙ ፡ ሺሕ ፡ ዓመታት ፡ ጀምሮ ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣውን ፡ የራሳቸውን ፡ አስተዳደግና ፡ የልጅ ፡ አቀጣጥ ፡ እንደዚሁም ፡ የሞራልን፡ ትምህርት ፡ እንዲቀር ፡ አድርገው ፡ የምዕራብ ፡ አገሮችን ፡ አስተዳደግ ፡ በመከተል ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ ። ጕዳቱ ፡ ለኛ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለመላው ፡ ዓለም ፡ ስለ ፡ ተረፈ ፡ በታሪክ ፡ ፊት ፡ ትልቅ ፡ አላፊነት ፡ አለባት ። የምዕራባውያንን ፡ ሥልጣኔ ፡ የሚቀዱ ፡ ሕዝቦች ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ መልካሙን ፡ ከመቅሠም ፡ ይልቅ ፡ መጥፎውን ፡ መውሰድ ፡ ይቀናቸዋል ፤ ስለዚህ ፡ በማንኛውም ፡ በኩል ፡ ከጕዳት ፡ በቀር ፡ ጥቅም ፡ አላገኙበትም ፡ ይላሉ ። ሂትለር ፡ ይህን ፡ አሳብ ፡ ከሚደግፉት ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡ ነበር ።

እንግዲህ ፡ ከእነዚህ ፡ ከሁለቱ ፡ አስተያየቶች ፡ እውነተኛው ፡ የትኛው ፡ ነው ? ከሁለቱም ፡ በኩል ፡ እውነት ፡ አለ ። የምዕራብ ፡ ሕዝቦች ፡ በማቴሪያሊስም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በመንፈስ ፡ በኩልም ፡ ያላቸው ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ በጣም ፡ የጠለቀ ፡ ነው ። ከግሪክ ፡ ፈላስፎች ፡ ጀምሮ ፡ አሁን ፡ እስካለንበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የተከታተሉት ፡ ፈላስፎቻቸውና ፡ ደራስያኖቻቸው ፡ በጻፏቸው ፡ መጻሕፍት ፡ መንፈሳቸው ፡ ስለ ፡ ተመገበ ፡ ባሕርያቸውና ፡ ጠባያቸው ፡ በጣም ፡ እየተሻሻለ ፡ ሄዷል ። ደግነት ፤ ርኅራኄና ፡ መንፈሰ ፡ ሰፊነት ፤ በእነሱ ፡ ዘንድ ፡ በሰፊው ፡ ይገኛል ። ስንት ፡ ፈላስፎች ፤ ስንት ፡ ሊቃውንት ፤ ስንት ፡ ደራስያን ፤ ስንት ፡ ጻድቃን ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ከግሪክ ፡ ሥልጣኔ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በሠሩት ፡ ሥራ ፡ የሰውን ፡ ሁኔታ ፡ በሞራል ፡ በኩል ፡ ባሕርዩን ፡ ለማሻሻል ፡ የደከሙት ፡ ድካም ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ታላቅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስናስተውለው ፡ ሥልጣኔ ፡ በማቴሪያሊስም ፡ በኩል ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የተራመደችው ፡ ብሎ ፡ ለማለት ፡ እንዴት ፡ እንደፍራለን ? የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ የዓለምን ፡ ሰዎች ፡



ሁሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ማለት ፡ ወንድማማቾች ፡ ሲያደርጋቸው ፡ የጭካኔን ፤ የትዕቢትን ፤ በጠቅላላው ፡ የክፋትን ፡ ሁሉ ፡ ምንጭ ፡ ደምስሶታል ።

ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ አሁን ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ሌላ ፡ አስተያየት ፡ ተፈጠረ ። ይኸውም ፡ የጥንት ፡ ሕዝቦች ፡ የሳይንስና ፡ የቴክኒክ ፡ ጥበብ ፡ ሳይገለጥላቸው ፡ ቀርቷል ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ። ነገር ፡ ግን ፡ በጣም ፡ ቢስፋፉና ፡ በተራ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ገብቶ ፡ ቢገኝ ፡ ከጥቅሙ ፡ ይልቅ ፡ ጕዳት ፡ እንደሚያመጣባቸው ፡ ስላወቁት ፡ ተሸፍኖ ፡ እንዲኖር ፡ አደረጉት ፡ የሚል ፡ ነው ። ለምሳሌ ፤ ሉሲያን ፡ ዱፕሌሲ ፡ (Lucien Duplessy) የተባለው ፡ ደራሲ ፡ የጻፈውን ፡ መጽሐፍ ፡ ስናነብ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ እናገኛለን ። «የጥንት ፡ ሕዝቦች ፡ የነበራቸው ፡ የሳይንስ ፡ ጥበብ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እኛ ፡ በተከተልነው ፡ መንገድ ፡ የሄደ ፡ ሆኖ ፡ ባይገኝ ፡ ይታመን ፡ ከነበረው ፡ የበለጠ ፡ ጥልቅ ፡ መሆኑ ፡ ተደርሶበታል ። ነገር ፡ ግን ፡ የጥንቲቱ ፡ ሳይንስ ፡ ምስጢሯ ፡ በተገለጠችላቸው ፡ በጥቂት ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ ተጠብቃ ፡ ትኖር ፡ የነበረች ፡ በመሆኗ ፡ እነዚህ ፡ የሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ምስጢሮች ፡ ገሀድ ፡ የወጡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተራው ፡ ሕዝብ ፡ አስፈላጊ ፡ ከሆነው ፡ በላይ ፡ ይሠራበታል ፡ በማለት ፡ ይፈሩ ፡ ነበር ። ግብጾች ፤ ከለዳውያን ፤ ግሪኮች ፤ ሮማውያን ፡ ለዚህ ፡ ዕውቀት ፡ ዋጋ ፡ ሲሰጡት ፤ ተስፋፍቶ ፡ እንዲሠራበት ፡ አላሰቡም ። መርምረው ፡ የደረሱባቸውን ፡ እነዚህን ፡ ዕውቀቶች ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ የተነዙ ፡ ከማድረግ ፡ ይጠነቀቁ ፡ ነበር ። ለቀላል ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ እንዲያገለግሉ ፡ ሲያደርጓቸው ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ እንዲህ ፡ የተሠራጨ ፡ ሆኖ ፡ በሚገኝበት ፡ አኳኋን ፡ እንዲሠራበት ፡ አልፈቀዱም ። ማዳም ፡ ዢና ፡ ሎምብሮዝ ፡ ብዙ ፡ ነገርና ፡ ብዙ ፡ አሳብ ፡ በሚገኝበት ፡ መጽሐፏ ፡ ውስጥ ፡ ስትናገር ፡ በቴአትርና ፡ በጦርነት ፡ ቦታ ፡ ይሠሩባቸው ፡ የነበሩት ፡ መሣሪያዎች ፡ ከኛ ፡ ሜካኒስሞች ፡ ጋራ ፡ በጣም ፡ የተቀራረቡ ፡ በመሆናቸው ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውሉ ፡ ሳያደርጓቸው ፡ የቀሩት ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ? ያሰኛል ፡ ስትል ፡ አሳስባለች ። እንዲህም ፡ ስትል ፡ መልሱን ፡ ሰጥታለች ። ምክንያቱ ፡ በሞራል ፡ በኩል ፡ ጕዳዩን ፡ ሲያስተውሉት ፡ መኪናነት ፡ ያላቸው ፡ መሣሪያዎች ፡ ሁሉ ፡ የሚያሰጉ ፡ እንጂ ፡ የማይጠቅሙ ፡ ሆነው ፡ ስላገኟቸው ፡ ነው ። በእነሱ ፡ አስተያየት ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ የተገመተው ፡ ሰውን ፡ ለማሻሻል ፡ እንጂ ፡ ድካምን ፡ ለመሸሽና ፡ ሀብትን ፡ ለማከማቸት ፡ ባለመሆኑ ፡ ነው» ።

እንሆ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ብልኆች ፡ የነበሩት ፡ የጥንት ፡ ሰዎች ፡ የቴክኒክን ፡ ዕውቀት ፡ ከደረሱበት ፡ በኋላ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ጕዳት ፡ አስ

ቀድመው ፡ ስለ ፡ ተረዱት ፡ እንዲስፋፋ ፡ አላደረጉትም ። አስተያየታቸው ፡ አጭር ፡ የሆነው ፡ ያሁኑ ፡ ዘመን ፡ ያውሮፓ ፡ ሊቃውንት ፡ ግን ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ያገኙ ፡ መስሏቸው ፡ በተራ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ እንዲገባ ፡ አደረጉት ፡ ሲሉ ፡ አንዳንድ ፡ ሊቃውንት ፡ ይናገራሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህንን ፡ ለማመን እንዴት ፡ ይቻላል ? የጥንቶቹ ፡ ሕዝቦች ፡ ጥበቡን ፡ ደርሰውበት ፡ ሳለ ፡ እንዲስፋፋ ፡ ለማድረግ ፡ ባለማሰባቸው ፡ ታድለዋል ፡ ቢባል ፡ ይመስላል ፤ ሊያስፋፉት ፡ ሲችሉ ፡ ጕዳቱን ፡ አመዛዝነው ፡ ተዉት ፡ ሲሉን ፡ ግን ፡ ለማመን ፡ ያስቸግራል ። የሆነው ፡ ሆኖ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የሳይንስና ፡ የቴክኒክ ፡ መስፋፋት ፡ ለሥልጣኔ ፡ አይበጅም ፡ ለማለት ፡ መሆኑ ፡ ግልጥ ፡ ነው ። ሳይንስና ፡ ቴክኒክ ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ የተጠሉበት ፡ ምክንያት ፡ ምንድነው ? ይህ ፡ ነገር ፡ ግራ ፡ ሆኖ ፡ ስለሚታየን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ከሥር ፡ እንመልከተው ።

ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ መጥፎ ፡ ነች ፡ ወይስ ፡ ጥሩ ? ጥሩነቷና ፡ መጥፎነቷ ፡ በምን ፡ ይታወቃል ? ለእነዚህ ፡ ጥያቄዎች ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ አይደለም ። ከሠለጠኑት ፡ አገሮች ፡ በሄድን ፡ ጊዜ ፡ የምንመለከታቸው ፡ ነገሮች ፡ በመንፈሳችን ፡ ውስጥ ፡ የመደነቅን ፡ ስሜት ፡ ያሳድሩብናል ። ከዚህ ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ፡ የብዙ ፡ ዘመን ፡ ድካም ፡ ጠይቋል ። የእግዚአብሔርን ፡ የፈጣሪነቱን ፡ ትልቅነት ፡ የምናደንቀው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ጐልተው ፡ የሚታዩትን ፡ እንደ ፡ ተራሮች ፤ ውቅያኖስ ፤ የመሬትን ፡ ስፋትና ፡ የሰማይን ፡ ከዋክብት ፡ እነዚህን ፡ የመሰሉትን ፡ ታላላቅ ፡ ነገሮች ፡ ልብ ፡ ብለን ፡ በተመለከትናቸው ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከዚህ ፡ ይበልጥ ፡ ደግሞ ፡ በሰው ፡ አካላት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ለምሳሌ ፤ የደም ፡ አካሄድ ፤ የምግብና ፡ የመጠጥ ፡ ወደ ፡ ደምና ፡ ወደ ፡ ሥጋ ፡ መለወጥ ፤ አንጐል ፡ በቀሩት ፡ ሕዋሳቶች ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ያዛዥነት ፡ ተግባር ፤ በሥጋና ፡ በመንፈስ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፤ እነዚህ ፡ ሁኔታዎች ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ ሥርዐትና ፡ ሕግ ፡ እየተከናወኑ ፡ ሁሉም ፡ በየበኩላቸው ፡ የሚፈጽሙትን ፡ ተግባር ፡ ስንመለከት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጥበብ ፡ ረቂቅነት ፡ ይበልጥ ፡ እናደንቃለን ። ይህም ፡ የሰው ፡ መንፈስ ፡ በመደነቅ ፡ የሚመታው ፡ አንድም ፡ ታላቅና ፡ ግዙፍ ፡ የሆነውን ፡ እንደ ፡ ፒራሚድ ፡ ያለውን ፡ በማየት ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በጣም ፡ ረቂቅ ፡ በሆነ ፡ ጥበብ ፡ ተሠርቶ ፡ የሚከናወነው ፡ በማስተዋል ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በእነዚህ ፡ በሠለጠኑት ፡ አገሮች ፡ ጐልቶ ፡ የምናየው ፡ እንደ ፡ ሕንጻ ፤ እንደ ፡ ፋብሪካ ፤ እንደ ፡ መንገዶችና ፡ እንደ ፡ ድልድዮች ፡ የመሰሉትን ፡ ግዙፍ ፡ ነገሮች ፡ ስንመለከት ፡ መደነቃችን ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ረዘም ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ በመካከላቸው ፡ ተቀምጠን ፡ ባኗኗራቸው ፡ ውስጥ ፡



ያሉትን ፡ ረቂቅ ፡ የሆኑ ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ ስናስተውል ፡ የበለጠ ፡ አድናቆት ፡ ያድርብናል ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አይገኝም ። ነገር ፡ ግን ፡ ከማድነቅ ፡ በቀር ፡ የሚነቀፍ ፡ ነገር ፡ የማይገኝባት ፡ መስላ ፡ በምትታየን ፡ በዚች ፡ ሥልጣኔ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ጕድለቶች ፡ ለማወቅ ፡ ስንፈልግ ፡ መሪዎች ፡ ሊሆኑን ፡ ከሚችሉት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የሁለት ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ እንጠቅሳለን ። ሁለቱም ፡ የህንድ ፡ ተወላጆች ፡ ናቸው ። ሁለቱም ፡ በቂ ፡ ትምህርት ፡ ያላቸው ፡ ብልኆች ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። እነሱም ፡ ቪቬካናንዳና ፡ ጋንዲ ፡ ናቸው ። የሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ አስተያየት ፡ በሚያስገርም ፡ አኳኋን ፡ የተለያየ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። ይህም ፡ ለምናደርገው ፡ ጥናት ፡ በጣም ፡ ይረዳናል ። ቪቬካናንዳ ፡ ንግግሩ ፡ ሁሉ ፡ ውብ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ በውነቱ ፡ እንደ ፡ (poète) ባለቅኔ ፡ ሊቈጠር ፡ የሚገባው ፡ መሆኑን ፡ ጨምረን ፡ ላንባቢ ፡ እናሳስባለን ።

# ቪ ቬ ካ ና ን ዳ ና ፡ ጋ ን ዲ ።

እንደ ፡ ቪቬካናንዳ ፡ አሳብ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የህንድ ፡ ሥልጣኔ ፡ በሃይማኖት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተች ፡ ናት ፡ የህንድ ፡ ሃይማኖት ፡ ደግሞ ፡ ከቀሩት ፡ ሃይማኖቶች ፡ ሁሉ ፡ የበለጠች ፡ ነች ። አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ እንደ ፡ ተናገሩት ፡ ሁሉ ፡ አባቴ ፡ ትንሽ ፡ ነው ፤ ሃይማኖቴም ፡ መጥፎ ፡ ነው ፤ የሚል ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ስለማይገኝ ፡ በሃይማኖት ፡ በኩል ፡ ቪቬካናንዳ ፡ ያለው ፡ አሳብ ፡ የግል ፡ ጉዳዩ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እናትተውም ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህንን ፡ ሲል ፡ ህንድ ፡ በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ ሃይማኖቷ ፡ ጠንካራ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የሕዝቡም ፡ ጠባይ ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ሲመራ ፡ ኖረ ። በኋላ ፡ ግን ፡ ሃይማኖታቸው ፡ እየላላ ፡ መልካም ፡ የነበ ረው ፡ ጠባያቸው ፡ እየተበላሸ ፡ ባጭሩ ፡ ሥልጣኔያቸውና ፡ ሃይማኖታ ቸው ፡ እያረጀ ፡ ስለሄደ ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ህንዶች ፡ ያሉበት ፡ ሁኔታ ፡ በጣም የሚያሳዝን ፡ መሆኑን ፡ ያምናል ። ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ በሳይንስና ፡ በቴክኒክ ፡ በኩል ፡ ትልቅ ፡ እርምጃ ፡ በማድረጓ ፡ ህንድ ፡ ይህንኑ ፡ ዕው ቀት ፡ ተምራ ፡ እጅ ፡ ብታደርገው ፡ ሕዝቧ ፡ ከድኽነትና ፡ ከችግር ፡እንዲ ወጣ ፡ ለማድረግ ፡ ችላ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ ትፈጽማለች ። እንደዚ ሁም ፡ ምዕራባዊውያን ፡ ሕዝቦች ፡ በደግነት ፤ በጠባይ ፡ ጥሩነት ፤ በርኅ ራኄና ፡ በአስተዳደግ ፡ በጠቅላላው ፡ (በሂውማኒቲ) ፡ በሰብአዊነት ፡ ከህንድ ፡ ሕዝብ ፡ ይበልጣሉ ። ስለዚህ ፡ በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ ቢሆን ፡ ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ለህንድ ፡ ትጠቅማለች ፡ ባይ ፡ ነው ። የተናገራ ቸውንም ፡ ቃሎች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ ጠቅሰናቸዋል ።

ቪቬካናንዳ ፡ የተባበሩትን ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥታት ፡ ሄዶ ፡ በጐ በኘ ፡ ጊዜ ፡ በቦስቶን ፡ ከተማ ፡ ተገኝቶ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥፋት ፡ የተፈረደ ባቸው ፡ ሴቶች ፡ የሚታሰሩበትን ፡ አንድ ፡ የእስር ፡ ቤት ፡ ጐብኝቷል ። እዚያም ፡ እስረኞቹን ፡ ደግነትና ፡ ርኅራኄ ፡ በሞላበት ፡ አያያዝ ፡ እንደ ሚያስተዳድሯቸው ፡ ተመልክቶ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ተናገረ ። «እስረኞቹ ፡ እንዴት ፡ ባለ ፡ ደግነት ፡ ተይዘዋል ፤ ለማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ጠቃሚዎች ፡ ሆነው ፡ እንዲገኙ ፡ እንዴት ፡ ባለ ፡ አኳኋን ፡ ጠባያቸውን ፡ ያሻሽሉታል ፤ ይህ ፡ ድርጅት ፡ የቱን ፡ ያኽል ፡ ታላቅና ፡ ውብ ፡ ነው ፤ እንድታምኑት ፡ ለማድረግ ፡ ባይናችሁ ፡ ልታዩት ፡ ያስፈልጋል ። በህ ንድ ፡ አገር ፡ ድኾችና ፡ ዝቅተኞች ፡ የሆኑትን ፡ ሰዎች ፡ እንዴት ፡ ባለ ፡

አስተያየት ፡ እንደምንመለከታቸው ፡ ሳስበው ፡ ልቤ ፡ ይታመማል ። ከወደቁበት ፡ ዝቅተኛ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲነሡ ፡ ለማድረግ ፡ የምንሠራላቸው ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለም ። በቀን ፡ በቀኑ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ እየወደቁ ፡ ይሄዳሉ ። በላያቸው ፡ ላይ ፡ ጨካኝ ፡ የሆነው ፡ የሕዝብ ፡ ማኅበር ፡ (société) የበትር ፡ ዝናም ፡ ሲያወርድባቸው ፡ ይሰማቸዋል ። በትሩም ፡ ከወዴት ፡ እንደሚመጣ ፡ አያውቁትም ። እነሱም ፡ ሰዎች ፡ መሆናቸውን ፡ ረስተውታል ። የዚህ ፡ ሁሉ ፡ ውጤት ፡ ባርነት ፡ ነው » ።

አሁን ፡ ደግሞ ፡ ቪቬካናንዳ ፡ ስለ ፡ አሜሪካ ፡ ሴቶች ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ እንስማ ። በእንግድነት ፡ እዚያ ፡ ሄዶ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ በደግነት ፡ መንፈስ ፡ ተቀብለው ፡ አስተናግደውታል ። እንግድነቱ ፡ እንዳይሰማው ፡ አስደናቂ ፡ በሆነ ፡ ስሜት ፡ ተጠንቅቀው ፡ ይዘውታል ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ በመንፈሱ ፡ ውስጥ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ አድናቆት ፡ ፈጠረበት ። የተናገረው ፡ ቃል ፡ ቀጥሎ ፡ የሚገኘው ፡ ነው ።

«የአሜሪካ ፡ ሴቶች ፡ ሆይ ፤ መቶ ፡ ሕይወቶች ፡ ቢኖሩኝ ፡ በናንተ ፡ በኩል ፡ ያለብኝን ፡ የውለታ ፡ ዕዳ ፡ ለመክፈል ፡ አይበቃኝም ። ባለፈው ፡ በጋ ፡ ወራት ፡ እዚህ ፡ አገር ፡ መጣሁ ። የመጣሁትም ፡ ያገሬን ፡ ሃይማኖት ፡ ለመስበክ ፡ ነው ። ስመጣም ፡ ያለገንዘብ ፤ ያለሹመት ፤ ወዳጅችና ፡ ረዳት ፡ ሳይኖሩኝ ፡ ፍጹም ፡ ራቍቴን ፡ ሆኜ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ እችላለሁ ። የአሜሪካ ፡ ሴቶች ፡ አጥናኑኝ ፤ መጠጊያና ፡ ምግብ ፡ ሰጡኝ ፤ በቤታቸው ፡ ተቀበሉኝ ፤ እንደ ፡ ገዛ ፡ ልጃቸው ፡ አድርገው ፡ ያዙኝ ። እንደ ፡ ወንድማቸው ። ካህናቶቻቸው ፡ «ይህን ፡ አደገኛ ፡ አረመኔ» ፡ የሚል ፡ ስም ፡ እየሰጡኝ ፡ እንዲያርቁኝ ፡ ለማድረግ ፡ ሲሞክሩ ፡ የቅርብ ፡ ወዳጆቻቸውም ፡ ይህን ፡ የባዕድ ፡ ሰው ፡ ምናልባትም ፡ «አደገኛ ፡ ሳይሆን ፡ የማይቀረውን ፡ አትርዱት»፡ እያሉ ፡ አጥብቀው ፡ ሲመክሯቸው ፡ ደጋፊዎቼ ፡ ሆነው ፡ ተገኙ ። ስለ ፡ ነፍስና ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ጠባይ ፡ ከሁሉ ፡ የበለጡ ፡ ዳኞች ፡ ናቸው ፤ ትክክለኛውን ፡ መልክ ፡ የሚቀዱ ፡ ንጹሕ ፡ መስተዋቶች ፡ ናቸው ።

ስንት ፡ የተከበሩ ፡ ንብረቶች ፡ አየሁ ፤ ስለ ፡ ንጽሕናቸውና ፡ ልጆቻቸውንም ፡ ጥቅም ፡ ባልተቀላቀለበት ፡ ፍቅር ፡ የሚወዱ ፤ ስለ ፡ መሆናቸው ፡ ለሚገባቸው ፡ ምስጋና ፡ ቃል ፡ የማይገኝላቸው ፡ ስንት ፡ እናቶች ፡ አየሁ ፤ በዲያን ፡ መቅደስ ፡ እንደሚገኘው ፡ መስተዋት ፡ ንጹሓት ፡ የሆኑ ፤ በጥበብ ፤ በአስተዳደግና ፡ በጣም ፡ ከፍተኛ ፡ በሆነ ፡ መንፈስ ፡ ሀብታሞች ፡ የሆኑ ፡ ስንት ፡ ልጃገረዶች ፡ ተመለከትኩ ። አሜሪካ ፡ በሴቶች ፡ አካላት ፡ ውስጥ ፡ መላእክት ፡ የሚገኙባት ፡ አገር ፡ መሆኗ ፡ ነውን ? ማንኛውም ፡ አገር ፡ ቢሆን ፡ ደግና ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ እንደሚገኝበት ፡ የታወቀ ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ ፍርድ ፡ ሲጣልበት ፡ ክፉት ፡ ተብሎ ፡ በሚጠራው ፡ በደካማ ፡ ጠባዮቹ ፡ ብቻ ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ። ምክንያቱም ፡ እንክርዳድ ፡ እንዳይኖር ፡ ለማድረግ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ስለማይቻል ፡ ነው ። መፍረድ ፡ የሚገባው ፡ መልካም ፤ ክቡር ፤ ንጹሕ ፤ በሕዝቡ ፡ ሕይወት ፡ ውስጥ ፡ የጠራና ፡ የጠነከረ ፡ ሆኖ ፡ በሚገኘው ፡ ባፈራው ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ሊሆን ፡ ይገባል» ።



ቪቬካናንዳ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ሂንዱኢስም ፡ ቢሆን ፡ ለቀሩት ፡ ሃይማኖቶች ፡ ሁሉ ፡ በተለየም ፡ ለክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አድናቆት ፡ ነበረው ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ በሮማ ፡ ከተማ ፡ ሳለ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የእመቤታችንን ፡ ሥዕል ፡ አቀረበለትና ፡ እባክኽ ፡ ባርከኽ ፡ ስጠኝ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፤ የሕፃኑን ፡ የክርስቶስን ፡ እግር ፡ ትልቅ ፡ አክብሮት ፡ በሚታይበት ፡ አኳኋን ፡ በእጁ ፡ ነካውና ፡ «እግሮቹን ፡ በእንባዬ ፡ ሳይሆን ፡ ከልቤ ፡ በሚወጣው ፡ ደም ፡ ባጥበው ፡ በወደድኩ ፡ ነበር» ፡ ብሎ ፡ በትሕትና ፡ ሳይባርክ ፡ ሥዕሉን ፡ ለደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ መለሰለት ፡ ይባላል ። ይህም ፡ በእኔ ፡ እጅ ፡ ሊባረክ ፡ አይገባውም ፡ ለማለት ፡ መሆኑ ፡ ግልጥ ፡ ነው ። ሃይማኖቱ ፡ ያልሆነውን ፡ እንደዚህ ፡ አድርጎ ፡ ሲያከብር ፡ የቱን ፡ ያኽል ፡ መንፈሱ ፡ ሰፊና ፡ በእውነት ፡ የሠለጠነ ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ ይገልጥልናል ። ፕሮቴስታንቶች ፤ ኦርቶዶክሶች ፤ ካቶሊካውያን ፡ ተብለን ፡ የምንጠራው ፡ ክርስቲያኖች ፡ የሆን ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ እንደዚህ ፡ እንከባበራለን ፡ ወይ ? የሕይወቱን ፡ ታሪክ ፡ የጻፈ ፡ ሰዋሚ ፡ ኒክሂላናንዳ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ ሲናገር ፡ የሱ ፡ አሳብ ፡ ጥንታዊ ፡ የሆነውን ፡ የህንድን ፡ (ሃይማኖት) ፡ ላሜሪካኖች ፡ ሰጥቶ ፡ ለዚህ ፡ ለውጥ ፡ የእነሱን ፡ የሳይንስና ፡ የቴክኒክ ፡ ዕውቀቶች ፡ ተቀብሎ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ለመውሰድ ፡ ነበር ፡ ይላል ።

አሁን ፡ እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ጋንዲ ፡ ዞረን ፡ የሱን ፡ አስተያየት ፡ እንመልከት ። ጋንዲ ፡ ስለ ፡ ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ የነበረው ፡ አሳብ ፡ ምንድነው ? በጋንዲ ፡ አስተያየት ፡ ከምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ የሚገኙት ፡ ዕውቀቶችና ፡ ጥበቦች ፡ ሁሉ ፡ ከጕዳት ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡ የማይሰጡ ፡ ናቸው ። የቴክኒክና ፡ የሳይንስ ፡ ዕውቀቶች ፡ የቀሩትም ፡ ጥበቦች ፡ ሁሉ ፡ የሰውን ፡ ባሕርይ ፡ የሚያበላሹና ፡ ሥነ ፡ ፍጥረቱን ፡ ዝቅ ፡ የሚያደርጉ ፡ ናቸው ። ሕግ ፤ ሕክምና ፤ አስትሮኖሚ ፤ ጂዖግራፊ ፤ የቀሩትም ፡ ጥበባት ፡ ሁሉ ፡ በጠቅላላው ፡ ለምንም ፡ የማያገለግሉ ፡ ከንቱ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ።

ጋንዲ ፡ ስለ ፡ ጠበቆችና ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ዐዋቂዎች ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ እንጠቅሰዋለን ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ ጋንዲ ፡ ራሱ ፡

በዩኒቤርሲቲ ፡ ተመርቆ ፡ የወጣ ፡ የሕግ ፡ ሊቅ ፡ መሆኑን ፡ እንዳንዘነጋው ፡
ያስፈልጋል ። እንደዚሁም ፡ በህንድ ፡ አገር ፡ በሂንዱዊዎችና ፡ በእስላሞች ፡
መካከል ፡ የሃይማኖት ፡ ጠብ ፡ መኖሩን ፡ ማወቅ ፡ አለብን ። የጋንዲ ፡ ንግ
ግር ፤ የሚከተለው ፡ ነው ፡ «ህንዶችና ፡ እስላሞች ፡ ይጣላሉ ። አስተዋይ
የሆነ ፡ ሰው ፡ ሁሉን ፡ ነገር ፡ እንዲረሱት ፡ ይነግራቸዋል ። በሁለቱም ፡
በኩል ፡ ጥፋት ፡ መኖሩ ፡ የማይጠረጠር ፡ መሆኑን ፡ ይገልጥላቸዋል ። ጠባ
ቸውን ፡ በዕርቅ ፡ እንዲጨርሱ ፡ ይመክራቸዋል ። እነሱም ፡ እንደዚህ ፡ ማድረ
ጋቸውን ፡ ትተው ፡ ሕግ ፡ ዐዋቂ ፡ ወደ ፡ ሆነው ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ ይሄዳሉ ።
የሕግ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ተግባር ፡ ደንበኞቻቸውን ፡ እውነተኞች ፡ ማድረግና ፡
ያላሰቡትን ፡ የመከራከሪያ ፡ መንገድ ፡ መስጠት ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።
ጠበቆች ፡ እንዲህ ፡ ባያደርጉ ፡ ኖሮ ፡ ሥራቸውን ፡ የሚያበላሹ ፡ ሆነው ፡
ይቈጠራሉ ። ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ በጠቅላላው ፡ የተፈጠረውን ፡ ጠብ ፡ እን
ዲበርድ ፡ በማድረግ ፡ ፈንታ ፡ እንዲጋጋል ፡ ያደርጋሉ ። ከዚህም ፡ በላይ ፡
በዚህ ፡ ሥራ ፡ የሚተዳደሩ ፡ ሰዎች ፡ ሥራቸውን ፡ የሚሠሩት ፡ የተቸገ
ሩትን ፡ ሰዎች ፡ ለመርዳት ፡ በመፈለግ ፡ ሳይሆን ፡ ለራሳቸው ፡ ሀብት ፡
ለማግኘት ፡ የሚፈልጉ ፡ በመሆናቸው ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ጥቅማቸው ፡ የጠ
ቡን ፡ ምክንያቶች ፡ ማብዛት ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። እኔም ፡ ጉዳዩን ፡ የማው
ቀው ፡ በመሆኔ ፡ መጠን ፡ ሰዎች ፡ የሚጣሉባቸውን ፡ ምክንያቶች ፡ ሲያ
ገኙ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ። አንዳንዶቹም ፡ መጥፎ ፡ የሆኑ ፡ ጠበቆች ፡ ምክንያ
ቶቹን ፡ ራሳቸው ፡ ይፈጥሯቸዋል ። የድኾቹን ፡ ሰዎች ፡ ደም ፡ እንደ ፡ ዐልቅት ፡
ይጠጡታል ። እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ሥራ ፡ የሚይዙ ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ የሌ
ለባቸው ፡ ሰነፎች ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። ምክንያቱም ፡ ለደስታ ፡ የሚ
ሆኗቸውን ፡ ነገሮች ፡ ለመሥራት ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚሰጣቸው ፡
ነው ። ይህ ፡ እኔ ፡ የምናገረው ፡ ትክክለኛው ፡ ነገር ፡ ሲሆን ፡ የቀረው ፡
ሁሉ ፡ ሰበብ ፡ ነው ። የእነሱ ፡ ተግባር ፡ የተከበረ ፡ ሥራ ፡ መሆኑን ፡ ያወ
ጁት ፡ እነሱ ፡ ራሳቸው ፡ ናቸው ። የግል ፡ ምስጋናቸውን ፡ እንደሚያበ
ጃጁት ፡ ሁሉ ፡ ሕጉንም ፡ እንደዚያው ፡ አድርገው ፡ ያበጃጁታል ። ምን ፡
ያኽል ፡ ገንዘብ ፡ እንደሚከፈላቸው ፡ የሚወስኑት ፡ እነሱ ፡ ራሳቸው ፡
ናቸው ። ነገሩንም ፡ እያሰማመሩ ፡ ከማቅረባቸው ፡ የተነሣ ፡ ምስኪኖች ፡
የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ነገራቸውን ፡ ከሰማይ ፡ እንደ ፡ ወረደ ፡ አድርገው ፡
ይቈጥሩታል ።

ልዩ ፡ ልዩ ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ ከሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ የበለጠ ፡ ገንዘብ ፡ እን
ዲከፈላቸው ፡ የሚጠይቁት ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ? እነሱ ፡ ላንድ ፡
አገር ፡ ከእጅ ፡ ሠራተኞች ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ምን ፡ ጥቅም ፡ ይሰጣሉ ? »



አሁን ፡ ደግሞ ፡ ጋንዲ ፡ ስለ ፡ እንግሊዝ ፡ ፓርለማ ፡ የተናገረውን ፡
እናዳምጠው ። ስለ ፡ ፓርለማ ፡ ሲናገር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፤ «በጠቅላላው ፡
በሚደረገው ፡ አስተያየት ፡ የፓርለማ ፡ አባሎች ፡ ግብዞችና ፡ የግል ፡ ጥቅ
ማቸውን ፡ ፈላጊዎች ፡ ናቸው ። ሥራቸው ፡ በፍርሀት ፡ ላይ ፡ የተመሠ
ረተ ፡ ነው ። ዛሬ ፡ የተወሰነው ፡ ነገ ፡ ሊፈርስ ፡ ይችላል ። በፓርለማ ፡
ተወጥኖ ፡ ፍጻሜው ፡ ምን ፡ እንደሚሆን ፡ የሚታወቅ ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡
እንኳ ፡ አይገኝም ። በጣም ፡ ከባድ ፡ የሆኑት ፡ ጉዳዮች ፡ እንኳ ፡ በሚቀር
ቡበት ፡ ቀን ፡ የፓርለማ ፡ አባሎች ፡ የሆኑት ፡ ሲያንቀላፉ ፤ በመቀመጫ
ቸው ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ሲንጠራሩ ፡ ለማየት ፡ ተችሏል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡
ሰሚዎችን ፡ እስቲያስቈጡ ፡ ድረስ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የሚለፈልፉበት ፡
ሰዓት ፡ አለ ። ካርላይል ፡ ፓርለማን ፥(የዓለም ፡ መለፍለፊያ ፡ መደብር) ፡
ብሎ ፡ ሰይሞታል ። . . . . ለፓርለማ ፡ የሚባክነው ፡ ጊዜና ፡ ገንዘብ ፡
ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ ላላቸው ፡ ሰዎች ፡ ተሰጥቶ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ የእንግሊዝ ፡ ደረጃ ፡
አሁን ፡ ካለበት ፡ የበለጠ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ በተገኘ ፡ ነበር ። ይህ ፡ አሁን ፡
እኔ ፡ የምሰጠው ፡ አስተያየት ፡ በተለየ ፡ ከእኔ ፡ ብቻ ፡ የመነጨ ፡ ሳይ
ሆን ፡ ብልኆች ፡ የሆኑ ፡ ብዙ ፡ የእንግሊዝ ፡ ተወላጆች ፡ ተናግረውታል ።
እውነተኛ ፡ ክርስቲያን ፡ የፓርለማ ፡ ሥራ ፡ ተካፋይ ፡ መሆንን ፡ አይ
ፈቅድም ፡ ሲል ፡ የፓርለማ ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አሁን ፡ በቅ
ርብ ፡ ጊዜ ፡ ተናግሯል ። ፓርለማ ፡ ማለት ፡ ሕፃን ፡ ልጅ ፡ ነው ። ከተቋ
ቋመ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ በመሆኑ ፡ ትልቅ ፡ ባያደርገው ፡ ኖሮ ፡
መቼም ፡ ቢሆን ፡ የሚያድግ ፡ መሆኑ ፡ የሚያጠራጥር ፡ በሆነ ፡ ነበር ፡
ሲል ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ አባል ፡ ደግሞ ፡ ተናግሯል» ። ጋንዲ ፡ ስለ ፡ ሕ
ክምና ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ ጠቅሰነዋል ።

«እኔ ፡ ለሕክምና ፡ ትልቅ ፡ አድናቆት ፡ በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ ነበረኝ ።
ስለ ፡ አገሬ ፡ ጥቅም ፡ ስል ፡ እንዲያውም ፡ ሐኪም ፡ ለመሆን ፡ የተመኘሁ
በት ፡ ጊዜ ፡ ነበር ፤ አሁን ፡ ግን ፡ አስተያየቴን ፡ ለውጫለሁ ። ሐኪሞች ፡
በኛ ፡ መካከል ፡ የክብር ፡ አስተያየት ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ እንደማይሰጣ
ቸው ፡ ተረዳሁት ። እንግሊዞች ፡ (የገዥነት) ፡ እጃቸውን ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ለመ
ጫን ፡ ሲፈልጉ ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ መሣሪያ ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ ሠሩበት ፡
አይጠረጠርም ። አንዳንድ ፡ የእንግሊዝ ፡ ሐኪሞች ፡ ከእስያ ፡ አገሮች ፡
ነገሥታት ፡ ላይ ፡ የፖለቲካ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ይህን ፡ ተግባራቸውን ፡
ምክንያት ፡ እያደረጉ ፡ እንደ ፡ ሠሩበት ፡ የታወቀ ፡ ሆኗል ።

«ሐኪሞች ፡ እኛን ፡ ሞኞች ፡ እያደረጉ ፡ ቀልደውብናል ። ከፍ ፡ ያለ ፡
ችሎታ ፡ ካለው ፡ ካንድ ፡ ሐኪም ፡ አጫዋች ፡ የሆነ ፡ አታላይ ፡ ሰው ፡
እንደሚሻል ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አስባለሁ ። ጉዳዩን ፡ እንመልከተው ፤ የሐ

ኪም ፡ ሥራ ፡ የሰውን ፡ አካል ፡ ጠብቆ ፡ መያዝ ፡ ነው ። ወይም ፡ ደግሞ ፡ በትክክል ፡ ለመናገር ፡ በአካል ፡ ላይ ፡ ሊደርሱበት ፡ የሚችሉትን ፡ ሕመሞች ፡ ማስወገድ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ሕመሞች ፡ (በሽታዎች) ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ የሚመጡት ? በችላ ፡ ባይነታችንና ፡ ባለመጠንቀቃችን ፡ ነው ። አለ ፡ መጠን ፡ እበላለሁ ፤ ቊንጣን ፡ ይይዘኛል ፤ ከሐኪም ፡ ዘንድ ፡ እሄድና ፡ እሱም ፡ መድኀኒት ፡ ሰጥቶኝ ፡ እድናለሁ ። ስለዚህ ፡ እመለስበትና ፡ ሲያመኝ ፡ መድኀኒቱን ፡ ደግሜ ፡ እውጣለሁ ። መድኀኒቱን ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ባላገኘው ፡ ኖሮ ፡ በሆዳምነቴ ፡ በደረሰብኝ ፡ ሕመም ፡ ስለምሠቃይ ፡ ሁለተኛ ፡ አልመለስበትም ፡ ነበር ። .... ሆፒታሎች ፡ የኀጢአቶች ፡ ማስፋፊያ ፡ ናቸው ። ሰዎች ፡ ስለ ፡ አካላቸው ፡ የሚያደርጉትን ፡ ጥበቃ ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ እየተዉት ፡ ይሄዳሉ ፤ የግብረ ፡ ገብነት ፡ ጒድለትም ፡ እየባሰ ፡ ይሄዳል ። ያውሮፓን ፡ ሕክምና ፡ ትምህርት ፡ መማር ፡ ወደ ፡ ባርነት ፡ ይበልጥ ፡ እየሰመጡ ፡ መሄድ ፡ ነው» ። ጋንዲ ፡ ስለ ፡ ምድር ፡ ባቡር ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ተናግሯል ።

«ባቡር ፡ ባይኖር ፡ ኖሮ ፡ እንግሊዞች ፡ የህንድን ፡ አገር ፡ ሊገዙት ፡ እንደማይችሉ ፡ በቀላሉ ፡ ልንረዳው ፡ እንችላለን ። የምድር ፡ ባቡር ፡ ተላላፊ ፡ የሆነውን ፡ (ፔስት) ፡ የተባለውን ፡ በሽታ ፡ እንዲስፋፋ ፡ ለማድረግ ፡ ረድቷል ። ባቡር ፡ ባይኖር ፡ ኖሮ ፡ ሰዎች ፡ እንዲህ ፡ በቀላሉ ፡ ካንዱ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ አገር ፡ ሊዘዋወሩና ፡ ከእነሱም ፡ ጋራ ፡ የበሽታን ፡ ጀርሞች ፡ አብረው ፡ እየወሰዱ ፡ ባልናኙት ፡ ነበር ። ... ባቡር ፡ እንደዚሁ ፡ ረኃብ ፡ በየጊዜው ፡ ባገራቱ ፡ ላይ ፡ እንዲመጣ ፡ አድርጓል ። ምክንያቱም ፡ እኽል ፡ በባቡር ፡ ካንዱ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ አገር ፡ በቀላሉ ፡ በመዘዋወሩና ፡ ሰዎች ፡ እኽላቸውን ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ዋጋ ፡ እንዲሸጡ ፡ በመደረጉ ፡ ነው ። በቀላሉ ፡ ሀብት ፡ ለማግኘት ፡ ስለ ፡ ቻሉ ፡ ሰዎችን ፡ ሰነፎች ፡ አደረጋቸው ። ይህም ፡ የረኃብን ፡ መቅሠፍት ፡ እያስፋፋው ፡ ሄደ ። በሰው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ መጥፎ ፡ ጠባይ ፡ እንዲስፋፋ ፡ ለማድረግ ፡ ባቡር ፡ ረድቷል ። ዐመፀኞች ፡ ሰዎች ፡ መጥፎ ፡ ተግባራቸውን ፡ ፈጣን ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ለመፈጸም ፡ ችለዋል ። በህንድ ፡ አገር ፡ የሚገኙት ፡ የተቀደሱ ፡ ስፍራዎች ፡ ቅድስናቸውን ፡ አጡ ። በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ ሰዎች ፡ ከእነዚህ ፡ ከተባሉት ፡ ስፍራዎች ፡ ለመድረስ ፡ የሚችሉት ፡ በብዙ ፡ ችግር ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ እዚያ ፡ የሚሄዱት ፡ በእውነት ፡ አማኞች ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ። በኛ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ የከፉት ፡ ሥራቸውን ፡ ለመሥራት ፡ ሲሉ ፡ ወስላቶች ፡ ሄደው ፡ ይገኛሉ» ።

ትምህርት ፡ ላገራችን ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ መሆኑን ፡ ታምንበት ፡ የለም ፡ ወይ ? ተብሎ ፡ ለቀረበለት ፡ ጥያቄ ፡ ጋንዲ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡



መልሷል ። «ትምህርት ፡ ማለት ፡ ምንድ ፡ ነው ? ማንበብና ፡ መጻፍን ፡ ማወቅ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ ደግን ፡ ወይም ፡ ክፉን ፡ ለመሥራት ፡ የሚቻልበትን ፡ መሣሪያ ፡ መጨበጥ ፡ ማለት ፡ ነው ። አንዱ ፡ መሣሪያ ፡ የታመመን ፡ ሰው ፡ ለማዳን ፡ ወይም ፡ ለመግደል ፡ እንደሚችል ፡ ሁሉ ፡ ትምህርት ፡ መማርም ፡ እንደዚሁ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ። በሚገባ ፡ ያቀረብኩትን ፡ አስተያየት ፡ ብትቀበሉኝ ፡ ትምህርት ፡ ክፋቱ ፡ ከደግነቱ ፡ በልጦ ፡ ታገኙታላችሁ ። ....

(በገጠር ፡ ለሚኖር ፡ ሰው) ፡ ትምህርት ፡ ለመስጠት ፡ የምትፈልጉት ፡ ለምንድነው ? ተጨማሪ ፡ ደስታ ፡ እንዲያገኝ ፡ ታደርጉታላችሁን ፤ በዕድሉ ፡ የተከፋ ፡ ሆኖ ፡ እንዲገኝ ፡ ትፈልጋላችሁን ፤ የምትፈልጉት ፡ ይህ ፡ ከሆነ ፡ ትምህርትን ፡ ሊወድ ፡ አይችልም ። በምዕራባዊ ፡ አሳብ ፡ ተስበን ፡ ጥቅሙንና ፡ ጒዳቱን ፡ ሳናመዛዝነው ፡ ሕዝባችን ፡ ትምህርት ፡ ያስፈልገዋል ፡ ብለን ፡ እንናገራለን ። እኔ ፡ ራሴ ፡ ጆግራፊን ፡ አስትሮኖሚን ፤ አልጀብርን ፤ ጆሜትሪን ፤ ተምሪያለሁ ። ለኔ ፡ ለራሴ ፡ ወይም ፡ በዙሪያዬ ፡ ላሉት ፡ ሰዎች ፡ የሰጠኝ ፡ ጥቅም ፡ ምንድነው ? ይህን ፡ ሁሉ ፡ ለምንድነው ፡ የተማርኩት ? ....

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የጠቀስኳቸው ፡ ትምህርቶች ፡ ሁሉ ፡ ስሜቶቼን ፡ እቈጣጠራቸው ፡ ዘንድ ፡ አላስቻሉኝም ። ስለዚህ ፡ የመጀመሪያው ፡ ደረጃ ፡ ትምህርትም ፡ ሆነ ፡ የከፍተኛው ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ለዋናው ፡ ነገር ፡ አስፈላጊ ፡ አይደሉም ፤ ሰዎች ፡ አያደርጉንም ፤ ተግባራችንን ፡ እንድንፈጽም ፡ አያስተምሩንም» ።

ጋንዲ ፡ ታሪክን ፡ መማር ፡ የማይጠቅም ፡ መሆኑን ፡ ይናገራል ። ምክንያቱም ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የሚሰጠው ፡ የታሪክ ፡ ትምህርት ፡ ስለ ፡ ጦርነት ፡ ብቻ ፡ የሚናገር ፡ በመሆኑ ፡ ይህ ፡ ታሪክ ፡ ተብሎ ፡ ሊጠራ ፡ እንደማይገባው ፡ ያሳስባል ። እንደዚህ ፡ አድርጎ ፡ ጋንዲ ፡ ከምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ የሚገኙትን ፡ ትምህርቶችና ፡ ዕውቀቶች ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ ሳይቀር ፡ በጠቅላላው ፡ ሁሉም ፡ ከንቱ ፡ መሆናቸውን ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ ላስተያየቱ ፡ እንደ ፡ መደምደሚያ ፡ ሊቈጠር ፡ የሚገባውን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተውን ፡ ቃል ፡ ይናገራል ። «ህንዶች ፡ የግል ፡ ሥልጣኔያቸው ፡ ከቀሩት ፡ ሥልጣኔዎች ፡ ሁሉ ፡ የበለጠች ፡ መሆኗን ፡ ያውቃሉ ፤ እንደዚሁም ፡ ያውሮፓ ፡ ሥልጣኔ ፡ የገለባ ፡ እሳት ፡ መሆኗን ፡ ያውቃሉ ፤ ከሷ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ነበሩት ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ ሥልጣኔዎች ፡ ሁሉ ፡ እሷም ፡ በፍጥነት ፡ ጠፊ ፡ ናት ።

እንሆ ፡ ቪቬካናንዳና ፡ ጋንዲ ፡ ስለ ፡ ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ያላቸውን ፡ አስተያየት ፡ ስናመዛዝነው ፡ በፍጹም ፡ የተለያየ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። ቪቬካናንዳ ፡ ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ያላትን ፡ የሳይንስና ፡ የቴክኒክ ፡ ዕውቀት ፡ ለህንድ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ አግኝቶታል ። ጋንዲ፡ ግን ፡ ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ሰይጣናዊ ፡ ጥበብ ፡ ስለ ፡ ሆነች ፡ ከክፋት ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ልማት ፡ እንደማይገኝባት ፡ ይናገራል ። እንግዲህ ፡ ትክክለኛው ፡ አስተያየት ፡ የማንኛው ፡ ይሆን ? ከዚህ ፡ በላይ ፡ የጠቀስናቸውን ፡ ጋንዲ ፡ የተናገራቸውን ፡ ቃሎች ፡ አንባቢ ፡ ከተመለከታቸው ፡ በኋላ ፡ በልቡ ፡ «የጋንዲም ፡ በዛ ! » ማለቱ ፡ አይጠረጠርም ። እንደ ፡ ጋንዲ ፡ አሳብ ፡ ከሆነ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ መዝጋት ፤ የተዘረጋውን ፡ የባቡር ፡ ሐዲድ ፡ ማፍረስ ፡ ፓርለማን ፡ መሠረዝ ፤ ታሪክን ፡ መፋቅ ፡ የፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ ዳኞች ፡ ማሰናበት ፤ ፋብሪኮችን ፡ ነቅሎ ፡ መጣል ፡ ያስፈልጋል ፡ ማለት ፡ ነው ። ከሠለጠኑትም ፡ ሆነ ፡ ለመሠልጠን ፡ ከሚጣጣሩት ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ እስቲ ፡ ማንኛው ፡ ነው ፡ ይህንን ፡ አድርግ ፡ ቢሉት ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ የሚፈጽመው ። እራሷ ፡ ህንድ ፡ እንሆ ፡ ዛሬ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችንና ፡ ሆስፒታሎችን ፡ ለማስፋፋት ፡ አዲስ ፡ መንገዶችና ፡ የባቡር ፡ ሐዲዶች ፡ ለመዘርጋት ፤ ብዙ ፡ ብረት ፡ ለማቅለጥና ፡ ፋብሪኮችን ፡ ለማብዛት ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሰሉትን ፡ የሥልጣኔ ፡ ድርጅቶች ፡ ለማቋቋም ፡ በትጋት ፡ ስትደክምና ፡ ስትጣጣር ፡ ትታይ ፡ የለም ፡ ወይ ? ጋንዲን ፡ የሚያኽል ፡ ዝናው ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ የገነነ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ የማይቀበለውን ፡ ነገር ፡ መናገሩ ፡ እብድ ፡ አያሰኘውምን ? የሥልጣኔ ፡ ጥቅም ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስላልገባው ፡ ነው ፡ እንዳንል ፡ ጋንዲ ፡ በዩኒቤርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ጨርሶ ፡ ተመርቆ ፡ የወጣ ፡ ሙሉ ፡ ትምህርት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው ። ቪቬካናንዳም ፡ እንደዚሁ ፡ በፍልስፍና፡ ከዩኒቤርሲቲ ፡ ተመርቆ ፡ ወጥቷል ። ስለዚህ ፡ ዕውቀት ፡ ጐድሎት ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ፈጽሞ ፡ አይቻልም ። ይህ ፡ ጉዳይ ፡ ምስጢሩ ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ አስቸጋሪ ፡ አይደለም ። ብዙዎች ፡ ያውሮፓ ፡ ሊቃውንቶች ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ እንደ ፡ ተናገርነው ፡ የገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ የግዙፍ ፡ አካል ፡ ጥበብና ፡ (ማቴሪያሊስም) ፡ የእግዚአብሔር ፡ ክሕደት ፡ እነዚህ ፡ ሦስት ፡ ሀይነት ፡ መርዞች ፡ በዛሬይቱ ፡ ሥልጣኔ ፡ የገነኑ ፡ ሆነው ፡ ስለሚታዩባት ፡ በጣም ፡ የሚያሠጋ ፡ እርምጃ ፡ የያዘች ፡ መሆኗን ፡ ከመናገር ፡ አልተወሰኑም ። ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ሁኔታዋ ፡ ሲታይ ፡ የነቀርሳ ፡ በሽታ ፡ (ካንሰር) ፡ በታመመ ፡ ሰው ፡ ልትመሰል ፡ ትችላለች ። አንድ ፡ ሰው ፡ የደም ፡ ግባቱ ፤ ወዙ ፤ ጠቅላላ ፡ ሁኔታው ፡ የበሽታ ፡ ምልክት ፡ የሌለበት ፡ ፈጽሞ ፡ ጤናማ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ። እሱም ፡ ራሱ ፡ ከጤንነት ፡ በቀር ፡ የሚሰማው ፡ ምንም ፡ ሕመም ፡ የለም ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ሐኪም ፡ ከመረመረው ፡ በኋላ ፡ አንዳንድ ፡



ምልክቶች ፡ ተከትሎ ፡ የካንሰር ፡ በሽታ ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ ያረጋግጥለታል ። ይህም ፡ መድኀኒት ፡ የሌለው ፡ በሽታ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከጥቂት ፡ ወራት ፡ በኋላ ፡ የሚሞት ፡ መሆኑን ፡ ይነግረዋል ። እነዚህም ፡ ሊቃውንት ፡ በዚች ፡ ባሁኗ ፡ ሥልጣኔ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ እነዚህ ፡ መርዞች ፡ ዓለምን ፡ ከጥፋት ፡ ዐዘቅት ፡ እንደሚጥሏት ፡ ይተነብያሉ ። ከእነሱም ፡ መካከል ፡ ግማሾቹ ፡ በምንም ፡ ዐይነት ፡ መንገድ ፡ ቢሆን ፡ ይህቺን ፡ ከመርዟ ፡ ጋራ ፡ አብራ ፡ ተፀንሳ ፡ አብራ ፡ የተወለደችውን ፡ ሥልጣኔ ፡ ከሞት ፡ ለማዳን ፡ እንደማይቻል ፡ ይናገራሉ ። ከእነዚሁም ፡ አንዱ ፡ ጋንዲ ፡ ነው ። ጋንዲ ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ሲናገር ፡ እኔ ፡ ይህን ፡ አስተያየት ፡ ራሴ ፡ አልፈጠርኩትም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ትልልቅ ፡ ሰዎች ፡ በሰፊው ፡ ተናግረውታል ፡ እያለ ፡ በንግግሩ ፡ ውስጥ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ጣልቃ ፡ እያገባ ፡ ማሳሰቡ ፡ አልቀረም ። የጋንዲ ፡ አስተያየት ፡ እኛ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ከተማርነውና ፡ ከምናምነው ፡ ጋራ ፡ የማይገናኝ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ መንፈሳችንን ፡ ግራ ፡ ሳያገባው ፡ አይቀርም ። ማንኛውም ፡ ዐዋቂ ፤ ማንኛውም ፡ ሊቅ ፡ ቢሆን ፡ እያረጋገጠ ፡ የሚሰጠንን ፡ አሳብ ፡ ዐይናችንን ፡ ጨፍነን ፡ እንዳንቀበልና ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ተጠራጣሪነት ፡ እንዲኖረን ፡ በፊት ፡ ሶክራት ፡ በኋላም ፡ ሞንቴኝ ፡ ያስጠነቀቁን ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ። ርግጠኛ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ያመንበት ፡ ትምህርት ፡ የማያሳስት ፤ ጥሩ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ የተከተልነው ፡ መንገድ ፡ ከጥፋት ፡ ላይ ፡ የሚጥለን ፤ የሚያዋጣ ፡ አድርገን ፡ የቈጠርነው ፡ አሳብ ፡ የሚያስረታን ፡ ሆኖ ፡ ልናገኘው ፡ እንችላለን ። ስለዚህ ፡ የጋንዲ ፡ አሳብ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ግራ ፡ ሆኖ ፡ ቢታየን ፡ ከመንቀፍ ፡ በፊት ፡ አስተያየቱን ፡ በዝርዝር ፡ መመርመር ፡ ይገባናል ። ይህንን ፡ ለማመዛዘን ፡ የሚረዱንን ፡ ነገሮች ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ባሉት ፡ ምዕራፎች ፡ እናገኛቸዋለን ። እንሆ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ጋንዲና ፡ ቪቬካናንዳ ፡ ካቀረቡልን ፡ በፍጹም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተቃራኒ ፡ ከሆኑት ፡ አስተያየቶች ፡ የትኛው ፡ ትክክለኛ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማወቅ ፡ እንሞክራለን ።

ይህም ፡ ስለ ፡ ጋንዲ ፡ የምንሰጠው ፡ ፍርድ ፡ በዚህ ፡ ብቻ ፡ አይፈጸምም ፡ ማለት ፡ ነው ። ስለ ፡ ጋንዲ ፡ ታሪክ ፡ ፍርድ ፡ መስጠት ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ አለመሆኑን ፡ አንባቢ ፡ ሊዘነጋው ፡ አይገባም ። ጋንዲ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ከተፈጠሩት ፡ በማንኛውም ፡ ዘመን ፡ ታሪክ ፡ ካፈራቻቸው ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ የሚቈጠር ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ስለ ፡ እሱ ፡ ፍርድ ፡ ከመስጠት ፡ በፊት ፡ ጉዳዩን ፡ በዝርዝርና ፡ በጥንቃቄ ፡ መመርመር ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ባሉት ፡ ምዕራፎች ፡ ከዋናው ፡ አርእስት ፡ ጋራ ፡ ጉዳዩ ፡ የተያያዘና ፡ የተሳሰረ ፡ ሆኖ ፡ በሚገኝበት ፡ መጠን ፡ የጋንዲን ፡ ታሪክ ፡ መልሰን ፡ መላልሰን ፡ በመመልከት ፡ የምናደርገውን ፡

ጥናት ፡ እንቀጥላለን ። አሁን ፡ ግን ፡ የጋንዲን ፡ ታሪክ ፡ በዚህ ፡ አቋመን ፡ በቪቬካናንዳና ፡ ባንድ ፡ የሱ ፡ ተማሪ ፡ ወይም ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ በሆነ ፡ ሰው ፡ መካከል ፡ የተደረገውን ፡ ንግግር ፡ እንጠቅሳለን ። ይህ ፡ ንግግር ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ የቪቪካናንዳ ፡ አስተያየት ፡ ከጋንዲ ፡ የቱን ፡ ያኸል ፡ የተለየ ፡ መሆኑን ፡ በትክክል ፡ አጥርቶ ፡ ሲገልጥልን ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ህንድ ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ መንገድ ፡ ለመራመድ ፡ ስትፈልግ ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የሕዝቧን ፡ ጠባይና ፡ ኑሮ ፡ ማሻሻል ፡ ግድ ፡ ስለሚሆንባት ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ከፊቷ ፡ የተደቀነው ፡ ችግር ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያለ ፡ ከባድ ፡ መሆኑን ፡ ያሳየናል ።

በቪቪካናንዳና ፡ በደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ መካከል ፡ የተደረገውን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ንግግር ፡ ይኸው ፡ የሱ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ጽፎት ፡ ይገኛል ። «እኔ ፡ ራሴ» ፡ ብሎ ፡ የሚል ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ነው ። «ሱዋሚ» ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ ግን ፡ ቪቪካናንዳ ፡ ነው ። ይህ ፡ ንግግር ፡ የተደረገው ፡ እንግሊዞች ፡ ህንድን ፡ ይገዙ ፡ በነበረበት ፡ ዘመን ፡ ነው ።

ሱዋሚ ፤ ምዕራባውያን ፡ የሆኑት ፡ ደቀ ፡ መዝሙሮች ፡ በጣም ፡ ሰፊ ፡ የሆነ ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ ለዚች ፡ አገር ፡ ሊሠሩላት ፡ ይችላሉ ። ያኗኗርን ፡ ሁኔታዎች ፡ ለማሻሻል ፡ የሚረዱትን ፡ ጠቃሚዎች ፡ የሚሆኑትን ፡ የሳይንስ ፡ ዕውቀቶች ፡ የሚገልጡላችሁ ፡ መምህራኖች ፡ ይሆኑላችኋል ።

እኔ ፡ ራሴ ፤ ሱዋሚ ፡ ሆይ ፤ ይህ ፡ እንዴት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ? እነሱ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ የጥላቻ ፡ ስሜት ፡ ስንመለከተው ፡ ጥቅም ፡ ሳያገኙበት ፡ ደግ ፡ ሥራ ፡ ይሠሩልናል ፡ ብሎ ፡ ለማሰብ ፡ የሚሆን ፡ ነገር ፡ አይመስልም ።

ሱዋሚ ፤ እንደዚህ ፡ አድርገው ፡ እኛን ፡ ይጠሉን ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ምክንያቶች ፡ አሏቸው ። ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ድል ፡ የሆን ፡ ሕዝብ ፡ ነን ። እንደ ፡ እኛ ፡ ለማኞች ፡ የሚበዙበት ፡ ሕዝብ ፡ ከቶ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ አይገኝም ። መደዴው ፡ ሕዝብ ፡ በጣም ፡ የተዋረደ ፡ በመሆኑ ፡ በከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ያሉት ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ በጭካኔ ፡ ሲገዙት ፡ ይኖራሉ ። እነሱም ፡ በተገኘው ፡ ምክንያት ፡ ሁሉ ፡ በጡጫና ፡ በእርግጫ ፡ ሲደበድቡት ፡ ኖረዋል ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ለማኝነትን ፡ እንደ ፡ ዋና ፡ ተግባር ፡ አድርጎት ፡ ይኖራል ። ከመደዴው ፡ ሕዝብ ፡ በላይ ፡ ያሉት ፡ የእንግሊዝ ፡ ቋንቋ ፡ በመጠኑ ፡ ለማንበብ ፡ የሚችሉት ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ የልመና ፡ ደብዳቤ ፡ ይዘው ፡ ሥራ ፡ ለመጠየቅ ፡ በየመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ መተላለፊያውን ፡ መንገድ ፡ ወረውት ፡ ይታያሉ ። ኻያ ፡ ወይም ፡ ሠላሳ ፡ ሩፒ ፡ ደሞዝ ፡ የሚገኝበት ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ ሲኖር ፡ የቢ ፡ ኤ ፡ ና ፡ የኤም ፡ ኤ ፡ ዲ



ግሪ ፡ ያላቸው ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ሥራ ፡ ጠያቂዎች ፡ ሆነው ፡ ይቀርባሉ ። የጥያቄዎቹ ፡ አጻጻፍ ፡ ደግሞ ፡ እንዴት ፡ የሚያስገርም ፡ ነው ። «በቤቴ ፡ ውስጥ ፡ የምበላው ፡ ምንም ፡ የለኝም ። ሚስቴና ፡ ልጆቼ ፡ በረኃብ ፡ ይሞታሉ ። እኔና ፡ ቤተ ፡ ሰቦቼ ፡ ለመኖር ፡ የምንችልበት ፡ እንጀራ ፡ እንድናገኝ ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ እንዲሰጡኝ ፡ እለምንዎታለሁ ፤ አለዚያ ፡ ግን ፡ በረኃብ ፡ ማለቃችን ፡ ነው ።

ሥራ ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ የክብር ፡ ስሜታቸውን ፡ በጣም ፡ የተዋረደ ፡ ያደርጉታል ። የሚከተሉትም ፡ በጣም ፡ ዝቅ ፡ ያለውን ፡ ታዛዥነት ፡ ነው ። እንሆ ፡ ይህ ፡ መደዴው ፡ ሕዝብ ፡ የሚኖርበት ፡ ሁኔታ ፡ ነው ። እንደ ፡ እናንተ ፡ ያሉት ፡ በትምህርት ፡ ከፍተኛውን ፡ ደረጃ ፡ የያዙት ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፡ ለብቻቸው ፡ ማኅበሮች ፡ እየፈጠሩ ፡ በመኖር ፡ ድምፃቸውን ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ እንደዚህ ፡ ሲሉ ፡ ይናገራሉ ።

«ህንድ ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ በመጓዝ ፡ ላይ ፡ ትገኛለች ። ገዥዎቻችን ፡ የሆናችሁት ፡ እንግሊዞች ፡ ሆይ ፤ ያገራችን ፡ ተወላጆች ፡ በመንግሥት ፡ ሥራ ፡ በየከፍተኞቹ ፡ ስፍራዎች ፡ ተሾመው ፡ እንዲሠሩ ፡ አድርጉላቸው ፤ ከረኃብ ፡ እንድንወጣ ፡ አድርጉልን» ።

ይህን ፡ በመሰለ ፡ በማያቋርጥ ፡ ጩኸት ፡ ሌትና ፡ ቀን ፡ አየሩን ፡ ይሞሉታል ።

«እንግሊዞች ፡ ሆይ ፤ ስጡን ፡ አሁንም ፡ ጨምራችሁ ፡ ስጡን !» ይላሉ ። ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ምን ፡ ይስጧችሁ ? ላገሪቱ ፡ ባቡሮች ፤ ቴሌግራፎች ፤ ሥራት ፡ ያለው ፡ አድሚኒስትራሲዮን ፡ ሰጡ ። ሌቦችን ፡ አጠፉ ፤ የሳይንስ ፡ ትምህርት ፡ ሰጡ ። ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ሊሰጧችሁ ፡ ይችላሉን ፤ ብዙ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ሰጥተዋችኋል ፤ ለዚህ ፡ ለውጥ ፡ እረ ፡ እናንተ ፡ ምን ፡ ሰጥታችኋቸዋል ? ብዬ ፡ እስቲ ፡ እኔ ፡ ልጠይቃችሁ ።

እኔ ፡ ራሴ ፤ ሱዋሚ ፡ ሆይ ፤ ምን ፡ ልንሰጣቸው ፡ ይገባናል ? ታክስ ፡ እንከፍላለን ።

ሱዋሚ ፤ በውነት ፡ ታደርጉታላችሁን ? ፈቅዳችሁ ፡ ታክስ ፡ ትከፍላላችሁ ፡ ወይስ ፡ ደግሞ ፡ ባገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ጸጥታ ፡ እንዲጠበቅ ፡ በማድረጋቸው ፡ በኀይል ፡ እያስገደዱ ፡ ያስከፍሏችኋል ? እነሱ ፡ ለናንተ ፡ ላደረጉላችሁ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እናንተ ፡ ለውጥ ፡ የሚሆን ፡ ምን ፡ እንደምትሰጧቸው ፡ ገልጠኸ ፡ ንገረኝ ። እነሱ ፡ የሚጐድላቸውን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እናንተም ፡ ልትሰጧቸው ፡ ትችላላችሁ ። ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ትሄ

ዳላችሁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ትምህርት ፡ እንዲሰጧችሁ ፡ ለማኞች ፡ ሆናችሁ ፡ ነው ፡ እዚያ ፡ የምትሄዱት ። እናንተ ፡ የምትሰጧቸ ው፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ማለት ፡ ነው ? ልትሰጧቸው ፡ የምትችሉት ፡ ዋጋው ፡ ሊገመት ፡ የማይችል ፡ አንድ ፡ ሀብት ፡ አላችሁ ፤ ፍልስፍናችሁን ፡ ስጧቸው ፤ ሃይማኖታችሁን ፡ ስጧቸው ። የፍጥረተ ፡ ዓለምን ፡ ታሪክ ፡ ተማሩ ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በማንኛውም ፡ ቦታ ፡ የምታገኙት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አሳብ ፡ ሁሉ ፡ ምንጩ ፡ ከህንድ ፡ አገር ፡ የመጣ ፡ ሆኖ ፡ ታገኙታላችሁ» ።

# የሥልጣኔ ፡ ደዌ ።

ኤመርሰን ፡ የተባለው ፡ ያሜሪካ ፡ ፈላስፋ ፡ የሰጠውን ፡ አሳብ ፡ የተከተልን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሰው ፡ በሁሉም ፡ በኩል ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ ሊፈጽም ፡ አይችልም ። ባንድ ፡ በኩል ፡ ሥራው ፡ የለማ ፡ ሲሆን ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ይበላሻል ። ባንድ ፡ በኩል ፡ ሲያገኝ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ያጐድላል ። በዚህ ፡ ምክንያትም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ የዛሬይቱ ፡ ሥልጣኔ ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ጒድለቶች ፡ እንደሚገኙባት ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ብቅል ፤ አሻሮና ፡ ጌሾ ፡ እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ ሲዋሐዱ ፡ ጠላ ፡ ተብለው ፡ ባንድ ፡ ስም ፡ እንደሚጠሩ ፡ ሁሉ ፡ የገንዘብ ፡ ፍቅር ፤ ማቴሪያሊስምና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ክሕደት ፡ እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ የምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ መርዞች ፡ የማይለያዩና ፡ የተደጋገፉ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የሥልጣኔ ፡ ደዌ ፡ ብለን ፡ ባንድ ፡ ስም ፡ ብንጠራቸው ፡ ቅር ፡ የሚያሰኝ ፡ አይሆንም ። የገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ የተባለው ፡ በንግድ ፡ ላይ ፡ ተመሥርቷል ። ምንጩም ፡ ኢንዱስትሪ ፡ (ፋብሪካ) ፡ ነው ። ማቴሪያሊስም ፡ ማለት ፡ ለምድራዊ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ተገዥ ፡ ሆኖ ፡ መገኘትና ፡ መስገብገብ ፡ በመንፈስ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ ሀብት ፡ መዘንጋት ፤ መካድም ፡ ነው ።

ሰው ፡ የገንዘብን ፡ ፍቅር ፡ ከሁሉ ፡ ነገር ፡ በላይ ፡ አድርጎ ፡ ከተመለከተ ፡ ከማቴሪያሊስም ፡ ሊያመልጥ ፡ አይችልም ። እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ ነገሮች ፡ የሃይማኖትን ፡ መቀዝቀዝ ፤ ወይም ፡ እግዚአብሔርን ፡ መካድ ፡ እንደሚያስከትሉ ፡ ግልጥ ፡ ሆኖ ፡ የሚታይ ፡ ነገር ፡ ነው ። ሰው ፡ በጣዖት ፡ እያመለከ ፡ ዐሠርቱ ፡ ቃላትን ፡ ሊጠብቅ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ይችላል ? ከሁለቱ ፡ አንዱን ፡ መምረጥ ፡ ይኖርበታል ። እንግዲህ ፡ የገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ ማለት ፡ ገንዘብን ፡ እንደ ፡ ጣዖት ፡ ማምለክ ፡ ነው ። የምዕራብ ፡ ሕዞቦች ፡ የሳይንስና ፡ የቴክኒክ ፡ ጥበብ ፡ ከተገለጠላቸው ፡ ጀምሮ ፡ አዲስ ፡ የሥልጣኔ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ተከፈተላቸው ፡ ታውቋል ። በኤሌክትሪሲቴ ፡ ኀይል ፡ የሚንቀሳቀሱት ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ ለሰው ፡ ኑሮ ፡ የሚጠቅሙትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ እየሠሩ ፡ ሲሰጡ ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ ታይቶና ፡ ተሰምቶ ፡ የማይታወቅ ፡ ሀብት ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ መጕረፍ ፡ ጀመረ ። ኢንዱስትሪዎች ፡ የሚተፉትን ፡ ሸቀጥ ፡ ለመላው ፡ የዓለም ፡ ሕዝብ ፡ ለመናኘት ፡ መርከቦችን ፡ በብዛት ፡ መሥራት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነ ። በነፋስ ፡ ይሄድ ፡ የነበረውም ፡ መርከብ ፡ ቀርቶ ፡ በላቦት ፡ ኀይል ፤ ቀጥሎ ፡ በኤሌክትሪሲቴ ፡

ኀይል ፡ የሚገሠግሡ ፡ መርከቦች ፡ ተሠሩ ። በዚህ ፡ ላይ ፡ ጠበንጃ ፤ መትረየስና ፡ መድፍ ፡ የሚባሉ ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ ተከትለው ፡ ወጡ ። መጥረቢያ ፡ የጫካን ፡ ዕንጨት ፡ እየቈረጠ ፡ እንደሚመነጥር ፡ ሁሉ ፡ መርከብ ፡ የባሕሩን ፡ መንገድ ፡ እየሠነጠቀ ፡ ሲሄድ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ዕንቅፋት ፡ ደግሞ ፡ ጠበንጃ ፡ መትረየስና ፡ መድፍ ፡ እየመነጠሩ ፡ ፋብሪካ ፡ ላፈሰሰው ፡ የሸቀጥ ፡ ጐርፍ ፡ መንገዱን ፡ ከፈቱለት ። ሸቀጥና ፡ እነዚህ ፡ የጠራናቸው ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ ወንድማማቾች ፡ ናቸው ። ሁሉም ፡ ኢንዱስትሪ ፡ የወለዳቸው ፡ ልጆች ፡ ናቸውና ። ወንድማማቾች ፡ እንደ ፡ መሆናቸው ፡ መጠን ፡ ተደጋጋፊ ፡ ሆኑ ። ሸቀጥ ፡ ማለት ፡ ገንዘብ ፤ ገንዘብ ፡ ማለት ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፤ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ማለት ፡ ሸቀጥ ፡ ሆነው ፡ ስለ ፡ ተገኙ ፡ መልካቸው ፡ እንደሚያሳስት ፡ እንደ ፡ ሦስት ፡ መንታ ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ የፋብሪካ ፡ ልጆች ፡ እየተቀላቀሉ ፡ ትርጉማቸው ፡ አስቸጋሪ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ ። በየዓለሙ ፡ ክፍል ፡ በተለየም ፡ በእስያና ፡ ባፍሪቃ ፡ የሚኖሩ ፡ ሕዝቦች ፡ ጧት ፡ ከመኝታቸው ፡ ሲነሡ ፡ ጠበንጃ ፤ መድፍና ፡ መትረየስ ፡ በመርከብ ፡ ተጭነው ፡ ድንገት ፡ ደርሰው ፡ የጥይት ፡ በረዶ ፡ ያወርዱባቸው ፡ ጀመር ። ምን ፡ አጠፋን ፡ ሲሉ ፡ ሸቀጥ ፡ እንድትገዙ ፡ ነው ፡ አሏቸው ። ሸቀጥ ፡ እንድንገዛ ፡ የምንገደድበት ፡ ምክንያቱ ፡ ምንድነው ? ሲሉ ፡ ሸቀጡ ፡ ገንዘብ ፡ ስለሚያወጣልን ፤ ገንዘቡም ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ስለሚሆን ፤ የጦር ፡ መሣሪያውም ፡ የመንግሥታችን ፡ ክብር ፤ ግርማና ፡ ሞገስ ፡ ታላቅነትም ፡ በመሆኑ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መለሱላቸው ። እነዚህ ፡ ሕዝቦች ፡ የዚህ ፡ ንግግር ፡ ትርጉሙ ፡ እስቲገለጥላቸው ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ወሰደባቸው ። እንሆ ፡ ባጭሩ ፡ የዘመናችን ፡ ቴአትር ፡ ወይም ፡ ድራማ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ይህ ፡ በምዕራባውያን ፡ ሕዝቦችና ፡ በቀሩት ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ የተፈጠረ ፡ ሁኔታ ፡ ሲሆን ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ከተፈጠረ ፡ በኋላ ፡ ራሳቸው ፡ ያውሮፖ ፡ ሕዝቦች ፡ ባገራቸው ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ እንደ ፡ ተወለደ ፡ እናስተውል ። የኢንዱስትሪ ፡ ጥበብ ፡ ከመጣ ፡ በኋላ ፡ ያውሮፓ ፡ ሕዝቦች ፡ አኗኗር ፡ ፈጽሞ ፡ ተለወጠ ። በየኢንዱስትሪው ፡ ውስጥ ፡ የሚሠሩ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ማግኘት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፡ የባላገሩ ፡ ሕዝብ ፡ እርሻውን ፡ እየተወ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ተሰበሰበ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የግብርናና ፡ የከብት ፡ ማርባት ፡ ሥራ ፡ እየተቀነሰና ፡ እየቀረ ፡ ሄደ ። ስለዚህ ፡ እነዚህ ፡ አገሮች ፡ ወይም ፡ ከፋብሪካ ፡ የመጣውን ፡ ሸቀጥ ፡ በውድ ፡ በመሸጥ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አትርፈው ፡ ምግብ ፡ በርካሽ ፡ እየገዙ ፡ ወይም ፡ የእርሻን ፡ ሥራ ፡ በመኪና ፡ እያረሱ ፡ በጥቂት ፡ ድካም ፡ ብዙ ፡ ሰብሎች ፡ በመሰብሰባቸው ፡ ሕዝባቸውን ፡ ይመግቡት ፡ ጀመር ። ነገር ፡ ግን ፡ በከተማቸው ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ በመከማቸቱ ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጉዳት ፡ አመጣባቸው ። ብዙ ፡ ፍሬ ፡ ተከማችቶ ፡ ሲቀመጥ ፡ እንደሚበሰብስ ፡ ሁሉ ፡ ሕዝቦችም ፡ እንደዚሁ ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ሲከማቹ ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጥፎ ፡ ጠባይ ፡ ያመጣሉ ። በጥንት ፡ ዘመን ፡ ሮማ ፡ የዓለም ፡ ገዥ ፡ ሆና ፡ የምዕራቡንና ፡ የምሥራቁን ፡ ክፍል ፡ ሕዝቦች ፡ በከተማዋ ፡ ውስጥ ፡ እየተሰበሰቡ ፡ እንዲኖሩ ፡ ባደረገች ፡ ጊዜ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሃይማኖቶችና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ባህሎች ፡ ያላቸው ፡ እነዚህ ፡ ሕዝቦች ፡ አንድነት ፡ እየተከማቹ ፡ ሲኖሩ ፤ የሕዝቧ ፡ ጠባይ ፡ እየተበላሸ ፡ ሄደ ። ከውጭ ፡ የመጣ ፡ የባዕድ ፡ ሃይማኖትና ፡ የባዕድ ፡ ዐመል ፡ በሕዝቡ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ሲስፋፋ ፡ እስከ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ደረሰ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ለምሳሌ ፡ ሄሊዎጋባል ፡ የተባለው ፡ ቄሳር ፡ ከሶርያ ፡ የመጣውን ፡ በዓል ፡ የተባለውን ፡ ጣዖት ፡ የሮማ ፡ መንግሥት ፡ ኦፊሲዬል ፡ ሃይማኖት ፡ እንዲሆንና ፡ እንዲሰገድለት ፡ አድርጎ ፡ እሱም ፡ ስሙን ፡ ለውጦ ፡ ሄሊዎጋባል ፡ ተባለ ። ይኸውም ፡ የበዓል ፡ አገልጋይ ፡ ወይም ፡ ካህን ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህ ፡ በሃይማኖት ፡ በኩል ፡ የተደረገ ፡ ሲሆን ፡ በጠባይ ፡ በኩልም ፡ እንደዚሁ ፡ ሮማውያን ፡ ከነቄሳሮቻቸው ፡ እየረከሱ ፡ ሄዱ ። እንደዚሁ ፡ ሁሉ ፡ ባሁን ፡ ዘመን ፡ በሠለጠኑት ፡ አገሮች ፡ የተከማቸው ፡ ሕዝብ ፡ ባሕርዩ ፡ ብዙ ፡ መጥፎ ፡ ግብር ፡ እየወረሰ ፡ መበላሸቱ ፡ ታውቋል ።



በግራ ፡ ቢስ ፡ አሳብ ፡ የተዋጠ ፤ በግል ፡ ክብር ፡ የሚታበይ ፡ በመሆኑ ፡ የታወቀው ፡ እንደዚሁም ፡ የሚያስፈራ ፡ አሳብ ፡ ጠባብነት ፡ ያደረበት ፡ ጐቢኖ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ልዩ ፡ ጠባይ ፡ የያዘ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኝ ፡ አንድ ፡ የጻፈው ፡ ቃል ፡ አለ ። ይህም ፡ ቃል ፡ ደራሲው ፡ ስለ ፡ ዛሬይቱ ፡ ሥልጣኔ ፡ አሥጊ ፡ ዕድል ፡ የነበረው ፡ አስተያየት ፡ መጥፎ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ የልቡን ፡ ትካዜ ፡ ይገልጥልናል ። ቃሉም ፡ የሚከተለው ፡ ነው ፤

Notre civilisation est comparable à ces îlots temporaires poussés au-dessus des mers par la puissance des volcans sous-marins. Livrés à l'action destructrice des courants et abandonnés à la force qui les avait d'abord soutenus ils fléchissent un jour et vont engloutir leurs débris dans les domaines des flots conquérants. Triste fin, et que bien des races généreuses ont dû subir avant nous. Il n' y a pas à détourner le mal. Il est inévitable. La sagesse ne peut que prévoir, et pas d'avantage. La prudence la plus consommée n'est pas capable de contrarier un seul instant les lois immuables du monde.'

«የእኛ ፡ ሥልጣኔ ፡ በውቅያኖስ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ የእሳተ ፡ ገሞራዎች ፡ ኀይል ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ እየገፋ ፡ ከባሕር ፡ ላይ ፡ ያንሳፈፋቸውን ፡ ጊዜያዊ ፡ የሆኑ ፡ ደሴቶችን ፡ ትመስላለች ። አጥፊ ፡ ከሆነው ፡ ከማዕበሎች ፡ ኀልበት ፡ ስለማያመልጡ ፡ ቀድሞ ፡ እንዲፈጠሩ ፡ አድርጓቸው ፡ ከነበረው ፡ ጉልበት ፡ የሚያድናቸው ፡ ነገር ፡ ስለሌለ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ተሸንፈው ፡ ይጠፋሉ ። በጠፉም ፡ ጊዜ ፡ ከእነሱ ፡ የተረፈው ፡ ፍራሽ ፡ ድል ፡ አድራጊ ፡ በሆነው ፡ የውሃ ፡ ማዕበል ፡ የተዋጠ ፤ የተጥለቀለቀ ፡ ሆኖ ፡ ይቀራል ። ይህም ፡ ከኛ ፡ በፊት ፡ በነበሩ ፡ ለጋሶች ፡ በሆኑ ፡ በብዙ ፡ የሰው ፡ ዘሮች ፡ ላይ ፡ የደረሰባቸው ፡ የሚያሳዝን ፡ ፍጻሜ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ ለማምለጥ ፡ የሚቻል ፡ አይዶለም ። አስተዋይነት ፡ ነገሩ ፡ እንደሚመጣ ፡ አስቀድማ ፡ ከማወቅ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ልታደርገው ፡ የምትችለው ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለም ። እጅግ ፡ ብልኅ ፡ የሆነችው ፡ ጠንቃቃነትም ፡ ሊለወጡ ፡ የማይችሉትን ፡ የዓለም ፡ ሕጎች ፡ ላንዲት ፡ ጊዜ ፡ እንኳ ፡ ተቃውማ ፡ ልታግዳቸው ፡ ዘንድ ፡ ከቶ ፡ ምንም ፡ ዐቅም ፡ የላትም» ።

ለምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ አሥጊ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘው ፡ አደጋ ፡ ጕቢኖ ፡ ባሰበበት ፡ በኩል ፡ ሳይሆን ፡ ከሌሎች ፡ ምንጮች ፡ ሊመጣ ፡ ይችላል ።

የኢንዱስትሪ ፡ ባለቤቶች ፡ የሆኑት ፡ ደግሞ ፡ ከሁሉም ፡ የባሰ ፡ ነገር ፡ ፈጠሩ ። ወሰን ፡ የሌለው ፤ ጠገብኩ ፡ ማለት ፡ የማያውቅ ፡ የገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ አደረባቸው ። በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ የሚፈልገው ፡ ለማጌጥ ፤ በምቾት ፡ ለመኖር ፡ ጥሩ ፡ ለመልበስ ፤ ጥሩ ፡ ለመብላትና ፡ ጥሩ ፡ ለመጠጣት ፡ ነበር ። ኢንዱስትሪ ፡ ከተፈጠረ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ባለቤቶች ፡ የሚመኙት ፡ ብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ሚሊያርድ ፡ አለው ፡ ለመባል ፡ ሆነ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ሀብታቸው ፡ ምንም ፡ ያኽል ፡ ከፍ ፡ ቢል ፡ ጠገብን ፡ በቃን ፡ አይሉም ። ከኢንዱስትሪያቸው ፡ የሚወጣውን ፡ ሸቀጥ ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ እየወሰዱ ፡ በመሸጥ ፡ እስከ ፡ የሌለውን ፡ ብልጽግና ፡ ያባርሩ ፡ ጀመር ። ገንዘብና ፡ የጦር ፡ ኀይል ፡ የማይለያዩ ፡ ሆነው ፡ ስለ ፡ ተገኙ ፤ እያንዳንዱ ፡ መንግሥት ፡ ዜጎቹ ፡ የሆኑትን ፡ ነጋዴዎች ፡ ይደግፍ ፡ ጀመር ። ይህ ፡ በመንግሥትና ፡ በነጋዴ ፡ መካከል ፡ የተፈጠረ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በመንግሥታት ፡ መካከል ፡ የንግድ ፡ ውድድር ፡ እንዲወለድ ፡ አደረገ ። በየዓለሙና ፡ በየአህጉሩ ፡ ሸቀጣቸውን ፡ ለመውሰድ ፡ እንዲመቻቸው ፡ የንግድ ፡ ጣቢያዎች ፡ ያቋቁሙ ፡ ጀመር ። እነዚሁም ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ ተብለው ፡ ተጠሩ ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የንግድ ፡ ዘመን ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመ ፡ ጊዜ ፡ መጣ ። አንዳንዶቹም ፡ ደራስያን ፡ «የትርፍና ፡ የኪሳራ ፡ ዘመን» ፡ ብለውታል ። ስለዚህ ፡ የንግድ ፡ መንፈስ ፡ ዐላማው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ባጭር ፡ ቃል ፡ ተጠቀለለ ። «ብዙ ፡



ገንዘብ ፡ ወደ ፡ አገር ፡ እንዲገባ ፡ ማድረግ ፤ ወደ ፡ ውጭ ፡ የሚወጣውን ፡ ገንዘብ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ መቀነስ ፤ ለዚህም ፡ መድኀኒቱ ፡ ብዙ ፡ ሸቀጥ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ መሸጥ ፤ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ከውጭ ፡ የሚገዛው ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ጥቂት ፡ እንዲሆን ፡ መጣጣር ፡ ነው» ። ካፒታሊስቶች ፡ ወይም ፡ ቡርገፑዋ ፡ ተብለው ፡ የሚጠሩት ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ባለቤቶች ፡ ከመንግሥታቸው ፡ ጋራ ፡ ተባብረው ፡ ይህንን ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ ለሠራተኞቻቸው ፡ እየሰጡ ፡ የገንዘብ ፡ ኀልበታቸውን ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ዘረጉት ። እነሱም ፡ ባገራቸው ፡ ውስጥ ፡ የሕዝቡንና ፡ የመንግሥቱን ፡ ኤኮኖሚ ፡ በእጃቸው ፡ ስለጨበጡት ፡ ላገሪቱ ፡ ሕይወት ፡ ባለቤቶች ፡ ሆኑ ። ያለገንዘብ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ለማድረግ ፡ የማይቻልበት ፡ ዘመን ፡ መጣ ። አንድ ፡ ብልኅ ፡ ሰው ፡ በሳይንስ ፡ ወይም ፡ በቴክኒክ ፡ አዲስ ፡ ጥበብ ፡ ቢፈልስፍ ፡ አንድ ፡ ሐኪም ፡ አዲስ ፡ መድኀኒት ፡ ቢያገኝ ፤ አንድ ፡ ደራሲ ፡ መጽሐፍ ፡ ቢጽፍ ፡ አንድ ፡ ሙዚቀኛ ፡ ባለሙያ ፡ ቢሆን ፤ ማንኛውም ፡ ዐይነት ፡ ጥበብ ፡ ቢወለድ ፡ ባለገንዘብ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ካልደገፉት ፤ ካላበረታቱት ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፤ ሊያድግና ፡ የሚገባውን ፡ ደረጃ ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልም ። የኢንዱስትሪ ፡ ባለቤቶች ፡ የሆኑት ፡ እነዚህ ፡ ሀብታሞች ፡ አሳባቸውን ፡ ለመፈጸምና ፡ የፈቀዱትን ፡ ለማድረግ ፡ የሚችሉበት ፡ መሣሪያ ፡ ጋዜጣ ፡ ነው ። የዓለም ፡ ጋዜጦች ፡ ሁሉ ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ በእነሱ ፡ የተገዙ ፡ ናቸው ። እነሱ ፡ የሚቃወሙትን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በጋዜጣ ፡ እንዲደበደብ ፡ ሲያደርጉት ፡ በዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ኅሊና ፡ ዘንድ ፡ የተነቀፈና ፡ ነውር ፡ የለበሰ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። የሚደግፉትን ፡ ነገር ፡ ደግሞ ፡ መጥፎም ፡ ቢሆን ፡ በዚሁ ፡ መጠን ፡ የተወደደና ፡ የተከበረ ፡ ያደርጉታል ። ሙሶሊኒ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመውረር ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ኀጢአቷ ፡ ብዙ ፡ ሆኖ ፡ እንዲታይና ፡ በዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ኅሊና ፡ ፊት ፡ እንዲፈረድባት ፡ ለማድረግ ፡ የዓለም ፡ ጋዜጦችን ፡ በገንዘብ ፡ እየገዛ ፡ በሰፊው ፡ ይህን ፡ መሣሪያ ፡ ሠርቶበታል ። ጋንዲ ፡ ስለ ፡ ጋዜጠኞች ፡ ሲናገር ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ።

«ላንድ ፡ የእንግሊዝ ፡ ተወላጅ ፡ የሱ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጋዜጣ ፡ ነው ። ከጋዜጣ ፡ የሚያገኘው ፡ አሳብ ፡ ሐሰት ፡ ነው ። ጋዜጦች ፡ አንዱን ፡ ነገር ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ ይተረጉሙታል ። አንድ ፡ ሰው ፡ ባንድ ፡ ጋዜጣ ፡ ወስላታ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ሲሰደብ ፡ በሌላ ፡ ጋዜጣ ፡ ደግሞ ፡ ለሌሎች ፡ ምሳሌ ፡ ሊሆን ፡ የሚገባው ፡ ትክክለኛ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይመሰገናል ። እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ጋዜጦች ፡ ወሬ ፡ የሚያቀበሉት ፡ ሕዝብ ፡ የመንፈሱ ፡ ሁኔታ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ? » በግልጥ ፡ ሳይሆን ፡ በሽፍን ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥልጣኔ ፡ የጨበጡት ፡ እነዚህ ፡ «ቡርገዞዋ»

የተባሉት ፡ ሀብታሞች ፡ በመላው ፡ ሕዝብ ፡ ሕይወት ፡ ላይ ፡ ኀይላቸው ፡ እያንዣበበ ፡ ሁሉን ፡ የሚቈጣጠርና ፡ በሁሉ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የተሰወረ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ የጨቋኝነቱን ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ። አስተዋዮች ፡ በሆኑ ፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ የተቃዋሚነትን ፡ መንፈስ ፡ እየቀሰቀሰ ፡ ይህን ፡ ሰይጣናዊ ፡ የሆነ ፡ ቀንበር ፡ ለመነቅነቅና ፡ ሰብሮ ፡ ለመጣል ፡ እንዲነግሡ ፡ አደረጋቸው ። መንግሥታትም ፡ ይህ ፡ አደጋ ፡ የሚያሠጋ ፡ ሆኖ ፡ ስላገኙት ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ይህን ፡ ሁኔታ ፡ ለማሻሻል ፡ ሞክረዋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ፍቱን ፡ የሆነ ፡ መድኀኒት ፡ አልተገኘለትም ። ሉሲያን ፡ ዱፕሌሲ ፡ የተባለው ፡ ደራሲ ፡ ቡርዡዋ ፡ ስለሚባሉት ፡ ሰዎች ፡ ሲናገር ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ጽፏል ፤ «ቡርዡዋ ፡ የሚስገበገበው ፡ ለክብር ፤ ለደም ፤ በሰፊ ፡ ግዛት ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ለማግኘት ፡ አይደለም ። ቡርዡዋ ፡ የሚመኘው ፡ ገንዘብ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ገንዘብ ፡ ለሱ ፡ አልፋና ፡ ዖሜጋ ፡ ነው» ። ዛሬ ፡ ለዓለም ፡ መቅሠፍት ፡ ሆኖ ፡ የተገኘው ፡ ኮሙኒስም ፡ የተፈጠረው ፡ በእነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ስናስበው ፡ መዘዛቸው ፡ የቱን ፡ ያኽል ፡ የከፋ ፡ መሆኑን ፡ ይገልጥልናል ። የገንዘብ ፡ ኀይል ፡ በመንግሥታትም ፡ ሆነ ፡ በተራው ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ የፍጡሮችን ፡ ሕይወት ፡ የሚያንቀሳቅስ ፡ ዋና ፡ መሣሪያ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ። ቧሎ ፡ የተባለው ፡ የፈረንሳይ ፡ ደራሲ ፤

L'Argent, l'argent, dit-on, sans lui tout est stérile,
La vertu sans argent, n'est qu'un meuble inutile.

«ገንዘብ ፡ ገንዘብ ፤ ያለእሱ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ መካን ፡ ነው ፡ ይባላል ፤ መልካም ፡ ምግባርም ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ የማትጠቅም ፡ ዕቃ ፡ ነች» ። ሲል ፡ ከሁለት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ የተናገረው ፡ የማይረሳ ፡ ቃል ፡ በሙሉ ፡ ከተፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ ላይ ፡ እንሆ ፡ ደርሰናል ። ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ያለገንዘብ ፡ በዛሬ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም ፤ የገንዘብ ፡ ኀይል ፡ ማለት ፡ ምንድነው ? ይህ ፡ በእነሱ ፡ ቃል ፡ (Ploutocratie) (ፕሉቶክራሲ) ፡ የሚባለው ፡ ነው ። ትርጉሙም ፡ የገንዘብ ፡ ጉልበት ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ ያለገንዘብ ፡ ምንም ፡ ለማድረግ ፡ አይቻልም ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ዋጋው ፡ የሚገመተው ፡ በገንዘብ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ። የፕሉቶክራሲን ፡ ትርጉም ፡ ሲሰጠን ፡ ረናን ፡ (Renan) የተባለው ፡ የፈረንሳይ ፡ ሊቅ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፤

«J'appelle ploutocratie un état de société où la richesse est le nerf principal de toutes les choses, où l'on ne peut rien faire sans être riche, où l'objet principal de l'ambition est de devenir riche, où la capacité et la moralité s'évaluent généralement (et avec plus ou moins de justesse) par la fortune.»



«ፕሉቶክራሲ ፡ ብዬ ፡ የምጠራው ፡ በሰዎች ፡ መካከል ፡ ለማንኛዎቹም ፡ ነገሮች ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ዋና ፡ የደም ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠርበትን ፡ ሁኔታ ፤ ባለጸጋ ፡ ካልሆኑ ፡ ምንም ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ የማይቻልበትን ፤ ሀብታም ፡ መሆን ፡ የምኞት ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ ሆኖ ፡ የሚታይበትን ፡ ችሎታና ፡ ግብረ ፡ ገብነት ፡ (ሞላ ፡ ከጐደል) ፡ በሀብት ፡ የሚገመቱበትን ፡ ነው» ።

ፔጊ ፡ የተባለውም ፡ የፈረንሳይ ፡ ደራሲ ፡ የሚቀጥለውን ፡ ቃል ፡ ጽፏል ፤

"Tous les autres mondes ... ont été des mondes de quelque spiritualité. Le monde moderne, seul étant le monde de l'argent, est le monde d'une totale et absolue matérialité."

«ሌሎቹ ፡ ዓለሞች ፡ ሁሉ ፡ ያንዳንድ ፡ መንፈሳዊነት ፡ ዓለሞች ፡ ነበሩ ። ያሁኑ ፡ ዓለም ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ የገንዘብ ፡ ዓለም ፡ በመሆኑ ፡ በሙሉና ፡ በፍጹም ፡ የግዙፍ ፡ አካል ፡ (matérialité) ዓለም ፡ ነው» ። እነሆ ፡ አንድ ፡ መንግሥት ፡ እንኳ ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ገንዘብ ፡ ከሌለው ፡ እጅና ፡ እግሩን ፡ ታስሮ ፡ ይቀመጣል ። በዘመናችን ፡ ማንኛውም ፡ መንግሥት ፡ ያለበት ፡ ተግባር ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንመልከት ። ሕዝቡን ፡ በሞላ ፡ ለማስተማር ፡ ሲፈልግ ፡ የትምህርት ፡ ቤት ፡ ሕንጻ ፡ አሠርቶ ፡ መምህራን ፡ ቀጥሮ ፤ መጻሕፍት ፡ ገዝቶ ፤ ሌላም ፡ አስፈላጊውን ፡ ድርጅት ፡ ማከናወን ፤ ወንድ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ በነፍስ ፡ ወከፍ ፡ የጦር ፡ ትምህርት ፡ በግድ ፡ እንዲማር ፡ ማድረግ ፤ በመንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ አውራጃዎች ፡ እንዲገናኙ ፡ ለማድረግ ፡ ባቡርና ፡ የመኪና ፡ መንገድ ፡ ማሠራት ፤ ኢንዱስትሪዎች ፡ ማቋቋም ፤ የሕዝቡ ፡ ጤና ፡ የሚጠበቅበትን ፡ ሥራ ፡ ማደራጀት ፡ የስልክና ፡ የራዲዮ ፡ ጣቢያ ፡ ማቋቋም ፤ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ፋብሪካ ፡ መፍጠር ፤ እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ ተግባሮችና ፡ እነሱንም ፡ የመሰሉትን ፡ ለማደራጀት ፡ ገንዘብ ፡ ያስፈልገዋል ። ይኸውም ፡ በብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ ሳይሆን ፡ በብዙ ፡ ሚሊያርድ ፡ የሚቈጠር ፡ ካልሆነ ፡ አይበቃውም ። ኀይለኞች ፡ የሆኑ ፡ መንግሥታት ፡ ደግሞ ፡ እንኳንስ ፡ ሊረዱት ፡ ከእሱ ፡ አገር ፡ የሚገኘውን ፡ ሀብት ፡ ዋጋውን ፡ ሰብረው ፡ በርካሽ ፡ እየገዙ ፡ የእነሱን ፡ ሸቀጥ ፡ በውድ ፡ በመሸጥ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ከሳራ ፡ ይገፋፉታል ። ቤንዚን ፡ ባገራቸው ፡ የተገኘ ፡ አገሮች ፡ ግን ፡ በጣም ፡ የተፈሩና ፡ የተከበሩ ፡ ሆነው ፡ ይቈጠራሉ ። ለምሳሌ ፤ አሁን ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ያልሠለጠነች ፡ እንዲያውም ፡ የሥልጣኔ ፡ ተቃዋሚ ፡ ሆና ፡ ትቈጠር ፡ የነበረችው ፡ የዐረቢ ፡ ሳውዲ ፡ አገር ፡ ቤንዚን ፡ በመሬቷ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፡ ይህንኑ ፡ እያወጣች ፡ ለመጠቀም ፡ ካሜሪካ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ተስማማች ፡ ዛሬ ፡ ይህች ፡ አገር ፡

ከሠለጠኑትና ፡ ብዙ ፡ መልካም ፡ ምግባር ፡ ካላቸው ፡ አገሮች ፡ በላይ ፡
ሆና ፡ ትቈጠራለች ። ንጉሥዋም ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ አገር ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ የተ
ባበሩት ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥታት ፡ ፕሬዚዴንት ፡ ለሌሎች ፡ ነገሥታት ፡
የማያደርገውን ፡ እስከ ፡ አኤሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ ድረስ ፡ ሄዶ ፡ ተቀብሎ
ታል ። ማነኛቹም ፡ የዓለም ፡ ኀያላን ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ በገንዘብና ፡ በሀብት ፡
ፊት ፡ ራሳቸውን ፡ ዝቅ ፡ ያደርጋሉ ። በዛሬ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በሠለጠ
ኑት ፡ አገሮች ፡ ሲሄድ ፡ በቂ ፡ ገንዘብ ፡ ኖሮት ፡ ብዙ ፡ ወጪ ፡ ያደረገ ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ በጣም ፡ ይከበራል ። ገንዘብ ፡ የሌለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡
ብዙ ፡ ወጪ ፡ ለማድረግ ፡ የማይችል ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ የሚደረግለት ፡ አስተ
ያየት ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ይሆናል ። እንደዚሁም ፡ አንድ ፡
መንግሥት ፡ ከእነዚህ ፡ ከሠለጠኑት ፡ አገሮች ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ሲያደርግ
ባመት ፡ ባመቱ ፡ የምን ፡ ያኽል ፡ ገንዘብ ፡ ሸቀጥ ፡ ለመግዛት ፡ የሚችል ፡
ሆኖ ፡ በሚገኝበት ፡ መጠን ፡ የወዳጅነቱ ፡ ጥቅም ፡ ከፍ ፡ ወይም ፡ ዝቅ ፡
ተደርጎ ፡ ይገመታል ። ብዙ ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ የሚያነሣ ፡ ከሆነ ፡ ጠቃ
ሚና ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ወዳጅ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ። የገዥነት ፡ ዐቅሙ ፡
ደካማ ፡ ከሆነ ፡ የማይረባ ፡ የማይጠቅም ፡ ወዳጅ ፡ ሆኖ ፡ በመታየት ፡ ይሸ
ሹታል ። ይህም ፡ የመንግሥታት ፡ ወዳጅነት ፡ የሚመጠነው ፡ በንግድ ፡
ዋጋ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ። ገንዘብ ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ በሆነበት ፡ ባሁኑ ፡ ዘ
መን ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፡ ማንኛውንም ፡ ዐመፅና ፡ ማንኛው
ንም ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ አይመለስም ። ሴትም ፡ ሆነች ፡ ወንድ ፡
ወራዳ ፡ ሥራ ፡ ይሠራሉ ።

የገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ የተባለው ፡ መርዝ ፡ ጠባዩ ፡ ይህ ፡ ሲሆን ፡ አሁን ፡
ደግሞ ፡ የሁለተኛውን ፡ መርዝ ፡ ማለት ፡ የማቴሪያሊስምን ፡ ጕዳይ ፡ ባሕ
ርዩ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንመልከት ። የሳይንስ ፡ ጥበብ ፡ ለሰዎች ፡ እየተ
ገለጠ ፡ ሲሄድ ፡ ሰው ፡ ከዐቅሙ ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ዕውቀት ፡ ባንጐሉ ፡
አደረበት ። ሊቃውንትም ፡ የሥነ ፡ ፍጥረትን ፡ ጥበብ ፡ በመመርመር ፡
ብቻ ፡ አሳባቸው ፡ ተጠመደ ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ የምናየው ፡ ነገር ፡
አብዛኛው ፡ ምስጢሩ ፡ ለኛ ፡ ለሰዎች ፡ የተሰወረ ፡ ነው ። ይህንንም ፡
በጣም ፡ ሰፊ ፡ የሆነውን ፡ የተሸፈነ ፡ ነገር ፡ እናውቃለን ፡ ብለን ፡ አንመ
ኝም ። ምክንያቱም ፡ ካቅማችን ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለምንረዳው ፡
ነው ። የሳይንስ ፡ ጥበብ ፡ ትልቅ ፡ እርምጃ ፡ ካደረገችበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡
ማለት ፡ ከሁለት ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ ወዲህ ፡ የሳይንስ ፡ ሊቃውንት ፡
ሰው ፡ አሳቡንና ፡ ድካሙን ፡ ሳይንስን ፡ በመመርመር ፡ ላይ ፡ ቢያው
ለው ፡ የተሸፈነውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለማወቅ ፡ ይችላል ፡ የሚል ፡ እምነት ፡
አደረባቸው ። እንደዚሁም ፡ በሳይንስ ፡ መርምረን ፡ የተረዳነውን ፡ በመ



ጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ተጽፎ ፡ ከሚገኘው ፡ ጋራ ፡ ስናስተያየው ፡ አይገናኝም ።
ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ራሱ ፡ እየመረመረ ፡ ማስረጃ ፡ ሲያ
ገኝለት ፡ ብቻ ፡ ሊቀበለው ፡ ይገባል ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ በነ
ቢያትና ፡ በቀሩትም ፡ የሃይማኖት ፡ መሪዎች ፡ አማካይነት ፡ ገለጠለት ፡
ወይም ፡ አስተማረው ፡ የሚባለውን ፡ (révélation) መቀበል ፡ አይገባንም ፡
የሚሉ ፡ ሊቃውንት ፡ ተገኙ ። ግማሾቹ ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ መኖሩ ፡
አይካድም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የአስትሮኖሚ ፡ ዕውቀት ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡
የተስፋፋ ፡ ሆኖ ፡ የቀድሞዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ያልደረሱበትን ፡ ዕውቀት ፡ ዛሬ ፡
ስለ ፡ ደረስንበት ፡ እኛ ፡ ሰዎች ፡ የምንኖርባት ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ ቅንጣት ፡
የምትቈጠር ፡ ታናሽ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ሆነች ፤ እግዚአብሔር ፡ ለዚች ፡ ታ
ናሽ ፡ ነገር ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ አይጨነቅበትም ፡ የሰዎችንም ፡ ግብር ፡
አይቈጣጠርም ፡ የሚሉ ፡ ናቸው ። ሌሎቹም ፡ ደግሞ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
ላይ ፡ ዘለዓለማዊነት ፡ ያለው ፡ ግዙፍ ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ ነው ። ግዙፍ ፡
አካል ፡ ማለት ፡ ከዋክብትና ፡ ፕላኔቶች ፡ በላያቸውም ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ እ
ንደ ፡ ዐፈር ፤ ድንጋይ ፤ ብረታብረትና ፡ ማዕድን ፡ የመሰለው ፡ ነው ። ግ
ዙፍ ፡ አካሎች ፡ የተባሉት ፡ እንደዬ ፡ በእሳት ፡ እየቀለጡ ፤ አንደዬም ፡ ብር
ሃን ፡ እየሆኑ ፤ አንደዬም ፡ እየቀዘቀዙ ፤ አንደዬም ፡ እየጋሉ ፤ አንደዬም ፡
እየፈረሱ ፡ ተመልሰው ፡ ደግሞ ፡ እየተቋቋሙ ፡ ጨርሶ ፡ መጥፋት ፡ ሳይ
ደርስባቸው ፡ ሲለዋወጡ ፡ ዘለዓለም ፡ ይኖራሉ ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ም
ንም ፡ ነገር ፡ አይፈጠርም ። ምንም ፡ ነገር ፡ ደግሞ ፡ ጨርሶ ፡ አይጠፋም ።
ሰውና ፡ በእስትንፋስ ፡ የሚኖሩ ፡ ፍጡሮች ፡ ግን ፡ አላፊ ፡ የሆኑ ፡ በድን
ገት ፡ እንዳጋጣሚ ፡ የተገኙና ፡ በቶሎ ፡ የሚጠፉ ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡
ዘለዓለማዊነት ፡ ያለው ፡ ግዙፍ ፡ አካል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ዘለዓለማዊ
ነት ፡ ያለው ፡ ፍጡር ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፡ ይላሉ ። ያም ፡ ሆነ ፡ ያ ፡ እነ
ዚህ ፡ አሳቦች ፡ ሁሉም ፡ የሃይማኖትን ፡ ሕንጻ ፡ የሚያፈርሱና ፡ ማቴሪያ
ሊስምን ፡ የሚደግፉ ፡ ናቸው ። የሁለቱን ፡ መርዞች ፡ ጠባይ ፡ ከተመለከትን
በኋላ ፡ ወደ ፡ ሦስተኛው ፡ ጕዳይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ክሕደት ፡ ወደ ፡ ተባ
ለው ፡ አልፈን ፡ እንመልከተው ። ሰው ፡ አንደኛ ፡ በገንዘብ ፡ ፍቅር ፡
ከተሸነፈ ፤ ሁለተኛ ፡ ሰው ፡ በሥነ ፡ ፍጥረቱ ፡ ብቱርና ፡ የተሰጠው ፡ መሆ
ኑን ፡ ከካደ ፡ ወይም ፡ ከተጠራጠረ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔርን ፡
መኖር ፡ ጨርሶ ፡ ቢክድ ፡ ምን ፡ ያስደንቃል ? ስለዚህ ፡ በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡
የተገኙት ፡ ከሀድያን ፡ የሆኑ ፡ ሊቃውንት ፡ ያለፍርሀትና ፡ ያለ ፡ ማመን
ታት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መኖር ፡ ጨርሰው ፡ ክደዋል ። ይህንኑም ፡ ወደ
ፊት ፡ ባሉት ፡ ምዕራፎች ፡ እንደርስበታለን ።

# የከተማ ፡ ሕዝብ ፡ (ዴሞክራሲ) ።

ሶሲዮሎዢን ፡ (የሕዝብ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ) ፡ ትምህርትን ፡ የሚከታ
ተሉ ፡ ሊቃውንት ፡ የሥልጣኔ ፡ መሠረት ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ መሆኑን ፡
ያስረዱናል ። አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻውን ፡ ሆኖ ፡ ማለት ፡ ከሰው ፡ ተለይቶ ፡
የሚኖር ፡ ቢሆን ፡ ብቻውን ፡ ምንም ፡ ለመሥራትና ፡ ለሥልጣኔ ፡ የሚሆን ፡
ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ አይችልም ። የሥልጣኔ ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ የሚወ
ለዱት ፤ የሚያድጉት ፤ የሚስፋፉትና ፡ የሚለሙት ፡ በሕዝብ ፡ መካከል ፡
ሲከናወኑ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሥልጣኔ ፡ የም
ትፈጸመው ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። የግሪኮችና ፡ የሮማውያን ፡
የቀሩትም ፡ ሕዝቦች ፡ ሥልጣኔያቸው ፡ የተወለደው ፡ በከተማቸው ፡ ው
ስጥ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ አዲስ ፡ ከተቋቋሙት ፡ ከተሞች ፡ ይልቅ ፡
ጥንታዊነት ፡ ያላቸው ፡ ከተሞች ፡ ሥልጣኔያቸው ፡ ይበልጥ ፡ የተራቀቀ ፡
ሆኖ ፡ ይገኛል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡
ጉዳት ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ አይካድም ። በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ሕዝብ ፡ ሲከ
ማች ፡ አንደኛ ፤ ለመኖር ፡ እንዲችል ፡ ሥራ ፡ መስጠት ፡ ያስፈልጋል ።

ሁለተኛ ፤ አኗኗሩ ፡ ሥራት ፡ እንዲያገኝ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ መስጠት ፤
የመመላለሻ ፡ ዘዴ ፡ መፍጠር ፤ ማስተማር ፡ ጤናውን ፡ መጠበቅ ፤ ለዚሁም ፡
ሁሉ ፡ ደንብና ፡ ሕግ ፡ ማውጣት ፡ የሚያሻ ፡ ይሆናል ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡
ዴሞክራሲ ፡ ይወለዳል ። ዐመፀ ፤ ወንጀል ፤ ብጥብጥ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ብል
ግና ፡ እነዚህን ፡ የመሰሉት ፡ በሰዎች ፡ መካከል ፡ የሚገኙ ፡ መጥፎ ፡ ጠባ
ዮች ፡ የሚስፋፉትና ፡ እየገነኑ ፡ የሚሄዱት ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ነው ።
የዴሞክራሲ ፡ ጉዳይም ፡ እንደዚሁ ፡ በሥልጣኔ ፡ በኩል ፡ ትልቅ ፡ ችግር ፡
እንደ ፡ ፈጠረ ፡ ብዙ ፡ ሊቃውንት ፡ ተናግረዋል ። ዴሞክራሲ ፡ ማለት ፡
ሕዝብ ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ ተካፋይ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኝበት ፡ አስተ
ዳደር ፡ ነው ። ትልቅ ፡ ጉዳይ ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ ሕዝብ ፡ አላፊነቱን ፡
ተካፋይ ፡ ሆኖ ፡ እንዲገኝ ፡ ወኪሎች ፡ መርጦ ፡ ይሰጣል ። ሕዝቡ ፡ ወኪ
ሎቹን ፡ ሲመርጥ ፡ ድምፁን ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡
የሚሰጠው ፡ ድምፅ ፡ እንዴት ፡ እኩል ፡ ይሆናል ? ከፍ ፡ ያለ ፡ ትምህ
ርት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ የሚሰጠው ፡ ድምፅ ፡ ትምህርት ፡ የሌለው ፤ ወይም ፡
በቂ ፡ ትምህርት ፡ ያልተማረ ፡ ሰው ፡ ከሚሰጠው ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ምን ፡
እኩል ፡ ሊቈጠር ፡ ይችላል ? እንደዚሁም ፡ ቴያትርና ፡ ሲኒማ ፡ ሲሰናዳ ፡

ዋናው ፡ ዐላማ ፡ ትምህርት ፡ ለመስጠትና ፡ የሕዝቡን ፡ ሞራል ፡ ከፍ ፡
ለማድረግ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ከተመልካቹ ፡ ሕዝብ ፡ የሚፈለገው ፡ እን
ዲማር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፍል ፡ በመሆኑ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲ
ከፍል ፡ ደግሞ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡ ነገር ፡ ማቅረብ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነ ።
ደስ ፡ እንዲለው ፡ ለማድረግ ፡ ደግሞ ፡ ስሜቱ ፡ የሚፈቅደውን ፡ ነገር ፡
ማቅረብ ፡ ያሻል ። ምስጢሩ ፡ የረቀቀና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ የሚጠ
ይቅ ፡ ነገር ፡ የቀረበለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሊገባው ፡ አይችልም ። ስለዚህ ፡
ወይም ፡ ምስጢሩንና ፡ ትርጉሙን ፡ በሕዝቡ ፡ የዕውቀት ፡ ደረጃ ፡ መጠን ፡
ዝቅ ፡ ማድረግ ፡ አለዚያም ፡ የሕዝቡን ፡ የዕውቀት ፡ ደረጃ ፡ በዚያው ፡
መጠን ፡ ከፍ ፡ ማድረግ ፡ ያሻል ። ነገር ፡ ግን ፡ በማንኛውም ፡ በሠለጠ
ነው ፡ አገር ፡ ቢሆን ፡ ታላላቅ ፡ ደራስያን ፡ ወይም ፡ አርቲስቶች ፡ የሚ
ያዘጋጁትን ፡ ሊከተሉ ፡ የሚችሉ ፡ ስንት ፡ ሰዎች ፡ ይገኛሉ ? ይህን ፡
ከመሰለው ፡ ደረጃ ፡ አብዛኛው ፡ ሕዝብ ፡ ከቶ ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ፡ ወይ ?
የድርሰትን ፤ የሙዚቃን ፤ የሥዕልንና ፡ በጠቅላላው ፡ የሥነ ፡ ጥበባትን ፡
ዋጋ ፡ በንግድ ፡ መልክ ፡ ከተመለከትነውና ፡ ፍርድ ፡ ሰጪው ፡ ተራው ፡
ሕዝብ ፡ እንዲሆን ፡ ከተፈለገ ፡ የእነዚህ ፡ ጥበቦች ፡ ደረጃ ፡ እያደገ ፡
በመሄድ ፡ ፈንታ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ እንደሚል ፡ ጥርጥር ፡ የለ
ውም ። ስለዚህ ፡ ነው ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የድርሰት ፡ የሙዚቃና ፡ የሥዕል ፡
ጣዕም ፡ ወደ ፡ መናኛነት ፡ እያዘነበለ ፡ ሲሄድ ፡ የሚታየው ። ይልቁንም ፡
ይህ ፡ ነገር ፡ በሲኒማ ፡ ላይ ፡ ጐልቶ ፡ ይታያል ። አንድ ፡ ሲኒማ ፡ በሕዝብ ፡
ዘንድ ፡ የተወደደ ፡ እንዲሆን ፡ ዋና ፡ ተጫዋች ፡ የሆነችው ፡ አርቲስት ፡
መልከ ፡ ቀና ፡ እንድትሆን ፡ ማድረግ ፡ ሲኒማውን ፡ የሚያዘጋጁት ፡ ሰዎች ፡
ዋና ፡ ነገር ፡ አድርገው ፡ ይዘውታል ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ሞራልን ፡ ያልጠ
በቀ ፡ ብዙ ፡ ብልግና ፡ ነገር ፡ ይታይበታል ። ትምህርት ፡ የሚሆነውን ፡
ነገር ፡ በመፈለግ ፡ ፈንታ ፡ የተራን ፡ ሰው ፡ ስሜት ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ ታስ
ቦ ፡ የተሠራ ፡ መሆኑ ፡ በግልጥ ፡ ይታወቃል ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የወንበ
ዴነትና ፡ የጋለሞታ ፡ ግብሮች ፡ ሰፊ ፡ ቦታ ፡ ተሰጥቷቸው ፡ ለተመልካች ፡
ይቀርባሉ ። ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የተቀዱት ፡ ታሪኮች ፡
እንኳ ፡ በሲኒማ ፡ ሲገቡ ፡ እውነተኛውን ፡ ታሪክ ፡ እየለቀቁ ፡ ዘመናዊ ፡
ከሆነው ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ፡ ጋራ ፡ እንዲቀራረቡ ፡ ተደርገው ፡ እንመለ
ከታለን ። ይህ ፡ የሚሆንበት ፡ ምክንያት ፡ ለሕዝቡ ፡ ጠቃሚ ፡ ትምህርት ፡
በመስጠት ፡ ፈንታ ፡ ባልታረመ ፡ ባሕርዩ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ መጥፎ ፡
የስሜት ፡ ዝንባሌዎች ፡ በማርካት ፡ ደስ ፡ እያለው ፡ ገንዘብ ፡ ከፍሎ ፡ እን
ዲመለከት ፡ ማለት ፡ ለገንዘብ ፡ መሰብሰቢያ ፡ እንዲሆን ፡ ታስቦና ፡ ተጠንቶ ፡
የተዘጋጀ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። ይህንኑ ፡ በመመልከት ፡ ዛሬ ፡ ብዙዎቹ ፡ አገ
ሮች ፡ ለሕዝባቸው ፡ ሞራል ፡ እንደሚስማማ ፡ እያደረጉ ፡ ራሳቸው ፡ የሲኒ



ማ ፡ ፊልም ፡ መሥራት ፡ የተሻለ ፡ ሆኖ ፡ አግኝተውታል ። በዚህ ፡ ረገድ ፡
ጃፓንና ፡ ህንድ ፡ ጥሩ ፡ ውጤት ፡ ለማግኘት ፡ ችለዋል ። ግብጽም ፡ ይህንኑ ፡
መንገድ ፡ ተከትላ ፡ በመጠኑ ፡ ለመሥራት ፡ ችላለች ። በሲኒማ ፡ በኩል ፡
ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በመጻሕፍትም ፡ በኩል ፡ እንደዚሁ ፡ ብዙ ፡ ደራስያን ፡
ቁም ፡ ነገር ፡ የሚገኝበት ፡ አሳብ ፡ መጻፋቸውን ፡ ትተው ፡ ከእውነት ፡
የራቀ ፡ ምንም ፡ ትምህርት ፡ የማይገኝበት ፡ ነገር ፡ ያቀርባሉ ። አንዳንዱም ፡
መጽሐፍ ፡ የቅዠትና ፡ የመተት ፡ አሳብ ፡ የሞላበት ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡
የሰውን ፡ አሳብ ፡ እንደ ፡ አሺሽ ፡ ለጊዜው ፡ እያሰከረ ፡ አላፊ ፡ በሆነና ፡
መሠረት ፡ በሌለው ፡ ደስታ ፡ ይመርዘዋል ። የማይረባ ፡ ፊልም ፡ ሁሉ ፡
የሚዘጋጀው ፡ ይህን ፡ ከመሰለ ፡ ከንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ እየተቀዳ ፡ መሆኑን ፡
ማወቅ ፡ ይገባል ። ይህንን ፡ ሁኔታ ፡ ልብ ፡ ብለን ፡ እንመልከተው ። በጥንት
የሮማ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ በመጨረሻው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡
ሆኖ ፡ በሮማ ፡ ከተማ ፡ ይተራመስ ፡ የነበረውን ፡ ግብሩ ፡ መጥፎ ፡ ሆኖ ፡
የታየውን ፡ ሕዝብ ፡ ያሳስበናል ። ኮሊዜ ፡ በተባለው ፡ የጨዋታ ፡ ቦታ ፡
ግላዲያተሮች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲተራረዱና ፡ ክርስቲያኖችን ፡ አራዊ
ቶች ፡ እየተጫወቱባቸው ፡ ሲበሏቸው ፡ መመልከት ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ለነበ
ረው ፡ የሮማ ፡ ሕዝብ ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ነበር ። አሁንም ፡ በየታላላቁ ፡
ከተማ ፡ የምንመለከተው ፡ ከዚህ ፡ ምንም ፡ ያኽል ፡ አይለያይም ። የሲርክ ፡
ጨዋታ ፡ በሚታይበት ፡ ስፍራ ፡ ስንት ፡ ጉድ ፡ አለ ። በሌላስ ፡ በልዩ ፡
ልዩ ፡ ቦታዎች ፡ ስንት ፡ የእብደትና ፡ የብልግና ፡ ነገር ፡ ሞልቷል ። ይህ ፡
ሁሉ ፡ በየከተማው ፡ የተከማቸውን ፡ ፍላጎቱና ፡ ዝንባሌው ፡ በትምህርትና ፡
በጥበብ ፡ ያልታረመውን ፡ ተራ ፡ ሕዝብ ፡ ማጫወትና ፡ ጊዜውን ፡ የሚያ
ሳልፍበትን ፡ ነገር ፡ መፍጠር ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ በመገኘቱ ፡ አይዶለምን?
እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ረቂቅ ፡ ስለ ፡ ሆኑት ፡ ከፍተኛ ፡ መንፈስ ፡ ስለሚጠ
ይቁት ፡ ጥበባት ፡ ምን ፡ ፍርድ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ? ሮማውያን ፡ ሕዝቡ ፡
ሥራ ፡ ፈትና ፡ የጭካኔ ፡ ነገር ፡ የሚታይበት ፡ ጨዋታ ፡ ወዳድ ፤ ነገሥታ
ቱና ፡ መኳንንቱ ፡ የርኩስነት ፡ ደስታ ፡ የሞላበትን ፡ አኗኗርን ፡ ፈላጊ
ዎች ፡ በሆኑበት ፡ ሰዓት ፡ ማንኛውም ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ ተነሥቶ ፡ ሕዝቡንና ፡
ወታደሩን ፡ በስብከትና ፡ ተጠንቶ ፡ በተደረገ ፡ የልግስና ፡ ሥራ ፡ ሲያታ
ልላቸው ፡ ከመንግሥቱ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ አውጥተው ፡ ያስቀምጡታል ።
እነ ፡ ኮሞድ ፤ ሄሊዎጋባል ፡ እነሱንም ፡ የመሰሉት ፡ የነገሡት ፡ በዚህ ፡
አኳኋን ፡ ነው ። ዛሬም ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የሚደረገው ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ።
ከኢንዱስትሪ ፡ የሚጐርፈውን ፡ ሸቀጥ ፡ ለመሸጥ ፡ የሚቻልበትን ፡ ዘዴ ፡
ማግኘት ፡ የታላላቅ ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ ፖሊቲካ ፡ የተመሠረተበት ፡
ዋና ፡ ጉዳይ ፡ ሆኖ ፡ በተገኘበት ፡ በየከተማው ፡ የተከማቹ ፡ በቂ ፡ ትምህ
ርት ፡ የሌላቸው ፡ የፋብሪካ ፡ ሠራተኞችና ፡ በገጠር ፡ ያለውን ፡ የግብር

ናና ፡ የእርሻ ፡ ሥራ ፡ እየጠሉ ፡ የከተማ ፡ ምቾት ፡ እየሳባቸው ፡ የተሰበሰቡት ፡ ሰዎች ፡ በዴሞክራሲ ፡ ስም ፡ ድምፅ ፡ በሚሰጡበት ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ ሕዝብ ፡ እየመረጣቸው ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ የሚጨብጡት ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ሂትለር ፤ ሙሶሊኒና ፡ ሌኒን ፡ የመሰሉ ፡ ናቸው ። ሕዝብ ፡ እንዲመርጣቸው ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ለሕዝቡ ፡ ያሳዩት ፡ መልካም ፡ ጠባይ፡ ምንድነው ? በጥንቲቱ ፡ ግሪክ ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ፔሪክሌስ ፡ በግብረ ፡ ገብነት ፡ የተወደዱ ፡ ሆነው ፡ ነውን ፡ አይዶለም ። ነገር ፡ ግን ፡ ርኅራኄ ፡ በሌለው ፡ ጦርነት ፡ የዓለምን ፡ ሕዝቦች ፡ ፈጅተው ፡ ለፋብሪካዎቻቸው ፡ መስፋፊያ ፡ የገበያውን ፡ መንገድ ፡ እንዲከፍቱለት ፡ ለሕዝቡ ፡ ቃል ፡ ይገቡለታል ። ከዚህ ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ ሂትለር ፡ ተሰምቶ ፡ የማይታወቅ ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ የጀርመን ፡ ሕዝብ ፡ ይህንኑ ፡ ያለመቃወም ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ተቀብሎታል ። ጀርመንን ፡ የመሰለች ፡ ታላላቅ ፡ ፈላስፎች ፡ እነ ፡ ካንት ፡ ታላላቅ ፡ ደራስያን ፡ እነ ፡ ጎት ፡ ታላላቅ ፡ ሙዚቀኞች ፡ እነ ፡ ባግነር ፡ የተወለዱባት ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ከሚታይ ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ የደረሰች ፡ አገር ፡ ሆና ፡ ሂትለርን ፡ የመሰለ ፡ ጨካኝ ፡ መሪ ፡ ተነሥቶ ፡ የዓለምን ፡ ሕዝቦች ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ ዐዘቅት ፡ የሚጥል ፡ ጦርነት ፡ ሲያዘጋጅ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርጎ ፡ ሕዝቡ ፡ ከዚህ ፡ ከወንጀለኛ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ያሳቡ ፡ ተካፋይ ፡ ተባባሪ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ ፡ ሲሉ ፡ ብዙ ፡ ሊቃውንት ፡ ተደንቀውበታል ። ይህ ፡ በጀርመን ፡ አገር ፡ የተደረገ ፡ ሲሆን ፡ በመስኮብ ፡ አገር ፡ የሆነውንም ፡ ብንመለከተው ፡ ከዚህ ፡ የባሰ ፡ እንጂ ፡ የተሻለ ፡ አይዶለም ። ሌኒን ፡ በመስኮብ ፡ አገር ፡ ኮሙኒስምን ፡ ሲያቋቁም ፡ የስንት ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ ደም ፡ አፍስሷል ። ይህ ፡ አልበቃ ፡ ብሎት ፡ የኮሙኒስምን ፡ ሕግ ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ለመዘርጋት ፡ ሲል ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ካሉት ፡ ሕዝቦች ፡ ካራት ፡ እጅ ፡ ሦስቱን ፡ ለመፍጀት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝ ፡ ያላንድ ፡ ቅሬታ ፡ እፈጽመዋለሁ ፡ ሲል ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ የሚረሳ ፡ አይዶለም ። ኮሙኒስም ፡ ማለት ፡ ትርጉሙ ፡ ባጭሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ የለም ፤ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ማለት ፡ ይህቺ ፡ የምንኖርባት ፡ መሬት ፡ ነች ፡ ማለት ፡ መሆኑን ፡ እናውቃለን ። ይህ ፡ የመጨረሻው ፡ የማቴሪያሊስም ፡ ትምህርት ፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ መሪዎች ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ ሊነሡ ፡ ቻሉ ? ይህንን ፡ ለመረዳት ፡ ስንፈልግ ፡ ለምሳሌ ፤ ባንዲት ፡ ትልቅ ፡ ከተማ ፡ በፓሪስ ፡ ወይም ፡ በሎንዶን ፡ የሚሆነውን ፡ እንመልከት ። የሕዝቡ ፡ መንፈስ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንመርምር ። የመንፈሱንም ፡ ዝንባሌ ፡ ለማወቅ ፡ የሚወደውና ፡ ጊዜውን ፡ የሚያሳልፍበት ፡ ጨዋታ ፡ ምን ዐይነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እናስተውል ። መጀመሪያ ፡ የጨዋታ ፡ ሁሉ ፡ ጉልላት ፡ ኦፔራ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። ኦፔራ ፡ ማለት ፡ ሙዚቃ ፡ ቅኔና ፡ ዳንስ ፡ ተዋሕደው ፡ የሚገኙበት ፡ የተከበረ ፡ ጨዋታ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ባለ



ፈው ፡ ምዕራፍ ፡ ያነበብነው ፡ ያ ፡ ከሜካ ፡ ውስጥ ፡ ሄዶ ፡ ዕንጨት ፡ ሲቈርጥ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ የተገለጠችለት ፡ መነኵሴ ፡ ከሰማት ፡ ሙዚቃ ፤ ጋራ ፡ የምትቀራረብ ፡ ሙዚቃ ፡ ፈጥረው ፡ ሰዎች ፡ ክብር ፡ ባለው ፡ ስሜት ፡ ጊዜያቸውን ፡ የሚያሳልፉበት ፡ ቦታ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ (ክላሲክ) ፡ የሆኑ ፡ ጥሩ ፡ ቴአትሮች ፡ የሚታዩባቸው ፡ ስፍራዎች ፡ ይገኛሉ ። ዕልፍ ፡ ብለን ፡ ስንሄድ ፡ በብዙ ፡ ሺሕ ፡ የሚቈጠሩ ፡ የጨዋታ ፡ ቦታዎች ፡ ተሠርተዋል ። እነዚሁም ፡ ሰው ፡ ከአንበሳና ፡ ከነብር ፡ ጋራ ፡ አደገኛ ፡ ጨዋታ ፡ የሚጫወትበት ፡ ሰዎች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ በቦክስ ፡ የሚደባደቡበት ፡ ወንበዴዎች ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩ ፡ የሚታዩበት ፡ (ሲኒማ) ፡ ርኩስ ፡ የሆነ ፡ የዳንስና ፡ የጋለሞታ ፡ ጨዋታ ፡ የሞላበት ፤ ሌሎችም ፡ ይህን ፡ የመሰሉ ፡ የመጨረሻ ፡ ብልግና ፡ የሰፈረባቸው ፡ የጨዋታ ፡ ቤቶች ፡ ናቸው ። እንግዴህ ፡ ወደ ፡ ኦፔራና ፡ ወደ ፡ ጥሩ ፡ የቴአትር ፡ ቤቶች ፡ የሚሄዱት ፡ ሰዎችና ፡ የርኩስነትና ፡ የጭካኔም ፡ ጠባይ ፡ ወዳለባቸው ፡ የጨዋታ ፡ ቤቶች ፡ የሚሄዱት ፡ ሰዎች ፡ ቍጥራቸው ፡ ስንት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አመዛዝነን ፡ ብንመለከተው ፡ እነዚህ ፡ የመጨረሾቹ ፡ ሺሕ ፡ ጊዜ ፡ የበለጡ ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ።

እንግዴህ ፡ እንደ ፡ እነ ፡ ሂትለር ፡ ያለ ፡ መሪ ፡ መሣሪያ ፡ አድርጎ ፡ የሚነሣው ፡ እነዚህን ፡ ብዛታቸው ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የሚገኘውን ፤ ሁኔታቸው ፡ ከሰብአዊነት ፡ ይልቅ ፡ ወደ ፡ አውሬነት ፡ የሚያደላውን ፤ የደም ፡ መፋሰስ ፡ ነገር ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛቸውን ፡ ሰዎች ፡ መሆኑን ፡ ልንዘነጋው ፡ አይገባም ። በሰው ፡ ውስጥ ፡ የመልአክነትና ፡ የአውሬነት ፡ ጠባዮች ፡ ተዋሕደው ፡ የሚኖሩ ፡ መሆናቸውን ፡ እናውቃለን ። ስለዚህ ፡ የማቴሪያሊስም ፡ ሥልጣኔ ፡ በገነነችበት ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ የአውሬነት ፡ ባሕርይ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ኀይል ፡ አግኝቶ ፡ ቢታይ ፡ ምንም ፡ የሚያስደንቅ ፡ አይዶለም ። ሂትለርና ፡ ሙሶሊኒ ፡ ዲስኩር ፡ ሲናገሩ ፡ በያደባባዩ ፡ ቦታ ፡ የሚያጨበጭቡላቸውና ፡ የሚያጋንኑላቸው ፡ እነዚህ ፡ ሕዝቦች ፡ መሆናቸውን ፡ መዘንጋት ፡ አይገባም ። አንዳንድ ፡ አስተዋዮች ፡ ሰዎች ፡ ቢገኙም ፡ በእነዚህ ፡ ተራ ፡ ሰዎች ፡ የተዋጡ ፡ በመሆናቸው ፡ ምንም ፡ ሊያደርጉ ፡ አይችሉም ። በዚህ ፡ ዐመፀኛ ፡ በሆነ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ የሚሠሩ ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የመዓት ፡ ሥራዎች ፡ አሉ ። ከእነዚህም ፡ አንዱ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የሚገኘው ፡ ነው ።

ሰው ፡ እስረኛ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የሚደርስበት ፡ መከራና ፡ ሥቃይ ፡ የመረረ ፡ እንዲሆን ፡ ለማድረግ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘዴ ፡ የሚፈጥሩ ፡ ሰዎች ፡ ተመርጠው ፡ ለመንግሥት ፡ ባለ ሥልጣኖች ፡ አሳብ ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ተደርጓል ። ይህን ፡ የመሰለው ፡ አሳብ ፡ የተፈጠረው ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡

በሳይንስ ፡ እየተጠና ፡ እንዲሠራ ፡ በሚደረግበት ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ የሰው ፡ ነፍስ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጭንቅ ፡ ሊደርስባት ፡ የሚችለው ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ ብትቀጣ ፡ ነው? ተብሎ ፡ ሲታሰብ ፡ ይህ ፡ ጉዳይ ፡ እንደ ፡ ቀሩት ፡ ሁሉ ፡ በሳይንስ ፡ መንገድ ፡ ካልተመረመረ ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ ሊሰጥ ፡ አይችልም ፡ በማለት ፡ ታስቦ ፡ የተደረገ ፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ያለ ፡ አሳብ ፡ የተፈጠረው ፡ በመጀመሪያው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ በጀርመን ፡ አገር ፡ ነው ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በሂትለር ፡ ዘመንና ፡ በመስኮብ ፡ አገር ፡ በኮሙኒስቶች ፡ ጊዜ ፡ ሰፊ ፡ ጥናት ፡ እየተደረገ ፡ ሲሠራበት ፡ ኖሯል ። በመስኮብ ፡ አገር ፡ ለተደረገውና ፡ አሁንም ፡ ለሚደረገው ፡ (Arthur Koestler) አርቱር ፡ ኬስትለር ፡ የተባለው ፡ ደራሲ ፡ የጻፈውን ፡ በፈረንሳይ ፡ (Le zéro et l'infini) በእንግሊዝኛ ፡ (Darkness at noon) የተባለውን ፡ መጽሐፍ ፡ ማንበብ ፡ ያስፈልጋል ። በሳይንስና ፡ በቴክኒክ ፡ ዕውቀቶች ፡ ሰው ፡ ሲሳይ ፤ ተድላ ፤ ምቾትና ፡ ደስታ ፡ እንዲያገኝ ፡ በሚደከምበት ፡ ዘመን ፡ ምድረ ፡ ገነትና ፡ ገሃነመ ፡ እሳት ፡ አብረው ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ሆነው ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ እንዲገኙ ፡ ለማድረግ ፡ ቢታሰብ ፡ ምን ፡ ይገርመናል ። የመንግሥታት ፡ ዐላማ ፡ ንግድ ፡ ሆኖ ፡ እስከሚኖርበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ በየፋብሪካው ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ መከማቸታቸው ፡ የማይቀር ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ስንመለከተው ፡ የሥልጣኔ ፡ ትርጉም ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማወቅ ፡ ያስቸግረናል ። ለምሳሌ ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወይም ፡ ህንድ ፡ ወይም ፡ የማንኛውም ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ዘመናዊውን ፡ ትምህርት ፡ ተምሯል ፤ አኗኗሩና ፡ አለባበሱ ፡ እንደ ፡ ሠለጠኑት ፡ የዘመኑ ፡ ሰዎች ፡ ነው ፤ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ራዲዮ ፤ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ ወንበሮች ፡ ፍሪጊዴር ፡ ይገኛሉ ። የሚሄደው ፡ በአቶሞቢል ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ በማቴሪያሊስምና ፡ ሃይማኖትን ፡ በመናቅ ፡ ነፍሱ ፡ ደረቅ ፡ ሆናለች ። ሸፋጭ ፤ ክፉ ፤ ጨካኝ ፤ መሠሪ ፤ ትዕቢተኛ ፤ ንፉግ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ሌላው ፡ ሰው ፡ ደግሞ ፡ ትምህርቱ ፡ ባገሩ ፡ ቋንቋ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ወይም ፡ ጨርሶ ፡ መሀይምን ፡ ነው ። ልብሱ ፡ እንደ ፡ አገሩ ፡ ልማድ ፡ ነው ። በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ዘመናዊ ፡ ዕቃ ፡ የለም ። የሚሄደውም ፡ በእግሩ ፡ ነው ። በጠባዩ ፡ ግን ፡ ደግ ፤ ርኅሩኅ ፤ ገር ፤ ትሑት ፤ እንግዳ ፡ ተቀባይ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ከሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ ሠልጥኗል ፡ ሊባል ፡ የሚገባው ፡ የትኛው ፡ ነው? ለዚህ ፡ ጥያቄ ፡ መልሱን ፡ ማግኘት ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ መስሎ ፡ አይታይም ። ከሥልጣኔ ፡ የሚፈለገው ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ደስታ ፡ መሆኑን ፡ የሚክድ ፡ ሰው ፡ ስለሌለ ፡ ደስታ ፡ ማለት ፡ ምንድነች? የምትገኘውስ ፡ እንዴት ፡ ነው? ብለን ፡ መርምረን ፡ ለዚህ ፡ ጥያቄ ፡ የሚሆነውን ፡ መልስ ፡ ስናገኝ ፡ ለዚያኛው ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ እንድንችል ፡ ያደርገናል ። ከፍ ፡ ብለን ፡ በሌላ ፡ ምዕራፍ ፡ ተናግረነው ፡ እ



ንደ ፡ ነበረው ፡ ይህንን ፡ ጉዳይ ፡ ፈላስፎች ፡ በየዘመኑ ፡ መርምረውታል ። ከሶክራት ፡ ጀምሮ ፡ ፕላቶን ፤ አሪስቶት ፤ ኤፒኩር ፤ ሴኔክ ፤ ማርክ ፤ ኦሬል ፤ ቅዱስ ፡ አጉስጢኖስ ፤ ቅዱስ ፡ ቶማስ ፡ ዳኪን ፡ ሞንቴኝ ፤ ባኮን ፤ ዴካርት ፤ ላይብኒዝ ፤ ፖስካል ፤ ስፒኖዛ ፤ ማለብራንሽ ፤ ቮልቴር ፤ ሩሶ ፤ ዲደሮ ፤ ሾፐንሃወር ፤ ካንት ፤ ኦጉስት ፤ ኮንት ፤ ኒች ፤ ቤርግሶን ፡ እነዚህና ፡ እነሱንም ፡ የመሰሉት ፡ ፈላስፎች ፡ ሙሉ ፡ ዕድሜያቸውን ፡ ጥበብን ፡ በመመርመር ፡ ያሳለፉት ፡ ይህንኑ ፡ ለማወቅ ፡ ነው ። ርግጥ ፡ ነው ፤ ሁሉም ፡ ባንድ ፡ አሳብ ፡ አልተስማሙም ። ያንዱ ፡ አስተያየት ፡ ከሌላው ፡ ጋራ ፡ ፈጽሞ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። ነገር ፡ ግን ፡ በጥሩ ፡ ኅሊና ፡ ጉዳዩን ፡ ስናመዛዝነው ፡ ለመካድ ፡ የማንችለውን ፡ ትምህርት ፡ የሰጡን ፡ ፈላስፎች ፡ አሉ ። የምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ትምህርት ፡ በግሪኮች ፡ ፍልስፍናና ፡ በክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ ለግሪክ ፡ ፍልስፍና ፡ አባት ፡ የሆነው ፡ ሶክራት ፡ ምን ፡ ትምህርት ፡ እንዳስተማረ ፡ እስቲ ፡ ጥቂት ፡ እንመልከተው ። ሶክራት ፡ ሲያስተምር ፡ ደስታ ፡ የምትገኘው ፡ ከውበት ፤ ከጉልበት ፤ ከንዋይ ፤ ከክብርና ፡ እነዚህንም ፡ ከመሰሉት ፡ ነገሮች ፡ አይደለም ። ሀብት ፡ በሀብታሞች ፡ ቤት ፡ ድኽነትም ፡ በድኾች ፡ ቤት ፡ አይኖሩም ፤ ሀብትና ፡ ድኽነት ፡ የሚገኙት ፡ በሰው ፡ ነፍስ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ ይለናል ።

ይህም ፡ የውስጥ ፡ ዓለምና ፡ የውጭ ፡ ዓለም ፡ ተብሎ ፡ በፍልስፍና ፡ የሚጠራው ፡ ነው ። በውጭ ፡ የምናየው ፡ ግዙፍ ፡ የሆነ ፡ ዓለም ፡ ሰፊ ፡ ሆኖ ፡ በሚገኝበት ፡ መጠን ፡ በነፍሳችን ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ዓለም ፡ ደግሞ ፡ ከሱ ፡ የበለጠ ፡ ታላቅና ፡ ሰፊ ፡ ነው ። ማንኛውም ፡ አዲስ ፡ ጥበብና ፡ ዕውቀት ፡ ሊሽሩት ፡ የማይችሉት ፡ ይህ ፡ ሶክራት ፡ ያስተማረው ፡ ትምህርት ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ተዘንግቷል ። የሰውን ፡ መንፈስ ፡ በመደነቅ ፡ የሚማርኩት ፡ ስንት ፡ ነገሮች ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ ተሠርተው ፡ ይታያሉ ። አቶሞቢል ፤ ራዲዮ ፤ ኤሌክትሪሲቲ ፤ አኤሮፕላን ፤ ባቡር ፤ ሲኒማ ፤ ቴሌቪዚዮን ፤ ሌሎችም ፡ እነዚህን ፡ የመሰሉ ፡ ሳይንስና ፡ ቴክኒክ ፡ ያፈሯቸው ፡ ነገሮች ፡ አሉ ። ሰው ፡ በእነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ተከቦ ፡ ሲገኝ ፡ ፍጹም ፡ ደስታን ፡ የወረሰ ፡ መስሎ ፡ ይታያል ። እሱም ፡ ራሱ ፡ ከእነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ጋራ ፡ ደስታ ፡ አብራ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ገብታለች ፡ ብሎ ፡ ማመኑ ፡ አልቀረም ። ነገር ፡ ግን ፡ ሶክራት ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ ሁሉ ፡ በሰው ፡ ነፍስ ፡ ውስጥ ፡ ልትገኝ ፡ የሚገባት ፡ እውነተኛይቱ ፡ ደስታ ፡ እንደ ፡ ጐደለችው ፡ ይሰማዋል ። እንዲያውም ፡ እነዚህ ፡ በዘመናችን ፡ የተፈጠሩት ፡ የግዙፍ ፡ አካል ፡ ጥበቦች ፡ እየበዙ ፡ በሄዱበት ፡ መጠን ፡ ተፈላጊ ፡ የሆነችው ፡ ደስታ ፡ እየራቀች ፡ ሄዳለች ። ሳይንስና ፡ ቴክኒክ ፡ በኢንዱስትሪ ፡ አማካ

ይነት ፡ እነዚህን ፡ የጥበብ ፡ ዕቃዎች ፡ ማጕረፍ ፡ በጀመሩበት ፡ ጊዜ ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ የክብርና ፡ የልማት ፡ የደስታና ፡ የሲሳይ ፡ አዲስ ፡ ዘመን ፡ ተከፈተለት ፡ በማለት ፡ የዘመናችን ፡ ሥልጣኔ፡ በማንኛውም ፡ ዘመን ፡ ከታዩት ፡ ሥልጣኔዎች ፡ ሁሉ ፡ የበለጠች ፡ መሆኗን ፡ እያጋነኑ ፡ ተናግረው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ተመልካቾች ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፡ ይህቺ ፡ ሥልጣኔ ፡ መዘዟ ፡ ያንኑ ፡ ያኽል ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ማሳሰባቸው፡ አልቀረም ። ለምሳሌ ፤ ኒች ፡ ቀድሞ ፡ ያውሮፖ ፡ መንግሥታት ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ነገሥታት ፡ ትውልድ ፡ (ማለት ፡ እገሌ ፡ ቀርቶ፡ እገሌ ፡ ይንገሥ ፡ በማለት) ፡ ጦርነት ፡ ይዋጉ ፡ እንደ፡ነበረ ፤ ይህም፡በሙሉ፡ የተገባ ፡ ሆኖ ፡ ባይገኝ ፡ እንኳ ፡ ጥቂት ፡ ክብር ፡ የሚታይበት ፡ ምክንያት፡ መሆኑን ፡ ካሳሰበ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚመጣው ፡ ጦርነት፡ግን፡ ከሁሉ፡ የከፋ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ የጦርነቱ ፡ ዐላማ ፡ የንግድን ፡ ጕዳዮች ፡ በመድፍ ፡ ጕልበት ፡ ለመወሰን ፡ ታስቦ፡የሚደረግ፡መሆኑን፡ይህም፡ክብር፡የሌለው፡ ዝቅተኛነትን ፡ የሚያሳይ ፡ ዐላማ፡ነው፡ሲል ፡ ተናግሯል ። የተናገረውም ፡ ቃል ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ። «ያውሮፓ ፡ ዴሞክራሲዎች ፡ ተብለው ፡ የሚጠሩት ፡ እነዚህ ፡ የባቤል ፡ መንግሥታት ፡ እስከ ፡ አምሳ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ የዓለምን ፡ ገበያዎች ፡ ለመሻማት ፡ ሲሉ ፡ እጅግ ፡ ከሚያስፈራ ፡ ጦርነት ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይተላለቃሉ» ። ኒች ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በጻፈ ፡ ጊዜ ፡ የዓለምና ፡ የደስታ ፡ ሰዓት ፡ ስለ፡ነበረ፡እንደ፡ እብድ ፡ ቈጠሩት ። በሰርግ ፡ ላይ ፡ ሰርገኞች ፡ የሆኑት ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ዘፈን ፡ ሲዘፍኑ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በዘፈናቸው ፡ መካከል ፡ ገብቶ ፡ ሲያለቅስ፡ ቢሰሙት ፡ ሰርገኞቹ ፡ የቱን ፡ ያኽል ፡ እንደሚጠሉት ፡ ልንገምተው ፡ እንችላለን ። የመከራ ፡ ትንቢት ፡ የሚናገሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ የሰዎችን ፡ ቍጣ ፡ ይቀሰቅሳሉ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ኒች ፡ ተናግሮት ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ሁሉ ፡ ወዲያው ፡ የመጀመሪያው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ስለ ፡ ፈነዳ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ በታሪክ ፡ ያልታየና ፡ ያልተሰማ ፡ ጥፋት ፡ አደረሰባቸው ። የጦርነቱ ፡ ምክንያት ፡ በታላላቆቹ ፡ መንግሥታት ፡ መካከል ፡ የተፈጠረው ፡ የንግድ ፡ ውድድር ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ። «የሰው ፡ ዐላማው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሊታወቅ ፡ የሚያስፈልግበት ፡ ጊዜው ፡ ደርሷል ። ለከፍተኛው ፡ ተስፋው ፡ ዘር ፡ የሚሆነውን ፡ ተክል ፡ ሰው ፡ ይተክል ፡ ዘንድ ፡ የሚያስፈልግበት ፡ ጊዜ ፡ ቀርቧል» ። ሲል ፡ ኒች ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ መልሱን ፡ እስካሁን ፡ አላገኘም ። ታላላቅ ፡ መንግሥታት ፡ የሚደክሙላት ፡ ሥልጣኔ ፡ ዐላማዋ ፡ ምንድነው ? ንግድ ፡ እያስፋፉ ፡ ለመሄድ ፡ ከሆነ ፡ ይህ ፡ የሚያኰራ ፡ ግብ ፡ ሆኖ ፡ አይገኝም ። መጨረሻውም ፡ ፍጅትና ፡ ጦርነት ፡ መተላለቅም ፡ ከመሆን ፡ አይዘልም። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ባለፉት ፡ ሁለት ፡ የዐለም ፡ ጦርነቶች ፡ የደረሰባቸው ፡



መከራ ፡ የማይረሳ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ አሁንም ፡ ደግሞ ፡ ዐላማቸውን ፡ ካለወጡ፡ ወደ ፡ ሦስተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ እንደሚጓዙ ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ። በመጀመሪያውና ፡ በሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነቶች ፡ ምክንያት ፡ የሞቱት ፡ ሰዎች ፡ ቍጥራቸው ፡ ከሰባ ፡ ሚሊዮን ፡ የደረሰ ፡ መሆኑን ፡ ማስታወስ ፡ ይገባል ።

ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ የምንሰጠው ፡ ባንድ ፡ ጋዜጣ ፡ ታትሞ ፡ ከወጣ ፡ አርቲክል ፡ የተቀዳ ፡ ጥቅስ ፡ የተማሩ ፡ ሰዎች ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ማለት ፡ ከመጀመሪያ ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ ሞራላቸው ፡ ከምን ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ይገልጥልናል ። ቃሉም ፡ የሚከተለው ፡ ነው ፤

"Plus de peintres, plus de littérature, plus de musiciens, plus de sculpteurs, plus de religions, plus de républicains, plus de royalistes, plus d'impérialistes, plus d'anarchistes, plus de socialistes, plus de bolchéviques, plus de politiques, plus de prolétaires, plus de démocrates, plus de bourgeois, plus d'armée, plus de police, plus de patrie, enfin toutes ces imbécilités, plus rien, plus rien, rien, rien, rien, rien."

«ሠዓሊዎች ፡ አያስፈልጉም ፤ ድርሰት ፡ አያስፈልግም ፤ ሃይማኖቶች ፡ አያስፈልጉም ፤ ሬፑብሊካውያን ፡ አያስፈልጉም ፤ ንጉሣውያን ፡ አያስፈልጉም ፤ ኤምፔሪያሊስቶች ፡ አያስፈልጉም ፤ አናርሺስቶች ፡ አያስፈልጉም ፤ ቦልሼቢኮች ፡ አያስፈልጉም ፤ የፖለቲካ ፡ ሰዎች ፡ አያስፈልጉም ፤ ፕሮሌቴሮች ፡ አያስፈልጉም ፤ ዴሞክራቶች ፡ አያስፈልጉም ፤ ቡርዦዎች ፡ አያስፈልጉም ፤ አሪስቶክራቶች ፡ አያስፈልጉም ፤ የጦር ፡ ሰራዊት ፡ አያስፈልግም ፤ ፖሊስ ፡ አያስፈልግም ፤ ትውልደ ፡ ሀገር ፡ አያስፈልግም ፤ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጅልነቶች ፡ አስፈላጊ ፡ አይደሉም ፤ ምንም ፡ አያስፈልግም ፡ ምንም ፡ አያስፈልግም ፡ ምንም ፤ ምንም ፤ ምንም ፤ ምንም» ።

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ኢንዱስትሪ ፡ በዓለም ፡ መንግሥታት ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ ሲያቃውሰውና ፡ ጦርነትንም ፡ እንዲነሳ ፡ ሲያደርግ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የያንዳንዱን ፡ ሰው ፡ ኑሮ ፡ አበላሽቶታል ። አልደስ ፡ ሃክስሌ ፡ ስለ ፡ ኢንዱስትሪ ፡ የተናገረውን ፡ እንስማ ።

«ኢንዱስትሪ ፡ እየተስፋፋ ፡ በሚሄድበት ፡ መጠን ፡ በታላላቅ ፡ ከተሞች ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ እንዲከማች ፡ ያደርጋል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሕይወት ፡ ለአእምሮ ፡ ጤና ፡ የተስማማ ፡ አይደለም ። (ሺዞፍሬኒ) ፡ የተባለው ፡ አሳብን ፡ የሚያናውጥ ፡ በሽታ ፡ የሚጠናው ፡ የኢንዱስትሪ ፡

ሠራተኞች ፡ በሚከማቹባቸው ፡ መንደሮች ፡ መሆኑ ፡ ተገልጦልናል ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ የተከማቸ ፡ ሕዝብ ፡ በሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ያለበትን ፡ አላፊነት ፡ እንዲያውቅ ፡ ለእውነተኛ ፡ ዴሞክራሲ ፡ ተቀዳሚ ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠረውን ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ የኅሊና ፡ ነጻነት ፡ ይህ ፡ አኗኗር ፡ የማይደግፍ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። የከተማ ፡ ኑሮ ፡ የሰውነትን ፡ ስሜት ፡ የሚቀንስ ፡ ያልተረጋገጠ ፡ ነው ። ሰዎች ፡ በመካከላቸው ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ በሰብአዊ ፡ ስሜት ፡ በመተርጐም ፡ ፈንታ ፡ በኤኮኖሚ ፡ መደብ ፡ አግብተው ፡ ይመለከቱታል ። ከሥራ ፡ ውጭ ፡ ሲሆኑ ፡ ደግሞ ፡ አላፊነት ፡ የተወገደላቸው ፡ እየሆኑ ፡ የሚፈልጉት ፡ ጊዜያቸውን ፡ የሚያሳልፉበትን ፡ ነገር ፡ ነው ። በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሕይወት ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ ብቸኛና ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ አድርጎ ፡ ይቈጥረዋል ። ኑሮውንም ፡ ዐላማና ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ አድርጎ ፡ ይመለከተዋል» ።

# ተጠራጣሪዎችና ፡ ከሓድያን ።

የታሪክን ፡ አካሄድ ፡ ስንከታተል ፡ የሰዎች ፡ እርምጃ ፡ በጣም ፡ ገፍቶ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ከገሠገሠ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የተራመደውን ፡ ያኽል ፡ ያፈገፍጋል ። አንዳንድ ፡ ሕዝቦች ፡ ከተሞቻቸውን ፡ አሳምረው ፤ የጦር ፡ ሰራዊታቸውን ፡ በጀግንነትም ፡ ሆነ ፡ በመንፈስ ፡ ጠንካራነት ፡ አሠልጥነው ፤ የሕዝቡን ፡ መንፈስ ፡ በትምህርትና ፡ በጥበብ ፡ የተራቀቀ ፡ እንዲሆን ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃቸውንም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እንዲል ፡ አድርገው ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ እርምጃቸውን ፡ በመቀጠል ፡ ፈንታ ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ይመለሳሉ ። እንደ ፡ ገና ፡ ሁሉን ፡ ነገር ፡ በችላ ፡ ባይነት ፡ በመመልከት ፤ ጠባያቸው ፡ ቀፍ ፡ ብሎ ፡ የነበረውን ፡ ያኽል ፡ ዝቅ ፡ በማድረግ ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ ልዕልና ፡ ያላቸው ፡ ሆነው ፡ የሚታዩትን ፡ እንደ ፡ ሃይማኖት ፡ ነጻነት ፤ ግብረ ፡ ገብነት ፡ የመሰሉትን ፡ ነገሮች ፡ አዋርደው ፡ በማሳየት ፡ ከሚያሳዝን ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ተመልሰው ፡ ይወድቃሉ ። ይህንንም ፡ በግሪኮችና ፡ በሮማውያን ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ በሙሉ ፡ እናገኘዋለን ።

ፕሉታርክ ፡ ታሪካቸውን ፡ የጻፈላቸው ፡ የግሪክና ፡ የሮማ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ አገሮች ፡ በብዙ ፡ ዘመን ፡ እርምጃ ፡ ባገኙት ፡ ሥልጣኔ ፡ መሠረት ፡ በመልካም ፡ አስተዳደግ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ሞራል ፤ በተራቀቀ ፡ ስሜትና ፡ የጋለ ፡ በሆነ ፡ ሃይማኖት ፡ ከደረሱበት ፡ የሥልጣኔ ፡ ውጤት ፡ የተገኙ ፡ ሰዎች ፡ መሆናቸውን ፡ እናውቃለን ። በኋላ ፡ ግን ፡ በእነ ፡ ዴሞስቴን ፡ ዘመን ፡ ግሪኮች ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ የቀድሞውን ፡ ትልቅነታቸውን ፡ ረስተውት ፡ ለነጻነታቸውም ፡ ሆነ ፡ ለክብራቸው ፡ አሳብ ፡ የሌላቸው ፡ ሆኑ ። ሮማውያንም ፡ የቀድሞዎቹ ፡ መሪዎቻቸው ፡ በባሕርያቸው ፡ ጥብቅነትና ፡ በግብራቸው ፡ ምስጉንነት ፡ ይደነቁ ፡ የነበሩትን ፡ ያኽል ፡ የኋለኞቹ ፡ ቄሳሮች ፡ ከሰው ፡ ባሕርይ ፡ እየወጡ ፡ ወደ ፡ እንስሳነት ፡ ተመለሱ ። ይህንኑም ፡ በኔሮን ፤ በካሊጉላ ፤ በቲቤር ፤ በካራካላ ፤ በኮምድና ፡ በሄሊዎጋባል ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ እናገኘዋለን ። የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ መጥቶ ፡ ወንጌል ፡ በተሰበከበት ፡ ዘመን ፡ የዓለም ፡ ገዥዎች ፡ የነበሩት ፡ ሮማውያን ፡ በባሕርያቸው ፡ ከፍ ፡ ብለው ፡ ይታዩበት ከነበረው ፡ ትልቅነታቸው ፡ ወርደው ፡ ከጭቃ ፡ ውስጥ ፡ ተንከባለሉ ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የዓለም ፡ መድኀኒትነቱን ፡ ይዞ ፡ ባይደርስ፡

ኖሮ ፡ መላውን ፡ ዓለም ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ ጐትተው ፡ ስም ፡ ከማይገኝለት ፡ ቈሻሽነት ፡ ውስጥ ፡ እንዲገባ ፡ በማድረግ ፡ መሬትን ፡ በኀጢአት ፡ የረከሰች ፡ ያደርጓት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አይጠረጠርም ። የዓለም ፡ ሕዝቦችም ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ከመርከስ ፡ ድነው ፡ ስለ ፡ ታደሱ ፡ የንጽሕናቸውን ፡ ውበትና ፡ የሥነ ፡ ፍጥረታቸውን ፡ ክቡርነት ፡ ተጐናጽፈው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ሆኑ ። ይህንኑም ፡ ቅዱስ ፡ አውጉስጢኖስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ከተማ ፡ (La Cité de Dieu) በተባለው ፡ መጽሐፉ ፡ ግሩም ፡ በሆነ ፡ አነጋገር ፤ ጥልቅ ፡ በሆነ ፡ ተመራማሪነት ፤ ወደር ፡ በሌለው ፡ አጻጻፍ ፡ ገልጦታል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሰማዕትነትን ፡ በተቀበሉበትና ፡ የክርስቶስ ፡ ወንጌል ፡ በዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ እንድትነገር ፡ ለማድረግ ፡ የሐዋርያትን ፡ ሥራ ፡ ባስፋፉበት ፡ ጊዜ ፡ ባሕርያቸው ፡ የሚያስደንቅና ፡ እውነትም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ያደረባቸው ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ግልጥ ፡ ሆኖ ፡ ይታይ ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ መጀመሪያ ፡ በክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ውስጥ ፡ መለያየት ፡ ተፈጠረ ፤ ቀጥሎ ፡ ክርስቲያን ፡ የሆኑት ፡ ሕዝቦችና ፡ ነገሥታት ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ጦርነት ፡ ሲዋጉ ፡ ኖሩ ። የእስላሞች ፡ ኀይለኛነት ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ መተባበርን ፡ ሰጥቷቸው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እስላሞችም ፡ በበኩላቸው ፡ ስለ ፡ ደከሙ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ተመልሰው ፡ ከመለያየትና ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ ከመተላለቅ ፡ ገቡ ። የሉተር ፡ መነሣት ፡ ደግሞ ፡ ባውሮፓ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ የባሰ ፡ ብጥብጥና ፡ ደም ፡ መፋሰስን ፡ አስከተለ ። የሆነው ፡ ሆኖ ፡ ታሪኩን ፡ አጠቃለን ፡ ስናየው ፡ በክርስቲያኖች ፡ ዘንድ ፡ የሆነው ፡ ሁከትና ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ መተላለቅ ፤ የተፈጸመው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ግፍና ፡ ወንጀል ፡ አረመኔዎች ፡ ከነበሩት ፡ ሕዝቦች ፡ የተሻለ ፡ ሆኖ ፡ አይታይም ። እንሆ ፡ በታሪክ ፡ መርማሪዎች ፡ ዘንድ ፡ የተሰጠው ፡ ግምት ፡ ይህ ፡ ነው ። ይህም ፡ ብዙዎቹን ፡ ታሪክ ፡ መርማሪዎች ፡ በክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ላይ ፡ ዘለፋን ፡ ከመናገርና ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ከመካድ ፡ እንዲደርሱ ፡ ለማድረግ ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ አገልግሏቸዋል ።

አንደኛ ፡ ሳይንስን ፡ ከማንኛውም ፡ ነገር ፡ ከሃይማኖትም ፡ ጭምር ፡ በላይ ፡ በማድረግ ፤ ሁለተኛ ፡ ታሪክን ፡ በመመርመር ፤ ሰዎች ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ በመቀበል ፡ ምንም ፡ ራሳቸውን ፡ ከሌሎች ፡ ሕዝቦች ፡ የተሻሉ ፡ አላደረጉትም ፡ በማለት ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ከምን ፡ ምንጭ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ እየተጠራጠሩ ፡ ብዙ ፡ ሊቃውንቶች ፡ በምንም ፡ ነገር ፡ የማያምኑ ፡ ሆነው ፡ ተገኙ ። በዓለም ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ነገሮችና ፡ ሰውም ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ተፈጠሩ ፡ ጨለማ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ደፍረን ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ አንችልም ፡ ማለትን ፡ አመጡ ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ መንፈሳቸው ፡ የሃይማኖት ፡ እምነት ፡ ጨርሶ ፡ የማይገኝበት ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሆነ ።



ሳይንስን ፡ ከሃይማኖት ፡ በላይ ፡ በማስቀመጥ ፡ ቀጥሎ ፡ በሰዎች ፡ አሳብ ፡ ውስጥ ፡ ጥርጣሬ ፡ እንዲፈጠር ፡ በመጨረሻም ፡ እስከ ፡ እግዚአብሔር ክሕደት ፡ እንዲደርስ ፡ በማድረግ ፡ አላፊዎች ፡ ሆነው ፡ የተገኙ ፡ ዋኖቹ ፡ ሰዎች ፡ ዳርዊን ፤ ጎቢኖ ፤ ረናን ፤ ኒችና ፡ ማርክስ ፡ ናቸው ። ከእነሱም ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ እነ ፡ ቮልቴር ፡ ያሉ ፡ አብረው ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሌሎች ፡ ብዙዎች ፡ ይገኛሉ ። ዳርዊን ፡ የሰው ፡ ትውልድ ፡ የመጣው ፡ ከዝንጀሮ ፡ ነው ፡ በማለቱ ፡ ጐቢኖ ፡ በሰው ፡ ዘሮች ፡ መካከል ፡ የበላይና ፡ የበታች ፡ ፍጥረቶች ፡ ይገኛሉ ፡ የሚል ፡ አሳብ ፡ ፈጥሮ ፡ ካንድ ፡ ምንጭ ፡ መምጣታቸውን ፡ በመካዱ ፡ ረናን ፤ ወደ ፡ ክሕደት ፡ የተቃረበ ፡ ጥርጣሬ ፡ በሃይማኖት ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ በመፍጠሩ ፤ በመጨረሻም ፡ ኒችና ፡ ማርክስ ፡ ጨርሶ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መኖር ፡ በመካዳቸው ፤ በዚህ ፡ ረገድ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተፈጠረው ፡ የክሕደት ፡ መንፈስና ፡ ፍጡር ፡ ከፈጣሪው ፡ ጋራ ፡ እየተራራቀና ፡ እየተለያየ ፡ እንዲሄድ ፡ ለተደረገው ፡ መጣጣር ፡ አላፊነቱ ፡ በእነዚህ ፡ በጠራናቸው ፡ ሰዎችና ፡ እነሱንም ፡ በመሰሉት ፡ ላይ ፡ መውደቁ ፡ አልቀረም ።

ታሪካቸውን ፡ በሰፊው ፡ ለማወቅ ፡ ሲፈለግ ፡ ከእነዚህም ፡ በቀር ፡ እግዚአብሔርን ፡ የመካድ ፡ ትምህርት ፡ ካስተማሩት ፡ ሊቃውንት ፡ ጋራ ፡ የላ ፡ ሜትሪን ፡ የዲደሮን ፡ የኦጉስት ፡ ኮምትን ፡ የፉኤርባክንና ፡ የሌሎችንም ፡ ስም ፡ መጨመር ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በቀሩት ፡ አህጉሮች ፡ በቀሩትም ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ ዩኒቬርስቲ ፡ ሲከፈትና ፡ የዘመናችን ፡ ሥልጣኔ ፡ ስትስፋፋ ፡ እነዚህ ፡ ለሰው ፡ መንፈስ ፡ መቅሠፍት ፡ የሆኑ ፡ ትምህርቶች ፡ በሱ ፡ አማካይነት ፡ ይነዛሉ ። አዳም ፡ የደረሰበትን ፡ ርግማን ፡ ለተወላጆቹ ፡ እንዳወረሳቸው ፡ ሁሉ ፡ እንሆ ፡ ይህም ፡ ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ለዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ የምታወርሳቸው ፡ ዕዳ ፡ አበሳ ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ።

ኒችን ፡ የመሰለ ፡ ትልቅ ፡ ፈላስፋ ፡ ከእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ስሕተት ፡ ላይ ፡ መውደቁ ፡ የሚያሳዝን ፡ ነው ። ባጭር ፡ ቃሎች ፡ ሰፊ ፡ ነገር ፡ ለመናገር ፡ የቻለ ፤ የፈላስፋነትንና ፡ የባለቅኔነትን ፡ ሙያ ፡ ደርቦ ፡ የያዘ ፤ አስደናቂ ፡ የሆነ ፡ ያሳብ ፡ ጥልቅነት ፡ የሞላበት ፡ መንፈስ ፡ ያለው ፤ ኒችን ፡ የመሰለ ፡ ሊቅ ፡ ለማግኘት ፡ ያስቸግራል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ምን ፡ ይሆናል ፤ ፍልስፍናው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ክሕደት ፡ የተመረዘ ፡ በመሆኑ ፡ ዋጋውን ፡ ሁሉ ፡ ገደል ፡ ጨምሮታል ። ሆኖም ፡ ኒች ፡ ስለ ፡ ሌሎች ፡ ጉዳዮች ፡ የተናገራቸውን ፡ ቃሎች ፡ አልፈን ፡ አልፈን ፡ ጠቅሰናቸዋል ። ኒች ፡ እንደ ፡ ዐቢይ ፡ ሥራ ፡ ሆኖ ፡

የሚቈጠርለት ፡ «እንዲህ ፡ ሲል ፡ ዛራቱስትራ ፡ ተናገረ» ። ብሎ ፡ የሰየመውን ፡ መጽሐፉን ፡ መጀመሪያ ፡ ጽፎ ፡ ባወጣ ፡ ጊዜ ፡ ንግግሩን ፡ ሁሉ ፡ የዘመኑ ፡ ሰዎች ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ ስላልሰጡት ፡ ከዐሥራ ፡ አራት ፡ መጻሕፍት ፡ በላይ ፡ ለመሸጥ ፡ አልቻለም ። እሱ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የጻፈው ፡ መጽሐፍ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ያውቅ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ማንም ፡ ደራሲ ፡ ቢሆን ፡ እንደ ፡ ጎትና ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ አድርጎ ፡ የጀርመንን ፡ ቋንቋ ፡ በእጁ ፡ ጨብጦ ፡ እያሳመረ ፡ እንደፈቀደው ፡ አድርጎ ፡ ሊሠራበት ፡ የቻለ ፡ አይገኝም ። እንዲያውም ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የተጻፉት ፡ ድርሰቶች ፡ ሁሉ ፡ አንድነት ፡ ቢሰበሰቡ ፡ ዛራቱስትራ ፡ ከተናገራቸው ፡ ዲስኩሮች ፡ አንዱን ፡ እንኳ ፡ አያኽሉም ፡ ሲል ፡ በድፍረት ፡ ተናገረ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ ማመስገን ፡ የማይገባው ፡ ቢሆን ፡ የፋርስን ፡ ሃይማኖት ፡ በጥንት ፡ ዘመን ፡ በመሠረተው ፡ ዛራቱስትራ ፡ በሚባለው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ አድርጎ ፡ ኒች ፡ የተናገራቸው ፡ ቃሎች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ እሱ ፡ የሚለውን ፡ ያኽል ፡ ሆኖ ፡ ባይገኝም ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ተጽፈው ፡ ከተገኙት ፡ ታላላቅ ፡ ድርሰቶች ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ዋጋው ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ እስኪታወቅ ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አስፈልጎታል ። ኒችም ፡ ይህንኑ ፡ ጊዜ ፡ ሲጠብቅ ፡ በሰዎች ፡ ዘንድ ፡ መናቅ ፡ መጠላት ፤ መነቀፍና ፡ ችላ ፡ መባል ፡ ደርሶበታል ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ በራሱ ፡ ዋጋ ፡ የተማመነ ፡ ባይሆን ፡ ኖሮ ፡ ኒች ፡ ሌሎች ፡ መጻሕፍት ፡ ሊጽፍ ፡ ባልቻለም ፡ ነበር ። እሱ ፡ ግን ፡ እምነቱ ፡ የማይናወጥ ፡ በመሆኑ ፡ የደረሰበትን ፡ መናቅ ፡ ሁሉ ፡ መልሶ ፡ እሱም ፡ በበኩሉ ፡ በንቀት ፡ ስለ ፡ ተመለከተው ፡ ድል ፡ አደረገ ፡ እንጂ ፡ ድል ፡ አልሆነም ። በእንዲህ ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ ይገኝ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ የተናገራቸው ፡ ቃሎች ፡ የማይረሱ ፡ ናቸው ። እነሱንም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ ጠቅሰናቸዋል ።

«Il y a en moi quelque chose d'invulnérable, quelque chose qu'on ne peut enterrer et qui fait sauter les rochers: cela s'appelle ma volonté.»

«በኔ ፡ ውስጥ ፡ ሊያቈስሉት ፡ የማይችሉት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ፤ ሊቀብሩት ፡ የማይችሉት ፤ አለቶችን ፡ ፈንቅሎ ፡ የሚጥል ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ፤ እሱም ፡ የኔ ፡ ፈቃድ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል» ።

«Je dois m'habituer à l'antipathie et l'accepter comme mon dû, car je suis incompris. Ce que l'homme ordinaire ne comprend pas, il le hait.»

«የተጠላሁ ፡ መሆኔን ፡ ልለምደውና ፡ እንደ ፡ ድርሻዬ ፡ ቈጥሬ ፡ ልቀበለው ፡ ይገባኛል ፤ ነገሬ ፡ አልገባቸውምና ፤ ተራ ፡ ሰው ፡ የማይገባውን ፡ ነገር ፡ ይጠላዋል» ።



«En vérité, il faut qu'il soit longtemps suspendu au sommet, comme un lourd orage, celui qui doit un jour allumer la lumière de l'avenir.»

«ለመጪው ፡ ዘመን ፡ ብርሃንን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የሚያበራ ፡ ሰው ፡ በውነቱ ፡ እንደ ፡ ታላቅ ፡ ዝናብ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የተንጠለጠለ ፡ ሆኖ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሊቆይ ፡ ያስፈልጋል» ።

«Je suis parmi ce peuple mon propre précurseur, mon propre chant du coq dans les rues obscures.»

«በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ጨለማ ፡ በሆኑት ፡ መንገዶች ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ራሴ ፡ መንገድ ፡ ከፋች ፡ ነኝ ፤ ስለ ፡ ራሴ ፡ የዶሮ ፡ ጩኸት ፡ ነኝ» ። እንደነ ፡ ቮልቴር ፤ ዣን ፡ ዣክ ፤ ሩሶ ፤ ረናን ፡ የመሰሉት ፡ ሊቃውንት ፡ እግዚአብሔር ፡ የለም ፡ ብለው ፡ በሙሉ ፡ አፋቸው ፡ አልተናገሩም ። የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ በትልቅ ፡ ሕንጻ ፡ እንመስለዋለን ። እነዚህ ፡ የጠራናቸው ፡ ሰዎች ፡ መሐንዲሶችን ፡ መስለው ፡ በሕንጻው ፡ ዙሪያ ፡ ከታች ፡ ወደ ፡ ላይ ፤ ከላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ከተመለከቱትና ፡ ከመረመሩት ፡ በኋላ ፡ መሠረቱ ፡ ጥሩ ፡ መሆኑ ፡ አይጠረጠርም ። ነገር ፡ ግን ፡ መስኮቱ ፡ መጥፎ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ ወለል ፡ አርጅቷል ፤ ጣራው ፡ ብላሽ ፡ ነው ፤ በሩ ፡ አያገለግልም ፤ ግድግዳው ፡ ለምንም ፡ አይጠቅምም ፤ ይላሉ ። መስኮቱ ፤ በሩ ፤ ጣራው ፤ ወለሉ ፤ ግድግዳው ፡ የማያገለግል ፡ ብላሽ ፡ ከሆነ ፡ የመሠረቱ ፡ ጥብቅነት ፡ ለምን ፡ ይጠቅማል ? እንደዚህ ፡ አድርገው ፡ ሕንጻው ፡ የተቋቋመባቸውን ፡ ነገሮች ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እያሉ ፡ አፍርሰው ፡ ሲጨርሱ ፡ በመጨረሻ ፡ እነ ፡ ማርክስ ፤ እነ ፡ ኒች ፡ መጥተው ፡ በሰው ፡ መንፈስ ፡ ውስጥ ፡ ታንጾ ፡ የተቋቋመውን ፡ ይህን ፡ የሃይማኖት ፡ ሕንጻ ፡ የፊተኞቹ ፡ ሰዎች ፡ ደፍረው ፡ ያልነኩትን ፡ እነሱ ፡ መሠረቱን ፡ አፈረሱት ። ይህን ፡ ታላቅ ፡ ሕንጻ ፡ ከሰው ፡ መንፈስ ፡ ውስጥ ፡ እንደዚህ ፡ አድርገው ፡ ጨርሰው ፡ ከደመሰሱት ፡ በኋላ ፡ በሱ ፡ ቦታ ፡ ምንም ፡ ሊተኩበት ፡ ስላልቻሉ ፡ የሰውን ፡ መንፈስ ፡ አራዊት ፡ የሚሠለጥኑበትና ፡ የሚፈነጩበት ፡ ባዶ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አደረጉት ። ዣን ፡ ዣክ ፡ ሩሶ ፡ የዘመናችንን ፡ ዕውቀት ፡ (በሞራል ፡ በኩል) ፡ ለማፍረስ ፡ እንጂ ፡ ለመሥራት ፡ ለማቋቋም ፡ አልታደለም ፡ ሲል ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ተፈጸመ ።

እነዚህ ፡ ሊቃውንት ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ ተቃውመው ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ከካዱ ፡ በኋላ ፡ እምነት ፡ የተባለው ፡ ነገር ፡ ጨርሶ ፡ በመወገዱ ፡ መንፈሳቸው ፡ ባዶ ፡ ወና ፡ ሲሆን ፡ ከእንዴት ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ወደቁ ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ፡ ይገልጥልናል ።

ረናን ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ እንስማ ፤

«C'est une pensée d'une effroyable tristesse que le peu de traces que laissent après eux les hommes ceux-là même qui - semblent jouer un rôle principal. Et quand on pense que des millions de millions d'êtres sont nés et sont morts de la sorte, sans qu'il en reste de souvenir, on éprouve le même effroi qu'en présence du néant ou de l'infini. Songez donc à ces misérables d'existences à peine caractérisées qui, chez les sauvages, apparaissent et disparaissent comme les vagues images d'un rêve. Songez aux innombrables générations qui se sont entassées dans ces cimetières de nos campagnes. Mortes, mortes à jamais!»

«ትልልቅ ፡ ሥራ ፡ የፈጸሙ ፡ መስለው ፡ የሚታዩት ፡ ሰዎች ፡ ካለፉ ፡ በኋላ ፡ የሚተዉት ፡ ምልክት ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ በመሆኑ ፡ ይህን ፡ ሲያስቡት ፡ የሚያስፈራ ፡ ሐዘን ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ በብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሚሊዮኖች ፡ የሆኑ ፡ ፍጡሮች ፡ ምንም ፡ መታሰቢያ ፡ ሳይተዉ ፡ የተወለዱና ፡ የሞቱ ፡ መሆናቸውን ፡ ስናስበው ፡ ከኢምንት ፡ ወይም ፡ ከዘለዓለም ፡ ፊት ፡ በመገኘት ፡ የሚደርስብንን ፡ የመሰለ ፡ ፍርሀት ፡ ይሰማናል ። በሕልም ፡ ውስጥ ፡ የሚታዩትን ፡ መልካቸው ፡ የማይለይ ፡ ሥዕሎች ፡ መስለው ፡ የሚጠፉትን ፤ ባውሬነት ፡ ኑሮ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩትን ፡ የሚለዩበት ፡ ጠባይ ፡ የሌላቸውን ፡ እነዚህን ፡ ምስኪኖች ፡ የሆኑትን ፡ ፍጥረቶች ፡ አስቧቸው ። በየገጠሮቻችን ፡ በሚገኙት ፡ የመቃብር ፡ ቦታዎች ፡ የተከማቹትን ፡ ተቈጥረው ፡ የማያልቁትን ፡ ትውልዶች ፡ አስቧቸው ፡ የሞቱትን ፤ እስከ ፡ መቼም ፡ ሞተው ፡ የቀሩትን !»

ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ ኒች ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ እንመልከት ፤

Le doute me dévore, j'ai tué la loi, la loi me fait horreur comme le cadavre au vivant.

«ጥርጣሬ ፡ በልቶ ፡ ጨረሰኝ ፤ ሕግን ፡ ገደልኳት ፤ በሕይወት ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ሬሳን ፡ እንደሚጠላ ፡ ሁሉ ፡ እኔም ፡ በዚሁ ፡ መጠን ፡ ሕግን ፡ ጠላኋት» ።

ያውሮፓ ፡ ሊቃውንት ፡ በደግም ፡ ሆነ ፡ በክፉ ፡ በኩል ፡ ለሠሩት ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ምንጩ ፡ ተጠራጣሪነታቸው ፡ ነው ። ኒች ፡ «ጥርጣሬ ፡ በልቶ ፡ ጨረሰኝ» ፡ ብሎ ፡ ቢናገር ፡ አይፈረድበትም ። እነ ፡ ሞንቴኝ ፤ እነ ፡ ዴካርት ፤ የቀሩትም ፡ ሊቃውንትና ፡ ፈላስፎች ፡ መሣሪያ ፡ አድርገው ፡ የሠሩበት ፡ ጥርጣሬን ፡ ነው ። ጥርጣሬ ፡ ለማንኛውም ፡ ዕውቀት ፡ በእነሱ ፡ ዘንድ ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ። ከዚህ ፡ በፊት ፡ የተማርነው ፤ ያወቅነው ፤ የተረዳነው ፤ ከትውልድ ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ እየተላለፈ ፡ እስከ ፡



እኛ ፡ ድረስ ፡ የመጣው ፤ የምንተማመንበት ፡ የተረጋገጠ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ብለን ፡ የተቀበልነው ፤ የዕውቀታችንና ፡ የጥበባችን ፤ የትምህርታችንና ፡ የሥልጣኔያችን ፡ መሠረት ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በእውነት ፡ ትክክለኛ ፡ መሆኑን ፡ በምን ፡ እናውቀዋለን ? በልማድ ፡ መሠረት ፡ ርግጠኛ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ የተባለውን ፡ ሁሉ ፡ እንዴት ፡ ለማመን ፡ ይቻላል ? ከኛ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ሊቃውንት ፤ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ተገልጦላቸዋል ፡ በማለት ፡ እነሱ ፡ የተናገሩትንና ፡ የጻፉትን ፡ መቀበል ፡ ሞኝነት ፡ አይሆንብንም ፡ ወይ ? እንሆ ፡ መንፈሳቸው ፡ በጥበብና ፡ በውቀት ፡ መስከር ፡ ከጀመረበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ያውሮፓ ፡ ሊቃውንት ፡ ከፊታቸው ፡ የተደቀኑት ፡ የጥርጣሬ ፡ ጥያቄዎች ፡ እነዚህ ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ የጠቀስናቸው ፡ ናቸው ። በሳይንስና ፡ በቴክኒክ ፡ በኩል ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ እየመረመሩ ፡ እንዲገልጡ ፡ ለማድረግ ፡ ይህ ፡ ጥርጣሬ ፡ በጣም ፡ ረድቷቸዋል ። በሃይማኖትና ፡ በሞራል ፡ በኩል ፡ ግን ፡ በእነሱ ፡ በኩል ፡ ለተፈጠረው ፡ ጉድለትና ፡ ጥፋት ፡ ምንጩ ፡ ይህ ፡ ተጠራጣሪነታቸው ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ጥበባቸው ፡ በሁለት ፡ በኩል ፡ ስለት ፡ እንዳለው ፡ ሰይፍ ፡ ሆኖ ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ሲጠቅም ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ሰውን ፡ የሚያበላሽ ፡ ሆኗል ።

ቴይሃርድ ፡ ደ ፡ ሻርደ ፡ (Teilhard de Chardin) የሚባለው ፡ ትልቅ ፡ ሊቅ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የተናገረው ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የጠቀስነው ፡ ቃል ፡ የማይረሳ ፡ ነው ።

«Le doute est le commencement de la science; qui ne doute rien n'examine rien; qui n'examine rien ne découvre rien; qui ne découvre rien est aveugle et demeure aveugle.»

«ጥርጣሬ ፡ የሳይንስ ፡ መጀመሪያ ፡ ነው ፤ ምንም ፡ የማይጠራጠር ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ አይመራመርም ፤ ምንም ፡ የማይመራመር ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ አያገኝም ፤ ምንም ፡ የማያገኝ ፡ ሰው ፡ ዕውር ፡ ነው ፤ ዕውር ፡ ሆኖ ፡ ይቀራል» ።

አሁን ፡ ደግሞ ፡ ዶስቶዬቭስኪ ፡ «ካራማዞብ ፡ ወንድማማቾች» ፡ በተባለው ፡ መጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ የሚናገረውን ፡ ቃል ፡ እናስተውለው ። ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ዶስቶዬቭስኪ ፡ ከሓዲ ፡ አለመሆኑን ፡ ማሰብ ፡ አለብን ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ በሱ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ የምንጠቅሰው ፡ በዘመኑ ፡ የነበረውን ፡ የጥርጣሬ ፡ መንፈስ ፡ ስለሚገልጥልን ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህ ፡ ቃል ፡ በዶስቶዬቭስኪ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ላንድ ፡ ካህን ፡ የተናገረው ፡ ነው ። «መጭው ፡ ሕይወት ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ምስጢር ፡ ነው ። ትርጉሙን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አያውቀውም ፡ እርስዎ፡

የሰውን ፡ ነፍስ ፡ የሚያውቋትና ፡ የሚያድኗት ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ይስሙኝ ። ርግጥ ፡ ነው ፡ በሙሉ ፡ ይመኑኝ ፡ ብዬ ፡ ልጠይቅዎት ፡ አልደፍርም ። ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ የምናገረው ፡ በቀላልነት ፡ አለመሆኑን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አክብሮት ፡ ባለበት ፡ አኳኋን ፡ አረጋግጥልዎታለሁ ። ከሞት ፡ በኋላ ፡ ያለውን ፡ ሕይወት ፡ ሳስበው ፡ እስከ ፡ መጨነቅ ፡ ድረስ ፤ እስከ ፡ መሸበር ፡ ድረስ ፡ እናወጣለሁ» ።

ከሃይማኖት ፡ ጋራ ፡ የሚፋለሱና ፡ ሰውን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሚያርቁ ፡ በምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ውስጥ ፡ መርዝ ፡ ሆነው ፡ የተነዙት ፡ ትምህርቶች ፡ ግባቸው ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ የስማቸው ፡ አጠራር ፡ ብዙ ፡ ነው። ዴኢስም ፤ ፓንቴኢስም ፤ ራሲዮናሊስም ፤ ኤግዚስታንሲያሊስም ፤ ፖዚቲቢስም ፤ ማቴሪያሊስም ፡ ዲያሌክቲክ ፤ ኤቮሊሲዮኒስም ፤ ሲያንቲስም ፡ ተብለው ፡ በመጠራት ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ስያሜያቸው ፡ የተለያየ ፡ ቢመስል ፡ ዞረው ፡ ዞረው ፡ ሁሉም ፡ በሰው ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ የጥርጣሬን ፡ የክሕደትን ፡ መንፈስ ፡ በማሳደር ፡ የሃይማኖቱን ፡ ግለት ፡ የሚያቀዘቅዙ ፡ ናቸው ።

እንሆ ፡ መመራመር ፡ የሚያበዙ ፡ ሊቃውንት ፡ ሰዎች ፡ ለምን ፡ ይወለዳሉ ? ለምን ፡ ይሞታሉ ? ሞተውስ ፡ ወዴት ፡ ይሄዳሉ ? በማለት ፡ እግዚአብሔር ፡ በሃይማኖት ፡ የገለጠውን ፡ ትምህርት ፡ በመከተል ፡ ፈንታ ፡ እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ በሳይንስ ፡ መንገድ ፡ ሊመረምሩት ፡ ይፈልጋሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ጉዳይ ፡ ትርጉም ፡ ሊያገኝ ፡ የሚችለው ፡ በሃይማኖት ፡ በኩል ፡ ለሰው ፡ የተገለጠውን ፡ ትምህርት ፡ በማመን ፡ ብቻ ፡ ነው ። ሃይማኖትና ፡ እምነት ፡ ከሌሉ ፡ ይህንን ፡ ምስጢር ፡ ዘልቆ ፡ ማን ፡ ሊያውቀው ፡ ይችላል ? እምነት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ኅሊናውን ፡ ፍርሀትና ፡ ሽብር ፡ አያናውጡትም ። እምነት ፡ በጐደለች ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ የሚከተለውን ፡ ሽብር ፡ ሳይንስ ፡ መድኀኒት ፡ ልታገኝለት ፡ አትችልም ። እንደ ፡ ኒች ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ የለም ፡ ዐሥርቱ ፡ ቃላት ፡ የተባለውም ፡ ሕገ ፡ ሙሴ ፡ ውሸት ፡ ነው ። ብሎ ፡ ሕግን ፡ ከገደላት ፡ በኋላ ፡ ኅሊናውን ፡ በልቶ ፡ የሚጨርሰው ፡ ሽብር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እሱ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ ሁሉ ፡ ጥርጣሬ ፡ አይደለም ። ሃይማኖት ፡ ከተከዳች ፡ በኋላ ፡ ነፍስን ፡ የሚማርኳት ፡ ፍርሀትና ፡ ሐዘን ፡ ለሰው ፡ የቁም ፡ ገሃነመ ፡ እሳት ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ። ለምሳሌ ፤ ረናን ፡ እነዚህ ፡ በየዘመኑና ፡ በየአህጉሩ ፡ በብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ በሕልም ፡ የምናየውን ፡ ቅዠት ፡ መስለው ፡ እየተወለዱ ፤ እየሞቱ ፤ እየተወለዱ ፤ እየሞቱ ፡ ያልፋሉ ። የሚፈጽሙት ፡ ተግባር ፡ ምንድነው ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ የሚሄዱት ? ይህንን ፡ በሳይንስ ፡ በኩል ፡ እንመርምረው ፡ ብለን ፡ ብንነሣ ፡ የማይዘለቅ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ልንደርስበት ፡ አንችልም ። በሃይማኖት ፡ በኩል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡



ሆነ ፡ ግን ፡ መልሱን ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስና ፡ በወንጌል ፡ እናገኘዋለን ። ረናን ፡ እንደሚለው ፡ የእነዚህ ፡ ሰዎች ፡ መፈጠር ፡ ለሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ መረጋገጫ ፡ መሰላል ፡ ሆኖ ፡ ለማገልገል ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የሚገኘውን ፡ ኒች ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ስንሰማ ፡ ኒች ፡ ሕግን ፡ ከገደላት ፡ በኋላ ፡ የደረሰበትን ፡ አሳብ ፡ ይገልጥልናል ። «Tu ne déroberas point. Tu ne tueras point.» Ces paroles jadis étaient appelées saintes, devant elles l'on pliait les genoux; l'on baissait la tête et l'on ôtait ses souliers. Mais je vous demande: où y eût-il jamais meilleurs brigands et meilleurs assassins dans le monde, que les brigands et les assassins provoqués par ces saintes paroles.»

«አትስረቅ ፤ አትግደል !» እነዚህ ፡ ቃሎች ፡ በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ የተቀደሱ ፡ ናቸው ፡ ተብለው ፡ ይጠሩ ፡ ነበር ። በእነሱ ፡ ፊት ፡ ሰዎች ፡ ይንበረከካሉ ። ራሳቸውን ፡ ይደፉላቸዋል ፤ ጫማቸውንም ፡ ያወልቁላቸው ፡ ነበር ። እኔ ፡ ግን ፡ እጠይቃችኋለሁ ፤ እነዚህ ፡ የተቀደሱ ፡ ቃሎች ፡ ካነሣሷቸው ፡ ወንበዴዎችና ፡ ነፍስ ፡ ገዳዮች ፡ የተሻሉ ፡ ወንበዴዎችና ፡ የተሻሉ ፡ ነፍስ ፡ ገዳዮች ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የተገኙበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፡ ወይ ? » እንሆ ፡ በኒች ፡ አስተያየት ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ወንበዴዎችንና ፡ ነፍስ ፡ ገዳዮችን ፡ ያነሣሣና ፡ እንዲፈጠሩ ፡ ያደረገ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ። ነገር ፡ ግን ፡ ጌታ ፡ ከተናገራቸው ፡ ቃሎች ፡ አንዳንዶቹን ፡ ስናስታውስ ፡ እነ ፡ ኒች ፡ ከፈጠሩት ፡ ስሕተት ፡ ላይ ፡ እንዳንወድቅ ፡ ያድኑናል ። «በነቢዩ ፡ በዳንኤል ፡ የተነገረውን ፡ የጥፋትን ፡ ርኵሰት ፡ በተቀደሰችው ፡ ስፍራ ፡ ቆሞ ፡ ሲታይ ፡ አንባቢ ፡ ያስተውል ፤ ማቴ ፡ ም ፡ ፳፬ ፡ ቍ ፡ ፲፭ ።»

እንደ ፡ ኒች ፡ በተቀደሰው ፡ በክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ላይ ፡ ካንደበት ፡ የሚወጣ ፡ ጥፋትና ፡ ርኵሰት ፡ የሚታይበትን ፡ ቃል ፡ የተናገሩ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። እነ ፡ ኒችን ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ቃል ፡ እንዲናገሩ ፡ ያደረጉዋቸው ፡ ንግዳቸውን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ለማስፋፋትና ፡ የቅኝ ፡ አገር ፡ ግዛታቸውን ፡ በሰፊው ፡ ለመዘርጋት ፡ ሲሉ ፡ የወንበዴነትንና ፡ የነፍስ ፡ ገዳይነትን ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩ ፡ የኖሩ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ነን ፡ የሚሉ ፡ ያውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ ናቸው ። ሆኖም ፡ ሰዎቹ ፡ ይወቀሡበት ፡ እንጂ ፡ ሃይማኖትን ፡ የሚያስድብ ፡ አልነበረም ። በኀጢአት ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡ መጨመር ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ በሞራል ፡ በኩል ፡ ተሠርቶና ፡ ተቋቍሞ ፡ የሚገኘው ፡ ሁለት ፡ ሺሕ ፡ ዘመን ፡ ሙሉ ፡ ከተደከመበት ፡ በኋላ ፡ የተመረተው ፡ የሥልጣኔ ፡ ሰብል ፡ ገደል ፡ እንደ ፡ ገባና ፡ እንደ ፡ ተበላሸ ፡ ሆኖ ፡ ተቈጠረ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ያውሮፓ ፡ ሊቃውንት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ እየተራራቁ ፡ መሄ
ድን ፡ ያመጡት ፡ የሳይንስ ፡ ዕውቀት ፡ እየተገለጠላቸው ፡ መሄድ ፡ ከጀ
መረ ፡ ወዲህ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሳይንስና ፡ ቴክኒክ ፡ በሰዎች ፡ ልብ ፡
ውስጥ ፡ ትዕቢት ፡ እንዲፈጠር ፡ ሲያደርጉ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ከሀ
ብትና ፡ ከብልጽግና ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መዘዞችን ፡ ጐትተው ፡ አም
ጥተዋል ። ስለዚህ ፡ ድንቅነታቸው ፡ የሚያስመካ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ የፈጠ
ሩት ፡ ጦስ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብንዘነጋው ፡ ጉዳዩን ፡ በሙሉ ፡ ሳይሆን ፡
በጐደሎ ፡ መመልከት ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠርብናል ። ሳይንስና ፡ ቴክኒክ ፡ ኢንዱ
ስትሪን ፡ ወልደው ፡ ዓለምን ፡ በሀብትና ፡ በተድላ ፡ ሲያጥለቀልቁት ፡ በታ
የ ፡ ጊዜ ፡ የድንቍርናና ፡ የመከራ ፡ ዘመን ፡ አልፎ ፡ ሰላምና ፡ ጥበብ ፡ የነገ
ሡበት ፡ ዘመን ፡ ተከፈተልን ፡ ብለው ፡ ሰዎች ፡ ደስ ፡ አላቸው ። በኋላ ፡ ግን ፡
በየፋብሪካው ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ግፍ ፡ ስለ ፡ ተቀበሉ ፡ መብታቸውን ፡
ለመጠየቅ ፡ የሚያደርጉት ፡ ትግል ፡ እየጠነከረ ፡ በመሄዱ ፡ በየከተማው ፡
ውስጥ ፡ የሆነውም ፡ የሕዝብ ፡ መከማቸት ፡ ሁከትና ፡ ብጥብጥ ፡ እየፈ
ጠረ ፡ የሕዝቡንም ፡ ቍጥር ፡ እየጨመረ ፡ እንዲሄድ ፡ እያደረገ ፡ ጸጥታንና ፡
ሰላምን ፡ ነሣቸው ። በዓለም ፡ መንግሥታትና ፡ በዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ መካ
ከል ፡ የሚገኘውም ፡ የኤንተርናሲዮናል ፡ ግንኙነት ፡ እየተበላሸና ፡ እየተ
መረዘ ፡ ሄደ ። ይጠበቅ ፡ በነበረው ፡ ሲሳይና ፡ ሰላም ፡ ቦታ ፡ ሁከትና ፡ ጦር
ነት ፡ ተወለዱ ። ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ኢንዱስትሪ ፡
ነው ። በኢንዱስትሪ ፡ ምክንያት ፡ የደረሰባቸውን ፡ ጣጣ ፡ ለማወቅ ፡ ሲፈ
ለግ ፡ መግለጫና ፡ ምሳሌ ፡ ሆኖ ፡ ሊያገለግለን ፡ የቻለ ፡ ጎት ፡ የጻፈው ፡
«ተማሪ ፡ ጠንቋይ» ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመው ፡ ድርሰት ፡ ነው ። አንድ ፡ ጠን
ቋይ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከቤቱ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ በሄደበት ፡ ጊዜ ፡ አሽ
ከሩ ፡ ጌታው ፡ የሚያደርገውን ፡ ነገር ፡ ይመለከት ፡ ነበርና ፡ እሱም ፡ እን
ዳየው ፡ ለማድረግ ፡ አስቦ ፡ በቃሉ ፡ አጥንቶ ፡ የነበረውን ፡ ድግምት ፡
ደገመ ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ መጥረጊያው ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ውሃ ፡ እየቀዳ ፡
ገላ ፡ መታጠቢያ ፡ በሆነው ፡ ገንዳ ፡ ውስጥ ፡ እያመላለሰ ፡ ይሞላ ፡ ጀመር ።
ነገር ፡ ግን ፡ እንዲቆም ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻልበትን ፡ ድግምት ፡ ተማሪው ፡
ባለማወቁ ፡ መጥረጊያው ፡ ወሃውን ፡ በላይ ፡ በላዩ ፡ እየጨመረ ፡ ቤቱን ፡
በውሃ ፡ አጥለቀለቀው ። አሽከር ፡ ይህን ፡ በማየት ፡ ተሸብሮ ፡ ወዲያና ፡
ወዲህ ፡ ሲሯሯጥና ፡ ሲርበተበት ፡ ባለቤት ፡ ደርሶ ፡ አሽከሩ ፡ ያላዋቂ ፡
ያበላሸውን ፡ የጥንቈላ ፡ ተግባር ፡ በደንብ ፡ ስላገባው ፡ መጥረጊያው ፡
ወደ ፡ ነበረበት ፡ ቦታ ፡ ተመለሰ ። አውሮፓውያንም ፡ እንደዚሁ ፡ ጥበቡ ፡
ተሸፍኖ ፡ እንደ ፡ ተሰወረ ፡ ይኖር ፡ የነበረውን ፡ የመኪና ፡ ዕውቀት ፡
ፈትተው ፡ ስለ ፡ ለቀቁት ፡ በመካከላቸው ፡ ሁከትን ፡ በፈጠረ ፡ ጊዜ ፡ ሊያቆ
ሙት ፡ አልቻሉም ።



ብልኖች ፡ የሆኑት ፡ ሊቃውንቶቻቸው ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ በመመልከት ፡
ተስፋ ፡ ስለ ፡ ቈረጡ ፡ ይህቺን ፡ የተሳሳተች ፡ ሥልጣኔ ፡ እየሸሹ ፡ እውነት ፡
ወዴት ፡ ነው ፡ ያለችው ? በማለት ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ እየተሰደዱ ፡ ይፈ
ልጓት ፡ ጀመር ። አብዛኞቹም ፡ በዚህ ፡ ሽሽት ፡ ዐይናቸውና ፡ እግራቸው ፡
ወደ ፡ ህንድ ፡ አገር ፡ ተመሩ ። የህንዶችን ፡ ፍልስፍና ፡ ከሁሉም ፡ የበ
ለጠች ፡ ሆና ፡ አገኟት ። ሰው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እየተመላለሰ ፡ ከተወለደ ፡ በ
ኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ወደ ፡ ኒርቫና ፡ ይገባል ፡ የሚለውን ፡ የሚያጠግብ ፡ ሆኖ ፡
ተመለከቱት ። ግማሾቹ ፡ ፓንቴኢስም ፡ ብለው ፡ አዲስ ፡ ስም ፡ ሰጡት ።
ኒችም ፡ ዘለዓለም ፡ መደጋገም ፡ መመላለስ ፡ (L'éternel retour) የሚል ፡ አ
ሳብ ፡ ፈጠረ ። ማዳም ፡ ብላቫትስኪ ፡ (Blavatsky) የተባለችው ፡ የመስኮብ ፡
ተወላጅ ፡ የሆነች ፡ ሴት ፡ ቴዎዞፊ ፡ (Théosophie) የተባለ ፡ ማኅበር ፡ ባቆ
መች ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በደስታ ፡ ተቀበሏት ። ቴዎዞፊ ፡ የተባለው ፡
በማኅበር ፡ ስም ፡ የተቋቋመው ፡ ይህ ፡ ሃይማኖት ፡ ወይም ፡ እምነት ፡ ዐላ
ማው ፡ በግዙፍ ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ሥልጣኔያችንን ፡ በመመሥረታችን ፡ ተሳ
ስተናል ። የመንፈሳችንንና ፡ የነፍሳችንን ፡ ኀይል ፡ አሠልጥነን ፡ ብንሠራ
በት ፡ ማነኛውንም ፡ ጥበብ ፡ ለመፈጸም ፡ እንችላለን ። ኀይላችን ፡ በመ
ኪና ፡ ዘዴ ፡ መቋቋሙ ፡ ቀርቶ ፡ የመንፈሳችንን ፡ ጕልበት ፡ ቢመረኰዝ ፡
ማንኛውንም ፡ ተአምር ፡ ሊሠራ ፡ ይችላል ፡ የሚል ፡ እምነት ፡ ነው ።

ይህቺ ፡ ሴት ፡ ወደ ፡ ህንድ ፡ አገር ፡ ሄዳ ፡ የህንዶች ፡ ሃይማኖት ፡
ምስጢር ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስቦ ፡ ከሚገኝበት ፤ መተትና ፡ አስማት ፤ ትንግር
ትና ፡ ራእይ ፡ ከሞሉበት ፤ የበቁ ፡ ሰዎች ፡ ከሚኖሩበት ፡ ቲቤት ፡ ከሚባ
ለው ፡ አገር ፡ ገብታ ፡ ጥበቡን ፡ ከምንጩ ፡ ከተማረችው ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡
ተአምር ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ጥንቈላ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ እያሳ
የች ፡ ሰዎችን ፡ ስታስደንቃቸው ፡ ኖራለች ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ብዙ ፡ ያው
ሮፓ ፡ ሊቃውንት ፡ መንፈሳቸው ፡ ወደ ፡ ህንድ ፡ ሃይማኖትና ፡ ፍልስፍና ፡
እየተሳበ ፡ መሄዱን ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ አላቋረጠም ። ህንድ ፡ ስለ ፡ ሥል
ጣኔ ፡ ጉዳይ ፡ በበኩሏ ፡ ያደረገችው ፡ ርዳታ ፡ አለ ። ይኸውም ፡ እንደሚከተ
ለው ፡ ነው ። የሕክምናን ፡ ትምህርት ፡ የሚከታተሉ ፡ ሰዎች ፡ የሰውን ፡ ሆድ ፡
ቀደው ፡ በአካላቱ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ሕዋሳቶች ፡ ማለት ፡ እነ ፡ አንጀትን ፤
ሳንባን ፤ ጕበትን ፤ ጣፊያን ፤ ልብን ፡ እያገላበጡ ፡ ሳይፈሩና ፡ ሳይጠየፉ ፡ በመ
መርመር ፡ አናቶሚን ፡ ይማራሉ ። ፈላስፎችና ፡ ሊቃውንትም ፡ እንደዚሁ ፡
የሥልጣኔን ፡ ሆድ ፡ ቀደው ፡ ሕዋሳቶቿ ፡ የሆኑትን ፡ እነ ፡ ሞራልን ፤
ሃይማኖትን ፤ ኤኮኖሚን ፤ ጦርነትን ፤ የሕዝብና ፡ የመንግሥት ፡ አስተዳ
ደርን ፤ የሕዝቦችና ፡ የመንግሥታት ፡ ግንኙነትን ፤ የትምህርት ፡ አሰጣ
ጥን ፤ ጠልቀው ፡ እየመረመሩ ፡ በእነዚህ ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡

ስሕተቶችና ፡ ጉድለቶች ፡ ሳይፈሩና ፡ ሳይጠየፉ ፡ ያጠኗቸዋል ። ይህንንም ፡ የሚያደርጉት ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ እንዴት ፡ ባለ ፡ ዘመንና ፡ እንዴት ፡ ባለ ፡ ሥልጣኔ ፡ ውስጥ ፡ የምንኖር ፡ መሆናችንን ፡ ለማወቅና ፡ በውስጡ ፡ ያለውን ፡ በሽታ ፡ ፈልጎ ፡ ለማግኘት ፡ ነው ።

የዓለም ፡ ፈላስፎችና ፡ ሊቃውንት ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ ሲፈጽሙ ፡ ህንድ ፡ ትልቅ ፡ ርዳታ ፡ ሰጥታለች ። ምክንያቱም ፡ የዚህን ፡ ሥራ ፡ ድካም ፡ ሊካፈሉ ፡ የቻሉ ፡ አምስት ፡ ሰዎች ፡ ለማበርከት ፡ በመቻሏ ፡ ነው ። እነሱም ፡ ራማ ፡ ክሪሽና ፤ ቪቬካናንዳ ፤ ጋንዲ ፤ ራቢንድራናት ፡ ታጐር ፤ አሮቢንዶ ፤ ጐዝ ፡ ናቸው ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ሰፊ ፡ ቦታ ፡ ይዘው ፡ ይገኛሉ ። ሊታረቁና ፡ ሊገናኙ ፡ የማይችሉ ፡ መስለው ፡ ይታዩ ፡ የነበሩት ፡ ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔና ፡ ምሥራቃዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ የሚቀራረቡበትንና ፡ የሚስማሙበትን ፡ መንገድ ፡ ለማግኘት ፡ እነዚህ ፡ የህንድ ፡ ተወላጆች ፡ በጣም ፡ ረድተዋል ።

ያም ፡ ሆነ ፡ ያ ፡ ጉዳዩ ፡ ቀጥሎ ፡ ካለው ፡ ነገር ፡ ሊዘል ፡ አይችልም ። ሼክስፒር ፡ «To be or not to be, that is the question.» «መኖር ፡ ወይም ፡ አለመኖር ፤ ጉዳዩ ፡ እንሆ ፡ ይህ ፡ ነው» ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ ሁሉ፡ አሁንም ፡ ዋናው ፡ ጉዳይ ፡ «እግዚአብሔር ፡ አለ ፡ ወይስ ፡ የለም ?» የሚል ፡ ነው ።

እግዚአብሔር ፡ ከሌለ ፡ እነ ፡ ማርክስ ፡ እንደሚሉት ፡ ሁሉ ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ምድራዊ ፡ በሆነ ፡ ነገር ፡ ይህም ፡ ማለት ፡ በሥራ ፤ በሀብት ፤ በሳይንስ ፤ በጠቅላላው ፡ በማቴሪያሊስም ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ሆኖ ፡ በመንፈሳዊ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ትርጉሙ ፡ ባዶና ፡ ከንቱ ፡ ሆኖ ፡ ይቀራል ።

እግዚአብሔር ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ለሚያምን ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ነገሩ ፡ በሙሉ ፡ ተለውጦ ፡ ሌላ ፡ ይሆናል ። በሳይንስ ፤ በቴክኒክ ፤ በጥበብና ፡ በዕውቀት ፤ በትምህርትና ፡ በሥልጣኔ ፡ ተሠርቶ ፡ የምናየው ፡ የሠለጠኑት ፡ የዓለም ፡ ኀያላን ፡ የሚመኩበት ፡ ሀብትና ፡ ገናናነት ፤ ዋጋ ፡ የሌለው ፤ ሰውን ፡ ወደ ፡ ምድራዊ ፡ ነገር ፡ እየሳበ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ የሚጐዳ ፡ እንጂ ፡ የማይደግፍ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ሙሴ ፡ በደብረ ፡ ሲና ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ እየተነጋገረ ፡ የዐሠርቱ ፡ ቃላትን ፡ ሕግ ፡ ተቀብሎ ፡ ሲመለስ ፡ ሕዝበ ፡ እስራኤል ፡ ለወርቅ ፡ ጥጃ ፡ ሲሰግዱ ፡ እንዳገኛቸው ፡ ሁሉ ፡ ዛሬም ፡ የሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ የሚያደርጉት ፡ ይህንኑ ፡ የመሰለ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ራዲዮ ፤ ሲኒማ ፤ አቶሞቢል ፤ አኤሮፕላን ፡ ቴሌቪዥን ፤ ባቡር ፤ መርከብ ፤ ይህን ፡ የመሰሉ ፡ ገንዘብና ፡ ሀብት ፡



የሚያፈራቸው ፡ የጥበብ ፡ መሣሪያዎች ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ የነፍሱን ፡ ነገር ፡ እየረሳ ፡ ለሀብት ፡ እንዲሰግድ ፡ የሚያደርጉ ፡ በመሆናቸው ፡ የወርቅ ፡ ጥጃን ፡ ጣዖት ፡ ቦታ ፡ ወርሰው ፡ የሰውን ፡ ልብ ፡ ለመማረክ ፡ የተፈጠሩ ፡ የሰይጣን ፡ መሣሪያዎች ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ ነው ። በማለዳ ፡ የንጋት ፡ ውጋጋን ፡ ሲታይ ፡ ጨለማ ፡ የደረሰበት ፡ ስፍራ ፡ ጠፍቶ ፡ እንዲወገድ ፡ ሁሉ ፡ እነዚህ ፡ ሥልጣኔ ፡ ያፈራቻቸው ፡ ጥበቦችም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸው ፡ ሆነው ፡ ይደመሰሳሉ ። ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ከእነሱ ፡ በኩል ፡ የሚመጣው ፡ ጉዳት ፡ ለነፍሱ ፡ መጥፊያዋ ፡ ሆኖ ፡ እንዳይገኝ ፡ መጠንቀቅ ፡ ይኖርበታል ። እነዚህን ፡ ጥበቦች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ክብር ፡ መግለጫና ፡ ለነጻነቱ ፡ መጠበቂያ ፡ የሚያገለግሉ ፡ መሣሪያዎች ፡ ሆነው ፡ እንዲገኙ ፡ እንጂ ፡ ነፍሱን ፡ ማርከው ፡ ወደ ፡ ኵነኔ ፡ እንዳይጥሉት ፡ ማሰብ ፡ ግዴታ ፡ ይሆንበታል ። ዓለምን ፡ በሙሉ ፡ አግኝተኸ ፡ ነፍስኸ ፡ ብትጠፋ ፡ ለምን ፡ ይጠቅመኻል ፡ ተብሎ ፡ በወንጌል ፡ የተጻፈው ፡ ቃል ፡ ከዚህ ፡ አደጋ፡ እንዲድን ፡ የተሰጠው ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ መሆኑን ፡ ማስታወስ ፡ ይኖርበታል ።

# የዓለም ፡ መንግሥታትና ፡
# የዓለም ፡ ሕዝቦች ።

ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ በ፫ ፡ ክፍል ፡ ይከፈላሉ ። አንደኛ፡
የሠለጠኑ ፤ ሁለተኛ ፡ ያልሠለጠኑ ፤ ሦስተኛ ፡ በመሠልጠን ፡ ላይ ፡ የሚገኙ ፡
ናቸው ። ሠለጠኑ ፡ የሚባሉት ፡ በሳይንስና ፡ በቴክኒክ ፡ በጣም ፡ ገፍተው፡
ማንኛውንም ፡ ለኑሮ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በመኪና ፡ የሚ
ያከናውኑና ፡ በኢንዱስትሪ ፡ የተራቀቁ ፡ በመሆናቸው ፡ በጦር ፡ ኀይልና ፡
በሀብት ፡ በኩል ፡ ከሌሎች ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ በጣም ፡ የበለጡ ፡
ሆነው ፡ ይገኛሉ ። እነሱም ፡ አሜሪካ ፤ መስኮብ ፤ እንግሊዝ ፤ ጀርመን ፤
ፈረንሳይ ፡ የቀሩትም ፡ ያውሮፓ ፡ ሕዝቦች ፡ ናቸው ። በሠለጠኑትና ፡ ባል
ሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሆኖ ፡
ሳለ ፡ ይህ ፡ ልዩነት ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ እየተራራቀ ፡ መሄዱን ፡ በመቀጠል ፡
ላይ ፡ ይገኛል ። ምክንያቱም ፡ ቀድመው ፡ የተራመዱት ፡ ሕዝቦች ፡ እርም
ጃቸው ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እየገፋ ፡ እንዲሄድ ፡ የሚረዷቸው ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡
ሲያገኙ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀሩት ፡ ሕዝቦች ፡ ደግሞ ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ እርም
ጃቸው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንዲጐተት ፡ የሚያደርግ ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕንቅፋ
ትና ፡ ችግር ፡ ስለሚገጥማቸው ፡ ነው ። እነሱም ፡ ሁኔታቸውን ፡ ከእነሱ ፡
በላይ ፡ ካሉት ፡ ሕዝቦች ፡ ሁኔታ ፡ ጋራ ፡ ሲያስተያዩት ፡ ድኽነታቸውና ፡
ደካማነታቸው ፡ በጣም ፡ ይሰማቸዋል ። ለምሳሌ ፤ ቲቦር ፡ ሜንድ ፡ የተባ
ለው ፡ ደራሲ ፡ በሀብታሞችና ፡ በድኾች ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡
ልዩነት ፡ ለማወቅ ፡ ስንፈልግ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ እንድንገነዘብ ፡
ያሳስበናል ። አሜሪካኖች ፡ ባገራቸው ፡ ውስጥ ፡ ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ ሺሕ ፡
በላይ ፡ የሲኒማ ፡ ቤቶች ፡ ሲኖሯቸው ፡ የሺና ፡ ሕዝብ ፡ (ቍጥሩ ፡ ከሦስት ፡
ጊዜ ፡ በላይ ፡ ከአሜሪካ ፡ ሕዝብ ፡ የሚበልጥ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ) ፡ በየሆቴ
ታሉ ፡ ለሕዝቡ ፡ ተዘጋጅተው ፡ የሚገኙት ፡ አልጋዎች ፡ በጠቅላላው ፡
ዐሥራ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። በኢንዱስትሪ ፡ በሳይንስና ፤ በቴ
ክኒክ ፡ የመጀመሪያውን ፡ ደረጃ ፡ ይዘው ፡ የሚገኙት ፡ ሕዝቦች ፡ እነዚህ ፡
ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀሩት ፡ ሕዝቦች ፡ መቼም ፡ ቢሆን ፡ ይደርሱብናል ፡ ብለው ፡
ስለማይጠረጥሩ ፡ በንቀት ፡ ዐይን ፡ ይመለከቷቸዋል ። እንደዚሁም ፡ ከኢ
ንዱስትሪያቸው ፡ እየተሠራ ፡ የሚወጣውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሸቀጥ ፡ ዕቃ ፡
እየገዙ ፡ እንዲኖሩ ፡ አድርገዋል ። ይህንኑም ፡ ለመግዛት ፡ ቤንዚን ፡ ያላ

ቸው ፡ ቤንዚናቸውን ፡ ቤንዚን ፡ የሌላቸው ፡ ባገራቸው ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ በዓለም ፡ ገበያ ፡ ላይ ፡ ተፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ እንደ ፡ ቆዳ ፤ ጥጥ ፤ ቡና ፤ ሐር ፤ ብረት ፤ ካካዎ ፤ ላስቲክ ፤ እኽል ፤ የመሰለውን ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ እየሸጡ ፡ ይከፍላሉ ። የሰሠጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ኢንዱስትሪዎቻቸው ፡ የሚያፈሯቸው ፡ ሸቀጦች ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ እየበረከቱና ፡ እየጨመሩ ፡ ስለሚሄዱ ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ ገዥዎች ፡ የሆኑት ፡ ሕዝቦች ፡ የሚያነሡላቸው ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ። ምክንያቱም ፡ እነሱም ፡ ፍላጎታቸው ፡ እየጨመረ ፡ ስለሚሄድ ፡ ነው ። በመሠልጠን ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ሕዝቦች ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ አዲስ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፤ አዲስ ፡ ሆፒታሎች ፤ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ የስልክ ፤ የራዲዮ ፤ የባቡር ፤ የአኤሮፕላን ፡ ድርጅቶች ፡ ማቋቋም ፡ ግድ ፡ ስለ ፡ ሆነባቸው ፡ ከውጭ ፡ የሚገዙት ፡ ሸቀጥ ፡ እየጨመረ ፡ መሄዱን ፡ ይቀጥላል ። ሸቀጡ ፡ በብዙ ፡ የሚሸጥለት ፡ መንግሥት ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ እያገኘ ፡ ፋብሪካውን ፡ ለማሻሻልና ፡ ለማስፋፋት ፤ ለሕዝቡም ፡ በሰፊው ፡ ሥራ ፡ ለመስጠት ፡ ስለሚችል ፡ በሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ፉክክር ፡ እንዲወለድ ፡ ምክንያት ፡ ሆነ ። አሁን ፡ ባለንበት ፡ በኢንዱስትሪ ፡ ዘመን ፡ ሸቀጥ ፡ ገዥዎች ፡ የሆኑት ፡ ሕዝቦች ፡ እንደ ፡ ግብር ፡ ከፋዮች ፡ ሆነው ፡ ይቈጠራሉ ። እነሱም ፡ ጕዳቱ ፡ ሳይሰማቸው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ቈዩ ። በንግድም ፡ ሆነ ፡ በፖሊቲካ ፤ ወይም ፡ በትምህርት ፡ በዓለም ፡ መንግሥታትና ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ ግንኙነት ፡ ይባላል ።

ኖኤል ፡ ድሮጋ ፡ (Noél Drogat) የተባለው ፡ ሰው ፡ ስለዚህ ፡ ጕዳይ ፡ በጻፈው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ በሠለጠኑትና ፡ ባልሠለጠኑት ፤ በሀብታሞችና ፡ በድኾች ፤ በኀይለኞችና ፡ በደካሞች ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ባጭር ፡ ቃል ፡ ሲገልጥልን ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ ጠቅሰነዋል ።

«ባ1955 ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ፡ የኮሚኒስት ፡ አገሮች ፡ ሳይጨመሩ ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ያፈሩት ፡ ሀብት ፡ (ከዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ አምስት) ፡ ፱፻፴፭ ፡ ሚሊያርድ ፡ ያሜሪካ ፡ ዶላር ፡ ደርሷል ። ከዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ሰባት ፡ ሚሊያርድ ፡ የተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ድርሻ ፡ ነው ። ሦስት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ አምስት ፡ ሚሊያርድ ፡ ያውሮፖ ፡ ነው ። በሥልጣኔ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀሩት ፡ አገሮች ፡ አንድነት ፡ ሆነው ፡ ያፈሩት ፡ ሲታሰብ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ አምስት ፡ ሚሊያርድ ፡ ዶላር ፡ ብቻ ፡ ነው ።

እያንዳንዱ ፡ ዜጋ ፡ (ባመት) ፡ ያፈራው ፡ ሀብት ፡ ሲታሰብ ፡ 1870 ዶላር ፡ ለተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ መንግሥታት ፤ 740 ፡ ዶላር ፡ ለፈረንሳይ ፤



120 ፡ ዶላር ፡ ለፔሩ ፤ 80 ፡ ዶላር ፡ ለታይላንድ ፤ 70 ፡ ዶላር ፡ ለፓኪስታን ፤ 60 ፡ ዶላር ፡ ለህንድ ፤ 50 ፡ ዶላር ፡ ለቢርማኒ ፡ ይደርሳቸዋል ።

ኀሊናችን ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ሳይገነዘበው ፡ ቢቀር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚያስገርም ፡ ልዩነት ፡ በሚገኝበት ፡ አሁን ፡ በምንኖርበት ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ በዚች ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ከሚኖሩት ፡ ሕዝቦች ፡ ከጠቅላላው ፡ ቍጥር ፡ ካሥር ፡ አንድ ፡ እጅ ፡ የሚሆኑት ፡ ሕዝቦች ፡ በጠቅላላው ፡ ካለው ፡ የዓለም ፡ ሀብት ፡ ሰማኒያ ፡ በመቶ ፡ (80%) የሚሆነውን ፡ በእጃቸው ፡ ጨብጠውታል» ።

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ዘጠና ፡ በመቶ ፡ (90%)ለሚሆኑት ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ የሚደርሳቸው ፡ ከጠቅላላው ፡ ሀብት ፡ ሃያ ፡ በመቶ ፡ (20%) ብቻ ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ በወገን ፡ በወገን ፡ እንዲለያዩ ፡ የሚያደርጓቸው ፡ ዋኖቹ ፡ ነገሮች ፡ ዘርና ፡ ሃይማኖት ፡ ናቸው ። የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ጥቍር ፤ ብጫ ፡ ነጭ ፡ ተብለው ፡ በሦስት ፡ ዐቢይ ፡ ጾታ ፡ ተከፍለዋል ። ጥቍሮች ፡ በአፍሪቃ ፤ ብጫዎች ፡ በእስያ ፤ ነጮች ፡ ባውሮፓና ፡ በአሜሪካ ፡ ተለይተው ፡ በክፍል ፡ በክፍላቸው ፡ አህጉሮች ፡ ይዘዋል ። ባለፉት ፡ ዘመናት ፡ ሕዝቦች ፡ እየተከፋፈሉ ፡ ጦርነት ፡ የሚያደርጉት ፡ በሃይማኖት ፡ ምክንያት ፡ ነበር ። እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ግን ፡ በቀለምና ፡ በአህጉር ፡ (ኰንቲና) ፡ እየተለዩ ፡ በሰላም ፡ ጊዜ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ትግል ፤ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ውጊያ ፡ ከሚያደርጉበት ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ ደርሰዋል ። ይኸውም ፡ ኦርዌል ፡ የተባለው ፡ ደራሲ ፡ 1984 በተባለው ፡ የልብ ፡ ወለድ ፡ ድርሰቱ ፡ ባሳቡ ፡ የፈጠረውን ፡ የመሰለ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ፡ ማለት ፡ ነው ። አሁን ፡ ለጊዜው ፡ የእስያና ፡ የአፍሪቃ ፡ ሕዝቦች ፡ አንድ ፡ የሆኑ ፡ ይመስላሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ አንድነት ፡ እስከ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚቈይ ፡ አይመስልም ።

ምክንያቱም ፡ ለምሳሌ ፡ ጃፓን ፡ በሳይንስና ፡ በቴክኒክ ፡ ተራምዳ ፡ ከነጮች ፡ ጋራ ፡ እኩል ፡ በሆነች ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ በቀሩት ፡ ሕዝቦች ፡ ላይ ፡ የፈጸመችው ፡ ባለቅኝ ፡ አገር ፡ የሆኑት ፡ መንግሥታት ፡ ከሚሠሩት ፡ የተሻለ ፡ ሆኖ ፡ አልተገኘም ። ነገ ፡ ደግሞ ፡ ሺና ፡ ያሁኑን ፡ እርምጃ ፡ ቀጥላ ፡ በጣም ፡ የተራመደች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቀሩት ፡ ሕዝቦች ፡ ላይ ፡ ይህንኑ ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ እንደምትሠራ ፡ አይጠረጠርም ። የሆነው ፡ ሆኖ ፡ ነጮች ፡ በሳይንስና ፡ በቴክኒክ ፡ በኩል ፡ ያደረጉት ፡ እርምጃ ፡ በጣም ፡ የዘለቀ ፡ በመሆኑ ፡ እስከ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የሥልጣኔ ፡ መሪዎች ፡ ሆነው ፡ እንደሚኖሩ ፡ ገምተውታል ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ የሚፈጠረውን ፡ አዲስ ፡ ጥበብ ፡ ሁሉ ፡ የሚያመነጩት ፡ እነሱ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፤ እውነትም ፡ ሌሎቹ ፡ ሕዝቦች ፡ አዲስ ፡

ጥበብ ፡ በመፍጠር ፡ በኩል ፡ ማለት ፡ በ (inventions) ከእነሱ ፡ ጋራ ፡ በቅርብ ፡
ዘመን ፡ ለመተካከል ፡ ይችላሉ ፡ ብለን ፡ ለማመን ፡ ያስቸግራል ።

"Crépuscule des dieux" «የአማልክት ፡ መጥፋት» ፡ በተባለው ፡
ድርሰቱ ፡ ውስጥ ፡ ቫግነር ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ጽፏል ፤

"Comme la fumée se dissipe, la race des dieux a passé. Je laisse le
monde sans guide. Mon haut savoir est le trésor que je lui donne."

«ጢስ ፡ በኖ ፡ እንደሚጠፋ ፡ ሁሉ ፡ የአማልክት ፡ ዘር ፡ አለፈ ።
ዓለምን ፡ ያለመሪ ፡ ተውኩት ። የማወርሰው ፡ ሀብት ፡ ከፍተኛው ፡ ዕው
ቀቴ ፡ ነው» ።

እንግዲህ ፡ የአማልክት ፡ ዘር ፡ ብሎ ፡ ቫግነር ፡ የሚጠራቸው ፡ ሊቃ
ውንትን ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ማንን ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ? ለዘመናችን ፡ ሥል
ጣኔ ፡ መሠረት ፡ የሆነውን ፡ አዲስ ፡ የሚወጣውንና ፡ የሚፈለሰፈውን ፡
ጥበብ ፡ ሁሉ ፡ ለዓለም ፡ እያወረሱት ፡ የሚገኘው ፡ ከእነሱ ፡ ነውና ።

እንሆ ፡ ዛሬ ፡ የኤሌክትሪክ ፡ ብርሃን ፡ እናበራለን ፤ በኦቶሞቢልና ፡
በአኤሮፕላን ፡ እንጓዛለን ፤ በራዲዮ ፡ የዓለምን ፡ ወሬ ፡ እንሰማለን ፤ ይህን
ንም ፡ እንደተለመደ ፡ ነገር ፡ አድርገን ፡ እንቈጥረዋለን ፡ እንጂ ፡ አሁን ፡
ላለንበት ፡ ዘመን ፡ በተለየ ፡ እንደ ፡ ተሰጠ ፡ እንደ ፡ ልዩ ፡ ጸጋ ፡ አድርገን ፡
አንቆጥረውም ፡ ይሆናል ። ኤሌክትሪኩንም ፤ ኦቶሞቢሉንም ፤ አኤሮፕላ
ኑንም ፤ ራዲዮኑንም ፡ ገንዘባችንን ፡ እየከፈልን ፡ የምናገኘው ፡ ነው ፡ ብለን ፡
እናስባለን ። ነገር ፡ ግን ፡ ከኛ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ አባቶቻችን ፡ ገንዘባቸ
ውን ፡ አውጥተው ፡ እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ ለማግኘት ፡ ይችሉ ፡ ኖረዋል ፡
ወይ ? ብለን ፡ ማሰብ ፡ ይገባናል ። እንግዲህ ፡ ይህን ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡
ለማግኘት ፡ የቻልነው ፡ ሊቃውንት ፡ በደከሙበትና ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡
ችግር ፡ እየደረሰባቸው ፡ በፈጠሩት ፡ ጥበብ ፡ መሆኑን ፡ እንወቅ ። እነዚህ ፡
ሊቃውንት ፡ ትውልዳቸው ፡ ግሪክ ፤ ጀርመን ፤ ፈረንሳይ ፤ እንግሊዝ ፡ ወ
ይም ፡ ጣሊያን ፡ ቢሆን ፡ የፈጠሩት ፡ ጥበብ ፡ የሚያገለግለውና ፡ የሚጠቅ
መው ፡ በተለየ ፡ ለተወለዱባት ፡ አገር ፡ ብቻ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ ለመላው ፡
ዓለም ፡ ሕዝብ ፡ ማለት ፡ ለሁላችንም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሁላችንም ፡ በልባችን ፡
ልንወዳቸውና ፡ ውለታቸውን ፡ ልናስታውሰው ፡ ያሻል ። እንደዚሁም ፡
ነገ ፡ የሚወለዱትን ፡ ጥበቦች ፡ በአንጎላቸው ፡ አርግዘው ፡ ዛሬ ፡ የሚደ
ክሙና ፡ የሚሠሩ ፡ ሊቃውንት ፡ ከእነሱ ፡ በሚገኘው ፡ ጥበብ ፡ ሁላች
ንም ፡ ስለምንጠቀምበት ፡ ስለ ፡ እነሱ ፡ ያለን ፡ አሳብ ፡ በአክብሮትና ፡
በውለተኛነት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ሊሆን ፡ ያስፈልጋል ።



ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ በሥልጣኔ ፡ በኩል ፡ ለሚደረገው ፡ መጣጣር ፡ ብዙ
ዎቹ ፡ ሕዝቦች ፡ ባንጐላቸው ፤ በሀብታቸውና ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሯቸው ፡ እ
የለፉ ፡ የሚያፈሩትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥበብ ፡ የመላው ፡ ዓለም ፡ ሕዝቦች ፡
እንዲጠቀሙበት ፡ ሲያደርጉ ፡ ግማሾቹ ፡ ሕዝቦች ፡ ግን ፡ ከመቀበል ፡
በቀር ፡ በበኩላቸው ፡ ለዓለም ፡ የሚያበረክቱት ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለም ።
ከመቀበል ፡ በቀር ፡ መስጠት ፡ አያውቁም ። የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ እንደ ፡ አ
ንድ ፡ ትልቅ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ይቈጠራሉ ። ባንድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ውስጥ ፡ አን
ዳንዶቹ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ እየሠሩና ፡ እየደከሙ ፡ የሚያገኙትን ፡ ገንዘብ ፡
አምጥተው ፡ ለቤተ ፡ ሰው ፡ ኑሮ ፡ እንዲያገለግል ፡ ሲያደርጉ ፤ ከመካከላ
ቸው ፡ አንዳንዶቹ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ተኝተው ፡ እነዚያ ፡ ያፈሩትን ፡ ሀብት ፡
ብቻ ፡ እየበሉና ፡ እየጠጡ ፡ ቢኖሩ ፡ ቅር ፡ አያሰኝም ፡ ወይ ? ይህን ፡ የመ
ሰለ ፡ የስንፍና ፡ ሁኔታ ፡ የሚታየው ፡ ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ በአፍሪቃ ፡ ሕዝ
ቦች ፡ በኩል ፡ ነው ። የአፍሪቃ ፡ ሕዝቦች ፡ ተጀምሮ ፡ እስቲጨረስ ፡ ለዓ
ለም ፡ ሥልጣኔ ፡ የሚጠቅም ፡ በሳይንስ ፤ በቴክኒክ ፤ በድርሰት ፤ ይህን ፡
በመሳሰለው ፡ በማንኛውም ፡ ጥበብ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ምንም ፡ ሥራ ፡ አለመ
ሥራታቸውን ፡ በማሳሰብ ፡ እንደ ፡ ዌልስ ፡ ያሉ ፡ ሊቃውንት ፡ የወቀሣ ፡
ድምፅ ፡ አሰምተዋል ።

ጐቢኖም ፡ እንደዚሁ ፡ የጥቍር ፡ ዘር ፡ ሕዝቦች ፡ በሥልጣኔ ፡ በኩል ፡
ዋጋ ፡ ያለው ፡ ምንም ፡ ሥራ ፡ አልሠሩም ፡ ሊሠሩም ፡ አይችሉም ፡ ሲል ፡
ተናግሯል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በምዕራባውያን ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ቅሬታ ፡
የሚፈጥር ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ። ለምሳሌ ፤ ባለ፲፯ ፡ ጥራዝ ፡ የሆነውን ፡
የላሩስን ፡ ትልቁን ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ (dictionnaire) ገልጠን ፡ የተመለ
ከትን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ሲናገር ፡ በጥንት ፡ ዘመን ፡
በብዙ ፡ ነገሮች ፡ ሥልጣኔን ፡ ለግብጽ ፡ መጀመሪያ ፡ የሰጠቻት ፡ ኢትዮ
ጵያ ፡ መሆኗን ፡ በግልጥ ፡ ያስረዳል ። አሁን ፡ በኻያኛው ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡
ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ አስተያየት ፡ እየቀረ ፡ እየተሻረ ፡ ሲሄድ
እንመለከታለን ። ይህም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የአድልዎ ፡ ሥራ ፡ መሆኑ ፡ ግልጥ ፡
ነገር ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ ለምሳሌ ፤ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሥዕ
ሎች ፡ አሠራር ፡ ጉዳይ ፡ ሲናገሩ ፡ በመናኛነቱ ፡ የታወቀ ፡ በብዛት ፡ እየ
ተሠራ ፡ በየቦታው ፡ የሚሸጥ ፡ የሥዕል ፡ አሠራር ፡ ስላለ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡
የኢትዮጵያ ፡ ሥዕል ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ አትመው ፡ የሚያወጡትና ፡ ለዓ
ለም ፡ የሚያቀርቡት ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ የአካል ፡ ሚዛ
ንም ፡ ሆነ ፡ የቅርብና ፡ የሩቅን ፡ አቀማመጥ ፡ የማይለይ ፡ ከመሆኑ ፡ የተ
ነሣ ፡ በሕፃናት ፡ እጅ ፡ የሚሠራ ፡ ሥዕል ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ።
ነገር ፡ ግን ፡ ለምሳሌ ፡ ባጅ ፡ በጻፈው ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ ያወጣቸውን ፡

የኢትዮጵያ ፡ ሥዕሎች ፡ ብንመለከት ፡ ውብ ፡ የሆኑትን ፡ እንደ ፡ መረጠ ፡ ልንረዳው ፡ እንችላለን ። እንደዚሁም ፡ የጀርመን ፡ አምባሳደር ፡ ባለቤት ፡ የሆኑት ፡ ማዳም ፡ ቢደር ፡ ከላሊበላ ፡ ያመጡትን ፡ ሥዕል ፡ ብንመለከተው ፡ ዋጋው ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ ነው ፡ የማይባል ፡ እንደ ፡ ዐቢይ ፡ ሥራ ፡ (chef-d'oeuvre) የሚቈጠር ፡ ነው ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ በአኵስም ፡ የሚኖሩ ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የሆኑ ፡ አሁንም ፡ በሕይወት ፡ ያሉ ፡ ሠዓሊ ፡ የሚሠሯቸውን ፡ ሥዕሎች ፡ ልንመለከታቸው ፡ እንችላለን ። እሳቸውም ፡ ከሠሯቸው ፡ ሥዕሎች ፡ አንዳንዶቹ ፡ በዩኒበርስቲ ፡ ኮሌጅ ፡ ይገኛሉ ። እኚህ ፡ ሠዓሊ ፡ ከምዕራባውያን ፡ ሠዓሊዎች ፡ ጋራ ፡ ምንም ፡ ግንኙነት ፡ የላቸውም ። የኢጣልያን ፡ አገር ፡ ሥዕሎች ፡ ለማወቅ ፡ ሲፈለግ ፡ የሚኬል ፡ አንጀሎን ፡ ወይም ፡ የሩፋኤልን ፡ እንደዚሁም ፡ የፈረንሳዊን ፡ ሥዕሎች ፡ ለማወቅ ፡ ሲፈለግ ፡ የረኗርን ፡ ወይም ፡ የዳቪድን ፡ ሥዕሎች ፡ መመልከት ፡ እንደሚያሻ ፡ ሁሉ ፡ የኢትዮጵያን ፡ እውነተኛ ፡ ሥዕሎች ፡ ለማወቅ ፡ ሲፈለግም ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ የጠቀስናቸውን ፡ ሥዕሎች ፡ ማየትና ፡ በእነሱ ፡ መሠረት ፡ መገመት ፡ ይገባል ። ነገር ፡ ግን ፡ አውሮፓ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሥዕል ፡ ጕዳይ ፡ ሲነሣ ፡ እነዚያን ፡ መናኛች ፡ የሆኑትን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሌላውን ፡ ለማወቅ ፡ አትፈልግም ። ይህ ፡ የተሳሳተ ፡ አሳብ ፡ የማይለቃቸው ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ለምሳሌ ፡ ኡሌንስኮ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሥዕሎች ፡ ታሪክ ፡ ያሳተመውን ፡ መጽሐፍ ፡ ስንመለከት ፡ በዚሁ ፡ አስተያየት ፡ ተደግፎ ፡ የተዘጋጀ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ።

ማንኛውም ፡ አገር ፡ ቢሆን ፡ በኪነ ፡ ጥበብ ፡ በኩል ፡ በሚያፈራው ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ዝንባሌ ፡ የሠረጸ ፡ አሠራር ፡ እንደሚኖረው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ለምሳሌ ፤ ስለ ፡ ፈረንሳይ ፡ ሥዕሎች ፡ ጕዳይ ፡ የሚናገር ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ (አብስትሬ) ፡ የሚባለውን ፡ ዝንባሌ ፡ ተከትለው ፡ የሚሠሩትን ፡ ሠዓሊዎች ፡ ብቻ ፡ ይጠቅሳልን ? ስለ ፡ ምን ፡ ባጅ ፡ ከጥሩዎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሥዕሎች ፡ መርጦ ፡ ሲያወጣ ፡ የዛሬዎቹ ፡ ሊቃውንት ፡ መናኛውን ፡ ሥዕል ፡ ብቻ ፡ በየመጻሕፍቱ  ያትማሉ ?

ምናልባት ፤ ይህ ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ እውነተኛ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሥዕል ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠረው ፡ ይህ ፡ በመሆኑና ፡ የቀረው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሥዕሎች ፡ አሠራር ፡ የተመራ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ፡ ይባል ፡ ይሆናል ። ይህ ፡ እንዳይባልማ ፡ ጠልቀን ፡ የተመለከትነው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በኪነ ፡ ጥበብ ፡ በኩል ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ (ኤንፍሉአንስ) ፡ ያልደረሰበት ፡ ከቶ ፡ አንድ ፡ አገር ፡ እንኳ ፡ ለማግኘት ፡ አይቻልም ።



እንግዲህ ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ተነሣንበት ፡ ጕዳይ ፡ ተመልሰን ፡ በሠለጠኑና ፡ በሥልጣኔ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ በቀሩ ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ሁኔታ ፡ መመልከታችንን ፡ እንቀጥል ።

የሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ኀይላቸውንና ፡ ትልቅነታቸውን ፡ በንግድ ፡ ላይ ፡ ሲመሠርቱ ፡ እነሱ ፡ የኢንዱስትሪያቸውን ፡ ሸቀጥ ፡ ለዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ሊሸጡ ፤ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ደግሞ ፡ ብዙ ፡ ትርፍ ፡ እየከፈሉ ፡ እንዲገዟቸው ፡ ሲያስቡ ፡ ይህ ፡ ሁኔታ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ይቈያል ፡ ብለው ፡ አላሰቡም ። የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ የኢንዱስትሪን ፡ ጥበብ ፡ መቼም ፡ ቢሆን ፡ ደርሰውበት ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ሊወዳደሩ ፡ አይችሉምና ፡ ይህ ፡ ገባርነታቸው ፡ ዘለዓለም ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ ብለው ፡ አምነው ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ነገር ፡ ግን ፡ አውሮፖውያን ፡ የሳይንስንና ፡ የቴክኒክን ፡ ጥበብ ፡ ለራሳቸው ፡ ብቻ ፡ እንዲያገለግል ፡ ምስጢር ፡ አድርገው ፡ ዘለዓለም ፡ ሊያኖሩት ፡ እንደማይችሉ ፡ አስተዋዮች ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ አልሳቱትም ፡ ነበር ። ለምሳሌ ፡ ያኽል ፡ ሄርደር ፡ (Herder) የሚባለው ፡ የጀርመን ፡ ሊቅ ፡ የጻፈውን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ጥቅስ ፡ እንስማ ፤

«Plus nous autres européens inventons de moyens et d'instruments pour vous subjuguer — vous les autres continents — vous duper et vous piller, peut-être un jour sera-ce justement votre tour de triompher. Nous fixons des chaînes au bout desquelles vous nous tirerez.»

«እናንተን ፡ ከቀንበር ፡ ለማግባት ፤ እናንተን ፡ ለማታለልና ፡ እናንተን ፡ ለመዝረፍ ፡ እኛ ፡ አውሮፓውያን ፡ ዘዴዎችና ፡ መሣሪያዎች ፡ እየፈጠርን ፡ በምንሄድበት ፡ መጠን ፡ እናንተ ፡ ሌሎች ፡ አህጉሮች ፡ ምናልባት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ድል ፡ ለማድረግ ፡ ተራ ፡ ታገኙ ፡ ይሆናል ። ጫፉን ፡ ይዛችሁ ፡ እኛን ፡ የምትጐትቱበትን ፡ ሰንሰለት ፡ ሠርተንላችኋል» ።

ሄርደር ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ከጻፈው ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሰማኒያ ፡ ስድስት፡ ዓመት ፡ ነው ። ይህ ፡ ጕዳይ ፡ የሚመለከታቸው ፡ አህጉሮች ፡ በተለየ ፡ አፍሪቃና ፡ እስያ ፡ ሲሆኑ ፡ በእነዚህ ፡ አህጉሮች ፡ ከሚኖሩት ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ መጀመሪያ ፡ ምስጢራቸውን ፡ ያገኘችባቸው ፡ ጃፓን ፡ ነች ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ የከብሩን ፡ አክሊል ፡ የተቀዳጀች ፡ እሷ ፡ መሆኗን ፡ ታሪክ፡ መስክሮላታል ። «ጀፓን ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ሠለጠነች ? » ፡ የተባለውን ፡ መጽሐፍ ፡ አንባቢ ፡ ሊመለከት ፡ ይችላል ።

ከጃፓን ፡ ቀጥሎ ፡ እንሆ ፡ አሁን ፡ ቪና ፡ የሳይንስና ፡ የቴክኒክን ፡ ጥበቦች ፡ በሙሉ ፡ እጅ ፡ በማድረግ ፡ ላይ ፡ ትገኛለች ። ከሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተፈጸመው ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡

ጉዳዮች ፡ ሆነው ፡ ሊቈጠሩ ፡ የሚገባቸው ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ። እ
ነሱም ፡ የአቶሚክና ፡ የሃይድሮጅን ፡ ቦምብ ፡ መገኘትና ፡ የቪና ፡ ከእን
ልፍ ፡ መንቃት ፡ ናቸው ። ቍጥሩ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ሚሊዮን ፡
የሚሆነው ፡ የቪና ፡ ሕዝብ ፡ ዛሬ ፡ መንገዶች ፤ ድልድዮችና ፡ ታላላቅ ፡
የውሃ ፡ ግድቦች ፡ በመሥራት ፤ የኤሌክትሪሲቲ ፡ ጕልበት ፡ በየቦታው ፡
በማቋቋም ፤ ብረት ፡ በብዙ ፡ እያቀለጠ ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ በመትከልና ፡
የጦር ፡ መሣሪያዎችም ፡ በመሥራት ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። ዛሬ ፡ ደግሞ ፡ የአ
ቶምና ፡ የሃድሮገኤን ፡ ቦምብ ፡ ለመሥራት ፡ በቅቷል ። ቍጥሩ ፡ ይህን ፡
ያኽል ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የሚገኝ ፡ ሕዝብ ፡ በሚያስደንቅ ፡ ኅብረት ፡ አንድ ፡
ሆኖ ፡ ላንድ ፡ ዐላማ ፡ ይደክማል ። ይኸውም ፡ ዐላማ ፡ ቪና ፡ ከሠለጠኑት ፡
አገሮች ፡ ጋራ ፡ እኩል ፡ ሆና ፡ እንድትገኝ ፡ ነው ። ጕዳዩን ፡ ያጠኑት ፡
ሰዎች ፡ እያያዙን ፡ ገምተው ፡ ከዚህ ፡ ዐላማ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ እንደሚደ
ርስ ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ አረጋግጠዋል ። እንግዲህ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ማዕድን ፡
ባገሩ ፡ የሞላ ፤ በጥንታዊ ፡ ሥልጣኔው ፡ ከዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ የመ
ጀመሪያውን ፡ ደረጃ ፡ ይዞ ፡ የሚገኝ ፤ አውሮፓና ፡ አሜሪካ ፡ መስኮብ ፡
ሳይጨመር ፡ አንድነት ፡ ሆነው ፡ ቢደመሩ ፡ ብቻውን ፡ ሆኖ ፡ በሕዝብ ፡
ቍጥር ፡ የሚተካከላቸው ፡ ይህ ፡ የግዙፎች ፡ ግዙፍ ፡ የሆነ ፡ ሕዝብ ፡ እ
ንደ ፡ አሜሪካና ፡ እንደ ፡ መስኮብ ፡ እንደ ፡ ጃፓንም ፡ በሳይንስና ፡ በቴ
ክኒክ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘለት ፡ እንደ ፡ ያለ ፡ የሚያሠጋ ፡
ነገር ፡ ለዓለም ፡ ሊፈጥር ፡ እንደሚችል ፡ አሳባችን ፡ በቀላሉ ፡ ሊገምተው ፡
የሚችል ፡ ነገር ፡ አይዶለም ። ባጭሩ ፡ የዓለም ፡ ሁኔታ ፡ መልክ ፡ በዚህ ፡
የተነሣ ፡ ጨርሶ ፡ እንደሚለወጥ ፡ ማመን ፡ ይገባናል ።

የቀሩትም ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ እንደ ፡ ቪና ፡ አሳባ
ቸውን ፡ በሙሉ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ሊያውሉት ፡ ባይችሉ ፡ ኢንዱስትሪን ፡
ባገራቸው ፡ እያቋቋሙ ፡ ላውሮፓውያንም ፡ ሆነ ፡ ለአሜሪካ ፡ ገባሮች ፡
ሆነው ፡ ከመኖር ፡ ሊድኑ ፡ ቈርጠዋል ። ህንድና ፡ ግብጽ ፡ ለምሳሌ ፡ በ
ጥጥ ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ራሳቸውን ፡ ለመቻልና ፡ ከራሳቸውም ፡ ተርፈው ፡
ወደ ፡ ውጭ ፡ ሸቀጣቸውን ፡ ለመሸጥ ፡ በመጣጣር ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ ። ከ
ዚህም ፡ የተነሣ ፡ ያውሮፓ ፡ ባለኢንዱስትሪዎች ፡ የጥጥ ፡ ፋብሪካችን ፡
በጣረ ፡ ሞት ፡ ላይ ፡ ይገኛል ፡ እያሉ ፡ በመጨነቅ ፡ ላይ ፡ ናቸው ። የዓ
ለም ፡ ሕዝቦች ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ለመታለል ፡ ስለማይችሉና ፡ ልዩ ፡
ልዩ ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ እያቋቋሙ ፡ መሄዳቸውን ፡ ስለማያቋርጡ ፡ ይህ ፡
ዛሬ ፡ በአውሮፓውያን ፡ የጥጥ ፡ ፋብሪካዎች ፡ ላይ ፡ የወደቀው ፡ አደጋ ፡
ነገ ፡ ደግሞ ፡ በቀሩት ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ ላይ ፡ እንደሚወድቅ ፡ የታወቀ ፡
ነው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ኀይላቸውንና ፡ የመንግሥታቸውን ፡ ገናናነት ፡ በኢ



ንዱስትሪ ፡ ላይ ፡ መሥርተው ፡ የሚገኙት ፡ ያውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡
ምን ፡ ይበጃቸዋል ? ደራስያን ፤ ፈላስፎች ፤ የሳይንስ ፡ ሊቃውንት ፡ በመ
ንፈሳቸው ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ የተሸፈነ ፡ ዕውቀት ፡ እንዲነሣ ፡ ለማድ
ረግ ፡ ቀስቃሽ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ አሳብ ፡ እንደሚያስፈልጋቸው ፡ ሁሉ ፡ ይ
ህንኑ ፡ የመሰለ ፡ ጠባይ ፡ በያንዳንዱ ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ይገኛል ። በተፈ
ጥሮ ፡ ባሕርያቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ ልዩ ፡ ስጦታ ፡ ያላ
ቸው ፡ ሕዝቦች ፡ ይገኛሉ ። ይህንኑም ፡ (vitalité) ብለው ፡ ይጠሩታል ።
ትርጉሙም ፡ (ሕያውነት) ፡ የሕይወት ፡ ጠባይ ፡ ያለው ፡ ማለት ፡ ነው ።
ሕይወት ፡ ማለት ፡ ምንድነው ? በሕይወት ፡ የሚኖር ፤ በሕይወት ፡ የቆመ፡
ማለት ፡ ነው ። ዣን ፡ ዣክ ፡ ሩሶ ፡ ስለዚህ ፡ ቃል ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ት
ርጉም ፡ ይሰጠናል ። (Vivre ce n'est pas respirer, c'est agir.) «መኖር ፡
ማለት ፡ መተንፈስ ፡ አይዶለም ፤ መሥራት ፡ ነው» ። እንግዲህ ፡ ወደ ፡
ታሪክ ፡ ገብተን ፡ ምሳሌ ፡ ስንፈልግ ፡ ግብጾች ፤ ግሪኮች ፤ ሮማውያን ፤ ቪና
ውያን ፤ ህንዶች ፡ የቀሩትም ፡ ብዙ ፡ ሕዝቦች ፡ በየዘመኑ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡
ድረስ ፡ ታሪካዊ ፡ መታሰቢያቸውን ፡ እንድናደንቅ ፡ የሚያደርጉን ፡ ሥራዎ
ችን ፡ የሠሩ ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ። ይህንኑም ፡ «የሥልጣኔ ፡ ገጸ ፡ በረከት» ፡
በሚለው ፡ አርእስት ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በሰፊው ፡ እንመለከተዋለን ።
ከታንሌ ፡ ጆን ፡ የተባለው ፡ የእንግሊዝ ፡ ተወላጅ ፡ ባ፲፰፻፳፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡
(እ ፡ ኤ ፡ አ) ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የሚገኘውን ፡ የማይረሳ ፡ ቃል ፡ ጽፏል ፤

«ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ አምስቱ ፡ የዓለም ፡ ክፍሎች ፡ በፈቃዳቸው ፡ የእኛ ፡
ገባሮች ፡ ሆነዋል ። የሰሜን ፡ አሜሪካና ፡ መስኮብ ፡ የስንዴ ፡ ማድቤቶቻ
ችን ፡ ናቸው ። ቺካጎ ፤ አዴሣ ፤ ጐተራዎቻችን ፡ ናቸው ። ካናዳ ፤ የባል
ቲክ ፡ አገሮች ፡ ጫካዎቻችን ፡ ናቸው ። አሜሪካ ፡ የበሬ ፡ መንጋዎቻችን ፡
የሚሰማሩባት ፡ አገር ፡ ነች ። ፔሩ ፡ ብሯን ፤ ካሊፎርኒ ፡ ወርቋን ፡ ይል
ኩልናል ። ቪናውያን ፡ ሻያቸውን ፡ የሚተክሉት ፡ ለኛ ፡ ነው ። የሰሜን
ህንድ ፡ አገሮች ፡ በባሕር ፡ ጠረፎቻችን ፡ በኩል ፡ ቡናን ፤ ስኳርን ፤ ቅመማ
ቅመምን ፡ ይልኩልናል ። ፈረንሳይና ፡ እስፓኝ ፡ የወይን ፡ ፍሬያቸውን ፡
ይልኩልናል ። በሜዲቴራኔ ፡ የሚገኘው ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ በያይነቱ ፡ ፍሬ ፡
ይተክልልናል ። ጥጥ ፡ ከተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ አገሮች ፡ ይመጣልናል» ።

ስታንሌ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ የጻፈው ፡ ከመቶ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ነው ።
በዚያ ፡ ዘመን ፡ የሚበልጠው ፡ የፋብሪካ ፡ ጥበብና ፡ ፋብሪካን ፡ የሚያን
ቀሳቅሰው ፡ የድንጋይ ፡ ከሰል ፡ (houille) የሚገኘው ፡ በእንግሊዝ ፡ እጅ ፡
ስለ ፡ ነበረ ፡ ከፋብሪኮቿ ፡ የሚወጣውን ፡ ሸቀጥ ፡ ለመላው ፡ ዓለም ፡ እየላ
ከች ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ሀብት ፡ በርካሽ ፡ ዋጋ ፡ ገዝታ ፡
ትጠቀምበት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ስንት ፡ ነገር ፡ ተለወጠ።

ያ ፡ ሁሉ ፡ ቀርቶ ፡ ዛሬ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የተፈጠረው ፡ ፈጽሞ ፡ አዲስ ፡ ሁኔታ ፡ ነው ። እንኳንስ ፡ እነ ፡ አሜሪካ ፤ እነ ፡ መስኮብ ፡ እነ ፡ ካናዳ ፤ ይቅሩና ፡ ዛሬ ፡ ሌሎቹም ፡ ሕዝቦች ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ የሚታለሉ ፡ አይደሉም ። ሁሉም ፡ ካገራቸው ፡ ሀብት ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ የሆነውን ፡ ፋብሪካ ፡ እየተከሉ ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ራሳቸው ፡ ሠርተው ፡ ይሸጣሉ ፡ እንጂ ፡ ያገራቸውን ፡ ሀብት ፡ ለባዕድ ፡ ፋብሪካ ፡ እንዲያገለግል ፡ አያደርጉም ። ብዙዎቹም ፡ ይህንን ፡ ሳያደርጉ ፡ ቢቀሩ ፡ ፋብሪካ ፡ ለመግዛት ፡ የገንዘብ ፡ ዐቅም፡ እያነሳቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ነገሩ ፡ ሳይገባቸው ፡ ቀርቶ ፡ አይደለም ። ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ነገሩ ፡ ከገባው ፡ በኋላ ፡ አይታለልም ። አንድ ፡ ሊቅ ፡ ሲናገር ፡ ሰውን ፡ አታስብ ፡ ብሎ ፡ መከልከል ፡ አይቻልም ፡ ብሏል ።

ኤመርሰን ፡ (Emerson) ሲናገር ፡ (Nous savons qu'une pensée est la mère de chaque action.) ይላል ፤ ትርጉሙም ፡ «እያንዳንዱ ፡ አሳብ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ሥራ ፡ እናቱ ፡ መሆኑን ፡ እናውቃለን» ። ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ አሳብና ፡ ሥራ ፡ የማይለያዩ ፡ መሆናቸውን ፡ ይገልጥልናል ። በዚህ፡ አኳኋን ፡ ታላላቅ ፡ አሳብ ፡ አስበው ፡ ታላላቅ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ የሚችሉ ፡ ሕያውነት ፡ በተፈጥሮ ፡ ጠባያቸው ፡ ውስጥ ፡ ተሸፍኖ ፡ የሚኖር ፡ ሕዝቦች ፡ ናቸው ። በያንዳንዱ ፡ ደራሲ ፤ በያንዳንዱ ፡ ፈላስፋና ፡ በያንዳንዱ ፡ የሳይንስ ፡ ሊቅ ፡ አሳብ ፡ ውስጥ ፡ የተረገዘው ፡ ዕውቀት ፡ እንዲገለጥ ፡ ለማድረግ ፡ ቀስቃሽ ፡ (አዋላጅ)፡ እንደሚፈልግ ፡ ሁሉ ፡ ይህንንም ፡ በያንዳንዱ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ የሚገኘውን ፡ የሕያውነት ፡ ባሕርይ ፡ ነቅንቀው ፤ ቀስቅሰው ፡ እንዲፈነዳ ፡ እንዲነሣሣ ፡ ለማድረግ ፡ የሚችሉ ፡ ጦርነት ፤ ትምህርት ፤ ሃይማኖት ፤ ንግድ ፡ ውድድር ፡ መሆናቸው ፡ ታውቋል ። ኒችና ፡ ቶይንቢ ፡ ሕዝቦችን ፡ ከእንቅልፋቸው ፡ የሚቀሰቅሳቸው ፡ ጦርነት ፡ መሆኑን ፡ ያረጋግጣሉ ። ሄጌልና ፡ ኒች ፡ ጦርነት ፡ ለሕዝቦች ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ይደግፋሉ ። ዕውቀታቸውን ፡ መልካም ፡ ጠባያቸውን ፤ ሙያቸውን ፤ ሥነ ፡ ጥበባቸውን ፤ እንዲለማ ፡ አዲስ ፡ ስልት ፡ እንዲያገኝና ፡ ወደፊት ፡ እንዲራመድ ፡ ለማድረግ ፡ የሚችል ፡ ጦርነት ፡ ነው ። ቅኔን ፡ ከትልቅ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ እንዲደርስ ፡ የሚያደርገው ፡ ጦርነት ፡ ነው ። ለምሳሌ ፤ የሆሜር ፡ ቅኔና ፡ የግሪክ ፡ ቴአትሮች ፡ የተወለዱት ፡ ከጦርነት ፡ ስሜት ፡ በመሆኑ ፡ አብነት ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ። እኛም ፡ ባገራችን ፡ የሰንጎ ፤ የሸለላና ፡ የቀረርቱ ፡ ዜማና ፡ ግጥም ፡ በቀሩት ፡ ግጥሞቻችንና ፡ የዜማ ፡ ስልቶቻችን ፡ መካከል ፡ ይዘው ፡ የሚገኙትን ፡ ደረጃ ፡ ብናመዛዝነው ፡ የጦርነት ፡ ስሜት ፡ እሳትነት ፡ ያለው ፡ ትልቅ ፡ የቅኔ ፡ ምንጭ ፡ መሆኑን ፡ ከኒች ፡ ጋራ ፡ እንስማማበታለን ።



እንሆ ፡ የኒች ፡ አሳብ ፡ ይህ ፡ ነው ። ይህ ፡ አሳብ ፡ በከፊል ፡ እውነት ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የሥልጣኔ ፡ ጠንቅ ፡ ጦርነት ፡ መሆኑ ፡ አይካድም ። ትሮያና ፡ ካርታጎ ፡ የጠፉት ፡ በጦርነት ፡ መሆኑን ፡ ማሰብ ፡ ይገባል ። ሕያውነት ፡ ያላቸው ፡ ሕዝቦችና ፡ ሕያውነት ፡ የሌላቸው ፡ ሕዝቦች ፡ ይገኛሉ ፡ የሚሉ ፡ ሊቃውንት ፡ ደግሞ ፡ አሉ ። በእነሱ ፡ አስተያየት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ታላላቅ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ በተፈጥሮ ፡ የታደሉ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ ያስፈልጋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሄርደር ፡ የተባለው ፡ የታሪክ ፡ ፍልስፍና ፡ ሊቅ ፡ ያቀረበውን ፡ አሳብ ፡ የተመለከትን ፡ እንደ ሆነ ፡ ደግሞ ፡ ታላላቅ ፡ ሥራ ፡ የሠሩ ፡ ሕዝቦች ፡ ዳግመኛ ፡ ተመልሰው ፡ በጥበብ ፡ ረገድ ፡ የጥንት ፡ ደረጃቸውን ፡ ለማግኘት ፡ አይችሉም ። የጽዋው ፡ ተራ ፡ ቀድሞ ፡ ላልደረሳቸው ፡ ሕዝቦች ፡ ሊተላለፍ ፡ ያስፈልጋል ። ይህ ፡ እንዳይባል ፡ ደግሞ ፡ ለምሳሌ ፡ ሮማውያን ፡ ከግሪኮች ፡ ቀጥለው ፡ በሥልጣኔ ፡ ከፍ ፡ ብለው ፡ ከታዩ ፡ በኋላ ፡ ወደቁ ። ቈይተው ፡ ደግሞ ፡ ካንድ ፡ ሺ ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፡ ሁለተኛ ፡ ልደት ፡ (Renaissance) ተብሎ ፡ በሚጠራው ፡ ዘመን ፡ ሥልጣኔ ፡ ታድሳ ፡ የለመለመችው ፡ በኢጣልያ ፡ አገር ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ። አሁን ፡ እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ጉዳያችን ፡ ተመልሰን ፡ የጀመርነውን ፡ ጥናት ፡ እንቀጥላለን ።

ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ የሠለጠኑትና ፡ ያልሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ማለት ፡ ሁሉቱም ፡ ወገኖች ፡ በችግር ፡ ላይ ፡ ናቸው ። የሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ከኢንዱስትሪዎቻቸው ፡ የሚገኘውን ፡ ሀብት ፡ ያልሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ካላነሡላቸው ፡ ኢንዱስትሪዎቻቸውን ፡ እየቀነሱ ፡ መሄድ ፡ ግድ ፡ ይሆንባቸዋል ። ይህም ፡ ሠራተኞቻቸውን ፡ ማሰናበትንና ፡ ሥራውን ፡ በጠባቡ ፡ መያዝን ፡ ያስከትልባቸዋል ። ሕዝቡም ፡ ሥራ ፡ ሲያጣ ፡ ሁከት ፡ ያመጣል ። ለምሳሌ ፡ ህንድና ፡ ግብጽ ፡ የጥጥ ፡ ፋብሪኮቻቸውን ፡ ሲያስፋፉ ፤ አንደኛ ፡ ካውሮፓ ፡ የሚመጣውን ፡ በጥጥ ፡ የተሠራ ፡ ሸቀጥ ፡ አይገዙም ። ሁለተኛ ፡ ባገራቸው ፡ የሚበቅለውን ፡ ጥጥ ፡ ላውሮፓ ፡ በመሸጥ ፡ ፈንታ ፡ ራሳቸው ፡ ሠርተው ፡ ሸቀጡን ፡ ይሸጣሉ ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ እነሱ ፡ በሁለት ፡ በኩል ፡ ሲጠቀሙ ፡ አውሮፓውያን ፡ ደግሞ ፡ በሁለት ፡ በኩል ፡ ይጐዳሉ ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀሩት ፡ አገሮች ፡ በሳይንስና ፡ በቴክኒክ ፡ በኩል፡ የሚያደርጉት ፡ እርምጃ ፡ በጣም ፡ ዳተኛ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ በካፒታልና ፡ በኤክስፔርቶች ፡ እንዲረዷቸው ፡ ያስፈልጋል ። ይህ ፡ ካልሆነ ፡ በእርሻ ፤ በከብት ፡ ርቢ ፤ በማዕድንና ፡ በንግድ ፡ ያገራቸውን ፡ ሀብት ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ሊያውሉት ፡ አይችሉም ። ይህ ፡ ካልሆነ ፡ ገንዘብ ፡ አግኝተው ፡ ከሠለጠኑት ፡ አገሮች ፡ የሚፈልጉትን ፡ የቴክኒክና ፡ የሳይንስ፡ መሣሪያ ፡ ለመግዛትና ፡ እርምጃቸውን ፡ ለማፋጠን ፡ አይችሉም ። ስለዚህ ፡ መ

ረዳዳት፡የሚያገለግለው፡ላንዱ፡ወገን፡ብቻ፡ሳይሆን፡ለጋራ፡ጥቅም፡ሆኖ፡ይገኛል። በእስያ፡በኩል፡የሺና፡ከእንቅልፍ፡መንቃት፡ከጃፓን፡ጋራ፡ሲጨመር፡ለወደ፡ፊቱ፡ነጮች፡በዚያ፡በኩል፡ምንም፡ጥቅም፡እንዳያገኙ፡በሩን፡ዘግቶባቸዋል። ስለዚህ፡ለጋራ፡ጥቅም፡የሚደረገው፡መረዳዳት፡ቢሆንም፡ባይሆንም፡ሊፈጸም፡የሚችለው፡ባውሮፓና፡ባአፍሪቃ፡መካከል፡ብቻ፡ሆኖ፡ተገኝቷል። ነገር፡ግን፡በነጮች፡ዘንድ፡ስለ፡ጥቍር፡ሕዝቦች፡የማይድን፡ንቀት፡ስላለ፡ከልብ፡የሆነ፡ርዳታ፡ሊያደርጉላቸው፡ምን፡ጊዜም፡ቢሆን፡አይፈልጉም። ስለዚህ፡ያፍሪቃ፡ሕዝቦች፡በራሳቸው፡ኀይል፡ብቻ፡ተጣጥረው፡መነሣት፡ወይም፡ነጮች፡እንዲረዷቸው፡በጎ፡ፈቃድ፡እስቲያገኙ፡ድረስ፡መጠበቅ፡ግድ፡ይሆንባቸዋል። ይህ፡ጉዳይ፡በየትኛው፡መንገድ፡እንደሚፈጸም፡ሊነግረን፡የሚችል፡መጭው፡ዘመን፡ብቻ፡ነው። ጃፓን፡የፈጸመችውን፡አስደናቂ፡የሆነ፡መነሣት፡ከአፍሪቃ፡አገሮች፡አንዲቱ፡አገር፡ብትፈጽመው፡ይህ፡ጉዳይ፡ዐውቆ፡ይፈታ፡ነበር። ነገር፡ግን፡የአፍሪቃ፡ሕዝቦች፡ሕያውነት፡ያለው፡መንቀሳቀስ፡ገና፡ያላሳዩ፡በመሆናቸው፡ነጮች፡ደግሞ፡እነሱ፡ጌቶች፤ያፍሪቃ፡ሕዝቦች፡ግን፡ባሮች፡ሆነው፡እንዲኖሩ፡ለማድረግ፡የምንችልበት፡የቀድሞ፡ዘመን፡ተመልሶ፡እንዲመጣ፡የሚያደርግ፡አንድ፡ነገር፡በዓለም፡ላይ፡ይወለዳል፡በማለት፡የተሸፈነ፡ምኞት፡ስላላቸው፡ጉዳዩ፡በዚህ፡ላይ፡የቆመ፡ሆኖ፡ይታያል። በተባበሩት፡መንግሥታት፡የቴክኒክ፡እርዳታ፡በኩል፡የሠለጠኑት፡ሕዝቦች፡ላፍሪቃ፡ሕዝቦች፡የሚያደርጉት፡ርዳታ፡ጠባብ፡ሆኖ፡የሚታየው፡በዚህ፡ምክንያት፡ነው። አንድ፡ሕዝብ፡በውነት፡ራሱን፡እንዲችል፡ለማድረግ፡ሲፈለግ፡አስፈላጊ፡ሆነው፡የሚገኙት፡ርዳታዎች፡የምድር፡ባቡር፡በያውራጃው፡መዘርጋት፤የውሃ፡ግድብ፡መሥራት፤ጥጥ፤ቡና፤እኽል፡በዘመናዊ፡መሣሪያና፡ዘዴ፡በሰፊው፡መትከል፡መዝራት፡ለሕዝቡ፡ቴክኒካዊን፡የእጅ፡ሥራ፡የሚያስተምሩ፡ቍጥራቸው፡በቂ፡የሆነ፡በብዙ፡ሺሕ፡የሚቈጠሩ፡ወጣቶች፡ማስተማር፡ናቸው። ይህን፡የመሰለ፡ርዳታ፡ብዙ፡ፍሬ፡ሰጥቶ፡ለረጂውም፡ሆነ፡ለተረጂው፡ይጠቅማል።

አሜሪካ፡ለሌሎች፡አገሮች፡ስለምታደርገው፡ርዳታ፡ጋብሪዬል፡ቬራልዲ፡(Gabriel Veraldi) በጻፈው፡መጽሐፍ፡የተናገረው፡የክሪቲክ፡ቃል፡ቀጥሎ፡ያለው፡ነው።

«አሜሪካኖች፡ባ፲፱፻፵፭፡ዓ፡ም፡በታሪክ፡ታይቶ፡ያልታወቀ፡ከፍ፡ያለ፡ግምት፡በመላው፡ዓለም፡ያፈሩ፡ሆነው፡ሳለ፡ስለ፡ኤኮኖሚ፡ያላቸው፡አሳብ፡ብሩህ፡ባለመሆኑ፡በሄዱበት፡ቦታ፡ሁሉ፡ሥራ



ቸው፡የተበላሸ፡ሆኖ፡ተገኝቷል። ሲሠራበት፡የኖረ፡አሁን፡ግን፡ጊዜ፡የሻረው፡አሳብ፡(ኤዴዎሎጊ)፡በመከተላቸው፡ከስሕተት፡ላይ፡ወደቁ።

የተባበሩት፡የአሜሪካ፡መንግሥታት፡በፊሊፒን፡አገር፡በሠሩት፡ሥራ፡ረዥም፡የሆነ፡ትምህርት፡(ኤክስፔሪያንስ)፡ገጥሟቸዋል። እንደ፡ልማዳቸው፡ሁሉ፡ከቴክኒክ፡የተገኘውን፡ንዋይ፡ችሮታ፡አድርገው፡ለመንገድ፡ለጤና፡ጥበቃና፡ይህንም፡ለመሰለው፡ርዳታቸውን፡ሰጡ። ይሁን፡እንጂ፡የኑሮ፡ደረጃ፡አኳኋን፡ተቀንሶ፡ያገሩ፡ገቢ፡ገንዘብ፡እየጐደለ፡ሄደ። የፊሊፒን፡ሕዝብ፡ሰባ፡በመቶው፡(70 %) የሚኖረው፡በእርሻ፡ስለሆነ፡እርሻም፡የመንግሥቱን፡ገቢ፡አምሳ፡በመቶ፡(50%) የሚችል፡ሆኖ፡ሳለ፡ከርዳታው፡ገንዘብ፡የደረሰው፡ኻያ፡አምስት፡በመቶ፡(25 %) ብቻ፡ነው። በሌላ፡በኩል፡ደግሞ፡ከባንክ፡የሚገኘው፡ትርፍ፡ኻያ፡አምስት፡በመቶ፡(25 %) ሲሆን፡ሰማንያ፡በመቶ፡(80 %)የሚሆነው፡ቀረጥ፡የወደቀው፡ለኑሮ፡አስፈላጊ፡በሆኑት፡ሸቀጦች፡ላይ፡ነው። የቤል፡ሪፖርት፡(Bel report) ተብሎ፡የሚጠራው፡ሰነድ፡እንደ፡ገለጠው፡ሁሉ፡ከተባበሩት፡ያሜሪካ፡መንግሥታት፡የተገኘው፡ርዳታ፡አብዛኛው፡ያለቀው፡ከውጭ፡አገር፡ለመጣ፡ልዩ፡ልዩ፡የጌጥ፡ዕቃ፤ለመኖሪያ፡ለሚሆን፡ሕንፃና፡ለፊናንስ፡ሥራ፡ማከናወኛ፡በመሆኑ፡ነው። አገሩ፡የሚያፈራው፡ሀብት፡እየጨመረ፡እንዲሄድ፡ለማድረግ፡የተደረገ፡ነገር፡የለም። ከመንግሥቱ፡ባጀት፡ሩብ፡የሚሆነው፡የወጣው፡ለጦር፡ሰራዊትና፡ለፖሊስ፡ነው። ፈረንሳይ፡ከፊሊፒን፡የተለየች፡አገር፡ናት፤ይሁን፡እንጂ፡ያሜሪካ፡አስተያየት፡ይህንኑ፡የመሰለ፡ነገር፡እንዲደርስባት፡አድርጓል።»

ባልሠለጠኑት፡ሕዝቦች፡ዘንድ፡ደግሞ፡እንደ፡ትልቅ፡ጉድለት፡ሆኖ፡የሚቈጠርባቸው፡አንዱም፡ዋና፡ነገር፡የገንዘብን፡አያያዝ፡አለማወቃቸው፡ነው። በእጃቸው፡ያለው፡ገንዘብ፡ጥቂት፡ሆኖ፡ከፊታቸው፡የተደቀነው፡ሥራ፡ግን፡አያሌ፡ነው። ማንኛውም፡ሥራ፡ያለ፡ገንዘብ፡የማይከናወን፡መሆኑ፡ሲታወቅ፡ገንዘባቸውን፡በቍጠባና፡በጥንቃቄ፡ጠብቀው፡በመያዝ፡ፈንታ፡ያለአገባብ፡ያባክኑታል፤ይሻሙታል፤ይዘርፉታል። ስለዚህ፡ሥራው፡እየሞተ፡የሥልጣኔያቸውም፡እርምጃ፡ወደ፡ኋላው፡እየተጐተተ፡ይሄዳል። ይኸውም፡አሜሪካኖች፡በሺና፡በፊሊፒንና፡በኢንዶኔዚያ፡የሰጡትን፡የገንዘብ፡ርዳታ፡ምክንያት፡በማድረግ፡ከዚህ፡ቀደም፡በሰፊው፡ገልጠው፡ጽፈውታል። ሀብታሞች፡አገሮች፡በማንኛውም፡አኳኋን፡ገንዘብ፡ቢያባክኑ፡የተረፋቸው፡ሀብታሞች፡በመሆናቸው፡አይነወርባቸውም። ድኾች፡ለሆኑ፡

አገሮች ፡ ግን ፡ ገንዘብን ፡ ማባከን ፡ እንደ ፡ ወንጀል ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠርባቸዋል ። ይህ ፡ ደግሞ ፡ አሜሪካኖች ፡ በበኩላቸው ፡ በሚገባ፡የሚመረሩበት፡ ነገር ፡ ነው ።

በዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የቀለም ፡ ጕዳይ ፡ ምን፡ያኽል፡ ከባድ ፡ መሆኑን ፡ ለመረዳት ፡ በአሜሪካ ፡ አገር ፡ በደቡብ ፡ አፍሪቃ ፤ በኮንጎ ፡ ቤልዥ ፤ በቀሩትም ፡ በነጮች ፡ እጅ ፡ በሚገዙት ፡ ያፍሪቃ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ በነጮችና ፡ በጥቍሮች ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ ሁኔታ ፡ ማስተዋል፡ያስፈልጋል።ይልቁንም፡በአሜሪካና፡በደቡብ፡አፍሪቃ፡ያለው፡ በጥቍሮች ፡ ላይ ፡ የወደቀ ፡ ጭቈና ፡ በምን ፡ ሁኔታ ፡ እንደሚፈጸም ፡ ለማየት ፡ መላው ፡ ዓለም ፡ በመናፈቅ ፡ የሚጠባበቀው ፡ ነገር ፡ ነው ። ምናልባት ፡ በእነዚህ ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ያለው ፡ ጕዳይ ፡ የሚያገኘው ፡ ፍጻሜ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በጠቅላላው፡ ስለ፡ጥቍሮች ፡ ሕዝቦች ፡ ጕዳይ ፡ ከሚወለደው፡ሁኔታ ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ ሆኖ ፡ ሳይገኝ፡ የሚቀር፡አይመስልም ።

ያውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ አሁን ፡ የሚደክሙበት ፡ አንድ ፡ መንግሥት ፡ የመሆንን ፡ አሳብ ፡ ከፍጻሜ ፡ የማድረሱ ፡ ሥራ ፡ ቢቀናላቸው ፡ በኅብረታቸው ፡ ከተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ መንግሥታትና ፡ ከመስኮብ ፡ ጋራ ፡ ሊወዳደር ፡ የሚችል ፡ ኀይልበት ፡ ለመፍጠር ፡ ይችላሉ ። ከዚህ ፡ ዐላማ ፡ የደረሱ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ፈረንሳይ፤ ጀርመን ፤ ኢጣልያና ፡ ሌሎችም ፡ ተጨምረው ፡ በአፍሪቃ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ግብ፡የተሰነዘረ፡ ፖሊቲካ ፡ ለማደራጀት ፡ የሚመኙና ፡ የሚችሉ ፡ መሆናቸውን ፡ እነሱ ፡ ራሳቸው ፡ በየጊዜው ፡ በግልጥ ፡ ተናግረዋል ። ይህ ፡ የእነሱ ፡ ዐቅድ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ውሳኔው ፡ በትክክል ፡ የታወቀ ፡ ባይሆን ፡ ላፍሪቃውያን ፡ የሚያሠጋ ፡ መሆኑ ፡ አይጠረጠርም ።

በዘመናችን ፡ ያለቿውን ፡ ይህቿን ፡ ሥልጣኔ ፡ መላው ፡ ዓለም ፡ እንዲወርሳት ፡ ለማድረግ ፡ አስባ ፡ አውሮፓ ፡ የተነሣች ፡ በመሆኗ ፡ ትልቅ ፡ አላፊነት ፡ ተሸክማለች ። ይህም ፡ የሚያስከትለው ፡ ነገር ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በትክክል ፡ ልታውቀው ፡ አልቻለችም ። በመሬት ፡ ላይ ፡ የሚኖሩ ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ የሷን ፡ ትምህርትና ፡ አስተዳደግ ፡ የሷን ፡ የኤኰኖሚ ፡ አመራር ፡ የሷን ፡ ሲያንስ ፡ የሷን ፡ ታሪክ ፡ የሷን ፡ የፓርለማ ፡ ሥርዐት ፡ የሷን ፡ ሊቴራቱር ፡ (ድርሰት)፡ የሷን ፡ ፍልስፍና ፡ በጠቅላላው፡ የሷ ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ክፉውንም ፡ ደጉንም ፡ ሳትመርጥና ፡ ሳትለይ ፡ ያላትን ፡ ሁሉ ፡ በጠቅላላው ፡ ለዓለም ፡ ለማውረስ ፡ አስባ ፡ የተነሣችናት ። ኰሚኒስምን ፡ ለመስኮብ ፡ የሰጠቻት ፡ እሷ ፡ ናት ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ መልሳ ፡ በዚሁ ፡ ትመረርበታለች ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እሷ ፡ ያፈራችው ፡



ነገር ፡ ሁሉ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ላሉ ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ የሚጠቅም ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ የሚቻል ፡ አይደለም ። ነገር ፡ ግን ፡ በግድ ፡ እንዲቀበሉት ፡ በመድፍና ፡ በቦምብ ፡ እየደበደበች ፡ አስገድዳቸዋለች ። በኋላም ፡ እንደዚህ ፡ አድርጋ ፡ እያስገደደች ፡ የሰጠቻቸው ፡ ሥልጣኔ ፡ በሌሎቹ ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ ጐጂ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ማስከተሉን ፡ ስትረዳው ፡ አላፊዎች ፡ ታደርጋቸዋለች ። አውሮፓዊም ፡ ሆነ ፡ ቀይ ፡ ቆዳ ፡ አሜሪካዊም ፡ ሆነ ፡ ሌላ ፡ ማንኛውም ፡ የዘር ፡ ልዩነት ፡ ሳይኖር ፡ ሰው ፡ ሲባል ፡ ሁሉም ፡ በሥነ ፡ ፍጥረቱ ፡ የሥልጣኔ ፡ ተቃዋሚ ፡ ነው ። እያንዳንዱ ፡ ሕዝብ ፡ ከሥር ፡ መሠረቱ ፡ ያልሠለጠነ ፡ ነበር ። ሥልጣኔ ፡ በሥነ ፡ ፍጥረቷ ፡ ከሰው ፡ ባሕርይ ፡ ጋራ ፡ የማትስማማ ፡ ናት ። በልክ ፡ እየተመጠነች ፡ ካልተሰጠች ፡ በቀር ፡ ከሞት ፡ ልታደርስ ፡ ትችላለች ። ሮፓውያን ፡ ከዚህ ፡ አሁን፡ ከሚገኙበት ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ የደረሱት ፡ ብዙ ፡ መቶ ፡ ዓመታት፡ በፈጀባቸው ፡ መሻሻልና ፡ ሁከትም ፡ በሞላበት ፡ መንገድ ፡ ካለፉ ፡ በኋላ ፡ ነው ። የምዕራብ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ የተባለው ፡ ያቋቋማቸው ፡ የሥልጣኔ ፡ ሥራቶችና ፡ ሕግጋቶች ፡ ሁሉ ፡ ጥሩ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ለማለት ፡ ፈጽሞ ፡ የማይቻል ፡ ነው ። ጐቢኖ ፡ እንኳ ፡ በዚህ ፡ ጕዳይ ፡ ላይ ፡ ባደረገው ፡ ጥልቅ ፡ በሆነ ፡ ጥናት ፡ ሲናገር ፡ በፖለቲካ ፡ ረገድ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ካውሮፓ ፡ በጣም ፡ የተሻለች ፡ መሆኗን ፡ ተናግሯል ። አሁንስ ፡ ቢሆን ፡ አውሮፓ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ የምታስተምረን ፡ ነገር ፡ ምንድነው ? የሬቦሊሲዮንን ፡ አሳቦችና ፡ ከሶሬልና ፡ ከማርክስ ፡ የተገኙትን ፡ የውስጥ ፡ ብጥብጥና ፡ የግፍ ፡ ሥራን ፡ አይደለምን ? በዚህ ፡ ረገድ ፡ አውሮፓ ፡ ያመጣችውን ፡ ጕዳት ፡ የሞላበትን ፡ በሰው ፡ ዘር ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ የሚታየውን ፡ ሁኔታ ፡ ቦድሌር ፡ የተባለው ፡ ባለቅኔ ፡ የተናገራቸው ፡ ቃሎች ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ ገልጠውልናል ። ቃሎቹም ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፤

ደስታንና ፡ ጥፋትን ፡ እንዳገኘሽ ፡ ትዘሪያለሽ ።

ሁሉን ፡ የምታስተዳድሪ ፡ ሆነሽ ፡ ሳለሽ ፡ በምንም ፡ ነገር ፡ አትጠየቂም ።

Tu sèmes au hasard la joie et les désastres
Et tu gouvernes tout et ne réponds de rien.

# የኢትዮጵያ፡ተግባር።

ወደ፡ራሳችን፡ጉዳይ፡አሁን፡መለስ፡ብለን፡ብንመለከት፡ብዙውን፡ነገር፡በግልጥ፡ልንረዳው፡እንችላለን። ከአዲሷ፡ሥልጣኔ፡የተገኙት፡እንደ፡አቶሞቢል፣ ራዲዮ፡ስልክ፡ሰዓት፡አኤሮፕላን፡ባቡር፡የመሰሉ፡የጥበብ፡ሥራዎች፡ወደ፡አገራችን፡ሲመጡ፡መዘዛቸውን፡ጨምረው፡መጥተዋል። ቀድሞ፡ባገራችን፡ያልነበሩ፡በሽታዎች፡አሁን፡ገብተው፡እንደሚገኙ፡ሁሉ፡በጠባይም፡በኩል፡እንደዚሁ፡ነው። አባቶቻችን፡ከሦስት፡ሺሕ፡ዘመናት፡በላይ፡የኢትዮጵያ፡ነጻነት፡ተጠብቆ፡እንዲኖር፡ለማድረግ፡የቻሉት፡በጀግንነታቸው፡ነው፡ብለን፡እናምናለን። ነገር፡ግን፡ያለመልካም፡ጠባይ፡ጀግንነት፡ብቻውን፡ዋጋ፡ሊኖረው፡አይችልም። አባቶቻችን፡የጀግንነታቸው፡ሕንጻ፡የተቋቋመው፡ጥብቅ፡በሆኑ፡መልካም፡ጠባዮች፡ላይ፡ነበር። ይኸውም፡ (vertu) የሚባለው፡ነው።

(ረናን)፡ስለዚህ፡ጉዳይ፡የተናገረውን፡ከዚህ፡ቀጥሎ፡ያለውን፡ቃል፡እናስተውል።

«La force d'une société réside en deux choses: d'abord la vertu populaire, ce grand réservoir de dévouement, de sacrifice, de force morale instinctive que les races nobles portent en elles comme un héritage de leurs ancêtres. . . . »

ያንድ፡ሕዝብ፡ጉልበቱ፡ከሁለት፡ነገሮች፡የሠረጸ፡ሆኖ፡ይገኛል። ከሁሉ፡አስቀድሞ፡የሕዝብ፡መልካም፡ምግባር፡ነው፣ የታማኝነት፣ የመሥዋዕትነት፣ ከተፈጥሮ፡የመጣ፡የሞራል፡ኀይል፡የሚገኙበትን፡ይህን፡ታላቅ፡መከማቻ፡ከቀድሞ፡አያቶቻቸው፡የወረሱት፡ቅርስ፡አድርገው፡የተከበሩ፡የሰው፡ዘሮች፡ይዘውት፡ይገኛሉ»።

ረናን፡ይህን፡በመጀመሪያ፡ደረጃ፡ሲያደርገው፡ከሱ፡ቀጥሎ፡የሚመጣ፡ትምህርት፡መሆኑን፡አሳስቧል። እንግዲህ፡ከአያት፡ከቅድም፡አያት፡ማለት፡ኢትዮጵያ፡ከተቋቋመች፡ጀምሮ፡ሲወርድ፡ሲዋረድ፡እየተከማቸ፡የመጣው፡የሕዝቡ፡መልካም፡ምግባር፡ይዟቸው፡የሚገኙት፡የትልቅነት፡ጠባዮች፡እንዴት፡ያሉ፡ኖረዋል? ለምሳሌ፣ እውነትን፡መውደድ፣ የወዳጅን፡ፍቅር፡ከገንዘብ፡ፍቅር፡በላይ፡አድ

ርኅ ፡ መመልከት ፤ በመካከላቸው ፡ የጋለ ፡ ወዳጅነት ፡ እንዲኖር ፡ መጣጣር ፤ እርስ ፡ በርስ ፡ መከባበር ፤ መሥዋዕትነትን ፡ መቀበል ፤ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ እነዚህን ፡ የመሰሉ ፡ ጠባዮች ፡ ይገኙ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ዝርዝራቸውን ፡ በሙሉ ፡ ለማግኘት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ላይ ፡ ትልቅ ፡ ጥናት ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል ። ይህንን ፡ ተግባር ፡ ወደ ፊት ፡ ለሚነሡ ፡ ደራስያን ፡ ትተንላቸዋል ። በቀድሞዎቹ ፡ ባለፉት ፡ ትውልዶች ፡ ሁሉ ፡ የነበረውን ፡ ትተን ፡ አሁን ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ በእነ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ አባቶቻችን ፡ የነበሯቸውን ፡ መልካም ፡ ጠባዮች ፡ በሕይወት ፡ ተርፈው ፡ ያሉ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ሲያጫውቱን ፡ ተረት ፡ ይመስለናል ። በእነሱ ፡ ዘንድ ፡ የነበረውን ፡ የትልቅነት ፡ ጠባይ ፡ መቼም ፡ ቢሆን ፡ እኛ ፡ ልናገኘው ፡ አንችልም ። በዘመናችን ፡ ሥልጣኔ ፡ እየተቀረጽንና ፡ እየተሻሻልንም ፡ ሆነ ፡ እየተመረዝን ፡ መሄድ ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ኋላችን ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ለመመለስ ፡ አንችልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዘመናችን ፡ ሥልጣኔ ፡ ቴክኒኩንና ፡ ሳይንሱን ፡ በሙሉ ፡ እጅ ፡ ሳናደርግ፡ የቀድሞ ፡ ቅርሳችንን ፡ ብናጣ ፡ ከሁለት ፡ ዛፍ ፡ የወደቅን ፡ እንሆናለን ።

በሥልጣኔ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀሩት ፡ አህጉሮች ፡ አፍሪቃና ፡ እስያ ፡ ሲሆኑ ፡ ለእስያ ፡ ሕዝቦች ፡ መጀመሪያ ፡ ጃፓን ፡ ቀጥሎ ፡ ሺና ፡ ግንባር ፡ ቀደምትነቱን ፡ ይዘው ፡ የሥልጣኔ ፡ መሪዎች ፡ ሆነው ፡ ተገኝተዋል ። በአፍሪቃ ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ይህንን ፡ ቦታ ፡ የምትይዝ ፡ የትኛይቱ ፡ አገር ፡ ነች ? በታሪክም ፡ ሆነ ፡ በጆግራፊ ፡ በጥንት ፡ ሥልጣኔዋም ፡ ሆነ ፡ አሁን ፡ ባለችበት ፡ ደረጃ ፡ ይህ ፡ ዕድል ፡ ኢትዮጵያ ፡ የታጨችለት ፡ ሆና ፡ ትገኛለች ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ዐላማ ፡ ለመድረስ ፡ ስትፈልግ ፡ በሁሉም ፡ በኩል ፡ የተዘጋጀች ፡ ሆና ፡ መገኘት ፡ ያስፈልጋታል ። ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የዘመናዊውን ፡ ትምህርት ፡ የሚማሩት ፡ ወጣቶች ፡ እስካሁን ፡ ቍጥራቸው ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ አለመገኘቱን ፡ ማሰብ ፡ ያስፈልጋል ። በጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ ጕዳይ ፡ የተቃና ፡ መንገድ ፡ የሚይዝበትን ፡ ዘዴ ፡ ማግኘት ፡ ይገባል ። ከፍ ፡ ብለን ፡ እንደ ፡ ተናገርነው ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ አንድ ፡ መንግሥት ፡ የሥልጣኔ ፡ ሥራዎችን ፡ ለማስፋፋት ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ወጪ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ። ገንዘቡም ፡ የሚመጣው ፡ ከሕዝቡ ፡ ካገሪቱ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ከመሰለው ፡ ታላቅ ፡ ዐላማ ፡ ለመድረስ ፡ እያንዳንዱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የግል ፡ ጥቅሙንና ፡ የግል ፡ ሀብቱን ፡ ለጠቅላላው ፡ ያገር ፡ ሀብትና ፡ ለጠቅላላው ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ ሲል ፡ መሥዋዕት ፡ ማድረግ ፡ ግድ ፡ ይሆንበታል ። ይህ ፡ ካልሆነ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በቀሩት ፡ የአፍሪቃ ፡ ሕዝቦችና ፡ በዓለም ፡ ፊት ፡ ልታከናውነው ፡ የሚገባት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ተግባር ፡ ፍጻሜ ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልም ። ባሁኑ ፡ ሁኔታ ፡



የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከአፍሪቃ ፡ አገሮች ፡ ብዙዎች ፡ በዘመኑ ፡ ትምህርት ፡ በኩል ፡ የቀደሚት ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ። እሷም ፡ በሥልጣኔ ፡ ግንባር ፡ ቀደም ፡ ሆና ፡ ለመገኘት ፡ ስትፈልግ ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ በትምህርት ፡ በኩል ፡ ብልጫ ፡ ያላት ፡ ሆና ፡ መገኘት ፡ አለባት ። ይህንን ፡ ስታደርግ ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ረናን ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ የቀድሞ ፡ ሥልጣኔዋ ፡ ቅርስ ፡ ላሁኑ ፡ ሥልጣኔ ፡ ጥብቅ ፡ የሆነ ፡ መሠረት ፡ እንዲያገኝ ፡ ስለሚያደርግላት ፡ በሌሎቹ ፡ የአፍሪቃ ፡ ሕዝቦች ፡ ላይ ፡ የሚኖራት ፡ ብልጫ ፡ የተረጋገጠ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። በዛሬው ፡ ሥልጣኔ ፡ የተበለጠች ፡ ሆና ፡ በቀድሞው ፡ ብቻ ፡ የበላይ ፡ ልሁን ፡ ብላ ፡ ብታስብ ፡ አሳቧ ፡ የተቃና ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

በትምህርት ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ጕዳይ ፡ ስንመለከት ፡ መንግሥት ፡ አሁን ፡ ባለው ፡ የገንዘብ ፡ ዐቅም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ በሙሉ ፡ ለማስተማር ፡ አይፈቀድለትም ። መንግሥት ፡ የሚሠራው ፡ ሕዝቡ ፡ በሚያፈራውና ፡ በሚገብረው ፡ ገቢ ፡ ገንዘብ ፡ መሠረት ፡ መሆኑን ፡ መዘንጋት ፡ አይገባም ። ያለውን ፡ ጠቅላላ ፡ ገቢ ፡ ለቀሩትም ፡ ሥራዎች ፡ እንዲዳረስ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ፡ እንጂ ፡ በሞላ ፡ ለትምህርት ፡ ብቻ ፡ እንዲውል ፡ ለማድረግ ፡ አይቻልም ። በኤኮኖሚ ፡ በኩል ፡ አገሪቱ ፡ ለጊዜው ፡ ደካማ ፡ ስለ ፡ ሆነች ፡ በሞላ ፡ የመንግሥቱን ፡ ገቢ ፡ ገንዘብ ፡ ለትምህርት ፡ ብቻ ፡ እንዲውል ፡ ቢደረግ ፡ እንኳ ፡ ትምህርትን ፡ በሙሉ ፡ እንዲዳረስ ፡ ለማድረግ ፡ የሚበቃ ፡ አይሆንም ። ስለዚህ ፡ ሕዝቡ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የጀመረውን ፡ የትምህርት ፡ ታክስ ፡ ምሳሌ ፡ አድርጎ ፡ ራሱ ፡ እንዲተጋበትና ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ መንግሥቱን ፡ እንዲደግፍ ፡ ያስፈልጋል ፡ እንጂ ፡ ሸክሙን ፡ በሙሉ ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ መጣል ፡ አይገባውም ። ይህንንም ፡ ለመፈጸም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የመረጃ ፡ ዘዴ ፡ ሊፈጠር ፡ ይቻላል ። በየጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ያሉት ፡ የትምህርት ፡ ቦርዶች ፡ ጕዳዩን ፡ በሰፊ ፡ አስተያየት ፡ ቢያጠኑት ፡ ብዙ ፡ መንገድ ፡ ሊያገኙለት ፡ ይችላሉ ።

ሰው ፡ በእሱ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ኀይልና ፡ ደካማነት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለይቶ ፡ ሲያውቀው ፡ ይህ ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ እርምጃ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠርለታል ። ይህንን ፡ ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ በሱ ፡ ዘንድ ፡ ትልቅ ፡ ደካማነት ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ማዕድን ፡ ያለባቸውንና ፡ የሌለባቸውን ፡ ቦታዎች ፡ ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ መመርመር ፡ ያስፈልጋል ። ሰዎችም ፡ እንደዚሁ ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ ነው ፡ ኤመርሰን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ የተናገረው ፤

«ሰማይን ፡ በሙሉ ፤ ሰባቱን ፡ ከዋክብት ፡ የዓመቱን ፡ ፀሐይ ፤ የቄሳርን ፡ ክንድ ፤ የፕላቶንን ፡ አንጐል ፤ የክርስቶስን ፡ ልብ ፤ የሼክስፒርን ፡ ዜማ ፤ በኔ ፡ ውስጥ ፡ ይገኜዋለሁ» ።

«Je possède en moi tout le ciel
Les sept étoiles, l'année solaire
Le bras de César et le cerveau de Platon
Et le coeur du Christ et le chant de Shakespeare.»

ይህም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ፕላቶን ፡ ፈላስፋ ፡ እንደ ፡ ቄሳር ፡ ጐበዝ ፤ እንደ ፡ ክርስቶስ ፡ ሩኅሩኅ ፤ እንደ ፡ ሼክስፒር ፡ ባለቅኔ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አይደለም ። ነገር ፡ ግን ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፤ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፤ ስለዚህ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ መመርመር ፡ ይገባዋል ፡ ለማለት ፡ ነው ። ራስን ፡ መመርመር ፡ ማለትም ፡ ትምህርትን ፡ ተመርኵዞ ፡ በተገኘው ፡ ዘዴ ፡ ሁሉ ፡ መሞከር ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻለው ፡ ወጣት ፡ ሁሉ ፡ ትምህርት ፡ ሲዳረሰው ፡ ነው ። መንግሥትና ፡ ሕዝብም ፡ እንደዚሁ ፡ ናቸው ። ኢትዮጵያ ፡ የመሬቷንና ፡ የሕዝቧን ፡ ችሎታ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ብታደርገው ፡ ምን ፡ ለመፈጸም ፡ እንደምትችልና ፡ ዕድሏ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሆኖ ፡ እንደሚገኝ ፡ ገና ፡ መርምራ ፡ አላወቀችውም ። ይህን ፡ በተረዳችው ፡ ጊዜ ፡ ለማድረግ ፡ የምትችለውንና ፡ የማትችለውን ፡ ነገር ፡ ለይታ ፡ ታውቃለች ። ይህም ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ እርምጃ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ። እንግዲህ ፡ ከዚህ ፡ ለመድረስ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይገባታል ? ቅርሷ ፡ የሆነውን ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ ሳትለቅ ፡ ትምህርትን ፡ በማስፋፋት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ከዚህ ፡ ዐላማ ፡ ለመድረስ ፡ የምትችለው ። አባቶቻችን ፡ ከሦስት ፡ ሺሕ ፡ ዘመናት ፡ በሚበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነጻነቷ ፡ ተከብሮ ፡ እንዲኖር ፡ ያደረጉት ፡ በጀግንነት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በመልካም ፡ ጠባያቸው ፡ ጭምር ፡ ነው ፡ ብለናል ።

ስለዚህ ፡ ጕዳይ ፡ አንድ ፡ ምሳሌ ፡ እጠቅሳለሁ ። ከቀድሞ፡ ሽማግሌዎች ፡ መካከል ፡ የማውቃቸው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበሩ ። እሳቸውም ፡ በጣም ፡ ባለጸጋ ፡ አይደሉም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ ከመጨረሻ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ የወደቁ ፡ ድኻ ፡ አልነበሩም ። በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ እንዲያውም ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ነበራቸው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ ገንዘባቸውን ፡ በብድር ፡ ሰጥተው ፡ ሳይመልሱላቸው ፡ ቀርተዋል ። በዕድሜያቸው ፡ ማለቂያ ፡ ላይ ፡ ጤንነት ፡ ስላጡ ፡ በተለየም ፡ ዐይናቸው ፡ ታውኮ ፡ ከቤት ፡ መዋል ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው ። ተበዳሪዎች ፡ ከሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የተቀበሉት ፡ ማስረጃ ፡ ሰነድ ፡ በእጃቸው ፡ ያለ ፡



በመሆኑ ፡ ዘመዶቻቸው ፡ ችግራቸውን ፡ በመመልከት ፡ ያበደሩትን ፡ ገንዘብ ፡ ከየሰዉ ፡ ላይ ፡ እንዲቀበሉ ፤ እንቢ ፡ የሚሉትንም ፡ በጠበቃ ፡ አማካይነት ፡ እየከሰሱ ፡ እንዲከፍሉ ፡ እንዲያስገድዷቸው ፡ ምክር ፡ ሲሰጧቸው ፡ እሳቸው ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ ይመልሱላቸዋል ። የተበደረኝ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ባይቸግረው ፡ ኖሮ ፡ አይበደርም ፡ ነበር ፤ ካበደርኩት ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ሳይመልስልኝ ፡ የቀረው ፡ ባያገኝ ፡ ነው ። እኔም ፡ ያበደርኩት ፡ ወዳጄ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሲቸገር ፡ በማየቴ ፡ ልረዳው ፡ ፈልጌ ፡ ነው ። አሁን ፡ ብከሰሰው ፡ ወዳጄ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ ጠላት ፡ ይሆነኛል ። ስለዚህ ፡ ከሰው ፡ ወይም ፡ ከገንዘብ ፡ አንዱን ፡ መምረጥ ፡ ስላለብኝ ፡ የሰውየው ፡ ፍቅር ፡ ይበልጥብኛልና ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡ ይመልስልኝ» ። ዘመዶቻቸውም ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ አሳሰበዋቸዋል ፤ «አንዳንዶቹ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ እርስዎ ፡ እንደሚሉት ፡ የማይከፍሉት ፡ ገንዘብ ፡ ስላጡ ፡ ይሆናል ፤ አብዛኞቹ ፡ ግን ፡ ሳይኖራቸው ፡ ቀርቶ ፡ አይደለም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለመክፈል ፡ ፈቃድ ፡ እየጐደላቸው ፡ ነው» ። እሳቸውም ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ ይመልሳሉ ፤ «እናንተ ፡ እንደምትሉት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ሊከፍል ፡ የሚችለውንና ፡ የማይችለውን ፡ በምን ፡ ለይቼ ፡ ዐውቀዋለሁ» ?

እኒህ ፡ ሰው ፡ በቤታቸው ፡ ውስጥ ፡ ችግር ፡ እያለ ፡ ብዙ ፡ ዓመታት ፡ ሕመምተኛ ፡ ሆነው ፡ ከቤት ፡ ሲውሉ ፡ ገንዘብ ፡ ከተበደሯቸው ፡ ሰዎች ፡ አንዱን ፡ እንኳ ፡ ሳይከሱ ፡ ለሞት ፡ በቁ ። እንዲያውም ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ገንዘብ ፡ በእጃቸው ፡ ሲገባ ፡ ለተቸገሩ ፡ ሰዎች ፡ ማበደራቸውን ፡ ይቀጥሉ ፡ ነበር ።

እኛ ፡ የዛሬ ፡ ዘመን ፡ ሰዎች ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ በሒሳብ ፡ መልክ ፡ እንመለከተዋለን ። እያንዳንዷ ፡ ሳንቲም ፡ ስትጠራቀም ፡ ሚሊዮን ፡ ብር ፡ ለመሆን ፡ እንደምትችልና ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ያለገንዘብ ፡ እንደማናገኝ ፡ ተምረነዋል ። ቍጠባ ፡ ለብልጽግና ፡ እናቱ ፡ መሆኗን ፡ ተረድተነዋል ። ገንዘብ ፡ ማባከን ፡ ከድኽነት ፡ ላይ ፡ የሚጥል ፡ መሆኑን ፡ ደርሰንበታል ። ይኸ ፡ መሆን ፡ ትርጉሙ ፡ ምን ፡ መሆኑን ፡ እናውቃለን ። አልቤር ፡ አይንሽታይን ፡ ትልቁ ፡ የሳይንስ ፡ ሊቅ ፡ የሕይወት ፡ ታሪኩን ፡ ስናነብ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ያገኝ ፡ የነበረውን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ለተቸገሩ ፡ ሰዎች ፡ መስጠት ፡ ልማዱ ፡ ነበር ። በሊቅነቱ ፡ የሚያደንቁት ፡ ሰዎች ፡ በዓል ፡ ሲሆን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስጦታ ፡ ያደርጉለታል ። የኑሮ ፡ ችግር ፡ ያለባቸው ፡ ሰዎች ፡ ቸር ፡ መሆኑን ፡ ስለሚያውቁ ፡ ሊለምኑት ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲሄዱ ፡ ያንን ፡ ያገኘውን ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብም ፡ ሆነ ፡ ዕቃ ፡ ያከፋፍላቸውና ፡ እሱ ፡ ባዶ ፡ እጁን ፡ ይቀራል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በኪሱ ፡ ያለውን ፡ ገንዘብ ፡ በየመንገዱ ፡ ለሚያገኛቸው ፡ ሰዎች ፡ ተቸግረው ፡ ሲለምኑት ፡ እየሰጠ ፡ ለ

ኦቶቡስና ፡ ለባቡር ፡ የሚከፍለው ፡ ገንዘብ ፡ ጐድሎበት ፡ የተቸገረበት ፡ ጊዜ ፡ ይገኛል ።

አንድ ፡ ሰው ፡ በእጁ ፡ ያለውን ፡ ገንዘብ ፡ በችሮታ ፡ ሰጥቶ ፡ ከችግር ፡ ላይ ፡ ሲወድቅ ፡ ሒሳብ ፡ የማያውቅ ፡ በመሆኑ ፤ የኤኮኖሚ ፡ ትምህርት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስላላነበበ ፡ ይህ ፡ ደረሰበት ፡ ብለን ፡ እንደ ፡ ሞኝ ፤ እንዳልተማረ ፡ አድርገን ፡ እንቈጥረዋለን ። ነገር ፡ ግን ፡ ከአይንሽታይን ፡ የበለጠ ፡ ሒሳብ ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ ይገኛል ፡ ወይ ? የባንክ ፡ ሒሳብ ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ቤት ፡ (ኮንታቢሊቴ) ፡ መቀነስና ፡ መደመር ፡ አይሠራም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እሱ ፡ የሚሠራው ፡ ከሒሳቦች ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ የሆነውን ፡ ሒሳብ ፡ ነው ። የሚሠራውና ፡ የሚከታተለው ፡ ማቴማቲክ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ትምህርት ፡ የሚጠይቅና ፡ በጣም ፡ የጠለቀ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ሊገባቸው ፡ የሚችል ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ እንኳ ፡ አይገኙም ። ስለዚህ ፡ ሒሳብ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስላላወቀ ፡ ነው ፡ ገንዘቡን ፡ የሚያባክን ፡ ለማለት ፡ አንችልም ። ርግጥ ፡ ነው ፡ የነጋዴዎችንና ፡ የቸርቻሪዎችን ፡ ሒሳብ ፡ ለማወቅ ፡ ትልቅ ፡ የሆነችው ፡ ነፍሱ ፡ አልፈቀደችለትም ።

እንግዲህ ፡ አይንሽታይንና ፡ እኒያ ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ የጠቀስናቸው ፡ ሽማግሌ ፡ በሚያስደንቅ ፡ አኳኋን ፡ ይመሳሰላሉ ። ኢትዮጵያ ፡ በጥንት ፡ ሥልጣኔዋ ፡ ያፈራቻቸው ፡ ሰዎች ፡ እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ነበሩ ። ሰውን ፡ የጨዋ ፡ ልጅ ፡ ያሰኙትን ፡ ነገሮች ፡ ተረድተው ፡ እየተቀጡ ፡ በጥሩ ፡ አስተዳደግ ፡ በማደጋቸው ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ያዩ ፡ በመሆናቸው ፤ ገንዘብ ፡ በድን ፡ አካል ፡ ሲሆን ፡ ሰው ፡ ግን ፡ የተከበረ ፡ ፍጡር ፡ በመሆኑ ፡ ሁለቱን ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ስናስቀምጣቸው ፡ ሰው ፡ ሺሕ ፡ ጊዜ ፡ ከገንዘብ ፡ እንደሚበልጥ ፡ ስላወቁት ፡ ቸር ፡ ሆኑ ። አይንሽታይን ፡ ደግሞ ፡ በዘመናችን ፡ ሥልጣኔ ፡ ማለት ፡ በሳይንስ ፡ ያለው ፡ ዕውቀት ፡ በጣም ፡ የላቀ ፡ ሲሆንና ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ አይንሽታይንም ፡ በፊዚክ ፡ ያለውን ፡ ግዙፍ ፡ አካል ፡ የሆነውን ፡ ዓለም ፡ የሥነ ፡ ፍጥረቱን ፡ ጠባይ ፡ መርምሮ ፡ ሊረዳው ፡ ሲችል ፡ የሰውን ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ግን ፡ በሳይንስ ፡ መርምሮ ፡ አልደረሰበትም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በመራብ ፤ በመጠማት ፤ በመታመምና ፡ በመሞት ፡ በኩል ፡ በእሱ ፡ ማለት ፡ የሳይንስ ፡ ሊቀ ፡ ጠቢባን ፡ በሆነው ፡ በአይንሽታይንና ፡ ባንድ ፡ ለማኝ ፡ መካከል ፡ ምንም ፡ ልዩነት ፡ አለመኖሩን ፡ ያውቃል ። አይንታሽይንና ፡ አንድ ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ እኩል ፡ ይራባሉ ፤ እኩል ፡ ይጠማሉ ፤ እኩል ፡ ይታመማሉ ፤ እኩል ፡ ይሞታሉ ። ይህን ፡ የሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ሕግ ፡ ማንም ፡ ሊ ቅ ፡ ሊሽረው ፡ አልቻለም ። እንግዲህ ፡ የሦስት ፡ ሺሕ ፡ ዘመን ፡ ዕድሜ ፡ ያላት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔና ፡ የዛሬይቱ ፡ ሥልጣኔ ፡ ያፈሯቸው ፡ ሰዎች ፡ ሲበስሉ ፡ ሁለቱም ፡ ሰው ፡ ነፍሱ ፡ ከፍተኛነት ፡ እንድታ



ገኝና ፡ የለጋስነት ፡ ጠባይ ፡ እንዲያድርባት ፡ ከሚያደርገው ፡ አስተያየት ፡ ላይ ፡ የደረሱ ፡ መሆናቸውን ፡ ይገልጥልናል ።

በዘመናችን ፡ ሥልጣኔ ፡ ተከትበን ፡ ያደግነው ፡ እኛ ፡ የዛሬ ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ የተሰጠን ፡ አስተያየት ፡ ሌላ ፡ ነው ። በምንማርባቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ የኤኮኖሚ ፤ የባንክ ፤ የከፍተኛ ፡ ንግድ ፤ የኢንዱስትሪ ፤ ዕውቀቶች ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብ ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ መሆኑን ፡ አረጋግጠውልናል ። እንደዚሁም ፡ በሠለጠኑት ፡ አገሮች ፡ ሄደን ፡ እንደ ፡ ተመለከትነው ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብ ፡ የሌለው ፡ ድኻ ፡ ሰው ፡ በጨዎች ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ሲገኝ ፡ ለምጥ ፡ እንደ ፡ ያዘው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚያፍር ፡ መሆኑን ፡ አይተናል ። አይንሽታይንም ፡ ሆነ ፡ ማንም ፡ ሊቅ ፡ ይህንን ፡ የሚሽር ፡ አሳብ ፡ ቢሰጠን ፡ አይገባንም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የጋንዲንና ፡ የቪቬካናንዳን ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ብንመለከተው ፡ ከአይንሽታይንና ፡ ከኒያ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሽማግሌ ፡ ጋራ ፡ ተመሳሳይ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። ገንዘብን ፡ የናቁና ፡ እንደ ፡ ለምጥ ፡ የሚሸሹት ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። ገንዘብ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ለጋራ ፡ ጥቅም ፡ ማለት ፡ ለሆፒታል ፤ ለትምህርት ፡ ቤት ፤ ለጦር ፡ መሣሪያ ፤ እርስ ፡ በርስ ፡ ለመረዳዳት ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ ለመሰለ ፡ ላገሪቱ ፡ እድገት ፡ ሲያገለግል ፡ ብቻ ፡ ነው ። ያሜሪካ ፡ አገር ፡ ሀብታሞች ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ገንዘብ ፡ መሰብሰብን ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ሙያና ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ጀብዱ ፡ አድርገው ፡ ስለቈጠሩት ፡ ከገንዘባቸው ፡ ጋራ ፡ ተቈራኝተው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ከንቱነቱን ፡ እየተረዱት ፡ ስለ ፡ ሄዱ ፡ የሚያገኙትን ፡ ሀብት ፡ ለትምህርት ፡ ቤቶች ፤ ለሆፒታሎች ፤ ለሌላም ፡ ለበጎ ፡ አድራጎት ፡ ያውሉታል ። ገንዘብ ፡ ባንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ ተከማችቶ ፡ እንዳይቀመጥ ፡ በችሮታ ፡ ሥራና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገድ ፡ ለሕዝቡ ፡ እንዲዳረስ ፡ የሚጣጣሩ ፡ መሆናቸውን ፡ የተባበሩትን ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥታት ፡ ታሪክ ፡ የመረመሩ ፡ ደራስያን ፡ በጻፏቸው ፡ መጻሕፍቶች ፡ ያረጋግጡልናል ። ሮክፌለር ፡ የተባለው ፡ የአሜሪካ ፡ ሀብታም ፡ ብቻውን ፡ ለበጎ ፡ አድራጎት ፡ የሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ከሦስቶ ፡ መቶ ፡ ሚሊዮን ፡ ያሜሪካ ፡ ዶላር ፡ የደረሰ ፡ መሆኑን ፡ ቲቦር ፡ ሜንድ ፡ በጻፈው ፡ መጽሐፍ ፡ ይናገራል ። ይህም ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የሦስት ፡ ዓመት ፡ በጀት ፡ መሆኑ ፡ ነው ። የዓለም ፡ ሀብት ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስቦ ፡ የተከማቸባት ፡ በሆነችው ፡ በዚች ፡ አገር ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ መንፈስ ፡ ሲፈጠር ፡ መታየቱ ፡ (ቡርዧ) ፡ የተባሉት ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ባለቤቶች ፡ የሆኑት ፡ ባለጸጎች ፡ ፈጥረውት ፡ የነበረው ፡ የሰውን ፡ ጠባይ ፡ ደረቅ ፡ የሚያደርገው ፡ የገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ እየሞተ ፡ መሄዱን ፡ ይገልጥልናል ። ይህን ፡ ከመሰለው ፡ መንፈስ ፡ የደረሱት ፡ የነጋንዲን ፡ ታሪክ ፡ ተመልክተው ፡ ይሆን? የሀብትና ፡ የንዋይ ፡ የጦር ፡ መሣሪ

ያም ፡ ኀይል ፡ ምንጭ ፡ የሆኑትን ፡ ሳይንስንና ፡ ቴክኒክን ፡ ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ለዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ስታስተምራቸው ፡ የምሥራቅ ፡ ሕዝቦች ፡ የሥልጣኔ ፡ ወኪል ፡ የሆነው ፡ ጋንዲ ፡ ደግሞ ፡ ሰው ፡ በኪሱ ፡ አንድ ፡ ሳንቲም ፤ በኪሱ ፡ አንድ ፡ ሽጉጥ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ጠበንጃ ፡ በእጁ ፡ ሳይዝ ፡ በደግነትና ፡ በመንፈስ ፡ ኀይል ፡ ብቻ ፡ የሰውን ፡ ፍቅር ፡ እየማረከ ፡ ስሙን ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ የገነነ ፡ ለማድረግ ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ አስተማራቸው ።

ጋንዲ ፡ እንደዚህ ፡ ለመሆን ፡ የቻለው ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ አይደለም ። ነገር ፡ ግን ፡ በሕይወቱ ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ ደርሰውበት ፡ በመመልከት ፤ በነጮችና ፡ በቀለም ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ የሚሠራውን ፡ ግፍ ፡ በማስተዋል ፤ ስለ ፡ ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔና ፡ ስለ ፡ አገሩ ፡ ስለ ፡ ህንድ ፡ ጥንታዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ጥናት ፡ የሚናገሩ ፡ መጻሕፍት ፡ በማንበብ ፡ ዕውቀቱ ፡ እየበሰለ ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በጠባያችን ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ ካልታየን ፡ በቀሩት ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ የምንመኘውን ፡ ቦታ ፡ ለማግኘት ፡ አንችልም ። ቪቬካናንዳ ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ አገር ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ እግረ ፡ መንገዱን ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ እንዲደርስ ፡ ወዳጆቹ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ጠየቁት ። እሱም ፡ እንግሊዞችን ፡ በሕንድ ፡ አገር ፡ ያገሩ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሆነው ፡ ሲኖሩ ፡ ባገዛዛቸው ፡ ያውቃቸው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የሚሠሩትን ፡ ግፍ ፡ አስታውሶ ፡ የእንግሊዝን ፡ አገር ፡ በእግሩ ፡ ለመርገጥ ፡ አልፈለገም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ የህንድ ፡ ሃይማኖት ፡ ትልቅ ፡ መሆኑን ፡ ለማሳወቅና ፡ የነጮችን ፡ ሕዝብ ፡ ለመስበክ ፡ የሚደክም ፡ በመሆኑ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ደርሶ ፡ በየስፍራው ፡ ንግግር ፡ ማድረግ ፡ ግዴታ ፡ ሆነበት ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ የሚገኙትን ፡ የእንግሊዝ ፡ ተወላጆች ፡ በህንድ ፡ አገር ፡ ከሚያውቃቸው ፡ በጣም ፡ የተለዩ ፡ ሆነው ፡ አገኛቸው ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ቀዚህ ፡ ቀጥለን ፡ የምንጠቅሰውን ፡ ቃል ፡ ላገሩ ፡ ሰዎች ፡ ህንድ ፡ አገር ፡ ተመልሶ ፡ ከካልኩታ ፡ ከተማ ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ ተነግሯል ።

«ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ የእንግሊዝን ፡ አገር ፡ በእግሩ ፡ ሲረግጥ ፡ እንደኔ ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥላቻ ፡ በልቡ ፡ አሳድሮ ፡ የገባ ፡ የለም ። አሁን ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ ከኔ ፡ የበለጠ ፡ እንግሊዞችን ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ አይገኝም ።………… እንግሊዞች ፡ ያሜሪካኖችን ፡ ያኽል ፡ የሚደነቁ ፡ አይደሉም ። ነገር ፡ ግን ፡ ልባቸውን ፡ ከነካችኋቸው ፡ በኋላ ፡ ልባቸው ፡ ለሁል ፡ ጊዜ ፡ የናንተ ፡ ይሆናል ።………………



እግዚአብሔር ፡ ከማንኛቹም ፡ ሕዝቦች ፡ አብልጦ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ ባረካቸው ፡ አሁን ፡ ተረዳሁት ። ጠንካሮች ፤ ልባቸው ፡ ግልጥ ፤ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ስሜት ፡ የሚገኝባቸው ፡ ናቸው ።………… በመካከላቸው ፡ የእርስ ፡ በርስ ፡ ምቀኝነት ፡ የለባቸውም ፤ የዓለም ፡ ገዥዎች ፡ ለመሆን ፡ የበቁት ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው» ።

ቪቬካናንዳ ፡ አሜሪካንና ፡ አውሮፓን ፡ ጐብኝቶ ፡ አገሩ ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ የህንድ ፡ ሕዝብ ፡ ያደረገለትን ፡ የሚያስገርም ፡ አቀባበል ፡ ስናስበው ፡ የነበረው ፡ ክብር ፡ ከጋንዲ ፡ ምንም ፡ ያኽል ፡ አያንስም ። በማድራስ ፡ ከተማ ፡ የገባ ፡ ዕለት ፡ ተሰብስቦ ፡ ይጠብቀው ፡ የነበረው ፡ በብዙ ፡ ሺሕ ፡ የሚቈጠር ፡ ሕዝብ ፡ በከበሬታ ፡ ከእግሩ ፡ ላይ ፡ ወደቀ ። በየመንገዱ ፡ ላይ ፡ ለሱ ፡ ክብር ፡ ቅስቶች ፡ ተሠርተውለት ፡ ነበር ። ሕዝቡ ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማ ፡ ይዞ ፡ ሲያውለበልብ ፤ ግማሾቹም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዜማዎች ፡ ሲዘምሩ ፤ ሌሎች ፡ ሙዚቃ ፡ ይጫወቱ ፡ ነበር ። የቀሩትም ፡ እሱ ፡ በሚሄድበት ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ አበባ ፡ ይበትናሉ ። እንደዚሁም ፡ በያይነቱ ፡ ስጦታ ፡ የሚያቀርቡለት ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። ይህ ፡ ሰው ፡ ባገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ በተደረገለት ፡ አቀባበል ፡ ልንረዳው ፡ እንችላለን ። ይህ ፡ እሱ ፡ ስለ ፡ እንግሊዞች ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ሰው ፡ ጠባዩ ፡ መልካም ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፡ እንኳንስ ፡ በወዳጆቹ ፡ ዘንድ ፡ ይቅርና ፡ በጠላቶቹም ፡ በኩል ፡ ቢሆን ፡ መከበርንና ፡ መደነቅን ፡ እንደሚያፈራለት ፡ ይገልጥልናል ። ስለዚህ ፡ ጠባይ ፡ ከትምህርት ፡ በላይ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኝ ፡ መሆኑን ፡ ማወቅ ፡ አለብን ። እንግሊዞች ፡ ወዳጅነት ፡ የሚያውቁ ፡ መሆናቸውን ፡ ለመረዳት ፡ በኢጣሊያ ፡ ወረራ ፡ ጊዜ ፡ ምስተር ፡ ኤደን ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የደከሙትንና ፡ የታገሉትን ፡ ማስታወስ ፡ በቂ ፡ ነው ።

ከምንጭ ፡ ሄደው ፡ ውሃ ፡ የሚቀዱ ፡ ሰዎች ፡ በውሃው ፡ ላይ ፡ የሚንሳፈፈውን ፡ ጕድፍ ፡ በመቅጃው ፡ ገፋ ፡ ገፋ ፡ ካደረጉት ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ጠልቀው ፡ ይቀዳሉ ። ይህንንም ፡ የሚያደርጉት ፡ ጥሩ ፡ ውሃ ፡ የሚገኘው ፡ ከታች ፡ መሆኑን ፡ ስለሚያውቁ ፡ ነው ። እኛም ፡ እንደዚሁ ፡ ሥልጣኔን ፡ ስንቀዳ ፡ ከላይ ፡ ተንሳፎ ፡ የሚገኘውን ፡ ጕድፍ ፡ የያዘውን ፡ ሳይሆን ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ጠልቀን ፡ መውሰድ ፡ ይገባናል ። በሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ የሚገኘውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ብልግና ፡ መቅዳት ፡ መሠልጠን ፡ አለመሆኑን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ ሊያውቁት ፡ ይገባል ። ኢትዮጵያ ፡ በሞራል ፡ በኩል ፡ ራሷን ፡ የቻለች ፡ ናት ። ይህ ፡ ነገር ፡ ለሞራል ፡ ይጠቅማል ፡ ወይስ ፡ ይጐዳል ? የሚል ፡ ጥያቄ ፡ በኅሊናቸው ፡ ውስጥ ፡ ሲፈጠር ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ ከሆነው ፡ መምህር ፡ ይልቅ ፡ ሽማግሎች ፡ ከሆኑት ፡ ያገራቸው ፡ ሰዎች ፡ (ካባቶቻቸው) ፡ የተሻለውን ፡

ምክር ፡ ያገኛሉ ። በትምህርትና ፡ ባስተዳደግ ፡ ጠባይ ፡ መካከል ፡ ያሉትን ፡ ጉዳዮች ፡ ጥቂት ፡ በዝርዝር ፡ እስቲ ፡ እንመልከታቸው ። ላንድ ፡ ሕዝብ ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ነው ። ትምህርት ፡ በኋላ ፡ የሚገኝ ፡ ነገር ፡ ሲሆን ፡ ጠባይ ፡ ግን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከቤተ ፡ ሰብ ፡ ይመነጫል ። ቤተ ፡ ሰብም ፡ ይህንኑ ፡ የሚያገኘው ፡ ካለፉት ፡ ትውልዶች ፡ እየተላለፈ ፡ የመጣለትን ፡ በውርስ ፡ እየተቀበለ ፡ ነው ። አውሮፓውያን ፡ ከቀሩት ፡ ሕዝቦች ፡ በላይ ፡ ሆነው ፡ የሚገኙት ፡ በሳይንስና ፡ በቴክኒክ ፡ ማለት ፡ በዘመናችን ፡ ዕውቀት ፡ ብቻ ፡ መስሎን ፡ እንዳንታለል ፡ መጠንቀቅ ፡ ይገባናል ። ቪቬካናንዳ ፡ ያመሰገናቸው ፡ እነዚያ ፡ ያሜሪካ ፡ ሴቶች ፡ ጠባያቸው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በተናገረው ፡ ቃል ፡ ሰምተነዋል ። እንግዲህ ፡ እነዚያ ፡ «የተከበሩ ፡ ንብረቶች ፡ ቃል ፡ የማይገኝላቸው ፡ እናቶች ፤ በዲያን ፡ መቅደስ ፡ እንደሚገኘው ፡ መስተዋት ፡ ንጹሓት ፡ የሆኑ ፡ ልጃገረዶች ፡ እያለ ፡ በመወደስ ፡ የሚጠራቸው ፡ የልጆቻቸውን ፡ ጠባይ ፡ የሚቀርጹት ፡ እነሱ ፡ መሆናቸውን ፡ አንዘንጋው ። መምህር ፡ በትምህርት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ የሚታደለውን ፡ ትምህርት ፡ ይሰጣል ፡ እንጂ ፡ በወጣቶች ፡ ጠባይ ፡ ላይ ፡ አግባብ ፡ የለውም ። ጠባይ ፡ የሚመነጨው ፡ ከቤተ ፡ ሰብ ፡ ነው ። ይህንኑም ፡ ዣን ፡ ዣክ ፡ ሩሶ ፡ በሰፊው ፡ እያተተ ፡ የተጠናቀቀ ፡ ጥናት ፡ ያደረገበት ፡ ጉዳይ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይህንኑ ፡ አጽድቆ ፡ ተናግሮታል ።

# ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴና ፡ ጋንዲ ።

ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ከትልቅ ፡ ፈተና ፡ ላይ ፡ እንድትወድቅ ፡ ያደረጓት ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፤ እነሱም ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴና ፡ ጋንዲ ፡ ናቸው ። ያውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ በሳይንስና ፡ በቴክኒክ ፡ ዕውቀታቸው ፡ ትዕቢት ፡ አድሮባቸው ፡ ሲኖሩ ፡ የመጀመሪያው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ሲነሣ ፡ መከራ ፡ የውሃ ፡ ሙላት ፡ ሆኖ ፡ አጥለቀለቃቸው ። ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ የጦርነት ፡ መዓት ፡ ቢመጣ ፡ እንደማይድኑ ፡ ስለ ፡ ተሰማቸው ፡ እንዳይመለስ ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻልበትን ፡ መንገድ ፡ ማግኘት ፡ የመንግሥትን ፡ ኃላፊነት ፡ ለተረከቡ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ትልቅ ፡ ጉዳይ ፡ ሆኖ ፡ ከፊታቸው ፡ ቀረበ ። ከውሃ ፡ ውስጥ ፡ የሰጠመ ፡ ሰው ፡ ሊድንበት ፡ የሚችል ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ በእጁ ፡ ፈልጎ ፡ ሲያገኝ ፡ እሱን ፡ ጨብጦ ፡ አንቆ ፡ እንደሚይዘው ፡ ሁሉ ፡ እነሱም ፡ እንደዚሁ ፡ የዓለም ፡ መንግሥታትን ፡ በሞራል ፡ መንገድ ፡ አስሮ ፡ የሚይዛቸው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ያለበት ፡ አንድ ፡ ውል ፡ መፍጠር ፡ ከሁሉም ፡ የተሻለ ፡ ዘዴ ፡ ሆኖ ፡ አገኙት ። ይህንንም ፡ ሲያደርጉ ፡ በሳይንስና ፡ በማቴሪያሊስም ፡ በኩል ፡ የነበራቸው ፡ እምነት ፡ በጣም ፡ ተቀንሶ ፡ ለሞራል ፡ ውል ፡ የበለጠ ፡ ዋጋ ፡ እንደሰጡት ፡ የሚመሰክር ፡ ነው ።

እንሆ ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ የተባለው ፡ የተቋቋመው ፡ በዚህ ፡ መንፈስ ፡ ነበር ። ኢትዮጵያ ፡ ከዚህ ፡ ማኅበር ፡ ለመግባት ፡ ፈቅዳ ፡ በጠየቀች ፡ ጊዜ ፡ የሚበልጡት ፡ የተቃዋሚነት ፡ መንፈስ ፡ አሳዩ ። ነገር ፡ ግን ፡ ራሷን ፡ የቻለች ፡ ነጻ ፡ መንግሥት ፡ ስለ ፡ ሆነች ፡ እንቢ ፡ ለማለት ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ አልነበራቸውም ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ባሮችን ፡ ነጻ ፡ አላወጣችም ፡ በማለት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ የምትጠይቃቸውን ፡ ነገሮች ፡ አልፈጸመችም ፡ እያሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ በመፍጠር ፡ ካስቸገሩ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ተቀበሏት ።

ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የማኅበሩ ፡ አባል ፡ ለማድረግ ፡ ያንን ፡ ያኽል ፡ ጠንክረው ፡ ሲደክሙ ፡ ጥቅሙ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያውቁ ፡ ነበር ። በግርማዊነታቸው ፡ መሪነት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ መከተልን ፡ በመጀመር ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ነበረች ፡ ይህ ፡

አሳብ ፡ ፍጻሜ ፡ ለማግኘት ፡ እንዲችል ፡ በቂ ፡ ጊዜ ፡ ይጠይቅ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አልዘነጉትም ። እንደዚሁም ፡ ያውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ ዘመናዊ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የጐደላቸውን ፡ ሕዝቦች ፡ ነጻነታቸውን ፡ ለመግፈፍ ፡ ተግተው ፡ የሚሠሩበት ፡ ሰዓት ፡ በመሆኑ ፡ ከማንኛውም ፡ መንግሥት ፡ ይልቅ ፡ የዚህ ፡ ማኅበር ፡ ጠቃሚነት ፡ የሚያገለግለው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡በሙሉ ፡ ተረድተውት ፡ ነበር ።

ኢጣልያ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በግፍ ፡ ለመውረር ፡ በተነሣች ፡ ጊዜ ፡ ታላላቆች ፡ መንግሥታት ፡ ትልቅ ፡ ችግር ፡ ደረሰባቸው ። የዓለምን ፡ጸጥታና፡ ሰላም ፡ የሚያፈርስ ፡ ግፈኛ ፡ ቢነሣ ፡ «የጋራ ፡ ጸጥታ ፡ ጥበቃ ፡ ሴኩሪቲ ፡ ኮሌክቲብ» ፡ ተብሎ ፡ የተጠራውን ፡ ፕሬንሲፕ ፡ ማኅበሩ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ ነበረበት ። አንድ ፡ መንግሥት ፡ ወንበዴዎች ፡ ተነሥተው ፡ ወንጀል ፡ ሲሠሩ ፡ ተከታትሎ ፡ ለመያዝና ፡ እነሱን ፡ ለመቅጣት ፡ የሚችልበት ፡ የፖሊስ ፡ ኀይል ፡ ከሌለው ፡ መንግሥትነቱ ፡ የጸና ፡ ሊሆን፡ አይችልም ። ኢትዮጵያ ፡ ከተወረረች ፡ በኋላ ፡ ሕግ ፡ አፍራሽ ፡ ሆኖ ፡ የተነሣውን ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ በኀይል ፡ እንዲገደድ ፡ አድርጋ ፡ ሕጓን ፡ ካላስከበረች ፡ የማኅበሩ ፡ መሠረት ፡ እንደሚፈርስና ፡ የሁሉም ፡ ጸጥታቸው ፡ ባደጋ ፡ ላይ ፡ እንደሚገኝ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ በማኅበሩ ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ ራሳቸው ፡ ቀርበው ፡ በመገኘት ፡ የማይረሳ ፡ ሆኖ ፡ በሚኖረው ፡ ታሪካዊ ፡ ንግግራቸው ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ፡ የዓለምን ፡ ኅሊና፡ ከፈተና ፡ ላይ ፡ ጣለው ። ለማኅበሩ ፡ መንፈስ ፡ መሠረት ፡ የሆነው ፡ የሞራል ፡ ውል ፡ የሚከበርበትን ፡ መንገድ ፡ ማግኘት ፡ ለማኅበሩ ፡ አስፈላጊ ፡ ነበር ። ማኅበረተኞች ፡ የሆኑት ፡ መንግሥታት ፡ ይህን ፡ ሳያደርጉ ፡ ቢቀሩ ፡ ግን ፡ ኀይለኛ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ያሻውን ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ፡ በሚል ፡ ፕሬንሲፕ ፡ ላይ ፡ እምነታቸውን ፡ አሳርፈውበት ፡ ይህንኑ ፡ ለመፈጸም ፡ በመደራጀት ፡ ላይ ፡ ለነበሩት ፡ ሰዎች ፡ የሚረዳቸውን ፡ መንገድ ፡ ከፍተው ፡ መስጠት ፡ መሆኑን ፡ ያውቁት ፡ ነበር ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ከዚህ ፡ አደጋ ፡ እንደማይድኑ ፡ ጨምረው ፡ ተረድተውታል ። ከዚህ ፡ ፈተና ፡ ለመውጣት ፡ ያገኙት ፡ ዘዴ ፡ በሞራል ፡ በኩል ፡ ዓለም ፡ ዝቅ ፡ ካለ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ የወረደች ፡ ሆና ፡ መገኘቷን ፡ ከማስረዳት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ትርጉም ፡ አልነበረውም ። በሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለተነሣው ፡ ግፈኛ ፡ መሥዋዕት ፡ እንድትሆን ፡ ሲፈቅዱ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የኢጣልያ ፡ ሕግ ፡ አፍራሽነት ፡ ምሕረት ፡ የማይደረግለት ፡ ጥፋት ፡ መሆኑን ፡ ተስማሙበት ።

ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ተማምለው ፡ ውል ፡ ከተዋዋሉ ፡ በኋላ ፡ ከመካከላቸው ፡ አንዱ ፡ መሐላ ፡ ጥሶ ፡ ውሉን ፡ ቢያፈርስ ፡ በመካከላቸው ፡ ሆኖ ፡ ሊፈርድ ፡ የሚችል ፡ ማነው ? ከእግዚአብሔር ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ሊዳኛቸው ፡ አይችልም ። ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴም ፡ ለሞራል ፡ ሕግ ፡ ዳኛው ፡ እግዚአብሔር ፡ መሆኑን ፡ ባለመጠራጠር ፡ በሙሉ ፡ ልባቸው ፡ የሚያምኑ ፡ በመሆናቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚሠራውን ፡ ለማየት ፡ ይጠብቁ ፡ ጀመር ። ታላላቆች ፡ መንግሥታት ፡ ደግሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጉዳይ ፡ እያረጀ ፡ ይሄድና ፡ በጊዜ ፡ ብዛት ፡ ይረሳል ፡ ብለው ፡ በዚህ ፡ ሊያመልጡ ፡ አሰቡ ። ነገር ፡ ግን ፡ ጉዳዩ ፡ ከመረሳቱ ፡ በፊት ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ የንግግራቸው ፡ ድምፅ ፡ በአባሎቹ ፡ ጆሮና ፡ በዓለም ፡ ኅሊና ፡ በተሰሚነት ፡ ማስተጋባቱን ፡ ሳያቋርጥ ፡ ሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ እንደ ፡ መብረቅ ፡ ፈነዳ ። በዚች ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ለሞራል ፡ ማሰሪያ ፡ የሚሆን ፡ ምንም ፡ መድኀን ፡ የለውም ፡ ብሎ ፡ በትዕቢት ፡ ይናገር ፡ የነበረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጠላት ፡ የጦርነቱ ፡ ማዕበል ፡ ጠርጎ ፡ ሲወስደው ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ግን ፡ ተመልሰው ፡ በዙፋናቸው ፡ ላይ ፡ ተቀመጡ ።

የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ኀይልና ፡ የገንዘብ ፡ ጉልበት ፡ እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ ነገሮች ፡ የሚጐድሉት ፡ ሰው ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ ምንም ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ አይችልም ፡ ብለው ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ በሚያምኑበት ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴና ፡ ጋንዲ ፡ እነዚህን ፡ ሁለት ፡ መሣሪያዎች ፡ ሳይጨብጡ ፡ እምነታቸውን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ በማድረግ ፡ ድል ፡ አድራጊነትን ፡ አገኙ ።

ጋንዲ ፡ የጦር ፡ መሣሪያና ፡ ገንዘብ ፡ የሰይጣን ፡ ሀብቶች ፡ ናቸው ፤ ደግነትና ፡ ፍቅር ፡ የማይሸነፉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መሣሪያዎች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ እነሱን ፡ ብቻ ፡ ይዤ ፡ በመንፈስ ፡ ትግል ፡ የህንድን ፡ ሕዝብ ፡ ነጻ ፡ አወጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ተነሣ ። ደግነትንና ፡ ሰውን ፡ እንደ ፡ ራስ ፡ አድርጎ ፡ መውደድን ፡ እንደ ፡ ጋንዲ ፡ አድርጎ ፡ በሚያስደንቅ ፡ አፈጻጸም ፡ ሲሠራበት ፡ የታየ ፡ ሰው ፡ ከቶ ፡ በታሪክ ፡ ታይቶ ፡ አይታወቅም ። ጋንዲ ፡ ከዚህ ፡ አስተያየት ፡ ለመድረስ ፡ የቻለበትን ፡ ሁኔታ ፡ እስቲ ፡ እንከታተለው ። ጋንዲ ፡ ባውሮፓ ፡ ሥልጣኔ ፡ ሙሉ ፡ ትምህርት ፡ ካገኘ ፡ በኋላ ፡ ሥልጣኔ ፡ ማለት ፡ ምንድነች ? የሚል ፡ ጥያቄ ፡ በመንፈሱ ፡ ተወለደ ። ለዚህ ፡ ጥያቄ፡ የሚሆነውን ፡ መልስ ፡ ለማግኘት ፡ ተጣጣረ ። በነጮችና ፡ በቀለም ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ጉዳይና ፡ የሚሠራውንም ፡ ግፍ ፡ ተመለከተ ። በሃይማኖትና ፡ በሥልጣኔ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ መረመረ ። ሰው ፡ ዐላማው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወዴትስ ፡ ለመሄድ ፡ እንደሚፈልግ ፡ ለማወቅ ፡ ሞከረ ። ባውሮፓ ፡ ሥልጣኔ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ጉድለቶች ፡ መርምሮ ፡ ተረዳቸው ። የገንዘብ ፡ ፍቅር ፤ የሰብአዊ ፡ ጠባይ ፡

ደካማነት ፡ የሃይማኖት ፡ ንቀት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መራቅ ፤ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ እየገነኑ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ደግነትና ፡ ሰውን ፡ እንደ ፡ ራስ ፡ አድርጎ ፡ መውደድ ፤ እነዚህ ፡ የመንፈስ ፡ ሀብቶች ፡ ግን ፡ ከሰው ፡ ልብና ፡ ከሰው ፡ ኅሊና ፡ እየተፋቁ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ መሆናቸውን ፡ ተገንዘበው ። እነዚህ ፡ ሲቀነሱ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ የሚተርፈው ፡ ምንድነው ? ብሎ ፡ አሰበ ። እነ ፡ ጆግራፊ ፤ እነ ፡ ጕሜትሪ ፤ አስትሮኖሚ ፤ አልጀብር ፡ ናቸው ፤ እነዚህን ፡ ብቻ ፡ ይዞ ፡ ሲቀር ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ፍጡር ፡ ይሆናል ? ብሎ ፡ አመዛዘነ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ጥንታዊው ፡ የህንድ ፡ ሥልጣኔ ፡ ተመልሶ ፡ ቀድሞ ፡ ሀብታችን ፡ ምን ፡ ኖሯል ? ይህን ፡ ያኽል ፡ ዘመን ፡ ስንኖር ፡ ደግፎ ፡ የያዘንና ፡ መንፈሳችንን ፡ እየመገበ ፡ ሕይወት ፡ የሰጠው ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ጥበብ ፡ ነው ? ብሎ ፡ ተመራመረ ። ዛፍን ፡ በፍሬዋ ፡ ታውቋታላችሁ ፤ ጥሩ ፡ ዛፍ ፡ መጥፎ ፡ ፍሬ ፡ አታፈራም ፤ እንደዚሁም ፡ መጥፎ ፡ ዛፍ ፡ ጥሩ ፡ ፍሬ ፡ አታፈራም ፡ ተብሎ ፡ በወንጌል ፡ እንደ ፡ ተነገረው ፡ ሁሉ ፡ ጋንዲም ፡ ያውሮፓ ፡ ሥልጣኔ ፡ በውነት ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠች ፡ ጥሩ ፡ ሥልጣኔ ፡ ብትሆን ፡ ኖሮ ፡ እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ሰውን ፡ የሚያረክሱና ፡ ዝቅ ፡ አድርገው ፡ የሚያሳዩ ፡ ፍሬዎች ፡ አፍርታ ፡ አታሳየንም ፡ ነበር ። የምናየው ፡ ሁሉ ፡ የገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ እግዚአብሔርን ፡ መርሳት ፡ በሕዝቦችም ፡ መካከል ፡ መናናቅ ፡ ግፍ ፡ መሥራት ፡ በጦርነት ፡ መተላለቅ ፡ ነው ። ስለ ዚህ ፡ ይህች ፡ ሥልጣኔ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርጋ ፡ ዘለቄታ ፡ ሊኖራት ፡ ይችላል ? ብሎ ፡ ተስፋ ፡ ቈረጠ ። ሰው ፡ ደግ ፡ በመሆንና ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ራሱ ፡ አድርጎ ፡ በመውደድ ፡ የሚያተርፈው ፡ ጥቅም ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ ዐወቀ ። የገንዘብ ፡ ፍቅርና ፡ ዝሙት ፡ የኀጢአት ፡ ሁሉ ፡ ምንጭ ፡ መሆናቸውን ፡ ተረዳው ። ይህንንም ፡ ትምህርት ፡ ያገኘው ፡ ከህንድ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ።

እንደዚሁም ፡ በኢንዱስትሪ ፡ ምክንያት ፡ የሚመጣውን ፡ መዘዝ ፡ ሁሉ ፡ አስተዋለ ። በየፋብሪካው ፡ የሚሠሩ ፡ ሠራተኞች ፡ ከባርነት ፡ ጋራ ፡ የሚመሳሰል ፡ ግፍና ፡ ጭቈና ፡ እንደሚሠራባቸው ፡ ይህም ፡ ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔን ፡ ወደ ፡ ዐዘቅት ፡ እንዳይጨምራት ፡ የሚያስፈራውን ፡ (la lutte des classes) የተባለውን ፡ እንዲወለድና ፡ በገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ ብቻ ፡ የተመረዙት ፡ የፋብሪካ ፡ ጌቶች ፡ እንዲፈጠሩ ፡ ማድረጉን ፡ ተመለከተ ። እንግዲህ ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ነገሮች ፡ ከጋንዲ ፡ ብቻ ፡ የተገኙ ፡ አሳቦች ፡ አይደሉም ። ብዙ ፡ ተመራማሪዎችና ፡ ደራስያን ፡ በእነዚህ ፡ ጕዳዮች ፡ ላይ ፡ ሰፊ ፡ ጥናት ፡ እያደረጉ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ ጽፈዋል ። ሳይንስና ፡ ቴክኒክ ፡ ከመጡ ፡ ወዲህ ፡ የተደረጉት ፡ ሁለቱ ፡ የዓለም ፡ ጦርነቶች ፡ ያስከተሉት ፡ ጥፋት ፡ እጅግ ፡ የሚያስፈራ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ። በመጨረሻም ፡ አቶሚክ ፡ ቦምብና ፡ ሃይድሮጃን ፡ ቦምብ ፡ ተወለዱ ። በእነዚህ ፡ ቦምቦች ፡ ዓለምን ፡ ጨርሶ ፡ ለማጥፋትና ፡ እንዳልነበረች ፡ ለማድረግ ፡ እንደሚቻል ፡ በሳይንቲፊክ ፡ ተገምቶ ፡ ተረጋግጧል ። ያሁኗ ፡ ሥልጣኔ ፡ ራሷ ፡ የሠራችውን ፡ ሁሉ ፡ ራሷ ፡ መልሳ ፡ ካጠፋችው ፤ ከዚህም ፡ አልፋ ፡ ተርፋ ፡ ዓለምን ፡ በላይዋ ፡ ካሉት ፡ ፍጡሮች ፡ ጋራ ፡ አቃጥላ ፡ በሙሉ ፡ የምትደመስስ ፡ ከሆነ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ በየዘመኑ ፡ ከተገኙት ፡ ሥልጣኔዎች ፡ ሁሉ ፡ የከፋች ፡ የሰይጣን ፡ ሥራ ፡ ነች ፡ ቢባል ፡ ምን ፡ አለበት ? የጋንዲም ፡ ሆነ ፡ ይህንን ፡ አሳብ ፡ የተከተሉ ፡ የሌሎቹ ፡ ሰዎች ፡ አስተያየት ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ በሙሉ ፡ በእውነት ፡ ላይ ፡ የቆመ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ማሰብ ፡ ይኖርብናል ።



ከዚህም ፡ በቀር ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ጕዳይ ፡ አለ ። ለምሳሌ ፤ በጥንት ፡ ዘመን ፡ በግሪክና ፡ በሮማ ፡ ወይም ፡ በቺንና ፡ በህንድ ፡ አገሮች ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ጠባያቸው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንመልከት ። ታሪካቸውን ፡ እንመርምረው ። «መልካም ፡ ምግባር ፡ (vertu) የተባለችውን ፡ ለጠባያቸው ፡ ዐላማ ፡ አድርገው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ቃላቸውን ፡ ያከብራሉ ፤ ወዳጃቸውን ፡ አይክዱም ፤ ቈራጥነት ፡ ነበራቸው ፤ በተድላና ፡ በምቾት ፡ አይሸነፉም ፤ ፍትወታቸውን ፡ ጥብቅ ፡ በሆነ ፡ ፈቃድ ፡ ገተው ፡ ይይዙታል ፤ ራሳቸውን ፡ ይገዙታል ፡ ማለት ፡ ነው ። ከሁለት ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ዛሬ ፡ በሳይንስና ፡ በቴክኒክ ፡ የተሠራውን ፡ ግሩም ፡ የሆነውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ስንመለከት ፡ አድናቆታችን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ እሱን ፡ ራሱን ፡ ማለት ፡ የዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጥበብ ፡ ባለቤት ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ ስንመለከተው ፡ ከሁለት ፡ ሺሕ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ከሱ ፡ የተሻሉ ፡ ነበሩ ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ዛሬ ፡ ቃሉን ፡ የሚያከብር ፡ ሰው ፡ የለም ። ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ዛሬ ፡ የቀን ፡ የቀኑን ፡ ሁኔታ ፡ ተከትሎ ፡ ይለወጣል ፡ እንጂ ፡ ባመነበት ፡ ነገር ፡ ቈርጦ ፡ አይገፋም ። ተድላና ፡ ምቾት ፡ የወርቅ ፡ ጣቦት ፡ (ጣዖት) ፡ ሆነው ፡ ተገኝተዋል ። ስለነሱ ፡ ሲል ፡ ሰው ፡ ማንኛውንም ፡ የተከበረ ፡ ስሜቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ያደርጋል ። ራሱን ፡ ለማዘዝ ፡ የሚችል ፡ ሰው ፡ በዛሬ ፡ ጊዜ ፡ አይገኝም ። ሄዶኒስም ፡ (hédonisme) የሚባል ፡ ለልብ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ መፈለግ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ የፍልስፍና ፡ ዝንባሌ ፡ ተፈጥሯል ። ባጭሩ ፡ ሰይጣን ፡ የሠራቸው ፡ እንጂ ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ የተቋቋሙ ፡ የማይመስሉ ፡ ግዙፎች ፡ የሆኑ ፡ የፋብሪካ ፡ መኪናዎች ፡ የኤሌክትሪሲቲ ፡ ኀይል ፡ የሚሰጡ ፡ ቱርቢን ፡ ሞተሮች ፤ የውሃ ፡ ግድቦች ፤ ሌሎችም ፡ እነሱን ፡ የመሰሉ ፡ ነገሮች ፡ በተቋቋሙበት ፡ ዘመን ፡ ሰዎች ፡ በጠባያቸው ፡

በጣም ፡ ዝቅ ፡ እያሉ ፤ እየተዋረዱና ፡ እያነሱ ፡ ሲሄዱ ፡ ይታያሉ ። በእጃቸው ፡ የሠሯቸው ፡ እነዚህ ፡ የብረትና ፡ የኤሌክትሪክ ፡ ጕልበቶች ፡ ጥላቸውን ፡ እየጣሉባቸው ፡ የሥጋቸውን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የነፍሳቸውንና ፡ የመንፈሳቸውን ፡ ኀይል ፡ ደምስሰውታል ፡ ለማለት ፡ ያስደፍራል ። ስለዚህ ፡ ሰው ፡ እንደዚህ ፡ አድርጎ ፡ በነፍሱ ፡ ባሕርይ ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ እየወረደ ፡ ከሄደ ፡ ከሳይንስና ፡ ከቴክኖሎጂ ፡ የሚገኘው ፡ ጥበብ ፡ የሚሰጠው ፡ ፍሬ ፡ ለምን ፡ ሊጠቅም ፡ ይችላል ? የነፍስ ፡ ትልቅነት ፡ የመንፈስ ፡ ጸጥታ ፡ የውስጥ ፡ ሰላም ፤ ሰብአዊ ፡ ስሜትና ፡ የኀሊና ፡ ደስታ ፡ የሌሉባት ፡ ሥልጣኔ ፡ ለምን ፡ ትበጃለች ? ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ምክንያት ፡ የሆኑት ፡ እነዚያ ፡ ሦስት ፡ መርዞች ፡ አይደሉምን ?

ፕሉታርክ ፡ የተባለው ፡ የግሪክ ፡ ደራሲ ፡ በግሪክና ፡ በሮማ ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ጠባያቸው ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በጻፈልን ፡ መጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ እናገኘዋለን ። እስቲ ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ጠባያቸው ፡ ጥብቅ ፡ አስተያየታቸው ፡ ክቡር ፡ የሆነ ፡ በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ ሙሉነት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ በዓለም ፡ እናገኛለን ፡ ወይ ? እነዚያ ፡ ሰዎች ፡ ከክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ ናቸው ። የሰውን ፡ ነፍስ ፡ በውነቱ ፡ ትልቅ ፡ እንድትሆን ፡ የሚያደርጋትን ፡ የወንጌልን ፡ ቃል ፡ አልሰሙም ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ወንጌል ፡ ከተሰበከ ፡ ከሁለት ፡ ሺሕ ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፡ ሰው ፡ መንፈሱ ፡ የቱን ፡ ያኽል ፡ የተሻሻለ ፡ መሆን ፡ ይገባው ፡ ነበር ። ከሁለት ፡ ሺሕ ፡ ዓመታት ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ዘመን ፡ ሥልጣኔ ፡ ባደረገችው ፡ እርምጃ ፡ የሰዎች ፡ ጠባይ ፡ እንኳንስ ፡ ፕሉታርክ ፡ ታሪካቸውን ፡ ከጻፈው ፡ ሰዎች ፡ የተሻለና ፡ የበለጠ ፡ ሊሆን ፡ ይቅርና ፡ የሚተካከል ፡ እንኳ ፡ አይገኝም ። የእነሱንም ፡ መልካም ፡ ምግባር ፡ ዛሬ ፡ ስንመለከተው ፡ ተረት ፡ ይመስላል ። ለምሳሌ ፤ አንዲት ፡ የመኰንን ፡ ሚስት ፡ በጣም ፡ ትወደው ፡ የነበረ ፡ ባሏ ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ እሱ ፡ ከቀረ ፡ ሌላ ፡ ባል ፡ አላገባም ፡ በማለት ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ለጋብቻ ፡ ሲጠይቋት ፡ እንቢ ፡ ብላ ፡ ኖረች ። በኋላ ፡ እንዳጋጣሚ ፡ የሌላ ፡ አገር ፡ ንጉሥ ፡ እንዲያገባት ፡ ለመናት ። እሷ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቍርጥ ፡ አሳብ ፡ አድርጊያለሁና ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ የባሌን ፡ መታሰቢያ ፡ አላበላሽም ፡ ብላ ፡ እንቢ ፡ አለችው ፡ ይባላል ። ይህ ፡ ቈራጥነት ፡ በዛሬ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ይገኝ ፡ ይመስላችኋልን? የዛሬ ፡ ዘመን ፡ አርቲስቶች ፡ (ሲኒማ) ፡ ተጫዋቾች ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ሀብታሞች ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ እናውቃለን ። ነገር ፡ ግን ፡ ገንዘብ ፡ አልበቃ ፡ ብሏቸው ፡ የዓለምን ፡ ክብር ፡ ሲፈልጉ ፡ ክርስቲያንነታቸውን ፡ ክደው ፡ እስላሞች ፡ ከሆኑ ፡ ነገሥታትና ፡ ልዑላን ፡ ጋራ ፡ መጋባትን ፡ ከትልቅ ፡ ዕድል ፡ ይቈጥሩታል ። ጋዜጠኞችም ፡ እነሱን ፡ በመ



ውቀሥ ፡ ፈንታ ፡ ገንዘብ ፡ እየተቀበሉ ፡ ይህንኑ ፡ እያጋነኑ ፡ ይጽፉላቸዋል ። የሰዎች ፡ ጠባይ ፡ በብዙ ፡ ነገር ፡ ዝቅ ፡ እያለ ፡ ለመሄዱ ፡ ማስረጃ ፡ የሚሆን ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ስንት ፡ ነገር ፡ ልንጠቅስ ፡ እንችላለን ።

ጋንዲ ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ የተቃዋሚነት ፡ አሳብ ፡ በዛሬይቱ ፡ ሥልጣኔ ፡ ላይ ፡ ያደረበት ፡ ወንጌልን ፡ ካነበበ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ ይባላል ።

«የዓለምን ፡ ክብር ፡ ሁሉ ፡ ብታገኝ ፡ ለምን ፡ ይጠቅመሃል ፡ ነፍስኽ ፡ ከጠፋች» ።

«ቀኝ ፡ ጕንጭኽን ፡ ቢመቱኽ ፡ ግራ ፡ ጕንጭኽን ፡ ስጣቸው» ።

«ሰይፍ ፡ የሚመዝ ፡ በሰይፍ ፡ ይጠፋል» ።

እነዚህን ፡ በመሳሰሉት ፡ ቃሎች ፡ አምነናል ፡ የሚሉ ፡ ክርስቲያኖች ፡ የሆኑ ፡ ሕዝቦች ፡ ግብራቸው ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ? የህንድን ፡ ሕዝብ ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ ፈጅተው ፡ በተገዥነት ፡ ቀንበር ፡ ውስጥ ፡ ካገቡት ፡ በኋላ ፡ በጭካኔና ፡ በጭቈና ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ ዘመን ፡ አሳሩን ፡ሲያስጨርሱት ፡ የኖሩት ፡ እንግሊዞች ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ክርስቲያን ፡ አይደለምን ? የወንጌል ፡ ቃል ፡ ወዴት ፡ ሄዶ ፡ ነው ፡ ይህንን ፡ ግፍ ፡ ለመሥራት ፡ መንፈሳቸው ፡ የፈቀደላቸው ። በአስትራሊ ፡ የነበረውን ፡ ያገሩ ፡ ተወላጅ ፡ የሆነውን ፡ ሕዝብ ፡ ጨርሰው ፡ አጥፍተውት ፡ ዛሬ ፡ መሬቷ ፡ እንሆ ፡ የነጮች ፡ አገር ፡ ሆና ፡ የለምን ?

በወንጌል ፡ ቃልና ፡ ክርስቲያኖች ፡ ነን ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ሕዝቦች ፡ በሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ መካከል ፡ ትልቅ ፡ ልዩነት ፡ የሚገኝ ፡ በመሆኑ ፡ በጋንዲ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በብዙ ፡ ሊቃውንትና ፡ ፈላስፎች ፡ መንፈስ ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ ጕዳይ ፡ የሚያሳዝን ፡ መጥፎ ፡ አሳብ ፡ መፍጠሩ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ይህንኑም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በሌላ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ እንመለከተዋለን ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ደግሞ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ካቶሊካውያን ፤ ፕሮቴስታንቶች ፡ አርቶዶክሶች ፡ እየተባሉ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የተለያዩና ፡ የተነጣጠሉ ፡ ናቸው ። በመካከላቸውም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጠላትነት ፡ ስላለ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ስንት ፡ ደም ፡ ፈሰሰ ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ከውጭ ፡ ሆኖ ፡ የክርስቲያኖችን ፡ ታሪክ ፡ ለሚመለከተው ፡ መጥፎ ፡ ስሜት ፡ መፍጠሩ ፡ አያስደንቅም ።

የሳይንስ ፡ ሰዎች ፡ ግዙፍ ፡ የሆነውን ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ በመመርመር ፡ ብዙ ፡ ዕውቀት ፡ ፈጥረዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ በሰው ፡ ነፍስ ፡ ውስጥ ፡ ይህንኑ ፡ የሚያኽል ፡ ያልተመረመረ ፡ ሀብትና ፡ ጕልበት ፡ የሞላበት ፡ የጥበብ ፡

ምንጭ ፡ መኖሩን ፡ ዘንግተውታል ። ማንኛውም ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ተሰውሮ ፡ የተቀመጠው ፡ በሰው ፡ ነፍስ ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፤ ያኽል ፡ በህንድ ፡ ጥንታዊ ፡ ድርሰት ፡ ውስጥ ፡ ተጽፈው ፡ ከሚገኙት ፡ ታሪኮች ፡ አንዱን ፡ ስለ ፡ ሁለት ፡ ንጉሦች ፡ ታሪክ ፡ የሚናገረውን ፡ እንመልከት ።

ማሃሲላቫ ፡ ወይም ፡ ሲላቫ ፡ የሚባል ፡ ጽድቅን ፡ የሚሻ ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ። ኰዛላ ፡ የሚባለው ፡ (እብሪተኛ) ፡ የሆነ ፡ የሌላ ፡ አገር ፡ ንጉሥ ፡ የማሃሲላቫን ፡ መንግሥት ፡ እነጥቃለሁ ፡ ብሎ ፡ ተነሣ ። የጦር ፡ ሰራዊቱን ፡ አስከትቶ ፡ ዘመተበት ። የማሃሲላቫ ፡ መኳንንትና ፡ አርበኞች ፡ ኰዛላ ፡ ለዘመቻ ፡ ተሰናድቶ ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ የሚገሠግሥ ፡ መሆኑን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ከንጉሣቸው ፡ ዘንድ ፡ ቀርበው ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፤ «ንጉሥ ፡ ሆይ ፤ ኰዛላ ፡ ከከተማችን ፡ ሊገባ ፡ አስቦ ፡ መጥቷል ። ስለዚህ ፡ ጠረፋችንን ፡ ከመርገጡ ፡ በፊት ፡ ውጊያ ፡ ገጥመነው ፡ ሰራዊቱን ፡ አመድ ፡ ካደረግነው ፡ በኋላ ፡ እሱንም ፡ ማርከን ፡ እናመጣዋለን» ። ንጉሥ ፡ ማሃሲላቫ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አገዳቸው ፤

«ወዳጆቼ ፡ ሆይ ፡ እረፉ ፡ በኔ ፡ ምክንያት ፡ ሌሎች ፡ ፍጡሮች ፡ መከራ ፡ እንዲቀበሉ ፡ አልፈለግም ። መንግሥቴን ፡ ለመቀማት ፡ የተመኙት ፡ ሰዎች ፡ መጥተው ፡ ይውሰዱት» ።

ኰዛላ ፡ ጠረፉን ፡ አልፎ ፡ ካገሩ ፡ መካከል ፡ ገሥግሦ ፡ ገባ ። ሚኒስትሮቹ ፡ ተሰብስበው ፡ ወደ ፡ ማሃሲላቫ ፡ ዘንድ ፡ ቀረቡና ፡ ቀድሞ ፡ ተናግረውት ፡ የነበረውን ፡ ቃል ፡ መልሰው ፡ ተናገሩ ። ንጉሡም ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ እንዳይዋጉ ፡ ከለከላቸው ። ንጉሡ ፡ ኰዛላ ፡ ከከተማው ፡ ቅጥር ፡ አጠገብ ፡ ሲደርስ ፡ ሰፈረና ፡ ለታላቁ ፡ ንጉሥ ፡ ለሲላቫ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ መልእክት ፡ አስተላለፈለት ፤

«ወይም ፡ ወዲህ ፡ መጥተህ ፡ ውጊያ ፡ እናድርግ ፡ አለዚያም ፡ መንግሥትህን ፡ ልቀቅልኝ» ።

የጋራናዚ ፡ ንጉሥ ፡ (ማለት ፡ ማሃሲላቫ) ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መለሰ ፤ «ውጊያ ፡ እንዳላደርግ ፡ ባሳቤ ፡ የቈረጥኩ ፡ በመሆኔ ፡ መጥተኽ ፡ መንግሥቴን ፡ ውሰድ» ። ንጉሥ ፡ ኰዛላ ፡ ተከላካይ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ጠላት ፡ ሳያገኝ ፡ ሰተት ፡ ብሎ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ገባ ።

ንጉሥ ፡ ማሃሲላቫ ፡ ከነመኳንንቶቹ ፡ ተማረከ ፤ ሁሉም ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ተፈረደባቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዐይን ፡ የማይታየው ፡ በመካከላቸው ፡ ገብቶ ፡ ሥራውን ፡ ሠራ ፤ (እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው) ።



ውብ ፡ በሆነ ፡ ጌጥ ፡ ተሸልሞና ፡ አምሮ ፡ በተሠራው ፡ የክብር ፡ ዐልጋው ፡ ላይ ፡ ድል ፡ አድራጊ ፡ የሆነው ፡ ንጉሡ ፡ ኰዛላ ፡ ሌሊት ፡ ተኛ ። እንቅልፍ ፡ እልም ፡ አድርጎ ፡ ወስዶት ፡ ሳለ ፡ ንጉሡ ፡ ማሃሲላቫ ፡ ስለት ፡ በሌለበት ፡ በኩል ፡ በሰይፉ ፡ ሆዱ ፡ ላይ ፡ መታው ። ያም ፡ ደንግጦ ፡ ተነሣ ። በመብራቱ ፡ ብርሃን ፡ ታላቁ ፡ ንጉሥ ፡ ሲላቫ ፡ (ማሃሲላቫ) ፡ መሆኑን ፡ አየና ፡ ባወቀው ፡ ጊዜ ፡ ካልጋው ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ አሳቡን ፡ ከሰበሰበ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤

«ታላቁ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፤ በዚች ፡ ሌሊት ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ በሮች ፡ የተዘጉና ፡ በጥንቃቄ ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ፤ ዘብ ፡ የሚቆሙ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ፤ እዚህ ፡ ለመግባት ፡ ፈጽሞ ፡ የማይቻል ፡ ነው ፤ ይህ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ እንሆ ፡ ሰይፍኽን ፡ ታጥቀኽ ፡ አጠገቤ ፡ ቆመሃል ። እንደ ምን ፡ አድርገኽ ፡ ከመኝታ ፡ ቤቴ ፡ ለመግባት ፡ ቻልክ ?»

ማሃሲላቫ ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ለመግባት ፡ እንደ ፡ ቻለ ፡ ነገረው ።

ጧት ፡ ፀሐይ ፡ ስትወጣ ፡ ንጉሡ ፡ ኰዛላ ፡ ነጋሪት ፡ እንዲመታ ፡ አዘዘና ፡ መኳንንቶች ፤ ሚኒስትሮች ፤ ካህናትና ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ሹማምቶችም ፡ እንዲሰበሰቡ ፡ አደረገ ። የንጉሡን ፡ የሲላቫን ፡ ትልቅነት ፡ አመስግኖ ፡ ነገራቸው ። ሲያመሰግነውም ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ ስለምትገኘው ፡ ሙሉ ፡ ጨረቃ ፡ ስለ ፡ ውበቷ ፡ የሚናገር ፡ ይመስል ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የጋራናዚ ፡ ንጉሥ ፡ (ማሃሲላቫ) ፡ ይቅርታ ፡ እንዲያደርግለት ፡ በጉባኤው ፡ ላይ ፡ ለምኖት ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ተናግሮ ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ መለሰለት ።

«ከዛሬ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነጣቂዎች ፡ ቢመጡብኽ ፡ እኔ ፡ አለሁልኽ ። ባገርኽ ፡ ላይ ፡ ነግሠኽ ፡ ኑር ፤ እኔም ፡ የመንግሥትኽ ፡ ጠባቂ ፡ ሆኜ ፡ እገኛለሁ» ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ኰዛላ ፡ ሰራዊቱን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ተመለሰ ። ይህ ፡ በህንድ ፡ ድርሰት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ታሪክ ፡ ማቴሪያሊስት ፡ በሆኑት ፡ በዛሬ ፡ ዘመን ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተረት ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ፡ እንጂ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የሚቀበል ፡ አይገኝም ። ነገር ፡ ግን ፡ ጋንዲ ፡ የኀይልና ፡ የጕልበት ፡ መሠረቱ ፡ ደግነት ፡ ነው ፤ ጠላቶቻችን ፡ ለሚሠሩብን ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ እኛም ፡ ክፉ ፡ ሆነን ፡ ክፋትን ፡ ለክፋት ፡ እንመልስላቸው ፡ ሳንል ፡ ፍቅርን ፡ መሣሪያ ፡ አድርገን ፡ በፍቅር ፡ ብቻ ፡ እንዋጋቸው ፡ ብሎ ፡ ፖሊቲካውን ፡ በዚህ ፡ አሳብ ፡ ላይ ፡ በመሠረተ ፡ ጊዜ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ሞኝ ፡ ቈጠሩት ። እሱ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ አሳብ ፡ ላይ ፡ የነበ

ረው ፡ እምነት ፡ የማይናወጥ ፡ በመሆኑ ፡ አንድ ፡ ጥይት ፡ ሳይተኰስ ፡ ከዓለም ፡ ኀያላን ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ሆና ፡ ትታይ ፡ የነበረችውን ፡ ታላቂ ፡ ብሪታንያን ፡ ከህንድ ፡ አገር ፡ በሰላም ፡ አስወጥቶ ፡ ያገሩን ፡ ነጻነት ፡ አስመለሰ ።

ይህ ፡ ታሪክ ፡ የጋንዲ ፡ ፖለቲካ ፡ ከራሱ ፡ በፈጠረው ፡ እምነት ፡ ሳይሆን ፡ ካገሩ ፡ ፍልስፍናና ፡ ካገሩ ፡ ሃይማኖት ፡ ከተገኘ ፡ ይህን ፡ አሁን ፡ ያነበብነውን ፡ ከመሰለ ፡ ትምህርት ፡ የመነጨ ፡ መሆኑን ፡ ይገልጽልናል ።

«የሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ ያኽል ፡ እምነት ፡ ቢኖራችሁ ፡ ኖሮ ፡ ይህን ፡ ተራራ ፡ ተነሥተኽ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ ተዛወር ፡ ብትሉት ፡ ይታዘዝላችኋል» ፡ ሲል ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ እምነት ፡ ከሰው ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ የተፋቀች ፡ በሆነችበት ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ እንድትውል ፡ ያደረጋት ፡ ጋንዲ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ዛሬ ፡ ክርስቲያን ፡ የሆኑት ፡ መንግሥታት ፡ ግን ፡ በሳይንስና ፡ በቴክኒክ ፡ ዕውቀት ፡ ያልተጠናውንና ፡ ያልተረጋገጠውን ፡ ነገር ፡ አያምኑበትም ። በወንጌል ፡ «ሰይፍን ፡ የሚመዝ ፡ በሰይፍ ፡ ይሞታል» ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ በሳይንስ ፡ ያመኑበትን ፡ ያኽል ፡ በሳይንስ ፡ እንዳይጠፉ ፡ ያስፈራቸዋል ።

ይሁን ፡ እንጅ ፡ የጋንዲ ፡ አሳብ ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ደካማነትን ፡ የያዘ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ለፍርድ ፡ የሚያስቸግር ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ አንዘንጋ ። የትልቅነቱን ፡ ጠባይ ፡ ስንመለከተው ፡ ተወዳዳሪ ፡ የለውም ። ጋንዲ ፡ የህንድን ፡ ሕዝብ ፡ ነጻ ፡ ለማውጣት ፡ ከእንግሊዝ ፡ ጋራ ፡ ያደረገው ፡ ትግል ፡ ኰብራ ፡ በሚባለው ፡ በትልቁ ፡ እባብና ፡ ሽኮኮ ፡ ወይም ፡ ሽላን ፡ በመሰለችው ፡ ትንሽ ፡ እንስሳ ፡ መካከል ፡ ከሚደረገው ፡ ውጊያ ፡ ጋራ ፡ በጣም ፡ ይመሳሰላል ። ኰብራ ፡ መርዙ ፡ በጣም ፡ ኀይለኛ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ የሚተፋው ፡ መርዝ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ለመግደል ፡ የሚበቃ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ይህ ፡ ኀይለኛ ፡ የሆነ ፡ እባብ ፡ ራሱን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አንሥቶ ፡ መነጥር ፡ በሚመስሉት ፡ ዐይኖቹ ፡ ዘልቆ ፡ እየተመለከተ ፡ አስደናቂ ፡ በሆነ ፡ ፍጥነቱ ፡ የሚከታተላቸውን ፡ ፍጡሮች ፡ ሰዎችን ፡ ጭምር ፡ እየተጠናወተ ፡ ያጠቃቸዋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከዚች ፡ ትንሽ ፡ ከሆነች ፡ እንስሳ ፡ ጋራ ፡ ሲጋጭ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በትንሽነቷና ፡ በደካማነቷ ፡ ቢንቃት ፡ እሷ ፡ ከዐቅሟ ፡ ማነስ ፡ ጋራ ፡ ያላት ፡ ቅልጥፍና ፡ ለሱ ፡ ግዙፍነት ፡ የማትመች ፤ የማትጨበጥ ፡ እያደረገ ፡ ስለሚረዳት ፡ እሷን ፡ ለመያዝ ፡ የሚያደርገው ፡ መወርወር ፡ ለኰብራው ፡



በጣም ፡ አድርጎ ፡ ይጐዳዋል ። በኋላም ፡ ጕልበቱን ፡ ሁሉ ፡ ጨርሶ ፡ ሲደክመው ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ በእጅዋ ፡ ይወድቃል ።

ጋንዲም ፡ ግዙፍ ፡ ከሆነው ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ያደረገው ፡ ትግል ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ለእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ቀልድ ፡ ሆኖ ፡ ታይቶት ፡ ነበር ። በፈቀድኩ ፡ ጊዜ ፡ ጋንዲን ፡ እንዳልነበረ ፡ ለማድረግ ፡ እችላለሁ ፡ የማለት ፡ አሳብ ፡ ስላደረበት ፡ ጉዳዩን ፡ በንቀት ፡ ተመለከተው ። ትግላቸው ፡ እየከረረ ፡ ጠባቸው ፡ እየመረረ ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ከእንቅልፉ ፡ ሲነቃ ፡ ጋንዲን ፡ ለመጨበጥ ፡ ባደረገው ፡ መጣጣር ፡ ሁሉ ፡ ዝንብን ፡ ለመያዝ ፡ ጥፍሮቹን ፡ አውጥቶ ፡ የሚሰነዝር ፡ አንበሳ ፡ የገዛ ፡ ገላውን ፡ እንደሚያቈስል ፡ ሁሉ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥትም ፡ ጋንዲን ፡ ለመጕዳት ፡ የወረወረው ፡ ጦር ፡ መልሶ ፡ ራሱን ፡ ስለወጋው ፡ በመጨረሻ ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ በጋንዲ ፡ እጅ ፡ ወደቀ ። እንደ ፡ ዳዊትና ፡ እንደ ፡ ጐልያድ ፡ ውጊያ !

ያፍሪቃ ፡ ሕዝቦች ፡ በነጮች ፡ ግዛት ፡ ምክንያት ፡ የተጫነባቸው ፡ ቀንበር ፡ ከእስያ ፡ ሕዝቦች ፡ ይበልጥ ፡ የከበደ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ከዚህ ፡ ቀንበር ፡ ለመውጣት ፡ ስለ ፡ ነጻነታቸው ፡ የህንድ ፡ ሕዝብ ፡ ካደረገው ፡ ጋራ ፡ የሚመሳሰል ፡ ትግል ፡ ሲያደርጉና ፡ ከጋንዲ ፡ ጋራ ፡ የሚመሳሰል ፡ መሪ ፡ ሲያፈሩ ፡ አልታዩም ። በደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ በጥቍሮች ፡ ላይ ፡ የሚሠራውን ፡ ግፍ ፡ እስቲ ፡ እናስተውለው ። የቤልጂክ ፡ ግዛት ፡ በሆነው ፡ በኮንጎም ፡ የነበረውን ፡ ጭቈና ፡ እናስበው ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ የወደቀባቸውን ፡ ቀንበር ፡ ለመስበር ፡ የሚችሉበትን ፡ ትግል ፡ አለማሳየታቸው ፡ ደካማነታቸውን ፡ ይመሰክራል ።

በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ነገሩን ፡ ስናመዛዝነው ፡ ጃፓን ፡ ያውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ በሙሉ ፡ እጅ ፡ አድርጋ ፡ ባትታይ ፡ ኖሮ ፡ የእስያ ፡ ሕዝቦች ፡ ከቶ ፡ ለመንቀሳቀስ ፡ ይደፍሩ ፡ ኖሯል ፡ ወይ ? የማለት ፡ ጥያቄ ፡ ከፊታችን ፡ ስለሚቀርብ ፡ የህንድ ፡ ሕዝብና ፡ ጋንዲ ፡ ያደረጉት ፡ ትግል ፡ ከጃፓን ፡ ታሪክ ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ጃፓንም ፡ ሆነች ፡ ህንድ ፡ ሁለቱም ፡ የእስያ ፡ ሕዝቦች ፡ በመሆናቸው ፡ በየበኩላቸው ፡ ሁለቱም ፡ የሠሩት ፡ የሚያስመሰግን ፡ ሥራ ፡ ታሪካቸውን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ለማሳየት ፡ በቂ ፡ ሲሆን ፡ ያፍሪቃን ፡ ሕዝቦች ፡ ስንፍና ፡ የሚለውጠው ፡ ሆኖ ፡ አይገኝም ።

ሺን ፡ ደግሞ ፡ በበኩሏ ፡ እንሆ ፡ ዛሬ ፡ በዘመናዊው ፡ ሥልጣኔ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ግሥገሣ ፡ በመፈጸም ፡ ላይ ፡ ትገኛለች ። ይህንንም ፡ ለማድ

ረግ ፡ ያስገደዳት ፡ ያውሮፓ ፡ መንግሥታትና ፡ በተለየም ፡ ጃፓን ፡ የሠሩ
ባትን ፡ ግፍ ፡ በማስታወስና ፡ ለወደ ፡ ፊቱ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ጥቃት ፡
እንዳይሠራባት ፡ የማትደፈር ፡ ሆና ፡ ለመገኘት ፡ ስለ ፡ ፈለገች ፡ ነው ። የ
ሺና ፡ አያያዝ ፡ ለህንድ ፡ ጣጣ ፡ (ፕሮብሌም) ፡ ሳይፈጥርባት ፡ አይቀርም ።
ህንድ ፡ በበኩሏ ፡ በዘመናዊው ፡ ሥልጣኔ ፡ ራሷን ፡ ችላ ፡ ለመገኘት ፡ ስት
ጣጣር ፡ ትታያለች ። ነገር ፡ ግን ፡ ከሃይማኖቷ ፡ ጋራ ፡ የተያያዙ ፡ ብዙ ፡ ል
ማዶች ፡ ችግር ፡ ፈጥረውባታል ። ጐረቤቷ ፡ የሆነችው ፡ ሺና ፡ በተፋጠነ ፡
እርምጃ ፡ ቀድማት ፡ የሄደች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መቈጨትን ፡ እንዳያሳድር
ባት ፡ መጠቃትንም ፡ እዳይፈጥርባት ፡ ያሠጋታል ።

ጋንዲ ፡ ያውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ በሙሉ ፡ ተቃዋሚ ፡ መሆኑን ፡ ተመ
ልክተናል ። ኢንዱስትሪን ፡ ወደ ፡ ህንድ ፡ አገር ፡ በማግባት ፡ ፈንታ ፡
ሕዝቡ ፡ እንደ ፡ አባቶቹ ፡ በእጁ ፡ እየፈተለ ፡ ልብሱን ፡ እንዲለብስና ፡
ለኑሮው ፡ የሚያስፈልገውንም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ እንዲሠራ ፡ መክሮ
ታል ። ነገር ፡ ግን ፡ ጎረቤቱ ፡ የሆነው ፡ የሺና ፡ ሕዝብ ፡ ዘመናዊውን ፡ ሥ
ልጣኔ ፡ ተከትሎ ፡ ሀብት ፡ እያገኘና ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ እየሠራ ፡ በቀን፡
በቀኑ ፡ እድገቱን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ሲያደርግ ፡ የህንድ ፡ ሕዝብ ፡ ያባቶቹን ፡
አኗኗር ፡ ተከትሎ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርቶ ፡ ሊገኝ ፡ ፈቃደኛ ፡ ይሆናልን ?
በረኃብና ፡ በበሽታ ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ የሚያልቀው ፡ የህንድ ፡ ሕዝብ ፡ ቍ
ጥሩ ፡ አያሌ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ የሕዝቡ ፡
ቍጥር ፡ የሚወለደውና ፡ የሚሞተው ፡ ከተካካሰ ፡ በኋላ ፡ ባመት ፡ ባ
መቱ ፡ አንድ ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ እየጨመረ ፡ ይሄዳል ። ስለዚህ ፡ የህ
ንድ ፡ ሕዝብ ፡ ጎረቤቱ ፡ የሆነችው ፡ አገር ፡ ስትበልጠው ፡ እያየ ፡ ከጌ
ትነት ፡ ድኽነት ፡ ከማጥቃት ፡ መጠቃት ፤ ከተድላ ፡ መጐሳቈል ፡ ይሻለ
ኛል ፡ ብሎ ፡ ይቀመጣል ፡ ብሎ ፡ ለማመን ፡ ያስቸግራል ።

የጋንዲን ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ እስቲ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሰን ፡ እን
መልከተው ። የሕንድ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የጋንዲን ፡ አሳብ ፡ መቶ ፡
በመቶ ፡ ተቀብለው ፡ በሱ ፡ የሚመሩ ፡ ነበሩን ? ይህንን ፡ እንዳንል ፡ ጋን
ጋንድሐር ፡ ቲላክ ፡ የሚባለውን ፡ የመሰለ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሰው ፡ ባ
ገሩ ፡ ትምህርትና ፡ በዘመናዊው ፡ ያውሮፓ ፡ ዕውቀት ፡ የበሰለ ፡ ከመሆኑ ፡
በላይ ፡ በማቴማቲክ ፡ የተመሰገነ ፡ ሊቅ ፡ ነበር ። ህንድ ፡ መጀመሪያ ፡ ስለ ፡
ነጻነቷ ፡ መንቀሳቀስ ፡ በጀመረች ፡ ጊዜ ፡ ቲላክ ፡ መሪ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ።
ጋንዲም ፡ የሱ ፡ ተከታይና ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሰው ፡ ሞት ፡
ባይቀድመው ፡ ኖሮ ፡ ከመስኮቦች ፡ ወይም ፡ ከጃፓኖች ፡ ጋራ ፡ ስምምነት ፡
አድርጎ ፡ እንግሊዞችን ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ ኀይል ፡ ለማስወጣት ፡ ያሳብ ፡
ዝንባሌ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ሮመ ፡ ሮላ ፡ (Romain Rolland) የተባለው ፡



የጋንዲን ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ የጻፈ ፡ ደራሲ ፡ ገልጦልናል ። ነገር ፡ ግን ፡
ይህ ፡ ሰው ፡ የወጠነውን ፡ ፕሮግራም ፡ በሙሉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሳያው
ለው ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ በሱ ፡ እግር ፡ ጋንዲ ፡ ተተካ ።

ጋንዲ ፡ ከእንግሊዝ ፡ አገር ፡ እየተሠሩ ፡ የሚመጡትን ፡ ጨርቃ ፡ ጨ
ርቆች ፡ የህንድ ፡ ተወላጆች ፡ የሆኑት ፡ ከደባባይ ፡ ቦታ ፡ እያወጡ ፡ በእ
ሳት ፡ እንዲያቃጥሏቸው ፡ ባዘዘ ፡ ጊዜ ፡ ከህንድ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ አንዱ፡
የሆነው ፡ ራቢንድራናት ፡ ታጎር ፡ የሚባለው ፡ ስሙ ፡ በጣም ፡ የታወ
ቀው ፡ ባለቅኔ ፡ ነቅፎታል ። ሥልጣኔ ፡ ካፈራቻቸውና ፡ ሰዎች ፡ በጥበብ ፡
ደክመው ፡ ከፈጠሯቸው ፡ ፋብሪኮች ፡ የተገኙትን ፡ ጨርቆች ፡ በእሳት ፡
ማቃጠል ፡ የሥልጣኔ ፡ ተቃዋሚ ፡ መሆንን ፤ በጥበብ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በመ
ራመድ ፡ ፈንታ ፡ ወደ ፡ ድንቍርና ፡ እንመለስ ፡ ማለትን ፡ የሚያሳይ ፡ ነ
ገር ፡ በመሆኑ ፡ ይህ ፡ አደራረግ ፡ ሕዝብን ፡ የሚያባልግ ፡ ለኀሊናውም ፡
የሚጐዳው ፡ እንጂ ፡ የማይጠቅመው ፡ መሆኑን ፡ ታጎር ፡ እያሳሰበ ፡ የዘ
ለፋ ፡ ድምፁን ፡ ለጋንዲ ፡ አሰምቶታል ። በጋንዲና ፡ በታጎር ፡ መካከል ፡
የመከባበር ፡ መንፈስ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ጋንዲ ፡ ይህ ፡ ዘለፋ ፡ በሚገባ ፡ የተደ
ረገበት ፡ መሆኑ ፡ ሳይሰማው ፡ አልቀረም ።

የሆነው ፡ ሆኖ ፡ ጋንዲ ፡ የህንድ ፡ ነጻነት ፡ ሲቋቋም ፡ ባይኑ ፡ የማየ
ትን ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡ ካገኘ ፡ በኋላ ፡ ስለ፡ሞተ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ህንድ ፡
የሚገጥሟትን ፡ ችግሮች ፡ እስካሁን ፡ ቈይቶ ፡ ተካፋይ ፡ አልሆነም ። ዳሩ ፡
ግን ፡ የህንድ ፡ ሕዝብ ፡ በሥልጣኔ ፡ በኩል ፡ ሙሉ ፡ ድርጅት ፡ እንዲያኝ፡
ለማድረግ ፡ አስቦ ፡ ይህንኑ ፡ ለመፈጸም ፡ ቢነሣ ፡ ኖሮ ፡ በጣም ፡ አስቸ
ጋሪ ፡ እንደሚሆንበት ፡ አይጠረጠርም ። ለምሳሌ ፤ አሁን ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡
ከተባበሩት ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ በቴክኒክ ፡ ርዳታ ፡ ክ
ፍል ፡ ህንድ ፡ አገር ፡ ሔዶ ፡ የውሃ ፡ ጕድጓድ ፡ ቍፋሮ ፡ ይሠራ ፡ የነበር ፡
አንድ ፡ ቴክኒሲያን ፡ ሕዝቡ ፡ በውሃ ፡ እጦት ፡ በኩል ፡ ያለበትን ፡ ችግር ፡
ለማቃለል ፡ በመኪና ፡ ብዙ ፡ የውሃ ፡ ጕድጓዶች ፡ ከቈፈረ ፡ በኋላ ፡ ባካባ
ቢው ፡ የሚኖረው ፡ ሕዝብ ፡ ከተቀደሰው ፡ ከጋንዥ ፡ ወንዝ ፡ ከሚገኘው ፡
ውሃ ፡ በቀር ፡ ከሌላ ፡ ቦታ ፡ መቅዳት ፡ መቅሠፍት ፡ ያመጣል ፡ ብሎ ፡ የሚ
ያምን ፡ በመሆኑ ፡ ሌሊት ፡ በጨለማ ፡ መጥቶ ፡ የተቈፈሩትን ፡ የውሃ ፡
ጕድጓዶች ፡ መልሶ ፡ እንደ ፡ ደፈናቸው ፡ ይነገራል ። ሌላም ፡ ይህን ፡ የመ
ሰሉ ፡ የሕዝቡን ፡ አኗኗር ፡ ለማሻሻል ፡ ሲባል ፡ ማስቀረት ፡ የሚያስፈልግ ፡
ብዙ ፡ ልማዶች ፡ አሉ ። ሕንድ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚጠብቃት ፡ ችግር ፡ ይህ ፡
ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ጋንዲ ፡ ያገሩን ፡ ነጻነት ፡ ካቋቋመ ፡ በኋላ ፡ እነዚህ ፡ ጕጓዮች ፡
በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ አስቸኳይነታቸው ፡ ጊዜ ፡ የማይሰጥ ፡ ሆኖ ፡ ከፊቱ ፡
በሚቀርቡበት ፡ ሰዓት ፡ ሞተ ።

ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ግን ፡ አገራቸው ፡ ከሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ጋራ ፡ በዘመናዊ ፡ ጥበብ ፡ የተደራጀች ፡ ሆና ፡ እንድትገኝ ፡ ለዚህ ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ ሕይወታቸውን ፡ መሥዋዕት ፡ ለማድረግ ፡ ዕድል ፡ አግኝተዋል ። የህንድ ፡ ሕዝብ ፡ ዘጠና ፡ ዓመታት ፡ በሚጠጋ ፡ ዘመን ፡ የእንግሊዝ ፡ ተገዥ ፡ ሆኖ ፡ በመኖሩ ፡ በዚህ ፡ በባዕድ ፡ ግዛት ፡ ዘመን ፡ ሽፋጭነትን ፡ ማታለልን ፡ ራስን ፡ ማዋረድን ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ባርነት ፡ የሚያስከትለውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጥፎ ፡ ጠባይ ፡ እንደ ፡ ወረሰ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሊሆን ፡ የቻለው ፡ ህንድ ፡ በዘመናዊ ፡ ጥበብ ፡ ደካማ ፡ ሆና ፡ በመገኘቷ ፡ አይደለምን ? ወደ ፡ ፊትም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርታ ፡ በመገኘት ፡ ኀይለኛ ፡ የሆነ ፡ ሌላ ፡ አጥቂ ፡ ሲነሣባት ፡ ተመልሳ ፡ እዚያው ፡ እባርነት ፡ እንዳትገባ ፡ አያስፈራትም ፡ ወይ ? ለምሳሌ ፡ ጃፓን ፡ በዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ራሷን ፡ ለመቻል ፡ የበቃችው ፡ ብዙ ፡ የመሥዋዕትነት ፡ ሥራ ፡ ፈጽማ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ያደረገችው ፡ ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔን ፡ በሁሉም ፡ በኩል ፡ በመውደዷና ፡ በማድነቋ ፡ ሳይሆን ፡ ነጻነቷን ፡ ከመደፈር ፡ ለማዳን ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በጋንዲ ፡ አስተያየት ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ደካማነት ፡ አድርገን ፡ የምንቈጥረው ፡ ይህ ፡ ሲሆን ፡ አሁንም ፡ እንደ፡ገና ፡ ለመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ በሌላ ፡ አርእስት ፡ ላይ ፡ ጕዳዩን ፡ ደግመን ፡ እንመለከተዋለን ። ህንድ ፡ እንደምናየው፡ ነገሩን ፡ በማመዛዘን ፡ የጋንዲን ፡ አሳብ ፡ ትታ ፡ አሁን ፡ የያዘችውን ፡ በመከተል ፡ በሳይንስና ፡ በቴክኒክ ፡ ማለት ፡ በምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ራሷን ፡ እስከ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ሳትችል ፡ የቀረች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሺን ፡ ምክንያት ፡ ከኮሚኒስትነት ፡ ላይ ፡ እንዳትወድቅ ፡ በጣም ፡ ያሠጋታል ። ይህም ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ መቅሠፍት ፡ የሚቈጠርና ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አደጋ ፡ ሊያስከትል ፡ የሚችል ፡ ነገር ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ነጻ ፡ መውጣትና ፡ ጋንዲ ፡ የፈጸመው ፡ ሥራ ፡ በማቴሪያሊስም ፡ ለተመረዘችው ፡ የዛሬይቱ ፡ ዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ትምህርት ፡ ሆነው ፡ የሚቈጠሩ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ።

ይህን ፡ የመሰለው ፡ ሁኔታ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ሊፈጠር ፡ ቻለ ? ብለን ፡ ነገሩን ፡ ጠልቀን ፡ የመረመርነው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኢትዮጵያም ፡ ሆነች ፡ ህንድ ፡ ድኾች ፡ አገሮች ፡ አይደሉም ። ነገር ፡ ግን ፡ ከአውሮፓ ፡ አህጉር ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ አገሮች ፡ አንድ ፡ ዘመናዊ ፡ መንግሥት ፡ ስለ ፡ ኤኰኖሚ ፡ አስተዳደሩ ፡ በምን ፡ ዐይነት ፡ አካሄድ ፡ ሊመራ ፡ እንደሚገባው ፡ አያውቁትም ። ይህን ፡ ለመሰለው ፡ አሳብ ፡ እንግዶች ፡ ሆነው ፡ ይቈጠራሉ ። መርምረው ፡ ከተረዱት ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ሥራው ፡ ከባድ ፡



ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ የቀድሞውን ፡ ለውጠው ፡ ሊሠሩበት ፡ የሚችሉት ፡ ነገር ፡ አይደለም ። ይልቁንም ፡ ባለፈው ፡ ታሪካቸውና ፡ ባህሎቻቸው ፡ የሚመኩ ፡ አገሮች ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ ሊፈጽሙት ፡ ሲነሡ ፡ አስቸጋሪና ፡ ረዥምም ፡ ጊዜም ፡ የሚጠይቅ ፡ አዳጋች ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ ያገኙታል ።

# ሰውና ፡ ጥበብ ።

ሰው ፡ በጥበብ ፡ በኩል ፡ ለሚያደርገው ፡ እርምጃ ፡ ከዚህ ፡ አትለፍ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ የወሰነለት ፡ ድንበር ፡ መኖሩንና ፡ አለመኖሩን ፡ አናውቅም ። ነገር ፡ ግን ፡ በሳይንስ ፡ ምርመራ ፡ ሰዎች ፡ አሁን ፡ የደረሱበት ፡ ደረጃ ፡ እጅግ ፡ የሚያስደንቅ ፡ መሆኑን ፡ በየቀኑ ፡ በዐይናችን ፡ የምናየውና ፡ በጆሯችን ፡ የምንሰማው ፡ ነገር ፡ ነው ። ሰው ፡ ኑሮውን ፡ ለማሻሻል ፡ በሳይንስ ፡ በኩል ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሙቀት ፡ ብርሃንና ፡ በድን ፡ የሆነውን ፡ አካል ፡ (matière) የሚያንቀሳቅስበት ፡ የጕልበት ፡ ምንጭ ፡ የሆነ ፡ ጥበብ ፡ ማግኘት ፡ ነው ። ባሁኑ ፡ ጥበብ ፡ እነዚህ ፡ ሦስት ፡ ነገሮች ፡ ከኤሌክትሪሲቲ ፡ ይገኛሉ ። ፀሐይ ፡ በሥነ ፡ ፍጥረቷ ፡ ትልቅ ፡ የጕልበት ፡ ምንጭ ፡ መሆኗ ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ። ከፀሐይ ፡ የሚመጣው ፡ ሙቀት ፡ ከሚሊያርድ ፡ ቦታ ፡ ተከፍሎ ፤ ተቈራርሶ ፤ ከሚሊያርደኛው ፡ ቍራሽ ፡ ግማሹ ፡ ብቻ ፡ ለመሬት ፡ የሚደርሳት ፡ መሆኑን ፡ የሳይንስ ፡ ሊቃውንት ፡ ይናገራሉ ። የቀረው ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ ሥራ ፡ ሳይሠራበት ፡ የትም ፡ ባክኖ ፡ የሚቀር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይህንን ፡ በከንቱ ፡ የሚባክን ፡ ጕልበት ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻልበትን ፡ ዘዴ ፡ ሊቃውንት ፡ በማጥናት ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ ።

ስለ ፡ ፀሐይ ፡ ለመናገር ፡ ስንገደድ ፡ ስለ ፡ (ኰስሞስ) ፡ ማለት ፡ ስለ ፡ ፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ አኳኋን ፡ ጥቂት ፡ መግለጫ ፡ መስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ይህ ፡ ሲሆን ፡ መሬትን ፡ ትተን ፡ ወደ ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ መሄድ ፡ ይኖርብናል ። ከመጀመሪያዎቹ ፡ ምዕራፎች ፡ ጀምረን ፡ የሥልጣኔ ፡ ትርጉም ፡ በግዙፍ ፡ አካልና ፡ በመንፈስ ፡ ጠባይ ፡ በኩል ፡ ባሉት ፡ ነገሮች ፡ እንደሚከፈል ፡ ተናግረናል ። ካንት ፡ የሚባለው ፡ የጀርመን ፡ ፈላስፋ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ ያለው ፡ አድናቆትና ፡ ተመሥጦ ፡ ዘለዓለም ፡ ጸንቶ ፡ እንደሚኖር ፡ ሲያሳስብ ፡ እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ ምንና ፡ ምን ፡ መሆናቸውን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተጠቀሰው ፡ ቃል ፡ ገልጧቸዋል ።

«ከራሳችን ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ከዋክብት ፡ ያለበሱት ፡ ሰማይና ፡ በልባችን ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ የሞራል ፡ ሕግ ፡ ናቸው» ። «Le ciel étoilé au-dessus de nos têtes et la loi morale au fond de notre cœur.»

እንሆ ፡ ሰዎች ፡ በጥበብ ፡ የገፉ ፡ ዕውቀት ፡ ካገኙ ፡ ጀምሮ ፡ ከራሳቸው ፡ በላይ ፡ በሚገኘው ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ ተበታትነው ፡ የሚታዩትን ፡ ከዋክብት ፡ ምስጢራቸውን ፡ ለማግኘት ፡ ከመጓጓት ፡ ተወስነው ፡ አያውቁም ። ባቢሎናውያንና ፡ ከልዳውያን ፡ በከዋክብት ፡ በኩል ፡ የገፉ ፡ ዕውቀት ፡ ነበራቸው ። የጥንቶቹ ፡ ሰዎችና ፡ የዛሬዎቹ ፡ መንፈሳቸው ፡ ወደ ፡ ከዋክብት ፡ እኩል ፡ የተሳበ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ የጥበባቸው ፡ መንገድ ፡ የተለያየ ፡ ነው ። የጥንቶቹ ፡ በከዋክብትና ፡ በምድራውያን ፡ ሰዎች ፡ ዕድል ፡ መካከል ፡ ግንኙነት ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ስላመኑ ፡ ጥበባቸው ፡ ከጥንቈላ ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። የዛሬዎቹ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ከዋክብት ፡ ለማወቅ ፡ የሚሹት ፡ ሥነ ፡ ፍጥረታቸውን ፤ አዟዟራቸውን ፤ ክብደታቸውን ፡ ትልቅነታቸውን ፤ ብዛታቸውን ፤ በመካከላቸው ፡ ያለውን ፡ የመሳሳብ ፡ ግንኙነትና ፡ መራራቅ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ ሊቃውንት ፡ መርምረው ፡ የደረሱበትን ፡ ስንመለከተው ፡ በጣም ፡ አስደናቂ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ በጣም ፡ የጠለቀ ፡ ጥበብ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ያደረጉትን ፡ ሳይንቲፊክ ፡ የሆነ ፡ ምርመራ ፡ በሙሉ ፡ ለመከታተል ፡ አንችልም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሊገባን ፡ የሚችለውን ፡ ያኽል ፡ ዋና ፡ ዋናውን ፡ ነገር ፡ በመጠኑ ፡ ልንጠቅሰው ፡ እንችላለን ። ሌሊት ፡ ጨለማ ፡ ሲሆን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አንጋጠን ፡ ስንመለከት ፡ ካንድ ፡ ሺሕ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ከዋክብት ፡ በላይ ፡ በዐይናችን ፡ ለማየት ፤ እንደዚሁም ፡ ሰማዩ ፡ በጣም ፡ የጠራ ፡ በሆነበት ፡ ቀን ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ ካንድ ፡ ሺሕ ፡ ስምንት ፡ መቶና ፡ ከሁለት ፡ ሺሕ ፡ ከዋክብት ፡ የበለጠ ፡ ለመመልከት ፡ እንደማንችል ፡ የከዋክብት ፡ ሊቃውንት ፡ ያረጋግጡልናል ። ባይን ፡ ለማየት ፡ በጣም ፡ የሚያስቸግሩትን ፡ ጥቃቅን ፡ የሆኑትን ፡ ከዋክብት ፡ የጨመርን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እጅግ ፡ ግፋ ፡ ቢል ፡ አምስትና ፡ ስድስት ፡ ሺሕ ፡ ከዋክብት ፡ ለማየት ፡ ይቻል ፡ ይሆናል ፡ ሲሉ ፡ ጨምረው ፡ ያሳስባሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ በቴሌስኮፕ ፡ መነጥር ፡ አማካይነት ፡ ሰማዩን ፡ ሌሊት ፡ ብንመለከተው ፡ እንደ ፡ መነጥሩ ፡ ጥሩነትና ፡ ጥልቅነት ፡ ጠባብ ፡ በሆነ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ የምናያቸው ፡ ከዋክብት ፡ ቍጥራቸው ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ይደርሳል ። በአሜሪካ ፡ አገር ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ በሆነው ፡ ፓሎማር ፡ በሚባለው ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ በሚገኘው ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ካሉት ፡ ቴሌስኮፖች ፡ (መነጥሮች) ፡ ሁሉ ፡ በሚበልጠው ፡ የከዋክብት ፡ መመርመሪያ ፡ በሆነው ፡ ቴሌስኮፕ ፡ ስንመለከት ፡ ግን ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ሚሊያርድ ፡ የሚሆኑ ፡ ከዋክብት ፡ ለመቍጠር ፡ ይቻላል ። ነገር ፡ ግን ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ከዋክብት ፡ ብዛታቸው ፡ ሲታይ ፡ አንድ ፡ ሚሊያርድ ፡ እንደ ፡ ቀልድ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ። እኛ ፡ ምድራውያን ፡ የሆነው ፡ ሰዎች ፡ የምንመለከታቸው ፡ ከዋክብት ፡ በመካከላቸው ፡ ትልቅ ፡ ርቀት ፡ ያለ ፡ አይመስለንም ። ከዋክብቶቹ ፡



ጐን ፡ ለጐን ፡ ተቀራርበው ፡ ወይም ፡ ተደራርበው ፡ የተቀመጡ ፡ ይመስለናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የሚሆነው ፡ በእኛና ፡ በእነሱ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ርቀት ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ እያንዳንዱ ፡ ኮከብ ፡ ከሌላው ፡ ወይም ፡ ከሌሎቹ ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ መራራቅ ፡ ከግምት ፡ በላይ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ አውሮፓ ፤ ካውሮፓ ፡ አሜሪካ ፡ ያለው ፡ ርቀት ፡ ባምስትና ፡ ባሥር ፡ ሺሕ ፡ ኪሎሜትር ፡ ይሰፈራል ። በከዋክብት ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ርቀት ፡ ግን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ሺህ ፡ ኪሎሜትር ፤ ወይም ፡ ሚሊዮን ፡ ኪሎሜትር ፤ ወይም ፡ ሚሊያርድ ፡ ኪሎሜትር ፡ መስፈሪያ ፡ ሆኖ ፡ ሊያገለግል ፡ አይችልም ። በእኛና ፡ በከዋክብት ፡ እንደዚሁም ፡ ባንድ ፡ ኮከብና ፡ በሌላዪቱ ፡ ኮከብ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ርቀት ፡ ለመስፈር ፡ ሊቃውንት ፡ «ዓመት ፡ ብርሃን» ፡ የሚባል ፡ ስም ፡ አውጥተውለታል ። ይህም ፡ ብርሃን ፡ ባንድ ፡ ሰኮንድ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ኪሎሜትር ፡ የሚሄድ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ሲሆን ፡ ባንድ ፡ ዓመት ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ እንደሚድ ፡ ሲታሰብ ፡ በሚሰጠው ፡ መጠን ፡ መሆኑ ፡ ነው ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ብርሃን ፡ ማለት ፡ ከግምት ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ መሥፈሪያ ፡ ነው ። እስከ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ሚሊያርድ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ይደርሳል ።

እንደዚሁም ፡ ከዋክብት ፡ ሲቈጠሩ ፡ በሰፈራቸው ፡ እየተለዩ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ ተብለው ፡ ለመቍጠር ፡ ቢሞከር ፡ ኖሮ ፡ የሚገፋ ፡ ነገር ፡ አይደለም ። በሰማይ ፡ ላይ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ብዙ ፡ የከዋክብት ፡ ሰራዊት ፡ የሰፈሩባቸው ፡ የከዋክብት ፡ ሰፈሮች ፡ ይገኛሉ ። የከዋክብቶች ፡ ሰፈር ፡ ኔቡለዝ ፡ ወይም ፡ ጋላክሲ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። ባንድ ፡ የከዋክብት ፡ ሰፈርና ፡ በሌላው ፡ ሰፈር ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ርቀት ፡ በሰው ፡ አሳብ ፡ ሊገመት ፡ አይችልም ። እንደዚሁም ፡ ባንድ ፡ ሰፈር ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ከዋክብት ፡ የሰፈራቸው ፡ ወሰን ፡ በስፋት ፤ በጐን ፤ በጥልቀት ፡ ይገመታል ። ተሰብስበው ፡ የሚገኙበት ፡ ስፍራ ፡ በዋንጫ ፡ ወይም ፡ በሳህን ፡ ሊመሰል ፡ ይችላል ። ይህም ፡ የሠፈራቸው ፡ ቅርጽ ፡ ሁኔታ ፡ ዋንጫን ፡ ወይም ፡ ሳሕንን ፡ የመሰለ ፡ ቅርጽ ፡ ይዞ ፡ የሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሊቃውንት ፡ መርምረው ፡ ከደረሱባቸው ፡ ከብዙዎቹ ፡ የከዋክብት ፡ ሰፈሮች ፡ በጣም ፡ የራቀ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኘው ፡ የከዋክብት ፡ ሰፈር ፡ እኛ ፡ ካለንበት ፡ መሬት ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ መራራቅ ፡ ባምስት ፡ መቶ ፡ ሚሊዮን ፡ «ዓመት ፡ ብርሃን» ፡ ይሰፈራል ። በዚህ ፡ ሰፈር ፡ ያሉ ፡ ከዋክብት ፡ ብርሃናቸው ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ሚሊዮን ፡ ዓመታት ፡ ሲጓዝ ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ የሚደርሰው ፡ ማለት ፡ ነው ።

ከሁሉም ፡ ወደኛ ፡ የቀረበ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኘው ፡ የከዋክብት ፡ ሰፈር ፡ አንድሮሜድ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ ነው ። በእሱና ፡ በእኛ ፡ መካ

ከል ፡ ያለው ፡ ርቀት ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ብርሃን ፡ ነው ። የእኛ ፡ መሬት ፡ የምትገኝበት ፡ የከዋክብት ፡ ሰፈር ፡ ጋላክሲ ፡ ወይም ፡ (voie lactée) የወተት ፡ ጐዳና ፡ የሚባለው ፡ ነው ። የወተት ፡ ጐዳና ፡ የሚባል ፡ ስያሜ ፡ የተሰጠው ፡ የተከማቹት ፡ ከዋክብት ፡ ሰፈሩን ፡ ወተት ፡ የፈሰሰበት ፡ ነጭ ፡ ጥርጊያ ፡ መንገድ ፡ ስላስመሰሉት ፡ ነው ። ይህ ፡ የከዋክብት ፡ ሰፈር ፡ ጐኑ ፡ ዘጠና ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ብርሃን ፤ ውፍረቱ ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ብርሃን ፡ ነው ። በዚህ ፡ ሰፈር ፡ ተከማችተው ፡ የሚገኙት ፡ ከዋክብት ፡ ቍጥራቸው ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሚሊያርድ ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ። እንግዲህ ፡ ለእኛ ፡ ሙቀትንና ፡ ብርሃንን ፡ የምትሰጠን ፡ ፀሐይ ፡ ከእነዚህ ፡ ከዋክብት ፡ አንዷ ፡ ነች ። በፀሐይ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሙቀት ፡ ኻያ ፡ ሚሊዮን ፡ ደግሬ ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ።

በዚህ ፡ ረገድ ፡ ስለ ፡ ፀሐይ ፡ ሁኔታ ፡ ሊቃውንት ፡ የሚሰጡን ፡ የሳይንቲፊክ ፡ መግለጫ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ። በፀሐይ ፡ ውስጥ ፡ የሚፈጸመው ፡ ነገር ፡ (réactions thermonucléaires) ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ከከፍተኛ ፡ የሙቀት ፡ ኀይል ፡ የተነሣ ፡ የአቶሙ ፡ አስኳል ፡ ተገምሶ ፡ እየተከፈለ ፡ ሲሰበር ፡ ሂድሮገኤን ፡ ወደ ፡ ሄልዮም ፡ የሚለወጥ ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ።

ይህ ፡ ነገር ፡ የተፍታታ ፡ ሆኖ ፡ ላንባቢ ፡ እንዲገለጥለት ፡ ለማድረግ ፡ ሲፈለግ ፡ ሐተታውን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ አድርጎ ፡ ለማስረዳት ፡ ይቻላል ። ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ብረትም ፡ ሆነ ፡ ድንጋይ ፡ ዕንጨትም ፡ ሆነ ፡ ሌላ ፡ የተሠራው ፡ በማቲየር ፡ ነው ። ማቲየሮች ፡ (ነባር ፡ አካሎች) ፡ በተፈጥሯቸው ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ እንደ ፡ ተናገርነው ፡ በአቶሞች ፡ የተቀመሙ ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ የብረት ፡ አቶም ፡ የዕንጨት ፡ አቶም ፡ የሂድሮገኤን ፡ አቶም ፡ እየተባሉ ፡ ይጠራሉ ። አቶሞች ፡ ደግሞ ፡ በበኩላቸው ፡ particules ወይም ፡ corpuscules ወይም ፡ molécules ተብለው ፡ በሚጠሩ ፡ ደቂቅ ፡ ፍጡሮች ፡ ወይም ፡ ነባር ፡ ፍጡሮች ፡ ተቀምመው ፡ ተሠርተዋል ። እነሱም ፡ (proton, neutron, électron, positon, meson, photon) ይባላሉ ። አንዱን ፡ አካል ፡ (matière) እንዳልነበረ ፡ ሲያደርጉት ፡ እነዚህ ፡ በውሥጡ ፡ ያሉት ፡ ነባር ፡ ፍጡሮች ፡ ይፈነዳሉ ፤ ሲፈነዱም ፡ ብርሃንና ፡ ሙቀትን ፡ ጕልበትንም ፡ ይፈጥራሉ ። ለምሳሌ ፤ ለፀሐይ ፡ ይህንን ፡ የምናየውን ፡ የመሰለ ፡ ታላቅ ፡ ብርሃንና ፡ ሙቀት ፡ የሚሰጣት ፡ በውስጧ ፡ እየተቃጠለ ፡ የሚፈነዳ ፡ የሂድሮገኤን ፡ አቶም ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ። አቶምን ፡ የሚያፈነዳው ፡ ትልቅ ፡ የመጫን ፡ ኀይል ፡ ወይም ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የሙቀት ፡ ኀይል ፡ ነው ። በፀሐይ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ አቶም ፡ የሚያፈነዳው ፡ በኻያ ፡ ሚሊዮን ፡ ዲግሪ ፡ የሚመጠነው ፡ ሙቀት ፡ ነው ።



ፀሐይ ፡ አሁንም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ገና ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ሚሊያርድ ፡ ዓመታት ፡ ሳትጠፋ ፡ ለመቈየት ፡ እንደምትችል ፡ ሊቃውንት ፡ ገምተውታል ። የከዋክብት ፡ ሊቃውንትና ፡ የፊዚክ ፡ ሊቃውንት ፡ ሥራቸው ፡ በጣም ፡ የተቀራረበና ፡ የተያያዘ ፡ ሆኖ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ በተዘረዘሩት ፡ ምክንያቶች ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ እኛ ፡ የተፈጠርንባት ፡ መሬትና ፡ በሷም ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ፍጡሮች ፡ ሁሉ ፡ ተቀምመው ፡ የተሠሩት ፡ በዘጠና ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ (ኤሌሜንቶች) ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ። አቶም ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ እየተፈረፈረ ፤ እየደቀቀ ፡ እንደ ፡ ዱቄት ፡ እየተፈጨና ፡ እየተላመ ፡ ቢሄድ ፡ በመጨረሻ ፡ በጣም ፡ ከመድቀቁ ፡ የተነሣ ፡ ሊከፈል ፤ ሊፈረፈር ፡ የማይችል ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የዱቄቱ ፡ አንዷ ፡ ቅንጣት ፡ ማለት ፡ ልትፈርስ ፡ የማትችለው ፡ ክፍል ፡ አቶም ፡ ትባላለች ። አቶም ፡ በጣም ፡ ታናሽ ፡ ከመሆኗ ፡ የተነሣ ፡ ለምሳሌ ፡ በብረት ፡ ውስጥ ፡ ያለች ፡ አቶም ፡ አንድ ፡ ሚሊሜትር ፡ ብረት ፡ ለማግኘት ፡ አምስት ፡ ሚሊዮን ፡ አቶም ፡ መሰብሰብ ፡ ያስፈልጋል ። ስለ ፡ አቶም ፡ ጕዳይ ፡ ከዚህ ፡ የተረፈውን ፡ በሌላ ፡ ምዕራፍ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንመለከተዋለን ። ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ የሰው ፡ አንጐል ፡ የተጠመደው ፡ በጥበብ ፡ መኪናዎችና ፡ መሣሪያዎች ፡ ጕዳይ ፡ ብቻ ፡ በመሆኑ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ግል ፡ ሥነ ፡ ፍጥረቱና ፡ ስለ ፡ ነፍሱ ፡ ጠባዮች ፡ ለማሰብና ፡ ለመመርመር ፡ ጊዜ ፡ አላገኘም ። ሁሉንም ፡ ሥራ ፡ መኪናዎች ፡ እንዲሠሩለት ፡ አድርጓል ። ከሰው ፡ አንጐል ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ መሣሪያ ፡ ሊሠራ ፡ የማይቻል ፡ መስሎ ፡ ይገመት ፡ የነበረው ፡ ተግባር ፡ ሁሉ ፡ ዛሬ ፡ በመኪና ፡ ሲሠራ ፡ ይታያል ። በጣም ፡ የተወሳሰበ ፡ የሆነው ፡ የሒሳብ ፡ ሥራ ፡ (ፕሮብሌም) ፡ በመኪና ፡ ሊሠራ ፡ ጀምሯል ። በኤሌክትሮኒክ ፡ የተሠራ ፡ አንጐል ፡ ያላቸው ፡ መኪናዎች ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ሲፈጽሙ ፡ ይታያሉ ። አሁን ፡ የቀራቸው ፡ የድርሰትን ፡ ሥራ ፡ በእነሱ ፡ እንዲሠራ ፡ ማድረግ ፡ ብቻ ፡ ነው ። የእነ ፡ ሼክስፒር ፤ ገት ፤ ቮልቴር ፤ ዶስቶዬቭስኪ ፡ ተግባር ፡ በኤሌክትሮኒክ ፡ አንጐል ፡ ከሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ላይ ፡ እንደርስ ፡ ይሆን ? ተብሎ ፡ የሚያስጠይቅ ፡ ሆኗል ። በዓለም ፡ ላይ ፡ የሳይንስ ፡ ላቦራቷር ፡ በሚገኝበት ፡ በያንዳንዱ ፡ ቦታ ፡ በመጠናት ፡ ላይ ፡ የሚገኙ ፡ ጥበቦች ፡ ብዙ ፡ ከመሆናቸው ፡ የተነሣ ፡ ቈጥረን ፡ አንጨርሳቸውም ። አሁን ፡ እዚህ ፡ የምንጠቅሳቸው ፡ ዋናዎቹን ፡ ነገሮች ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ሌሊት ፡ ጨለማ ፡ የሚሆነው ፡ መሬት ፡ ስትዞር ፡ የራሷ ፡ ጥላ ፡ እያረፈባት ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ። ከመሬት ፡ በላይ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ በእ

የር ፡ ላይ ፡ የሚቆም ፡ በብረታብረት ፡ የተሠራ ፡ አንድ ፡ ጣቢያ ፡ ቢቋቋም ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ታላላቅ ፡ መስተዋቶች ፡ ተደርገው ፡ የፀሓይን ፡ ብርሃን ፡ እየተቀበሉ ፡ ጥላ ፡ በወደቀበት ፡ መሬት ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ ቢያብረቀርቁ ፡ ሌሊቱ ፡ ብርሃን ፡ እንደሚያገኝና ፡ ጨለማን ፡ ለመደምሰስ ፡ እንደሚቻል ፡ በሳይንስ ፡ ተጠንቶ ፡ ተረጋግጧል ። ይህም ፡ በአየር ፡ ላይ ፡ የሚሠራው ፡ ጣቢያ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ከዋክብት ፡ ለሚያደርጉት ፡ ጕዞ ፡ ከታቀደው ፡ ፕላን ፡ አሳብ ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ ነው ።

እንደዚሁም ፡ የኤሌክትሪሲቴ ፡ መሐንዲሶች ፡ የሆኑ ፡ የብረት ፡ ሰው ፡ (robot) እየሠሩ ፡ ቤት ፡ እንዲጠርግ ፤ ልብስና ፡ ሳሕን ፡ እንዲያጥብ ፤ እንዲላላክ ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የቤት ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ ፡ ለማድረግ ፡ አሁን ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ጥበቡን ፡ በሙሉ ፡ ደርሰውበታል ። ይህን ፡ የመሰለ ፡ የብረት ፡ ሰው ፡ ለመሥራት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ የተገኘው ፡ የአንጐሉን ፡ ሜካኒስም ፡ ማበጀቱ ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ። ነገር ፡ ግን ፡ የኤሌክትሮኒክ ፡ አንጐል ፡ ማበጀት ፡ እንደሚቻል ፡ አሁን ፡ ደርሰውበታል ። ወደ ፡ ፊት ፡ በብረት ፡ የተሠሩ ፡ ብዙ ፡ ወታደሮች ፡ ፈጥሮ ፡ የጦር ፡ ሰራዊት ፡ ለማቋቋም ፡ እንደሚቻል ፡ ይናገራሉ ። እነዚህም ፡ ወታደሮች ፡ ርኅራኄና ፡ ሰብአዊ ፡ ስሜት ፡ እንደማይኖራቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የብረት ፡ ሰው ፡ የሠሩ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ በመጨረሻ ፡ በሱው ፡ እጅ ፡ መሞታቸውን ፡ እንሰማለን ። በእጃቸው ፡ የሠሩት ፡ ይህ ፡ የብረት ፡ ሰው ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ ገደላቸው ፡ በሲያንቲፊክ ፡ በኩል ፡ ተመርምሮ ፡ ምስጢሩን ፡ ለማወቅ ፡ አልተቻለም ። ሰውን ፡ መፍጠር ፡ የእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ተግባር ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ በድፍረታቸው ፡ የተቀጡ ፡ መስሎ ፡ ይታያል ።

የኢንዱስትሪን ፡ መኪናዎች ፡ አቶማቲክ ፡ እየሆኑ ፡ እንዲሄዱ ፡ ለማድረግ ፡ የታቀደው ፡ አሳብ ፡ በቴክኒክ ፡ በኩል ፡ በመፈጸም ፡ ላይ ፡ ካሉት ፡ አስደናቂ ፡ ነገሮች ፡ አንዱ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፤ ባሁኑ ፡ ጥበብ ፡ ብዙ ፡ ሺሕ ፡ ሠራተኞች ፡ ይሠሩበት ፡ የነበረውን ፡ አንዳንድ ፡ ፋብሪካ ፡ በሦስትና ፡ ባራት ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ እንዲከናወን ፡ ለማድረግ ፡ ተችሏል ፡ ይባላል ። እንደዚሁም ፡ ለምሳሌ ፤ እንግሊዝ ፡ ለሕዝቧ ፡ ምግብ ፡ የሚሆን ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ እኽል ፡ ከመሬቷ ፡ እያረሰች ፡ ለማግኘት ፡ የማትችል ፡ በመሆኗ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ከቅኝ ፡ አገሮቿ ፡ ትወስድ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ እንነሱ ፡ ነጻ ፡ እየወጡ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ያሉት ፡ በሳይንስ ፡ ተቀምሞ ፡ የሚሠራ ፡ ምግብ ፡ በፋብሪካ ፡ እየሠራች ፡ ሕዝቧን ፡ ለመመገብ ፡ ተስፋ ፡ አላት ። ይህ ፡ ጥናት ፡ ሊፈጸም ፡ የሚችል ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ፡ ይባላል ። መሬቷ ፡ ሊመግብ ፡ የሚችለው ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡



ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ አሁን ፡ የሕዝቧ ፡ ቍጥር ፡ ካምሳ ፡ ሚሊዮን ፡ ደርሷል ። ስለዚህ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ መሰደድ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ዘዴ ፡ ፈጥሮ ፡ ሕዝቧን ፡ በጥበብ ፡ መመገብ ፡ ግድ ፡ ሆኖባታል ። ጥበብን ፡ በመፍጠር ፡ በኩል ፡ የያፌት ፡ ልጆች ፡ ሊሠሩት ፡ የማይችሉት ፡ ምን ፡ ነገር ፡ ይገኛል ? ይኸውም ፡ (photosynthèse radioactive) በተባለው ፡ ጥበብ ፡ መሠረት ፡ ሊፈጸም ፡ የታቀደ ፡ አሳብ ፡ ነው ።

ታላቁ ፡ የሳይንስ ፡ ሊቅ ፡ አይንሽታይን ፡ በጣም ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነገር ፡ ተናግሯል ። ከማንኛውም ፡ በድን ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ግራም ፡ ወስደን ፡ ጨርሶ ፡ እንዳልነበረ ፡ አድርገን ፡ ብናጠፋው ፡ (annihilation totale) ክብደቱ ፡ ኻያ ፡ ሚሊዮን ፡ ቶን ፡ ከሚመዝን ፡ ድንጋይ ፡ ከሰል ፡ ከሚገኝ ፡ ጕልበት ፡ ጋራ ፡ ሊመዛዘን ፡ የሚችል ፡ ጕልበት ፡ (énergie) ሊሰጠን ፡ ይችላል ። ይህም ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ የሚገኙ ፡ ሰዎች ፡ ለኑሯቸው ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አግኝተው ፡ ከዚህም ፡ በላይ ፡ አሁን ፡ አሜሪካኖች ፡ ያላቸውን ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ መነሻ ፡ በማድረግ ፡ ስድስት ፡ ጊዜ ፡ የበለጠ ፡ አድርገው ፡ የተሻለ ፡ ኑሮ ፡ ለመኖር ፡ ይችላሉ ፡ ሲል ፡ አረጋግጧል ።

ይህ ፡ አይንሽታይን ፡ የሰጠው ፡ አሳብ ፡ በሳይንስ ፡ በኩል ፡ አስደናቂ ፡ በመሆኑ ፡ ትክክለኛውን ፡ ትርጉም ፡ መንፈሳችን ፡ ሊደርስበት ፡ አይችልም ። ባጭሩ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ቍጥራቸው ፡ ሁለት ፡ ሚሊያርድ ፡ ተኩል ፡ የሚሆነው ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ድኽነትንና ፡ ችግርን ፡ ከኑሯቸው ፡ አስወግደው ፡ በጌትነትና ፡ በምቾት ፡ ሊኖሩ ፡ ይችላሉ ። ለምሳሌ ፡ በህንድ ፡ አገር ፡ ከድኽነት ፡ የተነሣ ፡ ረኃብና ፡ በሽታ ፡ በየመንገዱ ፡ ላይ ፡ የሚፈጃቸው ፡ ሕዝቦች ፡ አሁን ፡ ካሉበት ፡ ከሚያሳዝን ፡ ሁኔታ ፡ የሚድኑበት ፡ መንገድ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ይገኛል ፡ ማለት ፡ ነው ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ሳይንስም ፡ የመሬትን ፡ መልክና ፡ የሰዎችን ፡ አኗኗር ፡ ሁኔታ ፡ ፈጽሞ ፡ የሚለውጠው ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ዐላማ ፡ የፈጸመች ፡ ሆና ፡ ትገኛለች ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ማቴስ ፡ ያስተማረው ፡ ትምህርት ፡ የተሻረ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ከሳይንስ ፡ ዕውቀት ፡ የተገኘው ፡ አሳብ ፡ ለእኛ ፡ በሳይንስ ፡ ትምህርት ፡ የገፉ ፡ ዕውቀት ፡ ለሌለን ፡ ሰዎች ፡ ይገባን ፡ ዘንድ ፡ አስቸጋሪ ፡ በመሆኑ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ ከሊቃውንት ፡ የተገኘውን ፡ ተጨማሪ ፡ መግለጫ ፡ ስንገነዘበው ፡ ጕዳዩን ፡ በመጠኑ ፡ ባሳባችን ፡ ልንከተለው ፡ እንድንችል ፡ ይረዳናል ። ማንኛውንም ፡ በድን ፡ ወይም ፡ ግዙፍ ፡ አካል ፡ (matière) እንውሰድ ። ለምሳሌ ፤ እንደ ፡ ከሰል ፡ መርፌ ፡ ሲጋራ ፡

ይህን ፡ የመሰለው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ (ማቲየር) ፡ ይባላል ። እንግዲህ ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ነገር ፡ ክብደቱ ፡ ግማሽ ፡ ግራም ፡ የሚሆን ፡ ወስደን ፡ ብና ቃጥለው ፡ በነደደ ፡ ጊዜ ፡ ብርሃንና ፡ ሙቀት ፡ ይሰጠናል ። ይህም ፡ ኅል በት ፡ (énergie) ይባላል ። ያንኑ ፡ ግማሽ ፡ ግራም ፡ የሆነ ፡ ከሰል ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ በማንደድ ፡ ፈንታ ፡ እንዳልነበር ፡ ብናደርገው ፡ ወደ ፡ ኅል በት ፡ (énergie) ሲለወጥ ፡ በመሞቅና ፡ በመንደድ ፡ አምስት ፡ ሚሊያ ርድ ፡ ጊዜ ፡ የበለጠ ፡ ኅልበት ፡ ይሰጣል ። ይኸውም ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ መንገድ ፡ ሲተረጐም ፡ አንዲት ፡ የዐተር ፡ ፍሬ ፡ በምታኽል ፡ ከሰል ፡ ብቻ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ መርከብ ፡ ካውሮፓ ፡ ተነሥቶ ፡ አሜሪካ ፡ አገር ፡ ደርሶ ፡ ሊመለስ ፡ ይችላል ፡ ማለት ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ ሰው ፡ በሳይንስ ፡ በኩል ነገ ፡ እንደርስበታለን ፡ ብሎ ፡ የሚጠብቀው ፡ ታላቅ ፡ ተስፋ ፡ ይህ ፡ ነው ። ይህ ፡ አሳብ ፡ የተፈጸመ ፡ ዕለት ፡ ሰዎች ፡ ሳይደክሙና ፡ ሳይሠሩ ፡ በደ ስታና ፡ በሲሳይ ፡ ከሚኖሩበት ፡ ጊዜ ፡ ላይ ፡ ይደርሳሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ በ ዚያ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ችግር ፡ ይፈጠራል ። ይኸውም ፡ ሰዎች ፡ እሁን ፡ ጊዜያቸውን ፡ የሚያሳልፉት ፡ ለኑሯቸው ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፡ ነገር ፡ ለ ማግኘት ፡ በመሥራትና ፡ በመድከም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ የሲሳይ ፡ ዘመን ፡ የመጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጊዜያቸውን ፡ በምን ፡ ሊያሳልፉ ፡ ነው?

የአቶም ፡ ኀይል ፡ በሰላማዊ ፡ ሥራ ፡ ሙሉ ፡ አገልግሎቱን ፡ እንዲ ሰጥ ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ የድንጋይ ፡ ከሰልና ፡ ቤንዚን ፡ አስፈላጊነታ ቸው ፡ ይቀራል ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ብርሃንና ፡ ሙቀት ፡ ከአቶም ፡ ኀይል ፡ ይገኛሉ ። ኢንዱስትሪዎችንም ፡ የሚያስኬዳቸው ፡ እሱ ፡ ይሆናል ። በባ ሕር ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ወርቅ ፣ ብርና ፡ ፕላቲን ፡ በብዙ ፡ ለማግኘት ፡ ስ ለሚቻል ፡ እነዚህ ፡ ማዕድኖች ፡ ዝገት ፡ ስለማይነካቸውና ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በብዙ ፡ የሚገኙ ፡ በመሆናቸው ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ለሚቀበረው ፡ ለውሃ ፡ ቦምባና ፡ ለውሃ ፡ ማጠራቀሚያ ፡ በርሚል ፡ መሥሪያ ፡ ሆነው ፡ ያገለ ግላሉ ። በአቶም ፡ ኀይል ፡ እየተሳበ ፡ ብዙ ፡ ውሃ ፡ ለማውጣትና ፡ ለማግ ኘት ፡ ስለሚቻል ፡ ዛሬ ፡ በረሐ ፡ የሆኑት ፡ አገሮች ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በቂ ፡ ውሃ ፡ አግኝተው ፡ ይለማሉ ።

• በአቶም ፡ ኀይል ፡ የሚሄዱት ፡ አኤሮፕላኖች ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ለም ሳሌ ፣ ካዲስ ፡ አበባ ፡ በ፮ ፡ ሰዓት ፡ ተነሥተው ፡ በ፮ ፡ ሰዓት ፡ ሎንዶን ፡ ይገ ባሉ ። ዛሬ ፡ ረዥም ፡ ጕዞ ፡ የሚወስደው ፡ ሰዓት ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጨርሶ ፡ ይደመሰሳል ፡ ማለት ፡ ነው ። (ካንድ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ መሄድ ፡ በ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ ካንድ ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ክፍል ፡ እንደ ፡ መተላ ለፍ ፡ ያኽል ፣ ይቈጠራል ፡ ማለት ፡ ነው) ። የካንሰርንም ፡ በሽታ ፡ በቀ ላሉ ፡ ለማዳን ፡ ይቻላል ። ይህንን ፡ መግለጫ ፡ የሰጠ ፡ ዶክተር ፡ አርቱር ፡



ኮምፕተን ፡ (Dr. Arthur Compton) የሚባለው ፡ የኖቤል ፡ ሽልማት ፡ ያገኘ ፡ አሜሪካዊ ፡ የሆነ ፡ የአቶም ፡ ሊቅ ፡ ነው ።

አሁን ፡ ደግሞ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ እንመልከት ። መሬት ፡ በአየር ፡ ላይ ፡ ተንሳፋ ፡ የቆመች ፡ ኳስ ፡ (globe) መሆኗን ፡ እናውቃ ለን ። ይህ ፡ ያለችበት ፡ አቀማመጥ ፡ በምን ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ እን ደሚገኝ ፡ ጥቂት ፡ እናስተውል ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰማይና ፡ መሬት ፡ ያልፋሉ ፡ ቃሌ ፡ ግን ፡ አያልፍም ፡ ብሎ ፡ በመናገር ፡ የዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ እንደሚሆን ፡ አስጠንቅቆናል ። እንግዲህ ፡ ዓለም ፡ በምን ፡ ዐይ ነት ፡ አኳኋን ፡ ልታልፍ ፡ እንደምትችል ፡ የሳይንስ ፡ ሊቃውንት ፡ የሚ ናገሩትን ፡ እንስማ ።

የዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ በብዙ ፡ ዐይነት ፡ አኳኋን ፡ ሊደርስ ፡ እንደሚችል ፡ የሳይንስ ፡ ሊቃውንት ፡ ይናገራሉ ። ይኸውም ፡ ቀጥሎ ፡ እንደ ፡ ተመለ ከተው ፡ ነው ።

ጨረቃ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ እየተጠጋች ፡ መሄዷ ፡ የተረጋገጠ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ወድቃ ፡ ልታጠፋት ፡ ትችላለች ።

ሁለተኛ ፡ ጨረቃ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ በጣም ፡ በተጠጋች ፡ ጊዜ ፡ ራሷ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ መውደቋ ፡ ቀርቶ ፡ የውቅያኖስን ፡ ውሃ ፡ ከፍ ፡ አድርጋ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አንሥታ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ተገልብጦ ፡ እንዲፈስ ፡ በማድረግ ፡ በኖኅ ፡ ጊዜ ፡ ከሆነው ፡ ይበልጥ ፡ በጣም ፡ የከፋ ፡ የውሃ ፡ ጥፋት ፡ ልታ መጣ ፡ ትችላለች ።

ሦስተኛ ፡ በመሬት ፡ አቅራቢያ ፡ በአየር ፡ ላይ ፡ የሚዘዋወሩ ፡ አምሳ ፡ ሺ ፡ የሚሆኑ ፡ ድንጋዮችና ፡ ታላላቅ ፡ አለቶች ፡ መኖራቸው ፡ ታውቋል ። እነሱም ፡ የመጡት ፡ በፀሐይ ፡ አቅራቢያ ፡ የነበረች ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ፀሐይ ፡ በፈነዳች ፡ ጊዜ ፡ የተበታተኑ ፡ ናቸው ፡ ይባላል ። እነዚህ ፡ ጥቃቅን ፡ የሆኑ ፡ ፕላኔቶች ፡ ባንድ ፡ ሰኰንድ ፡ ስድሳ ፡ ስድስት ፡ ኪሎሜትር ፡ ይሄዳሉ ። ከእነሱም ፡ መካከል ፡ አምስት ፡ ሺሕ ፡ የሚሆኑት ፡ በከዋክብት ፡ መመር መሪያ ፡ መነጥር ፡ (በቴሌስኮፕ) ፡ የሚታዩ ፡ ናቸው ። አንዳንዶቹም ፡ በትልቅነታቸው ፡ በጣም ፡ የታወቁ ፡ ከመሆናቸው ፡ የተነሣ ፡ ሴሬስ ፣ ፓላስ ፣ ቬስታ ፣ ዡኖን ፣ ሲባሉ ፡ ከእነሱ ፡ የሚያንሱት ፡ ደግሞ ፡ አሞር ፣ አፖሎ ፣ አዶኒስ ፣ ሔርሜስ ፣ ይባላሉ ። የጐናቸው ፡ ስፋት ፡ (ዲያሜትር) ፡ ከሰባት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ዐሥር ፡ ኪሎሜትር ፡ ከዚ ህም ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ሔርሜስ ፣ የተባለችው ፡ በቅርብ ፡ ዘመን ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ አውሮፓ ፡ ዘመን ፡ አቈጣጠር ፡ ባ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡

እስከ ፡ 800.000 ፡ ኪሎሜትር ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ተጠግታ ፡ መሬትን ፡ ለመንካት ፡ የሩብ ፡ ሰዓት ፡ ጕዞ ፡ ቀርቷት ፡ ነበር ።

እንግዲህ ፡ ከነዚህ ፡ አምሳ ፡ ሺሕ ፡ ከሚሆኑት ፡ ጥቃቅን ፡ ፕላኔቶች ፡ አንዷ ፡ መሬትን ፡ ብትገጫት ፡ የዓለም ፡ ጥፋት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

አራተኛ ፡ ፀሐይ ፡ እየቀዘቀዘች ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ስለምትገኝ ፡ ብርሃንና ፡ ሙቀትን ፡ ጨርሳ ፡ ለመስጠት ፡ የማትችልበት ፡ ጊዜ ፡ ደርሶ ፡ በቀዘቀዘች ፡ ጊዜ ፡ መሬትን ፡ በረዶ ፡ ያለብሳትና ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ፍጡሮች ፡ በብርድ ፡ ያልቃሉ ።

አምስተኛ ፡ ፀሐይ ፡ እየቀዘቀዘች ፡ መሄዷ ፡ ቀርቶ ፡ እየጋለች ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ትገኛለች ። ስለዚህ ፡ ሙቀቷ ፡ በጣም ፡ ሲግል ፡ መሬትን ፡ እንደ ፡ ሠም ፡ የምታቀልጥበት ፡ ጊዜ ፡ ይደርሳል ፡ ሲሉ ፡ አፍራሽ ፡ የሆነ ፡ አሳብ ፡ (ቴዎሪ) ፡ የሚያቀርቡ ፡ ሊቃውንት ፡ አሉ ። ስለዚህ ፡ መሬት ፡ ከፍ ፡ ብለው ፡ ከተዘረዘሩት ፡ ምክንያቶች ፡ ባንደኛው ፡ ዐይነት ፡ አደጋ ፡ ልትጠፋ ፡ እንደምትችል ፡ በሊቃውንት ፡ ዘንድ ፡ ይገመታል ። በዚህ ፡ ላይ ፡ የአቶም ፡ ቦምብና ፡ የሃይድሮጂን ፡ ቦምብ ፡ መኖራቸውን ፡ ጨምረን ፡ ማሰብ ፡ አለብን ።

በዚህ ፡ ረገድ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ለማወቅ ፡ ስንፈልግ ፡ ለምሳሌ ፤ ያኽል ፡ (Les Grands Bouleversements terrestres) «በመሬት ፡ ላይ ፡ የደረሱ ፡ ታላላቅ ፡ መገለባበጦች» ፡ የተባለውን ፡ ከ(Immanuel Velikovsky) ኢማኑኤል ፡ ቤሊኮብስኪ ፡ የተጻፈውን ፡ መጽሐፍ ፡ ማንበብ ፡ ያስፈልጋል ። ይህ ፡ ሊቅ ፡ በጻፈው ፡ መጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ የተናገረውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሊቃውንት ፡ በሙሉ ፡ ባይቀበሉትም ፡ እኛም ፡ እሱ ፡ የተናገረው ፡ ሁሉ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ማለታችን ፡ ሳይሆን ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ሊደርሱ ፡ የሚችሉትን ፡ ከሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ሊመጡ ፡ የሚችሉትንም ፡ አደጋዎች ፡ ስለሚገልጥልን ፡ ሆኗል ፡ ለማለት ፡ ሳይሆን ፡ ሊሆን ፡ የሚችለውን ፡ ለማወቅ ፡ ያኽል ፡ ይረዳናል ።

(Photo - synthèse radioactive) የተባለው ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ የጠቀስነው ፡ ጥበብ ፡ (chlorophyle) ተብላ ፡ ከምትጠራው ፡ አስደናቂ ፡ ከሆነችው ፡ ነገር ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ ነው ። እሷም ፡ በዕፀዋት ፡ ሕይወት ፡ ውስጥ ፡ የፀሐይን ፡ ብርሃን ፡ እየተቀበለች ፡ ትልቅ ፡ ተግባር ፡ የምትፈጽም ፡ የሥነ ፡ ፍጥረት ፡ መሣሪያ ፡ ነች ።

የኦቶማቲስም ፡ ጥበብ ፡ ደግሞ ፡ በበኩሉ ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ እንደ ፡ ተመለከትነው ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ ባንጐሉ ፡ የሚሠራቸውን ፡ አድካሚ ፡ የሆኑ ፡



ሥራዎች ፡ እንዲቃለሉለት ፡ የሚረዳው ፡ ጥበብ ፡ ነው ። ይህ ፡ ጥበብ ፡ በጣም ፡ እየተሻሻለ ፡ ሄዶ ፡ እድገት ፡ ከማግኘቱ ፡ የተነሣ ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ አንድ ፡ የጥበብ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ ተቈጠረ ፡ (cybernétique) ሲቤርኔቲክ ፡ የተባለ ፡ መታወቂያ ፡ ስም ፡ በሳይንስ ፡ መደብ ፡ ተሰጥቶታል ።

ያሁኑ ፡ ዘመን ፡ ሳይንስ ፡ ለኮከብ ፡ መርማሪዎች ፡ ሊቃውንት ፡ በጣም ፡ ኀይለኞች ፡ የሆኑ ፡ መሣሪያዎች ፡ እየሠራች ፡ ስላቀረበችላቸው ፡ እኒህ ፡ ሊቃውንት ፡ ስለ ፡ ፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ ሁኔታ ፡ ጕዳይ ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ አስደናቂ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ሊገልጡልን ፡ ችለዋል ። ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ ዋኖች ፡ ነገሮች ፡ የሆኑትን ፡ እንዘረዝራቸዋለን ።

ከዋክብት ፡ እንዴት ፡ እንደሚፈጠሩ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ መጋጨት ፡ ሲደርስባቸው ፡ የሚሆነው ፡ ነገር ፡ (supernova) ና ፡ ነጭ ፡ ድንክዮች) ፡ ስለሚባሉት ፡ ከዋክብት ፡ ምስጢር ፡ ሊቃውንት ፡ የሚሰጡት ፡ ሐተታ ፡ (Lemaître) የተባለው ፡ ሊቅ ፡ ፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ እየተለጠጠ ፡ እየሰፋ ፡ የሚሄድ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ የገለጠው ፡ አሳብ ፡ ከሥር ፡ ከመሠረት ፡ የነበረው ፡ አንድ ፡ አቶም ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሱም ፡ ሙቀት ፡ አንድ ፡ ሺ ፡ ሚሊያርድ ፡ ዲግሬ ፡ ነበር ፡ የሚባለው ፡ አሳብ ፡ ዓለም ፡ የተቀመመው ፡ በዘጠና ፡ ሁለት ፡ (ዛሬ ፡ ግን ፡ ከመቶ ፡ ሦስት ፡ ደርሷል)፤ ነባር ፡ አካሎች ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ሲሆን ፡ ዕድሜው ፡ ከ፳ና ፡ ከ፤ ፡ ሚሊያርድ ፡ ዓመታት ፡ አይበልጥም ፡ የሚባለው ፡ ትምህርት ፡ በብዙ ፡ ሚሊያርድ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ጋላክሲዮች ፡ ባለማቋረጥ ፡ የሚያደርጉት ፡ ፈጣን ፡ ግሥገሣ ፡ ከእነሱም ፡ መካከል ፡ አንዳንዶቹ ፡ የሚያስፈራ ፡ ሆኖ ፡ ለመንፈስ ፡ በሚቀርበው ፡ በብርሃን ፡ ፍጥነት ፡ ልክ ፡ ማለት ፡ ባንድ ፡ ሰዓት ፡ ካንድ ፡ ሚሊያርድ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ የበለጠ ፡ ይነጕዳሉ ፡ ተብሎ ፡ የሚታመነው ፡ እንሆ ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ነገሮች ፡ መንፈስን ፡ የሚያፈዙና ፡ የቅኔን ፡ ስሜት ፡ በሰው ፡ ልብ ፡ የሚያሳድሩ ፡ በመሆናቸው ፡ ማንኛውም ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ፡ የሚጽፍ ፡ ያሳብ ፡ ባለጸጋ ፡ የሆነ ፡ ደራሲ ፡ ሊፈጥረው ፡ ከሚችል ፡ የበለጠ ፡ አስደናቂ ፡ ሆነው ፡ ይቈጠራሉ ።

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የከዋክብት ፡ ዕውቀት ፡ (አስትሮኖሚ) ፡ ያቶም ፡ ኀይል ፡ ፎቶሴንቴዝና ፡ ሲቤርኔቲክ ፡ እነዚህ ፡ አራቱ ፡ ነገሮች ፡ በዛሬው ፡ ዘመናዊ ፡ ሳይንስ ፡ ውስጥ ፡ ትንግርት ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ ፈጽመው ፡ የተገኙ ፡ የሳይንስ ፡ መሠረታዊ ፡ ነገሮች ፡ ሆነው ፡ ተገምተዋል ።

ከዚህ ፡ በቀር ፡ ደግሞ ፡ ሊቃውንት ፡ ያቀዱት ፡ አንድ ፡ አስደናቂ ፡ ነገር ፡ አለ ። ይኸውም ፡ በቢዮሎጊ ፡ ክፍል ፡ "génes" ተብለው ፡ በሚ

ጠሩት ፡ አማካይነት ፡ የሰውን ፡ ሁኔታና ፡ ጠባይ ፡ በሥጋም ፡ ሆነ ፡ በመንፈስ ፡ ረገድ ፡ እያሻሻልን ፡ ሥነ ፡ ፍጥረቱን ፡ ለማቃናት ፡ እንችላለን ፡ ሲሉ ፡ የገለጡት ፡ አሳብ ፡ ነው ።

አሁን ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ በሰው ፡ ልጅ ፡ ጠባይና ፡ በጥበብ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ሁኔታ ፡ እናስተውል ። ማንኛውም ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ በተፈጥሮ ፡ መንፈሱ ፡ በምንም ፡ ነገር ፡ ራሱን ፡ ከማንም ፡ በታች ፡ አድርጎ ፡ አይመለከትም ። አንድ ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ ያኽል ፡ ደኻ ፡ ምንም ፡ ያኽል ፡ ደካማ ፡ ምንም ፡ ያኽል ፡ ደንቄሮ ፡ ቢሆን ፡ ራሱን ፡ በጣም ፡ ባለጸጋ ፤ በጣም ፡ ጐበዝና ፡ በጣም ፡ ብልኅ ፡ አድርጎ ፡ ይቈጥረዋል ። ይህ ፡ አብሮን ፡ የሚወለድ ፡ ሰብአዊ ፡ ዥራት ፡ የሚባል ፡ የተፈጥሮ ፡ ባሕርያችን ፡ ነው ። ሰው ፡ ድኻ ፡ መሆኑ ፡ ቢሰማው ፡ እንኳ ፡ የሱን ፡ ገንዘብ ፡ ማጣት ፡ ገንዘብ ፡ ካላቸው ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ አመዛዝኖ ፡ የሱ ፡ ድኻ ፡ መሆን ፡ የተሻለ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኝበትን ፡ ነገር ፡ ፈጥሮ ፡ ያካክሰዋል ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ይህ ፡ አስተያየቱ ፡ እውነት ፡ ሆኖ ፡ ሊገኝ ፡ ይችላል ። እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ እንዲኖር ፡ የሚያደርገው ፡ እንሆ ፡ ይህ ፡ ስሕተተኛ ፡ እምነት ፡ መሆኑን ፡ ኢብሰን ፡ (Ibsen) የተባለው ፡ ደራሲ ፡ ሲያሳስበን ፡ ይህንኑ ፡ ስሕተት ፡ «ሕይወታዊ ፡ ውሸት» ፡ (mensonge vital) ብሎ ፡ ሰይሞታል ። እንግዲህ ፡ ሰው ፡ ይህንን ፡ ስሕተተኛ ፡ ውሸት ፡ የገፈፉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወዮለት ። እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በዕውቀቱ ፤ በመልኩ ፤ በጕብዝናው ፡ ራሱን ፡ ከሌሎቹ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ አድርጎ ፡ የሚቈጥርበት ፡ ውስጣዊ ፡ ስሜት ፡ በልቡ ፡ አድሮበት ፡ ይገኛል ። ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ በመዛናት ፡ እንዲናገር ፤ ትዳሩን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እያደረገ ፡ ለመሄድ ፡ እንዲፍጨረጨር ፤ በመንፈሱ ፡ ውስጥ ፡ ተደሳችነት ፡ እንዲኖር ፡ የሚፈቅድለት ፡ ይህ ፡ ውስጣዊ ፡ ስሜት ፡ ነው ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የተሸፈነ ፡ ሆኖ ፡ ሲኖር ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታውና ፡ በንግግሩ ፡ እየፈነዳ ፡ የሚገለጥበት ፡ ሰዓት ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ።

በያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ መንፈስ ፡ ውስጥ ፡ ኢብሰን ፡ «ሕይወታዊ ፡ ውሸት» ፡ ብሎ ፡ የሚጠራው ፡ የሞራል ፡ ቪታሚን ፡ ሆኖ ፡ ሊቈጠር ፡ የሚገባው ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ራሱን ፡ በሁሉም ፡ ነገር ፡ ከቀሩት ፡ ሰዎች ፡ በላይ ፡ አድርጎ ፡ እንዲመለከት ፡ የሚያደርግለት ፡ ውስጣዊ ፡ ስሜት ፡ ባይኖር ፡ ኖሮ ፡ ሰው ፡ በቀሩት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ እየታገለ ፡ ለመኖር ፡ በቂ ፡ የመንፈስ ፡ ጕልበት ፡ አያገኝም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ስሜት ፡ በግማሾቹ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ልኩ ፡ (ዶዙ) ፡ መጠነኛ ፡ ሲሆን ፡ በግማሾቹ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ በጣም ፡ የገነነ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ይህ ፡ ሁኔታ ፡ ባንዳንድ ፡ በኩል ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ክብሩን ፡ ጠብቆ ፡ እንዲኖር ፡ በማድረግ ፡ የሚረዳ ፡ ሲሆን ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ግን ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ዐቅሙን ፡ ዐውቆ ፡ እንዲኖር ፡ በማድረግ ፡ ፈንታ ፡ ዐጕል ፡ ትምክሕት ፡ እየፈጠረ ፡ ሥርዐት ፡ እንዲጠፋ ፤ ደንብ ፡ እንዳይጠበቅ ፤ ሕግና ፡ ዲስፕሊን ፡ እንዳይከበሩ ፡ እያደረገ ፡ በሰዎች ፡ መካከል ፡ ለሚፈጠረው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁከት ፡ ምንጭ ፡ ይሆናል ። ስለዚህ ፡ ጥቅሙንና ፡ ጕዳቱን ፡ ስናመዝነው ፡ ጐጂነቱ ፡ የበለጠ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ።



ዴሞክራሲ ፡ ይህ ፡ ዐጕል ፡ እምነት ፡ በሰዎች ፡ ዘንድ ፡ እየገነነ ፡ እንዲሄድ ፡ ለማድረግ ፡ በጣም ፡ የሚረዳ ፡ መሆኑን ፡ ልንዘነጋው ፡ አይገባም ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ደረጃውን ፡ እንዳያውቅና ፡ መከባበርም ፡ እንዳይኖር ፡ በማድረግ ፡ ሊጐዳ ፡ ይችላል ። አድለርና ፡ ኦርቴጋ ፡ ኢ ፡ ጋሴ ፡ እነዚህ ፡ ሊቃውንት ፡ ይህንን ፡ ጕዳይ ፡ በሰፊው ፡ ጥናት ፡ አድርገውበት ፡ አትተውታል ። ጥሩ ፡ ፕሮግራም ፡ ተከትሎ ፡ የሚሄድ ፡ ትምህርት ፡ ሰውን ፡ ከዚህ ፡ ስሕተት ፡ ሊመልሰው ፡ ይችላል ፡ ብለን ፡ እናምናለን ። በመጥፎ ፡ አካሄድ ፡ የሚመራ ፡ ትምህርት ፡ ደግሞ ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ የባሰ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ።

ባለፈው ፡ አርእስት ፡ እንደ ፡ ተመለከትነው ፡ ኤመርሰን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ፕላቶን ፡ ፈላስፋ ፡ እንደ ፡ ቄሳር ፡ ጀግና ፤ እንደ ፡ ሼክስፒር ፡ ባለቅኔ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ጽፏል ። ይህም ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ሙያ ፡ ሳይኖረው ፡ አይቀርም ፡ ማለት ፡ መሆኑን ፡ ተናግረናል ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ኢብሰን ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ መሠረት ፡ በሌለው ፡ እምነት ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ሕይወታዊ ፡ ውሸት ፡ እየተመገበ ፡ ራሱን ፡ ሲያታልል ፡ ይኖራል ። እንግዲህ ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ በራሱ ፡ እንዲተማመን ፡ ኤመርሰን ፡ ሲፈቅድለት ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ኢብሰን ፡ ውሸት ፡ በሆነ ፡ ደስታ ፡ ሰው ፡ የሚታለል ፡ መሆኑን ፡ ሲያሳስበው ፡ ሰው ፡ የትኛውን ፡ ወገን ፡ መያዝ ፡ ይሻለዋል ? በእነዚህ ፡ በሁለቱ ፡ ነገሮች ፡ መካከል ፡ ሚዛን ፡ የሚሆነውን ፡ መካከለኛ ፡ ሁኔታ ፡ ፈልጎ ፡ መያዝ ፡ የሚገባ ፡ መሆኑ ፡ ግልጥ ፡ ነው ። ይህም ፡ ምኞትን ፡ ጨርሶ ፡ ሳይገድሉና ፡ ዐጕል ፡ ትዕቢት ፡ በልብ ፡ ሳያሳድሩ ፡ መኖርና ፡ መሥራት ፡ ያስፈልጋል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ይልቁንም ፡ አሁን ፡ ዴሞክራሲ ፡ የተባለውን ፡ መንፈስ ፡ ምዕራባውያን ፡ ሕዝቦች ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ስለ ፡ ነዙት ፡ ዘመናዊውን ፡ ሥልጣኔ ፡ በመቀበል ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ ባዛዥና ፡ በታዛዥ ፤ በበላይና ፡ በበታች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ እያቃወሰው ፡ የሕዝቡን ፡ ጠባይ ፡ ስላበላሸው ፡ ትልቅ ፡ ችግር ፡ ፈጥሯል ። ስለዚህ ፡ ጕዳይ ፡ ፓኒካር ፡ (Panikkar) የተባለው ፡ የህንድ ፡ ደራሲ ፡ የጻፈውን ፡ መጽሐፍ ፡

መመልከት ፡ ይጠቅማል ። ዲሲፕሊን ፡ በሌለበት ፡ አገር ፡ ሕዝቡ ፡ ካደጋ ፡ ላይ ፡ ይወድቃል ። ዲሲፕሊንን ፡ የሚያከብሩ ፡ ሕዝቦች ፡ ግን ፡ ኀይለኞችና ፡ ሀብታሞች ፡ ናቸው ። ለዚሁም ፡ እንግሊዝ ፤ ጀርመንና ፡ ጃፓን ፡ አብነት ፡ ሆነው ፡ ሊጠቀሱ ፡ ይቻላል ።

ሰው ፡ በተፈጥሮ ፡ ጠባዩ ፡ እንዲህ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የትምህርት ፡ ነገር ፡ ይመጣል ። ትምህርት ፡ ማለት ፡ በተፈጥሮ ፡ አእምሯችን ፡ ከምናውቀው ፡ የበለጠ ፡ ተጨማሪ ፡ ዕውቀት ፡ የሚሰጠን ፡ የአስተዋይነት ፡ ችሎታ ፡ ማግኘት ፡ ማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ጥንቱን ፡ በመሠረቱ ፡ የሰዎች ፡ የተፈጥሮ ፡ ዕውቀት ፡ በመጠነኛ ፡ ዕውቀትና ፡ በከፍተኛ ፡ ዕውቀት ፡ ይለያል ። ይህም ፡ አብዛኞቹ ፡ ሰዎች ፡ የተፈጥሮ ፡ ብልኅነታቸው ፡ መጠነኛ ፡ (normal) ሲሆን ፡ አንዳንዶቹ ፡ ግን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ብልኅነት ፡ ተሰጥቷቸው ፡ ይፈጠራሉ ። አሁን ፡ እነዚህን ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ ለየብቻ ፡ ለይተን ፡ እንመልከታቸው ። መጠነኛ ፡ ዕውቀት ፡ የግሉ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ አደጋ ፡ አለው ። በዓለም ፡ ላይ ፡ ለሚገኙት ፡ ክፉ ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ ምንጩ ፡ ዐጕል ፡ ትዕቢት ፡ መሆኑን ፡ ሞንቴኝ ፡ የሚባለው ፡ ፈላስፋ ፡ ይነግረናል ። ሰዎች ፡ ትምህርት ፡ ሲማሩ ፡ ሁሉን ፡ ነገር ፡ ያውቁ ፡ ይመስላቸዋል ። ስለዚህ ፡ ቀድሞ ፡ የተሠራውን ፡ መንቀፍ ፤ መናቅ ፤ ማኩሰስ ፡ ያመጣሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ሲያደርጉ ፡ የነበረውን ፡ ለውጠው ፤ አፍርሰው ፤ በጥብጠው ፡ የሚፈጽሙት ፡ ማሻሻል ፡ ቀድሞ ፡ ከነበረው ፡ የተሻለ ፡ ለመሆኑ ፡ ምንም ፡ ማስረጃ ፡ የላቸውም ። ይህን ፡ የመሰለ ፡ ዐጕል ፡ ትዕቢት ፡ ካደረባቸው ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መኖር ፡ ለመካድ ፡ የሚነሡ ፡ እንደሚገኙባቸው ፡ ሞንቴኝ ፡ ጨምሮ ፡ ይነግረናል ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ አንድ ፡ ሊቅ ፡ ያስተማረውን ፡ ሌላው ፡ ሊቅ ፡ ሲነቅፈው ፡ ሲገለብጠው ፡ ይኖራል ። በጠቅላላው ፡ ለዓለም ፡ መቅሠፍት ፡ ሆኖ ፡ የሚገኘውን ፡ ሥራ ፡ ሰዎችን ፡ የሚያሠራቸው ፡ ይህ ፡ ትዕቢት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በሽታ ፡ የሚድኑበትን ፡ ነገር ፡ መፈለግ ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ሞንቴኝ ፡ ያስጠነቅቃል ።

ብዙ ፡ ጕዳት ፡ የሚያስከትል ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ትዕቢት ፡ የሚወለደው ፡ አጭር ፡ ከሆነ ፡ ትምህርት ፡ ነው ። እየጨመረና ፡ እየቀጠለ ፡ የማይሄድ ፡ ትምህርት ፡ ሁሉ ፡ እየተቀነሰ ፡ ያድራል ። ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ አደጋ ፡ ለመዳን ፡ ሲል ፡ ስለ ፡ ዕውቀቱ ፡ ተጣጣሪ ፡ መሆንና ፡ ያለ ፡ ማቋረጥ ፡ በዕውቀት ፡ እያደገ ፡ ለመሄድ ፡ ሲል ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ጥበብን ፡ መከታተል ፡ ይገባዋል ። በጣም ፡ ለጥበብ ፡ መትጋት ፡ እየቀዘቀዘ ፡ ሲሄድ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ዐውቃለሁ ፡ የሚያሰኝ ፡ ጠባብ ፡ የሆነ ፡ መንፈስ ፡ በሰው ፡ ውስጥ ፡ እያደረ ፡ ይጠነክራል ።



አሁን ፡ ደግሞ ፡ የዚያኛውን ፡ ሰው ፡ ሁኔታ ፡ እንመልከተው ። በህንዶች ፡ ፍልስፍና ፡ መሠረት ፡ በተፈጥሯቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ብልኅነት ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተመላልሰው ፡ የተፈጠሩ ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ ያምናሉ ። እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ በጣም ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። እነሱም ፡ ልዩ ፡ በሆነው ፡ በተፈጥሮ ፡ ዕውቀታቸው ፡ ላይ ፡ ትምህርት ፡ ሲጨምሩበት ፡ ዕውቀታቸው ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ የላቀና ፡ የጠለቀ ፡ የገነነም ፡ ይሆናል ።

ለዚህ ፡ ጕዳይ ፡ አንድ ፡ ምሳሌ ፡ እንፈልግለት ። በባላገር ፡ የሚኖር ፡ መልኩ ፡ የተኰሳቈለ ፡ ልብሱ ፡ የቈሸሸ ፤ ከተማ ፡ ገብቶ ፡ የማያውቅ ፤ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በገጠር ፡ የሚቀመጥ ፡ አንድ ፡ ገበሬ ፡ እንዳጋጣሚ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ይገባል ። በመደብር ፡ ውስጥ ፡ ረዥም ፡ መስተዋት ፡ ያገኝና ፡ ሰውነቱን ፡ ከእግር ፡ እስከ ፡ ራሱ ፡ ይመለከታል ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የመልኩና ፡ የልብሱ ፡ ሁኔታ ፡ ወለል ፡ ብሎ ፡ ይገለጥለታል ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የመልኩን ፡ አለማማርና ፡ የልብሱን ፡ ማደፍ ፡ በከተማ ፡ ከሚኖሩት ፡ መልካቸውና ፡ ልብሳቸው ፡ የጠዳ ፡ ሆኖ ፡ ከሚገኘው ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ካስተያየና ፡ ካመዛዘነ ፡ በኋላ ፡ ሰውነቱን ፡ ይንቃል ፤ በሁኔታው ፡ ያፍራል ፤ ሕይወቱንም ፡ ይጠላል ።

ያም ፡ በተፈጥሮ ፡ ልዩ ፡ ብልኅነት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ ትምህርት ፡ ሲጨምርበት ፡ የሚደርስበት ፡ ነገር ፡ ይህንኑ ፡ የመሰለ ፡ ነው ። ትምህርት ፡ ተምሮና ፡ ዕውቀት ፡ የሚገኝባቸውን ፡ ታላላቅ ፡ መጻሕፍት ፡ አንብቦ ፡ ሲጨርስ ፡ በሥጋና ፡ በነፍስ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ሥነ ፡ ፍጥረቱን ፡ በቢዮሎጊ ፡ በፍልስፍናና ፡ በአስትሮኖሚ ፡ መስተዋት ፡ ሲመለከተው ፡ ወለል ፡ ብሎ ፡ ይታየዋል ። ሰው ፡ በነፍስና ፡ በሥጋው ፡ የታረመ ፡ ፍጹምነት ፡ ያለው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያለ ፡ ጥሩ ፡ ሕይወት ፡ ለመኖር ፡ ይችል ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ያስባል ። ይህንንም ፡ አሳብ ፡ ሊፈጸም ፡ የሚችል ፡ አድርጎ ፡ ይቈጥረዋል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፍጹማን ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ሊኖሩባት ፡ የሚገባውን ፡ ከተማ ፡ በመንፈሱ ፡ ውስጥ ፡ ፈጥሮ ፡ እንደ ፡ ራእይ ፤ እንደ ፡ ሲኒማ ፡ ይመለከታታል ። በዚህ ፡ እሱ ፡ በፈጠራትና ፡ በሚንጓላት ፡ የመንፈስ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩትን ፡ ፍጹማን ፡ የሆኑትን ፡ ሰዎች ፡ ባይኑ ፡ ከሚያያቸው ፡ አብረውት ፡ ከሚኖሩት ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ እያስተያየ ፡ በመካከላቸው ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ሲያመዛዝነው ፡ ሐዘን ፡ ይሰማዋል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዓለምንም ፡ ራሱንም ፡ የሚያየውንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይንቃል ፤ ይጠላል ።

በነ ፡ ፕላቶን ፤ በነ ፡ ካንት ፤ በነ ፡ ሾፐንሃወር ፤ በነ ፡ ኒች ፤ በነ ፡ ጓንዲ ፤ እነሱንም ፡ በመሰሉት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የደረሰባቸው ፡ ነገር ፡ እንሆ ፡ ይህ ፡ ነው ። ጋንዲ ፡ የተማረው ፡ ትምህርት ፡ አልጌብር ፤ ዥሜትሪ ፤ ዥግራፊ ፤ አስ

ትሮኖሚ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ለምንም ፡ አልጠቀመኝም ፤ የተማሩ ፡ ሰዎችም ፡
ካልተማሩት ፡ በምንም ፡ ነገር ፡ አይሻሉም ፡ ያለው ፡ ለዚህ ፡ ነው ። በሱ ፡
መንፈስ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩትን ፡ የመሰሉ ፡ ሰዎች
በዙሪያው ፡ አላገኘም ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ትምህርት ፡ ይልቁንም ፡ ሜታ
ፊዝክና ፡ ሎዢክ ፡ (ፍልስፍና) ፡ ለሰው ፡ አይጠቅምም ፤ ምክንያቱም ፡
ትምህርት ፡ የሚፈለገው ፡ ደስታን ፡ ለማግኘት ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ይህ ፡ መሆኑ ፡
ቀርቶ ፡ ሰው ፡ በተማረ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ዕውቀቱ ፡ አጭር ፡ በመሆኑ ፡ ዐ
ጕል ፡ ትዕቢት ፡ ያድርበትና ፡ ያልተማሩትን ፡ ሰዎች ፡ (እሱ ፡ ከእነሱ ፡
ምንም ፡ የማይሻል ፡ ሆኖ ፡ ሳለ) ፡ ይንቃቸዋል ። ወይም ፡ ደግሞ ፡ እንደነ ፡
ጋንዲ ፡ በጣም ፡ ብልኅ ፡ በመሆን ፡ ዓለምንና ፡ ራሱንም ፡ ከመጥላትና ፡
ከመናቅ ፡ ይደርሳል ። ይህም ፡ ትምህርት ፡ ሰውን ፡ በሁለቱም ፡ በኩል ፡ ይጐዳ
ዋል ፡ እንጂ ፡ አይጠቅመውም ፡ ማለት ፡ ነው ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የሥልጣኔ ፡
ትርጉም ፡ እንደ ፡ ላስቲክ ፡ እየተሳበ ፡ እሱ ፡ ሲሸሽን ፡ እኛም ፡ ስንከተ
ለው ፡ እየገሠገሠ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይዞን ፡ የሄደ ፡ መስሎን ፡ ነበር ። አሁን ፡
ግን ፡ ብንመለከተው ፡ እንደ ፡ መቀነት ፡ እየዞረ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ወስዶን ፡
ኖሮ ፡ ተመልሰን ፡ እዚያ ፡ እነበርንበት ፡ ቦታ ፡ ማለት ፡ የፍጡር ፡ መነሻ ፡
ከሆነው ፡ ድንቊርና ፡ ከሚባለው ፡ ትርጉም ፡ ላይ ፡ አድርሶን ፡ አገኘነው ።
ይህም ፡ ዕውቀትና ፡ ድንቊርና ፡ ዞረው ፡ ዞረው ፡ ይገናኛሉ ፡ ይገጥማሉ ፡
ማለት ፡ ነው ። ሰው ፡ ከዕድሜው ፡ ግማሹን ፡ ክፍል ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡
ግማሹን ፡ ደግሞ ፡ መጻሕፍትና ፡ ዕውቀት ፡ በመመርመር ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡
እንደ ፡ ጋንዲ ፡ የተማረውን ፡ ሁሉ ፡ ነቅፎ ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡ አላገኘሁበ
ትም ፡ ብሎ ፡ በግልጥ ፡ እያረጋገጠ ፡ ከተናገረ ፡ እንግዲህ ፡ በመማርና ፡
ባለመማር ፡ በጥበብና ፡ በድንቊርና ፡ መካከል ፡ ምንም ፡ ልዩነት ፡ የለም ፡
ማለት ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ የዕውቀትና ፡ የድንቊርና ፡ ትርጉም ፡ ዞሮ ፡ በመ
ግጠም ፡ ተቀላቅሎ ፡ መገኘቱን ፡ መሰከረ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህ ፡ ሁሉ ፡
ምን ፡ ያሳየናል ? ቃል ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፤ ወሰንና ፡ ድንበር ፡ ጠረ
ፍና ፡ መጨረሻ ፡ የሌለው ፡ የሰው ፡ አሳብ ፡ ለማንኛውም ፡ ነገር ፡ ሚዛኑ ፡
እሱ ፡ ስለሆነ ፡ እሱ ፡ የሚሰጠን ፡ ዋስትና ፡ የማያስተማምን ፡ መሆኑን ፡
ያስረዳናል ። እሱም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ የሰጠው ፡ ልዩ ፡ ጸጋ ፡
ስለ ፡ ሆነ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምስጢር ፡ እንደማንደርስበት ፡ ሁሉ ፡ አሳ
ብንም ፡ ልንጨብጠው ፡ አንችልም ። እንደ ፡ ተጨማሪ ፡ አድርገን ፡ አሁ
ንም ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ልናስተውለው ፡ ይገባል ።

ለምሳሌ ፤ ከአሜሪካ ፡ አገር ፡ ሄደን ፡ ከኒውዮርክ ፡ ከተማ ፡ ስንገባ ፡
የሕንጻዎቹን ፡ ግዙፍነት ፤ ሕዝቡም ፡ የተማረ ፡ ሆኖ ፡ ባኗኗሩ ፡ ያለውን ፡
ምቾትና ፡ ተድላ ፡ ስናስተውል ፡ እንደነቃለን ። ባፍሪቃ ፡ ወይም ፡ በእስያ ፤



ወይም ፡ ባንዳንድ ፡ ደሴት ፡ የሚኖሩ ፡ ሕዝቦች ፡ በትንንሽ ፡ ጐጆች ፡
ውስጥ ፡ ተቀምጠው ፡ ራቍታቸውን ፡ ሲሄዱ ፡ አይተን ፡ እንዴት ፡ ባለ ፡
የመከራና ፡ የጣር ፡ ኑሮ ፡ እየኖሩ ፡ ዕድሜያቸውን ፡ እንደሚገፉ ፡ ተረድ
ተን ፡ የእነዚህን ፡ ኑሮ ፡ ከአሜሪካ ፡ ሕዝብ ፡ ኑሮ ፡ ጋራ ፡ ስናስተያየው ፡
በጣም ፡ የሚያስደንቅ ፡ ልዩነት ፡ እናገኝበታለን ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡
ልዩነት ፡ እነዚህን ፡ መላእክት ፤ እነዚያን ፡ እንስሳት ፡ ብለን ፡ ከመጥራት ፡
አያደርሰንም ። ይህ ፡ የድኽነት ፡ ኑሮ ፡ ከዚያ ፡ ከተድላ ፡ ኑሮ ፡ የሚሻል
በት ፡ ነገር ፡ ይኖራል ። ብዙ ፡ ሊቃውንት ፡ ያንን ፡ የተድላና ፡ የሥልጣኔ ፡
ኑሮ ፡ እየጠሉ ፡ ከእነዚያ ፡ ያልሠለጠኑ ፡ ደንቈሮች ፡ ተብለው ፡ ከሚጠ
ሩት ፡ ሕዝቦች ፡ ጋራ ፡ መኖር ፡ ሺሕ ፡ ጊዜ ፡ የተሻለና ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ጋራ ፡ ይበልጥ ፡ የሚያቀራርብ ፡ ሆኖ ፡ አግኝተውታል ። እንዲህ ፡ ሆኖ ፡
ሲገኝ ፡ ሥልጣኔ ፡ ያለችው ፡ ከወዴት ፡ ነች? በኒውዮርክ ፡ ከተማ ፡ ወይስ ፡
በዚያ ፡ ጐጆ ፡ ቀልሶ ፡ ራቍቱን ፡ በሚሄደው ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ? ብዙ ፡ ሊቃ
ውንት ፡ ይህን ፡ ምርጫ ፡ የሚያደርጉት ፡ ሠለጠኑ ፡ በተባሉት ፡ ሰዎች ፡
ዘንድ ፡ ያለውን ፡ የጠባይ ፡ መበላሸት ፡ በማየትና ፡ በእነዚህ ፡ በድኽነት ፡
በሚኖሩት ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ በጣም ፡ የተሻለ ፡ የደግነትና ፡ የገርነት ፡
ባሕርይ ፡ ለማግኘት ፡ ስለሚችሉ ፡ ነው ። የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ምንም ፡
እንኳ ፡ በቋንቋና ፡ በባህል ፡ በሃይማኖትና ፡ በዘር ፡ የተለያዩ ፡ ቢሆኑ ፡ ዞሮ ፡
ዞሮ ፡ ካንድ ፡ ምንጭ ፡ የተቀዱ ፡ መሆናቸውን ፡ የሚገልጽልን ፡ በብዙ ፡
ነገር ፡ ተመሳሳይነት ፡ ይዘው ፡ የሚገኙ ፡ በመሆናቸው ፡ ነው ። ባልሠለጠ
ኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ የሚገኝ ፡ እንደ ፡ ጥንቈላ ፤ ለጣዖታት ፡ ሰውን ፡
ጭዳ ፡ አርዶ ፡ መሥዋዕት ፡ ማቅረብ ፤ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ከድንቊር
ናና ፡ ካረመኔ ፡ እምነት ፡ የመጣውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ልማድ ፡ ስንመለከተው ፡
በሠለጠኑትና ፡ ባልሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ትልቅ ፡ ልዩነት ፡ እና
ገኛለን ። ለምሳሌ ፤ ሰውነታቸውን ፡ ጭቃ ፡ ወይም ፡ አደመድ ፡ የሚቀቡ ፤
እንደ ፡ መግላሊት ፡ ባለ ፡ ነገር ፡ ከንፈራቸውን ፡ የሚወጥሩ ፤ እንደዚ
ሁም ፡ በህንድ ፡ አገር ፡ የላሞችን ፡ እበትና ፡ ሽንት ፡ እንደ ፡ እመትና ፡
እንደ ፡ ጠበል ፡ ቈጥረው ፡ ሰውነታቸውን ፡ የሚቀቡ ፡ ሕዝቦች ፡ አሉ ።
ይህ ፡ ሁሉ ፡ ድንቊርናን ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ። አንዳንዶቹ ፡ ሕዝቦች ፡ ደግሞ ፡
ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ነውረኛ ፡ ልማድ ፡ አልፈውት ፡ ባህላቸውንና ፡ ልማ
ዳቸውን ፡ አርመው ፡ በመንፈሳቸው ፡ ክፍ ፡ ካለ ፡ ደረጃ ፡ ደርሰዋል ።
በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ስንመለከተው ፡ ጠባያቸውና ፡ ባህላቸው ፡ እንደ
ዚህ ፡ የታረመ ፡ ሆኖ ፡ የምናያቸው ፡ ሕዝቦች ፡ ባልሠለጠኑበት ፡ ዘመን ፡
ይህንኑ ፡ የመሰለ ፡ የሚያሳፍር ፡ ገመና ፡ በባሕርያቸውና ፡ በልማዳቸው ፡
ውስጥ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በታሪክ ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ። ስለዚህ ፡ የግማሾቹ ፡
በሥልጣኔ ፡ መገሥገሥና ፡ የሌሎቹም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ዘግይቶ ፡ መቅረት ፡

ያሁኑን ፡ ልዩነት ፡ ፈጥሮ ፡ ከመታየቱ ፡ በቀር ፡ የሰዎች ፡ ታሪክ ፡ በሚያስደንቅ ፡ አኳኋን ፡ ተመሳሳይነት ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ አይካድም ። ይህ ፡ በባህልና ፡ በጠባይ ፡ በኩል ፡ የሚደረግ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በአካላቸው ፡ ሥነ ፡ ፍጥረትም ፡ በኩል ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። በጥቍሮች ፤ በብጫዎችና ፡ በነጮች ፡ መካከል ፡ በቀለም ፤ በመልክ ፡ ቅርጽ ፤ በደም ፡ ግባትና ፡ ባቋቋም ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ሁኔታ ፡ ስናስተያየው ፡ በዝርዝር ፡ ነገር ፡ የተለያዩ ፡ በጠቅላላ ፡ ሥነ ፡ ፍጥረታቸው ፡ ግን ፡ ባንድ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ የተቋቋሙ ፡ ናቸው ። ካንድ ፡ እናት ፡ ሆድ ፡ የወጡና ፡ ካንድ ፡ አባት ፡ የተገኙ ፡ ብዙ ፡ ልጆች ፡ ግማሾቹ ፡ ቀይ ፤ ግማሾቹ ፡ ጠይም ፤ ግማሾቹ ፡ ጥቍር ፤ ግማሾቹ ፡ ረዥም ፤ ግማሾቹ ፡ አጭር ፡ ሆነው ፡ ልዩነት ፡ ሲያሳዩ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ በገጥታም ፡ ሆነ ፡ በደም ፡ ግባት ፡ ካንድ ፡ ዘር ፡ የወጡ ፡ መሆናቸውን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ተመሳሳይነት ፡ ያላቸው ፡ ሆነው ፡ እንደሚታዩ ፡ ሁሉ ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦችም ፡ እንደዚሁ ፡ በዝርዝር ፡ ነገር ፡ በባህልና ፡ በሥልጣኔ ፡ በመልክና ፡ ባቋቋም ፡ በሚያስደንቅ ፡ አኳኋን ፡ የተለያዩ ፡ ሆነው ፡ ሲገኙ ፡ በጠቅላላ ፡ ሁኔታቸው ፡ ግን ፡ ማለት ፡ በሥነ ፡ ፍጥረታቸው ፡ በሚያስገርም ፡ አኳኋን ፡ ተመሳሳዮች ፡ ሆነው ፡ እናገኛቸዋለን ። በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ በኩል ፡ ያሉ ፡ እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ተቃራኒ ፡ ነገሮች ፡ ማለት ፡ ልዩነትና ፡ ተመሳሳይነት ፡ በሰው ፡ ፍጥረት ፡ ውስጥ ፡ ተዋሕደው ፡ የሚገኙበትን ፡ ምስጢር ፡ መፍቻውን ፡ በእጁ ፡ የያዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

ናፖሌዎን ፡ ቅድስት ፡ እሌኒ ፡ በምትባለው ፡ ደሴት ፡ ላይ ፡ በእስረኛነት ፡ ሲኖር ፡ የአሲያኒ ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ ቶቢ ፡ የሚባል ፡ ጥቍር ፡ ባሪያ ፡ በዚች ፡ ደሴት ፡ ላይ ፡ ይኖር ፡ ነበር ። ይህ ፡ ባሪያ ፡ ከቤተ ፡ ሰቦቹና ፡ ከቤተ ፡ ዘመዶቹ ፡ ተለያይቶ ፡ በዚች ፡ ደሴት ፡ ላይ ፡ ወገኑ ፡ የሆነ ፡ ምንም ፡ ሰው ፡ ስላልነበረው ፡ ናፖሌዎን ፡ በጣም ፡ ያዝንለትና ፡ ይረዳውም ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ቀን ፡ በቶቢ ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ በማዘን ፡ እየተመለከተው ፡ ናፖሌዎን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ተናገረ ።

«ለመሆኑ ፡ ሰው ፡ የሚሉት ፡ ይህ ፡ ምስኪን ፡ መኪና ፡ የሚያስገርም ፡ ነው ። መሸፈኛው ፡ አንዱ ፡ ከሌላው ፡ ጋራ ፡ አይመሳሰልም ። ውስጡ ፡ አንዱ ፡ ከሌላው ፡ ጋራ ፡ በምንም ፡ አይለያይም ። ብዙ ፡ ስሕተት ፡ ሲሠራ ፡ የሚኖረው ፡ ይህን ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ሰዎች ፡ ሳይቀበሉ ፡ ከመቅረታቸው ፡ የተነሣ ፡ ነው» ።

ሰው ፡ በሜታፊዚክ ፤ በአስትሮኖሚ ፡ በቢዮሎዢ ፡ በኩል ፡ ከፊቱ ፡ የሚቀርቡትን ፡ ጥያቄዎች ፡ መርምሮ ፡ መልሱን ፡ ለማግኘት ፡ ሲሞክር ፡ የሰው ፡ ዕውቀት ፡ ሊደርስባቸው ፡ የማይችል ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ ያገኛል ።



ሰው ፡ መጀመሪያ ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ማነው ? ዕውቀቱን ፡ በምን ፡ ላይ ፡ መሥርቶ ፡ ነው ፡ ለነዚህ ፡ ጥያቄዎች ፡ የሚሆነውን ፡ መልስ ፡ ሊፈልግና ፡ ሊያገኝ ፡ የሚችለው ? ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ለቀረቡት ፡ ጥያቄዎች ፡ መልሱን ፡ ሊሰጥ ፡ የቻለ ፡ ሊቅ ፡ ወይም ፡ ፈላስፋ ፡ አልተገኘም ። በማቴሪያሊስም ፡ በኩል ፡ (በግዙፍ ፡ አካሎች) ፡ የሰው ፡ ጥበብ ፡ በጣም ፡ ዘልቃለች ፡ ለማለት ፡ እንችላለን ። በሜታፊዚክ ፡ በኩል ፡ ግን ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ እሱ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ የተደረገው ፡ እርምጃ ፡ አጥጋቢ ፡ አይደለም ። ምክንያቱም ፡ በፈጣሪና ፡ በፍጡር ፤ በዚህ ፡ ዓለምና ፡ በወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ መካከል ፡ የተዘረጋውን ፡ መጋረጃ ፡ ሊገልጠው ፡ የሚችል ፡ ባለመኖሩ ፡ ነው ። የሰውን ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ በሳይንስና ፡ በፍልስፍና ፡ አስተያየት ፡ የተመለከትነው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዕውቀታችን ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ስንት ፡ ነገር ፡ አለ ። እያሌ ፡ ሕፃናት ፡ በየቀኑ ፡ ሲወለዱ ፡ ሌሎች ፡ ብዙ ፡ ሕፃናት ፡ ደግሞ ፡ ይሞታሉ ፤ ለምን ፡ ተወለዱና ፡ ለምንስ ፡ ይሞታሉ ? እንደዚሁም ፡ በብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሕዝቦች ፡ በዚህች ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ይወለዳሉ ። ከተወለዱት ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ ሳይቀር ፡ ሁሉም ፡ እየሞቱ ፡ ሌሎች ፡ ይተካሉ ። አላፊና ፡ መጭ ፡ የሆኑት ፡ ትውልዶች ፡ ባለማቋረጥ ፡ ይፈራረቃሉ ። እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ምንም ፡ መታሰቢያ ፡ የለውም ። አንድ ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ ሲሞት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ አይቈጠርም ። ምክንያቱም ፡ ምንም ፡ የማያጐድል ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። በሱ ፡ ቦታ ፡ እሱን ፡ የመሰሉ ፡ በሚሊዮን ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ እየተወለዱ ፡ ይተካሉ ። ይህ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ የማያጐድል ፡ የሆነው ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ በላኋ ፡ በወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ ለምን ፡ ይጠቅማል? እሱን ፡ የመሰሉ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ምንም ፡ ሥራ ፡ ሳይፈጽሙ ፡ በከንቱ ፡ እየተወለዱ ፡ የሚሞቱት ፡ በብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ የሚቈጠሩት ፡ ሰዎች ፡ መፈጠራቸው ፡ ለምን ፡ ያገለግላል ? በወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ የሚሰጣቸው ፡ ተግባር ፡ ምን ፡ ይሆን ? አንድ ፡ ሰው ፡ ደግሞ ፡ በሳይንስ ፡ ወይም ፡ በፍልስፍና ፡ ወይም ፡ በቴክኒክ ፡ ዕውቀት ፡ ለዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ታላቅ ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጥ ፡ ጥበብ ፡ ይፈጥራል ። ይህንንም ፡ ለመፈጸም ፡ ዕድሜውን ፡ ሙሉ ፡ በድካምና ፡ በድኽነት ፡ ፈጅቶ ፡ ይሞታል ። እሱ ፡ በፈለሰፈው ፡ ጥበብ ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ በሙሉ ፡ ይጠቀሙበታል ። ይህ ፡ ሰው ፡ ዋጋውን ፡ ከማን ፡ ያገኛል ? ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ለስሙ ፡ መታሰቢያ ፡ ከሚሠሩለት ፡ እንደ ፡ ሐውልት ፡ ከመሰሉት ፡ ነገሮች ፡ የሚገኘው ፡ ደስታ ፡ በወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ ለሱ ፡ ይሰማዋልን ? ወይስ ፡ ደግሞ ፡ ድካሙ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ይቀራል? ልናውቃቸው ፡ የማንችል ፡ እነዚህን ፡ የመሰሉ ፡ ስንት ፡ ነገሮች ፡ አሉ ። ይህንን ፡ በሳይንስ ፡ ወይም ፡ በፍልስፍና ፡ መርምረን ፡ ልንደርስበት ፡ እንችላለን ፡ ወይ ? የሰው ፡ ልጅ ፡ እስካሁን ፡ ከታየው ፡ የበ

ለጠ ፡ ጥበብ ፡ አግኝቶ ፡ በአየር ፡ ላይ ፡ እየበረረ ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ ከዋክብትና ፡ ፕላኔቶች ፡ መካከል ፡ እየተዘዋወረ ፡ ቢሄድ ፤ ምንም ፡ ያኽል ፡ ከሳይንስና ፡ ከቴክኒክ ፡ የሚያገኘው ፡ ሀብትና ፡ ጕልበት ፡ የላቀ ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝ ፤ በቀሩትም ፡ ዕውቀቶች ፡ ሁሉ ፡ እንደዚሁ ፡ የሚያስደንቅ ፡ እርምጃ ፡ ቢያደርግ ፤ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ዞሮ ፡ ዞሮ ፡ ባፈር ፡ የተሠራ ፡ ፍጡር ፡ መሆኑን ፡ ሊለውጠው ፡ አይችልም ። መጨነቅ ፤ መታመምና ፡ መሞት ፡ ዘለዓለም ፡ ከሥነ ፡ ፍጥረቱ ፡ ጋራ ፡ ተቈራኝተው ፡ በደረሰበት ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ይከታተሉታል ። ሰው ፡ በብረት ፤ በክቡር ፡ ድንጋይ ፡ ጠንካራ ፡ በሆኑ ፡ ማዕድኖች ፡ በብዙ ፡ ሺሕ ፡ የሚቈጠር ፡ ዘመን ፡ የሚኖሩ ፡ መሣሪያዎች ፡ ሊሠራ ፡ ይችላል ። የራሱን ፡ አካል ፡ ግን ፡ ለውጦ ፡ እንደ ፡ አልማዝ ፡ በጠነከረ ፡ አሠራር ፡ ሊያሻሽለው ፡ ከቶ ፡ መብት ፡ አላገኘም ። የእሱን ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ያዘጋጀው ፡ ሠሪ ፡ ፈጣሪ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ሥነ ፡ ፍጥረቱን ፡ ሊለውጠው ፡ እንደማይችል ፡ አድርጎ ፡ ሠርቶታልና ። እንደዚሁም ፡ ማንኛውንም ፡ ጥበብ ፡ ቢሠራ ፡ ደስታ ፡ ሊያገኝ ፡ የሚችለው ፡ ከመንፈሱ ፡ ሁኔታ ፡ እንጂ ፡ ከበድን ፡ አካል ፡ አይዶለም ። የመንፈሱ ፡ ሁኔታ ፡ የማይመረመር ፡ ረቂቅ ፡ ምስጢር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ መፍቻውና ፡ ቊልፉ ፡ የሚገኘው ፡ በፈጣሪ ፡ እጅ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

የቢዖሎግር ፡ ሊቃውንት ፡ ሰውን ፡ ሞት ፡ እንዳይነካው ፡ ለማድረግ ፡ ቢችሉ ፡ እንኳ ፡ ይህ ፡ የሚያገኙት ፡ የሥራ ፡ ውጤት ፡ ለምንም ፡ የማይጠቅም ፡ መሆኑን ፡ መዘንጋት ፡ አይገባም ። ከፍ ፡ ብለን ፡ በዝርዝር ፡ እንደ ፡ ተመለከትነው ፡ ሁሉ ፡ ለምሳሌ ፤ በገጸ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ መዓት ፡ የሚቈጠሩ ፡ የመገለባበጥ ፡ አደጋዎች ፡ ቢደርሱ ፡ የአቶም ፡ ወይም ፡ የሂድሮዤን ፡ ቦምቦች ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ ተወርውረው ፡ ቢፈነዱ ፡ ወይም ፡ የኛ ፡ ፕላኔት ፡ ከሌሎች ፡ የሰማይ ፡ አካሎች ፡ ጋራ ፡ ተጋጭታ ፡ ብትበታተን ፡ ብትፈርስ ፡ ሰው ፡ ባካሉ ፡ በኩል ፡ ሞት ፡ የማይነካው ፡ ለማድረግ ፡ ቢቻልም ፡ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ይህንን ፡ ጥበብ ፡ ፍሬ ፡ የማይሰጥ ፡ ከንቱ ፡ ሊያደርጉት ፡ ይችላሉ ። የኮስሞስን ፡ ሁኔታ ፡ ስናስተውለው ፡ የሰው ፡ ደካማነት ፡ መድኀኒት ፡ የሌለው ፡ ነገር ፡ ነው ። በውሃ ፡ ጥፋት ፡ ዘመን ፡ ለነበሩ ፡ ተውጠው ፡ ለቀሩ ፡ በፖምፔኢ ፡ የተነሣው ፡ እሳት ፡ ገሞራ ፡ መሬት ፡ ቀብሮ ፡ ላስቀራቸው ፡ በሂሮሺማ ፡ የወደቀው ፡ የአቶም ፡ ቦምብ ፡ ብን ፡ አድርጎ ፡ ላጠፋቸው ፡ ሰዎች ፡ ሞት ፡ የማይነካቸው ፡ መሆን ፡ ተሰጥቷቸው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ለምን ፡ ሊጠቅማቸው ፡ ይችል ፡ ኖሯል ?

እዚህ ፡ ላይ ፡ መመልከት ፡ የሚኖርብን ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አለ ። ይኸውም ፡ ኩትልቁ ፡ ሊቅ ፡ ከአይንሽታይን ፡ ተገኘ ፡ ተብሎ ፡ ሌሎች ፡ ሊቃውንት ፡ የተረጐሙልን ፡ (le non - vieillissement) «አለማርጀት» ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመው ፡ አሳብ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ እንደዚህ ፡ ነው ። ትልቁ ፡ ሊቅ ፡ አይንሽታይን ፡ (meson) የተባለችው ፡ ነባር ፡ ፍጡር ፡ ያላትን ፡ ጠባይ ፡ በመመልከት ፡ ሰው ፡ በብርሃን ፡ ፍጥነት ፡ መጠን ፡ የሚገሠግሥ ፡ መሣሪያ ፡ ሠርቶ ፡ በሱ ፡ ለመጓዝ ፡ ቢችል ፡ ማርጀት ፡ አይደርስበትም ፡ ተብሎ ፡ የሚታሰበው ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ለማወቅ ፡ ሲፈለግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ ያሻዋል ፤ ሊቃውንት ፡ ይህን ፡ አሳብ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ አድርገው ፡ ለማሳየት ፡ ይችሉ ፡ ዘንድ ፡ በሳይንቲፊክም ፡ ሆነ ፡ በቴክኒክ ፡ በኩል ፡ ብዙ ፡ ሐተታ ፡ ያለበት ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ።



በሳይንስና ፡ በቴክኒክ ፡ ባደረገችው ፡ እርምጃ ፡ በሀብቷ ፡ ስፋትና ፡ በሰበሰበችው ፡ የገንዘብ ፡ ብዛት ፡ ዛሬ ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ የሚያደንቋትና ፡ የሚቀኑባት ፡ አሜሪካ ፡ መሆኗን ፡ እናውቃለን ። ከማቴሪያል ስም ፡ ሥልጣኔ ፡ እውነተኛ ፡ ክብርና ፡ አድናቆት ፡ ደስታም ፡ የሚገኝ ፡ ከሆነ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ከሷ ፡ ጋራ ፡ ሊወዳደር ፡ የሚችል ፡ ሌላ ፡ ሕዝብ ፡ እንደሌለ ፡ ማንም ፡ አይስተውም ። እንኳንስ ፡ የገዛ ፡ ዜጎቿ ፡ ይቅሩና ፡ ወዳጆቿ ፡ እንኳ ፡ ይመኩባታል ። ነገር ፡ ግን ፡ በውስጧ ፡ ያለውን ፡ ሁኔታ ፡ ጠልቀን ፡ ለማወቅ ፡ ስንፈልግ ፡ በቤቷ ፡ ውስጥ ፡ ደስታ ፡ የሚገኝ ፡ ሆኖ ፡ አይታይም ። ዜጎቿ ፡ ከሆኑት ፡ አንዱ ፡ ስሙ ፡ በጣም ፡ የታወቀው ፡ ዎልት ፡ ዊትማን ፡ (Walt Whitman) የተባለው ፡ ባለቅኔ ፡ የጻፈውን ፡ ቃል ፡ ለዚህ ፡ አርእስት ፡ መደምደምያ ፡ አድርገን ፡ ጠቅሰነዋል ።

«የተባበሩት ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥታት ፡ ሕዝብ ፡ መንፈሱ ፡ ምስኪን ፤ ባለጌ ፤ በሁሉ ፡ ነገር ፡ የሚያምንና ፡ የበሰበሰ ፡ ነው ።.........መቼም ፡ ቢሆን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ታይቶ ፡ የማይታወቅ ፡ የነፍስ ፡ ደረቅነት ፡ ዛሬ ፡ እዚህ ፡ በተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ መንግሥታት ፡ ዘንድ ፡ ይገኛል ። መሠረት ፡ ያለው ፡ እምነት ፡ ሁሉ ፡ ከኛ ፡ ዘንድ ፡ የተወገደ ፤ የተሰደደ ፡ ይመስላል ። ታላላቆች ፡ ከተሞች ፡ በወስላታነትና ፡ በወንበዴነት ፡ የተመረዙ ፡ ናቸው ። ንጹሕ ፡ የሆነ ፡ ልብስ ፡ የለበሱት ፡ ሰዎች ፡ በውስጣቸው ፡ የሚገኘው ፡ ቀላልነት ፤ ቀዝቃዛ ፡ የሆነ ፡ ፍቅር ፤ ጥቃቅን ፡ ክሕደቶች ፤ ምስኪን ፡ የሆኑ ፡ ወይም ፡ ጨርሰው ፡ የሌሉ ፡ ጊዜን ፡ ለማሳለፍ ፡ ብቻ ፡ የሚያገለግሉ ፡ ዐላማዎች ፡ ናቸው ። ማቴሪያሊስም ፡ በሆነ ፡ ሥልጣኔ ፡ ሕዝቡን ፡ ከጭቃ ፡ ላይ ፡ በማንሣትና ፡ በቂ ፡ ያልሆነ ፡ መሠረቱ ፡ የላላ ፡ ትምህርት ፡ በማስተማር ፡ አዲሱ ፡ የዓለም ፡ ዴሞክራሲያችን ፡ የፈጸመው ፡ መልካም ፡ ተግባር ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝ ፡ ስለ ፡ ሕዝባዊ ፡ ኑሮ ፡ ጥቅም ፡ ተሠርተዋል ፡ በሚባሉት ፡ ሥራዎች ፡ በኩል ፡ ይህ ፡ ዴሞክራሲ ፡ የደከመው ፡ ድካም ፡ በሙሉ ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ እደፍ

ራለሁ ። ኀይላችንን ፡ ወደ ፡ ገናናነት ፡ እየመራን ፡ የትልቁ ፡ እስክንድር ፡ የነበረውን ፡ ዓለም ፤ የሮማ ፡ መንግሥት ፡ ደርሶበት ፡ የነበረውን ፡ ደረጃ ፤ ጥንታዊ ፡ የነበረውንም ፡ ዓለም ፡ አልፈነው ፡ የሄድን ፡ ሆነን ፡ ለመገኘት ፡ የምናደርጋቸው ፡ ታላላቅ ፡ እርምጃዎች ፡ በከንቱ ፡ ነው ። ግዛታችን ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ከካናዳ ፤ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ከኩባ ፡ እንዲደርስ ፡ ያደረግነው ፤ ቴክሳስን ፡ ካሊፎርኒንና ፡ አላስካን ፡ ከግዛታችን ፡ ጋራ ፡ ያቀላቀልናቸው ፡ በከንቱ ፡ ነው ።

በዚህ ፡ አሁን ፡ ባለንበት ፡ ሁኔታ ፡ በጣም ፡ ግዙፍ ፡ የሆነና ፡ በዝቶ ፡ የሚታይ ፡ አካል ፡ ተሸክመን ፡ ነፍሳችን ፡ ግን ፡ በጣም ፡ የመነመነች ፡ ወይም ፡ ጨርሳ ፡ የተፋቀች ፡ ፍጡር ፡ ሆነን ፡ ተገኝተናል» ።

# ጥበብ ፡ ከየት ፡ ተገኘች ?

አንዳንድ ፡ ሊቃውንት ፡ ሰው ፡ ጥንት ፡ ዝንጀሮ ፡ ወይም ፡ ከዝንጀሮ ፡ ጋራ ፡ የሚመሳሰል ፡ እንስሳ ፡ ነበር ፤ ወደ ፡ ሰብአዊነት ፡ የተለወጠው ፡ በመሻሻል ፡ ነው ። ይህንንም ፡ እርምጃ ፡ ለማድረግ ፡ በብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ የሚቈጠር ፡ ዘመን ፡ ፈጅቶበታል ፤ እንደዚሁም ፡ ቋንቋን ፡ ለመፍጠር ፡ የቻለው ፡ በኋላ ፡ ነው ፤ ቀድሞ ፡ ግን ፡ አሳቡን ፡ ለመግለጥ ፡ ሲፈልግ ፡ እንደ ፡ እንስሳ ፡ ትርጉም ፡ የሌለው ፡ ድምፅ ፡ በማሰማት ፡ ብቻ ፡ ይወሰን ፡ ነበር ፡ ይላሉ ። ይህንኑ ፡ አሳብ ፡ ተደግፈው ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የሚገኙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆኑት ፡ የሰው ፡ ዘሮች ፡ ማለት ፡ ጥቍሮች ፤ ብጫዎች ፤ ነጮች ፡ ተብለው ፡ የሚጠሩት ፡ ሕዝቦች ፡ ካንድ ፡ አባትና ፡ ካንድ ፡ እናት ፡ የመጡ ፡ ሊሆኑ ፡ አይችሉም ፡ ይላሉ ።

ነገር ፡ ግን ፡ በሰውና ፡ በእንስሳ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ በጣም፡ የተራራቀ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ በሥነ ፡ ፍጥረታቸው ፡ ካንድ ፡ ምንጭ ፡ ሊቀዱ ፡ (ሊፈጠሩ) ፡ እንደማይችሉ ፡ ሁሉ ፡ ዋና ፡ የጥበብ ፡ መሣሪያ ፡ የሆነውም ፡ የሰው ፡ ቋንቋ ፡ በልማድ ፡ መሻሻል ፡ (በኤቮሊሲዮን) ፡ ሊመጣ ፡ ይችላል ፡ ብሎ ፡ ለማመን ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ጕዳይ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ በዝርዝር ፡ እንመለከተዋለን ።

በሰማይ ፡ ወለል ፡ (espace) ላይ ፡ ኳሶች ፡ መስለው ፡ ተበታትነው ፡ የሚገኙ ፡ በብዙ ፡ ሚሊያርድ ፡ የሚቆጠሩት ፡ ፀሐዮች ፤ ከዋክብት ፤ ፕላኔቶች ፤ ሁሉም ፡ ይንቀሳቀሳሉ ፤ ይዞዋወራሉ ፤ ይሽከረከራሉ ። ይህ ፡ የሚያደርጉት ፡ መንቀሳቀስ ፡ ኒውተን ፡ የተባለው ፡ የእንግሊዝ ፡ ሊቅ ፡ እንደ ፡ ገለጠው ፡ ሁሉ ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ጥበብ ፡ ትምህርት ፡ የመሳሳብ ፡ ሕግ ፡ (loi de l'attraction universelle) ይባላል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ይህ ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ሕግ ፡ የመንቀሳቀሳቸው ፡ ሁኔታ ፡ የሚከናወንበትን ፡ ሥራት ፡ በሳይንቲፊክ ፡ በኩል ፡ የሚያስረዳና ፡ የሚገልጥ ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝ ፡ የመጀመሪያውን ፡ ንቅናቄ ፡ የሰጣቸው ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አይነግረንም ። ስለዚህ ፡ እነዚህን ፡ የሰማይ ፡ አካላት ፡ መጀመሪያ ፡ ያንቀሳቀሳቸው ፡ መንፈስ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የሚገኘው ፡ የዕውቀትና ፡ የጥበብ ፡ ንቅናቄ ፡ እንዲወለድ ፡ ያደረገ ፡ እሱ ፡ መሆኑ ፡

ግልጥ ፡ ነው ። በላይኛው ፡ ስፍራና ፡ (ሰማይ) ፡ በታችኛው ፡ ቦታ ፡ (መሬት ፡
ላይ ፡ ለሚገኙት ፡ ሕገጋት ፡ ባለቤት ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡
ነውና ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሰማይ ፡ ላለው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ምሳ
ሌውን ፡ በምድር ፡ ታገኙታላችሁ ፡ ብሎናል ። ስለዚህ ፡ ለማንኛውም ፡
ሕግ ፤ ለማንኛውም ፡ ጥበብና ፡ ለማንኛውም ፡ ዕውቀት ፡ መሠረቱ ፡ እሱ ፡
ስለ ፡ ሆነ ፡ በላይም ፡ በታችም ፡ ያሉ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ የሱ ፡ መንፈስ ፡ ምል
ክት ፡ የታተመባቸው ፡ ሆነው ፡ እናገኛቸዋለን ። ይህንኑም ፡ እንደ ፡ ጉዳዩ ፡
ዐይነት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በሥጋዊ ፡ ዐይን ፡ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ በአእምሮ ፡
ዐይን ፡ ተመልክተን ፡ ልናየው ፡ የምንችለው ፡ ሆነን ፡ ስንገኝ ፡ ለመመራመ
ርና ፡ ለመፈለግ ፡ ግን ፡ ከኛ ፡ በኩል ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ ሊኖር ፡ ያስፈልጋል ።

ስለዚህ ፡ የሰዎች ፡ ጥበቦችም ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ እንደ ፡ ጠቀስናቸው ፡
በሰማይ ፡ ላይ ፡ እንዳሉት ፡ ግዙፍ ፡ አካሎች ፡ በትልቅ ፡ ወለል ፡ ላይ ፡
ተቀምጠው ፡ በሚገኙ ፡ በብዙ ፡ ኳሶች ፡ ይመሰላሉ ። አንዱ ፡ ኳስ ፡ ሲንከ
ባለል ፡ ሌላውን ፡ ይነካውና ፡ እንዲንከባለል ፡ ያደርገዋል ። ያም ፡ ሌላ
ውን ፤ ሌላውም ፡ ሌላውን ፡ እየገፋ ፡ ብዙዎች ፡ ኳሶች ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡
የሚንቀሳቀሱ ፡ ሆነው ፡ እንደሚገኙ ፡ ሁሉ ፡ ሰዎችም ፡ እንደዚሁ ፡ ያን
ዱን ፡ ዕውቀት ፡ አንዱ ፡ ይቀሰቅሰዋል ። የመጀመሪያውን ፡ ኳስ ፡ እንዲን
ቀሳቀስ ፡ የሚያደርግ ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ ሆኖ ፡ እንደሚገኝ ፡ ሁሉ ፡ የመጀመ
ሪያውን ፡ ሰው ፡ በዕውቀት ፡ እንዲንቀሳቀስ ፡ ያደረገ ፡ የጥበብ ፡ ሁሉ ፡
ምንጭ ፡ የሆነው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ። ኳሶችን ፡ የሚያንቀሳቅሳቸው ፡
ሰው ፡ ወደ ፡ ዐጕል ፡ ቦታ ፡ እንዳይወድቁ ፡ እንደሚጠብቃቸው ፡ ሁሉ ፡
የሰዎች ፡ ዕውቀትም ፡ እንዳይቆምና ፡ ጨርሶ ፡ እንዳይሞት ፡ ወይም ፡ ከጥ
ፋት ፡ ላይ ፡ እንዳይወድቅ ፡ የሚጠብቀው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

ተበድሮ ፡ በልቶ ፡ ዕዳውን ፡ ሳይከፍል ፡ የሞተ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በኋሊ
ናው ፡ ላይ ፡ ሲከብደው ፡ የሚሰማው ፡ ትልቅ ፡ ጭነት ፡ ሳይወርድለት ፡
በመሄዱ ፡ የተጐዳ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ። ያለእናትና ፡ ያለአባት ፡ ተወለ
ድኩ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ቢገኝ ፡ የሚሰሙት ፡ ሰዎች ፡ መሣቂያ ፡ ያደርጉ
ታል ። እንደዚሁም ፡ የማንንም ፡ መጽሐፍ ፡ ሳላነብ ፡ ከራሴ ፡ ብቻ ፡ ያገኘ
ሁትን ፡ ነው ፡ በመጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ያስፈርኩት ፡ የሚል ፡ ደራሲ ፡ ስት
ሰሙ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ሐሰተኛ ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ዋጋ ፡
የሌለው ፡ ድርሰት ፡ መጻፉን ፡ ልትረዱት ፡ ትችላላችሁ ። የእናቱን ፡ ጡት ፡
ሳይጠባና ፡ ወተት ፡ ሳይጋት ፡ አድጎ ፡ እንጀራና ፡ ውሀ ፡ ለመመገብ ፡ የሚ
ችል ፡ ሰው ፡ እንደማይገኝ ፡ ሁሉ ፡ እንደዚሁም ፡ ሳይማርና ፡ ከሊቃው



ንት ፡ ድርሰት ፡ የሚገኘውን ፡ የጥበብ ፡ ወተት ፡ መጀመሪያ ፡ ሳይጠባ ፡
ዕውቀት ፡ ከማፍራት ፡ የሚደርስ ፡ ሊቅ ፡ ጨርሶ ፡ የለም ። ዲናሚት ፡ ጕል
በቱ ፡ እጅግ ፡ የሚያስፈራ ፡ ኀይለኛ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ እሳት ፡ ካልነካው ፡ አይ
ነሣም ፤ አይፈነዳም ። እንደዚሁም ፡ ማንም ፡ ደራሲ ፤ ማንም ፡ የሳይንስ ፡
ሊቅ ፤ ማንም ፡ ፈላስፋ ፡ ቢሆን ፡ አዲስ ፡ ዕውቀት ፡ የያዘ ፡ መጽሐፍ ፡
ሊጽፍ ፤ ወይም ፡ ጥበብ ፡ ሊፈጥር ፤ ወይም ፡ ትምህርት ፡ ሊያፈራ ፡ የሚ
ችለው ፡ በሱ ፡ አንጐል ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ዕውቀት ፡ የሚያነሣሣው ፤
የሚቀሰቅሰው ፤ እንዲፈነዳ ፡ የሚያደርገው ፡ አንድ ፡ ድርሰት ፡ ለማንበብ ፡
ዕድል ፡ ባገኘ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ ዕውቀት ፡ ያረገዘ ፡ ደራሲ ፡
ወይም ፡ የሳይንስ ፡ ሊቅ ፡ ወይም ፡ ፈላስፋ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። ምክን
ያቱም ፡ የሰው ፡ ሁሉ ፡ መንፈስ ፡ የዲናሚትነት ፡ ጠባይ ፡ ስለሌለው ፡
ነው ። እንደዚህ ፡ ሆኖ ፡ ለመገኘት ፡ ስጦታ ፡ ያሻል ። ይህንኑም ፡ የድር
ሰት ፡ ታሪክ ፡ በሚለው ፡ ምዕራፍ ፡ ተመልክተነዋል ። ታላላቆች ፡
ደራስያን ፡ ሁሉ ፡ እያንዳንዱን ፡ መጽሐፋቸውን ፡ ሲጽፉ ፡ አሳቡን ፡ ከወ
ዴት ፡ እንደፀነሱትና ፡ የማንን ፡ መጽሐፍ ፡ አንብበው ፡ መጽሐፍ ፡ ለመ
ጻፍ ፡ አሳባቸው ፡ እንደ ፡ ተነሣሣ ፡ በግልጥ ፡ ይናገራሉ ። ለምሳሌ ፤ ኒች ፡
ወደ ፡ ፈላስፋነትና ፡ ወደ ፡ ደራሲነት ፡ ተግባር ፡ ለመመራት ፡ የበቃው ፡
ሾፐንሐወር ፡ የተባለው ፡ ፈላስፋ ፡ የጻፋቸውን ፡ መጻሕፍት ፡ ባነበበ ፡
ጊዜ ፡ መሆኑን ፡ በዝርዝር ፡ ገልጦልናል ።

አንድ ፡ ደራሲ ፡ ያነበባቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ምንም ፡ ያኽል ፡ ብዙዎች ፡
ቢሆኑ ፡ ሰው ፡ ሁለት ፡ እግር ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ ከሁለት ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ አይወ
ጣም ፡ እንደሚባለው ፡ ሁሉ ፡ እሱም ፡ ደራሲ ፡ ለመሆን ፡ ሲያስብ ፡ ያከማ
ቻቸውን ፡ ዕውቀቶች ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ችቦ ፡ ሰብስቦ ፡ ባንድ ፡ አስተያየት ፡
ያስራቸዋል ። የተበታተነውን ፡ ዕውቀት ፡ ለመሰብሰብ ፡ የማይችል ፡
ሰው ፡ አሳቡ ፡ የባከነ ፡ ሆኖ ፡ ስለሚቀር ፡ ደራሲ ፡ ወይም ፡ ፈላስፋ ፡ ሊሆን ፡
አይችልም ።

አንድ ፡ ዛፍ ፡ ምንም ፡ ያኽል ፡ ቅርንጫፎቹና ፡ ክንፎቹ ፡ ቢስፋፉና ፡
ቢዘረጉ ፤ ምንም ፡ ያኽል ፡ አናቱ ፡ እንደ ፡ ክምር ፡ የተደመደመ ፡ መስሎ ፡
ቢታይ ፤ ከሥር ፡ የቆመበት ፡ ግንድ ፡ አንድ ፡ እንጂ ፡ ብዙ ፡ ሊሆን ፡ እን
ደማይችል ፡ ሁሉ ፡ ጫፉም ፡ እንደዚሁ ፡ አንድ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ከዚ
ህም ፡ የተነሣ ፡ የቀሩት ፡ ቅርንጫፎችና ፡ ክንፎች ፡ አመራራቸው ፡ ወደ ፡
ጫፉ ፡ የሚመለከት ፡ ወይም ፡ ከጫፉ ፡ ጋራ ፡ የሚነጣጠር ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ።

የደራሲ ፡ ተግባርም ፡ በዚሁ ፡ ይመሰላል ። ማንኛውም ፡ ደራሲ ፡
ቢሆን ፡ መጻሕፍት ፡ ሊጽፍ ፡ ሲጀምር ፡ እንደ ፡ ዐላማ ፡ አድርጎ ፡ የሚ
መለከተው ፡ በአንጐሉ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ አሳብ ፡ መኖር ፡ አለበት ። ነገር ፡

ግን ፡ ደራሲው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ዐላማ ፡ ለራሱም ፡ ቢሆን ፡ በትክክል ፡
ጐልቶ ፡ ሳይገለጥለት ፡ ይቀርና ፡ በውስጣዊ ፡ ኅሊና ፡ (subconscience)
እንደ ፡ ጭላንጭል ፡ ይታየዋል ። ወይም ፡ ደግሞ ፡ የሚሰማውን ፡ ዐላማ ፡
በትክክል ፡ እስቲገልጠው ፡ ድረስ ፡ ጊዜ ፡ ይፈልግበታል ። ይህም ፡ ቤር
ግሶን ፡ የሚባለው ፡ የፈረንሳይ ፡ ፈላስፋ ፡ (Schéma Dynamique) ብሎ ፡
ከሚጠራው ፡ ጋራ ፡ የሚመሳሰል ፡ ነው ። የሆነው ፡ ሆኖ ፡ አንድ ፡ ደራሲ ፡
ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ ሲጽፍ ፡ የአሳቡን ፡ ዐላማ ፡ በትክክል ፡ ገልጦ ፡ የሚ
ያሳይለት ፡ እንደ ፡ ማጠቃለያ ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠር ፡ አንድ ፡ ድርሰት ፡ መጻፍ ፡
አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ያገኘዋል ። ፈላስፋው ፡ ሶክራት ፡ እናቴ ፡ አዋላጅ ፡ ነች ፡
እኔም ፡ እንደዚሁ ፡ የመንፈስ ፡ አዋላጅ ፡ ሆኜ ፡ በሌሎች ፡ ሰዎች ፡ መን
ፈስ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ዕውቀት ፡ እንዲወለድ ፤ እንዲገለጥ ፡ ለማድረግ ፡
እሞክራለሁ ፡ እንጂ ፡ ራሴ ፡ የማውቀው ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለም ። እኔ ፡
የማውቀው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የማ
ላውቅ ፡ መሆኔን ፡ ነው ፡ ይል ፡ ነበር ።

በዚህ ፡ ንግግር ፡ ውስጥ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ትሕትና ፤ እንዴት ፡ ያለ ፡
አስተዋይነትና ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ጥልቅ ፡ ጥበብ ፡ ይገኝበታል ! ሶክራት ፡
ይህንን ፡ ሲናገር ፡ ራሱን ፡ ዝቅ ፡ ለማድረግና ፡ ትሑት ፡ ሆኖ ፡ ለመታየት ፡
አይዶለም ። ነገር ፡ ግን ፡ ለምሳሌ ፤ ማርኮኒ ፡ ራዲዮን ፡ (ማለት ፡ ሽቦ ፡ የሌ
ለውን ፡ ስልክ) ፡ እንደ ፡ ፈለሰፈ ፤ እንደ ፡ ፈጠረ ፡ ሁሉ ፡ ሶክራትም ፡ እንደ
ዚሁ ፡ ጥበብን ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፡ ያገኘው ፡ ትልቁ ፡ አዲስ ፡ ዕውቀት ፡
ይህ ፡ መሆኑን ፡ መረዳት ፡ ይገባናል ። የሰው ፡ መልክ ፡ ያንዱ ፡ ካንዱ ፡
የማይገጥም ፡ የተለያየ ፡ ሆኖ ፡ በሚገኝበት ፡ መጠን ፡ በአንጐሉ ፡ ውስጥ ፡
ያለው ፡ አሳብና ፡ ዕውቀትም ፡ እንደዚሁ ፡ የተለያየ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡
እነዚህ ፡ በያንዳንዱ ፡ ደራሲ ፤ በያንዳንዱ ፡ ፈላስፋና ፡ በያንዳንዱ ፡ ሊቅ ፡
አንጐል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ያሳብ ፡ ጫካዎች ፡ ሸፍነው ፡ የያዟቸው ፡
ዕውቀቶች ፡ ተሰውረው ፤ ተረግዘው ፤ ተቀብረው ፡ ስለሚኖሩ ፡ በርብሮ ፤
ሰርስሮ ፤ ፈልፍሎ ፤ ቀስቅሶ ፡ ገላልጦ ፡ የሚያወጣቸው ፡ የጥበብ ፡ አዋ
ላጅ ፡ (ወጌሻ) ፡ ማግኘት ፡ ያስፈልጋል ።

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ያንድ ፡ ደራሲ ፡ ተግባር ፡ ዋጋ ፡ የሚያገኘው ፡ ብዙ ፡
መጻሕፍት ፡ በማንበብና ፡ ለሚያቀርበው ፡ አሳብ ፡ ደጋፊ ፡ የሚሆኑትን ፡
የታወቁ ፡ ደራስያን ፡ በማተት ፤ በመተቸት ፤ እነሱን ፡ መሪ ፡ በማድረ
ግና ፡ ምሳሌያቸውን ፡ በመጥቀስ ፡ ነው ። በማንበብና ፡ በመመርመር ፡ ለዕ
ውቀቱ ፡ ጠንካራ ፡ መሠረት ፡ ካልሰጠው ፡ አሳቡና ፡ ተግባሩ ፡ ዋጋ ፡ ሊኖ
ረው ፡ አይችልም ። ከምንም ፡ ምንም ፡ ሊገኝ ፡ አይችልም ፡ እንደሚባ
ለው ፡ ሁሉ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እሱ ፡ በሚጽፈው ፡ ድርሰት ፡ ውስጥ ፡



የእሱ ፡ የሆነውና ፡ ከሌሎቹ ፡ የተገኘው ፡ በምን ፡ ይለያል? የሚል ፡
ጥያቄ ፡ መፈጠሩ ፡ አይቀርም ። እንደዚህ ፡ ከሆነማ ፡ ያንድ ፡ ደራሲ ፡ ተግ
ባር ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ መጻሕፍት ፡ እየሰበሰበ ፡ መጽሐፉን ፡
በመሙላት ፡ የድርሰቱን ፡ ሥራ ፡ ሊፈጽም ፡ ይችላል ፡ የሚያሰኝ ፡ ይሆ
ናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ እንዳይባል ፡ ሞንቴኝ ፡ የሚባለው ፡ ፈላስፋ ፡
በዚህ ፡ ረገድ ፡ ራሱ ፡ የተከተለውን ፡ መንገድ ፡ ሲገልጥልን ፡ አስፈላጊውን
መልስ ፡ ሰጥቶናል ። ንቦች ፡ ከዚህም ፡ ከዚያም ፡ አበቦችን ፡ ከቀሠሙ ፡
በኋላ ፡ የራሳቸው ፡ የሆነውን ፡ ማር ፡ ይሠራሉ ፡ ይለናል ። እነሱ ፡ የሠ
ሩት ፡ ማርና ፡ ካበቦቹ ፡ ቀሥመው ፡ ያመጡት ፡ ነገር ፡ የማይገናኙ ፡ ሁለት ፡
ልዩ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ። ካበቦቹ ፡ የመጣው ፡ በማሩ ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ።
ነገር ፡ ግን ፡ ማሩን ፡ የሠሩት ፡ ንቦች ፡ ናቸው ። ከእነሱ ፡ በቀር ፡ ማሩን ፡
ሊሠራው ፡ የሚችል ፡ የለም ። ሩቅ ፡ ምን ፡ ያስኬደናል ። ለምሳሌ ፤ ከየፋ
ብሪካው ፡ የሚገኙት ፡ ነገሮች ፡ ማለት ፡ ዕቃዎች ፡ ከጥጥ ፡ ወይም ፡ ከብ
ረት ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ ከመሰለው ፡ እኛ ፡ ከምናውቀው ፡ ነገር ፡ ተሠርተው ፡
ይወጣሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ዕቃውን ፡ ያማረና ፡ የተጣራ ፡ አድርጎ ፡ ለማከና
ወን ፡ ከመኪኖቹ ፡ በቀር ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ እንደማይሠራው ፡ እናውቃለን ።

ከትልቅ ፡ ሰው ፡ የተወለደ ፡ ልጅ ፡ ባባቱ ፡ ስም ፡ መጠራትን ፡ አያፍ
ርበትም ። አባቱን ፡ መስሎ ፡ ቢቻለው ፡ ለመብለጥ ፡ ባይቻለው ፡ ደግሞ ፡
ለመተካከል ፡ (እንደ ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር) ፡ ይጣጣራል ። በሥራው ፤
በሙያው ፡ ራሱን ፡ ትልቅ ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ አባቱ ፡ ትንሽ ፡ ሰው ፡
ቢሆንም ፡ አያፍርበትም ፤ የሱ ፡ ትልቅነት ፡ በጣም ፡ የላቀ ፡ ከመሆኑ ፡
የተነሣ ፡ (እንደ ፡ ናፖሊዎን) ፡ ላባቱም ፡ ተርፎ ፡ እንደሚያኰራው ፡ ያው
ቃልና ። ናፖሌዎን ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡ አባቴ ፡ ይህንን ፡ ደስታ ፡ ሳያይ ፡ በመ
ሞቱ ፡ ይቈጨኛል ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። ከትንሽ ፡ አባት ፡
የተወለደ ፡ እሱም ፡ ራሱ ፡ ትንሽ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ባባቱ ፡ ስም ፡
ለመጠራት ፡ የሚያፍር ።

በድርሰትም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። እንኳንስ ፡ ከትልቅ ፡ ድርሰት ፡ መሪ ፡
አሳብ ፡ ማግኘት ፡ ይቅርና ፡ የሚቻል ፡ ከሆነ ፡ ከትንሽ ፡ ድርሰት ፡ ው
ስጥ ፡ ባገኘው ፡ አሳብ ፡ ትልቅ ፡ ድርሰት ፡ ለመውለድ ፡ የቻለ ፡ ደራሲ ፡
ቢገኝ ፡ እንኳ ፡ ይህንኑ ፡ ገልጦ ፡ ቢናገር ፡ አያሳፍረውም ። በሳይንስና ፡
በፍልስፍና ፡ በኩል ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ የተለመደ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ለም
ሳሌ ፡ ኒውተን ፡ ማታ ፡ በጨረቃ ፡ ከመስክ ፡ ላይ ፡ ተኝቶ ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡
የበሰለ ፡ ፍሬ ፡ ሲወድቅ ፡ አይቶ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ወደ
ቀ ? በማለት ፡ ነገሩ ፡ ከነከነው ። ይህንኑ ፡ ሲመረምር ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የሚ
ገኙ ፡ አካላት ፡ ሁሉ ፡ በመካከላቸው ፡ የመሳሳብ ፡ ሕግ ፡ መኖሩን ፡ ደረሰ

በት ። ይህም ፡ በሳይንስ ፡ በኩል ፡ ኒውተን ፡ ስሙ ፡ የታወቀ ፡ ሆኖ ፡ የሚኖርበት ፡ የገለጠው ፡ ትልቅ ፡ ጥበብ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ደራስያን ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ አያፍሩበትም ። ቪርጊል ፡ ትልቁን ፡ ድርሰት ፡ «ኤኔኢዴ» ፡ የተባለው ን፡ የጻፈው ፡ የሆሜርን ፡ መንገድ ፡ ተከትሎ ፡ ነው ። ዳንቴ ፡ ደግሞ ፡ «ዲቪና ፡ ኮሜዲያን» ፡ ሲጽፍ ፡ መሪው ፤ መምህሩ ፡ ቪርጊል ፡ መሆኑን ፡ ይናገራል ። ኒች ፡ ከድርሰቶቹ ፡ አንዱ ፡ የሆነውን ፡ «ቂም» ፡ የተባለውን ፡ ለመጻፍ ፡ ያበቃው ፡ «የተቀበረ ፡ መንፈስ» ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመውን ፡ የዶስቶዬብስኪን ፡ ድርሰት ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ መሆኑን ፡ ራሱ ፡ ተናግሮታል ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ተቈጥሮ ፡ የማያልቅ ፡ ምሳሌ ፡ ለመጥቀስ ፡ እንችላለን ።

ሥራና ፡ ሠራተኛ ፤ ሙያና ፡ ባለሙያ ፤ ግብርና ፡ ገባሪ ፤ የተያያዙና ፡ የማይለያዩ ፡ ናቸው ። ያለሰው ፡ ሥራ ፡ ተፈጻሚነትን ፡ አያገኝም ። እያንዳንዱ ፡ ሥራ ፡ ባለቤት ፡ አለው ። የተናቀ ፡ ሥራ ፡ ሠራተኛውም ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ ዝቅተኛ ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፤ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ደግሞ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሠራተኛ ፡ ይኖረዋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ትልቁም ፡ ሆነ ፡ ትንሹ ፡ ሥራ ፡ ሁለቱም ፡ ከሠራተኛ ፡ የተገኙ ፡ ናቸው ። እንደዚሁም ፡ እያንዳንዱ ፡ ቤትና ፡ እያንዳንዱ ፡ ሕንጻ ፡ ባለቤት ፡ አለው ። አንድ ፡ ጥንድ ፡ ጫማ ፡ ስናገኝ ፡ ይህን ፡ ጫማ ፡ የሠራው ፡ ሰው ፡ በባለሙያነት ፤ የገዛው ፡ ሰው ፡ በባለገንዘብነት ፤ ሁለት ፡ ባለቤቶች ፡ አሉት ። ውብ ፡ የሆኑ ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ ለምሳሌ ፡ በሰሌዳ ፡ ላይ ፡ የተሠራ ፡ ሥዕል ፤ በመጽሐፍ ፡ የቀረበ ፡ ድርሰት ፤ ሌሎችም ፡ የሥነ ፡ ጥበባት ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ በባለሙያነት ፡ የሠራቸው ፡ ሰው ፡ አለ ። ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ ሥራዎች ፡ ሠራተኛው ፡ በባለሙያነቱ ፡ የሚታወቅበትን ፡ የስጦታ ፡ ምልክት ፡ ይዘው ፡ የሚገኙ ፡ በመሆናቸው ፡ በዚሁ ፡ ብቻ ፡ የሠሪውን ፡ ስም ፡ የሚናገሩ ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ። ራምብራንድ ፡ ወይም ፡ ዲክ ፡ የሠሯቸውን ፡ ሥዕሎች ፡ በማየት ፡ ብቻ ፡ ባለመሳሳት ፡ ሠራተኛውን ፡ ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ ይቻላል ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሥራ ፡ ባለቤቱን ፡ የሚያሳውቅ ፡ ሲሆን ፤ ባለቤት ፡ የሆነውም ፡ ስለ ፡ ፈጸማቸው ፡ ሥራዎች ፡ በያንዱንዱ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የባለቤትነቱን ፡ መብት ፡ ጠያቂ ፡ ነው ። አንድ ፡ ሠዓሊ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ደራሲ ፡ ሥራውን ፡ ሸጦ ፡ የድካሙን ፡ ዋጋ ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ እንኳ ፡ የባለገንዘብነቱ ፡ መብት ፡ ይቀርበታል ፡ እንጂ ፡ በባለሙያነት ፡ ለስሙ ፡ መጠሪያ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ መቼም ፡ ቢሆን ፡ አይነጠቅም ። የገዛውም ፡ ሰው ፡ የባለገንዘብነትን ፡ መብት ፡ ብቻ ፡ ይይዛል ፡ እንጂ ፡ የባለሙያነትን ፡ መብት ፡ ከሠሪው ፡ ላይ ፡ ፍቆ ፡ ለራሱ ፡ ሊያደርገው ፡ አይችልም ።



ይህም ፡ በሕግ ፡ የተደነገገና ፡ የታወጀ ፡ ሆኖ ፡ ይኖራል ። ሰዎች ፡ የግል ፡ መብታቸውን ፡ ለመጠበቅ ፡ ይኸን ፡ ያኽል ፡ ጠንካሮች ፡ ሆነው ፡ ሲታዩ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የፈጣሪነቱን ፡ መብት ፡ ሊያውቁለት ፡ አይፈልጉም ፡ ማለት ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ሥራና ፡ ሠራተኛ ፤ ሙያና ፡ ባለሙያ ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ የተያያዙና ፡ አንዱ ፡ ያለሌላው ፡ ለመገኘትና ፡ ለመኖር ፡ የማይችል ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፤ ይህ ፡ ዓለም ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ጕድለት ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ ቢታየን ፡ ሠሪ ፤ ፈጣሪ ፤ ባለቤት ፡ ሳይኖረው ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ተሠርቶ ፡ ሊገኝ ፡ ቻለ? ስለዚህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መኖር ፡ የሚክዱና ፡ የሚጠራጠሩ ፡ ሰዎች ፡ አሳባቸው ፡ የተሳሳተ ፡ መሆኑን ፡ በዚህ ፡ ብቻ ፡ ልንደርስበትና ፡ ፕላቶን ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ መኖር ፡ ያስተማረው ፡ ትምህርት ፡ ጥብቅ ፡ በሆነ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ የቆመ ፡ መሆኑን ፡ ልንረዳው ፡ እንችላለን ። ከሁለት ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ ወዲህ ፡ በሳይንስና ፡ በቴክኒክ ፡ በኩል ፡ የተፈጸመውን ፡ እርምጃ ፡ እንመልከት ። በኬሚ ፤ በፊዚክ ፤ በቢዎሎጂ ፤ በቴርሞ ፡ ዲናሚክ ፤ በቴሌግራፊ ፡ ሱማሪን ፤ የብርሃን ፡ ኤሌክትሮማኜቲክ ፤ በቴዎሪ ፡ ኤሌክትሮኒክ ፤ በሬዮን ፡ ኢክስ ፤ በፌኖሜን ፡ ራዲዮአክቲብ ፤ በቴዎሪ ፡ ዴ ፡ ላ ፡ ረላቲቢቴ ፤ በቴርሞ ፡ ኬሚ ፤ እነዚህን ፡ በመሰሉት ፡ በኩል ፡ ለተደረገው ፡ ለያንዳንዱ ፡ ጥበብ ፡ ዕውቀቱን ፡ የገለጠው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ሊቃውንትም ፡ የጀርመን ፤ የእንግሊዝ ፤ የፈረንሳይ ፤ የሆላንድ ፤ ያሜሪካ ፡ ተወላጆች ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ማንኛውም ፡ አገር ፡ በጥበብና ፡ በሥልጣኔ ፡ በኩል ፡ ያደረገው ፡ እድገት ፡ በሊቃውንቶቹ ፡ አማካይነት ፡ ብቻ ፡ የተገኘ ፡ ነው ። ፈረንሳይ ፡ በ1871 ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ፡ ጀርመን ፡ ድል ፡ አድርጓት ፡ ስለ ፡ ጦር ፡ ካሳ ፡ በከፈለችው ፡ አምስት ፡ ሚሊያርድ ፡ ፍራንክ ፡ የደረሰባትን ፡ ጕዳት ፡ ፓስተር ፡ የሚባለው ፡ ሊቅ ፡ በሕክምና ፡ (ከክትባት) ፡ ባገኘው ፡ ጥበብ ፡ ተክሳለች ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ፡ ሲል ፡ አንድ ፡ የእንግሊዝ ፡ ተወላጅ ፡ ተናግሯል ። ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ አዲስ ፡ የሚፈለሰፍ ፡ ጥበብ ፡ ሁሉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እየዋለ ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ እንዲጠቀሙበት ፡ የሚደረግ ፡ በመሆኑ ፡ በንግድ ፡ መደብ ፡ እየገባ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ ያተርፋል ። ኖቤል ፡ የሚባለው ፡ የሱዊድን ፡ ተወላጅ ፡ ዲናሚት ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ የማይበገሩትን ፡ ተራሮች ፤ ገደሎችና ፡ ታላላቅ ፡ አለቶች ፡ የሚገኙበትን ፡ ስፍራ ፡ ለመሰንጠቅና ፡ ለማፍረስ ፡ በጣም ፡ የሚረዳ ፡ ሆኖ ፡ በመገኘቱ ፡ የዓለም ፡ ሰዎች ፡ በተጠቀሙበት ፡ መጠን ፡ ጥበቡን ፡ ያገኘው ፡ ኖቤል ፡ የተባለው ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አግኝቶበታል ። እንሆ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ በሥነ ፡ ጥበብ ፤ በሳይንስና ፡ በቴክኒክ ፡ በኩል ፡ ለተገለጡት ፡ ዕውቀቶች ፡ ሁሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ጥበብ ፡ አንዳንድ ፡ ባለቤት ፡ አለው ። ስለዚህ ፡ እንደ

ዚህ ፡ ያለ ፡ ሥርዐት ፡ ያለበት ፡ ዓለም ፡ ያላንድ ፡ ባለቤት ፤ ያላንድ ፡ ሥርዐት ፡ ተፈጠረ ፡ ብሎ ፡ ለማመን ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ይቻላል? ይህ ፡ የዓለም ፡ ፈጣሪ ፡ ባለቤት ፡ የሆነው ፡ ሰውን ፡ የፈጠረው ፡ ለምንድነው? ይህ ፡ ዓለም ፡ የመጨረሻ ፡ ዐላማው ፡ ምንድነው? የፈጣሪው ፡ ጠባይ ፡ ምንድነው? ክፉት ፡ ከወዴት ፡ መጣ? የክፉት ፡ ባሕርይ ፡ ምንድነው? ሰው ፡ በሥን ፡ ፍጥረቱ ፡ ለሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በነጻነቱ ፡ የሚሠራው ፡ ባላፊነት ፡ የሚጠየቅበት ፡ ወሰኑ ፡ እስከ ፡ ምን ፡ ድረስ ፡ ነው? ከነጻነቱና ፡ ካቅሙ ፡ በላይ ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠረው ፡ ተግባር ፡ ምንድነው? ለእነዚህ ፡ ጥያቄዎች ፡ መልሱን ፡ ለመስጠት ፡ ብዙ ፡ ፈላስፎች ፡ ደክመውበታል ። ነገር ፡ ግን ፡ የሰው ፡ ዕውቀት ፡ ያለው ፡ ችሎታ ፡ የተወሰነ ፡ በመሆኑ ፡ ከድንበሩ ፡ ለማለፍ ፡ አልቻሉም ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ በእነዚህ ፡ ጕዳዮች ፡ ላይ ፡ የሚሰጡን ፡ መልሶች ፡ በሙሉ ፡ አያጠግቡንም ።

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ባሳባችን ፡ ልንደርስባቸው ፡ የማንችል ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ ስላሉ ፡ ይህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መኖር ፡ ለመካድ ፡ ምክንያት ፡ ሊሆነን ፡ አይገባም ። እግዚአብሔርን ፡ ለማግኘት ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በብዙ ፡ ዐይነት ፡ መንገድ ፡ ሊደርስበት ፡ ይችላል ። እግዚአብሔርም ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ይገለጥለታል ። እንደዚሁም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመካድ ፡ ያሳብ ፡ ዝንባሌ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሰወርበታል ። ወዳጆች ፡ የሆኑ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ በመካከላቸው ፡ ፍቅር ፡ ካለ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የሚኖሩበት ፡ አገር ፡ በጣም ፡ የተራራቀ ፡ ቢሆን ፡ በደብዳቤ ፤ በስልክ ፤ በሰው  አማካይነት ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ መንገድ ፡ ሊጠያየቁና ፡ ሊገናኙ ፡ ይችላሉ ። በመካከላቸው ፡ ፍቅር ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ እየተራራቁና ፡ እየተረሳሱ ፡ ይሄዳሉ ። በመጨረሻም ፡ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ መፈጠሩንና ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የሚኖር ፡ መሆኑን ፡ እስከ ፡ መዘንጋት ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ የበቁ ፡ ሰዎች ፡ እግዚአብሔርን ፡ በግልጥ ፡ የሚያዩት ፡ መሆኑን ፡ እናውቃለን ። ብዙ ፡ ጻድቃን ፡ ድንግል ፡ ማርያምን ፡ በግልጥ ፡ አይተዋታል ። ክርስቶስም ፡ ለብዙዎች ፡ ይገለጥላቸዋል ። ይህም ፡ በየጊዜው ፡ የሚደርስና ፡ እኛም ፡ ሁላችን ፡ የምንሰማው ፡ ነገር ፡ ነው ። ከሓድያን ፡ በሆኑት ፡ ሊቃውንት ፡ በኩል ፡ ግን ፡ በምንም ፡ ዐይነት ፡ መንገድ ፡ ቢሆን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማየት ፡ አይቻልም ። ምክንያቱም ፡ ኪሚና ፡ ፊዚክ ፡ በሚመረመሩበት ፡ ላቦራቷር ፡ ውስጥ ፡ በሚገኙት ፡ መሣሪያዎች ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚገለጥበትን ፡ መንገድ ፡ ለማግኘት ፡ የማይችሉ ፡ በመሆናቸው ፡ ነው ።

በዳዊት ፡ መዝሙር ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ እናገኛለን ።



«ከደግ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ አንተ ፡ ደግ ፡ ነህ ፡ ከትክክለኛ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ትክክለኛ ፡ ነህ ፤ ከንጹህ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ንጹህ ፡ ነህ ፡ ከጠማማ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ግን ፡ አንተም ፡ ብልጥ ፡ ትሆንበታለህ» ።

የጀርመኑ ፡ ሊቅ ፡ መምህር ፡ ኤካርት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ቃል ፡ ጽፏል ።

«በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ እሱ ፡ የሚፈልገውን ፡ ነገር ፡ አያውቅም» ።

ዲያብሎስ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ከመቅደስ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ አውጥቶ ፡ በፈተነው ፡ ጊዜ ፡ እውነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ከሆንክ ፡ ራስኽን ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ጣለው ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ሁሉ ፡ እግርኽ ፡ በድንጋይ ፡ እንዳይሰናከል ፡ መላእክት ፡ እንዲደግፉኽ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጥልሃል ፡ ቢለው ፤ ክርስቶስ ፡ ጌታኽን ፡ አምላክኽን ፡ እንዳትፈታተነው ፡ ይህም ፡ የተጻፈ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ መልሶለታል ። ይህም ፡ በወንጌል ፡ ተጽፎ ፡ የምናገኘው ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ሰው ፡ በሰይጣን ፡ እግር ፡ ተተክቶ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አምላኩን ፡ ይፈታተነው ፡ ዘንድ ፡ አልተፈቀደለትም ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አለ ። ከፍ ፡ ብለን ፡ በዚሁ ፡ ምዕራፍ ፡ ተመልክተነው ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ሶክራት ፡ ሲናገር ፡ እኔ ፡ በሌሎቹ ፡ ሰዎች ፡ አንጐል ፡ ውስጥ ፡ ተሸፍኖ ፤ ተፀንሶ ፡ የሚገኘውን ፡ ዕውቀት ፡ እንዲወለድ ፡ ለማድረግ ፡ እረዳለሁ ፡ እንጂ ፡ ራሴ ፡ የምፈጽመው ፡ ምንም ፡ ተጨማሪ ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ብሏል ። እንደዚህ ፡ ከሆነ ፡ በሰዎች ፡ አንጐል ፡ ውስጥ ፡ ተረግዞ ፡ የሚገኝ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕውቀትና ፡ ጥበብ ፡ ከወዴት ፡ የመጣ ፡ ነው ? ለምሳሌ ፤ ፓስካል ፡ በዡሜትሪ ፤ ሞዛር ፡ በሙዚቃ ፡ ገና ፡ በሕፃንነታቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስጦታ ፡ ያላቸው ፡ ሆነው ፡ ተገኝተዋል ። ይህ ፡ ስጦታ ፡ ይህ ፡ ዕውቀት ፡ ምንጩ ፡ ከየት ፡ የመጣ ፡ ነው? ሰው ፡ የዕውቀትና ፡ የጥበብ ፡ መሠረት ፡ ከሆነ ፡ ከሌላ ፡ ምንጭ ፡ የመጣ ፡ ለመሆኑ ፡ ይህም ፡ አንድ ፡ ማስረጃ ፡ መሆኑን ፡ ሶክራትና ፡ ፕላቶን ፡ ያስገነዝቡናል ። ሰው ፡ ትምህርት ፡ ሲያስተምሩት ፡ ገባው ፡ ይባላል ። ገባው ፡ ማለት ፡ ምንድነው ? ቀድሞ ፡ ከመፈጠሩ ፡ በፊት ፡ ያውቀው ፡ የነበረውን ፡ ነገር ፡ ሲነግሩት ፡ አስታውሶ ፡ ደረሰበት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የማያውቀውን ፡ ነገር ፡ ዐወቀ ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ከሥር ፡ ከመሠረቱ ፡ ጨርሶ ፡ የማያውቀው ፡ ቢሆንማ ፡ ኖሮ ፡ ሊገባው ፡ አይችልም ፡ ነበር ። እንስሳን ፡ ለምሳሌ ፡ ዝንጀሮን ፡ ትምህርት ፡ ብናስተምረው ፡ አይገባውም። ምክንያቱም ፡ ሥነ ፡ ፍጥረቱ ፡ ከዕውቀት ፤ ከጥበብ ፡ ምንጭ ፡ የመጣ ፡ ባለመሆኑ ፡ ነው ።

# የሥልጣኔ ፡ ገጸ ፡ በረከት ።

የሥልጣኔ ፡ አካሄድ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ የሚፈሰውን ፡ ውሃ ፡ መስሎ ፡ ይታያል ። ከመሬት ፡ እየመነጨ ፡ ወይም ፡ ከሰማይ ፡ እየዘነበ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ የሚፈስ ፡ ውሃ ፡ ጐርፍ ፤ ጅረት ፤ ወንዝ ፤ እየሆነ ፡ መሬትን ፡ እያራሰና ፡ እያጠጣ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ሁሉም ፡ ሂዶ ፤ ሂዶ ፤ ከውቅያኖስ ፡ ይገባል ። ውቅያኖሶችም ፡ ዞረው ፡ ዞረው ፡ ይገጥማሉ ፡ ይገናኛሉ ።

በመሬት ፡ ላይ ፡ ተበታትነው ፡ በየአህጉሩ ፡ የሚኖሩት ፡ ሕዝቦችም ፡ እንደዚሁ ፡ በየበኩላቸው ፡ ኑሯቸውን ፡ ለማሻሻል ፡ ጥበብ ፡ አፍቃሪዎች ፡ በመሆን ፡ የፈጠሩት ፡ ዘዴና ፡ ዕውቀት ፡ ለራሳቸው ፡ ካገለገላቸው ፡ በኋላ ፡ ለጎረቤቶቻቸው ፡ ቀጥሎም ፡ ሩቅ ፡ ላሉት ፡ እየተላለፈ ፡ ዞሮ ፡ ዞሮ ፡ ይገናኝና ፡ እየተጠራቀመ ፡ የጥበብ ፡ ውቅያኖስ ፡ ሆኖ ፡ ይከማቻል ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ በጠቅላላው ፡ ለሰው ፡ ዘር ፡ ሁሉ ፡ የሚያገለግልና ፡ የሚጠቅም ፡ ሆኖ ፡ የተገኘው ፡ ይህ ፡ የተከማቸ ፡ ጥበብና ፡ ዕውቀት ፡ ሥልጣኔ ፡ ለመባል ፡ በቃ ።

ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የተከበረች ፡ ሆና ፡ ለምትታየው ፡ ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ መሥራቾች ፡ ግሪኮች ፡ ናቸው ፡ ብለን ፡ ስንናገር ፡ እነሱ ፡ ይህቺን ፡ በሳይንስ ፡ ላይ ፡ የቆመቸውን ፡ የተተከለችውን ፡ ሥልጣኔ ፡ ሲፈጥሩ ፡ መነሻ ፡ የሆናቸው ፡ ያ ፡ ከዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ በየዘመኑና ፡ በየቦታው ፡ ተሠርቶ ፡ የጠፋ ፤ ከጠፋው ፡ በኋላ ፡ የተረፈው ፡ ተከማችቶ ፡ የተገኘ ፡ ጠቅላላ ፡ ውጤት ፡ መሆኑን ፡ ማወቅ ፡ ይገባናል ።

እያንዳንዱ ፡ ሕዝብ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ በየዘመኑ ፡ ለሥልጣኔ ፡ የሠጠውን ፡ የጥበብ ፡ ውጤት ፡ እንደ ፡ መተያያ ፡ አድርጎ ፡ ያቀረበውን ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ በዝርዝር ፡ ለማወቅ ፡ የተፈለገ ፡ እንደሆነ ፡ ከቶ ፡ የሚቻል ፡ የሚዘለቅ ፡ ነገር ፡ አይዶለም ። ምክንያቱም ፡ እንደ ፡ ዛፍ ፡ ሐረግ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ያለው ፡ መተሳሰርና ፡ ቅልቅልነት ፡ የማበጠሩንና ፡ የማጣራቱን ፡ ሥራ ፡ አስቸጋሪ ፡ ስለሚያደርገው ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሊቃውንት ፡ ይህንኑ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ለመለየት ፡ የደከሙበት ፡ በመሆናቸው ፡ ሞላ ፡ ከጐደል ፡ ሊታወቅ ፡ ተችሏል ። ስለዚህ ፡ ይህንኑ ፡ በሰፊው ፡ ሳይሆን ፡ ባጭሩ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ እንመለከተዋለን ።

ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ስንጽፍ ፡ ዐላማ ፡ አድርገን ፡ የተከተልነው ፡ አሳብ ፡ የሥልጣኔን ፡ ፍሬዎች ፡ በዝርዝርም ፡ ሆነ ፡ በክፊል ፡ እየለዩ ፡ ለመመልከት ፡ ሳይሆን ፡ ሥልጣኔ ፡ የተባለችው ፡ ቃል ፡ በትርጉም ፡ መንፈስ ፡ የያዘችውን ፡ አመራር ፤ የምትሰጠንን ፡ ስሜት ፡ የምትከተለውን ፡ አዝማሚያ ፡ ወይም ፡ ዝንባሌ ፡ ለማወቅ ፡ መሆኑን ፡ ደጋግመን ፡ በጥብቅ ፡ ማሳሰብ ፡ እንወዳለን ። አለዚያማ ፡ በየዘመኑ ፡ የሥልጣኔን ፡ ሥራ ፡ የፈጸሙ ፡ ሕዝቦች ፡ ምን ፡ እንደሠሩ ፡ ዘመኑንና ፡ ቦታውን ፡ በመጥቀስ ፡ መናገር፡ ግዴታ ፡ ይሆንብናል ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ «የሥልጣኔ ፡ ታሪክ» ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ተነሥቶ ፡ መሥራት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። አሁን ፡ ግን ፡ የተነሣነው ፡ ይህን ፡ ለመሰለ ፡ አቀራረብ ፡ ባለመሆኑ ፡ የሥልጣኔን ፡ ትርጉም ፡ ለመፈለግ ፡ የምንሞክር ፡ በመሆናችን ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የምንናገረውን ፡ በዚሁ ፡ ለመወሰንና ፡ አካሄዳችን ፡ ከዚህ ፡ ዐላማ ፡ ሳይዛባ ፡ እንዲቀጥል ፡ ለማድረግ ፡ እንጣጣራለን ።

ለሥልጣኔ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ የሚሆን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ ፈጽመው ፡ ላቀረቡት ፡ ሕዝቦች ፡ ውለታ ፡ እንደ ፡ መግለጥ ፡ ያኽል ፡ አድርገን ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ የተስማሙበትን ፡ ባጭሩ ፡ እንጠቅሰዋለን ።

የሥልጣኔን ፡ ተግባር ፡ የፈጸሙ ፡ ሕዝቦች ፡ ተግባራቸውና ፡ ሙያቸው ፡ የተለያየ ፡ ነው ። ጥበብን ፡ ለመፍጠር ፡ ለመፈልሰፍ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ ሕዝቦች ፡ አሉ ። እነሱም ፡ ቀድሞ ፡ ያልነበረውን ፡ ዘዴ ፤ ብልኀት ፤ ወይም ፡ ጥበብ ፡ እንዲገኝ ፡ ለማድረግ ፡ ስጦታ ፡ ያላቸው ፡ መሆናቸውን ፡ የገለጡ ፡ ሕዝቦች ፡ ናቸው ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ ሺና ፤ የጥንቲቱ ፡ ግብጽ ፤ ግሪክ ፤ ቶልቴክ ፤ አዝቴክና ፡ ኢንካ ፡ የተባሉት ፡ ሕዝቦች ፡ የነበራቸው ፡ ሙያ ፡ በታሪክ ፡ ተመስክሮላቸዋል ። ሁለተኛ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ተወልዶ ፡ የተገኘውን ፡ ተቀብለው ፡ እያሻሻሉ ፡ እያስፋፉና ፡ አዲስ ፡ ውበት ፡ እየሰጡ ፡ እንዳይሞት ፡ እንዳይጠፋ ፡ ጠብቀውና ፡ ሕይወት ፡ ሰጥተው ፡ ለቀሩት ፡ ሕዝቦች ፡ እንዲተላለፍ ፡ ለማድረግ ፡ በዚህ ፡ ስጦታ ፡ አንደኛውን ፡ ደረጃ ፡ ይዘው ፡ የሚገኙ ፡ ግሪክና ፡ ሮማ ፡ ናቸው ።

እንደዚህ ፡ ተደክሞበት ፡ የተገኘውን ፡ ሥልጣኔ ፡ ወይም ፡ ጥበብ ፡ ለመቀበልና ፡ ወደ ፡ ከፍተኛነት ፡ ደረጃ ፡ እንዲደርስ ፡ ለማድረግ ፡ ልዩ ፡ ሙያ ፡ ያላቸው ፡ ሆነው ፡ የተገኙ ፡ ያውሮፓና ፡ የእስያ ፡ ሕዝቦች ፡ ናቸው ።

የቋንቋንና ፡ የጽሕፈትን ፡ ጥበብ ፡ ሰው ፡ የተቀበለው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ብለን ፡ በሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ መሠረት ፡ ማመን ፡ ይገባናል ። ነገር ፡ ግን ፡ አንዳንድ ፡ ሊቃውንት ፡ እንደሚናገሩት ፡ ሁሉ ፡ የንግግርንና ፡ የጽሕፈትን ፡ ዘዴ ፡ ሰው ፡ ያገኘው ፡ በመጣጣርና ፡ በዕውቀት ፡



መራመድ ፡ ነው ፡ ያልን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህን ፡ ዘዴ ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ ሰው ፡ ሊያገኘው ፡ ቻለ ፡ እንደዚህ ፡ ከሆነ ፡ እንደ ፡ ዝንጀሮና ፡ እንደ ፡ ዝሆን ፡ ያሉ ፡ ብልኀነት ፡ የሚታይባቸው ፡ እንስሳት ፡ ለምን ፡ ሳያገኙት ፡ ቀሩ ? ብለን ፡ ስንመራመር ፡ ለዚህ ፡ አጥጋቢ ፡ የሆነ ፡ መልስ ፡ ሊሰጠን ፡ የሚችል ፡ ሊቅ ፡ ከቶ ፡ አናገኝም ።

ጨዋታ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጥበብን ፡ የሚወልድ ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ። ምክንያቱም ፡ መንፈስን ፡ እንዲሠራ ፤ እንዲነቃና ፡ እንዲግል ፡ ስለሚያደርገው ፡ ነው ። ግሪኮች ፡ የኦሌምፒክ ፡ ጨዋታዎች ፡ ብለው ፡ በሚጠሯቸውና ፡ በቅኔ ፡ ውድድሮቻቸው ፤ ሮማውያን ፡ በሲርክ ፡ ውስጥ ፡ ያደርጉት ፡ የነበረ ፡ ውጊያ ፤ በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ባውሮፓ ፡ የተለመደ ፡ የነበረው ፡ መሳፍንትና ፡ መኳንንት ፡ የብረት ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ በፈረስ ፡ ተቀምጠው ፡ በጦር ፡ ያደርጉት ፡ የነበር ፡ (tournoi) የሚባል ፡ ውጊያ ፤ በእስፓኛ ፡ አገር ፡ ከፈጋ ፡ በሬ ፡ ጋራ ፡ ሰዎች ፡ የሚያደርጉት ፡ የቶሬሮ ፡ ውጊያ ፤ በጃፓን ፡ አገር ፡ በተለየ ፡ እየተቀለቡ ፡ የሚኖሩ ፡ ግዙፎች ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ የሚያደርጉት ፡ ትግል ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የሰውን ፡ መንፈስ ፡ የሚያነቃና ፡ ወደ ፡ ጥበብ ፡ የሚያንቀሳቅሰው ፡ ዘዴና ፡ ብልኀት ፡ እንዲፈጥር ፡ የሚረዳው ፡ ሆኖ ፡ ተቈጥሯል ። እንደዚሁም ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ ኦፔራ ፤ ቴአትር ፤ ሲኒማ ፤ ቴሌቪዚዮን ፡ እነዚህ ፡ ጨዋታዎች ፡ ከሥነ ፡ ጥበብና ፡ ከቴክኒክ ፡ ጥበብ ፡ ጋራ ፡ በቅርብ ፡ የሚገናኙ ፡ በመሆናቸው ፡ ጠቃሚዎች ፡ ሆነው ፡ ተገኝተዋል ። ብዙውንም ፡ ጊዜ ፡ የሥነ ፡ ጥበብና ፡ የቴክኒክ ፡ እርምጃ ፡ የደረሰበትን ፡ እድገት ፡ ለማወቅ ፡ የሚያስችሉ ፡ ናቸው ።

የአስትሮኖሚ ፡ ዕውቀት ፡ ከሥር ፡ ከመሠረቱ ፡ የመጣው ፡ ከሜዞፖታሚና ፡ ከግብጽ ፡ ነው ። በኋላም ፡ በግሪክ ፡ አገር ፡ ተገኝቷል ። ነገር ፡ ግን ፡ በተለየ ፡ በሜዞፖታሚና ፡ በግብጽ ፡ ይህ ፡ ጥበብ ፡ ካስትሮሎጊ ፡ ጋራ ፡ ተቀላቅሎ ፡ ይኖር ፡ ነበር ።

የጥንት ፡ ሰዎች ፡ በድንቍርና ፡ ሳሉ ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ ይኖሩ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አንድ ፡ ሊቅ ፡ ሲገልጥልን ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፤

«ቈርፋዳ ፡ ደበሎ ፡ ለባሾች ፤ ንግግር ፡ የማያበዙ ፤ አተኵረው ፡ መመልከት ፡ የሚወዱ ፤ ቶሎ ፡ የሚደነግጡ ፤ ለውጊያ ፡ ደፋሮች ፤ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚሆነውን ፡ ነገር ፡ አስቀድመው ፡ ለማሰብ ፡ የማይችሉ ፤ በቤተ ፡ ሰብ ፡ እየተከፈሉ ፡ የሚሰፍሩ ፤ ቀጥሎ ፡ በጐሣ ፡ ተለያይተው ፡ የሚኖሩ ፤ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ሳሉ ፡ ሕይወታቸውን ፡ የማያሻሽሉ ፤ በቍጥር ፡ የሚበልጣቸው ፡ ሌላ ፡ ጐሣ ፡ ሲነሣባቸው ፡ ቦታቸውን ፡ ለቀው ፡ የሚሄዱ ፡ ናቸው» ።

እንሆ ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ብለው ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፤ የሚጠሯቸው ፡ (hommes primitifs) የተባሉት ፡ አኗኗራቸው ፡ እንደዚህ ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መጀመሪያ ፡ እሳት ፡ የማንደድን ፡ ዘዴ ፡ አገኙ ። ቀጥሎ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሥራና ፡ የመከላከያ ፡ መሣሪያዎች ፡ ከደንጊያ ፡ አገኙ ። ቀጥሎ ፡ የዕንጨትና ፡ የደንጊያ ፡ መሣሪያዎች ፡ አበጁ ። እነ ፡ ሸክላ ፤ ፈትል ፤ እኽል ፡ መዝራት ፡ ማብሰልና ፡ መፍጨት ፤ የቤት ፡ እንስሳትን ፡ ማስለመድና ፡ ማርባት ፤ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ መሥራት ፤ ደንቦችና ፡ ሕጋትን ፡ ማውጣት ፡ ቀጥሎ ፡ የመጡ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ። ለቤት ፡ ሰብ ፡ አስተዳደር ፤ ለጐሣ ፡ አኗኗር ፤ ቀጥሎ ፡ ለመንደር ፡ ሕዝብ ፡ ከዚያም ፡ ለከተማ ፡ ሕዝብ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ሥራትና ፡ ደንብ ፡ ሕግና ፡ ዐዋጅ ፡ ማውጣት ፡ ቻሉ ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ የሥልጣኔን ፡ ሥራ ፡ መጀመሪያ ፡ የፈጸሙ ፡ ሜዞፖታሚ ፤ ግብጽ ፤ ቀጥሎ ፡ ሺንና ፡ ህንድ ፡ ናቸው ። ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ሃይማኖት ፡ የመጀመሪያውን ፡ ደረጃ ፡ ይዞ ፡ ሥራትና ፡ ሕጋት ፡ አግኝቶ ፡ በሁሉም ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ በጥንታዊነት ፡ ይኖር ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ተረጋግጧል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የሃይማኖትን ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የሳይንስን ፤ ሌላም ፡ ጊዜ ፡ ፍርሀትን ፡ የተንተራሰ ፡ አምልኮትን ፡ እየተጠጋ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ እየተሰጠው ፡ የጥንቈላ ፡ ሥራ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በጥንት ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ የነበረ ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ።

ብረትን ፡ ብርን ፡ ወርቅን ፤ መዳብን ፡ በእሳት ፡ ማቅለጥና ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ እንዲውል ፡ ማድረግ ፡ የተጀመረው ፡ በሜዞፖታሚ ፡ ነው ። ከፍ ፡ ብሎ ፡ በተገለጠው ፡ አኳኋን ፡ ሰዎች ፡ በማኅበር ፡ መንፈስ ፡ እየተሰበሰቡ ፡ ቤት ፡ መሥራት ፡ ከብት ፡ ማርባት ፤ እኽል ፡ መዝራት ፤ ከዚያም ፡ ከተማ ፡ ቈርቍረው ፡ በማኅበር ፡ እየሠሩና ፡ በማኅበር ፡ እየኖሩ ፡ ሀብት ፡ መሰብሰብ ፡ የጽሕፈትን ፡ ዘዴ ፡ አግኝተው ፡ መጽሐፍ ፡ መጻፍና ፡ ዕውቀት ፡ ማከማቸት ፡ ሲጀምሩ ፤ ዘላን ፡ የሆኑ ፡ ሕዝቦች ፡ መሬት ፡ በመፈለግና ፡ በተለየም ፡ ሀብት ፡ ሲያዩ ፡ የዘረፋ ፡ ምኞት ፡ እየሳባቸው ፡ አደጋ ፡ እየጣሉ ፡ ንብረታቸውን ፡ አቃጥለው ፡ ሀብታቸውን ፡ ዘርፈው ፡ እነሱንም ፡ ፈጅተው ፡ መሬታቸውን ፡ ይነጥቋቸዋል ። ዘላን ፡ የሆኑ ፡ ሕዝቦች ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የሥልጣኔ ፡ ጠንቅ ፡ ለመሆናቸው ፡ ታሪክ ፡ ይናገራል ። ባውሮፓም ፡ ሆነ ፡ በእስያ ፡ ወይም ፡ ባፍሪቃ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ በየዘመኑ ፡ እየተደጋገመ ፡ ሲደርስ ፡ ታይቷል ። ዘላን ፡ ሕዝቦች ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በጦር ፡ ኀይለኞች ፡ ሆነው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። የተሠራው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ እንደዚህ ፡ ሆኖ ፡ ከጠፋ ፡ በኋላ ፡ እነዚያ ፡ የሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ በወረሯቸው ፡ ዘላን ፡ ሕዝቦች ፡ እየተገዙ ፡ ወይም ፡ ተቀላቅለው ፡ መኖር ፡ ግድ ፡ እየሆነባቸው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሰው ፡ በጥበብ ፡ መንገድ ፡ ጕዞ ፡ ይጀምራሉ ።



ስለዚህ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሕዝብ ፡ የሠራውን ፡ የሥልጣኔ ፡ ሥራ ፡ ስንመለከተው ፡ እርምጃው ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ በየጊዜው ፡ እየተቋረጠና ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ እየተመለሰ ፡ የኖረ ፡ መሆኑን ፡ ጨምረን ፡ አንድነት ፡ ማሰብ ፡ አለብን ።

በደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ የሥልጣኔ ፡ ምንጮች ፡ የሆኑት ፡ አገሮች ፡ ሜክስክ ፤ ጓቴማላ ፤ ዩካታ ፤ ኮሎምቢ ፤ ፔሩ ፡ የሚባሉት ፡ ናቸው ። በሜክሲክ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥልጣኔ ፡ የነበራቸው ፡ ቶልቴክና ፡ ቴዎቲሃካን ፡ የሚባሉት ፡ ሕዝቦች ፡ ናቸው ። እነሱም ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ጥጥ ፤ ማሽላ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የምግብ ፡ አታክልቶች ፡ ይዘሩና ፡ ይተክሉ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ሸክላ ፡ የመሥራትና ፡ በድንጋይ ፡ ሐውልት ፡ የመቅረጽ ፡ ችሎታ ፡ እንደ ፡ ነበራቸው ፡ ታውቋል ። በኋላም ፡ በ1324 ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ፡ ወደ ፡ ሜክሲክ ፡ የገቡት ፡ አዝቴክ ፡ የተባሉት ፡ ሕዝቦች ፡ ወርቅ ፤ ነሐስ ፤ እርሳስ ፤ ያቀልጡ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ለማወቅ ፡ ተችሏል ። ይህንንም ፡ ያስተማሯቸው ፡ ከእነሱ ፡ በፊት ፡ በዚህ ፡ ጥበብ ፡ ችሎታ ፡ የነበራቸው ፡ የኮሎምቢና ፡ የፔሩ ፡ ሕዝቦች ፡ ናቸው ። በዩካታ ፡ የነበሩት ፡ ማያ ፡ የተባሉት ፡ ሕዝቦች ፡ ሐውልት ፡ በመቅረጽ ፤ በኪነ ፡ ጥበብና ፡ በጽሕፈትም ፡ ልዩ ፡ ችሎታ ፡ የነበራቸው ፡ ሆነው ፡ ተቈጥረዋል ። በፔሩ ፤ በኤኳተር ፤ በኮሎምቢ ፡ እንደዚሁም ፡ በከፊል ፡ በአርጃንቲንና ፡ በሺሊ ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ ጦረኞች ፡ የነበሩት ፡ ኢንካ ፡ የተባሉት ፡ ሕዝቦች ፡ በፈርዖኖች ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ ይታይ ፡ የነበረውን ፡ የመሰለ ፡ የሕዝብና ፡ የመንግሥትን ፡ አስተዳደር ፡ ለሚመሩ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ አቋቋም ፡ ሥነ ፡ ሥርዐትና ፡ ሕጋት ፡ የፈጠሩ ፡ ለመሆናቸው ፡ በታሪክ ፡ ተመስክሮላቸዋል ።

የሰንጠረዥ ፡ ጨዋታ ፡ የተገኘው ፡ ከህንድ ፡ ነው ። ገብስና ፡ ስንዴ ፡ መጀመሪያ ፡ በቅለው ፡ የተገኙት ፡ ከሜዞፖታሚ ፡ ነው ። ሩዝ ፡ ከህንድ ፡ ወይንና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የፍሬ ፡ አታክልት ፡ በጥንታዊ ፡ ዘመን ፡ ከእስያ ፤ የወይራ ፡ ፍሬ ፡ ከፓሌስቲንና ፡ ከባቢሎን ፤ ሱፍና ፡ የተልባ ፡ እግር ፡ ከመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ አገር ፤ ጥጥ ፡ ከሱዳንና ፡ ከግብጽ ፤ ቡና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሎሚ ፡ ብርቱኳን ፤ ሐር ፡ ከሺን ፡ የመጡ ፡ ናቸው ። ስኳር ፡ መጀመሪያ ፡ በሲሮፕ ፡ መልክ ፡ ተሠርቶ ፡ በህንድ ፡ አገር ፡ ተገኘና ፡ ሺን ፡ ከህንድ ፡ ተቀበለች ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሺናውያን ፡ ለፋርሶችና ፡ ለሜዞፖታሚ ፤ ሜዞፖታሚ ፡ ላረቦች ፤ ዐረቦች ፡ ላውሮፓ ፡ እያቀበሉ ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የተገኘ ፡ ለመሆን ፡ በቃ ። ነጮች ፡ ከመግባታቸው ፡ በፊት ፡ ያሜሪካ ፡

አገር ፡ ሕዝቦች ፡ ማሽላን ፤ ድንችን ፤ አደንጓሬን ፤ ቲማቲምን ፤ ትንባኾን ፤ ኮካን ፤ ባገራቸው ፡ ይዘሩና ፡ ይተክሉ ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እነዚህን ፡ እኽሎችና ፡ አታክልቶች ፡ ነጮች ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፤ እስፓኛና ፡ ስሜን ፡ አፍሪካ ፡ አስተላለፏቸው ።

አትክልትና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የጌጥ ፡ ዛፎች ፡ እንደዚሁም ፡ የጌጥ ፡ እንስሳት ፡ መጀመሪያ ፡ የተገኙት ፡ በግብጽ ፡ በሺንና ፡ በፋርስ ፡ ነው ። ነሐስና ፡ ብረት ፡ መጀመሪያ ፡ የተገኙት ፡ ከሜዞፖታሚና ፡ ከትንሹ ፡ እስያ ፡ ነው ። የድንጋይ ፡ ከሰልን ፤ የከብት ፡ ጭነትን ፡ ዘዴ ፤ ወረቀትን ፡ የማተሚያ ፡ ጥበብን ፤ ሐር ፡ መፍተልን ፤ የፖርስሌንን ፡ ዕቃ ፤ ባሩድን ፡ እነዚህን ፡ መጀመሪያ ፡ የሠሩ ፡ በመሆናቸው ፡ የሺን ፡ ሕዝብ ፡ በሥልጣኔ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ዋናውን ፡ ምዕራፍ ፡ ይዘው ፡ ተገኝተዋል ። በሜክሲክና ፡ በፔሩ ፡ የነበሩት ፡ ሕዝቦች ፡ ሥልጣኔያቸው ፡ በጣም ፡ የገፋና ፡ የተራመደ ፡ በመሆኑ ፡ ያከማቹት ፡ ሀብትም ፡ ብዙ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ በከተሞቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ሥራ ፡ ሳይሠሩ ፡ ብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝቦች ፡ ቍጭ ፡ ብለው ፡ እንዲበሉ ፡ ለማድረግ ፡ ያስችላቸው ፡ ነበር ። በጌጥ ፡ በድሎትና ፡ በሲሳይ ፡ የነበራቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እድገት ፡ ባገራቸው ፡ ውስጥ ፡ መቀማጠል ፡ በጣም ፡ የተራቀቀ ፡ ሆኖ ፡ በኑሯቸው ፡ ውስጥ ፡ ተፈጥሮ ፡ እንዲገኝ ፡ አደርጎ ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

ሺን ፡ በሥልጣኔ ፡ በኩል ፡ የፈጸመችው ፡ በጣም ፡ የተመሰገነችበት ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አለ ። ይኸውም ፡ ታሪክን ፤ የሰውን ፡ ሕይወት ፡ ዜና ፤ ያገር ፡ መጐብኘትን ፡ ታሪክ ፤ የጦርነትን ፡ ጥበብ ፡ ኤኮኖሚን ፤ ፖለቲክን ፤ የእርሻን ፡ ሙያ ፤ ጥንቆላን ፤ ሙዚቃን ፤ የሥዕልን ፡ ሙያ ፤ ቅኔን ፤ ልብ ፡ ወለድን ፤ ቴአትርን ፤ የኤንሲክሎፔዲ ፡ መልክ ፡ የያዘ ፡ መዝገበ ፡ ጥበብን ፤ እነዚህን ፡ ዕውቀቶችና ፡ ጥበባት ፡ በጽሑፍ ፡ እየገለጡ ፡ ማቅረብ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ በሺን ፡ የተለመደ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጨዋታ ፡ ለሕዝብ ፡ ማሳየት ፤ የቴአትር ፡ አቀራረብ ፡ የቅኔና ፡ የልብ ፡ ወለድ ፡ ድርሰት ፡ አጻጻፍ ፡ በህንድ ፡ አገርም ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ተረጋግጧል ። ከዋክብት ፡ የሚያደርጕትን ፡ መንቀሳቀስ ፡ እየተመለከቱ ፡ (አስትሮሎጊ) ፡ በተባለው ፡ ጥበብ ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ ሰዎች ፡ ዕድል ፡ ትንቢት ፡ መናገርና ፡ የጥንቈላ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ በባቢሎን ፤ በግብጽ ፤ በፋርስ ፤ በህንድ ፤ በሺን ፤ በሜክሲክ ፤ የተለመደ ፡ ሆኖ ፡ ይኖር ፡ ነበር ። የሕክምና ፡ ሥራ ፡ በጥንት ፡ ዘመን ፡ በተለየም ፡ ገላ ፡ በመቅደድ ፡ የሚደረግ ፡ ሕክምና ፡ በግብጽ ፤ በህንድና ፡ በሺን ፡ ከከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ለመድረሱና ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡ ለመሆኑ ፡ የተገኙት ፡ ጽሑፎች ፡ ማስረጃ ፡ ሆነዋል ።



በእነዚህ ፡ አገሮች ፡ በጥንት ፡ ዘመን ፡ ስለሚሠራው ፡ የጥጥ ፤ የተልባ ፡ እግርና ፡ የሐር ፡ ጨርቃጨርቅ ፡ በፈትሉ ፡ ረቂቅነትም ፡ ሆነ ፡ በቀለሙ ፡ ደማቅነትና ፡ ጥሩነት ፡ እንደዚሁም ፡ በጌጡና ፡ በጥበቡ ፡ ማማር ፡ ደርሰውበት ፡ የነበረው ፡ ደረጃ ፡ ዛሬ ፡ በመኪና ፡ ማለት ፡ በእንዱስትሪ ፡ ከሚሠራው ፡ ጋራ ፡ ሲመዛዘን ፡ በምንም ፡ አኳኋን ፡ የማያንስ ፡ መሆኑ ፡ ተመስክሯል ። በተጠረበ ፡ ድንጋይና ፡ በሸክላ ፡ የተሠሩት ፡ በሜዞፖታሚና ፡ በግብጽ ፡ የነበሩት ፡ ሕንፃዎች ፡ በአርሺቴክቱር ፡ በኩል ፡ እንከን ፡ የማይገኝባቸው ፡ ነበሩ ። ለዚሁም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ቆመው ፡ ያሉት ፡ ፒራሚዶች ፡ ማስረጃ ፡ ናቸው ። የሜዞፖታሚ ፡ ንጉሥ ፡ የነበረው ፡ ሃሙራቢ ፡ የሚባለው ፡ ቀጥሎ ፡ ትልቁ ፡ እስክንድርና ፡ የሮማ ፡ መንግሥታት ፡ ዓለምን ፡ ከዳር ፡ እዳር ፡ ለመግዛት ፡ ምኞት ፡ ነበራቸው ።

ኪነ ፡ ጥበብ ፤ ሳይንስ ፤ በጠቅላላው ፡ ዕውቀትና ፡ ሥልጣኔ ፡ እንዲስፋፉና ፡ እድገት ፡ እንዲያገኙ ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻለው ፡ በሀብት ፡ መሆኑ ፡ ሊዘነጋ ፡ አይገባውም ። ብዙ ፡ ሀብትና ፡ ንዋይ ፡ ለማከማቸት ፡ የቻሉ ፡ ሕዝቦች ፡ የሊቃውንት ፡ አገሮች ፡ ለመሆን ፡ በቅተዋል ። ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሥራ ፡ ሳይሠሩ ፡ መጻሕፍትን ፡ በመመልከትና ፡ ጥበብን ፡ በመመርመር ፡ እንዲኖሩ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ያገኙትንም ፡ ዕውቀት ፡ ላገሪቱ ፡ እንዲያበረክቱ ፡ አስፈላጊውን ፡ ሁሉ ፡ መስጠት ፡ ስለሚያሻ ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ እንደምንመለከተው ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ እንዲፋጠን ፡ ለማድረግ ፡ የቻሉ ፡ ባለጸጎች ፡ የሆኑ ፡ አገሮች ፡ ናቸው ። በሺን ፤ በግብጽና ፡ በሜዞፖታሚ ፡ የነበሩት ፡ እንደዚሁም ፡ እነ ፡ ኢንካ ፤ ማያ ፤ አዝቴክ ፤ የተባሉት ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ የጠቀስናቸው ፡ ሕዝቦች ፡ ለሰው ፡ ዘር ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሥልጣኔ ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸምና ፡ እንደ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ አድርገው ፡ ይህንኑ ፡ ለመስጠት ፡ የቻሉበት ፡ ምክንያት ፡ በዚህ ፡ ይተረጐማል ።

ሰው ፡ ማለት ፡ ሥራውን ፡ በቃል ፡ የሚገልጥ ፡ እንደዚሁም ፡ ቃሉን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚያውል ፡ በቀሩት ፡ እንስሳት ፡ መካከል ፡ የሚኖር ፡ ለፍላፊ ፡ እንስሳ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ አንድ ፡ ሊቅ ፡ ተናግሯል ። እንግዲህ ፡ እስከ ፡ የግሪኮች ፡ ሥልጣኔ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ሰው ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ ይህ ፡ ለፍላፊ ፡ እንስሳ ፡ የፈጸመው ፡ የሥልጣኔ ፡ ሥራ ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ ሲታይ ፡ ይህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተገለጠው ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ።

በአፍሪቃ ፡ ውስጥ ፡ በየዘመኑ ፡ ተገኝተው ፡ የነበሩት ፡ ሥልጣኔዎች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተገለጡት ፡ ናቸው ።

ኢትዮጵያ ፡ ከብዙ ፡ ሺ ፡ ዓመታት ፡ ጀምሮ ፡ የነበራት ፡ ታሪክ ፡ ክብር ፡ የሞላበት ፡ ሲሆን ፡ በየዘመኑ ፡ የደረሰባትን ፡ ብዙ ፡ ችግርና ፡

ፈተና ፡ አሸንፋ ፡ እያለፈች ፡ ከዛሬው ፡ ዘመን ፡ ታሪክ ፡ ነጻነቷን ፡ እንደ ፡ ያዘች ፡ ገብታለች ። ጥንታዊ ፡ በሆነችው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መናገሻ ፡ ከተማ ፡ በአክሱም ፡ ወድቆ ፡ የሚገኘው ፡ የድንጋይ ፡ ሐውልት ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ካሉት ፡ እሱን ፡ ከመሰሉት ፡ ሐውልቶች ፡ ሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡ ነው ።

መርዌና ፡ ናፓታ ፡ የሚባሉት ፡ በሱዳን ፡ ግዛት ፡ የሚገኙት ፡ የጥንት ፡ ከተሞች ፡ በጥንት ፡ ዘመን ፡ ውብ ፡ የሆነ ፡ ሥልጣኔ ፡ እንደ ፡ ነበራቸው ፡ ታውቋል ። አሁን ፡ ግን ፡ ይህቺ ፡ ሥልጣኔ ፡ ጨርሳ ፡ ጠፍታለች ።

በኒጀሪያ ፡ ቤኒን ፡ በሚባለው ፡ ባሕር ፡ እንደዚሁም ፡ ዮሩምባና ፡ ኢፌ ፡ በሚባሉት ፡ ከተሞች ፡ የተገኙት ፡ እንደ ፡ ዐቢይ ፡ ሥራ ፡ የሚቈጠሩ ፡ የሰው ፡ መልክ ፡ ቅርጾች ፡ በዚያች ፡ አገር ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ በጣም ፡ የተራቀቀች ፡ ሥልጣኔ ፡ የነበረች ፡ ለመሆኗ ፡ ማስረጃ ፡ ናቸው ።

(ሮዴዚ) ፡ በምትባለው ፡ አገር ፡ ዜምባቡዌ ፡ ተብላ ፡ በምትጠራው ፡ ቦታ ፡ ግዙፎች ፡ የሆኑ ፡ አስደናቂ ፡ የሕንጻ ፡ ግንቦች ፡ ፈርሰው ፡ ስለሚገኙ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ሕዝቦች ፡ እንዳነጿቸው ፡ በምንስ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ተሠሩ ፡ ለማወቅ ፡ ባለመቻሉ ፡ ለታሪክ ፡ መርማሪዎች ፡ ፍቺው ፡ የተሰወረ ፡ ምስጢር ፡ ሆኖባቸዋል ። እንደዚሁም ፡ የጋና ፡ መንግሥት ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ከከፍተኛ ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ደርሶ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ውበቱንና ፡ ገናናነቱን ፡ ታሪክ ፡ መርማሪዎች ፡ እየጠቀሱ ፡ አስደናቂ ፡ ከሆነ ፡ ደረጃ ፡ ደርሶ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ይናገራሉ ።

# ጋንዲና ፡ እንዱስትሪ ።

ጋንዲ ፡ ያውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ እየተነተነ ፡ ስለእያንዳንዱ ፡ ጉዳይ ፡ አስተያየቱን ፡ ሲገልጽ ፡ ህንድ ፡ ኢንዱስትሪን ፡ ማቋቋም ፡ አይገባትም ፡ ብሏል ። ምክንያቱም ፡ ጋንዲ ፡ ኢንዱስትሪ ፡ በሠለጠኑት ፡ አገሮች ፡ ያስከተለውን ፡ ጣጣና ፡ መዘዝ ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ስለሚያውቀውና ፡ ብዙ ፡ ሊቃውንት ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ያደረጉትን ፡ ጥናት ፡ የገለጡትንም ፡ አሳብ ፡ ስላነበበ ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ ህንድ ፡ የኢንዱስትሪን ፡ ጥበብ ፡ የጨበጠች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኀይል ፡ ሲሰማት ፡ በሷ ፡ ላይ ፡ የተሠራባትን ፡ ግፍ ፡ በሌሎች ፡ ሕዝቦች ፡ ላይ ፡ እንዳትሠራ ፡ ነው ።

ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ የሠለጠኑት ፡ ያውሮፓ ፡ ሕዝቦች ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የነዙት ፡ ትምህርት ፡ የጽሕፈትን ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ የሚያስወድድና ፡ የእጅ ፡ ሥራን ፡ የሚያስጠላ ፡ በመሆኑ ፡ የህንድ ፡ ሕዝብ ፡ በተፈጥሮ ፡ የሚኖረው ፡ በእርሻ ፡ ሥራ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ትምህርት ፡ ለሱ ፡ ማስተማር ፡ እንደ ፡ ዐመፅ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ጋንዲ ፡ ጨምሮ ፡ ተናግሯል ።

ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ በዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ለተፈጠረው ፡ ልዩነት ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ኢንዱስትሪ ፡ መሆኑን ፡ ተመልክተናል ።

ሂትለር ፡ ጥቍሮችና ፡ ብጫዎች ፡ ሕዝቦች ፡ በዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ተስፋ ፡ የሌላቸው ፡ በመሆናቸው ፡ እነሱ ፡ ከመሬት ፡ ካርታ ፡ ላይ ፡ ሊሠረዙ ፡ ይገባቸዋል ፡ ሲል ፡ አሳቡን ፡ ገልጧል ። እሱ ፡ ቀንቶት ፡ ድል ፡ ቢያደርግ ፡ ኖሮ ፡ ይህንን ፡ አሳብ ፡ ይፈጽመው ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ አይጠረጠርም ። ሂትለር ፡ ይህን ፡ ቢናገር ፡ የግል ፡ አስተያየቱ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ዋጋ ፡ የለውም ፡ እንል ፡ ይሆናል ። ይህ ፡ በኛ ፡ በኩል ፡ ትልቅ ፡ ስሕተት ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ። ሂትለር ፡ የጀርመን ፡ ሕዝብ ፡ በሙሉ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ባሳብ ፡ የተባበረ ፡ ባይሆን ፡ ኖሮ ፡ የመንግሥቱ ፡ መሪ ፡ ለመሆንና ፡ ያንን ፡ ታይቶ ፡ የማይታወቅ ፡ ታላቅ ፡ ጦርነት ፡ ለማንሣት ፡ እንደማይችል ፡ መዘንጋት ፡ አይገባንም ። ደግሞ ፡ አንድ ፡ የሕዝብ ፡ ጐሣ ፡ ሌላውን ፡ ማጥፋቱና ፡ ከመሬት ፡ ላይ ፡ መሠረዙ ፡ የተለመደ ፡ እንጂ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አይዶለም ። በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ የተከፈለው ፡ ባራት ፡ ዐቢይ ፡ ነገዶች ፡ ነበር ። እነሱም ፡ ነጮች ፤ ጥቍሮች ፤ ብጫዎችና ፡ ቀዮች ፡ ሕዝቦች ፡ ናቸው ። ቀዮች ፡

የሚባሉትን ፡ ባሜሪካ ፡ አገሮች ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩትን ፡ ሕዝቦች ፡ ነጮች ፡ ጨርሰው ፡ አጥፍተዋቸዋል ። ስለዚህ ፡ አሁን ፡ የቀሩት ፡ ሦስት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። ጥቂቶች ፡ ተርፈው ፡ በላቲን ፡ አሜሪካ ፡ ቢገኙ ፡ እነሱም ፡ እንሆ ፡ እየተቀላቀሉና ፡ እየተደባለቁ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ ። ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ በሌሎቹ ፡ የተዋጡ ፡ ሆነው ፡ ከመደምሰስ ፡ በቀር ፡ ዳግመኛ ፡ የልዩነታቸውን ፡ ሁኔታ ፡ አግኝተው ፡ በዚች ፡ ፕላኔት ፡ ላይ ፡ ለመታየት ፡ የማይችሉ ፡ መሆናቸው ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ በዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ኢንዱስትሪ ፡ በባሩድ ፡ ከሚተኰስ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ጋራ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ አደጋ ፡ የፈጠረ ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡ አደጋው ፡ የተሰነዘረባቸው ፡ ሕዝቦች ፡ ጕዳዩን ፡ በጣም ፡ አስበውበት ፡ አስፈላጊውን ፡ ሊያደርጉ ፡ ይገባቸው ፡ ነበር። ይህንንም ፡ በቀላል ፡ መንገድ ፡ ሊፈጽሙት ፡ ይችላሉ ።

የጋንዲን ፡ ምሳሌ ፡ ተከትለው ፡ ባገራችን ፡ የማንሠራውን ፡ ነገር ፡ ከሌላ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ መግዛት ፡ አይገባንም ፡ ብለው ፡ ይህንን ፡ ደንብ ፡ በማጽደቅ ፡ ቢሠሩበት ፡ ኖሮ ፡ ነጮች ፡ የሚመኩበትን ፡ ገናናነት ፡ በሽክላ ፡ እግር ፡ ላይ ፡ የቆመ ፡ ተሰባሪ ፡ ግዙፍ ፡ ሊያደርጉት ፡ ይችላሉ ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጕዳዩ ፡ ዐውቆ ፡ ይፈታል ። የዓለም ፡ መንግሥታትም ፡ የዓለምን ፡ ኤኮኖሚ ፡ ሁኔታ ፡ ለዘለቄታው ፡ የተካከለ ፡ ለማድረግ ፡ በጥበብ ፡ ያስቡበት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ለመፈጸም ፡ መተባበር ፡ ያሻል ። አንድ ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ አገሮች ፡ ቢያደርጉት ፡ በቂ ፡ አይሆንም ። በደካሞች ፡ ሕዝቦች ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ጕድለት ፡ የሥራ ፡ ስንፍና ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ መተባበር ፡ ፈጽሞ ፡ አይሆንላቸውም ። እነሱ ፡ የነጮችን ፡ ሸቀጥ ፡ ካልገዙ ፡ ነጮችም ፡ ከእነሱ ፡ አገር ፡ የሚገኘውን ፡ ሀብት ፡ አይገዟቸውም ፡ ይባል ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ የትኛው ፡ ይበልጥ ፡ ሊጐዳ ፡ ነው ? ደካሞች ፡ አገሮች ፡ ወጣም ፡ ወረደም ፡ የሚቀርባቸው ፡ ዐጕል ፡ ድሎትና ፡ ዐጕል ፡ መጊያጊያጥን ፡ መልመድ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የንግድ ፡ መለዋወጥ ፡ ሊፈጥሩ ፡ ይችላሉ ። ነጮች ፡ ግን ፡ ገበያቸው ፡ ሲቀነስባቸው ፡ የቆሙበት ፡ የሀብት ፡ ተራራ ፡ ተንዶ ፡ ዐዘቅት ፡ ሆኖ ፡ ይውጣቸዋል ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ እንዳይሆንባቸው ፡ ለዚህ ፡ ችግር ፡ አስፈላጊውን ፡ ነገር ፡ ለማድረግ ፡ በቸልተኛነት ፡ ሳይሆን ፡ በቁም ፡ ነገር ፡ ተግተው ፡ መድኀኒቱን ፡ ያገኙለት ፡ ነበር ። አለዚያ ፡ ግን ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ባላቸውና ፡ በሌላቸው ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ እየተራራቀ ፡ ይሄዳል ። ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀሩት ፡ ሕዝቦች ፡ ምንም ፡ ያኽል ፡ ቢደክሙና ፡ ቢጥሩ ፡ ከቀደሟቸው ፡ ሕዝቦች ፡ ጋራ ፡ ሊተካከሉ ፡ አይችሉም ። ዛሬ ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ጥበብ ፡ በኦቶማቲስምና ፡



በአቶም ፡ ኀይል ፡ እየተለወጠ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ ሁኔታ ፡ በመዛወር ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። ይህም ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቅ ፡ ከመሆኑ ፡ በላይ ፡ ጥበቡ ፡ ከፊተኛው ፡ የበለጠ ፡ ጥልቅ ፡ ነው ።

አሁን ፡ የሚደረገውን ፡ ነገር ፡ እስቲ ፡ እንመልከተው ። ከሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ እንሆ ፡ ጀርመን ፡ ባዲስ ፡ ጕልበትና ፡ ባዲስ ፡ ጥበብ ፡ በያይነቱ ፡ ዕቃ ፤ አቶሞቢልና ፡ ሌላም ፡ ሸቀጥ ፡ እየሠራች ፡ የዓለምን ፡ ገበያ ፡ አጥለቅልቃዋለች ። የዓለም ፡ ሕዝቦችም ፡ የበለጠና ፡ የተሻለ ፡ ሆኖ ፡ ስለሚያገኙት ፡ ከሌላው ፡ ይልቅ ፡ የእሷን ፡ ዕቃ ፡ መግዛት ፡ ይፈቅዳሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህንን ፡ ሲያደርጉ ፡ ነገ ፡ እነሱ ፡ የሚጠፉበትን ፡ መሣሪያ ፡ በገዛ ፡ እጃቸው ፡ እንደሚሰጧት ፡ አያስቡም ። ዛሬ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ከመዋጋት ፡ ይልቅ ፡ ማንኛውንም ፡ አገር ፡ ለመጕዳት ፡ ሲፈለግ ፡ ዕቃውን ፡ አለመግዛት ፡ የበለጠ ፡ ጕዳት ፡ የሚያመጣበት ፡ መሆኑን ፡ ተረድተው ፡ ይህን ፡ መሣሪያ ፡ አልተጠቀሙበትም ። ይህ ፡ መሣሪያ ፡ ኀይለኛ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ለደካሞች ፡ ሕዝቦች ፡ እንደሚያገለግል ፡ ተረድቶት ፡ የሠራበት ፡ ጋንዲ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህም ፡ ስለ ፡ ተባለ ፡ ደካሞች ፡ የሆኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ቈራጥነት ፡ አግኝተው ፡ ይህንን ፡ ቢያደርጉ ፡ ዐላማቸው ፡ የቀደሟቸውን ፡ ሕዝቦች ፡ ግሥገሣ ፡ ጥቂት ፡ እንዲገታ ፡ ለማድረግና ፡ ይደርሱባቸው ፡ ዘንድ ፡ ለእነሱ ፡ ጊዜ ፡ በመስጠት ፡ እንዲረዳቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሥልጣኔን ፡ እርምጃ ፡ ለማሰናከል ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ አይገባውም። ለዚህ ፡ ካልሆነ ፡ የሥልጣኔ ፡ ዕንቅፋት ፡ ከመሆን ፡ ቢጠፉም ፡ ባይጠፉም፡ እንደዚሁ ፡ ገባሮች ፡ ሆነው ፡ መኖር ፡ ይሻላቸዋል ።

ሂትለር ፡ ከተናገራቸው ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ከሚገኝባቸው ፡ ቃሎች ፡ አንዱ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ። ታሪክን ፡ ብንመለከት ፡ ማንኛውም ፡ ሕዝብ ፡ ቢሆን ፡ ለሌላው ፡ ሕዝብ ፡ ሥልጣኔን ፡ ሰጥቶ ፡ ራሱን ፡ ሲያስችለው ፡ ታይቶ ፡ አይታወቅም ። አንድ ፡ ሕዝብ ፡ ሠልጥኖ ፡ ራሱን ፡ እንዲችል ፡ ቈራጥነቱ ፤ ትጋቱና ፡ ጕልበቱ ፡ ከገዛ ፡ ራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ፈንቅሎ ፡ እንዲመጣ ፡ ያስፈልጋል ። ሂትለር ፡ የተናገረው ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ በሙሉ ፡ እውነት ፡ ነው ። ጦርነት ፡ ባይኖር ፡ ኖሮ ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ባላስቸገረ ፡ ነበር ።

እስቲ ፡ ይህንን ፡ ጕዳይ ፡ ጠልቀን ፡ እንመልከተው ። የሠለጠኑት ፡ መንግሥታት ፡ ላልሠለጠኑት ፡ አገሮች ፡ ጥቂት ፡ ፋብሪካዎች ፡ እንዲያቋቁሙ ፤ ሕዝባቸውን ፡ ለማስተማር ፡ አንዳንድ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ እንዲከፍቱ ፤ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ድርጅት ፡ እንዲኖራቸው ፡ በሚሠሩላቸው ፡ የእርዳታ ፡ ሥራ ፡ ካለመሠልጠን ፡ አውጥተው ፡ ወደ ፡ መሠል

ጠን ፡ ሊያደርሷቸው ፡ ይችላሉን ? አንድን ፡ ሕዝብ ፡ ሠለጠነ ፡ የሚያሰኙት ፡ የታወቁና ፡ የተወሰኑ ፡ ነገሮች ፡ መሆናቸውን ፡ አንዘንጋ ። ስንት ፡ ሚሊያርድ ፡ ኪሎዋት ፡ የኤሌክትሪክ ፡ ኀይል ፡ እንደሚጨርስ ፡ ስንት ፡ ሚሊዮን ፡ ቶን ፡ ብረት ፡ እንደሚያቀልጥ ፣ በሳይንስ ፡ ግንባር ፡ ቀደም ፡ ከሆኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ጋራ ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ሆኖ ፡ መገኘቱ ፣ እያንዳንዱ ፡ ዜጋ ፡ ባመት ፡ ስንት ፡ ገንዘብ ፡ እንደሚያፈራ ፣ ስንት ፡ ዲቪዚዮን ፡ ወታደር ፡ ለማሰለፍ ፡ እንደሚችል ፣ ጦርነት ፡ ቢመጣበት ፡ በረኃብና ፡ በችግር ፡ ሳይፈታ ፡ ስንት ፡ ዓመት ፡ ራሱን ፡ ችሎ ፡ ለመመከትና ፡ ለመዋጋት ፡ እንደሚችል ፣ ሕዝቡ ፡ መቶ ፡ በመቶ ፡ የተማረ ፡ መሆኑ ፣ እንዳንዱ ፡ ዜጋ ፡ የጦር ፡ ትምህርት ፡ አገልግሎት ፡ መፈጸሙ ፣ እንሆ ፡ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ እየታዩ ፡ ነው ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃው ፡ የሚገመተው ። ከእነዚህ ፡ አንዱ ፡ ከጐደለ ፡ የሥልጣኔው ፡ እድገት ፡ ሙሉ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ። እንግዲህ ፡ ሂትለር ፡ ማንኛውንም ፡ ሕዝብ ፡ ቢሆን ፡ ሌላ ፡ ሕዝብ ፡ ሲያሠለጥ ነው ፡ በታሪክ ፡ ታይቶ ፡ አይታወቅም ፡ ብሎ ፡ሲናገር ፡ በሌላ ፡ ሕዝብ ፡ ርዳታ ፡ ከእነዚህ ፡ ግቦች ፡ የደረሰ ፡ ሕዝብ ፡ አለመኖሩን ፡ ለማሳሰብ ፡ ነው ። ይህ ፡ የማይካድ ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነው ። አንድ ፡ ሕዝብ ፡ ለመሠልጠን ፡ የሚችል ፡ ሲሆን ፡ የሌላውን ፡ ሕዝብ ፡ ርዳታ ፡ ማግኘት ፡ አያስፈልገውም ። ለመሠልጠን ፡ የማይችል ፡ ሲሆን ፡ ደግሞ ፡ የሌላው ፡ ሕዝብ ፡ ርዳታ ፡ ለምንም ፡ አይጠቅመውም ። ሂትለር ፡ ከተናገራቸው ፡ ቃሎች ፡ ደራሲው ፡ ሊጠቅሰው ፡ የሚወድ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አለ ። በያንዳንዱ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ አስተያየቱን ፡ ሲገልጽ ፡ በእሱ ፡ ግምት ፡ የተባበሩት ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥታት ፡ በአይሁዶችና ፡ በጥቍሮች ፡ ምክንያት ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ የሚጓዙ ፡ ናቸው ። መስኮብ ፡ ኰሚኒስት ፡ በመሆኗ ፡ የሥልጣኔ ፡ ጠንቅና ፡ የዓለም ፡ መቅሠፍት ፡ ሆና ፡ ትቈጠራለች ፡ እንጂ ፡ በሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ደረጃ ፡ ገብታ ፡ የምትገመት ፡ አይደለችም ። እንግሊዝ ፡ መጥፊያዋ ፡ ሰዓት ፡ የተቃረበ ፡ አገር ፡ ናት ። ፈረንሳይ ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ተስፋ ፡ ሊጣልባት ፡ የማትችል ፡ የወደቀች ፡ አገር ፡ ነች ። ኢጣሊያ ፡ የራሷ ፡ ደካማነት ፡ ዐቅመ ፡ ቢስነት ፡ ከራሷ ፡ አልፎ ፡ ለወዳጇ ፡ የሚተርፍ ፡ በመሆኑ ፡ ጀርመንን ፡ ድል ፡ ከመሆን ፡ ያደረሳት ፡ ኢጣሊያን ፡ የጦር ፡ ጓደኛ ፡ በማድረጓ ፡ ነው ። የላቲን ፡ አሜሪካ ፡ አገሮች ፡ ምንም ፡ ሀብት ፡ ቢኖራቸውና ፡ አገራቸውን ፡ አሳምረው ፡ ቢታዩ ፡ ነፍስ ፡ እንደ ሌላቸው ፡ በድን ፡ አካላት ፡ የሚቈጠሩ ፡ ናቸው ። የሥልጣኔን ፡ ሞገስ ፡ በሙሉ ፡ ተጐናጽፈው ፡ የሚታዩ ፡ ጀርመንና ፡ ጃፓን ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። ሂትለር ፡ በሌሎቹ ፡ ታላላቅ ፡ መንግሥታት ፡ ላይ ፡ የተናገረው ፡ ይህ ፡ የነቀፌታና ፡ የንቀት ፡ ንግግር ፡ እሱን ፡ ከጥፋት ፡ ላይ ፡ የጣለው ፡ ስሕተት ፡ መሆኑ ፡ ግልጥ ፡ ነው ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ስንመለከተው ፡ ግን ፡



ጃፓን ፡ በመላው ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ (ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ በሂትለር ፡ ዘንድ ፡ እንኳ) ፡ ያገኘችው ፡ ግምት ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መሆኑን ፡ ይገልጥልናል ።

የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ከምቾትና ፡ ከሕክምና ፡ የተነሣ ፡ ቍጥራቸው ፡ እየጨመረ ፡ በመሄዱ ፡ በተለየም ፡ በእስያ ፡ ሕዝቦች ፡ በኩል ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ለዓለም ፡ ትልቅ ፡ ችግር ፡ የሚፈጥር ፡ መሆኑን ፡ የኤኮኖሚንና ፡ የሶሲዮሎዢን ፡ ሁኔታ ፡ የሚያጠኑ ፡ ሊቃውንት ፡ እነ ፡ ቲቦር ፡ ሜንድ ፣ እነ ፡ ጋስፓር ፣ እነ ፡ ሃክስሌ ፣ እነ ፡ ሲግፍሪድ ፣ እነ ፡ ኖኤል ፡ ድሮጋ ፣ ሌሎችም ፡ በጻፏቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ተገልጦ ፡ ይገኛል ። ቍጥራቸው ፡ እንኳንስ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ጨምሮ ፣ ይቅርና ፡ የእስያ ፡ ሕዝቦች ፡ አሁን ፡ በሚገኙበት ፡ ሁኔታም ፡ ቢሆን ፡ ከመራባቸውና ፡ ከመቸገራቸው ፡ የተነሣ ፡ እየተሰደዱ ፡ የሚሄዱበት ፡ አገር ፡ አጥተው ፡ በመፈለግ ፡ ላይ ፡ ናቸው ። ለምሳሌ ፣ ህንዶች ፡ በብዙ ፡ የአፍሪቃ ፡ አገሮች ፡ እንደ ፡ ዋዛ ፡ ገብተው ፡ ከተሰገሰጉ ፡ በኋላ ፡ አሁን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ጠያቂዎች ፡ ሆነው ፡ ጣጣ ፡ ፈጥረዋል ። ለዚህ ፡ ነገር ፡ ምክንያት ፡ የሆኑት ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉት ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ። በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ በሽታዎች ፡ ረኃብ ፣ ሌሎችም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ተውሳኮች ፡ በተለየ ፡ የሕዝባቸው ፡ ቍጥር ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ በሚታየው ፡ በእስያ ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ እየዘመቱባቸው ፡ የመሬቱ ፡ ሀብትና ፡ የሕዝቡ ፡ ቍጥር ፡ ተመዛዛኝ ፡ እንዲሆን ፡ ያስተካክሉት ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ ግን ፡ እነሱን ፡ በዘመናዊ ፡ ሕክምና ፡ በእነ ፡ አንቲቢዮቲክ ፡ በቀላሉ ፡ ለማሸነፍ ፡ ተችሏል ። እንደዚሁም ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ በሚባለው ፡ ዘመን ፡ አመጣሽ ፡ በሆነው ፡ ፈሊጥ ፡ መሠረት ፡ ሁሉም ፡ የኑሮውን ፡ ደረጃ ፡ ካሜሪካ ፡ ሕዝብ ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ጋራ ፡ እያነጣጠረ ፡ በምቾትና ፡ በተድላ ፡ ለመኖር ፡ ፈላጊ ፡ ነው ። እንደ ፡ ቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ ከሚወለዱት ፡ ልጆች ፡ የሚበልጡት ፡ መሞታቸው ፡ ቀረ ። ዛሬ ፡ እነ ፡ ቺንን ፣ እነ ፡ ህንድን ፣ እነ ፡ ጃፓንን ፣ እነ ፡ ግብጽን ፡ ለገጠማቸው ፡ ሁከት ፡ ምክንያቱ ፡ ይህ ፡ የሕዝብ ፡ ብዛት ፡ ነው ። ማልቱስ ፡ (Malthus) የተባለው ፡ የኤኮኖሚ ፡ ሊቅ ፡ ያስተማረው ፡ ትምህርት ፡ ባለፉት ፡ ዘመናት ፡ ያረጀ ፡ መስሎ ፡ ታይቶ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ። የእሱ ፡ (ቴዎሪ) ፡ ትምህርት ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ፣ የያንዳንዱ ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ በ፳፭ ፡ ዓመት ፡ ዕጥፍ ፡ እየሆነ ፡ ይሄዳል ። ለኑሮ ፡ ተፈላጊ ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ በተለየም ፡ ምግብ ፡ የማይለወጥ ፣ የማይጨምር ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡ የሰዎች ፡ ብዛት ፡ ግን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ እየጨመረ ፡ ያድራል ። የመሬት ፡ ስፋት ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ያው ፡ መሆኑ ፡ የማይካድ ፡ ነው ። ለኑሮ ፡ ተፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ እንዲበረክት ፡ ለማድረግ ፡ ከቶ ፡ በምንም ፡ መንገድ ፡

የሚቻል ፡ አይዶለም ። ይህም ፡ በሕዝብ ፡ ብዛትና ፡ በምግብ ፡ መካከል ፡
ሚዛን ፡ እንዲኖር ፡ ለማድረግ ፡ አይቻልም ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህንን ፡ ለማ
ስተካከል ፡ የሚችሉ ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። ባንድ ፡ በኩል ፡
ረኃብና ፡ በሽታ ፡ ሲሆኑ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ጦርነት ፡ ነው ። ረኃብና ፡ በሽታ ፡
ከኑሮ ፡ ጕደሎነት ፡ ከድኽነትና ፡ ከችግር ፡ የሚመነጩ ፡ ከሥነ ፡ ፍጥ
ረት ፡ ሕግ ፡ የሚመጡ ፡ ሲሆን ፡ ጦርነት ፡ ደግሞ ፡ መሬትን ፡ ለመሻማት ፡
በሰዎች ፡ መካከል ፡ የሚደረግ ፡ ትግል ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ለዚያም ፡
ሆነ ፡ ለዚህ ፡ ምክንያቱ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የሕዝብ ፡ ቍጥር ፡ መብዛት ፡ ሆኖ ፡
ይገኛል ። ማልቱስ ፡ ይህንን ፡ አሳብ ፡ ሲገልጽ ፡ ለትምህርቱ ፡ እንደ ፡ መዝ
ጊያ ፡ አድርጎ ፡ ያቀረበው ፡ የሚያሰቅቅ ፡ ቃል ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተው ፡
ነው ፤

ከሱ ፡ በፊት ፡ ተወልደው ፡ የሚገኙ ፡ ሰዎች ፡ በቀዳሚነታቸው ፡
ስፍራውን ፡ ይዘውት ፡ በሚገኙበት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ በኋላ ፡ ጊዜ ፡
የሚመጣ ፡ ልጅ ፡ ወላጆቹ ፡ መግበው ፡ ሊያሳድጉት ፤ አስተዳዳሪዎቹ ፡
የሆኑት ፡ ባለሥልጣኖችም ፡ እንጀራ ፡ ሊያገኝ ፡ የሚችልበትን ፡ ሥራ ፡ ሊ
ፈጥሩለት ፡ የማይችሉ ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ልጅ ፡ አብሉኝ ፤ አጠ
ጡኝ ፤ አልብሱኝ ፡ ብሎ ፡ ለማስቸገር ፡ ምንም ፡ መብት ፡ የለውም ። እሱ ፡
በዚች ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ትርፍ ፡ ፍጡር ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠር ፡ ነውና ።
ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ (nature) አሰናድታ ፡ በዘረጋችው ፡ በታላቁ ፡ የድግስ ፡
ማእድ ፡ ላይ ፡ ለሱ ፡ የሚሆን ፡ ቦታ ፡ አልተመደበለትም ። ስለዚህ ፡ ሥነ ፡
ፍጥረት ፡ ወደ ፡ መጣበት ፡ ቦታ ፡ እንዲመለስ ፡ (ማለት ፡ እንዲሞት) ፡
ትመክረዋለች ። እንቢ ፡ ቢል ፡ ግን ፡ በሽታን ፤ ረኃብን ፤ መሣሪያ ፡ አድ
ርጋ ፡ ያስገዳጅነት ፡ ሥራዋን ፡ ያለ ፡ ርኅራኄ ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ትፈጽምበታ
ለች ። የእስያ ፡ ሕዝቦች ፡ ቍጥራቸው ፡ እየበረከተ ፡ ሲሄድ ፡ የእርሻን ፡
ሥራ ፡ ለማስፋፋትና ፡ ለማሻሻል ፡ አስፈላጊውን ፡ ነገር ፡ ባለማድረጋ
ቸው ፤ እንዲሁም ፡ በጠቅላላው ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሥራ ፡
በጣም ፡ ሲስፋፋ ፡ የእርሻን ፡ ሥራ ፡ እየጠበበ ፡ እንዲሄድ ፡ ስላደረገው ፡
እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ምክንያቶች ፡ ዓለም ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ የገጠማትን ፡ ሥ
ጋት ፡ ይበልጥ ፡ የጠነከረ ፡ አድርገውታል ። እንግዲህ ፡ ማልቱስ ፡ የተናገረው ፡
ነገር ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አሁን ፡ አዲስ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡
ነው ። መዘዙም ፡በዚህ ፡ ብቻ ፡ የማይቆም ፡ መሆኑን ፡ ልንገነዘበው ፡ የሚ
ያስፈልግ ፡ ነው ።

ከአርባ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ አሁን ፡ ሁለት ፡ ሚሊያርድ ፡ ተኩል ፡ የሆ
ነው ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ቍጥር ፡ ከስድስትና ፡ ከሰባት ፡ ሚሊያርድ ፡ እን
ደሚደርስ ፡ ተገምቷል ። አርባ ፡ ዓመት ፡ ሩቅ ፡ አይዶለም ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡



ሺን ፡ ባውሮፓ ፡ ሥልጣኔ ፡ በሙሉ ፡ ራሷን ፡ የቻለች ፡ እንደምትሆን ፡
አይጠረጠርም ።

በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የተባበሩት ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ይህንን ፡ መድ
ረሻ ፡ የሚያጣውን ፡ የእስያን ፡ ሕዝብ ፡ ከወዴት ፡ ወስዶ ፡ ማፍሰስ ፡ እን
ደሚቻል ፡ በሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ ዘዴ ፡ መፈለግ ፡ ግዴታ ፡ ይሆንባቸዋል ።
ኒውዚላንድና ፡ አስትራሊ ፡ በሚያሠጋ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ይወድቃሉ ።
በሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ ለጕዳዩ ፡ ብልኀት ፡ ሳይገኝለት ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
ግን ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ በቀለም ፡ እየተለዩ ፡ ጦርነት ፡ ከሚዋጉበት ፡
ዘመን ፡ ላይ ፡ ይደርሳሉ ። ምሕረት ፡ የሌለው ፡ መተላለቅ ፤ የመጨረሻው ፡
የሕዝቦች ፡ የኑሮ ፡ ትግል ፤ የግዙፎች ፡ ውጊያ ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ይፈጸ
ማል ። ያ ፡ ጦርነት ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ በዚች ፡ ፕላኔት ፡ ላይ ፡ እን
ዴት ፡ ያለ ፡ ትርኢት ፡ ይታይ ፡ ይሆን ? በዮሐንስ ፡ ራእይ ፡ ተጽፎ ፡ የሚ
ገኘውን ፡ የመሰለ ፡ እንደሚሆን ፡ አይጠረጠርም ። ያፍሪቃ ፡ ሕዝቦች ፡
ቍጥራቸው ፡ ጥቂት ፡ ሆኖ ፡ ሰፊ ፡ መሬት ፡ ይዘዋል ፡ እየተባሉ ፡ ይታማሉ።
ስለዚህ ፡ ይህ ፡ አደጋ ፡ በጣም ፡ የሚያሠጋው ፡ ለእነሱ ፡ ነው ። ከዚህም ፡
በቀር ፡ ይህ ፡ ጦርነት ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማንኛውም ፡ ሕዝብ ፡ ቢሆን ፡
ገለልተኛ ፡ ለመሆን ፡ ስለማይችል ፡ አፍሪቃውያን ፡ ለብቻቸው ፡ እንዳይ
ሆኑ ፡ ብዛታቸውም ፡ ሆነ ፡ የሥልጣኔያቸው ፡ ድርጅት ፡ የሚፈቅድላቸው ፡
ባለመሆኑ ፡ ከሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ መርጠው ፡ካንዱ ፡ ጋራ ፡ መተባበር ፡ ግዴታ
ሆኖ ፡ ያገኙታል ። ወይም ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ጃፓንና ፡ ሺን ፡ እንደ ፡
ተዋጉ ፡ ሁሉ ፡ የእስያ ፡ ሕዝቦች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይተላለቃሉ ። ዓለ
ምን ፡ ከዚህ ፡ አደጋ ፡ ሊያድናት ፡ የሚችል ፡ በተባበሩት ፡ የዓለም ፡ መን
ግሥታት ፡ ድርጅት ፡ አማካይነት ፡ በሰላም ፡ መንገድ ፡ አስቀድሞ ፡ አንድ፡
ዘዴ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ እንደሚወራው ፡ ሁሉ ፡ ሳይንስ ፡
ሀብት ፡ ለማፍራት ፡ በቀላል ፡ መንገድ ፡ የሚቻልበትን ፡ ጥበብ ፡ የፈጠ
ረች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

የሚቻል ፡ አይዶለም ። ይህም ፡ በሕዝብ ፡ ብዛትና ፡ በምግብ ፡ መካከል ፡
ሚዛን ፡ እንዲኖር ፡ ለማድረግ ፡ አይቻልም ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህንን ፡ ለማ
ስተካከል ፡ የሚችሉ ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። ባንድ ፡ በኩል ፡
ረኃብና ፡ በሽታ ፡ ሲሆኑ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ጦርነት ፡ ነው ። ረኃብና ፡ በሽታ ፡
ከኑሮ ፡ ጕደሎነት ፡ ከድኽነትና ፡ ከችግር ፡ የሚመነጩ ፡ ከሥነ ፡ ፍጥ
ረት ፡ ሕግ ፡ የሚመጡ ፡ ሲሆን ፡ ጦርነት ፡ ደግሞ ፡ መሬትን ፡ ለመሻማት ፡
በሰዎች ፡ መካከል ፡ የሚደረግ ፡ ትግል ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ለዚያም ፡
ሆነ ፡ ለዚህ ፡ ምክንያቱ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የሕዝብ ፡ ቍጥር ፡ መብዛት ፡ ሆኖ ፡
ይገኛል ። ማልቱስ ፡ ይህንን ፡ አሳብ ፡ ሲገልጽ ፡ ለትምህርቱ ፡ እንደ ፡ መዝ
ጊያ ፡ አድርጎ ፡ ያቀረበው ፡ የሚያስቅቅ ፡ ቃል ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተው ፡
ነው ፤

ከሱ ፡ በፊት ፡ ተወልደው ፡ የሚገኙ ፡ ሰዎች ፡ በቀዳሚነታቸው ፡
ስፍራውን ፡ ይዘውት ፡ በሚገኙበት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ በኋላ ፡ ጊዜ ፡
የሚመጣ ፡ ልጅ ፡ ወላጆቹ ፡ መግበው ፡ ሊያሳድጉት ፤ አስተዳዳሪዎቹ ፡
የሆኑት ፡ ባለሥልጣኖችም ፡ እንጀራ ፡ ሊያገኝ ፡ የሚችልበትን ፡ ሥራ ፡ ሊ
ፈጥሩለት ፡ የማይችሉ ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ልጅ ፡ አብሉኝ ፤ አጠ
ጡኝ ፤ አልብሱኝ ፡ ብሎ ፡ ለማስቸገር ፡ ምንም ፡ መብት ፡ የለውም ። እሱ ፡
በዚች ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ትርፍ ፡ ፍጡር ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠር ፡ ነውና ።
ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ (nature) አሰናድታ ፡ በዘረጋችው ፡ በታላቁ ፡ የድግስ ፡
ማእድ ፡ ላይ ፡ ለሱ ፡ የሚሆን ፡ ቦታ ፡ አልተመደበለትም ። ስለዚህ ፡ ሥነ ፡
ፍጥረት ፡ ወደ ፡ መጣበት ፡ ቦታ ፡ እንዲመለስ ፡ (ማለት ፡ እንዲሞት) ፡
ትመክረዋለች ። እንቢ ፡ ቢል ፡ ግን ፡ በሽታን ፤ ረኃብን ፤ መሣሪያ ፡ አድ
ርጋ ፡ ያስገዳጅነት ፡ ሥራዋን ፡ ያለ ፡ ርኅራኄ ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ትፈጽምበታ
ለች ። የእስያ ፡ ሕዝቦች ፡ ቍጥራቸው ፡ እየበረከተ ፡ ሲሄድ ፡ የእርሻን ፡
ሥራ ፡ ለማስፋፋትና ፡ ለማሻሻል ፡ አስፈላጊውን ፡ ነገር ፡ ባለማድረጋ
ቸው ፤ እንዲሁም ፡ በጠቅላላው ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሥራ ፡
በጣም ፡ ሲስፋፋ ፡ የእርሻን ፡ ሥራ ፡ እየጠበበ ፡ እንዲሄድ ፡ ስላደረገው ፡
እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ምክንያቶች ፡ ዓለም ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ የገጠማትን ፡ ሥ
ጋት ፡ ይበልጥ ፡ የጠነከረ ፡ አድርገውታል ። እንሆ ፡ ማልቱስ ፡ የተናገረው ፡
ነገር ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አሁን ፡ አዲስ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡
ነው ። መዘዙም ፡ በዚህ ፡ ብቻ ፡ የማይቆም ፡ መሆኑን ፡ ልንገነዘበው ፡ የሚ
ያስፈልግ ፡ ነው ።

ከአርባ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ አሁን ፡ ሁለት ፡ ሚሊያርድ ፡ ተኩል ፡ የሆ
ነው ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ቍጥር ፡ ከስድስትና ፡ ከሰባት ፡ ሚሊያርድ ፡ እን
ደሚደርስ ፡ ተገምቷል ። አርባ ፡ ዓመት ፡ ሩቅ ፡ አይዶለም ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡



ቪን ፡ ባውሮፓ ፡ ሥልጣኔ ፡ በሙሉ ፡ ራሷን ፡ የቻለች ፡ እንደምትሆን ፡
አይጠረጠርም ።

በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የተባበሩት ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ይህንን ፡ መድ
ረሻ ፡ የሚያጣውን ፡ የእስያን ፡ ሕዝብ ፡ ከወዴት ፡ ወስዶ ፡ ማፍሰስ ፡ እን
ደሚቻል ፡ በሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ ዘዴ ፡ መፈለግ ፡ ግዴታ ፡ ይሆንባቸዋል ።
ኒውዚላንድና ፡ አስትራሊ ፡ በሚያሠጋ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ይወድቃሉ ።
በሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ ለጕዳዩ ፡ ብልኀት ፡ ሳይገኝለት ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
ግን ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ በቀለም ፡ እየተለዩ ፡ ጦርነት ፡ ከሚዋጉበት ፡
ዘመን ፡ ላይ ፡ ይደርሳሉ ። ምሕረት ፡ የሌለው ፡ መተላለቅ ፤ የመጨረሻው ፡
የሕዝቦች ፡ የኑሮ ፡ ትግል ፤ የግዙፎች ፡ ውጊያ ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ይፈጸ
ማል ። ያ ፡ ጦርነት ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ በዚች ፡ ፕላኔት ፡ ላይ ፡ እን
ዴት ፡ ያለ ፡ ትርኢት ፡ ይታይ ፡ ይሆን ? በዮሐንስ ፡ ራእይ ፡ ተጽፎ ፡ የሚ
ገኘውን ፡ የመሰለ ፡ እንደሚሆን ፡ አይጠረጠርም ። ያፍሪቃ ፡ ሕዝቦች ፡
ቍጥራቸው ፡ ጥቂት ፡ ሆኖ ፡ ሰፊ ፡ መሬት ፡ ይዘዋል ፡ እየተባሉ ፡ ይታማሉ።
ስለዚህ ፡ ይህ ፡ አደጋ ፡ በጣም ፡ የሚያሠጋው ፡ ለእነሱ ፡ ነው ። ከዚህም ፡
በቀር ፡ ይህ ፡ ጦርነት ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማንኛውም ፡ ሕዝብ ፡ ቢሆን ፡
ገለልተኛ ፡ ለመሆን ፡ ስለማይችል ፡ አፍሪቃውያን ፡ ለብቻቸው ፡ እንዳይ
ሆኑ ፡ ብዛታቸውም ፡ ሆነ ፡ የሥልጣኔያቸው ፡ ድርጅት ፡ የሚፈቅድላቸው ፡
ባለመሆኑ ፡ ከሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ መርጠው ፡ ካንዱ ፡ ጋራ ፡ መተባበር ፡ ግዴታ
ሆኖ ፡ ያገኙታል ። ወይም ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ጃፓንና ፡ ቪን ፡ እንደ ፡
ተዋጉ ፡ ሁሉ ፡ የእስያ ፡ ሕዝቦች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይተላለቃሉ ። ዓለ
ምን ፡ ከዚህ ፡ አደጋ ፡ ሊያድናት ፡ የሚችል ፡ በተባበሩት ፡ የዓለም ፡ መን
ግሥታት ፡ ድርጅት ፡ አማካይነት ፡ በሰላም ፡ መንገድ ፡ አስቀድሞ ፡ አንድ ፡
ዘዴ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ እንደሚወራው ፡ ሁሉ ፡ ሳይንስ ፡
ሀብት ፡ ለማፍራት ፡ በቀላል ፡ መንገድ ፡ የሚቻልበትን ፡ ጥበብ ፡ የፈጠ
ረች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

# ጋንዲና ፡ ሙስጠፋ ፡ ከማል ።

ጋንዲ ፡ ሀንድ ፡ ነጻ ፡ ከወጣች ፡ በኋላ ፡ ቶሎ ፡ ባይሞት ፡ ኖሮ ፡ አገ
ሪቱ ፡ ነጻነቷን ፡ ካገኘች ፡ በኋላ ፡ የገጠሟትን ፡ ጣጣዎች ፡ ለመውጣት ፡
ምን ፡ ማድረግ ፡ እንደሚገባት ፡ ስለ ፡ ተደረገው ፡ ጥናት ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡
መንገድ ፡ ይከተል ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ማወቅ ፡ ለታሪክ ፡መርማሪ፡ የሚያጓጓ ፡
ነገር ፡ ነው ። አንድን ፡ አገር ፡ ለማሠልጠን ፡ ያለበትን ፡ ጣጣ ፡ ለመረዳት ፡
ከከማል ፡ ፓሻ ፡ ታሪክ ፡ የተሻለ ፡ አይገኝም ። ስለዚህ ፡ ነው ፡ የከማልን ፡
ታሪክ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ልዩ ፡ ምዕራፍ ፡ የሰጠነው ።

ከዚህ ፡ በፊት ፡ የጋንዲንና ፡ የቪቪካናንዳን ፡ አሳቦች ፡ እያስተያየንና ፡
እያመዛዘንን ፡ ልዩነታቸውን ፡ ከተረዳን ፡ በኋላ ፡ ምክንያቱን ፡ በመዘር
ዘር ፡ ጥናት ፡ አድርገናል ። ይኸውም ፡ ስለ ፡ ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ያላቸ
ውን ፡ ፍርድ ፡ ለማወቅ ፡ ነው ። ጋንዲ ፡ አገሩን ፡ በዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡
መንገድ ፡ እንድትመራ ፡ ለማድረግ ፡ አስቦ ፡ ይህንኑ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ለማ
ዋል ፡ ቈርጦ ፡ ቢነሣ ፡ ኖሮ ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ ይገጥመው ፡ ነበር ፡ ብለን ፡
ተናግረናል ። ሊገጥሙት ፡ የሚችሉት ፡ ችግሮችና ፡ ዕንቅፋቶች ፡ እንደ ፡
ምን ፡ ያሉ ፡ ናቸው ? ሲባል ፡ እነዚህኑ ፡ ለማወቅ ፡ ሁሉንም ፡ በሙስጠፋ ፡
ከማል ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ እናገኘዋለን ።

ጋንዲ ፡ ጦርነትና ፡ ጭካኔን ፡ በመጥላት ፡ ሰውን ፡ ከመግደል ፡ በሰው፡
እጅ ፡ መሞት ፡ ይሻላል ፡ ብሎ ፡ በፍቅርና ፡ በሰላም ፡ መንገድ ፡ ታገለ ።
የሀንድ ፡ ሕዝብ ፡ ያባቶቹን ፡ ሃይማኖት ፡ ያባቶቹን ፡ ልማድ ፡ ያባቶቹን ፡
ባህል ፡ አክብሮ ፡ የዘመኑን ፡ ጥበብ ፡ እንዲጠላ ፤ ፋብሪካንና ፡ ዘመናዊውን፡
ትምህርት ፡ እንዲንቅ ፤ ባገሩ ፡ ሥልጣኔ ፡ እንዲኰራ ፡ መከረው ። ይህ
ንኑም ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በዝርዝር ፡ ተመልክተነዋል ።

ጋንዲ ፡ የኀይል ፡ ሥራና ፡ ደም ፡ መፋሰስን ፡ ጠልቶ ፡ ሰላማዊና ፡
ፍቅራዊ ፡ የሆነውን ፡ ይህንን ፡ መንገድ ፡ የተከተለው ፡ ለፖለቲካው ፡
አካሄድ ፡ የሚጠቅመው ፡ ሆኖ ፡ ስላገኘው ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡
ይተረጕሙታል ። ሀንድ ፡ እንግሊዞችን ፡ በኀይል ፡ ለማስወጣት ፡ ስለማ
ትችል ፡ በሰላም ፡ መንገድ ፡ መታገልን ፡ በመምረጡ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ያስ
ባሉ ። ይህ ፡ የተሳሳተ ፡ አስተያየት ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ የጋንዲን ፡ ታሪክ
በሚገባ ፡ አለማወቅ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ። ጋንዲ ፡ ራሱን ፡ የማያታልል ፡
ሌሎችንም ፡ ለማታለል ፡ የማያስብ ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

በ (utilitarisme) ላይ ፡ የቆመ ፡ ፖሊቲካ ፡ ለመፍጠር ፡ ክብር ፡ ያላት ፡ ነፍሱ ፡ አትፈቅድለትም ። ስለዚህ ፡ የተከተለው ፡ አሳብና ፡ የተናገራቸው ፡ ቃሎች ፡ በሙሉ ፡ ልቡ ፡ ያመነባቸው ፡ ናቸው ። ይህ ፡ ባይሆን ፡ ኖሮ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ ክብር ፡ የተሰጠውን ፡ ታሪክና ፡ ዝና ፡ ሊፈጥር ፡ ሥራውም ፡ የተቃና ፡ ሊሆንለት ፡ አይችልም ፡ ነበር ።

ጋንዲ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ትግል ፡ በፈጸመበት ፡ ዘመን ፡ በቱርክ ፡ አገር ፡ ያለው ፡ የሕዝብ ፡ መሪ ፡ ከዚህ ፡ የተለየ ፡ የሆነውን ፡ መንገድ ፡ ተከትሎ ፡ ይገኛል ። እሱም ፡ ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ ነው ። ይህ ፡ ሰው ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ጋንዲ ፡ አገሩን ፡ ማለት ፡ ቱርክን ፡ ይወዳታል ። ዘመናዊውን ፡ ትምህርት ፡ በጦር ፡ አካዴሚ ፡ ውስጥ ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ ተምሯል ። ለተወለደበት ፡ አገር ፡ ያለው ፡ ፍቅር ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ ነው ፡ አይባልም ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ላገሬ ፡ የሚበጃት ፡ ነገር ፡ ምንድነው ? ብሎ ፡ አሰበ ። በዚህ ፡ አሳብ ፡ በጣም ፡ ተጨነቀበት ። ታሪክን ፡ መርምሮ ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ዓለም ፡ የምትገኝበትን ፡ ሁኔታ ፡ አስተውሎ ፡ ካመዛዘነ ፡ በኋላ ፡ አሳቡን ፡ ወሰነ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህንን ፡ እሱ ፡ ያመነበትን ፡ አሳብ ፡ ከፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ ዕንቅፋቶች ፡ ነበሩበት ። እነዚህም ፡ ዕንቅፋቶች ፡ በሁለት ፡ ይከፈላሉ ። እነሱም ፡ ከውጭ ፡ መንግሥታት ፡ በኩል ፡ የተፈጠሩ ፡ ዕንቅፋቶችና ፡ ባገሩ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ዕንቅፋቶች ፡ ነበሩ ። እነዚህን ፡ በሁለት ፡ የተከፈሉ ፡ ችግሮች ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ለቱርክ ፡ ይበጃታል ፡ ብሎ ፡ ያመነበትን ፡ መንገድ ፡ እንድትከተል ፡ ለማድረግ ፡ ሲያስብ ፡ የውጭ ፡ ጠላቶቹን ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ድል ፡ ለማድረግና ፡ የውስጥ ፡ ዕንቅፋቶቹን ፡ ለማጥፋት ፡ ጦርነትንና ፡ ጭካኔን ፡ መሣሪያ ፡ አድርጎ ፡ ሊሠራባቸው ፡ አስፈላጊና ፡ ግዴታ ፡ ሆኖበታል ።

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ተግባሩን ፡ ሲያከናውን ፡ የደረሰበትን ፡ ችግርና ፡ የተወጣውን ፡ ዕንቅፋት ፡ ስንመለከተው ፡ ሕዝብን ፡ ለማሠልጠንና ፡ ዘመናዊውን ፡ መንፈስ ፡ ተከትሎ ፡ በሥራት ፡ እንዲሄድ ፡ ለማድረግ ፡ ሲታሰብ ፡ ያለው ፡ ችግር ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ አዳጋች ፡ ነገር ፡ መሆኑን ፡ ይገልጥልናል ። ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ ለቱርክ ፡ የሚበጃት ፡ አሳብ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ገና ፡ ተራ ፡ የጦር ፡ መኰንን ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ዐቅዱን ፡ ባቀረበ ፡ ጊዜ ፡ የሚሰማው ፡ ሰው ፡ አላገኘም ። የመጀመሪያው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ከፈነዳ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ቱርክ ፡ ከጀርመን ፡ ጋራ ፡ ሆና ፡ ስትዋጋ ፡ እንደዚሁ ፡ የሚበጀውን ፡ ነገር ፡ እሱ ፡ ሲያመለክት ፡ ሁሉም ፡ በየበኩላቸው ፡ የማይጠቅም ፡ አሳብ ፡ ተከትለው ፡ እሱን ፡ ሊሰሙት ፡ አልፈለጉም ። ቱርክ ፡ ድል ፡ ሆና ፡ በድል ፡ አድራጊዎች ፡ እጅ ፡ ስትገባ ፡ የተከፋፈለች ፡ ሆና ፡ ከታላላቆቹ ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ እግር ፡ ላይ ፡ ወድቃ ፡ የምትዋረድበትን ፡ የዕርቅ ፡



ውል ፡ ለመፈራረም ፡ የመንግሥቱ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የተዘጋጁ ፡ ሆነው ፡ ተገኙ ። እሱ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ተቃውሞ ፡ በራሱ ፡ አላፊነትና ፡ በራሱ ፡ ቈራጥነት ፡ ብቻ ፡ ጦርነቱን ፡ ለመቀጠል ፡ አሰቦ ፡ ተነሣ ። ይህንንም ፡ ሲያደርግ ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ የመንግሥቱን ፡ አሳብ ፡ ተቃዋሚ ፡ በመሆኑ ፡ ካገሩ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጋራ ፡ ሲጋጭ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ጀርመንን ፡ ድል ፡ ካደረጓት ፡ የጦር ፡ ጓደኞች ፡ ጋራ ፡ ጠብን ፡ አበቀለ ። እነሱም ፡ እንግሊዝ ፤ ፈረንሳይ ፤ ኢጣልያ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ጀርመንን ፡ የሚያኽል ፡ ታላቅ ፡ መንግሥት ፡ ድል ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ቱርክን ፡ ለማጥፋት ፡ ያቅታቸዋል ፡ ብሎ ፡ ማሰብ ፡ ከእብደት ፡ የሚቈጠር ፡ ሆኖ ፡ የሚገመት ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ ዕድል ፡ የረዳው ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ ማመን ፡ አለብን ። ራስኽን ፡ ርዳ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ይረዳኻል ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ርዳታ ፡ ባይጨመርበት ፡ ኖሮ ፡ ከታላላቆቹ ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ጋራ ፡ ያበቀለው ፡ ጠብ ፡ ገደል ፡ ሊጨምረው ፡ ይችል ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እነሱ ፡ ትልቁ ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ረዥም ፡ ጊዜ ፡ የወሰደ ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ ውጊያ ፡ ስልችቷቸው ፡ ሕዝባቸው ፡ በመናፈቅ ፡ ይመኘው ፡ የነበረውን ፡ ሰላም ፡ በመስጠትና ፡ የጠፋውን ፡ ንብረቱን ፡ ለማቋቋም ፡ የሚቻልበትን ፡ መንገድ ፡ በማደራጀት ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ ጦርነቱን ፡ ለመቀጠል ፡ ቈርጦ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ የግጦር ፡ ለማስከተት ፡ ስላልፈቀዱ ፡ ጉዳዩን ፡ ቬኒዜሎስ ፡ ለተባለው ፡ የግሪክ ፡ የጦር ፡ መሪ ፡ አሳልፈው ፡ በመስጠት ፡ አሳባቸውን ፡ ወሰኑ ። ቱርክ ፡ በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ የጀርመን ፡ የጦር ፡ ጓደኛ ፡ ሆና ፡ ስትዋጋ ፡ እንግሊዝና ፡ ፈረንሳይ ፡ ወደ ፡ ቱርክ ፡ አገር ፡ ልከውት ፡ ከነበረው ፡ ጦር ፡ ጋራ ፡ በሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ መሪነት ፡ ውጊያ ፡ ገጥሞ ፡ የተከራከረው ፡ የቱርክ ፡ ጦር ፡ ያደረገውን ፡ የጀግንነት ፡ ውጊያ ፡ በማስታወስ ፡ በዚህ ፡ ጀግና ፡ በሆነ ፡ የጦር ፡ አበጋዝ ፡ መሪነት ፡ የተነሣውን ፡ ቈራጡን ፡ የቱርክ ፡ ሕዝብ ፡ ለመግጠም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የጦር ፡ ሰራዊት ፡ መላክ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ተረድተው ፡ ሸክሙን ፡ በግሪክ ፡ ላይ ፡ አሳልፈው ፡ መጣል ፡ የተሻለ ፡ ሆኖ ፡ አገኙት ።

ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ የግሪክን ፡ ጦር ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ የቱርክን ፡ ነጻነት ፡ ታላላቆቹ ፡ መንግሥታት ፡ እንዲቀበሉና ፡ ቀድሞ ፡ ተፈራርመውት ፡ የነበረውን ፡ የዕርቅ ፡ ውል ፡ እንዲሠርዙት ፡ በግሪክና ፡ በቱርክ ፡ መካከል ፡ ያሉትንም ፡ ጉዳዮች ፡ እሱ ፡ በሚፈልገው ፡ አኳኋን ፡ እንዲስማሙባቸው ፡ አስገደዳቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጦርነቱ ፡ ሲፈጸም ፡ ቱርክ ፡ በሥልጣኔ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀረች ፡ በመሆኗ ፡ ምክንያት ፡ የደረሰባትን ፡ ጉዳት ፡ ተመልክቶ ፡ ለወደ ፡

ፊቱ ፡ ከሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ጋራ ፡ እኩል ፡ ሆና ፡ እንድትገኝ ፡ ለማድረግ ፡ ባሰበ ፡ ጊዜ ፡ የገጠመውን ፡ ዕንቅፋትና ፡ እሱም ፡ የተከተለውን ፡ መንገድ ፡ እስቲ ፡ ባጭሩ ፡ እንመልከተው ።

የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በራሱ ፡ አሳብ ፡ ብቻ ፡ መወሰን ፡ የማይገባ ፡ መስሎ ፡ ስለ ፡ ታየው ፡ የሕዝቡ ፡ መብት ፡ የተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡እንዲገኝ፡ የዴሞክራሲን ፡ መንፈስ ፡ አክብሮ ፡ ማንኛውም ፡ ጕዳይ ፡ በፓርለማ ፡ አማካይነት ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ እንዲወሰን ፡ አደረገ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በየጊዜው ፡ በፓርለማ ፡ በኩል ፡ የገጠመው ፡ ችግር ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ የሚያስቸሹልና ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ጕዳይ ፡ ለፓርለማው ፡ ቀርቦለት ፡ እሱም ፡ ራሱ ፡ በጉባኤው ፡ ላይ፡ ተገኝቶ ፡ ውሳኔውን ፡ ለማፋጠን ፡ ሲያስረዳና ፡ ሲከራከር ፡ ቈየ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከፓርለማው ፡ አባሎች ፡ አንዳንዶቹ ፡ የነገር ፡ ዐረቄ ፡ በማውጣት ፡ ጕዳዩን ፡ ሲጐትቱት ፡ ጊዜው ፡ በንትርክ ፡ ብቻ ፡ ከማለፉም ፡ በላይ ፡ ከቶ ፡ መቍረጫ ፡ የሚገኝለት ፡ መስሎ ፡ አልታየም ። ስለዚህ ፡ ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ በመጨረሻ ፡ ትዕግሥቱ ፡ ስላለቀ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ተናገረ፤

«እንግዲህ ፡ ይብቃ ! የእናንተን ፡ ልፍለፋ ፡ ስሰማ ፡ እንሆ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ በከንቱ ፡ አሳለፍኩ ፡ . . . በተገባ ፡ መብት ፡ ላይ ፡ የተቋቋመውን ፡ ይህን ፡ እኔ ፡ ያቀረብኩትን ፡ አሳብ ፡ እያንዳንዱ ፡ የዚህ ፡ ጉባኤ ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ ቢስማማበት ፡ የተሻለ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሳይሆን ፡ ቢቀርም ፡ ሊሻሻል ፡ የማይቻል ፡ የሆነው ፡ ይህ ፡ ጕዳይ ፡ ነገሮቹ ፡ የማይለወጡ ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ መጠንቀቅ ፡ ያሻል ፤ . . -ብዙ ፡ እናቶች ፡ እየተቈረጡ ፡ ሲወድቁ ፡ ሊታዩ ፡ ይችላል» ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የጉባኤው ፡ ፕሬዚደንት ፡ ተነሥቶ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ተናገረ ፤

«ጌቶቼ ! ጌቶቼ ! ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ እኛ ፡ በተመለከትነው ፡ መንገድ ፡ ሳይሆን ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ አቀራረብ ፡ አድርጎ ፡ ጕዳዩን ፡ አመጣብን ። ስለዚህ ፡ አስተያየታችንን ፡ ብንለውጠው ፡ የተሻለ ፡ መስሎ ፡ ይታየኛል» ።

እንሆ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ እሱ ፡ ባቀረበው ፡ አሳብ ፡ ጉባኤው ፡ እንዲስማማ ፡ ለማድረግ ፡ በክርክር ፡ ሳይሆንለት ፡ ቢቀር ፡ በሰይፍ ፡ ማለት ፤ በሞት ፡ ቅጣት ፡ ሊያስፈራራቸው ፡ ግዴታ ፡ ሆነበት ።

ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ በእስላም ፡ ሃይማኖት ፡ መሠረት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥልጣን ፡ የያዘውን ፡ ከሊፋ ፡ የሚባለውን ፡ ከስድስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡



ጀምሮ ፡ በቱርክ ፡ አገር ፡ የጸና ፡ ሆኖ ፡ የሚኖረውን ፡ ለእስላሞች ፡ የሃይማኖት ፡ አለቃ ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ ለመሻር ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ተቃዋሚዎች ፡ ተነሡበት ። ከሊፋ ፡ የሚባለውን ፡ የሃይማኖት ፡ ባለሥልጣን ፡ እንዲቀር ፡ ማድረግ ፡ በክርስቲያኖች ፡ ዘንድ ፡ የቤተ ፡ ክህነትን ፡ ዋና ፡ ባለሥልጣን ፡ መሻር ፡ ማለት ፡ ነው ። ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ ላገር ፡ ይጠቅማል ፡ ብሎ ፡ ያመነበትን ፡ ነገር ፡ ለመፈጸም ፡ ሥራውን ፡ ሲሠራ ፡ የሚ የሚፈጠረውን ፡ ዕንቅፋት ፡ ፈርቶ ፡ የሚያመነታና ፡ ወደ ፡ ኋላም ፡ የሚ መለስ ፡ ሰው ፡ ባለመሆኑ ፡ የወጠነውን ፡ አሳብ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ገፋበት ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ጉዳዩ ፡ እየከረረ ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ የተናገረው ፡ በእስላም ፡ ቃል ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ይገኛል ። ይህም ፡ የዘለፋ ፡ ቃል ፡ ሃይማኖትና ፡ በሃይማኖቱ ፡ መሪዎች ፡ ላይ ፡ የተነገረ ፡ ነው ።

«ከአምስት ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ በላይ ፡ ከሚሆን ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ ያስተ ሼክ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ያረብ ፡ ሽማግሌ ፡ ያወጣቸውን ፡ ደንቦችና ፡ የሆኑ ፡ ማራቸውን ፡ ትምህርቶች ፡ እንደዚሁም ፡ ቈሻሾችና ፡ ደንቈሮች ፡ የሆኑ ፡ ትር የብዙ ፡ ትውልዶች ፡ ካህናት ፡ የፈጠሯቸውን ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆኑ ፡ መቅ ጉሞች ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርንና ፡ የወንጀለኛ ፡ ጫን ፡ ሕጎች ፡ ከዝርዝር ፡ ነገሮቻቸው ፡ ጋራ ፡ በቱርክ ፡ አገር ፡ የጸኑ ፡ ሆነው ፡ እንዲኖሩ ፡ ተደርጓል ። ለሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ቅርጽ ፡ የሰጡት ፡ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ። የመንግሥቱ ፡ ዜጋ ፡ የሆነው ፡ የያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ታናናሾች ፡ ነገሮቹና ፡ አደራረጎቹ ፤ ምግቡ ፤ ከእንቅልፍ ፡ የመን ቂያውና ፡ የመኝታው ፡ ሰዓት ፤ የልብሱ ፡ ቅድ ፤ በትምህርት ፡ ቤት ፡ የሚ ማረው ፤ ባህሎቹና ፡ የግል ፡ አሳቦቹ ፡ እንኳ ፡ ሳይቀሩ ፡ በእነሱ ፡ የተቀ ረጹ ፡ ናቸው ። ሞራል ፡ ከሌለው ፡ ካንድ ፡ በደዊን ፡ የተገኘ ፡ የእስላም ፡ ሃይማኖት ፡ የተባለው ፡ ይህ ፡ ትምህርተ ፡ ሃይማኖት ፡ ሕይወታችንን ፡ የመረዘው ፡ የበሰበሰ ፡ ሬሳ ፡ ነው» ።

በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ተናግሯል ፤

«እነዚህን ፡ ምንም ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ የማይሰጡትን ፡ ሰነፎች ፡ ከየመስጊዶቹና ፡ ከየገዳማቶቹ ፡ አስወጥቼ ፡ አባርራቸዋለሁ ። የሕዝቡን ፡ ወዝ ፡ ይጠጣሉና ፤ በእሱ ፡ ላብ ፡ እነሱ ፡ ስለሚሠቡበት ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የመንግሥቱን ፡ መሠረት ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እየሰረሰሩ ፡ በማፍረስ ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ ። ወጣት ፡ ዛፍ ፡ የሆነችውን ፡ ቱርክን ፡ በመውረር ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ይህን ፡ አረም ፡ የሆነ ፡ የአረግ ፡ ዕንጨት ፡ ነቅዬ ፡ ሳልጥለው ፡ ሰላም ፡ የለኝም ፤ ዕረፍት ፡ አላገኝም» ።

ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የመንግሥቱ ፡ ሃይማኖት ፡ የሆነውን ፡ በመቃወም ፡ የእስላም ፡ ሃይማኖት ፡ ከመንግሥቱ ፡ ጋራ ፡ የተለያየ ፡ የማይገናኝ ፡ ለማድረግ ርጦ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ የሃይማኖቱ ፡ መሪዎች ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ የሕዝቡን ፡ መንፈስ ፡ በስብከታቸው ፡ ቀስቅሰው ፡ እንዲናወጥ ፡ አደረጉት ። ባገሩ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ሕዝብ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የእስላም ፡ አገሮች ፡ የሆኑት ፡ ሁሉ ፡ አንድነት ፡ ተናወጡ ። በየመን ፤ በኢራን ፤ በኢራክ ፡ በግብጽ ፤ በሶርያ ፤ በያለበት ፡ ያሉት ፡ እስላሞች ፡ እንደዚህ ፡ አድርጎ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚያረክሰውን ፡ ሰው ፡ ለማጥፋት ፡ በመንፈስ ፡ ተባበሩበት ። አጋ ፡ ካንና ፡ ኤሚር ፡ ዐሊ ፡ የሚባሉት ፡ በህንድ ፡ አገር ፡ ያሉ ፡ ሁለት ፡ የእስላም ፡ መሳፍንቶች ፡ ይህን ፡ አደራረግ ፡ በሙሉ ፡ የሚቃወሙ ፡ መሆናቸውን ፡ ገልጠው ፡ በመናገር ፡ ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ የመንግሥቱ ፡ መሪ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ በዚህ ፡ በተናገረው ፡ አስተያየት ፡ ጥልቅ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ የተቀየሙ ፡ መሆናቸውን ፡ አፌሲዬል ፡ የሆነ ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፈው ፡ አስታወቁት ። ባጭሩ ፡ የእስላም ፡ አገሮች ፡ ተነሡበት ፡ ማለት ፡ ነው ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ ገና ፡ ከዚህ ፡ ከፍ ፡ ካለው ፡ የማዕርግ ፡ ደረጃ ፡ ሳይደርስ ፡ አስቀድሞ ፡ ቱርክ ፡ ልትከተለው ፡ የሚገባትን ፡ መንገድ ፡ መርምሮ ፡ አግኝቶታል ። ሊሻሻሉ ፤ ጨርሰው ፡ ሊሠረዙና ፤ ሊለወጡ ፡ የሚገባቸውን ፡ ነገሮች ፡ አጥንቷቸዋል ። ቱርክ ፡ መዳኛ ፡ የሚሆናት ፡ አስተዳደር ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በበኩሉ ፡ ያመነበት ፡ ፕላን ፡ በእጁ ፡ ይገኛል ። የመንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ ከመጨበጡ ፡ በፊትም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ቱርክ ፡ ዘለቄታ ፡ አኗኗር ፡ ያለውን ፡ አሳብና ፤ አስተያየት ፡ ሳይደብቅ ፡ ለወዳጆቹና ፡ ለሥራ ፡ ጓደኞቹ ፡ በየጊዜው ፡ ገልጦላቸዋል ። ለቱርክ ፡ የሚበጃት ፡ ዘመናዊውን ፡ ሥልጣኔ ፡ መከተል ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ስላመነ ፡ ለዚህ ፡ እምነቱ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ያለማመንታት ፡ ሊፈጽማቸው ፡ ቈርጦ ፡ ተነሥቷል ። ስለ ፡ ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ የነበረውን ፡ አስተያየት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በሚገኘው ፡ እሱ ፡ በተናገረው ፡ ቃል ፡ ገልጦታል ።

«ሥልጣኔ ፡ በእሳት ፡ ትመስላለች ፤ ከሷ ፡ ውጭ ፡ ሆኖ ፡ ለመኖር ፡ የሚፈልገውን ፡ ሁሉ ፡ አቃጥላ ፡ ታጠፋዋለች ። የቀረው ፡ ዓለም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እየተራመደ ፡ ሲሄድ ፡ እኛ ፡ ከነበርንበት ፡ ቦታ ፡ ሳንንቀሳቀስ ፡ በመኖራችን ፡ የደረሰብን ፡ ጉዳት ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ሊገመት ፡ አይችልም ። አሁን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ መገሥገሥ ፡ የኛ ፡ ተራ ፡ ነው ። ሥልጣኔንና ፡ ሳይንስን ፡ ለማግኘት ፡ እንመኛለን ፤ ይህ ፡ አሁን ፡ የያዝነው ፡ መንገድ ፡ ከዚህ ፡ ዐላማ ፡ ያደርሰናል» ።



ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ እሱ ፡ ያመነበት ፡ አሳብ ፡ ይህ ፡ በመሆኑ ፡ ከዚህ ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ ማንኛውንም ፡ መሥዋዕት ፡ ለመፈጸም ፡ አልተመለሰም ። ስለዚህ ፡ በውስጥና ፡ በውጭ ፡ የተነሡበት ፡ ተቃዋሚዎች ፡ ሊያግዱት ፡ ሳይችሉ ፡ ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ የከሊፉን ፡ ሥልጣን ፡ ከቱርክ ፡ አገር ፡ ደመሰሰው ፤ ፋቀው ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የቱርክን ፡ ሥልጣን ፡ በእጁ ፡ ጨብጦ ፡ ይኖር ፡ የነበረውን ፡ ዐብዱል ፡ መጅድ ፡ የሚባለውን ፡ ሰው ፡ ተሰዶ ፡ ወደ ፡ ስዊስ ፡ አገር ፡ እንዲሄድ ፡ አስገደደው ። የቱርክ ፡ ሕዝብ ፡ ከሥር ፡ ከመሠረቱ ፡ አመጣጡ ፡ ከሞንጎሊ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እነ ፡ ጄንጂስካን ፡ በዘመናቸው ፡ በእስላም ፡ ሃይማኖት ፡ ላይ ፡ አሳይተው ፡ የነበረውን ፡ የተቃዋሚነትና ፡ የጨካኝነት ፡ መንፈስ ፡ ተከትሎ ፡ ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ ይህን ፡ ሲፈጽም ፡ መታየቱ ፡ ወገኖቹን ፡ መስሎ ፡ ለመገኘት ፡ የሠራው ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ያስደፍራል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ምንም ፡ ችግር ፡ ሳይገጥመው ፡ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ ሊፈጸሙ ፡ የሚገባቸውን ፡ ሥራዎች ፡ በሰላም ፡ ለመሥራት ፡ መንገዱ ፡ ሊከፈትለት ፡ ችሏል ፡ ብሎ ፡ አንባቢ ፡ ሳያስብ ፡ አይቀርም ። ነገር ፡ ግን ፡ ቱርክ ፡ የሥልጣኔን ፡ መንገድ ፡ እንድትይዝ ፡ ለማድረግ ፡ እሱ ፡ ያቀደውን ፡ አሳብ ፡ ለመፈጸም ፡ ሲያስብ ፡ ከዚህ ፡ የባሰና ፡ ከትልቅ ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ሊጥለው ፡ የሚችል ፡ ብርቱ ፡ ዕንቅፋት ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ከፊቱ ፡ ይጠብቀው ፡ ነበር ። ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ የቱርክ ፡ ሕዝብ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ በጦርነት ፡ ላይ ፡ ሲኖር ፡ በዚሁ ፡ ዘመን ፡ የጦር ፡ መሪ ፡ የነበረው ፡ እሱ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ ለዘመናዊው ፡ ጦርነት ፡ መመከት ፡ እንዲችል ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ ሲያስብ ፡ ምን ፡ እንደሚያስፈልገው ፡ በኤክስፔሪያንስ ፡ ተምሮት ፡ ነበር ። ጦርነት ፡ ለሱ ፡ ትልቅ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሆኖ ፡ አገልግሎታል ። ሰላም ፡ ማለት ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚወለደውን ፡ ጦርነት ፡ ለመግጠም ፡ እንዲችል ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ አስፈላጊውን ፡ ድርጅት ፡ የሚያከናውንበት ፡ ሰዓት ፡ መሆኑን ፡ ዐውቆታል ። ታላላቅ ፡ መንግሥታት ፡ የሆኑትም ፡ የግል ፡ ጥቅማቸውን ፡ ብቻ ፡ እየፈለጉ ፡ ደካማ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘውን ፡ ሕዝብ ፡ ከጥፋት ፡ ላይ ፡ ለመጣልና ፡ ከሱ ፡ የሚገኘውን ፡ ጥቅም ፡ ለመከፋፈል ፡ ብቻ ፡ የሚፈልጉ ፡ መሆናቸውን ፡ ተረድቶታል ። እንደዚሁም ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ በማንኛውም ፡ ነገር ፡ ከሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ጋራ ፡ እኩል ፡ ሆኖ ፡ ለመገኘት ፡ ሲፈልግና ፡ በውነት ፡ ከዚህ ፡ ዐላማ ፡ ልድረስ ፡ ብሎ ፡ ቈርጦ ፡ ሲነሣ ፡ ይህ ፡ ተግባር ፡ ቀልድና ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ አለመሆኑን ፡ ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ በሙሉ ፡ ገብቶት ፡ ነበር ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለሕዝቡ ፡ ባደረገው ፡ ንግግር ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ተናግሯል ።

«የዓለምን ፡ መንግሥታት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ዐውቂያቸዋለሁ ። በመድፍ ፡ እሳት ፡ መካከል ፤ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ሆኜ ፡ በመገኘት ፡ ያንድ ፡ ሕዝብ ፡ ጠባይ ፡ ዕራቁቱን ፡ ሆኖ ፡ በሚታይበት ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ መርምሬያቸዋለሁ» ።

ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ ይህን ፡ አሳብ ፡ ተከትሎ ፡ የፈጸማቸውን ፡ ሥራዎች ፡ እንመልከት ። በቱርክ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ኩርዲስታን ፡ የሚባሉ ፡ የሕዝብ ፡ ነገድ ፡ የሚኖሩበት ፡ አገር ፡ አለ ። እነሱም ፡ አገር ፡ በጥባጮች፤ ሞገደኞች ፤ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሁከት ፡ የሚፈጥሩና ፡ ላገሪቱ ፡ ሰላም ፡ የሚነሡ ፡ መሆናቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በጠረፍ ፡ አቅራቢያ ፡ የሚገኙ ፡ ከመሆናቸው ፡ የተነሣ ፡ በየዘመኑ ፡ ከኢራክና ፡ ከፋርስ ፡ በኩል ፡ እየተሰበኩ ፡ ሁከት ፡ መፍጠር ፡ ልማዳቸው ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ የእስላምን ፡ ሃይማኖት ፡ በፋናቲክነት ፡ መንፈስ ፡ ያቀፉትና ፡ የሚደግፉት ፡ በመሆናቸው ፡ የቱርክ ፡ መንግሥት ፡ የከሊፋን ፡ ሥልጣን ፡ የሻረበትን ፡ ዐዋጅ ፡ መላው ፡ የቱርክ ፡ ሕዝብ ፡ ተቀብሎ ፡ ሲፈጽመው ፡ እነሱ ፡ እንቢ ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ልማዳቸው ፡ አስቸገሩ ። እንግሊዝ ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ ሲሠለጥን ፡ ማየት ፡ የማትወድ ፡ በመሆኗ ፡ ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ ቱርክን ፡ ለማሠልጠን ፡ የወጠነውን ፡ ሥራ ፡ ለማሰናከል ፡ ፈልጋ ፡ እነዚህ ፡ ሁከተኞች ፡ የሆኑ ፡ ሕዝቦች ፡ ያነሡት ፡ ብጥብጥ ፡ እየተፋፋመ ፡ እንዲሄድ ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ትረዳቸው ፡ ጀመር ። ስለዚህ ፡ ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ዲቪዚዮን ፡ የሚሆን ፡ ጦር ፡ በእነዚህ ፡ ሁከተኞች ፡ ላይ ፡ ልኮ ፡ አገራቸውን ፡ በጦር ፡ እሳት ፡ አቃጠለው ። ወንዶቹ ፡ ሥቃይ ፡ ተቀብለው ፡ እየተሰቀሉ ፡ ሲሞቱ ፡ የሚኖሩባቸው ፡ መንደሮቻቸው ፡ አመድ ፡ ሆኑ ። እርሻቸው ፡ ተዘረፈ ፤ ሴቶቻቸው ፡ ከተደፈሩ ፡ በኋላ ፡ ተገደሉ ፤ ለተነሣው ፡ ሁከት ፡ መሪዎች ፡ የሆኑት ፡ አርባ ፡ ስድስት ፡ ሰዎች ፡ ዲያቤኪር ፡ በሚባለው ፡ ቦታ ፡ ተሰቀሉ ። ዳግመኛ ፡ ሊነሡና ፡ ሊቋቋሙ ፡ እንደማይችሉ ፡ አድርጎ ፡ ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ ከሕዝቦች ፡ ሕይወት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ ስማቸውን ፡ ፋቀው ።

ይህን ፡ ሁሉ ፡ ዕንቅፋት ፡ አልፎ ፡ ሥራውን ፡ በሰላም ፡ ሊቀጥል ፡ ሲሞክር ፡ ቱርክም ፡ ወደ ፡ ሰላማዊ ፡ ሕይወት ፡ ስትተላለፍ ፡ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ ችግሮች ፡ ገጠሟት ። ወደቦችና ፡ መንገዶች ፡ መሥራት ፤ ባቡር ፡ መዘርጋት ፤ እርሻንና ፡ ኢንዱስትሪን ፡ ማስፋፋት ፡ ነበረባት ። ባንድ ፡ በኩል ፡ የፈረሰውን ፡ መልሶ ፡ ማደስ ፤ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ቀድሞ ፡ ጨርሶ ፡ ያልነበረውን ፡ መፍጠርና ፡ ማቋቋም ፡ ያስፈልግ ፡ ነበር ። ይህንንም ፡ ለመፈጸም ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ አልነበረም ። ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ለኢንዱስትሪ ፡ የሚሆን ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ (matières premières) ማግኘት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሲገኝ ፡ ማመላለሻ ፡ ይጐድላል ። ማመላለሻ ፡ ሲገኝ ፡ የኢንዱ



ስትሪ ፡ መኪናዎች ፡ አይገኙም ። መኪናዎቹ ፡ ሲገኙ ፡ ሥራ ፡ ማስኬጃ ፡ ገንዘብ ፡ ይታጣል ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ሲገኝ ፡ ደግሞ ፡ ሠራተኞችና ፡ ፋብሪካዎቹንም ፡ የሚያስኬዱቸው ፤ መኪናዎቹም ፡ በተበላሹ ፡ ጊዜ ፡ የሚያድሷቸው ፡ በእጅ ፡ ሥራ ፡ የሠለጠኑ ፡ ሰዎችም ፡ ይጐድላሉ ።

በዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ችግር ፡ ተፈጠረ ። የቱርክ ፡ ሕዝብ ፡ ጦርነቱ ፡ እስከ ፡ ተነሣበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የሚተዳደረው ፡ እኩሉ ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፤ ሹምና ፡ ሠራተኛ ፡ በመሆን ፤ ግማሹም ፡ በገበሬነትና ፡ በወታደርነት ፡ ብቻ ፡ ነበር ። በኢንዱስትሪና ፡ በእጅ ፡ ሥራ ፡ ምንም ፡ ዕውቀት ፡ አልነበረውም ። ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ በጦርነቱ ፡ ምክንያት ፡ ባገሩ ፡ ውስጥ ፡ በብዛት ፡ ይገኙ ፡ የነበሩትን ፡ ግሪኮችና ፡ አርመኖች ፡ ከፈጃቸው ፡ በኋላ ፡ ከጦርነት ፡ የተረፉትንም ፡ በዕርቁ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ካገሩ ፡ አስወጣቸው ። የንግድን ፡ የኢንዱስትሪንና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የእጅ ፡ ሥራዎችን ፡ የሚያከናውኑ ፡ እነሱ ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ቱርኮችም ፡ እነዚህን ፡ ተግባሮች ፡ ለመፈጸም ፡ በቂ ፡ ችሎታ ፡ የሌላቸው ፡ በመሆናቸው ፡ ባገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ትልቅ ፡ ችግር ፡ ተፈጠረ ። ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ ያገሪቱን ፡ ሕይወት ፡ ለማንቀሳቀስ ፡ አስፈላጊዎች ፡ የሆኑትን ፡ ቴክኒሲያኖች ፡ ይቅሩልኝ ፡ ብሎ ፡ ከግሪኮችና ፡ ካርመኖች ፡ መካከል ፡ ለእነዚህ ፡ ሥራዎች ፡ ችሎታ ፡ ያላቸውን ፡ መር ጦ ፡ እንዲቀሩ ፡ አላደረገም ።

ቱርኮች ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ብቻቸውን ፡ ስለ ፡ ቀሩ ፡ የባንክን ፡ ሥራ ፡ ማካሄድ ፤ ኢንዱስትሪን ፡ ማንቀሳቀስ ፤ ባቡርን ፡ መንዳት ፤ ካገሪቱ ፡ የሚገኘውን ፡ ሀብት ፡ እየሸጡ ፡ የንግድን ፡ ሥራ ፡ ማካሄድ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፤ ታላላቅ ፡ ሕንጻዎችን ፡ በመሐንዲስነት ፡ ማቋቋም ፡ ባጭሩ ፡ እነዚህን ፡ ቀድሞ ፡ ግሪኮችና ፡ አርመኖች ፡ ይሠሯቸው ፡ የነበሩትን ፡ ተግባሮች ፡ በእነሱ ፡ እግር ፡ ተተክተው ፡ መፈጸም ፡ ግዴታ ፡ ሆነባቸው ። ቱርኮች ፡ በእነዚህ ፡ ሥራዎች ፡ ልማድና ፡ ችሎታ ፡ ስለሚጐድላቸው ፡ የገጠማቸው ፡ ችግር ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ ነው ፡ አይባልም ። ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ የሚፈልገው ፡ ይህንኑ ፡ ነበር ። ተማሪዎች ፡ ብዙ ፡ ደብተሮች ፡ ሳያበላሹና ፡ ሳያጨማልቁ ፡ ጽሕፈትን ፡ ለመማር ፡ እንደማይችሉ ፡ ሁሉ ፡ ትልልቅ ፡ ሰዎችም ፡ እንደዚሁ ፡ ስሕተት ፡ ሳያደርጉ ፡ ራሳቸውን ፡ እንደማይችሉ ፡ ያውቅ ፡ ነበር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የተፈጠረው ፡ የኤኮኖሚ ፡ ሁከት ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ አልሆነም ። በዚህ ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ተከታትሎ ፡ የተሰበሰበው ፡ ሰብል ፡ ላገሪቱ ፡ የማይበቃ ፡ ሆኖ ፡ የእኽል ፡ ችግር ፡ በመፈጠሩ ፡ ይህም ፡ አንድ ፡ ተጨማሪ ፡ ችግር ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ትልቅ ፡ ተስፋ ፡ መቍረጥ ፡ ሆነ ። የሕዝቡን ፡ ኑሮ ፡ ያንቀሳቀሰው ፡ የነበረ ፡ ሁኔታ ፡ ቀጥ ፡

ብሎ ፡ ቆመ ። ቀድሞ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ያስኬዷቸው ፡ የነበሩትን ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ ቱርኮች ፡ ተረክበው ፡ ብቻቸውን ፡ ሊያስኬዱት ፡ ይችላሉ ፡ ብሎ ፡ ቀድሞውንም ፡ ቢሆን ፡ መታሰቡ ፡ ትልቅ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡ ተቃዋሚዎች ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ተነሡ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በመንግሥቱ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ መካከል ፡ ትልቅ ፡ ሤራ ፡ ተፈጠረ ። በሤረኞቹም ፡ መካከል ፡ ለሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ የቅርብ ፡ ወዳጆቹ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። ለዚህ ፡ ለተፈጠረው ፡ የኤኮኖሚ ፡ ችግር ፡ አላፊው ፡ ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ባገሪቱ ፡ ላይ ፡ የወደቀውን ፡ የኤኮኖሚ ፡ ሁከት ፡ እያየ ፡ የጉዳዩን ፡ ከባድነት ፡ ሊረዳውና ፡ ሊያውቀው ፡ የማይፈልግ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ከውጭ ፡ መንግሥታት ፡ ዘንድ ፡ ገንዘብ ፡ ተበድረን ፡ ይህን ፡ ሁኔታ ፡ እንድናሻሽል ፡ አሳብ ፡ ስናቀርብለት ፡ ብድር ፡ መጠየቅ ፡ አስፈላጊ ፡ አይዶለም ፡ ባይ ፡ ሆኖ ፡ በመገኘቱ ፡ አገሪቱን ፡ ከጥፋት ፡ ላይ ፡ ሊጥላት ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ሤረኞቹ ፡ ይህን ፡ አስተያየት ፡ ለተነሡበት ፡ ዐድማ ፡ መደገፊያ ፡ አደረጉት ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ሙስጠፋ ፡ ከማልን ፡ በቦምብ ፡ ለመግደል ፡ ቋጥረውት ፡ የነበረው ፡ ሤራ ፡ አሳባቸውን ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ከማዋላቸው ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ተገለጠባቸው ፡ ሤረኞቹ ፡ ተያዙ ። በሤረኞቹ ፡ መካከል ፡ በፊናንስ ፡ ጉዳይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ቀድሞ ፡ የቱርክ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትር ፡ የነበር ፡ ጃቪድ ፡ የሚባል ፡ ትውልዱ ፡ አይሁዳዊ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ሤረኞቹ ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ ጃቪድ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ የሤረኞቹ ፡ አሳብ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ይገልጥልናል ። ቃሉም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

«ባገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ሥራዎች ፡ በጣም ፡ ተበላሽተዋል ። የሕዝቡ ፡ ቍጣ ፡ ትዕቢተኛ ፡ በሆነውና ፡ ችሎታ ፡ በሚጐድለው ፡ በመንግሥቱ ፡ መሪ ፡ ላይ ፡ ተነሥቶበታል ። ይህ ፡ ያሁኑ ፡ ፍርድ ፡ በሕዝቡ ፡ በኩል ፡ የተነሣውን ፡ ቍጣ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ለማዞር ፡ የሚሞከርበት ፡ ዘዴ ፡ ነው ። አገሪቱን ፡ መልሶ ፡ የማቋቋሙን ፡ ሥራ ፡ አሰናክላችኋል ፡ ብሎ ፡ እኛን ፡ ሲከሰን ፡ መንግሥት ፡ እውነተኞቹን ፡ ምክንያቶች ፡ ሊሸፍናቸው ፡ ፈልጎ ፡ ነው ። እነዚህን ፡ ምክንያቶች ፡ እኔ ፡ እነግራችኋለሁ ፤ እኛን ፡ የሚመሩን ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ሐውልት ፡ ጐልቶ ፡ ከሚታየው ፡ ከችሎታቢስነታቸው ፡ የመጡ ፡ ከማል ፡ በነደፋቸው ፡ መቼም ፡ ቢሆን ፡ ሊፈጸሙ ፡ በማይችሉት ፡ ፕሮግራሞች ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኘው ፡ ስሕተት ፡ የመነጩ ፡ ምክንያቶች ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ ፕሮግራሞች ፡ ለመፈጸም ፡ የማይችሉ ፡ በመሆናቸው ፡ መቼም ፡ ቢሆን ፡ አይፈጸሙም ። ከማል ፡ ፓሻ ፡ ጥሩ ፡ የጦር ፡ ሰው ፡ መሆኑ ፡ ምንም ፡ ጥርጥር ፡ የለበትም ። እሱ ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ ስፈሩ ፡



ይመለስና ፡ እነዚህን ፡ ሥራዎች ፡ ዕውቀት ፡ ላላቸው ፡ ሰዎች ፡ አሳልፎ ፡ ያስረክብ ። ጌቶቼ ፡ ሆይ ! በዚህ ፡ ቀልድ ፡ (ኰሜዲ) ፡ እንዳትታለሉ ፤ እንደዚሁም ፡ የዚህ ፡ ዐመፅ ፡ ተካፋዮች ፡ ሁናችሁ ፡ እንዳትገኙ» ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ጃቪድ ፡ ይህ ፡ የዐፈ ፡ ርቱዕነት ፡ ሙያ ፡ የሚታበት ፡ ንግግሩ ፡ ከፍርድ ፡ አላዳነውም ። ሤረኞቹ ፡ ሁሉ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ተፈርዶባቸው ፡ ተሰቀሉ ። ኮሎኔል ፡ አሪፍ ፡ የሚባል ፡ ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ ምስጢሩን ፡ ሁሉ ፡ ያካፍለው ፡ የነበረ ፡ በጣም ፡ የቅርብ ፡ ወዳጁ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ በዚሁ ፡ ሤራ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ በመገኘቱ ፡ ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ ለሱ ፡ እንኳ ፡ ምሕረት ፡ አላደረገለትም ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከማል ፡ ፓሻ ፡ ማንኛውም ፡ የቴክኒክም ፡ ሆነ ፡ የንግድ ፡ የባንክም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በቱርኮች ፡ እጅ ፡ እንዲሠራ ፡ አድርጎ ፡ የመጀመሪያውን ፡ እርምጃ ፡ ችግር ፡ በትዕግሥትና ፡ በቈራጥነት ፡ ከተወጣው ፡ በኋላ ፡ የሥራውን ፡ ፍሬ ፡ መሰብሰብ ፡ ጀመረ ። የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታት ፡ ከችግር ፡ ላይ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ የገንዘብ ፡ ብድር ፡ ይጠይቀናል ፡ ብለው ፡ አሰፍስፈው ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ። እሱ ፡ ግን ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ እንዳይበደር ፡ በልቡ ፡ ቆርጦ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በዚህ ፡ አሳቡ ፡ ጸንቶ ፡ ኖረ ።

ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቱርክን ፡ ለማሠልጠን ፡ ያቀደውን ፡ ፕሮግራም ፡ ተከትሎ ፡ ሲሠራ ፡ የፈጸማቸውን ፡ ነገሮች ፡ ባጭሩ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ እንጠቅሳቸዋለን ።

የቱርክ ፡ ሕዝብ ፡ የሚለብሰው ፡ እንዳገሩ ፡ ልማድ ፡ ነበር ። አንድ ፡ ቀን ፡ ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ እንደ ፡ አውሮፓ ፡ ሕዝብ ፡ አለባበስ ፡ ልብሱን ፡ ለውጦ ፡ ለብሶ ፡ ለሕዝቡ ፡ ታየ ። በቁርአን ፡ የተጻፈውን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የቱርክ ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ መለዮ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ የሚደፋውን ፡ ቀይ ፡ ቆብ ፡ በተለየ ፡ ከሃይማኖት ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ አድርጎ ፡ ይቈጥረው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የመንግሥቱ ፡ መሪ ፡ ይህንን ፡ የተከበረውን ፡ ቆብ ፡ ጥሎ ፡ የፈረንጆችን ፡ ባርኔጣ ፡ አድርጎ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ዕንቅፋት ፡ አድርጎ ፡ ቈጠረው ። ብዙ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ቱርክ ፡ አገር ፡ ሲሄዱ ፡ ያገሩን ፡ ሕዝብ ፡ ደስ ፡ ለማሰኘትና ፡ ፍቅሩን ፡ ለማግኘት ፡ ሲሉ ፡ የቱርክ ፡ ሕዝብ ፡ የሚለብሰውን ፡ ልብስ ፡ እየለበሱ ፡ ይታዩ ፡ ነበር ። እነሱም ፡ ግሪኮች ፤ አይሁዶችና ፡ አሜሪካኖች ፡ ናቸው ። አሁን ፡ ግን ፡ የሕዝቡ ፡ መሪ ፡ የሆነው ፡ ያገሩን ፡ ሕዝብ ፡ ባህል ፡ ሽሮ ፡ በመታየቱ ፡ ያገሩን ፡ ሰዎች ፡ በጣም ፡ ቅር ፡ አሰኛቸው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እሱ ፡ የሚሠራው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ላገር ፡ የሚጠቅም ፡ እንጂ ፡ የሚጐዳ ፡

ነው ፡ ብሎ ፡ የሚተረጉም ፡ ሰው ፡ ባለመኖሩ ፡ የዚያኑ ፡ ዕለት ፡ ባካባቢው ፡
ያለው ፡ ሕዝብ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ይደፋ ፡ የነበረውን ፡ ቆብ ፡ እያወለቀ ፡
ወረወረውና ፡ ከከማል ፡ ፓሻ ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ ተሰብስቦ ፡ የደስታና ፡ የፍ
ቅር ፡ መግለጫ ፡ ድምፅ ፡ እያሰማ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ባሳብ ፡ የተባበረ ፡ መሆ
ኑን ፡ ገለጠለት ። ከማል ፡ ፓሻ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ለሕዝቡ ፡ ከዚህ ፡ ቀ
ጥሎ ፡ የሚገኘውን ፡ ቃል ፡ ተናገረ ።

«በጥቂት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ከጥፋት ፡ ልንድን ፡ የቻልነው ፡ አስ
ተያየታችንን ፡ በመለወጣችን ፡ ነው ። አሁንም ፡ በዚህ ፡ ለመቆም ፡ አን
ችልም ። በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ ቢሆን ፡ ወደፊት ፡ መራመድ ፡ ያስፈልገ
ናል ። እንደ ፡ አንድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ሆነው ፡ በሚኖሩት ፡ በሠለጠኑት ፡ ሕዝ
ቦች ፡ መካከል ፡ የሚገባንን ፡ ቦታ ፡ የያዝን ፡ በመሆናችን ፡ እሱን ፡ ጠብ
ቀን ፡ እንኖራለን ። መልካም ፡ አኗኗር ፡ ደስታና ፡ መከበር ፡ የሚገኙት ፡
እንሆ ፡ በዚህ ፡ ነው» ።

በማግስቱ ፡ ከማል ፡ ፓሻ ፡ ይህንን ፡ ካደረገበት ፡ ቦታ ፡ ተነሥቶ ፡ ኢ
ኒቦሉ ፡ ወደምትባለው ፡ ከተማ ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ እዚያም ፡ ሕዝቡ ፡ ተሰ
ብስቦ ፡ ጠበቀውና ፤

«የምትፈቅደውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ጠይቀን ፡ እኛም ፡ ልንፈጽመው ፡
የተዘጋጀን ፡ ነን ። ጀግናና ፡ ሠራተኛ ፡ ለሆነው ፡ ሕዝባችን ፡ መሪው ፡
መድኅኒቱና ፡ አስተዳዳሪው ፡ አንተ ፡ ነኽ» ፡ ሲል ፡ አሳቡን ፡ ገለጠለት ።

ከማል ፡ ፓሻ ፡ አንካራ ፡ ከተማ ፡ ሲገባ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡
የመንግሥቱን ፡ መሪ ፡ አሳብ ፡ ተከትሎ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡
የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ያውሮፓን ፡ ባርኔጣ ፡ እንዲያደርግ ፡ የሚያስገድድ ፡ ውሳኔ ፡
ሰጠ ። ጋዜጦችም ፡ እንቢተኞች ፡ ሆነው ፡ ባርኔጣቸውንና ፡ ልብሳቸውን ፡
ሳይለውጡ ፡ የቀሩትን ፡ ሰዎች ፡ እያሽሟጠጡ ፡ መሣቂያ ፡ አደረጓቸው ።
የሃይማኖት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የሆኑት ፡ እንደ ፡ ልማዳቸው ፡ ማጕረምረ
ማቸውን ፡ አመጡ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጉዳዩ ፡ ከፓርለማ ፡ ቀረበና ፡ ያገር ፡
ቆብ ፡ የነበረው ፡ ቀርቶ ፡ በሱ ፡ ፈንታ ፡ ሕዝቡ ፡ ያውሮፓን ፡ ባርኔጣ ፡
እንዲያደርግ ፡ የሚያዘውን ፡ ዐዋጅ ፡ ሁለት ፡ አባሎች ፡ ብቻ ፡ ሲቃወሙ ፡
ሁሉም ፡ ባንድ ፡ ድምፅ ፡ ተስማምተውበት ፡ የጸና ፡ ሆነ ። ይህ ፡ ዐዋጅ ፡
ለሕዝብ ፡ በተነገረ ፡ ጊዜ ፡ ዳር ፡ አገር ፡ በሆኑት ፡ አውራጃዎች ፡ ባሉት ፡
ከሥልጣኔ ፡ መንፈስ ፡ ርቀው ፡ በሚኖሩት ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ የሃይማኖት ፡
ምልክት ፡ የሆነው ፡ ቆብ ፡ በመከልከሉ ፡ ትልቅ ፡ ቅያሜ ፡ ተፈጠረና ፡
ሁከተኞች ፡ የሆኑ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ብጥብጥ ፡ አነሡ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡



መንግሥቱ ፡ ጦር ፡ ልኮ ፡ ለእንቢተኞቹ ፡ መሪ ፡ የሆኑት ፡ አርባ ፡ ሰዎች ፡
ተይዘው ፡ በሞትና ፡ በእስራት ፡ ተቀጡ ። ሙስጠፋ ፡ ከማል ፡ የሃይማ
ኖት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ የፈጠሩትን ፡ የተቃዋሚ
ነት ፡ መንፈስ ፡ ለመከላከል ፡ ሲል ፡ እሱው ፡ ራሱ ፡ በየቦታው ፡ ላይ ፡ እየ
ተገኘ ፡ ይህ ፡ ውሳኔ ፡ የድንቊርና ፡ ምልክት ፡ የሆነውን ፡ ሠርዞ ፡ የሥል
ጣኔ ፡ መግለጫ ፡ የሆነውን ፡ እንደሚደግፍ ፡ ለማስረዳት ፡ ብዙ ፡ ንግግር ፡
አደረገ ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የቱርክ ፡ ሴቶች ፡ ፊታቸውን ፡ ተሸፋፍነው ፡ ይኖሩ ፡
ስለ ፡ ነበረ ፡ ይህ ፡ ልማድ ፡ እንዲቀር ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠ ። ምክርንና ፡ ግዴ
ታን ፡ እያፈራረቀ ፡ ከቤታቸው ፡ ሲወጡና ፡ በየመንገዱ ፡ ሲሄዱ ፡ ፊታቸ
ውን ፡ የሚሸፍኑበትን ፡ ጨርቅ ፡ እንዲጥሉ ፡ በማዘዝ ፡ ይህንኑ ፡ ውሳኔ ፡
ሕግ ፡ አድርጎ ፡ አጸናው ።

ጋንዲ ፡ የህንድ ፡ ሕዝብ ፡ ያውሮፓን ፡ ልብስ ፡ እያወለቀ ፡ እንዲያቃ
ጥልና ፡ በሱ ፡ ቦታ ፡ ያባቶቹን ፡ ልብስ ፡ እንዲለብስ ፡ ባዘዘበት ፡ ዘመን ፡
ከማል ፡ ፓሻ ፡ የቱርክ ፡ ሕዝብ ፡ ያባቶቹን ፡ ልብስ ፡ እያወለቀ ፡ ጥሎ ፡
ያውሮፓን ፡ ሕዝብ ፡ ልብስ ፡ እንዲቀበል ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥቶ ፡ እንቢተኞ
ቹን ፡ በሞት ፡ እየቀጣ ፡ አስገድዷል ። እንግዲህ ፡ ሥልጣኔ ፡ ያለችው ፡
በማንኛው ፡ በኩል ፡ ነው ? በጋንዲ ፡ ወይስ ፡ በከማል ፡ ፓሻ ፡ በኩል ?
ይህም ፡ የሚደረገው ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ በጋዜጣ ፡ በመጽሐፍ ፡ በራ
ዲዮ ፡ በባቡር ፡ በአኤሮፕላን ፡ ተቀራርበው ፡ በሚኖሩበት ፡ ዘመን ፡ በመ
ሆኑ ፡ ያስደንቃል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሁለቱም ፡ ይህንን ፡ ያደረጉት ፡ ላገራ
ቸውና ፡ ለሕዝባቸው ፡ የሚጠቅም ፡ ሆኖ ፡ ስላገኙት ፡ ነው ።

የቱርክ ፡ ሕዝብ ፡ ቀድሞ ፡ የሚተዳደረው ፡ በቊራን ፡ ሕግ ፡ መሠ
ረት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ከማል ፡ ፓሻ ፡ ይህ ፡ እንዲቀርና ፡ በቱርክ ፡ ግዛት ፡
ውስጥ ፡ ያሉት ፡ እስላሞችና ፡ ሌሎችም ፡ እስላሞች ፡ ያልሆኑት ፡ ሕዝ
ቦች ፡ እንደ ፡ ሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡
እንዲተዳደሩ ፡ አደረገ ። በስዊስ ፡ አገር ፡ የሚሠራበት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡
በቱርክ ፡ አገር ፡ የጸና ፡ እንዲሆን ፡ አሳብ ፡ ባቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ ባንድ ፡
ድምፅ ፡ አጸደቁት ። የጋብቻና ፡ የፍቺ ፡ ሥራት ፡ በቊራን ፡ መሠረት ፡
መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ አዲስ ፡ በወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ተፈጻሚ ፡ እንዲ
ሆን ፡ ተደረገ ። በእስላሞች ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ብዙ ፡ ሚስቶች ፡ ማግባ
ትም ፡ ተከለከለ ። የቱርክ ፡ መንግሥት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርን ፡ ሕግ ፡ ከስ

ዊስ ፤ የወንጀለኛ ፡ መቅጫን ፡ ሕግ ፡ ከኢጣሊያ ፡ የንግድን ፡ ሕግ ፡ ከጀርመን ፡ ቀድቶ ፡ ባገሩ ፡ ውስጥ ፡ አጸናው ።

ከማል ፡ ፓሻ ፡ እንደዚህ ፡ አድርጎ ፡ ዋና ፡ ዋናቹን ፡ ነገሮች ፡ በትጋትና ፡ በቈራጥነት ፡ ካደላደለ ፡ በኋላ ፡ በያይነቱ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ኮሌጆች ፤ ኢንስቲቱቶችና ፡ ለእርሻ ፡ ትምህርት ፡ የሚያገለግሉ ፡ ድርጅቶች ፡ አቋቋመ ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ ያከናወነው ፡ ሥራ ፡ በጣም ፡ ሰፊ ፡ ነው ።

መንግሥቱንም ፡ ጸጥ ፡ አድርጎ ፡ የራሱንም ፡ ሥልጣን ፡ አደላድሎ ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ የሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ የመንግሥታቸውን ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ የተቃና ፡ ወይም ፡ የተዛባ ፡ መሆኑን ፡ ሊረዱት ፡ የሚችሉት ፡ ተቃዋሚ ፡ የሆነ ፡ የፖለቲክ ፡ ክፍል ፡ (opposition) በመኖሩ ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ ተገነዘበው ፡ በሱ ፡ መሪነት ፡ ለተቋቋመው ፡ መንግሥት ፡ ተቃዋሚ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ የፖሊቲካ ፡ ክፍል ፡ ሊፈጥርለት ፡ አሰበ ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጋዜጦች ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ እየተመለከቱ ፡ የሚነቅፉትን ፡ ነገር ፡ ሳይፈሩ ፡ በግልጥ ፡ እንዲናገሩና ፡ እንዲተቹ ፡ ተፈቀደላቸው ። ታማኞች ፡ ከሆኑት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ መካከል ፡ ሰዎች ፡ ተመርጠው ፡ የተቃዋሚው ፡ ፖሊቲካ ፡ ክፍል ፡ መሪዎች ፡ እንዲሆኑ ፡ ታዘዙ ። ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ጋዜጠኛ ፡ በመንግሥቱ ፡ ላይ ፡ የዘለፋ ፡ ቃል ፡ ደፍሮ ፡ ቢጽፍ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ተፈርዶበት ፡ ተሰቅሎ ፡ እንዲሞት ፡ በመደረጉ ፡ አሁን ፡ ከማል ፡ ፓሻ ፡ ተቃዋሚዎች ፡ እንዲነሡ ፡ ሲፈቅድ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በተንኰል ፡ መንፈስ ፡ የተደረገ ፡ አድርገው ፡ ሳይተረጕሙበት ፡ አልቈሩም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እሱ ፡ ላገሪቱ ፡ የጐደላት ፡ ነገር ፡ አድርጎ ፡ የቆጠረውን ፡ ይህን ፡ የሥልጣኔ ፡ መሣሪያ ፡ ሊሰጣት ፡ ቈርጦ ፡ ስለ ፡ ተነሣ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ሊያግደው ፡ ሳይችል ፡ አሳቡን ፡ በሥራ ፡ እንዲፈጸም ፡ አደረገ ።

ይህ ፡ ሥራ ፡ በተቋቋመ ፡ ጊዜ ፡ አፋቸው ፡ በፍርሀት ፡ ታስሮ ፡ የነበረው ፡ የተቃዋሚነት ፡ መንፈስ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ የዘለፋና ፡ የሐሜት ፡ የነቀፌታና ፡ የተቃዋሚነት ፡ አሳባቸውን ፡ ማገጃ ፡ በሌለው ፡ አርነት ፡ በመንግሥቱ ፡ ላይ ፡ ያጐርፉበት ፡ ጀመር ። በመንግሥቱና ፡ በባለሥልጣኖች ፡ ላይ ፡ በጋዜጦች ፡ አማካይነት ፡ የትችት ፤ የዘለፋና ፡ የስድብ ፡ መዓት ፡ ወረደባቸው ። ይህም ፡ ነገር ፡ በብዙ ፡ ስፍራዎች ፡ በሕዝብ ፡ መካከል ፡ ብጥብጥና ፡ አምባጓሮ ፡ አስከተለ ። በፖሊስና ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ግጭት ፡ እየሆነ ፡ ደም ፡ ስለ ፡ ተፋሰሱ ፡ ሥራትን ፡ ለማስከበር ፡ እሱው ፡ ራሱ ፡ ከማል ፡ ፓሻ ፡ በጕዳዩ ፡ ውስጥ ፡ እየገባ ፡ ጠቡን ፡ እንዲረጋጋ ፡ ማድረግ ፡ ግዴታ ፡ ሆነበት ። አስተዋዮች ፡ የሆኑ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡



ከማል ፡ ፓሻ ፡ የሕዝብ ፡ መሪነቱን ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ በሚያከናውነው ፡ ተግባር ፡ ከሚገባው ፡ ወሰን ፡ ያለፈ ፡ መስሎ ፡ ታያቸው ። በመጨረሻ ፡ የሕዝቡ ፡ ጸጥታ ፡ ከሚያሠጋ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ በመድረሱ ፡ ከማል ፡ ፓሻ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ያቀጣጠለውን ፡ እሳት ፡ መልሶ ፡ ማጥፋት ፡ ግዴታ ፡ ሆነበት ። አቋቁሞት ፡ የነበረውን ፡ ተቃዋሚ ፡ የሆነ ፡ የፖሊቲካ ፡ ክፍል ፡ ሠረዘው ። በሕዝቡ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡ መሰል ፡ የሌለው ፡ መሆንኑ ፡ ከማንኛውም ፡ ነገር ፡ ይልቅ ፡ ይህ ፡ ጕዳይ ፡ ገልጦ ፡ ለዓለም ፡ ያስረዳለት ፡ መሆኑን ፡ ማመንና ፡ መቀበል ፡ የሚገባ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ዲክታተር ፡ (አባይ ፡ ገነን) ፡ በዕውቀትና ፡ በሥልጣኔ ፡ ያልበሰለውን ፡ ሕዝብ ፡ ከሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ጋራ ፡ በመንፈስ ፡ እኩል ፡ ላድርገው ፡ ብሎ ፡ ቢያስብ ፡ ሊሆንለት ፡ የማይችል ፡ ነገር ፡ መሆኑን ፡ ከማል ፡ ፓሻ ፡ እንዲረዳው ፡ ይህ ፡ ጕዳይ ፡ ትምህርት ፡ ሆኖ ፡ አገልግሎታል ።

ከማል ፡ ፓሻ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የቱርክ ፡ ሕዝብ ፡ ካውሮፓ ፡ በር ፡ ላይ ፡ የሚኖር ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ከሥልጣኔ ፡ ውጭ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ አይገባውም ፡ በማለት፡ የተነሣበትን ፡ አሳብ ፡ ሞላ ፡ ከጐደል ፡ ፈጽሞታል ። የቱርክን ፡ ሕዝብ ፡ በሥልጣኔ ፡ በሙሉ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ባያደርገው ፡ እንኳ ፡ በቀሩት ፡ መንግሥታት ፡ ዘንድ ፡ ተንቆ ፡ የነበረውን ፡ ያኸል ፡ የታፈረና ፡ የተከበረ ፡ አድርጎት ፡ ከማል ፡ ፓሻ ፡ በ1938 ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ፡ ሞተ ። የቱርክን ፡ ሕዝብ ፡ ሕግ ፤ ልማድና ፡ ባህል ፡ የሚያሻሽሉ ፡ እሱ ፡ የፈጸማቸው ፡ ተግባሮች ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። ጨካኝነትን ፡ መሣሪያ ፡ አድርጎ ፡ የሕዝብ ፡ አስተዳዳሪነትን ፡ ሥራ ፡ ሲያከናውን ፡ ባሳየው ፡ የሥራ ፡ ችሎታና ፡ ቈራጥነት ፡ ከትልቁ ፡ ጴጥሮስ ፡ ጋራ ፡ ያመሳስሉታል ። ጆን ፡ ጋንተር ፡ የተባለው ፡ ያሜሪካ ፡ ደራሲ ፡ ሲናገር ፡ በዲክታተርነታቸው ፡ ሂትለርና ፡ ሙሶሊኒ ፡ በሕዝባቸው ፡ ላይ ፡ የፈጸሙትን ፡ ሥራ ፡ ከማል ፡ ፓሻ ፡ ካከናወነው ፡ ጋራ ፡ ስናስተያየው ፡ የእነሱ ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ ቀልድና ፡ እንደ ፡ ጨዋታ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ፡ ሲል ፡ መስክሮለታል ። በከማል ፡ ፓሻ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ጕድለት ፡ ሆኖ ፡ የሚታይ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ። ይኸውም ፡ ያሳቡ ፡ ስፋነት ፤ የመንፈሱ ፡ ድፍረትና ፡ የጠባዩ ፡ ቈራጥነት ፡ ሙሉ ፡ የሥራ ፡ ፍሬውን ፡ እንዲሰጥ ፡ ቱርክን ፡ ለመሰለች ፡ ትንሽ ፡ አገር ፡ የታጨ ፡ ሊሆን ፡ አይገባውም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ከሱ ፡ ከራሱ ፡ የመጣ ፡ ነገር ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ ሲፈጠር ፡ ከተሰጠው ፡ ዕድል ፡ የመጣ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የምኞትን ፡ አስተያየት ፡ የሚመለከት ፡ እንጂ ፡ በታሪክ ፡ ብይን ፡ ውስጥ ፡ የሚገባ ፡ አይዶለም ።

ከማል ፡ ፓሻ ፡ ይህንን ፡ በቱርክ ፡ አገር ፡ ሲሠራ ፡ ቀድሞ ፡ ፋርስ ፡ ተብላ ፡ በምትጠራው ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ ኢራን ፡ በምትባለው ፡ አገር ፡ ሬዛ ፡ ሻህ ፡ የሚባለው ፡ ኀይለኛ ፡ ሰው ፡ ከድኽነት ፡ ተነሥቶ ፡ አገሪቱን ፡ ለማሠልጠን ፡ ድንቅ ፡ የሆነ ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ሠርቷል ፡፡ ይህንን ፡ ሰው ፡ መጀመሪያ ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ አህያ ፡ እየነዳ ፡ ሲሄድ ፡ ባቋቋሙ ፡ መርጠው ፡ ለወታደርነት ፡ ቀጠሩት ፡፡ በኋላም ፡ በጀግንነቱና ፡ ባስተዋይነቱ ፡ ነገሠ ፡፡ እሱም ፡ ላሁኑ ፡ ንጉሥ ፡ (ሻህ) ፡ አባቱ ፡ ነው ፡፡ ፓህሌቢ ፡ የተባለውን ፡ ነጋሢ ፡ ትውልድ ፡ (ዲናስቲ) ፡ የመሠረተ ፡ እሱ ፡ ነው ፡፡

# የተስፋ ፡ ጮራ ፡፡

ከሥልጣኔ ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ ተያይዘው ፡ የሚገኙትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጉዳዮች ፡ በመጠኑ ፡ በመልክ ፡ በመልካቸው ፡ ከተመለከትነው ፡ በኋላ ፡ እንግዲህ ፡ የታየንን ፡ አሳብ ፡ ለመናገር ፡ እንችላለን ፡፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የሰው ፡ ድካም ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የሰው ፡ ጥረት ፡ መጨረሻው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሊያውቀው ፡ የሚችል ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡፡ ማንም ፡ ነቢይ ፡ ወይም ፡ ማንኛውም ፡ ሊቅ ፡ ቢሆን ፡ ሊደርስበት ፡ አይችልም ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ከጥፋት ፡ ላይ ፡ በወደቀ ፡ ቍጥር ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የተስፋ ፡ ጮራ ፡ ያገኘ ፡ ለመሆኑ ፡ ታሪክ ፡ ያረጋግጥልናል ፡፡ አዳምና ፡ ሔዋን ፡ ፈጣሪያቸውን ፡ በበደሉ ፡ ጊዜ ፡ ከገነት ፡ ሲሰደዱ ፡ ጌታ ፡ ከሱ ፡ ዘር ፡ ተወልዶ ፡ እንደሚያድነው ፡ ለአዳም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገባለት ፡፡ በኖኅ ፡ ጊዜ ፡ የውሃ ፡ ጥፋት ፡ ሲሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከቍጣው ፡ ተመልሶ ፡ ሁለተኛ ፡ ዓለምን ፡ በውሃ ፡ ላያጠፋት ፡ ቃል ፡ ገብቶ ፡ ለዚህም ፡ መታሰቢያ ፡ እንዲሆን ፡ ቀስተ ፡ ደመናን ፡ ፈጠረ ፡፡ ስለዚህ ፡ የሰዎችን ፡ ክፋት ፡ እግዚአብሔር ፡ በመሐሪነቱ ፡ ጠባይ ፡ የሚመለከት ፡ መሆኑ ፡ የተለመደ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አሁንም ፡ የዘመናችን ፡ ሥልጣኔ ፡ ላደረገችው ፡ እርምጃ ፡ የተደከመውን ፡ ድካም ፡ ተመልክቶ ፡ በምሕረት ፡ ዐይን ፡ ሰውን ፡ እንደሚጐበኘው ፡ እናምናለን ፡፡

በዛሬዪቱ ፡ ሥልጣኔ ፡ ከሳይንስና ፡ ከቴክኒክ ፡ የተገኙትን ፡ ጥበቦች ፡ ስንመለከታቸው ፡ ለምሳሌ ፡ ባቡር ፤ አኤሮፕላን ፤ ራዲዮ ፡ እነዚህ ፡ ዘመናዊ ፡ የሆኑ ፡ መጓሪያዎች ፡ ዐላማቸው ፡ ተራርቀው ፡ የሚገኙትን ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ማቀራረብ ፡ ነው ፡፡ ይህ ፡ ይጠቅማል ፡ ወይስ ፡ ይጐዳል ? ለምሳሌ ፤ የሮማ ፡ መንግሥትና ፡ የግሪክ ፡ ሥልጣኔ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ፈረሱ ? ከሰሜን ፡ አውሮፓና ፡ ከእስያ ፡ ያሉት ፡ (barbares) የሚባሉት ፡ አሕዛቦች ፡ ስላጥለቀለቋቸው ፡ መሆኑን ፡ እናውቃለን ፡፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ የዓለምን ፡ ሕዝቦች ፡ የሚያቀራርቧቸው ፡ መጓሪያዎች ፡ ቢኖሯቸው ፡ ኖሮ ፡ ለመተዋወቅና ፡ አሳብ ፡ ላሳብ ፡ ተከፋፍለው ፡ ጕዳያቸውን ፡ በሰላም ፡ መንገድ ፡ ለመጨረስ ፡ ይረዳቸው ፡ ነበር ፡፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ የዓለምን ፡ ሕዝቦች ፡ እንዲለያዩ ፡ የሚያደርጋቸው ፡ አንዱም ፡ የቋንቋ ፡ ጕዳይ ፡ ነበር ፡፡ አሁን ፡ ግን ፡ በቋንቋ ፡ ለመገናኘት ፡ ችለዋል ፡፡ እንደዚሁም ፡ የሕክምና ፡ ዕውቀት ፡ መስፋፋት ፡ መጥፎ ፡ ነው ፡ አይባልም ፡፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡

ክርስቶስ ፡ በሰዎች ፡ መካከል ፡ በተገኘበት ፡ ጊዜ ፡ ዕውራንን ፡ ሲያበራ ፡
አንካሶችን ፡ ቆመው ፡ እንዲሄዱ ፡ ሲያደርግ ፤ ለምጻሞችን ፡ ሲያነጻና ፡
ሙታንን ፡ ሲያስነሣ ፡ መታየቱ ፡ በደዌ ፡ ለሚሠቃዩት ፡ ሰዎች ፡ ማዘን ፤
ሕመማቸው ፡ የሚታገሥበትንም ፡ መንገድ ፡ ለማግኘት ፡ በመፈለግ ፡ ልን
ረዳቸው ፡ እንደሚገባን ፡ ሲያስተምረን ፡ ነው ። የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ እስከ ፡
ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በመካከላቸው ፡ ያለውን ፡ አለመግባባት ፡ በውጊያና ፡ እርስ ፡
በርስ ፡ በመተላለቅ ፡ ሲወስኑ ፡ በመኖራቸው ፡ በጦርነት ፡ እየተቀጠ
ቀጡ ፡ ከተሞቻቸው ፡ እየፈረሱና ፡ አገራቸውም ፡ ከመከራና ፡ ከድኽነት ፡
ላይ ፡ እየወደቀ ፡ በመሄዳቸው ፡ ሰብአዊ ፡ ስሜት ፡ ያለው ፡ ፍጡር ፡ ሁሉ ፡
ይህን ፡ በማየት ፡ ኀዘን ፡ ሳይሰማው ፡ ሊቀር ፡ አይችልም ። ወደ ፡ ፊት ፡
ግን ፡ የቦታን ፡ መራራቅ ፡ ደምስሰው ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ እንዲቀራረቡ ፡
በሚያደርጓቸው ፡ ዘመናዊ ፡ መሣሪያዎች ፡ አማካይነት ፡ እየተገናኙ ፡
በመካከላቸው ፡ የሚፈጠረውን ፡ ችግር ፡ በሰላም ፡ መንገድ ፡ ሊጨርሱት ፡
ይችላሉ ። ይህንንም ፡ ለማድረግ ፡ የሚችሉት ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡
ወኪሎች ፡ በሚገኙበት ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ መልክ ፡ በተቋቋመ ፡
ጉባኤ ፡ አማካይነት ፡ ሊሆን ፡ ያስፈልጋል ። እንዲሁም ፡ በሳይንስ ፡
በኩል ፡ የሚወለዱት ፡ ጥበቦች ፡ ሁሉ ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ መተላለቂያ ፡ የሚ
ሆን ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ በመሥራት ፡ ፈንታ ፡ ጠቃሚ ፡ ለሆነ ፡ ነገር ፡ እን
ዲውሉ ፡ ከተደረገ ፡ ከተድላ ፡ ድኽነት ፤ ከጤንነት ፡ በሽታ ፤ ከመብላት ፡
መራብ ፤ ከመቀራረብ ፡ መራራቅ ፡ ይሻላል ፡ ለማለት ፡ ኀሊናችን ፡ እንደ ፡
ምን ፡ ይፈቅድልናል ? ስለዚህ ፡ በመጠናት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የሳይንስና ፡
የቴክኒክ ፡ ዕውቀት ፡ እንደዚሁም ፡ የሰውን ፡ ጠባይ ፡ ለማረም ፡ ሊቃው
ንት ፡ የሚደክሙበትን ፡ አሳብ ፡ ስናስተውለው ፡ መልካም ፡ ዘመን ፡ ይመ
ጣል ፡ ብለን ፡ ማመን ፡ ይገባናል ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከባድ ፡ ሆኖ ፡ ከሚ
ያንዣብበው ፡ ሥጋትን ፡ ከተሸከመ ፡ ጥቍር ፡ ደመና ፡ ውስጥ ፡ ፈልቆ ፡
የወጣ ፡ ብሩሃናዊ ፡ የሆነ ፡ የተስፋ ፡ ጮራ ፡ ይታየናል ። ከሁለተኛው ፡ የዓ
ለም ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ጦርነት ፡ ሁሉንም ፡ በጠቅላ
ላው ፡ የሚጐዳና ፡ ለማንም ፡ የማይበጅ ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ ተረዱት ፡ ለመ
ቀራረብ ፡ ፈቅደው ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅትን ፡ ፈጠሩ ። እሱም ፡
ብዙ ፡ ጕድለት ፡ እንዳለው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡
እየተሻሻለ ፡ እንደሚሄድና ፡ ከሚታሰበው ፡ ዓላማ ፡ ሊደርስ ፡ የሚቻል
በት ፡ መንገድ ፡ እንደሚገኝለት ፡ ማመን ፡ ይገባል ። የሚታየው ፡ ከሁ
ሉም ፡ በኩል ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ መኖሩ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ መሻ
ሻል ፡ የሚፈጸመው ፡ ከሶስተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ ወይስ ፡
በፊት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አናውቅም ።



በእግዚአብሔር ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ይኸ ፡ ሲሆን ፡ በሰዎች ፡ በኩ
ልም ፡ እንደዚሁ ፡ ተስፋ ፡ እንዲኖረን ፡ የሚረዳን ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ይገኛል ።
ለምሳሌ ፤ ከመጀመሪያው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ በፊት ፡ ነጮች ፡ የዓለምን ፡
ሕዝቦች ፡ በእግራቸው ፡ ረግጠው ፡ ዘለዓለም ፡ ለማኖር ፡ አሳብ ፡ ነበራ
ቸው ። እነሱ ፡ ከሳይንስ ፤ ከቴክኒክና ፡ ከኢንዱስትሪ ፡ ያገኙትን ፡ ጥበብ ፡
ሌሎቹ ፡ ደርሰውበት ፡ ይወዳደሩናል ፡ ብለው ፡ ስላልጠረጠሩና ፡ በሌላም ፡
በምንም ፡ ዐይነት ፡ መንገድ ፡ በመካከላቸው ፡ ያለውን ፡ ብልጫ ፡ የሚቀ
ንሰው ፡ ነገር ፡ ይመጣል ፡ ብለው ፡ ስላላሰቡ ፡ አስተያየታቸው ፡ በንቀትና ፡
በትዕቢት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ጦርነቱ ፡ ካላሰቡት ፡
በላይ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ቈይቶ ፡ የደረሰባቸው ፡ ጕዳት ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡
ሆኖ ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፡ ተገዥዎቻቸው ፡ በሆኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ነጻነ
ታቸው ፡ የተፈጠረውን ፡ የመንፈስ ፡ መንቀሳቀስ ፡ ለማስወገድ ፡ አልቻ
ሉም ። ስለዚህ ፡ ጕዳዩን ፡ በትዕቢትና ፡ በጕልበት ፡ ከመያዝ ፡ ይልቅ ፡
በትዕግሥትና ፡ ባስተዋይነት ፡ መመርመር ፡ የተሻለ ፡ መሆኑን ፡ ዐወቁት ።
ሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ደግሞ ፡ በመንፈስም ፡ ሆነ ፡ በግዙፍ ፡
አካል ፡ በኩል ፡ ያላቸውን ፡ ጕልበት ፡ በጣም ፡ አድርጎ ፡ ስላደቀቀው ፡
በዚያው ፡ መጠን ፡ ለተጠቁት ፡ ሕዝቦች ፡ የበለጠ ፡ ተስፋ ፡ ሰጥቶ ፡ መንፈ
ሳቸው ፡ እየበረታ ፡ እንዲሄድ ፡ አደረገው ። ቅኝ ፡ አገሮች ፡ የሌላቸው ፡
መንግሥታት ፡ እንደ ፡ መስኮብና ፡ እንደ ፡ አሜሪካ ፡ ያሉት ፡ በኢንተርና
ሲዮናል ፡ ፖለቲካ ፡ በኩል ፡ የበላይነቱን ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ ያዙ ፡ ተገዥዎች ፡
የሆኑትን ፡ ሕዝቦች ፡ ይደግፏቸው ፡ ጀመር ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ነጻነታቸ
ውን ፡ ለተገፈፉት ፡ ሕዝቦች ፡ ነጻነታቸውን ፡ መስጠት ፡ ግዴታ ፡ የሆ
ነበት ፡ ጊዜ ፡ ደረሰ ።

ስለዚህ ፡ ሁለቱ ፡ የዓለም ፡ ጦርነቶች ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ እንዲወለድ ፡
የረዱ ፡ የምጥ ፡ ሰዓት ፡ ሆነው ፡ ተቈጥረዋል ። ትልቅ ፡ ጭንቅ ፡ ሲመጣ ፡
መልካም ፡ ነገር ፡ መወለዱ ፡ አይቀርም ። የሁከት ፡ ሰዓት ፡ በመጣ ፡ ቍ
ጥር ፡ ሰዎች ፡ አስተዋይነትን ፡ ይማራሉ ።

እንደዚሁም ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰዎችን ፡ ከስሕተት ፡ ለመመለስ ፡ ሲፈ
ልግ ፡ ብዙ ፡ ምክንያት ፡ ይፈጥራል ። ከፈርዖን ፡ እጅ ፡ ሕዝበ ፡ እስራኤ
ልን ፡ ነጻ ፡ ለማውጣት ፡ ሲያስብ ፡ ሙሴን ፡ አስነሣ ። የእስራኤል ፡ ሕ
ዝብ ፡ ከባርነት ፡ ቀንበር ፡ እንዲወጣ ፡ የተወሰነበት ፡ ጊዜ ፡ መድረሱን ፡ ለፈ
ርዖን ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ አስረዳው ። ፈርዖንም ፡ በእንቢተኛነቱ ፡ ጸንቶ ፡
ቢያስቸግር ፡ በባሕረ ፡ ኤርትራ ፡ ሰጥሞ ፡ እንዲቀር ፡ በማድረግ ፡ ለብ
ቻው ፡ ነጥሎ ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ ቀጣው ፡ እንጂ ፡ በሱ ፡ ኀጢአት ፡ የግብ
ጽን ፡ ሕዝብ ፡ በሙሉ ፡ አላጠፋውም ።

አሁንም ፡ የዘመናችን ፡ ሥልጣኔ ፡ በሁለት ፡ ነገሮች ፡ ተከፍላ ፡ ከት ልቅ ፡ ፈተና ፡ ላይ ፡ የወደቀች ፡ ሆና ፡ ትታያለች ። ባንድ ፡ በኩል ፡ የማ ቴሪያሊስም ፡ ኀይል ፡ በጣም ፡ የገነነ ፡ ሆኖ ፡ በመታየቱ ፡ አብዛኞቹ ፡ ሰዎች ፡ በሰው ፡ ልጅ ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ውስጥ ፡ የፍርድን ፡ የሞራልና ፡ የመንፈ ስን ፡ ጕዳይ ፡ ዋጋ ፡ እንደሌለው ፡ አድርገው ፡ ከመቍጠር ፡ ደርሰዋል ። በዐ ይን ፡ የሚታይና ፡ በእጅ ፡ የሚዳሰስ ፡ ሀብትና ፡ ጕልበት ፡ ካልሆነ ፡ ከዚህ ፡ ውጭ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ሞኝነትና ፡ እንደ ፡ ድንቍርና ፡ አድርገው ፡ ይመለከቱታል ። እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ በግራና ፡ በቀኝ ፡ እንዲያይና ፡ በግራና ፡ በቀኝ ፡ እንዲሰማ ፡ ሁለት ፡ ዐይኖችና ፡ ሁለት ፡ ጆሮች ፡ እንደ ፡ ሰጠው ፡ ሁሉ ፡ የዚያኛውንና ፡ የዚህኛውን ፡ ዐለሞች ፡ ጕዳዮች ፡ ሳይዘነጋ ፡ ሁለቱንም ፡ አጣምሮ ፡ እንዲያስብ ፡ ነፍስና ፡ ሥጋ ፡ ሰጠው ። ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ የዓለም ፡ ሰዎች ፡ የነፍስ ፡ መሣሪያዎች ፡ የሆኑ ትን ፡ ሞራልንና ፡ መንፈስን ፡ ዘንግተውና ፡ ክደው ፡ የሥጋንና ፡ የምድ ርን ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ መያዛቸው ፡ አንድ ፡ ዐይን ፤ አንድ ፡ ጆሮ ፡ ይበቃናል ፡ ብለው ፤ ሁለተኛውን ፡ ዐይንና ፡ ሁለተኛውን ፡ ጆሮ ፡ አውጥተውና ፡ ቈር ጠው ፡ ወይም ፡ ደፍነው ፡ እንደመቀነስ ፡ ያኽል ፡ ሊቈጠርባቸው ፡ ይገ ባል ። ከወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ ጋራ ፡ የሚያገናኘውን ፡ መሣሪያ ፡ ሲሠር ዙት ፡ ጕዳቱ ፡ የቱን ፡ ያኽል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መሆኑን ፡ በቀላሉ ፡ ልንገም ተው ፡ እንችላለን ።

የዛሬ ፡ ዘመን ፡ ሥልጣኔ ፡ ጥበብ ፡ የተቋቋመው ፡ በሚጨበጥ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ኤኮኖሚ ፤ እስታቲስቲክ ፤ ኢንዱስትሪ ፤ ፋናንስ ፤ ቴክ ኒክ ፤ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ሥራቸውን ፡ የሚያከናውኑት ፡ አንድና ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ ሁለትና ፡ ሁለት ፡ አራት ፡ እያሉ ፡ ነው ። ለማንኛውም ፡ ጥበብ ፡ መሠረቱ ፡ ቍጥር ፡ ነው ። አሜሪካ ፡ ዛሬ ፡ ከቀሩት ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ የምትበልጠው ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ስናስብ ፡ የምናገኘው ፡ መልስ ፡ በያመቱ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ሚሊዮን ፡ ቶን ፡ ብረት ፡ ታቀልጣ ለች ፡ የሚል ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ ለሁለት ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ የሚበቃ ፡ ብረትና ፡ ቤንዚን ፡ አላት ። ያውሮፓ ፡ ሕዝቦች ፡ ከየፋብሪካዎቻቸው ፡ የሚወጣውን ፡ ሸቀጥ ፡ የሚሸጡት ፡ ለሕዝባቸው ፡ ሲሆን ፡ ገበያቸው ፡ በሕዝባቸው ፡ መ ጠን ፡ ጠባብ ፡ ነው ። አሜሪካ ፡ ግን ፡ ለሁለት ፡ መቶ ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ ትሠራለች ። (የውጭው ፡ ገበያ ፡ ሳይቈጠር ፡ ማለት ፡ ነው) ። መስኮብም ፡ እንደዚሁ ፡ በብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ ቶን ፡ የሚቈጠር ፡ ማዕድን ፡ በመሬቷ ፡ ውስጥ ፡ ያላት ፡ ሲሆን ፡ የሕዝቧ ፡ ቍጥር ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሃያ ፡ ሚሊዮን ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ፋብሪኮቿ ፡ የሚሠሩት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕቃ ፡ ለሁለት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ የሚያገለግል ፡ ነው ። አሜሪካና ፡ መስኮብ ፡ እያንዳን



ዳቸው ፡ ለሁለት ፡ መቶ ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ የሚሠሩ ፡ ሲሆኑ ፡ ለምሳሌ ፡ እንግሊዝና ፡ ፈረንሳይ ፡ ላርባ ፡ አምስት ፡ ሚሊዮንና ፡ ላምሳ ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ ብቻ ፡ እየሠሩ ፡ ከአሜሪካና ፡ ከመስኮብ ፡ ጋራ ፡ ሊወዳደሩ ፡ አይ ችሉም ።

የአኤሮፕላንና ፡ የባቡር ፡ ሥራ ፡ እየተሻሻለ ፡ ሲሄድ ፡ ከሁሉም ፡ የበለጠ ፡ እርምጃ ፡ የተደረገው ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማወቅ ፡ ሲፈለግ ፡ በሰዓት ፡ ስንት ፡ ኪሎሜትር ፡ ወይም ፡ ማይልስ ፡ እንደሚሄድ ፡ ይጠየቃል ። አይንሽታይን ፡ በሳይንስ ፡ በኩል ፡ የገለጠው ፡ ጥበብ ፡ የሚ ያስደንቅ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀው ፡ ማንኛውም ፡ በድን ፡ ፍጡር ፡ (ማቲየር) ፡ እንዳልነበረ ፡ ሲሆን ፡ የሚሰጠው ፡ ጕልበት ፡ በተለምዶ ፡ አገልግሎቱ ፡ ከሚሰጠው ፡ በላይ ፡ አምስት ፡ ሚሊያርድ ፡ ጊዜ ፡ የላቀ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። እንሆ ፡ ለግዙፍ ፡ ጥበብ ፡ ሁሉ ፡ መግለ ጫው ፡ ቍጥር ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ አንድ ፡ መንግሥት ፡ የጦር ፡ ጕል በቱ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማወቅ ፡ ሲፈልግ ፤ ስንት ፡ የጦር ፡ ዲቪዚዮን ፤ ስንት ፡ ብረት ፡ ለበስ ፡ መኪና ፤ ስንት ፡ ታንክ ፤ ስንት ፡ አኤሮፕላን ፡ አ ለው ? ተብሎ ፡ ይጠየቃል ። ሰባ ፡ ዓመት ፡ ከማይሞላ ፡ ዘመን ፡ በፊት ፡ ግን ፡ የሚጠየቀው ፡ የሕዝቡ ፡ ጀግንነት ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ? ፈሪ ፡ ነው ፡ ጐበዝ ? ድካም ፡ ይችላል ፡ አይችልም ? ሞራሉ ፡ ጥብቅ ፡ ነው ፡ ደካማ ? እየተባለ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ቀረ ። ወደ ፡ ፊት ፡ ደግሞ ፡ ይበ ልጥ ፡ እየቀረ ፡ ይሄዳል ።

በቍጥር ፡ የማይተረጐም ፡ ጕልበት ፡ የሌለው ፡ መንግሥት ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ ዋጋ ፡ የለውም ። እሱም ፡ የተፈራ ፡ ለመሆን ፡ ሲፈልግ ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ ዲቢዚዮን ፡ አሰልፋለሁ ፤ ይህን ፡ ያኽል ፡ አኤሮፕላኖች ፡ አሉኝ ፤ በባንክ ፡ ይኸን ፡ ያኽል ፡ የወርቅ ፡ ገንዘብ ፡ አስቀምጫለሁ ፡ ማለት ፡ አለበት ።

ኢትዮጵያ ፡ በተወረረችበት ፡ ሰዓት ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ «እግዚአብሔርና ፡ ታሪክ ፡ ለምትሰጡት ፡ ፍርድ ፡ ምስክር ፡ ሆ ነው ፡ ይመለከታሉ» ። ሲሉ ፡ በዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ ቀርበው ፡ በተናገሩት ፡ ቃል ፡ የዓለም ፡ ኃያላን ፡ የሆኑትን ፡ በአእም ሯቸው ፡ ውስጥ ፡ የሚያንቀላፋውን ፡ የኅሊና ፡ ሕይወት ፡ ሊቀሰቅሱት ፡ ሞክረው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ በሒሳብ ፡ በሚተረጐምበትና ፡ በቍጥር ፡ በሚገለጥበት ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ ኢትዮጵያ ፡ የጦር ፡ መሣሪያና ፡ ገንዘብ ፡ ከሌላት ፡ ጕዳይዋ ፡ መድኀኒት ፡ የለውም ፡ በማለት ፡ ሁሉም ፡ እን ዳልሰማ ፡ ሰምተው ፡ አሳልፈው ፡ ለጠላት ፡ ሰጧት ። እግዚአብሔር ፡ ግን ፡

የታሪክ ፡ ተአምር ፡ ሆኖ ፡ በሚቈጠር ፡ አኳኋን ፡ በጥበቡ ፡ ከጠላት ፡ እጅ ፡ መንጥቆ ፡ አወጣት ።

ነገር ፡ ግን ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ የዓለም ፡ ሰዎች ፡ መቼ ፡ በተአምር ፡ ያምናሉ ? ኢትዮጵያ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተአምር ፡ ነጻ ፡ ወጣች ፡ ከማለት ፡ ይልቅ ፡ ጕዳዩን ፡ በታሪክ ፡ አካሄድ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ ዘርዝረው ፡ ማስረዳትን ፡ ይመርጣሉ ።

የጋንዲን ፡ ጕዳይ ፡ ደግሞ ፡ እስቲ ፡ ለመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ አሁንም ፡ ደግመን ፡ እናስተውለው ። የጋንዲ ፡ አስተያየት ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ላለው ፡ ለህንድ ፡ ዘለቄታ ፡ የማይበጅ ፡ መሆኑን ፡ ባለፈው ፡ ሌላ ፡ ምዕራፍ ፡ አሳስበናል ። ነገር ፡ ግን ፡ የወንጌልን ፡ ቃል ፡ በሙሉ ፡ የፈጸመ ፡ ፍጹም ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በደግነት ፡ ላይ ፡ የተቋቋመው ፡ የሱ ፡ ፖሊቲካ ፡ እንዲህ ፡ በቀላሉ ፡ የሚናወጥ ፡ አይዶለም ። እናንተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ የወንጌልን ፡ ቃል ፡ የተቀበላችሁ ፡ ከሆናችሁ ፤

«ቀኝ ፡ ጕንጭኽን ፡ ቢመታኽ ፡ ግራኽን ፡ ስጠው ፤
ካባኽን ፡ ቢነጥቅኽ ፡ ቀሚስኽን ፡ ጨምርለት ፤
፩ ፡ ምዕራፍ ፡ ቢጐትትኽ ፡ ፪ ፡ ምዕራፍ ፡ ሂድለት» ፡

ተብሎ ፡ በወንጌል ፡ የተጻፈውን ፡ ቃል ፡ የምትፈጽሙት ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ ነው ? በጦርነት ፡ ሲወጓችሁ ፡ መልሳችሁ ፡ ከተዋጋችሁ ፤ ሊገድሏችሁ ፡ ሲፈልጉ ፡ አልሞት ፡ ባይ ፡ ተጋዳዮች ፡ ሆናችሁ ፡ ደም ፡ ካፈሰሳችሁ ፡ የወንጌልን ፡ ቃል ፡ አፈረሳችሁ ፡ እንጂ ፡ መቼ ፡ ፈጸማችሁት ። ክርስቶስ ፡ ሲገርፉት ፤ ሲያዋርዱትና ፡ ሲሰቅሉት ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ በትዕግሥት ፡ መቀበሉ ፡ በቃል ፡ ያስተማረውን ፡ ትምህርት ፡ በሥራ ፡ ፈጽሞ ፡ ለማሳየትና ፡ እናንተም ፡ እንደ ፡ እሱ ፡ እንድታደርጉ ፡ ለማስተማር ፡ አይዶለም ፡ ወይ ? ብሎ ፡ ቢጠይቅ ፡ ምን ፡ ይመለስለታል ?

የህንድ ፡ ሕዝብ ፡ በጋንዲ ፡ መሪነት ፡ ስለ ፡ ነጻነቱ ፡ ይታገል ፡ በነበረበት ፡ ሰዓት ፡ እንግሊዞች ፡ በጠበንጃና ፡ በመትረየስ ፡ ህንዶችን ፡ ሲፈጅዋቸው ፡ ጋንዲ ፡ ራሳችሁን ፡ መሥዋዕት ፡ በማድረግ ፡ እለቁ ፡ እንጂ ፡ በተከላካይነት ፡ እንግሊዞችን ፡ አትግደሏቸው ። እኔ ፡ እንግሊዞችን ፡ ድል ፡ ላደረጋቸው ፡ የምፈልገው ፡ በምቀበለው ፡ መከራ ፡ እንጂ ፡ በኀይል ፡ ሥራ ፡ አይዶለም ። ጠላታችንንም ፡ ቢሆን ፡ እንድንገድለው ፡ አልተፈቀደልንም ። ሰው ፡ የፈጣሪነት ፡ ችሎታ ፡ ስለሌለው ፡ እንደዚሁም ፡ የገዳይነት ፡ መብት ፡ ሊኖረው ፡ አይገባም ፡ ብሎ ፡ ከልክሏቸዋል ። እንደዚሁም ፡ ያገሩ ፡ ሰዎች ፡ እነሱ ፡ ሲገድሉን ፡ እኛ ፡ ስለምን ፡ ዝም ፡ እንላለን ? ቢሉት ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ኀጢአት ፡ ሲሠራ ፡ እኔ ፡ እንዴት ፡ ዝም ፡ እላለሁ ፡ ለማለት ፡ እንዴት ፡ ይቻላል ? ሲል ፡ መልሶላቸዋል ። ስለዚህ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ፍጹም ፡ ደግ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ስሕተት ፡ ሠርቷል ፡ ለማለት ፡ እንዴት ፡ ይቻላል ? ይህንን ፡ ስንመለከተው ፡ ጋንዲ ፡ ብቻውን ፡ በከሳሽነት ፡ ካንድ ፡ ወገን ፡ ሆኖ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሁሉ ፡ በተከሳሽነት ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ሆነው ፡ ክርስቲያኖች ፡ ነን ፡ ትላላችሁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የወንጌልን ፡ ቃል ፡ ካልፈጸማችሁ ፡ ውሸት ፡ ነው ፡ ክርስቲያኖች ፡ አይደላችሁም ፡ ሲል ፡ ይወቅሣቸዋል ።



ቪኖባ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ እንዳሳሰበው ፡ ሁሉ ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ትልቅ ፡ ጕዳይ ፡ በምሥራቅና ፡ በምዕራብ ፡ ማለት ፡ በመስኮብና ፡ በአሜሪካ ፡ መካከል ፡ የተፈጠረው ፡ ጠብ ፡ መስሎ ፡ ይታየናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ውሸት ፡ ነው ። አሜሪካ ፡ የምትፈልገው ፡ ምንድነው ? ሀብቷን ፡ መሣሪያ ፡ አድርጋ ፡ ሥራዋን ፡ ለመሥራትና ፡ ንግዷን ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ለመዘርጋት ፡ ነው ። መስኮብ ፡ የምትፈልገው ፡ ምንድነው ? ከምድራዊ ፡ ሲሳይ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ የለውም ፡ ነፍስና ፡ ሥጋ ፡ ካንድ ፡ ምንጭ ፡ የተቀዱ ፡ ልዩነት ፡ የሌላቸው ፡ ናቸው ፡ ብላችሁ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ አብራችሁ ፡ እመኑ ፡ ለማለት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ሁለቱም ፡ የሚከተሉት ፡ በማቴሪያሊስም ፡ የተደገፈ ፡ ዐላማ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አደራረጉ ፡ ይለወጣል ፡ እንጂ ፡ ግቡ ፡ ያው ፡ ነው ።

ትልቅ ፡ ጕዳይ ፡ ሆኖ ፡ ዛሬ ፡ በዓለም ፡ ፊት ፡ የተደቀነው ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ኢንዱስትሪ ፤ ኤኮኖሚ ፤ ሳይንስ ፤ ቴክኒክ ፤ ፊናንስ ፡ በሚባሉ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አጠራር ፡ የተሸፈነው ፡ ማቴሪያሊስም ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ፍቅር ፤ ሞራል ፡ ፍርድ ፤ ኅሊና ፡ መንፈስ ፤ በጎ ፡ ምግባር ፡ በሚባሉ ፡ ስሞች ፡ የምትጠራው ፡ ሃይማኖት ፡ በእነዚህ ፡ በሁለቱ ፡ ማለት ፡ በማቴሪያሊስምና ፡ በሃይማኖት ፡ መካከል ፡ የተነሣው ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ እየከረረ ፤ እያመረቀዘ ፡ የሚሄደው ፡ ጠብ ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በስደት ፡ ዘመን ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ በነበሩ ፡ ጊዜ ፡ ሙሶሊኒ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የሆኑት ፡ እዚያ ፡ ተቀምጠው ፡ የሚጠብቁት ፡ ከቶ ፡ እንዴት ፡ ያለውን ፡ ተስፋ ፡ ይሆን ? ብሎ ፡ ጠየቀ ፡ ይባላል ። ተስፋቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ሰዎች ፡ ቢመልሱለት ፤ እግዚአብሔርን ፡ ከሆነ ፡ የኔንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ጨምሬላቸዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፡ ይባላል ። ይህንን ፡ ቃል ፡ ባይናገረውም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ፈጽሞታል ።

የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ስንት ፡ የጦር ፡ ዲቪዚዮን ፡ አላቸው ፡ ይሆን ? ሲል ፡ እስታሊን ፡ በማሾፍ ፡ ተናገረ ፡ ይባላል ። የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስም ፡ ይህንን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ልጄ ፡ ስታሊን ፡ የኔን ፡ የጦር ፡ ዲቪዚዮን ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ሳይሆን ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ ያገኛቸዋል ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ መለሱ ፡ ይነገራል ።

ጋንዲ ፡ እንግሊዞችን ፡ ያለጦርነት ፡ ያለኀይል ፡ ሥራ ፡ በሰላማዊ ፡ ትግል ፤ በመንፈስ ፡ ጕልበት ፤ በፍቅር ፡ ውጊያ ፡ ብቻ ፡ ከህንድ ፡ አገር ፡ ሊያስወጣቸው ፡ ፎክሮ ፡ በተነሣበት ፡ ዘመን ፡ የፕሮቴስታንት ፡ ካህን ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንግሊዝን ፡ የመሰለ ፡ ገናና ፡ የሆነ ፡ መንግሥት ፡ አንተ ፡ አንድ ፡ ታናሽ ፡ ሰው ፡ በመንፈስ ፡ ጕልበት ፡ ድል ፡ ለማድረግ ፡ እችላለሁ ፡ ብለኽ ፡ የተነሣኸው ፡ እንዲያው ፡ ለነገሩ ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ የሞኝነት ፡ እምነት ፡ በልብኽ ፡ ያሳደረብኽ ፡ ከቶ ፡ ምን ፡ ይሆን ? ብሎ ፡ ጠየቀው ፡ ይባላል ። ጋንዲም ፡ በመንፈሴ ፡ ውስጥ ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ ጕልበት ፡ የሚገኝ ፡ መሆኑን ፡ መጀመሪያ ፡ የተረዳሁት ፡ ወንጌልን ፡ ባነበብኩ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ባገሬ ፡ ሃይማኖት ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ የተጻፈው ፡ ትምህርት ፡ ሁሉ ፡ የተገለጠልኝ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። በእጅ ፡ የያዙት ፡ ወርቅ ፡ እንደ ፡ መዳብ ፡ ይቈጠራል ፡ እንደሚባለው ፡ ተረት ፡ የክርስቶስ ፡ ትምህርት ፡ ክርስቲያን ፡ ላልሆነው ፡ ለጋንዲ ፡ እንደ ዚህ ፡ ሲጠቅመው ፡ ክርስቲያኖች ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ እሱን ፡ አስቀምጠው ፡ ሌላ ፡ እውነት ፡ ሊፈልጉ ፡ ወደ ፡ ህንድ ፡ አገር ፡ ይሄዳሉ ።

ማቴሪያሊስምና ፡ ሃይማኖት ፡ ከመቼውም ፡ ይልቅ ፡ ጽኑ ፡ በሆነ ፡ ጠብ ፡ ላይ ፡ በሚገኙበት ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ እግዚአብሔር ፡ የሃይማኖት ፡ መሠረቱና ፡ ምንጩ ፡ እሱ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሕዝበ ፡ እስራኤልን ፡ ከባርነት ፡ እንዳወጣው ፡ ሁሉ ፡ ሃይማኖትንም ፡ ከማቴሪያሊስም ፡ ቀንበር ፡ እንደሚያድናት ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ። ለእግዚአብሔር ፡ የሚሳነው ፡ ነገር ፡ የለምና ።

የኢትዮጵያ ፡ ጕዳይ ፡ በዓለም ፡ ፊት ፡ እንዲፈጠርና ፡ የህንድ ፡ ሕዝብ ፡ ስለ ፡ ነጻነቱ ፡ እንዲከራከር ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴና ፡ ጋንዲ ፡ ማቴሪያሊስምን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እምነት ፡ ብቻ ፡ ድል ፡ እንዲመቱ ፡ ያደረገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ። ሰዎችን ፡ ከስሕተት ፡ ለመመለስ ፡ አሁንም ፡ ነገ ፡ ምን ፡ እንደሚፈጥር ፡ አናውቅም ። እምነት ፡ በልባችን ፡ ውስጥ ፡ ካለ ፡ እንድናለን ፤ ከሰዎች ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ እምነት ፡ የተፋቀች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ዓለም ፡ ትጠፋለች ።



እንደዚሁም ፡ ሰው ፡ በሃይማኖት ፡ እምነት ፡ እንጂ ፡ በሳይንስ ፡ እምነት ፡ ሊድን ፡ አይችልም ።

ክርስቶስ ፡ ዕውራን ፡ ዐይናቸው ፡ እንዲበራ ፡ ለምጻሞች ፡ እንዲነጹ ፤ የሞቱት ፡ እንዲነሡ ፡ ሲያደርግ ፡ እምነትኽ ፡ አዳነኽ ፡ ሲል ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የተናገረው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ። እነዚህ ፡ የማይገናኙ ፡ ሁለት ፡ ልዩ ፡ መንገዶች ፡ ናቸው ። ሰው ፡ ነፍሱን ፡ ከጥፋት ፡ የሚያድናት ፡ በማመን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በመመራመር ፡ አይደለም ። ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ስለ ፡ ዚህ ፡ ጕዳይ ፡ የተናገረውን ፡ በምዕራፍ ፡ ፩ ፡ ቍጥር ፡ ፲፰ ፡ እስከ ፡ ፳፭ ፡ ተመልከት ።

ለቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ በጻፈው ፡ መልእክቱ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፤

«መስቀል ፡ የሚናገረው ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ጥፋታቸው ፡ ለሚሄዱ ፡ ሰዎች ፡ እብደት ፡ ነው ፤ ለኛ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ኀይል ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተጽፏልና ፡ የጠቢባንን ፡ ጥበብ ፡ አጠፋዋለሁ ፤ የሊቃውንትንም ፡ ዕውቀት ፡ እንዳልነበረ ፡ አደርገዋለሁ ። (ኢሳ ፡ ፳፱-፲፬) ፡ ጥበበኛ ፡ ወዴት ፡ ነው ? ዐዋቂ ፡ የት ፡ አለ ? ተከራካሪ ፡ የት ፡ ነው ? እግዚአብሔር ፡ የዓለምን ፡ ጥበብ ፡ ከንቱ ፡ አላደረገውምን ? ዓለም ፡ በጥበቧ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመለኮታዊነቱ ፡ ጥበብ ፡ ሳታውቀው ፡ ስለ ፡ ቀረች ፡ እግዚአብሔር ፡ በእሱ ፡ ያመኑትን ፡ ሰዎች ፡ እብደት ፡ በሆነ ፡ መልክቱ ፡ ሊያድናቸው ፡ ፈቃዱ ፡ ሆነ» ። *

ዓለም ፡ ከዚህ ፡ ከደረሰባት ፡ መጥፎ ፡ ፈተና ፡ ወጥታ ፡ ከደኅና ፡ ዘመን ፡ ትደርሳለች ፡ ብለን ፡ እንድናምን ፡ የሚያደርግልን ፡ አሁንም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ እናገኛለን ። በነጮች ፡ ዘንድ ፡ ልናደንቀውና ፡ ልናመሰግነው ፡ የሚገባን ፡ አንድ ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ አለ ። ይኸውም ፡ (ክሪቲክን) ፡ ዘለፋን ፡ የሥልጣኔ ፡ ዋና ፡ መሣሪያ ፡ አድርገው ፡ ሲሠሩበት ፡ መታየቱ ፡ ነው ። (élite) የሚባሉት ፡ ሊቃውንቶቻቸው ፡ ደራስያኖቻቸውም ፡ በሚሠራው ፡ ጥበብ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ጕድለት ፡ በርብረው ፡ ከመፈለግና ፡ ገልጠው ፡ ከማሳወቅ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ቦዝነው ፡ አያውቁም ። ጋንዲ ፡ ለምዕራባዊ ፡

* ስለ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ጥቅስ ፡ በፈረንሣይ ፡ (folie) በእንግሊዝ ፡ (foolishness) የሚለውን ፡ አማርኛው ፡ ባንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ ሞኝነት ፡ ሲል ፡ ባንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ ደካማነት ፡ ይለዋል ። እኛ ፡ ግን ፡ ትርጕሙን ፡ በመከተል ፡ እብደት ፡ ብለን ፡ ትክክለኛውን ፡ ቃል ፡ ሰጥተነዋል ።

ሥልጣኔ ፡ ያለውን ፡ መጥፎ ፡ አስተያየት ፡ ያገኘው ፡ ካውሮፓ ፡ ሊቃውንት ፡ መሆኑን ፡ ተመልክተነዋል ። አንዳንዶቹም ፡ ባንዳንዱ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የሚያመጡት ፡ ዘለፋ ፡ (ክሪቲክ) ፡ በጣም ፡ የከረረ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ በእውነቱ ፡ የተሠራውን ፡ የጥበብ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ ርባና ፡ የሌለውና ፡ የማይጠቅም ፡ አድርጎ ፡ ያሳያል ። ይህ ፡ ሁሉ፡ የመሻሻልን ፡ መንገድ ፡ ለመፈለግና ፡ ፍጹም ፡ ወደ ፡ ሆነ ፡ ሥልጣኔ ፡ ለመድረስ ፡ በማሰብ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ራሳቸውን ፡ ለማረም ፡ ይህንን ፡ ያኽል ፡ በሚተጉና ፡ በጎ ፡ ፈቃድም ፡ ባላቸው ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ የተዛነፈውን ፡ ለማቃናትና ፡ ከሚመጣው ፡ ጉዳት ፡ ለመዳን ፡ የሚቻልበትን ፡ መንገድ ፡ ያገኛሉ ፡ ብለን ፡ ለማመን ፡ የምንችልበትን ፡ ተስፋ ፡ ይሰጠናል ።

ራሳቸውን ፡ ለመዝለፍ ፤ ለመተቸት ፤ ለመናቅ ፤ ለመጠራጠር ፤ ያላቸው ፡ ጠባይ ፡ በጣም ፡ የጠነከረ ፡ በመሆኑ ፡ ይህ ፡ ኃይላቸውና ፡ ጥበባቸው ፡ የተሸፈነበት ፡ ምስጢር ፡ ነው ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ በፀሓይ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ አቶሞች ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እየፈነዱ ፡ ለፀሓይ ፡ የማይጠፋና ፡ የማይደክም ፡ ጉልበት ፡ እንደሚሰጧት ፡ ሁሉ ፤ ለእነሱም ፡ ይህ ፡ ክሪቲክን ፡ የሚያስወድድ ፡ ባሕርያቸው ፡ ጥበባቸው ፡ እንዳትሞትና፡ ዘለዓለም፡ ጉልበቷ ፡ እየታደሰ ፡ እንዲኖር ፡ ለማድረግ ፡ አገልግሏቸዋል ። ይህ ፡ የተከበረ ፡ ጠባይ ፡ በእነሱ ፡ ዘንድ ፡ እስካለ ፡ ድረስ ፡ ስለ ፡ ዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ያለን ፡ ተስፋ ፡ ሊሞት ፡ አይገባውም ።

የዓለም ፡ ሰዎች ፡ አሁን ፡ የሚገኙበት ፡ ሁኔታ ፡ በጫካ ፡ በጨለማና ፡ በዝናብ ፡ ውስጥ ፡ በሚሄዱ ፡ መንገዱ ፡ በጠፋባቸው ፡ ሰዎች ፡ ይመሰላል ። በማያውቁት ፡ አገር ፡ ገብተው ፡ በጫካ ፡ ውስጥ ፡ ሲሄዱ ፡ ይመሸባቸውና ፡ ዝናብም ፡ ሲይዛቸው ፡ የሚደፎስባቸውን ፡ ነገር ፡ እንመልከተው ። ባንድ ፡ በኩል ፡ ዝናብና ፡ በረዶ ፡ ይቀጠቅጣቸዋል ። ነፋስና ፡ ብርድ ፡ ያቈራምዳቸዋል ። ተርበዋል ፤ ተጠምተዋልም ። ከጨለማ ፡ በቀር ፡ ባይናቸው ፡ የሚያዩት ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለም ። ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ ደግሞ ፡ የዱር ፡ አውሬ ፡ እንዳይበላቸው ፡ ይፈራሉ ። ይህን ፡ በመሰለ ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፡ ተስፋ ፡ ቈርጠው ፡ ሲጓዙ ፡ በሩቅ ፡ የብርሃን ፡ ውጋጋን ፡ ይመለከታሉ ። ይህም ፡ ውጋጋን ፡ ከሁለት ፡ መስኮቶች ፡ የወጣ ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ቤቱ ፡ የሚታየው ፡ ከሩቅ ፡ ቢሆን ፡ ብርሃኑ ፡ ከመስኮቶች ፡ የወጣ ፡ መሆኑን ፡ ለይተው ፡ ዐውቀውታል ። የቤቱ ፡ ባለቤት ፡ ማን፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባያውቁትም ፡ ሰው ፡ ከሚኖርበት ፡ ቦታ ፡ በመድረሳቸው ፡ ብቻ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ። ከዝናብ ፤ ከበረዶ ፤ ከብርድ ፡ ድነው ፡ ከሚያርፉበት ፤ የሚበሉትና ፡ የሚጠጡት ፡ ነገር ፡ ከሚያገኙበት ፤ ተኝተው ፡ ከሚያድሩበት ፤



የዱር ፡ አውሬ ፡ እራት ፡ ከመሆን ፡ ከሚድኑበት ፡ ቦታ ፡ የደረሱ ፡ መሆናቸውን ፡ በማሰብ ፡ ደስታ ፡ ይሰማቸዋል ።

ሁከት ፡ በሞላበት ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ የሚኖሩ ፡ የዓለም ፡ ሰዎችም ፡ እንደዚሁ ፡ በእንዱስትሪ ፡ ምክንያት ፡ የመጣ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ሁከት ፡ የፍርድ ፡ መጉደል ፤ በሕዝቦች ፡ መካከል ፡ የተፈጠረ ፡ የቀለም ፡ ልዩነት ፤ በኢንቴርናሲዮናል ፡ ግንኙነት ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ አለመግባባት ፡ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ የፈጠሩት ፡ ሁከትና ፡ ችግር ፡ እንደ ፡ ጨለማ ፡ እንደ ፡ ዝናብ ፡ እንደ ፡ በረዶና ፡ እንደ ፡ ብርድ ፡ ሆነው ፡ ይቀጠቅጧቸዋል ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ጦርነት ፡ የሚባለው ፡ በዱር ፡ አውሬ ፡ ሊመሰል ፡ የሚችለው ፡ እንዳይመጣባቸውና ፡ ጨርሶ ፡ እንዳያጠፋቸው ፡ ከሁሉም ፡ የበለጠ ፡ ሥጋት ፡ ሆኖባቸዋል ። በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ሲሆኑ ፡ ጋንዲ ፡ ጦርነትና ፡ ደም ፡ መፋሰስ ፡ መናናቅና ፡ መተላለቅ ፡ ከሰዎች ፡ መካከል ፡ የተወገዱ ፡ ሆነው ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ በመካከላቸው ፡ ያለውን ፡ አለመግባባት ፡ በፍቅር ፡ በሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ ብቻ ፡ ሊጨርሱ ፡ ይችላሉ ፡ ሲል ፡ የፈጠረው ፡ «ያለ ፡ ኀይል» ፡ (non-violence) ተብሎ ፡ የተሠየመውን ፡ አዲስ ፡ ፍልስፍና ፤ አዲስ ፡ እምነት ፡ ባፍ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በሥራ ፡ እየፈጸመ ፡ አሳይቷል ።

እንደዚሁም ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ጦርነት ፡ ቢዋጉ ፤ በመካከላቸውም ፡ ብጥብጥ ፡ ቢፈጥሩ ፡ ይህን ፡ ለመሰለው ፡ በመንግሥታትና ፡ በሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ለሚገኘው ፡ ለማንኛውም ፡ ሁከት ፡ ሁሉ ፡ ምክንያቱ ፡ ድኽነት ፡ ነው ። ችግርና ፡ ድኽነት ፡ ከሰዎች ፡ ጫንቃ ፡ ላይ ፡ የሚወገዱበት ፡ ዘዴ ፡ ቢገኝ ፡ ኖሮ ፡ በሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ሰላምና ፡ ፍቅር ፡ ይወርድ ፡ ነበር ፡ ተብሎ ፡ ይታመናል ። ይህ ፡ እውነት ፡ ከሆነ ፡ የመጨረሻዎቹ ፡ የሳይንስ ፡ ሊቃውንት ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች፡ ሁሉ ፡ ከድኽነት ፡ ወጥተው ፡ በተድላ ፡ የሚኖሩበትን ፡ ሁኔታ ፡ ለማግኘት ፡ የአቶም ፡ ኀይል ፡ ለሰላማዊ ፡ ሥራ ፡ አገልግሎቱን ፡ እንዲሰጥ ፡ ያቀዱት ፡ አሳብ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ለማድረግ ፡ የሚችሉበትን ፡ ጊዜ ፡ መጠበቅ ፡ ያስፈልጋል ።

ጋንዲና ፡ የሳይንስ ፡ ሊቃውንት ፡ የወለዷቸው ፡ እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ትልቅ ፡ አሳቦች ፡ እነዚያ ፡ የጠቀስናቸው ፡ በጨለማና ፡ በዝናብ ፡ ውስጥ ፡ የሚጓዙ ፡ የመሸባቸውና ፡ መንገድ ፡ የጠፋባቸው ፡ መንገደኞች ፡ ከሩቅ ፡ ሆነው ፡ በተመለከቷቸው ፡ የብርሃን ፡ ውጋጋን ፡ በሚታይባቸው ፡ በነዚያ ፡ በሁለቱ ፡ መስኮቶች ፡ ይመሰላሉ ። ሁከትና ፡ ብጥብጥ ፡ ትዕቢትና ፡ ጥላቻ ፡ ጭካኔና ፡ ክፋት ፡ አስጨንቀው ፡ የያዟቸው ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ የሳይን

ስና ፡ የጋንዲ ፡ አሳቦች ፡ ተፈጽመው ፡ ሙሉ ፡ ሰላም ፡ ከሚጸናበት ፡ አ ዲስ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ገብተን ፡ ዕረፍት ፡ እናገኛለን ፡ ብለው ፡ የተስፋ ውን ፡ ጮራ ፡ በመመኘት ፡ በሩቅ ፡ ይመለከቱታል ። እጅግ ፡ ውብ ፡ ከመ ሆኑም ፡ የተነሣ ፡ ልባቸው ፡ በጣም ፡ ይጓጓለታል ።

ወይስ ፡ ደግሞ ፡ በካፍካ ፡ ድርሰት ፡ ውስጥ ፡ እንደምናገኘው ፡ ታሪክ ፡ እንደዚያ ፡ እንደ ፡ መስፍኑ ፡ ግቢ ፡ ቀላድ ፡ ጣዩ ፡ በሩቅ ፡ እያ የው ፡ መቼም ፡ እንዳይገባ ፡ ተከልክሎ ፡ እንደ ፡ ቀረ ፡ ሁሉ ፡ እሱ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድረስ ፡ ተስፋ ፡ ሳይቈርጥ ፡ ባለመታከት ፡ በከንቱ ፡ ሲጣጣር ፡ እንደ ፡ ኖረው ፡ ሁሉ ፡ እንነዚህም ፡ ሁለት ፡ የተስፋ ፡ ጮራ ዎች ፡ መቸም ፡ የማይፈጸሙ ፡ ከንቱ ፡ ነገሮች ፡ ሆነው ፡ ይቀሩ ፡ ይሆን ? በማለት ፡ የሚያጠራጥረን ፡ ነው ።

ሐኪሞች ፡ የሰውን ፡ ውስጣዊ ፡ አካል ፡ በመቅደድ ፡ ሳይጠየፉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ በሽታዎች ፡ በሕዋሳቶቹ ፡ ላይ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ጉዳት ፡ እየ መረመሩ ፡ ሰው ፡ የሚሞትበትን ፡ ምክንያት ፡ የሚድንበትንም ፡ ዘዴ ፡ እየፈ ለጉ ፡ እንደሚያጠኑ ፡ ሁሉ ፡ እንደዚሁም ፡ የሶሲዮሎጊ ፤ የኤትኖግ ራፊ ፤ የኤኮኖሚና ፡ የፍልስፍና ፡ ሊቃውንትም ፡ ከዘመናችን ፡ ሥል ጣኔ ፡ የሚመጣውን ፡ ጉዳትና ፡ ጥቅም ፡ ለይተው ፡ ለማወቅ ፡ ይጣጣራሉ ። ይህንንም ፡ ለማድረግ ፡ ሳይፈሩና ፡ ሳይጠየፉ ፡ ያለይሉኙታ ፡ የሥልጣ ኔን ፡ ሆድ ፡ ዕቃ ፡ ቀደው ፡ ሕዋሳቶቿ ፡ በሆኑት ፡ ድርጅቶች ፡ ውስጥ ፡ ያለ ውን ፡ በሽታ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እያበጠሩ ፡ ጥናት ፡ ያደርጋሉ ። ይ ህን ፡ የመሰለውን ፡ ታላቅና ፡ የተከበረ ፡ የሆነውን ፡ ተግባር ፡ የዓለም ፡ ሊቃውንት ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ሲፈጽሙ ፡ የህንድ ፡ ሊቃውንት ፡ እነ ፡ ራማ ፡ ክሪሽና ፤ ቪቪካናንዳ ፤ ጋንዲ ፤ ራቢንድራናት ፡ ታጎር ፤ አሮቢንዶ ፡ ጎዝ ፤ የድካማቸው ፡ ተካፋዮች ፡ ሆነዋል ። ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔና ፡ ም ሥራቃዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ሊታረቁና ፡ ሊግባቡ ፡ የማይችሉ ፡ መስለው ፡ ሲ ታዩ ፡ በእነዚህ ፡ በህንድ ፡ ሊቃውንት ፡ እርዳታ ፡ የሚቀራረቡበትንና ፡ የ ሚስማሙበትን ፡ መንገድ ፡ ለማጥናት ፡ ተችሏል ።

ህንድ ፡ ከምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ተለይታ ፡ የግል ፡ ሥልጣኔዋን ፡ ብቻ ፡ በመያዝ ፡ ህንድነቷን ፡ ጠብቃ ፡ መኖር ፡ ይገባታል ፡ በሚል ፡ አ ሳብ ፡ ጋንዲ ፡ የነበረውን ፡ አስተያየት ፡ ታጎር ፡ ተቃዋሚ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በ ዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የሚገኘውን ፡ ሊጠቀስ ፡ የሚገባውን ፡ ቃል ፡ ለጋንዲ ፡ ጽፎለታል ፤

(ከምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ) ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ አድርጎ ፡ መኖር ፡ ይጐ ዳል ፡ ብሎ ፡ መናገር ፡ ጠባብ ፡ የሆነውን ፡ ያሳብ ፡ ድኻ ፡ ከመሆን ፡ በ



ቀር ፡ ሌላ ፡ ፍሬ ፡ የማያፈራውን ፡ መንፈስ ፡ ማበረታታት ፡ ይሆናል ። . . . ዛሬ ፡ የገጠመን ፡ ጉዳይ ፡ መላ ፡ ዓለምን ፡ የሚመለከት ፡ ነው ። ማንኛውም ፡ ሕዝብ ፡ ቢሆን ፡ ከሌሎቹ ፡ ተለይቶ ፡ መዳኛውን ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልም ፤ ወይም ፡ አብሮ ፡ መዳን ፡ ወይም ፡ አብሮ ፡ መጥፋት ፡ ነው» ።

እኛም ፡ በዚህ ፡ ባለቅኔው ፡ ታጐር ፡ በተናገረው ፡ ቃል በሙሉ ፡ ስለምንስማማበት ፡ ለዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ መዝጊያ ፡ አድርገን ፡ ቆጥ ረነዋል ።

# የማይሞቱ ፡ ቃሎች ።

ደራስያን ፡ ከጻፏቸውና ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ከተናገሯቸው ፡ ንግግሮች ፡ ውስጥ ፡ የማይሞቱ ፤ የማይረሱ ፡ ተብለው ፡ የሚጠሩ ፡ ቃሎች ፡ ይገኛሉ ። ምክንያቱም ፡ በሊቃውንት ፡ ዘንድ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ የተሰጣቸው ፡ በመሆናቸው ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የማይሞቱና ፡ የማይረሱ ፡ ሲባል ፡ የአነጋገር ፡ ፈሊጥ ፡ መሆኑን ፡ አለመዘንጋት ፡ ያስፈልጋል ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ የማይሞት ፤ የማይረሳና ፡ የማይዘነጋ ፡ ነገር ፡ የለም ። ሰው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ይሞታል ፡ ይባላል ፤ አንደኛ ፡ የተወለደ ፡ ዕለት ፤ ሁለተኛ ፡ የተቀበረ ፡ ዕለት ፤ ሦስተኛ ፡ የተረሳ ፡ ዕለት ። ይህ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሕግ ፡ ነው ።

ደራስያንና ፡ ፈላስፎች ፡ ዘለዓለም ፡ ሲያትቱትና ፡ ሲያሳስቡት ፡ የሚኖሩትን ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ እስቲ ፡ ጥቂት ፡ እንመልከተው ። አንዳንድ ፡ አቶሞች ፡ ከተፈጠሩ ፡ ሰባት ፡ ሚሊያርድ ፡ ዓመታት ፡ መሆኑን ፡ የሳይንስ ፡ ሊቃውንት ፡ ይናገራሉ ። ያንድ ፡ ሰው ፡ ዕድሜ ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ ከሰማኒያ ፡ ዓመት ፡ አያልፍም ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ ቢኖርም ፡ የመዥገዥትና ፡ የመገርጀፍ ፡ የመጠንጠን ፡ ኑሮ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከሕይወት ፡ አይቈጠርም ። ስለዚህ ፡ የሰዎች ፡ ዕድሜ ፡ በሚያሳዝን ፡ አኳኋን ፡ አጭር ፡ መሆኑ ፡ አይካድም ። ባንድ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ተወልደው ፤ ኖረው ፤ ዓለማቸውን ፡ አይተው ፤ ዕድሜያቸውን ፡ ጨርሰው ፡ የሚሞቱ ፡ ነፍሳቶች ፡ መኖራቸውን ፡ የሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ሊቃውንት ፡ ይነግሩናል ። የሰው ፡ ዕድሜም ፡ ከዘለዓለም ፡ ጋራ ፡ ሲመዛዘን ፡ እንደዚሁ ፡ ከእነዚህ ፡ ዕድሜያቸውን ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ጀንበር ፡ ጨርሰው ፡ ከሚያልፉት ፡ ነፍሳት ፡ ምንም ፡ ያኸል ፡ አይሻልም ።

ይህቺ ፡ የምንኖርባት ፡ መሬት ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ በእሳተ ፡ ገሞራ ፡ እየተቃጠለችና ፡ እየቀለጠች ፡ ተለዋውጣለች ። መሬቱን ፡ ባሕር ፡ እያለበሰው ፤ ባሕር ፡ የነበረው ፡ ምድር ፡ እየሆነ ፡ የመሬት ፡ መልክ ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ ተለዋውጧል ። ስንት ፡ ከተሞች ፡ በጦርነት ፤ በመሬት ፡ መናወጥና ፡ በእሳተ ፡ ገመራ ፡ ጠፍተዋል ። በመሬት ፡ መናወጥና ፡ በእሳተ ፡ ገሞራ ፡ ከጠፉት ፡ ከተሞች ፡ ይልቅ ፡ በጦርነት ፡ የጠፉ ፡ ቍጥራቸው ፡ በጣም ፡ ይበልጣል ። ይህም ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ ከሌላው ፡ መቅሠፍት ፡ ሁሉ ፡ የባሰ ፡ መቅሠፍት ፡ መሆኑን ፡ ይገልጥልናል ።

ሰዎች ፡ ክፉት ፡ የሚሠሩት ፡ እርስ ፡ በርስቸው ፡ የሚተላለቁት ፤ በቂምና ፡ በበቀል ፡ የሚታመሱት ፤ ለዓለም ፡ ነገር ፡ የሚስገበገቡት ፤ ይህቺ ፡ የምንኖርባት ፡ መሬት ፡ የቱን ፡ ያኽል ፡ ከንቱ ፡ መሆኗን ፡ ሳይገነዘቡት ፡ በመቅረታቸው ፡ ነው ። ወይም ፡ ደግሞ ፡ ቢያውቁትም ፡ ደካማነት ፡ የተፈጥሮ ፡ ጠባያቸው ፡ በመሆኑ ፡ በመንፈሳቸው ፡ መሬትን ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ለመነሣት ፡ አይሆንላቸውም ። ሾፐንሃወር ፡ ስለዚህ ፡ ጒዳይ ፡ ሲናገር ፡ የተፈጥሮ ፡ ዕውቀት ፡ ሁለት ፡ ዐይነት ፡ ጠባዮች ፡ አሉት ። በብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ የሚረግጡትን ፡ መንገድ ፡ ብቻ ፡ የሚያሳያቸው ፡ የፋኖስ ፡ መብራት ፡ ሆኖ ፡ ያገለግላቸዋል ። ላንዳንዶቹ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ዓለምን ፡ በሙሉ ፡ ገልጦ ፡ ያሳያቸዋል ፡ ይለናል ። የዓለምን ፡ ከንቱነት ፡ ሰው ፡ በሁለት ፡ መንገዶች ፡ ማለት ፡ አንደኛ ፡ በመንፈሳዊነት ፤ ሁለተኛ ፡ በጥበብ ፡ ሊደርስበት ፡ ይችላል ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ፈላስፎችና ፡ ሊቃውንት ፡ አሳባቸው ፡ ከምድራዊ ፡ ነገሮች ፡ በላይ ፡ በመሆኑ ፡ አኗኗራቸው ፡ እንደ ፡ ባሕታውያን ፡ ነው ። በመንፈሳዊነት ፡ በኩል ፡ ሰው ፡ ይመረጥ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልዩ ፡ ጸጋ ፡ እንዲሰጠው ፡ ያስፈልጋል ። በጥበብ ፡ በኩል ፡ ግን ፡ የሰው ፡ ሁሉ ፡ ዕውቀት ፡ ሊደርስባቸው ፡ የሚችሉትን ፡ ነገሮች ፡ በመረዳት ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ አስተያየቱን ፡ ከፍ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ።

ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ብልኆች ፡ የሆኑ ፡ ነገሥታት ፡ (እንደ ፡ ሰሎሞንና ፡ እንደ ፡ ማርክ ፤ አሬል) ፡ የሕዝብ ፡ መሪዎች ፤ ሊቃውንት ፤ ፈላስፎችና ፡ ደራስያን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የሚነግሩን ፡ የዓለምን ፡ ከንቱነት ፡ ነው ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ በጣም ፡ የሚደንቅ ፡ ነገር ፡ አለ ። ለዓለም ፡ የሚጠቅም ፡ ምንም ፡ ሥራ ፡ ሳይሠሩ ፡ የሚያልፉ ፡ ሰዎች ፡ የዓለምን ፡ ሀብትና ፡ ክብር ፡ የመጨረሻ ፡ ደስታ ፡ አድርገው ፡ ይቈጥሩታል ። ታላላቅ ፡ ሥራዎች ፡ የፈጸሙ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ በሥራቸው ፡ ትልቅነት ፡ መጠን ፡ የዓለም ፡ ከንቱነት ፡ በጣም ፡ ጐልቶ ፡ የሚታያቸው ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ። ለምሳሌ ፡ ያኽል ፡ የትልቁ ፡ እስክንድርን ፡ ታሪክ ፡ እንመልከተው ። ይህ ፡ ሰው ፡ ያን ፡ ያኽል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ ሲያገኝ ፡ በምድራዊ ፡ ሀብትና ፡ ክብር ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንኳ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ አያውቅም ፡ ነበር ። ሁል ፡ ጊዜ ፡ መንፈሱ ፡ የሚመለከተው ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በላይ ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ነበር ። ታላላቅ ፡ ሕዝቦች ፡ ይናገሩባቸው ፡ የነበሩ ፡ ቋንቋዎች ፡ ሞተው ፤ ተረስተው ፡ ጠፍተዋል ። ስንት ፡ ሥልጣኔዎች ፡ የዘመን ፡ ዐዘቅት ፡ ውጧቸው ፡ ቀርተዋል ።

የግሪክ ፡ ባለቅኔዎች ፡ የሆኑት ፡ ኤሺልና ፡ ሶፎክል ፡ ከጻፏቸው ፡ ቴአትሮች ፡ አብዛኞቹ ፡ አልተገኙም ። ስንት ፡ ዕውቀትና ፡ ውበት ፡ ነው ፡



ከእነሱ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ የተቀበረ ። ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ ብዙ ፡ ከዋክብት ፡ በዘመን ፡ ብዛት ፡ ብርሃናቸው ፡ ጠፍቶ ፤ ግለታቸው ፡ ቀዝቅዞ ፡ ያረጁ ፡ በመሆናቸው ፡ ስፉቱ ፡ ወሰን ፡ በሌለው ፡ ባዶ ፡ በሆነው ፡ በሰማይ ፡ ቦታ ፡ (espace) ውስጥ ፡ ወድቀው ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ እንደሚንሳፈፍ ፡ ጒድፍ ፡ ተወርውረው ፡ ጨለማ ፡ ውጧቸው ፡ የትም ፡ ሲንከባለሉ ፡ የሚኖሩ ፡ መሆናቸውን ፡ የከዋክብት ፡ ሊቃውንት ፡ (አስትሮኖሞች) ፡ ይነግሩናል ። ስለዚህ ፡ መፈጠር ፤ መኖር ፤ ማርጀትና ፡ መሞት ፡ የሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እንኳንስ ፡ ለደካሞች ፡ ምድራውያን ፡ ለሆኑት ፡ ፍጡሮች ፡ ይቅርና ፡ ከዋክብት ፡ እንኳ ፡ ከዚህ ፡ ሕግ ፡ ሊያመልጡ ፡ አልቻሉም ። ይህቺ ፡ እኛ ፡ የምንኖርባት ፡ መሬትም ፡ ራሷ ፡ ቀድሞ ፡ ብርሃንና ፡ ሙቀት ፡ ለምታፈልቅ ፡ ላንዲት ፡ ፀሐይ ፡ አካሏ ፡ ነበረች ። ያች ፡ ፀሐይ ፡ በፈነዳች ፡ ጊዜ ፡ የሚበልጠው ፡ ክፍል ፡ ተበታትኖ ፡ ሲጠፋ ፡ መሬት ፡ ሳትፈርስ ፡ ተገምሳ ፡ በመለየት ፡ ስለ ፡ ቀረች ፡ በጊዜ ፡ ብዛት ፡ እየቀዘቀዘች ፡ ከሄደች ፡ በኋላ ፡ ዕፀዋት ፡ ሊበቅሉባትና ፡ በእስትንፋስ ፡ የሚኖሩ ፡ ፍጡሮች ፡ ሊሰፍሩባት ፡ ቻሉ ። ወደ ፡ ፊት ፡ ደግሞ ፡ አርጅታ ፡ በጠፉች ፡ ጊዜ ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ እንደጠቀስናቸው ፡ ከዋክብት ፡ ቅብዝብዝ ፤ ከርታታ ፤ ያረጀች ፡ ፕላኔት ፡ ሆና ፡ ትወድቃለች ፤ ትረሳለች ። ወይም ፡ ደግሞ ፡ ጨርሳ ፡ ትፈርስና ፡ ትበታተናለች ።

«ሁሉም ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ያረጃሉ ፤ እንደ ፡ መጐናጸፊያ ፡ ትለዋውጣቸዋለኽ ፤ እነሱም ፡ ይለወጣሉ ። አንተ ፡ ግን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ያው ፡ ነኽ» ። ሲል ፡ ዳዊት ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ይፈጸማል ።

አሁን ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ጒዳያችን ፡ እንመለስ ። የማይሞቱ ፡ ወይም ፡ የማይረሱ ፡ ቃሎች ፡ የሚባሉት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አሳብ ፡ የያዙና ፡ ውብ ፡ በሆነ ፡ አገላለጥ ፡ ከታላላቅ ፡ ሰዎችና ፡ ከደራስያን ፡ የተገኙ ፡ ናቸው ። የናፖሌዎን ፡ ንግግሮች ፡ አብዛኞቹ ፡ ብርቱነት ፡ ውበትና ፡ ከፍተኛነትም ፡ ያላቸው ፡ በመሆናቸው ፡ ሲጠቀሱ ፡ ይኖራሉ ። ከእነሱም ፡ መካከል ፡ ኒች ፡ በጣም ፡ የሚያደንቃቸው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ነው ።

«ዐዘቅቱን ፡ መልሼ ፡ ደፈንኩት ፤ ድብልቅልቅ ፡ የነበረውን ፡ ሥራት ፡ አበጀሁለት ፤ ለሕዝቦች ፡ መሳፍንትነትን ፡ ሰጠኋቸው» ።

«ካራማዞብ ፡ ወንድማማቾች» ፡ በተባለው ፡ መጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ዶስቶየቭስኪ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ጽፏል ።

«የሰውን ፡ ዘር ፡ እወዳለሁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የሰውን ፡ ዘር ፡ በጠቅላላው ፡ ይበልጥ ፡ በምወደው ፡ መጠን ፡ እያንዳንዳቸውን ፡ ለይቼ ፡ በግል ፡

ስወስዳቸው ፡ ለሰዎች ፡ ያለኝ ፡ ፍቅር ፡ የተቀነሰና ፡ የቀዘቀዘ ፡ በመሆኑ ፡ ይደንቀኛል ። . . . ሰዎችን ፡ ስቀርባቸው ፡ ጠላታቸው ፡ እሆናለሁ ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ በዚሁ ፡ አኳኋን ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ተለይተው ፡ ሰዎች ፡ ለየብቻቸው ፡ ሲሆኑ ፡ እነሱን ፡ በምጠላቸው ፡ መጠን ፡ በጠቅላላው ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ዘር ፡ በፍቅር ፡ የተቃጠልኩ ፡ ነኝ» ።

ናፖሌዎን ፡ ታስሮ ፡ በሞተባት ፡ ቅድስት ፡ እሌኒ ፡ በምትባለው ፡ ደሴት ፡ ላይ ፡ ሲኖር ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ተናግሯል ።

«ሁሉን ፡ ለማድረግ ፡ የሚችል ፡ በሆነው ፡ ኀይሌ ፡ ደመና ፡ እንደ ፡ ተሸፈንኩና ፡ በዙፋኔ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ነበርኩ ፡ ሞቼ ፡ ብሆን ፡ ኖሮ ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ የተሰወርኩ ፡ ምስጢር ፡ እሆንባቸው ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ ግን ፡ ዕድሜ ፡ ለደረሰብኝ ፡ መከራ ፡ ተገልጬ ፡ የምታይ ፡ ስለ ፡ ሆንኩ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ሰዎች ፡ የመሰላቸውን ፡ ሊፈርዱ ፡ ይችላሉ» ።

***   ***   ***

ከሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ የማይመሳሰል ፡ ሰው ፡ እሱ ፡ በውነት ፡ ሰው ፡ ተብሎ ፡ ሊጠራ ፡ ይገባዋል ።

ላዎ ፡ ትሴ ።

***   ***   ***

አንተ ፡ ሕይወትን ፡ መርምረኽ ፡ ያላወቅኸ ፡ ሆነኸ ፡ ሳለ ፡ ሞት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማወቅ ፡ እንዴት ፡ ትችላለኸ ?

ኮንፉሲዮስ ።

***   ***   ***

ሊቃውንት ፡ ረኸም ፡ በሆነ ፡ ሌሊት ፡ ውስጥ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ የሚታዩ ፡ የሰማይ ፡ ብልጭታ ፡ ናቸው ።

ፑዋንካሬ ።

***   ***   ***

ምን ፡ ወንጀል ፡ ሠርተን ፡ ነው ፡ እንድንፈጠር ፡ የተፈረደብን ።

ላማርቲን ።



ከፈጣሪ ፡ እጅ ፡ ሲወጣ ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ጥሩ ፡ ነው ፤ በሰው ፡ እጅ ፡ ሲገባ ፡ ማነኛውም ፡ ነገር ፡ ይበላሻል ።

ዣን ፡ ዣክ ፡ ሩሶ ።

***   ***   ***

ርኅራኄንና ፡ ቸርነትን ፡ እንዳውቅ ፡ ያደረገችልኝ ፡ እናቴ ፡ ነች ። ክፉ ፡ ሥራ ፡ አለመሥራትን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ጨርሼ ፡ እንዳላስበው ፡ እንኳ ፡ አስተምራኛለች ፤ ከዚህም ፡ በቀር ፡ በመጠን ፡ እንድኖር ፡ ያስለመደችኝ ፡ እሷ ፡ ነች ።

ማርቆስ ፡ አውሬልዮስ ።

(የሮማ ፡ ቄሳር) ፡

***   ***   ***